# የግእዝ ቅኔያት

## የስነ ጥበብ ቅርስ

ሁለተኛ ክፍል

ንባቡ ከነትርጓሜው

ከኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚ
ባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር

www.ethiopianorthodox.org

መፅሃፉን በከፊልም ሆነ በሙሉ ለማሳተም
መብቱ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚ ነው

ክፍል ሁለት መጀመሪያ እትም 1984

ዝግጅት ፡

አለቃ አፈወርቅ ዘውዴ፣
በትርጎማ፣ ምስጠራና ትረካ

ቀፀላ መንግስቱ
ዝግጅትና ቅንብር

መልክአ ክርስቶስ ነቢዩ
በግእዝና አማርኛ ታይፕ ስራ

ክነፈርግብ አታለል
እርማትና ህትመት ክትትል፡

መታሰቢያነቱ

ለመንግስቱ ለማና ለቀፀላ መንግስቱ

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org

# ማውጫ


ገፅ

መግቢያ 5

የግእዝ ቅኔያት ከነትርጉማቸው 7

የባለቅኔዎች አጫጭር የህይወት ታሪክ 389

የባለቅኔዎቹ ስም ከነቅኔዎቻቸው ተራ ቁጥር ጋር


# መግቢያ

የዚህ መጽሀፍ አንደኛ ክፍል በ1980 ዓ.ም ታትሞ ለህዝብ መቀረቡ ይታወቃል። የመፅሀፋ መታተም ዋና አላማ ዘመናዊ ትምህርት ያላቸውን አንባብያንን ከግእዝ ቅኔ ቀርስ ጋር ማስተዋወቅና ደረጃ በደረጃ ማለማመድ መሆኑ በዚህ በአንደኛው ክፍል መግቢያ ላይ ተገልጧል።

በዚሁ መሰረት አንደኛው ክፍል

1·ለዘመናውያን የስነ ግጥም ደራስያን ከሙያው አንፃር የቅኔን ቴክኒክና መንገድ በመመርመር አያሌ ቁም ነገሮችን አስጨብጧል።

2·የሀገራችንን ባህላዊ ቀርሶች ለአዲሱ ትውልድ ማስተላለፍ በባህል እድገት መስክ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል።

3·የመፅሀፋ መታተምና መሰራጨት ለስነ ግጥማችን እድገት አጋዥ ሆኗል።

4·ወጣቱን ትውልድ የአገሩን የስነ ግጥም ቀርስ ገንዘቡ አድርጎ ዘመናዊውን ከጥንታዊው ጋር ለማገናዘብና ለማዛመድ አስችሏል ።

ስለዚህ በዚሁ መፅሀፍ መግቢያ ላይ እንደተገለፀው 2ኛውን ክፍል "የግእዝ ቅኔ የስነ ጥበብ ቀርስ" መፅሀፍ አዘጋጅተን ለህትመት አቀርበናል። ወደፊትም አቅም በፈቀደ መጠን 3ኛው ክፍል የሚቀጥል መሆኑን ለመግለፅ እንወዳለን።

የግእዝ ቅኔ ተተርጉሞ በዘመናዊ የስነ ፅሁፍ ስልት ተዘጋጅቶ ተቀናጅቶና ተቀናብሮ መቀረብ ለልሳነ ግእዝ እንግዳ የሆኑ አንባብያንን ከቋንቋውና ከስነ ፅሁፉ ጋር ለማስተዋወቅ የሚጠቅም ነው። ለደራስያን የቅኔ ጥበብን፡ ለቋንቋ ባለሙያዎችም ለስያሜ ስራ የሚያገለግሉ ቃላትን እንደሚያበረክት ታምኖበታል።

በተጨማሪም መፅሀፋ የግእዝ ቅኔን በነፃ በማስተማር፡ ይህ ታላቅ የቋንቋና የስነ ፅሁፍ ቀርስ ከትውልድ ወደትውልድ ሲተላለፍ መጥቶ ከእኛ ደርሶ ታትሞ ለህዝብ እንዲቀርብ ከፍተኛ ጥረት ላደረጉ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ታሪክ የመታሰቢያ ሃውልት ነው።

ከዚህ ላይ አቶ መንግስቱ ለማና አቶ ቀፀላ መንግስቱ ታላቅ ምሳሌዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ሁለቱም ዛሬ በህይወት የሉም።

www.ethiopianorthodox.org

1·ለቶ መንግስቱ ለማ የዚህ መፅሀፍ አንደኛ ክፍል
ሀ·ከፊቱ የተጋረጡትን ልዩ ልዩ መሰናክሎች አልፎ ለህትመት እንዲበቃ ያላቋረጠ ጥረት አድርገዋል።
ለ·የቅኔውን ትርጉም አንባብያን በቀላል ዘዴ እንዲረዱት ዘመናዊ የአተረጓጎም ዘዴን የያዘ መመሪያ አውጥተዋል።
ሐ·መፅሀፉ ዘመናዊ የስነ ፅሁፍ ስልትና አሰራር እንዲኖረው የቀርብ ክትትል በማድረግና መመሪያ በመስጠት ታሪክ ሊረሳው የማይችል ስራ ሰርተው አልፈዋል።
2·ለቶ ቀፀላ መንግስቱ ለአንደኛውና ለዚህ ለሁለተኛው ክፍል
ሀ·በታሪካቸውና በምስጢራቸው ለዘመኑ ትውልድ የሚጠቅሙትን ቅኔያት በመምረጥ
ለ·ዋቢ መፃህፍትን በማሰባሰብ
ሐ·ግእዙና አማርኛው ትክክለኛ ትርጉም መያዛቸውን በማገናዘብ፡
መ·መፅሀፉ ዘመናዊ የስነ ፅሁፍ ውበት እንዲኖረው አድርጎ በማዘጋጀትና በማቀናበር የነበራቸውን የስነ ፅሁፍ ችሎታ ለትውልድ ተተው አልፈዋል።

እንዲያውም ይህንን ሁለተኛውን ክፍል ህይወታቸው ልታልፍ የስድስት ሰአት ጊዜ ብቻ እስከሚቀራት ድረስ በቢሮአቸው ሆነው በማዘጋጀት ከፍተኛ የስራ ፍቅር የነበራቸው ምሁር መሆናቸውን በተግባር አስመስክረዋል።

ስለዚህ ይህ ሁለተኛ ክፍል መታሰቢያነቱ ለለቶ መንግስቱ ለማና ለለቶ ቀፀላ መንግስቱ ዳንኤል እንዲሆን አድርገናል።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካደሚ

*1· ግእዝ ጉባኤ ቃና ስ*
*ዘገብረ ስላሴ ክንፉ (መምህር ፡ ዘኤልያስ)*
*አድኅነት ዕፅ እምተወክፎ ዝናም ከማሃ ፤*
*ሆላ አንስተ እለ አጽለላ ታሕቴሃ ።*

## ትርጉም

እንጨት እንደርሷ ዝናብን ከመቀበል
ከበታቿ ያረፉትን ሴቶች ሁሉ አዳነች ።

## ምስጢር

እንጨት (ዛፍ) በእርሷ ላይ የሚዘንበው ዝናብ እንዳይዘንብባቸው መንገደኞችን እንደምታድናቸው በእንጨት የተመሰለች ቅድስት ማርያምም በዝናብ የተመሰለውን የእግዚአብሄርን ቃል ወለደች ። ሌሎች ሴቶች ግን እንደርሷ ሊወልዱት አልቻሉም በማለት ባለቅኔው አመስጥረዋል ። ታሪኩ በ1980 አ.ም. በታተመው በአንደኛው መፅሃፍ በገፅ 35—36 ተተርኳል ።

*2· ዘእምላኪየ ስ*
*ዘጥፋንህ (እሊቀ ፡ ዘቦታ ኪዳነ ምህረት)*
*ነሚእኪ ማዕረ ምግበ አፉኪ በሊሐ*
*መርድዕ ዕዋለ እድግት ኢትንበሪ በሀ ፤*
*አኮኑ ይትመዋዕ በምግበ አፉኪ ጽርነ ።*

## ትርጉም

የአህያ ውርንጫ በሃ እንዳትኖሪ
የአፍሽ ምግብ የሆነ ሳርን ይዘሽ ጨኸትን ተማሪ ፤
በአፍሽ ምግብ ሳር ጠላት! ሃ ይሸነፋልና ።

## ምስጢር

ፈደል ቆጣሪ ልጅ ፊደሎቹን አላይ (አላጠና) ስትል መምህሯ "ሁልጊዜ ሃ ስትዪ እንዳትኖሪ በሳር የየፊደሉን እግር እግሩን እየነካሽ

ልብ ብለሽ ተማሪ" ይላታል ። እንዲሁም ባለቅኔው የአህያ ምግቧ ሳር መሆኑንና ጩኸቷም" ሃ ፣ ሃ ፣ ሃ ..." መሆኑን በልጇቱ ትምህርት አንፃር አስረድተዋል ።

*3. ሥላሴ (85) አ*

*ዘንሉ (ቄስ ገበዝ ፡ ዘዲማ)*

*ለሳኦል ይላህዎ*
*ሳሙኤል ሖረ ፍና ኀዘን ፤*
*ውእቱ ሳኦል መሲሑ እስመ ኢኮነ መሲሐ*
*ወመፍትው ከማሁ ከመ ትግበር ላሐ*
*ለደብረ ድማኅ ቤትከ ሰማዕተ ዝየ ወከሃ ፤*
*ሀየንተ ዘወርቅ ቀጸላሃ*
*አምጣነ ብርሀት ወፅአ ላዕሌሃ*
*ወድማኅ ኢኮነት ድማኅ ።*

## ትርጉም

ለሳኦል ያለቅስለት ዘንድ
ሳሙኤል የአዘንን መንገድ ሄደ ፤
ርሱው ንጉሱ ሳኦል ንጉስ አልሆነምና ።
የዚህና የዚያ ሰማእት ጊዮርጊስ ! ለዲማ ደብር ቤትህ እንደርሱው ልቅሶን ታደርግ ዘንድ ተገቢ ነው ፤
በወርቅ ቀፀላዋ ፈንታ በራነት በርሷ ላይ ወጥቷልና ፣
ዲማም (አናትም) ዲማ አልሆነችምና ።

## ምስጢር

አምላክ የእስራኤል ንጉስ ሳኦልን ሲንቀውና ሲጥለው ቀብቶ ያነገሰው ነቢይ ሳሙኤል እንዳዘነለት ቅዱስ ጊዮርጊስም በስሙ ለተሰራችው ለደብረ ድማህ ቤተ ክርስቲያን ማዘን ይገባዋል ። ሳኦል ከመንግስቱ እንደወረደ የደብረ ድማህ ድማህ ቤተ ክርስቲያንም ቅፈፍ የሆነውን ገጠር ማስገበሯ ቀረ ። መሃል ራስ በራስ ጠጉር እንደምትከበር በመሃል ራስ የተሰየመችው ፣ የቅዱስ ጊዮርጊስም ቤተ ክርስቲያን የሚገኝባት ዲማ በደብርነቷ የምትከበረው ቅፈፍ በሆነው በገጠሩ ብዛት ነበር ። የገጠሩ ቅፈፍ ከቀረ ግን በደብርነቷ መከበርን አታገኝም ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

## ታሪክ

የእስራኤል መስፍንና ነቢይ የነበረው ሳሙኤል ከነገደ ብንያም የተወለደ የቂስ ልጅ ሳኦልን በእግዚአብሄር ትእዛዝ ቀብቶ በእስራኤል ላይ አነገሰው ። ሳኦል ግን የእግዚአብሄርን ትእዛዝ በየጊዜው በመጣሉና የሳሙኤልንም ምክር ባለመቀበሉ እግዚአብሄር የንጉስነት ስልጣኑን ከነገደ ይሁዳ ለተወለደ ለዳዊት ሰጠበት ። ሳሙኤልም ቀብቶ ያነገሰው የእስራኤል ንጉስ ሳኦል ሃጢአተኛ በመሆኑ ስለእርሱ አልቅሷል (1ሳሙ. 8—15) ።

ራስ አሊ ጎጃምን ወረው ሲያስገብሩና ሲገዙ የጎጃም ባላባት የሆኑት የሃይሉ ዮሴዴቅ ልጅ ደጃች ብሩ ለራስ አሊ ሊታጠቁ ስላልፈቀዱ ሶማ ከተባለው አምባ ውስጥ ገቡ ። እዚያ ሆነው በሶማ አካባቢ ያለውን የደብረ ድማህን ቅፈፍ ጨምረው የገጠሩን ህዝብ ያስገብሩ ጀመር ። ከዚያ በፊት የደብር ቅፈፍ የሆኑት ገጠሮች ለዚያው ለደብራቸው ይገብሩ ነበር እንጂ ለመሳፍንንትና ለመኳንንት አይታዘዙም ነበር ። ስለዚህም "ደብሩ ተደፈረብን ፣ ደብርህን አስከብር" ሲሉ የዲማ ተወላጅ የሆኑት ቄስ ገበዝ ጓሉ ለሰማእቱ ለቅዱስ ጊዮርጊስ ይህን ቅኔ አበርክተዋል ።

*4. ሥላሴ (283) አ*

*ቶማስ ሐዋርያ*

*ወቶማስ ሊቅ አመ ወረዱ*
*ለጸቢት በደርግ ባሕረ ተመትሮ ስሩሐ*
*ቶማስ አሐዱ ግርማዝ ኢፈርሀ ፤*
*ለኀዲግ እግር ወእድ እስመ አልጸቀ ወበጽሐ ፤*
*ካልኡሰ ቶማስ ኢተበውሐ*
*ላዕለ ግብረ ጸቢት በዝየ ወበከሃ ፤*
*እስመ ዓዲ መስነቅቶ ኢፈትሐ ።*


www.ethiopianorthodox.org

## ትርጉም

ስፌ ባህር/መቈረጥን
በአንድነት ለመዋኘት
ሃዋርያ ቶማስና ሊቅ ቶማስ በወረዱ ጊዜ
አንዱ ቶማስ የዚህ ግርማን አልፈራም ፤
እጅንና እግርን ለመጣል ፈፅሞ ደርሷልና ፥
በዚህና በዚያ ለመዋኘት ስራ ግን
ሁለተኛው ቶማስ አልሰለጠነም ፤
ገና አቅማዳውን አልፈታምና ።

## ምስጢር

ሁለት ጓደኞች ለውሃ ዋና ወደወንዝ ወርደው ሲዋኙ አንዱ ጓደኛ ዋናውን ሲለማመደው እጁን ማለ ይባላል ። የመርአስ ኤጲስ ቆጶስ ቶማስም በሰማእትነት ሲሰቃይ እጁንም እግሩንም ተቆረጠ ። ደግሞ ሁለተኛው ጓደኛ ዋና እስኪለማመድ አቅማዳውን ከወገቡ አይፈታም ። የሀንደኬው ሃዋርያ ዲዲሞስ የሚባለው ቶማስ እንደበግ ተገፍፎ አቅማዳ የሆነ ቆዳውን ከአሸዋ ጋር ተሸከመ በማለት ባለቅኔው የሰማእታትን ስቃይ ፅናት በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል ።

ታሪኩ በአንደኛው መፅሃፍ በገጽ 52 ተተርኳል ።

*5· አጭር ዘይእዜ (306) አ*

*ጽጌ ለወይን ታስተፌሥሓ ፤*
*ወመንግሥተ ዮሐንስ ወይን ለዓለመ ጽልመት ከማሃ ።*

## ትርጉም

አበባ አይንን ታስደስታለች ፤
የዮሃንስ መንግስት/ወይንም የጨለማ አለምን እንደርሷ ታስደስታለች።

## ምስጢር

አበባዪቱ በወይኒቱ ላይ ፈክታ ስትታይ ወይኒቱም በአበባዪቱ አስደሳች ሆና ትታያለች ። ባለቅኔውም የአፄ ዮሃንስ መንግስት በድንቁርና ውስጥ የነበረችውን አለም አሰለጠናት በማለት ለአፄ ዮሃንስ ዘመነ መንግስት ያላቸውን አስተያየት በቅኔያቸው አመስጥረዋል ።

*6· መወድስ (98)ጎ*

*ዘወልደ ጊዮርጊስ (ሊቀ ጠበብት)*

*ገብረ ሥላሴ ፈድፈደ ፍድፋዴ ሕማማ*
*ለዘወሀብከኒ ምድር ወኢጥዕየት እምደዌሃ ፤*
*አምጣነ ሰናፔ ትመስል መንግሥተ ሰማያት ስፍሐ*
*ወዲናር ቆማ የአክል እራኃ ፥*
*ወእክለ ሲሳይ ኢታበቁል*
*ገዳፍያነ ሐብል ሕዝብ እስመ ሖሩ ላዕሌሃ ።*
*ይትርፍሰ ዘነገርኩከ ሕማመ ዚአሃ*
*ኮነት እብነ አፍአ ብእሲተ ሎጥ ዞለንታሃ ፤*
*ወበዛ መሬት ከመ ኢይግበር ፍሥሓ*
*በምርዋጸ አፍራስ ተቀብረት ራሔል ጽነፊሃ ።*

## ትርጉም

ገብረ ስላሴ! የሰጠኸኝ ምድር የቧሽታዋ
ብዛት በረከተ ፡ ከበሽታዋም አልዳነችም ፡
መንግስተ ሰማይ/ስፋቷ ሰናፍጭን ትመስላለችና ፥
አላድ/ቁመቷም መዳፍ ያህላልና ፥
የምግብ እህልንም አታበቅልም
ቀላድ (ገመድ) ጣዮች ህዝብ በርሷ ላይ ስለሄዱ ።
የነገርኩህስ በሽታዋ ይቅርና
የሎጥ ሚስት ሁለንተናዋ የውጭ ድንጋይን ሆነች ፡
በዚችም መሬት ደስታን እንዳላደርግ
ራሄል ዳርቻዋ በፈረሶች መሮጫ ተቀበረች ።

## ምስጢር

በሽታዋ እየጠናባት የሄደ ሴት የቅርብ ዘመዶቿን ተስፋ እንደምታስቆርጥ ፀሀፌ ትእዛዝ ገብረ ስላሴ ለባለቅኔው የሰጧቸው መሬትም


www.ethiopianorthodox.org

ተውሳካም ሆነች ፤ ከዘረ ቀርጥምነቷ አልወጣችም ። መንግስተ ሰማይ በሰናፍጭ ቅንጣት እንደምትመሰል የባለቅኔው መሬት ስፋት እንዲሁ ጠበበች ። የብር አላድ እንደ መሀል እጅ ጠባብ እንደሆነች የባለቅኔው የመሬት መጠንም ትንሽ ሆነ ። የህዝብ መመላለሻ የሆነ መሬትም (አውራ መንገድ) እህል እንደማያበቅል ቀላድ የሚጥሉ ሰዎች የለኳት መሬት ለእህል የማትሆን ናት ። የሎጥ ሚስት የጨው ሃውልት እንደሆነች የባለቅኔው መሬት ድንጋያማ ሆነች ። ራሄልም በፈረሶች መራወጫ እንደተቀበረች ድንበሯ የፈረሶች መጋለቢያ ነው በማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

## ታሪክ

ባለቅኔው ለፀሀፌ ትእዛዝ ገብረ ስላሴ ይህን መወድስ ያበረከቷቸው የተሰጣቸው መሬት የማይጠቅም መሆኑን በቅኔያቸው ምስጢር አስገንዝበው ሌላ አንድ ጋሻ መሬት እንዲሰጣቸው የፈለጉ ይመስላል ።

ያእቆብ ከሴኬም ምድር ወደቤቴል እንዲወጣ እግዚአብሔር በነገረው ጊዜ ወደቤቴል ሄደ ። ከቤቴልም ተነስቶ ወደኤፍራታ ሊደርስ ጥቂት ሲቀረው ሚስቱ ራሄልን ምጥ ያዛትና በወሊድ ሞተች ። ስለዚህም ወደ ኤፍራታ በምትወስድ በቤተ ልሄም መንገድ ዳር ቀበሯት ። ያእቆብም በመቃብሯ ላይ ሀውልት አቆመ ። የግእዙ መፅሃፍ መቃብሯን "በምርዋፀ አፍራስ ፡ በፈረስ መሮጫ" ስላለው ባለቅኔው" በምርዋፀ አፍራስ" በማለት ተቀኝተዋል ። (ዘፍ. 35 ፡ 1—21)

*7· ግእዝ ክብር ይእቲ (7)ጎ*
*ዘሀብቴ (ደብተራ ፡ ዘሽንኩርት ሚካኤል)*

*ኀሕለወ አብ በግማደ ሥጋ ኤልያስሀ*
*ወበአሐዱ በግዕ አብርሃምሃ መሢሐ ፤*
*እመሰ ኀቤነ መክሊተ ፍቅሩ አርብሐ*
*ወልዶ ኢምሕከ ፡ ለቤዛ ኵልነ እስመ ጠብሐ ።*

### ትርጉም

አብ በስጋ ቁራጭ ኤልያስን ሸነገለ
በአንድ በግም ሹም /አብርሃምን ሸነገለ ፤
በእኛ ዘንድ ግን ፍቅሩ/ወርቅን ባረባ ጊዜ
ለልጁ አላዘነም ፤ ለሁላችን ቤዛ አርዷልና ።

## ምስጢር

አንዳንድ ሃብታም ድሃውን እንግዳ ትንሽ ስጋ አቅምሶ ይሸኘዋል ፤ የተሾመ ሃብታም እንግዳ ሲመጣበት ደግሞ የበግ ሙክት አርዶ ያስተናግደዋል ። እግዚአብሄር አብም ለነቢዩ ኤልያስ በቁራ አመላላሽነት የመገበው ስጋ ለሌላው አልተረፈም ፤ ለይስሃቅ ቤዛ ሊሆን ለአብርሃም የወረደለት በግም ቤዛነቱ ለይስሃቅ ብቻ ሆኖ ቀረ ። ቸር ሃብታም የልብ ወዳጁን በየጊዜው እየጠራ እንደሚጋብዘው የእግዚአብሄር አብም የባህርይ ልጁ ክርስቶስ የሰጠን ስጋና ደም ለሁሉም የዘላለም ህይወት ናቸው ። እግዚአብሄር አብ አብርሃምንና ኤልያስን ከመውደዱ ይልቅ እኛን ሁዋለኞችን መውደዱ በለጠ ይላሉ ባለቅኔው ።

ታሪኩ በአንደኛው መፅሃፍ በገፅ 88 ተተርኳል ።

*8· ዋዜማ ስ*
*ዘተዋነይ*
*የአምን ወይገኒ*
*ኵሉ ዓለም በዘፈጠረ ለሊሁ*
*ብዙኃን እንዘ ይገንዩ ይሰግዱ ቅድሜሁ ፤*
*ለነጽሮ ዝኒ ነገር ከመ እስራኤል ይፍርሁ*
*ሙሴ ፈጠረ ፈጣሪሁ*
*ወፈጣሪ ፈጠረ ኪያሁ ።*

### ትርጉም

አለም ሁሉ
ብዙዎች እየተገዙ በፊቱ ይሰግዱ ዘንድ
እርሱ ራሱ በፈለሰፈው ያምናል ይገዛልም ፤
ይህንም ነገር ለመመልከት እስራኤል ይፈሩ ዘንድ ሙሴ ፈጣሪውን ፈለሰፈ (ወደደ)
ፈጣሪም እርሱን ፈጠረ (ወደደ) ።


www.ethiopianorthodox.org

## ምስጢር

የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ስእል እየሳሉና ታቦት እየቀረፁ ስእሉንና ታቦቱን የፈጣሪያቸው አምልኮትና ፍቅር መግለጫ ፣ እንደፎቶ ግራፍ ማስታወሻ ያደርጋሉ ። ነቢይ ሙሴም "እግሌ ቅኔ ፈጣሪ ነው" እንደሚባል ፈጣሪውን በልቡ ምርምር ማወቁን ፣ ፈጣሪውም የሙሴን ታማኝነት ማረጋገጡን በመግለጥ የቅኔ አባት ተዋነይ ቅኔውን አመስጥሯል ።

*9· ዋዜማ/ጎ*

*ወልደ አብ ይፌውሶ*

*ጽዋዐ ወርቁ ምሉዐ እንዘ ይከዑ ላዕሌሁ*
*ለነዳይ ብእሲ ዘየብሰት እዴሁ ፤*
*ወእመ በንባብ ፈጠረ ዓለመ ትርጓሜ ለሊሁ*
*ይፀዐቁ ሕዝብ ይሰምዑ በጉባኤሁ*
*ሞገሰ ቃሉ ወጣዕመ ነገሩ ወሣዕሣዐ አፉሁ ።*

## ትርጉም

ወልደ አብ
የወርቁ ጽዋን በላዩ ላይ እያፈሰሰ
እጁ የደረቀች ድሃ ሰውን ይፈውሰዋል ፤
ትርጓሜ/አለምንም በንግግር እርሱ በፈጠረ ጊዜ
የቃሉን ሞገስና የንግግሩን ጣእም የአፉንም ቅልጥፍና በጉባኤው
ይሰሙ ዘንድ ህዝቡ ይጨናነቃሉ ።

## ምስጢር

የታመመ ሰው በካህን ፀሎት በተቀደሰ ፀበል በመጠመቅ እንደሚፈወስ ወልደአብ የተባሉት የጎንደር ሊቅ ድሃውን ሰው በመጠጥ አረኩት ። አምላክ አለምን በመናገር እንደፈጠረ ሊቁ መምህር ወልደአብም የመፃህፍትን አንድምታ ትርጓሜ ፈለሰፉ ይላሉ ባለቅኔው ። በዚህም ላይ ኢየሱስ በአይሁድ ምኩራብ ገብቶ ሲሰብክ የአይሁድ ሊቃውንት እንዳደነቁትና ህዝቡም ትምህርቱን ለመስማት



www.ethiopianorthodox.org

እንደተጋፋ የአለቃ ወልደ አብ ጉባኤ ሰፍቶ ለህዝቡ ተዳረሰ ። የአተረጓጐማቸውም ስልትና የተሰጣቸው ሃብተ ምስጢር አስገራሚ ሆኑ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

## ታሪክ

አለቃ ወልደ ዐብ በጣም ቸር ስለነበሩና የመፃህፍትን አንድምታ ትርጓሜ በጎንደር ስላስፋፉ ከደቀ መዛሙርታቸው አንዱ ቸሮታቸውንና የትርጓሜ ስጦታቸውን በዚህ ዋዜማ ቅኔ ገልጧል ።

*10. ዋዜማ(14)አ*

*ለኢዮስያስ በፋሲካሁ*

*እለ አልህምተ ሦዑ ወአባግዐ ዘጠብሑ*
*ኢያትረፉ ለሣኒታሁ ወበልዕዎ አሜሁ፤*
*በግዐ ፋሲካነሰ እንዘ አሐዱ ለሊሁ*
*ዮም ይትበላዕ ዠለንታሁ*
*ወጌሠመ ይትረከብ ከማሁ ።*

## ትርጉም

በኢዮስያስ ፋሲካ
በሬዎችንና በጎችን ያረዱ ሰዎች
ለማግስቱ አላተረፉም በዚያው ጊዜም በሉት ፤
የፋሲካችን በግ ግን አንድ ሲሆን
ሁለንተናው ዛሬ ይበላል ፤
በነጋውም እንደዚያው ይገኛል ።

## ምስጢር

የኢትዮጵያ ፋሲካ ምንም ታላቅ ቢሆን የተሰውት (የታረዱት) በሬዎችና በጎች ብዙዎች ሲሆኑ ፤ በአንድ ቀን ተጨርሰው ተበሉ እንጂ እንደብዛታቸው ስጋቸው አልተትረፈረፈም ነበር ፣ የእኛ የፋሲካችን በግ እግዚአብሄር ወልድ ግን አንድ ሲሆን ስጋው ዛሬም ነገም ይገኛል ።

ከአለም መፈጠር በፊት ከአብ በባህርይ ተወልዶ ከአለም መፈጠር በሁዋላ ከድንግል ማርያም በስጋ ሲወለድ ተቀዳሚና ተከታይ የለውም አንድ ነው ስጋው በህብስት ፡ ደሙ በወይን ሲሰጥ ጉድለት የለበትም የዘላለም ህይወት አለው ይላሉ ባለቅኔው ።

## ታሪክ

ኢዮስያስ ከዳዊት ወገን ከነገሱት ነገስታት አስራ ስድስተኛው የይሁዳ ንጉስ ነበር ። በዘመነ መንግስቱ በግዛቱ ውስጥ አምልኮ ባእድን አጠፋ ። የእግዚአብሄርን ቤት ሲያሳድስ ጠፍቶ የነበረው የህግ መፅሀፍ ተገኘ ። በዚህም ምክንያት ፋሲካን በታላቅ ክብር አከበረ(ኤር፡1፡2፤22፡ 15፡16) ።

*11. ሥላሴ (29)አ*
*ዘአድማሱ ጀንበሬ (መልአከ ብርሃን)*

*ሰአልዎ እስራኤል*
*ለሙሴ ይትገልበብ በሰንዱናት*
*ኅጠተ ብርሃን ንስቲተ በገጹ አመ ነጽሮተ ፈርሁ ።*
*ይእዜሰ እምኀበ ኢኮነ ብርሃኑ ከማሁ*
*እግዚአ ሙሴ ክርስቶስ ለዘሀለው ምስሌሁ*
*በምንት ይትገልበብ ገጸ ዚአሁ ?*
*እስመ ከመ–መብረቅ በረቀ አልባሲሁ*
*እስከ ስዕኑ ነጽሮ ኪያሁ ።*

## ትርጉም

እስራኤል ትንሽ
የብርሃን ቅንጣትን በፊቱ
ማየትን ቢፈሩ በበፍታ (ነጭ ልብስ) ፊቱን ይሸፍን ዘንድ ሙሴን
ለመኑት ፤
ዛሬ ግን ብርሃኑ እንደርሱ ካልሆነ ዘንድ
የሙሴ ጌታ ክርስቶስ ከርሱ ጋር አብረው ላሉት
ፊቱን በምን ይሸፍን?
እርሱን ማየትን እስኪሳናቸው ድረስ
ልብሱ እንደ መብረቅ በርቋልና



www.ethiopianorthodox.org

## ምስጢር

ሙሴ በፊቱ ነፀብራቅ ቢያስፈራቸው ነፀብራቅ በሌለው ልብሱ ፊቱን ቢሸፍነው ከፊቱ ነፀብራቅ እንደሚድኑ እስራኤል ተስፋ አደረጉ ። ከክርስቶስ ጋር በደብረ ታቦር የነበሩት ሙሴ ፡ ኤልያስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ዮሐንስና ያዕቆብ ግን ከፊቱ ነፀብራቅ በልብሱ ሽፋን እንዳይድኑ ፤ ልብሱም የመብረቅ ብልጭታ ያለበት ስለሆነ ፊቱን በልብሱ ቢሸፍንላቸውም ያው ነው ። ስለዚህ እንደ እስራኤል ከፊቱ ነፀብራቅ በልብስ ሽፋን የመዳን ተስፋ የላቸውምና ሶስቱ ሐዋርያት (ጴጥሮስ ፡ ዮሐንስና ያዕቆብ) በግንባራቸው ወደቁ ፤ ሁለቱም ነቢያት (ሙሴና ኤልያስ) ሸሹ በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

ታሪኩ በአንደኛው መፅሃፍ በገፅ 50 እና 207 ተተርኳል ።

*12. ዘይእዜ (300)አ*
*ዘአድማሱ ጀንበሬ (መልአከ ብርሃን)*

*ይቶስሑ ማየ በውስተ ወይን*
*መያስያኒሃ ለጽዮን ለዘረፈቁ ይምስሑ*
*እንዘ ይብል ነቢይ ከመ ገሠጸ*
*አመ ደምፀ በእዘኒሆሙ ለነቢይ ጽራሑ*
*መያስያነ ወልድ ኃይላት እምነውረ መያሲ ከመ ይንጽሑ ፤*
*ውስተ ማይ ወይነ እንዘ ይቶስሑ*
*ጥዑመ ወይነ ለእለ ረፈቁ ቀድሑ*
*ውስተ ማይ ወይነ እንዘ ይቶስሑ ።*

## ትርጉም

የፅዮን ጠጅ አሳላፊዎች
ምሳ ሊበሉ ለተቀመጡት በወይን ውስጥ ውሃን ይቀላቅላሉ
እያለ ነቢይ እንደገሰፃት
የነቢይ ጩኸት በጆሮዎቻቸው ቢሰማ
የወልድ ጠጅ አዳዮች (ተአምሮች) ከጠጅ አዳይነት ነውር ይኖር
ዘንድ ፤

በውሃ ውስጥ ወይንን እየቀላቀሉ
የጣፈጠ ወይንን ለተቀመጡት ቀዱ ።

## ምስጢር

ወንጀለኛ ሲቀጣ ያየ ሰው እንደወንጀለኛው እንዳይቀጣ በከፉ ፈንታ መልካምን ይሰራል ። የፅዮን ጠጅ አሳላፊዎች በወይኑ ውስጥ ውሃን መቀላቀላቸው ወይኑን ውሃ ቢያደርገው የክርስቶስ ተአምሮች በውሃ የቀጠነውን ወይን አወፈሩት ። ውሃውንም የወይን ጠጅ አደረጉት በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

ታሪኩ በአንደኛው መፅሃፍ በገጽ 196 ተተርኳል ።

*13. መወድስ (42) አ*

*ለዘመጽአ ፈርዖን መንገለ ኤርትራ*
*ኢይሰድዶ መልአክ ወኢያወፅኦ እምውሳጤሁ ፤*
*እስመ ኀበ ቦአ ዳታን ሐዋርያሁ*
*ውስተ ልበ ምድር ይበውእ ምስሌሁ*
*ወእንዘ ለውስጥ አውፃኢሁ*
*ለእንተ አፍአ ማኔዎስ ሚካኤል አባኢሁ ።*
*ባሕርኒ መፍቀሬ ሰብእ ሰራዊተ ግብጽ ሐራሁ*
*እምከመ እምድር ተለዐለ ይስሕብ መንገሌሁ ፤*
*ወድኀረ ኵሎ ፈጸመ በትሕትናሁ*
*ገብአ ወተመይጠ ኀበ ዘትካት ሀላዌሁ ።*

## ትርጉም

ወደኤርትራ የመጣ ፈርኦንን
መልአክ አያባርረውም ፤ ከውስጡም አያወጣውም ፤
ሐዋርያው ዳታን ወደገባበት
በምድር ልብ ውስጥ ከእርሱ ጋር ይገባልና ፤
የውስጥንም አውጪው ሲሆን
የውጪውን ፈርኦንን ሚካኤል አግቢው ነውና ።



www.ethiopianorthodox.org

ሰውን ወዳጅ ባህርም የግብፅ ሰራዊት ወታደሮችን
ከምድር ከፍ ካለ በሁዋላ ወደእርሱ ይስባል ፤
በትህትናውም ሁሉን ከፈፀመ በሁዋላ
ወደቀድሞ ኑሮው ተመልሶ ገባ ።

## ምስጢር

ኢየሱስ "ወደእኔ የመጣውን አልሰደውም ፤ ወደውጭም አላወጣውም" እንዳለ የኤርትራ ባህርም ወደርሱ የመጣውን ፈርኦንን አላሻገረውም በውስጡ አስጠመው እንጂ ፤ ሐዋርያትም "ክርስቶስ ወደገባበት እንገባለን" እንዳሉ ቀደም ያለው ዳታን በተዋጠበት የምድር ልብ ውስጥም ፈርኦን ተዋጠ ።

አንዳንዱ ሰው ከተሾመ በሁዋላ ወዳጆቹን እንደሚጠቅማቸውና ጠላቶቹን እንደሚጎዳቸው ፤ ባህር እስራኤልን እንደ ግድግዳ ቆሞ ካሻገራቸው በሁዋላ የግብፅ ንጉስ ፈርኦንንና ሰራዊቱን አሰጠማቸው ። ትጉህ ሰራተኛም ስራውን ፈፅሞ እንደሚመለስ የኤርትራ ውሃ ከተከፈለ በሁዋላ እንደነበረ ሆነ በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

ታሪኩ በአንደኛው መፅሃፍ በገፅ 125 እና 190 ተተርኳል ።

*14. መወድስ (54) አ*
*ዘወልደ ኢየሱስ (ሊቀ ጠበብት)*

*እብነ ቢታንያ ይትካፈል ቅድመ ሆሣዕና*
*ምሁርካ ይሁዳ ሰብሐተ ምስለ ሕፃናት አኀዊሁ ፤*
*ወዘእንበለ ያእምር ቅድመ ሰምየ ፈጣሪ አቡሁ*
*ኀይለ ሕዝበ አይሁድ ከመ ይንግእ*
*ሕፃን እብነ ቢታንያ ከሠተ አፋሁ ፤*
*መንግሥት ጥበበ ልብ*
*እም ኤፍሬም ባዕድ ትጠፍዕ በጊዜሁ ።*
*ካህንኒ ሆሣዕና ሀልወ መስቀል ለሊሁ*
*ይባርክ ቅንዋተ ሰፍሐ እደዊሁ ፤*
*ወእለ ቡሩካነ ኮኑ ቅንዋቲሁ*
*ተመጠዉ ተመጥዎ ደሞ ምስለ ሥጋሁ ።*

## ትርጉም

የቢታንያ ድንጋይ በሆሳእና ፊት
የይሁዳ ምርኮ /ምስጋናን ከህፃናት ጋር ይካፈላል ፤
ፈጣሪ/ አባቱን መጥራትንም ቀድሞ ሳያውቅ
የአይሁድ ህዝብ ሃይልን (መሳሪያን) ይቀበል ዘንድ
ህፃን /የቢታንያ ድንጋይ አፉን ከፈተ ፤
መንግስት/ የልብ ጥበብም
ከኤፍሬም ባእድ በጊዜው ትጠፋለች ።
እርሱ መስቀል ያለው ሆሳእና /ካህንም
ችንካሮችን ሊባርክ እጆቹን ዘረጋ
የተባረኩ የሆኑ ምእመናን/ ችንካሮቹም
ደሙን ከነስጋው መቀበልን ተቀበሉ ።

## ምስጢር

"ህፃን አባባና እማማ ማለትን ሳይችል ፤ "የደማስቆን ሃይል ይወስዳል ፤ የሶርያንም ምርኮ ይካፈላል" ተብሎ ስለክርስቶስ መወለድና እጅ መንሻን መቀበል ተተንብቷል ። እንዲሁም በአንፃሩ ይሁዳ ሊፈፅመው የሚገባውን ሆሳእናን ማመስገንን የቢታንያ ድንጋይ ፈፀመ ፤ በማመስገኑም ከህፃናት ጋር ተባበረ ። ህፃኑም አበና እመ ማለቱን ሳይችል የደማስቆን ሃይልና የሶርያን ምርኮ እንደወሰደ አምላክን ለማመስገን ያልተፈጠረው ድንጋይ ለማመስገን የተፈጠሩትን አይሁድን በማመስገን ላቃቸው (በለጣቸው) ይላሉ ባለቅኔው ።

ያንድ ቤተ ክርስቲያን ቄስ ምእመናንን በመስቀል ለመባረክ እጆቹን ይዘረጋል ። ምእመናኑም በመስቀል ከተባረኩና ንስሃ ከገቡ በሁዋላ የክርስቶስን ስጋና ደም ይቀበላሉ ። እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ በእለተ አርብ በመስቀል ላይ እጆቹን ዘርግቶ በቾንካሮች ተቾነከረ ። ችንካሮችም ደሙን አፈሰሱ ፤ ስጋውንም በጣጠሱ በማለትም አመስጥረዋል ።

ታሪኩ በአንደኛው መፅሃፍ በገፅ 62 እና 90 ተተርኳል ።

*15. መወድስ (24) ጎ*
*ዘገብረ ኢየሱስ (ቅኔ ፈጣሪ)*



*ስቁለ ዐይነ ሰቅል ምንትከ ሰቅለ ሜዶናዊ*
*በሰቅለ ቀራንዮስ ትድሉ መክሊተ ዘጌላቡሄ?*
*ሕጹጽኑ በኵሉ ወበኵለሄ*
*ዘኀቱም በማኅተመ እዝራ ዕንቊከ ሰባሔ*
*እስመ በፀሐይ ወበብናሴ*
*ፍትሐ ሰሎሞን ፈታሕከ ኢትፍታሕ ፍትሐ ዮፍታሔ ።*
*ትትላጸይሰ ጽሕመ ዘኮነ ጎበ ርእስከ መራሔ*
*አራዊተ ዳርዮስ በአሐቲ መላጼ አሐቲ ጽሕመ ፋቁሔ ።*
*እስመ በዘአምኑ ለከ ዘነገሥተ ፋርስ እማኄ*
*ወቦ እለ ጸዐኑ አፍራሰ ዘቴቁሔ ።*

## ትርጉም

እንደሚዛን ቋት የተሰቀልህ (ክርስቶስ) ! የሜዶኑ ሃማ ሚዛን ምንህ ነው?
የጌላቡሄን ወርቅ በቀራንዮ ሚዛን ትመዝን ዘንድ
በእዝራ መቁጠሪያ የተቆጠረ ወርቅህ /ምስጋና
በሰው ሁሉና በአገሩ ሁሉ ትንሽ ነውን?
በፀሃይና በጨረቃ
የዮፍታሄን ፍርድ እንዳትፈርድ የሰሎሞንን ፍርድ ፈርደሃልና ።
ግን በአንዲት ያንዲት የፋቁሄ ጢም ምላጭ
የዳርዮስን አራዊት ወደ ራስህ መሪ የሆነ የይሁዳን ጢም ትላጫለህ ፤
የፋርስ ነገስታትን እጅ መንሳትን እጅ የነሱህ አሉና ፤
የቴቁሄንም ፈረሶች የጫኑልህ አሉና ።

## ምስጢር

የሚዛን ቋት በመመዘኛው እንጨት እንደሚንጠለጠል እንዲሁም ክርስቶስ ሆይ ! በእንጨት ላይ ተሰቀልህ ። የሜዶኑ ሃማ የተሰቀለው ስቅላት ምንህ ነው? አይገባህም ነበር ። ሳኦል በጌላቡሄ በገዛ እጁ የሞተውን ሞት በቀራንዮ ትሞት ዘንድ ወርቅ በማህተም እንደሚታተምና እንደሚቆጠር በእዝራ የሰመረ ምስጋናህ በየሰውና በያገሩ አይጓደ



www.ethiopianorthodox.org

ልም ። እውነተኛ ፈራጅ የመድሎኛ ፈራጅ ፍርድን እንደማይፈርድና የእውነተኛውን ፈራጅ ፍርድ በተፋራጆች ላይ እንደሚፈርድ ሁሉ የተቀበሉትን ወገኖቹን እንደተበቀለ እንደ ዮፍታሄ የሰቀሉህን አይሁድን አልተበቀልሃቸውም ። እንደዮፍታሄም ሌላን አልሰዋህም ራስህን ሰዋህ እንጂ ። ሰሎሞን ሲተኛ አይኑ እንደሚገለጥ እንዲሁም አንተ ሞተህ ስትገነዝ አይኖችህን አገለባበጥህ ። ሰሎሞን አንዱ ልጅ ለሁለት እንዲከፈል እንዳዘዘ አንተም የስቅላትህን ቀን ጨለማም ብርሃንም አደረግኸው ።

ጢሞን በምላጭ እንደመላጩት ራስህን በዘንግ ያስመታህን የይሁዳን ህይወት አጠፋህ ። የዳርዮስን አማናውያን (ሰማጆች በህይወት ያሉ) ዝሆንና አንበሳ ከእስክንድር የአንበሳና የዝሆን ምስሎች መድፎች ጋር ተጋጭተው በምስሎቹ ተኩስ እንደሞቱ የእነርሱ ድርጊት በአንተ ላይ ተደረገ ። ፋቁሄም የጦር ምክርን እንዳካሄደ በአንተም ምክረ ሞት ተፈፀመብህ በጦርም ተወጋህ ።

ሰብአ ሰገል እንደሰገዱልህና እንደገበሩልህ የአይሁድ ጦሮች ሰገዱልህ ከርቤን ከሀሞት ጋር ጠጣህ ለወርቅ ተሸጥህ ።

ቴቁሄ የልቅሶ አገር እንደሆነች እናትህና ሌሎች ሴቶች አለቀሱልህ። ይሁዳ የዳርዮስን አራዊት ወደራስህ መራ በማለት የዳርዮስ ገዳይ ተሰቅሎ እንደሞተ በመስቀል ላይ ሞትህ ይላሉ ባለቅኔው ።

## ታሪክ

እዝራ በእንዚራ ሲዘምርና አምላኩን ሲያመሰግን ኖሮ ከዚህ አለም በህይወቱ (ሳይሞት) ወደ ገነት ገብቷል ይባላል ።

ሰሎሞን ሲተኛ አይኑ ይገለጣል ሲነቃ ደግሞ ይጨፈናል እየተባለ ይተረካል ። ክርስቶስም ሞቶ የአርማትያስ ሰው ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ሲገንዙት አይኑን እያገለባበጠ "ለምን ዝም ብላችሁ ትገንዙኛላችሁ? ቅዱስ እግዚአብሔር ፣ ቅዱስ ኃያል ፣ ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት" እያላችሁ ገንዙኝ እንጅ ማለቱን የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ይተርካሉ።

በሜዶን ዳርዮስ እየተባሉ በመጀመሪያው ዳርዮስ ስም የነገሱ ነገስታት አሉ ። ከእነርሱም መካከል በእስክንድር ንጉስ ፅርእ ዘመን የነበረው ዳርዮስ አንዱ ነው ። ለማዳዎች የሆኑ ዝሆንና አንበሳ ነበሩት ። በዘመኑ የፅርእ ንጉስ የነበረው እስክንድር የበላይ ሊሆንበት (ሊያስገብ



www.ethiopianorthodox.org

ረው) ይፈልግ ነበር ። ስለዚህም እስክንድር በዳርዮስ ዝሆንና አንበሳ አምሳል የሚተኮሱ የመድፍ አንበሳና ዝሆን አሰርቶ ዘመተበት ። እስክንድርና ዳርዮስ ሲሰለፉ የዳርዮስ አንበሳና ዝሆን የእስክንድርን የአንበሳና የዝሆን መድፎች ሲገጯቸው ጊዜ ተተኩሰው ገደሏቸው ።

ዳርዮስንም የገዛ አሽከሩ አዘናግቶ መታውና ሊሞት ሲያጣጥር እስክንድር ደረሰበት ፤ እንደማይድን ስላወቀ አዘነና "እኔ የበላይነቴን እንጂ መሞትህንስ አልፈለግሁም ነበር አለው" እርሱም በመልካም ቃል ስላነጋገረው እንዳዘነለት አወቀና "የገደለኝ የገዛ አሽከሬ ነው ፤ እባክህ ጌታዬ ሆይ ተበቀልልኝ" አለው ። ስለዚህም እስክንድር "የዳርዮስን ገዳይ ባውቀው ከሁሉ በላይ አደርገዋለሁ" የሚል ቃል አወጀ ። ገዳዩም እሾማለሁ ብሎ "እኔ ነኝ" አለና ከእስክንድር ፊት ቀረበ ። እስክንድርም የዳርዮስን ገዳይ በእንጨት ላይ አሰቀለው ። (ዜና እስክንድር) ።

*16. ዕዝል ጉባኤ ቃና (489) አ*

*እሳት ወዕፀ ገዳም ሰፋሕ*

*ጊዮርጊስ ሰማዕት ወካህደ ልቡና ርሱሕ ።*

## ትርጉም

ሰማእት ጊዮርጊስና የተጠራጣሪ ሰው ልብ

እሳትና የሰፊ ዱር እንጨት ናቸው ።

## ምስጢር

እንጨቱን እሳት እንደሚባለው ከህደትን ጊዮርጊስ አጠፋው ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

*17· ዘአምላኪየ (106) አ*

*ዘአድማሱ ጀንበሬ (መልአከ ብርሃን)*

*ኦ ጠቢብ ለፍቅረ ዓለም ፍርሆ ፤*

*ዓለም አመ ቀርበተከ ወትብለከ አሆ*

*እስመ ትክህደከ ሥልሰ እስከነ ይነቁ ዶርሆ ።*

## ትርጉም

ብልህ ሆይ! የአለምን ፍቅር ፍራው ፣
አለም ብትቀርብህና እሺ በጀ ብትልህ
ዶሮ እስኪጮህ ድረስ ሶስት ጊዜ ትክድሃለችና ።

## ምስጢር

ሰውን ለማጥመድ ያህል የወደደ የሚመስል ሰው አለ ፤ እንደዚህ ያለው ሰው ተለዋዋጭ ስለሆነ እርሱን መራቅ እንጂ መቅረብ አይገባም ። ስለአለም ፍላጎት ያለመጠን መንሰፍሰፍም "ከሁለት ያጣ ጎመን" ያደርጋል ። ጴጥሮስ ዶሮ ሳይጮህ ክርስቶስን ሶስት ጊዜ እንደካደው ሁሉ ሰው ተወልዶ በህፃንነቱ ሲታመም ፣ ካደገም በሁዋላ አግብቶ ሲጣላና ሲፋታ ፣ ተሾሞ ሲሻር ፤ ወይም እንደተወለደና እንዳገባ ፣ እንደተሾመም ወዲያው ሲሞት በመወለዱና በማግባቱ ፣ በመሾሙም የነበረችው የአለም (ደስታ) ትቀርበታለች ። ዶሮ እስኪጮህ በማለትም ባለቅኔው ክርስቶስ በዳግም ምፅአቱ (ሁለተኛ ጊዜ ሲመጣ) ወዴት ነበራችሁ? ምንስ ሰራችሁ?" ብሎ የሚጠይቅ መሆኑን ያስረዳሉ ።

ታሪኩ በአንደኛው መጽሀፍ በገፅ 76 ተተርኳል ።

18· መወድስ (30)ኀ
ዘዘወልዱ (አለቃ)

ቀለመ ኢሳይያስ አብ ሶበ አማሰነ
ወልደ አንበሳ ኀይል ስምዖን አረጋዊ ፍርሃት መርሆ
ሞተ ወልደ ምውት ብልጣሶር እንበለ ይርአይ መሢሐ
ቃላተ አቡሁ ኢሳይያስ
አበየ ኢንቢ ወኢንብል አሆ ፤
እስመ ለጽልመት ያበርሆ
ወያጸልሞ ለበርሀ እስከ ድምፀ ዖፍ ወድምፀ ዶርሆ ፤
ወእስከነ ይወፅእ ባሕረ እዝራ አልባሰ ነፋሳት አንጺሖ
መካሕ ብእሴ ኀይል ከመ ኢሳይያስ ተመክሐ
በድምፀ አንበሳ ለላሕም እንዘ ያፈርሆ
ወለአንበሳ በድምፀ ላሕም እምንዋመ ባሮክ ያነቅሖ ።



www.ethiopianorthodox.org

## ትርጉም

የፍራት መከፈቻ ሽማግሌ የሆነ
የሃይል (አንበሳ ልጅ) ስምኦን የኢሳይያስን ቀለም ባጠፋ ጊዜ
የሙት ልጅ ሞት /ብልጣሶር መሲሁን (ክርስቶስን) ሳያይ
የአባቱ ኢሳይያስን ቃሎች
እንቢ አለ አንልም እሺም አለ አንልም ፤
ጨለማን ያበራዋልና
ብርሃንንም እስከወፍ ጫጫታና እስከዶሮ ጩኸት ያጨልመዋልና
እንደ ኢሳይያስም መመካትን የሚመካ የሃይል ሰው
የነፋሶች ልብሶችን አንፅቶ ከእዝራ ባህር እስኪወጣ
በአንበሳ ድምፅ ላምን እያስፈራው ነውና
አንበሳንም በላም ድምፅ ከባሮክ እንቅልፍ ያነቃዋል ።

## ምስጢር

አንድ የቁም ጸሃፊ ልጅ አባቱ የሚፅፍበትን ቀለም ከቀለም ቀንዱ ውስጥ ባፈሰሰ ጊዜ ፣ የአባቱን ቃል የማያከብር ባለጌ ይባላል ። አባቱ የሚፅፍበትን ቀለሙን ፣ ብእሩንና ብራናውን በጥንቃቄ ሲያስቀምጥ ግን ታዛዥ ፣ የአባቱን ፈቃድ ፈፃሚ መሆኑ ይረጋገጣል ። ነቢዩ ኢሳይያስ "ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች" ያለውን ቃል ስምኦን የተባለው አረጋዊ የአሪት ካህን "ሴት ልጅ ትፀንሳለች" ብሎ በመለወጥ ፅፏል ። በዚህ አፃፃፉ ስምኦን የነቢዩ ኢሳይያስን ቃል ማስተሃቀሩ (ማቃለሉና መናቁ) ሲሆን ባለቅኔው ግን አጠፋም አለማም አንልም ይላሉ። ምክንያቱም እርሱ ራሱ ከድንግሊቱ የተወለደው መሲህ ክርስቶስ ጨለማውን በብርሃን ፣ ብርሃኑን በጨለማ የሚለውጥ ነውና ። አንድ ጀግና ሰው ልዩ ጀብዱ ሰርቶ ከጦር አደጋ እንደሚወጣ መሲሁ ክርስቶስም በእዝራ በኩል ባህርን የሚገስፅ ነፋስ ሆኖ ታይቷል ፤ በኢሳይያስም በኩል በመመኪያ አርበኛ አምሳል ተገልጧል ይላሉ ባለቅኔው (ኢሳ· 7፡14) ።

19· ግእዝ ጉባኤ ቃና ስ

ድንግል ጠየቀት ዘአበዊነ አምሳለ ፤
ጸዋሬ ዜና መልአክ አምጣነ ኢበልዐ ቃለ ።

## ትርጉም

ድንግል የአባቶቻችንን ምሳሌ ተረዳች ፤
ወሬን የተሸከመ መልአክ ገብርኤል ቃልን አልበላምና ።

## ምስጢር

አባቶች የአንድን ሰው ሃቀኛነት ሲመሰክሩ እገሌ "ቃሉን አይበላም" ይላሉ ። በአንፃሩም የተበላ እንደማይገኝ የተናገረውን የማይፈፅም ሰውን ቃለ–በል ይሉታል ። ያልተበላ እንደሚገኝ እውነትም እያደረ ይገለጣል ። መልአኩ ገብርኤልም ቅድስት ማርያምን ያበሰራት ብስራት ትክክለኛነት በእግዚአብሄር ቃል ወልድ ሰው መሆን ታወቀ በማለት ባለቅኔው ያስረዳሉ ።

*20· ዕዝል ጉባኤ ቃና (108)አ*
*ለበሊዐ ኅብስተ ሮምያ መስቀለ*
*ቦአ ቃል እንግዳ ዐውደ ቀራንዮ መርጡለ ።*

## ትርጉም

የሮምያ እንጀራ መስቀልን ለመብላት
ቃል/እንግዳ ወደ ቀራንዮ አደባባይ ቤት ገባ ።

## ምስጢር

እንግዳ ሰው ምግብን ለመብላት ወደጋባዡ ቤት ይገባል ። ቃል የተባለ ክርስቶስም በመስቀል ለመሰቀል ወደ ቀራንዮ ሄደ ማለት በቅኔው ተገልጧል ።

*21· እዝል ጉባኤ ቃና (111)አ*
*ዘአፈወርቅ (መምህር ፡ ዘአክሱም)*
*አብ በታቦር እመ ነሠሥከ ዳግማየ ቃል ቃለ*
*ኢንረክብ ለከ ይእዜ ዳግሚተ ድንግል ድንግለ ።*



www.ethiopianorthodox.org

## ትርጉም

አብ! በታቦር የቃል ሁለተኛ ቃልን ብትሻ
የድንግል ሁለተኛ ድንግልን አናገኝልህም ።

## ምስጢር

አንድ ዝንጉ የሆነ ሰው የጣለውን እቃ ዘመዶቹ ፈልገው ከሰጡት በሁዋላ "አንተ ሰው የሰጠንህን እቃ ደህና አድርገህ ያዝ ፤ እንደገና ብትጥለው አናገኝልህም" ይሉታል ። እግዚአብሄር አብም በደብረታቦር ቃሉን ለቃሉ ለእግዚአብሄር ወልድ ቢያስማም ከድንግል ማርያም የተወለደውን ቃሉን ሌላዩቱ ድንግል በድጋሜ ልትወልደው አትችልም ይላሉ ባለቅኔው ።

*22· ዋዜማ/ስ*
*ዘጥፉነህ(አለቃ ፡ ዘቦታ ኪዳነ ምህረት)*
*በትልመ ገራህቱ ከመ ይረድ*
*ማየ ነቅዐ አቤል ሞት ዘእምነ እብን ፈልፈለ*
*አቢብ በዐለ አትክልት ዘለመደ ተክለ*
*ኅበ ታሕት ወላዕል እንዘ ያንሶሱ ወዐለ ፤*
*ማኅበረ ሕፃናት ድቀተ ዘሙሴ አኅጉለ*
*እስመ ወልድ በዓመት ከፈለ ።*

## ትርጉም

ከድንጋይ የመነጨ የአቤል
ምንጭ ውሃ/ሞት በእርሻው ትልም ይወርድ ዘንድ ፤
ተክልን የለመደ በአለ አትክልት/አቢብ
ወደታችና ወደላይ ሲመላለስ ዋለ ፤
ሙሴ ያስታጐለውን የህፃናት ማኅበር/ውድቀትን
ወልድ በአመት ከፍሏልና ።

## ምስጢር

የተክልን ጥቅም የለመደ ገበሬ ከድንጋይ ስር የፈለቀ የምንጭ ውሃ በእርሻው ትልም እንዲወርድለት ለማድረግ ወደታችና ወደላይ ይመላለ

ሳል ። የአትክልተኛው ምሳሌ አቡነ አቢብ በዛፍ ስር ሰይፍን ተክለው ከዛፉ ላይ ወደሰይፉ ተወርውረው ወደቁ ። እንደ እርሻም ቦይ ሰውነታቸውን በሰይፍ ሸነተራቸው (ወጋቸው) ። ከድንጋይ ስር የመነጨ ውሃ በእርሻው ትልም እንደሚወርድ በሰይፍ በተሸነተረው በአቢብ ሰውነት በድንጋይ ጭፍለቃ የተፈጠረ የአቤል ሞት ደረሰበት ።

አንድ የህፃናት ማኅበር (አለቃ) ሙሴ ያስታጎለውን የህፃናትን ማህበር አንዱ ልጅ በአሞት እንደሚከፍል የድንግል ማርያም ልጅም ህፃናት የሚወድቁትን መውደቅ ኮቲባ በተባለች አገልጋይ እጅ ወደቀ ። የማህበሩ ሙሴ ማህበሩን እንደማያስታጉለው የእስራኤል ነቢይና መስፍን ሙሴ በደብረ ታቦር አልወደቀም ይላሉ ባለቅኔው ።

## ታሪክ

የክርስቶስ ተከታይ የሆኑ ፃድቅ አቡነ አቢብ ክርስቶስ በእንጨት መስቀል ላይ ተሰቅሎ በዕለተ አርብ የሞተውን ሞት በማስታወስ አርብ አርብ ከእንጨት ስር ሰይፍንና ጦርን እየተከሉና ከዛፍ ላይ እየወጡ ከዛፉ ላይ እየተወረወሩ በሰይፍና በጦሩ ላይ ይተከሉ (ቁልቁል ይወድቁ) እንደነበር በገድላቸው ተፅፏል ።

ቅድስት ማርያም ህፃኗን ክርስቶስን ከሄሮድስ ሰይፍ ለማዳን ወደ ግብፅ በተሰደደች ጊዜ ችግር ስለፀናባት ከመንገዱ ወደ መንደር ጎራ ብላ ቁራሽ ብትለምን ኮቲባ የተባለች አገልጋይ ልጇ ክርስቶስን ነጥቃ በመሬት ላይ ጣለችው ይባላል ። ስለዚህም ባለቅኔው “ወልድ በአመት ከፈለ” ብለዋል (ነገረ ማርያም) ።

*23· መወድስ (193)አ*

*ዘዋሴ (አለቃ ፣ ዘድንግራ ማርያም)*

*ዘካርያስ አብ ቅድመ አቅልሎታ*
*ጾረ ከዊኖቱ ኅቱመ አውሥአተ ቃል ኢክሀለ ፤*
*ዘሰ ጽድቀ ማኅፀነ ማርያም ሐብለ ፤*
*ኢኮኑ በኢያቅልሎ*
*ክቡደ ጾረ ተደንግሎ አውሥአነ ቃለ ፣*
*ወበእንተዝ ቃለ አውሥኦ*
*በዘሰሎሜ ሰሌዳ ፊደለ ኑፋቄ ተሥዕለ ።*



www.ethiopianorthodox.org

*ላዕለ ደብርሂ ከዊኖታ ማርያምሃ ድንግለ*
*እሳተ መለኮት ዘተዋሐደ ማኅፀነ ማርያም ሐመልማለ*
*ይጠይቅ ቀርበ ወኢተአንተለ*
*ወልደ ዕንበረም እደ ሰሎሜ ዘተፍዕመ ነበልባል ።*

## ትርጉም

አባት ዘካርያስ ዝግ መሆኑ/ሸክምን
ከማቃለሉ በፊት ቃልን ማውሳትን አልቻለም ፤
ይህን እውነት ግን የማርያም ማህፀን አበለ(ዋሸ) ፤
ከባድ ሸክም/መደንገልን
ባለማቅለል ቃልን አውስቶናልና
ስለዚህም የማውሳት ቃል
በሰሎሜ (ብራና ፊደል) ጥርጣሬ ተሳለ (ተፃፈ)።
ነበልባልን የጎረሰ የእንበረም ልጅ/የሰሎሜ እጅም
ድንግል ማርያምን በመሆኗ/ተራራ ላይ
የመላእክት እሳትን የተዋሀደ
የማርያም ማህፀን/ልምላሜን ሊረዳ ቀረበ ፤ ቻልም አላለም ።

## ምስጢር

ከባድ ሸክምን ተሸክሞ በጣም የደከመ ተሸካሚ ሸክሙን አውርዶ እስኪያርፍ ድረስ ቢያናግሩትም መልስ አይሰጥም ። እንዲሁም የተሸካሚው ምሳሌ የሆነው ዘካርያስ በመልአክ የተዘጋው አፉ እስኪፈታለት ድረስ ሊናገር አልቻለም ነበር ። ግን አንዳንድ ሰው እውነቱን እንደሚያስተባብል የቅድስት ማርያም ማህፀን እንደ ዘካርያስ አፍ ዝግ ሲሆን የዘካርያስን በዝግነት አለመናገርን ነቀፈ ፣ ድንግልነትን ያለማቅለል የእግዚአብሔር አብ ቃል እግዚአብሔር ወልድን በድንግልና መውለድ ቻለ ። ብርቱ ኅበዝ ከባድ ሸክምን እንደተሸከመ ሳያወርደው በቃሉ በመዝፈንና በማቅራራት ከድካሙ እንደሚፅናናና ጉዞውን እንደሚቀጥል የቅድስት ማርያም ማህፀንም እግዚአብሔር ወልድን ከወለደ በሁዋላ በድንግልነት ኖረ ። የሰብአዊ ቃል ፊደል በብራና ወይም በወረቀት እንደሚፃፍ ሁሉ ድንግሊቱ ማርያም ሰማያዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድን

መፅነሷ በሰሎሜ ልብ ጥርጥርን ፈጠረ ። ከዚህም ሌላ ሙሴ በደብረ ሲና የተዋሀደች ለምለም እንጨትን እንዳየና ሊረዳ እንደቀረበ ፣ ቅድስት ማርያም አምላክን በመፅነሷ የተነሳ ተጠራጥራ ሆዷን የዳሰሰቻት የሰሎሜ እጅ በማህፀነ ማርያም በተፀነሰው በመለኮት እሳትነት ተኰማተረች ይላሉ ባለቅኔው (ነገረ ማርያም) ።

## ታሪክ

የአሪት ቤተ መቅደስ ሊቀ ካህናት ዘካርያስ የመጥመቁ ዮሃንስ አባት ነው ። ሚስቱ ኤልሳቤጥ መከነችበት ። ባልና ሚስት ስላዘኑ አምላክ ሰማቸውና ዮሃንስን እንደሚወልዱ የሚነግራቸውን መልአክ ላከላቸው ። መልአኩም ይህን ለዘካርያስ ቢነግረው የመውለድ ጊዜያቸው ከማለፉ የተነሳ የመልአኩን ቃል አላመነውም ። ስለዚህ መልአኩ "ይህ የተጠራጠርከው ነገር ሆኖ እስከታየው ድረስ አፈ ድዳ ሁን" አለው ።

መልአኩ እንዳለውም ዘካርያስም ዮሃንስ እስኪወለድ ድረስ አፈ ዲዳ ሆኖ ቆየ (ዘፀ·3፡1–7። ሉቁ·1፡5–25) ።

*24· ግእዝ ጉባኤ ቃና ስ*

*ተሣየጡ ጴወ ገባእተ ታሕቱ ወላዕሉ ፤*
*በኀዳጥ ጼው አምጣነ ይትቄሰም ዙሉ ።*

## ትርጉም

የታችና የላይ ገበሬዎች ጨውን ግዙ ፤
በጥቂት ጨው ሁሉ ይጣፍጣልና ።

## ምስጢር

በርበሬና ቅመማ ቅመም ሁሉ በጨው ይጣፈጣል ። የሰማይ መላእክትና የምድር ሰዎች ሁሉም በጨው በተመሰለው አምላክ በእግዚአብሄር ወልድ እውቀትን አገኙ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል (ማቴ·5፡13) ።

*25· ግእዝ ጉባኤ ቃና/ስ*

*በመካነ ሰላም ከመ ንትዋነይ ይደሉ ፤*
*ሰላም ርስት እስመ ተከፍለ ለዙሉ ።*



## ትርጉም

በሰላም/ቦታ እንጫወት ዘንድ ይገባል ፤
ሰላም/ርስት ለሁሉ ተከፍሏልና ።

## ምስጢር

ርስት ለሁሉ ሲከፈል ያገኙት ሁሉ በደስታ እርስ በርሳቸው ይዋደዳሉ ። ክርስቶስም ለአለሙ ሁሉ ሰላምን አደለ (ሰጠ) ይላሉ ባለቅኔው ።

*26· ሚበዝኑ/ስ*

*ዘምሥራቅ (አለቃ ፣ ዘኤልሻማ)*

*አዝማደ ሱራፌ አክናፍ*
*ተወከፍዎ ደርገ ለተክለ ሃይማኖት መፍቀሬ ዙሉ*
*ምንት እግር ገደፈከ እንዘ ይብሉ ፤*
*አኮኑ ርእይዎ ዘምስለ ዕሥራ ካህናት ወአርባዕቱ ዘላዕሉ ።*

## ትርጉም

የሁሉ ወዳጅ ተክለ ሃይማኖትን
ምን እግር ጣለህ እያሉ የሱራፌ
ዘመዶች/ክንፎች በአንድነት ተቀበሉት ፤
ከሃያ አራት የላይ ካህናት ጋር አይተውታልና ።

## ምስጢር

ተወዳጅ የሆነ ዘመድ በድንገት ከተፍ ሲል ዘመዶቹ "ዛሬስ ምን እግር ጣለህ እያሉ" በአንድነት ይቀበሉታል ። የሱራፌ ክንፎችም ለተክለ ሃይማኖት ስለተሰበረው እግሩ ምትክ ተሰጡት ። ከሃያ አራት የሰማይ ካህናት ጋርም እንዲያመሰግን አደረጉት በማለት ባለቅኔው የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን ተጋድሎና በተጋድሎአቸውም ያገኙትን ሰማያዊ ዋጋ አስረድተዋል ።

ታሪኩ በአንደኛው መጽሃፍ በገፅ 111 እና 237 ተተርኳል ።

*27· ዋዜማ (42)ኀ*



www.ethiopianorthodox.org

*ጸውዐ ሕማማተ*
*እመ ሕሊናሁ ፈቀደ መጥዎተ ርእስ ለእሉ*
*ቃል በጸጋ ዘኢኮነ ብዕሉ ፤*
*ቅንዋትሂ ጸድቃን ቀዊመ አእጋር ዘክህሉ*
*በሰፊሐ አእዳው ቆሙ ኀበ መስቀሉ*
*እስከ ይቤ ተፈጸመ ኵሉ*

## ትርጉም

ራሱን ለነርሱ
መስጠትን ቢወድ ቃል ብልፅግናው
በአይደለ ፀጋ መከራዎችን ጠራ ፤
የእግሮች ቁመትን የቻሉ ችንካሮች/ፃድቃንም
ሁሉ ተፈፀመ እስኪል ድረስ እጆችን
በመዘርጋት በመስቀሉ ዘንድ ቆሙ ።

## ምስጢር

አንድ ጌታ ሎሌዎቹን በቃሉ እንደሚጠራቸው የአብ ቃል እግዚአብሄር ወልድ መከራዎቹን በፈቃዱ ተቀበላቸው ፡ ራሱንም አሳልፎ ለእነርሱ ሰጠ ። ፃድቃንም በእግሮቻቸው ቆመው እጆቻቸውን በመዘርጋት እንደሚፀልዩ ችንካሮች በክርስቶስ እግሮች ገቡ ፡ እጆቹንም ከመስቀሉ ጋር ጠረቋቸው (አጥብቀው አሰሯቸው) ። የተጀመረ ስራ ተሰርቶ እንደሚፈፀም በክርስቶስም በመከራው ፍፃሜ ነፍሱን በስልጣኑ አወጣ በማለት ባለቅኔው የክርስቶስን (ሕማማተ መስቀል ፡ በመስቀል ላይ የተቀበላቸውን መከራና ስቃይ) በቅኔያቸው ምስጢር ተርከዋል ።

*28· ሥላሴ (47)ኀ*

*አዳም በትረ ተክህኖ*
*እንተ ቅርጸታ በትረ መንግሥት*
*እምነ አሐዱ ወሂአ ማእከሌነ ትሄሉ ፡*
*ወተቀሥፈ ባቲ ጸላኢነ ኵሉ ።*
*እመኒ ንኤብስ በታሕተ ሰማይ ዘላዕሉ*
*አበሳ ለሞት እንተ ይደሉ*
*ብነ ሀየ ጰራቅሊጦስ ቃሉ*
*እንተ ነሥአ ማቴዎስ አምሳሉ ።*



www.ethiopianorthodox.org

## ትርጉም

ቅርፅዋ የመንግስት ዘንግ
የሆነ ያማረች የክህነት ዘንግ
ከአንዱ ማርቆስ ወጥታ በመካከላችን ትኖራለች ፤
በርሷም ጠላታችን ሁሉ ተገረፈ ።
ለሞት የሚገባ በደልንም
ከላይኛው ሰማይ ብንበድል
አምሳያው/ማቴዎስ የያዘው (የተቀበለው)
ቃሉ/ ጰራቅሊጦስ በዚያ አለን ።

## ምስጢር

ቁመትዋ ቀጥ ያለ አንዲት ልምጭ ከአንድ ዛፍ ተቆርጣ ያጠፉ ልጆች ሁሉ ይገረፉባታል ። እንዲሁም ከቤተ መንግስት እኩል የሆነች የቤተ ክህነት ስልጣን ከወንጌላዊው ማርቆስ ተያይዛ መጥታ በኢትዮጵያ ገነነች ። ተቃዋሚም ሁሉ ይረታባታል ። በጰራቅሊጦስ (በመንፈስ ቅዱስ) ርዳታ ሃጢአት እንዲሰረይ የኢትዮጵያ ጳጳስ የነበሩት ግብፃዊው አቡነ ማቴዎስ ከማርቆስ በተቀበሉት ስልጣነ ክህነትም ይቅርታ ይገኛል ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

*29· አጭር ዥልክሙ (240)አ*

*አስቈቀወ ወልድ ዕጼ መቃብር በቃሉ ፤*
*እስመ ይመስሎ ዘይትበላዕ ኵሉ ።*

## ትርጉም

የመቃብር ትል/ልጅ በቃሉ አለቀሰ ፡
ሁሉ የሚበላ ይመስለዋልና ።

## ምስጢር

ልጅ ያየው ሁሉ የሚበላ ይመስለዋል ፡ የሌላውን ሰው ገንዘብም ካልወሰድሁ ብሎ ያለቅሳል ። በቅድስት ማርያም መቃብር የተቀበረለትን የማርያምን ስጋ ትል አላፈረሰውምና ልማዱን ለወጠ ይላሉ ባለቅኔው (ስንክሣር 21 ፡ ነሃሴ 16) ።

*30· ዘአምላኪየ/ስ*

*ዘአፈ ወርቅ ዘውዴ (አለቃ)*

*በመልዕልተ አእባን ተሐውር እንዘ ፀብረ ክረምት ትሌሊ*
*ወልድኪ እንተ የዐቅባ መቅደስኪ ጠሊ*
*ኦ ባዕልት እመ ኖላዊ ከሃሊ ።*

## ትርጉም

የቻይ ጠባቂ እናት/ባለፀጋ ሆይ! ልጅሽ የሚጠብቃት
መቅደስሽ ፍየል የክረምት ጭቃን እየለየች
በድንጋዮች ላይ ትሄዳለች ።

## ምስጢር

ልጅ የሚጠብቃት የባለፀጋ ፍየል በክረምት ጭቃ ላይ አትሄድም ፤ ጭቃውንም እየዘለለች በድንጋዮች ላይ ትራመዳለች ። የቅድስት ማርያም ልጅ ክርስቶስ የመሰረታትና ያፀናት የማርያም ቤተ መቅደስም በጭቃ ሳትገነባ በሶስት ድንጋዮች ብቻ ተሰራች ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ስንክ· ሰኔ 20 ፡ 21/ ።

*31· መወድስ (289) አ*

*ዘወርቅ አገኘሁ (አለቃ)*

*መጠነ ሀላዌየ ኮነ በመጠነ ቆሙ*
*ለመጸብሐዊ ዘኬዎስ ዘዐርገ ዲበ ሰግላ*
*ጊዜ ረኀቡ ይሴሰይ ኅጽሮተ አምላክ አስካላ*
*አነ እስመ ኮንክዎሙ በዓለም ኵላ*
*ለዐበይተ ጊዜ ከመ ኳሄላ*
*ከማሆሙ እኩን ኀበ ኢተውሀበኒ ተድላ ።*
*ልብየሰ አግዓዚት በምክረ ጻድቅ ክፋላ*
*ታንሶሱ ውስተ ደብር አክሊለ ስብሐት ተቀጺላ ፤*
*አምጣነ ምስሌሁ አቀመት ጽንዐ ተፋቅሮ መሐላ*
*እንዘ ኑፋቄ ዐረፍተ ጽልዕ ኢይትሐነጽ ማእከላ ።*



## ትርጉም

በራቡ ጊዜ አምላክን ማየት/ፍሬን
ይመገብ ዘንድ በሾላ ላይ በወጣ በገበሬ ወገን ዘኬዎስ
ቁመት ልክ የኑሮዬ ልክ ሆነ ፤
ለጊዜ ታላላቆች እንደጥንግ (ኳስ)
በሁሏ አለም እኔ ሆኛቸዋለሁና ፤
እንደነርሱ እንድሆን ድልድል ካልተሰጠች ዘንድ።
ልቤ/እመቤት ግን በእድሏ/የፃድቅ ምክር
ምስጋና/ አክሊልን ተቀዳጅታ ወደ ደብር ትመላለሳለች ፤
የጠብ ግድግዳ በመካከሏ ሳይሰራ
የመፋቀር ጥናት/መሃላን ከእርሱ ጋር አቁማለችና።

## ምስጢር

የራበው ሰው በራቡ ጊዜ ፍሬ ለመብላት እሾላ ላይ ይወጣል ። ዘኬዎስም በሾላ ላይ ኢየሱስን ለማየት ወጣ። የአንዳንድ ሰዎች ቁመት እንደሚተካከል የባለቅኔው ኑሮም እንደ ዘኬዎስ ቁመት አጭር ሆነ ። ምክንያቱም ኳስን ተጫዋቾቹ ወዲያና ወዲህ እንደሚያጉኑት ባለቅኔውንም ዘመናዮች አጉላሏቸው ።

ኳስ ተጫዋቾች እንዳደረጉት እንደሚሆን የባለቅኔውም እድል በጊዜያቸው በነበሩ ባለስልጣኖች አሳብ ተወሰነ ። ኳስ በደልዳላ ቦታ ላይ ካላኖሩት እንደሚንከባለል ባለቅኔውም ዘመናዮችን ለመምሰል እድል አላጋጠማቸውም ።

ንግስት አክሊልን ተቀዳጅታ(አክሊል በራሷ ላይ ደፍታ) በቤተ መንግስት ውስጥ እንደምትዘዋወር የባለቅኔው ልብም እድሏ በሆነ በመናኙ ፃድቅ ምክር ፀናች ። እግዚአብሄርንም ማመስገንን አዘውትራ በደብር መኖርን መረጠች ። የሚተማመኑ ሁለት ጓደኞች መሃላን ከተማማሉ በሁዋላ እንደማይከዳዱ የባለቅኔው አእምሮም እግዚአብሄርን በማመስገን ፍቅር ፀና ። የአንዳንድ ሰው ቤት የእንግዳ መቀበያ ክፍል በግድግዳ እንደማይከፈል የባለቅኔውም ልብ በመጠራጠር አይወላውልም በማለት ባለቅኔው ቤተ ክርስቲያንን ማገልገልንና ማስተማርን መርጠው የትውልድ ቦታቸውን ሳይለቁ መኖራቸውን በቅኔያቸው ገልጠዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

*32· አጭር ዋዜማ (301) አ*
*ዘገብረ ሥላሴ (መምህር ፡ ዘኤልያስ)*
*ክርዳድ ብሂሎተ በልዖ ለዮሴፍ ድንጋሌ*
*አርዌ ግብጽ ዮሴፍ በልሳነ አይሁድ ስንዳሌ ።*

## ትርጉም

ዮሴፍ ድንግልናን የግብፅ አውሬ ዮሴፍ
በላው ማለት እንክርዳድ በአይሁድ አንደበት ስንዴ አለ ።

## ምስጢር

እንክርዳድ ስንዴውን ዋጠው ማለት በገበሬው አንደበት ፡ ዮሴፍን የግብፅ አውሬ በላው ማለት በወንድሞቹ አንደበት እንደ ተነገረ የድንግል ማርያም ዘመድ ዮሴፍ የቅድስት ማርያምን ድንግልና አማሰነ ማለት በአይሁድ አንደበት ተነገረ ይላሉ ባለቅኔው ።

## ታሪክ

ኢየሱስ ክርስቶስ በድንግልና ተፀንሶ ፡ በድንግልና ከቅድስት ማርያም ሲወለድ ምቀኞች አይሁድ የዮሴፍ ልጅ ነው ብለውታል (ማቴ· 1 ፡ 18 25 ፡ 2፡ 13 15 ፡ 19 23)።

*33· ግእዝ ጉባኤ ቃና ስ*
*ዘደለለ (መሪጌታ ፡ ዘዋሸራ)*
*ተጋብኡ ሕዝብ በቤተ ስሞዖን ባዕል*
*አምጣነ የአምር ስምዖን አስተራክቦ ሰብእ ወእክል ።*

## ትርጉም

ህዝብ በስምኦን ባለጠጋ ቤት ተሰበሰቡ ፡
ስምኦን ሰውንና እህልን ማገናኘትን ያውቃልና ።

## ምስጢር

እነሆ ቸር ሰው ድግስ ደግሶ የመንደሩን ሰው ጠርቶ ሲያበላና ሲያጠጣ "እገሌ ሰውና እህልን ማገናኘት ያውቃል" ይባላል ። በአንፃሩም



በላኤ ሰብእ የሚባለው ስምኦን እህልን በበላበት ሆዱ ሰውንም በላበት በማለት ባለቅኔው ያስረዳሉ ።

*34· ዕዝል ጉባኤ ቃና/ስ*
*አይሁድ እግዚአ ኢረሰይዎ ለወልደ አምላክ ልዑል ፡*
*እስመ ምስለ ኖሎት ይውዕል እንዘ ይሰክብ በጎል ።*

## ትርጉም

አይሁድ የልኡል አምላክ ልጅን ጌታ አላደረጉትም ፡
በበረት እየተኛ ከእረኞች ጋር ይውላልና ።

## ምስጢር

የአንድ በሃብቱና በእውቀቱ የታወቀ ሰው ልጅ ከእረኞች ጋር በከብቶች በረት ውስጥ ተጋድሞ ሲውል የአባቱን ፈለግ አልተከተለም ፡ እንደአባቱም ትልቅ ሰው አልሆነም ይባላል ። አይሁድም ኢየሱስ ክርስቶስ በበረት ውስጥ ተወልዶ ባዩት ጊዜ አምላክ አልመሰላቸውም ይላሉ ባለቅኔው (ማቴ·1) ።

*35· ግእዝ ጉባኤ ቃና (10) ይ*
*ዘደስታ (አለቃ)*
*ይትወላወል ሰብእ ልበ ፈሪሳዊ ቀሊል*
*እምጊዜ ልደቱ አሪት እስከ ጊዜ ሞቱ ወንጌል ።*

## ትርጉም

ከመወለዱ ጊዜ/ኦሪት እስከ ሞቱ ጊዜ/ወንጌል
የፋሬስ ወገን የኒቆዲሞስ ልብ/ሰው ይወላውላል (ይዋልላል) ።

## ምስጢር

አንዳንድ ሰው ከልጅነቱ እስከሞቱ ጊዜ ሲዋልል ይኖራል ፡ ባቀደውና በሚሰራው አይፀናም ። የጀመረውን ሳይጨርስ ሌላ ይወጥናል። የአይሁድ አለቃ ኒቆዲሞስም በሌሊት የወንጌል ትምህርት ፡ በቀን የኦሪት ትምህርት ተከታይ በመሆን ዋለለ (ዋዠቀ) በማለት ባለቅኔው ያስረዳሉ።

ታሪኩ በአንደኛው መፅሃፍ በገፅ 288 ተተርኳል ።

www.ethiopianorthodox.org

*36· ዘአምላኪየ (405)አ*

*ዘገብረ ሥላሴ (መምህር ዘኤልያስ)*

*ፍቱለ ክሣዱ ለይስሐቅ መጥባሕተ አብርሃም ሐብል*
*ኮነ ማዕሠሮ ለበግዕ ዘሐቅል*
*መቃብሪሁ ለዮሴፍ በከመ ኮኖ ለቃል ።*

## ትርጉም

የዮሴፍ መቃብር ለቃል (ለእግዚአብሄር ወልድ)
እንደሆነ ሁሉ ለይስሃቅ አንገት
የተፈተለ የአብርሃም ቢላዋ/ገመድ የዱር በግ ማሰሪያ ሆነ ።

## ምስጢር

ለአንዱ በግ አንገት ማሰሪያ የተፈተለው ገመድ ለሌላው በግ አንገት ማሰሪያ ይሆናል ። እንዲሁም ለይስሃቅ አንገት ማረጃ በተቃጣው የአብርሃም ቢላዋ ለይስሃቅ ቤዛ የወረደው በግ ተሰዋበት ይላሉ ባለቅኔው።

## ታሪክ

ባለፀጋ የሆነ የአርማትያስ ሰው ዮሴፍ የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዝሙር ነበር ። ከአለት ድንጋይ የወቀረውን (የሰራውን) አዲስ መቃብር ለራሱ አዘጋጅቶ ሲኖር የስቅላት ሞት የተፈረደበት መምህሩ ኢየሱስ በመስቀል ተሰቅሎ ሞተ ። ቀኑ ሲመሽ ዮሴፍ ከአገሩ ከአርማትያስ መጥቶ የኢየሱስን ስጋ እንዲሰጠው ጲላጦስን ለመነው ። ጲላጦስም የኢየሱስን ስጋ እንዲሰጡት ዘበኞችን አዘዘለት ። ዮሴፍም የኢየሱስን ስጋ ከመስቀሉ አውርዶ ፣ በንፁህ በፍታ ገንዞ በዚያው ለራሱ ባዘጋጀው አዲስ መቃብር እንደ ቀበረው መቃብሩንም በታላቅ ድንጋይ ገጥሞት ወዳገሩ እንደሄደ ተፅፏል ።(ማቴ· 27 ፡ 57 61) ።

*37· ዋዜማ (511) አ*

*ዘነጋሽ ኀይሉ (አለቃ)*

*ሰይፍ መስተገብር*
*እምተገብሮ አዕረፈ በምድረ ጊዮርጊስ አካል ፤*
*ሳብዒት ዓመተ ኅድገት አኮኑ በዓል ፤*
*ወአመ ተፍጻሜት ብሀለ ንጉሠ ባቢሎን ገድል*
*"አኮኑ ሠለስተ ወደይነ ውስተ ነበልባል"፤*
*ራብዑሰ ገብርኤል አክሊል ።*

## ትርጉም

ሰይፍ/ገበሬ
ከማረስ በጊዮርጊስ ምድር/አካል አረፈ ፤
ሰባተኛዪቱ የመተው አመት በአል ናትና ፤
በፍፃሜው ጊዜ የባቢሎን ንጉስ/ገድል
"ከእሳት ውስጥ ሶስት ሰዎችን ጨምረን አልነበረምን?" አለ፤
አራተኛው ግን ገብርኤል/አክሊል ነው ።

## ምስጢር

በአራት ዘመን ገበሬው ምድሩን ስድስት አመት አርሶ በሰባተኛው አመት ያሳድረዋል (ምድሩ አይታረስም) ። ስለዚህ በሰባተኛዪቱ አመት የአመተ ህድገት በአል (ምድርን ከእርሻ የማሳረፍ በአል) ይደረጋል ። ሰይፍ የጊዮርጊስን አካል በሰባተኛው የስቃይ አመት ቆርጦ አሳረፈው ። የባቢሎን ንጉስ ናቡከደነፆር ሶስቱን የመንግስት ልጆች በእሳት ጉድጓድ አስጥሏቸው በማግስቱ ቢያያቸው አራት ሆኑበት ። ስለዚህ "የጣልናቸው ሰዎች ሶስት አልነበሩምን? አራተኛ አያለሁ እርሱም የእግዚአብሄርን ልጅ ይመስላል" እንዳለ ገድልም ሶስት ጊዜ ጊዮርጊስን አስገደለ ። ከሞት በሁዋላም አክሊልን አወረደ ይላሉ ባለቅኔው (ዳን·3) ።

ታሪኩ በአንደኛው መፅሀፍ በገፅ 55 ፡ 61 እና 101 ተተርኳል ።

*38· ዋዜማ (510) አ*

*ዘወልደ ማርያም ሀብቴ (አለቃ)*

*ኢመልአ ከመ ትካት*
*በርደተ መና ዝናም ዐውደ ዘካርያስ እክል ፤*
*ፋኑኤል ደመና አኮኑ ቀሊል*
*ወአመ በናዝሬት ይትገበር ከብካበ መርዓሁ ለቃል*
*ሁፅፍተ ልብሰ ወርቅ ይእቲ አጽባዕተ ድንግል ፤*
*ወሥዕርታ ዘሜላት ፋቱል ።*

## ትርጉም

የዘካርያስ እህል/
አውድማ በዝናብ/መና አወራረድ እንደቀድሞ አልሞላም ፡
ፋኑኤል/ደመና ቀላል ነውና ።
የቃል ሙሽርነት ሰርግም በናዝሬት በተደረገ ጊዜ
የድንግል ጣት/ሙሽራ የወርቅ ልብስን የተጎናፀፈች ሆነች ፡
ሃር የመሰለ ፀጉሯም የተሸረበ ነው ።

## ምስጢር

ዝናብ ሲያንስ (ድርቅ በሆነበት ዘመን) የነበሬው አውድማ እንደ ድሮው በእህል ምርት አይሞላም ። የዘካርያስም ሆድ መና አልገባበትም ። አውድማው በምርት ያልሞላው ደመናው አነስተኛ ሆኖ ዝናብን ባያዘንብ እንደሆነ የዘካርያስ ሆድም መናን ያልተመገበው መልአኩ ቅዱስ ፋኑኤል መናውንና ወይኑን እንደያዘ ወደላይ ስለተመለሰ ነው ።

የወንድ ሙሽራን መምጣት የምትጠባበቅ ሴት ሙሽራ በአዳዲስ ልብስና ጌጥ አሸብርቃ እንድትታይ ፡ የወልድ ሰው መሆን በገሊላ በተበሰረ ጊዜ የቅድስት ማርያም ጣት ሃርንና ወርቅን በማስማማት ፈተለች ። የሙሽራዩቱም ጠጉር ሃር ይመስላል እንደሚባል ማርያም የፈተለችውም ንፁህ ሃር ነው በማለት ባለቅኔው የማርያምን ፍፁም ድንግልናና የእጅ ስራ ባለሙያነት በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል ።

*39· ዋዜማ (513) አ*

*ቀለም ዘርአ ብእሲ*
*እንዘ ኢይቀድም ምንተ በዘፍጡራን ባህል*
*እምድንግል ጠማረ ብእሲ ተሠገወ ቃል ፡*
*እንዘ ኢይትረኀው ምንተ ማኅተመ ጠማር ድንግል*
*እስመ ለሕይወት መጽአ ቃለ ሚካኤል*
*ዘጸውዖ ገብርኤል አምሳል ።*

## ትርጉም

ቀለም/የሰው ዘር
በፍጥረቶች ባህል ምንም ሳይቀድም
ከድንግል/የሰው ደብዳቤ ቃል ሰው ሆነ ፤



የድንግል/ደብዳቤ መዝጊያ ሳይከፈት
ገብርኤል/ምሳሌ የጠራው
የሚካኤል ቃል ለህይወት መጥቷልና ።

## ምስጢር

ቅድስት ማርያም የእግዚአብሄር አብ ቃል እግዚአብሄር ወልድን በድንግልና ያለወንድ ዘር እንደፀነሰች የባህራን ጠማረ ሞት (የሞት ደብዳቤም) ሳትገለጥ ፤ በውስጧ የተፃፈውም የሞት መልእክት ሳይነበብ፤ ለባህራን ህይወት የሆነ የጋብቻ ቃል ተፅፎ ተገኘባት ። መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል የእግዚአብሄር አብ ቃል እግዚአብሄር ወልድ አዳምን ፡ ሄዋንንና የእነርሱንም ዘር ለማዳን ሰው እንደሚሆን ምስራች እንደተናገረ የቅዱስ ሚካኤል ቃልም ስለባህራን ህይወት ተነገረ ይላሉ ባለቅኔው (ስንክ·ሰኔ 12) ።

*40· ዋዜማ (72)ኀ*

*አባግዕ በዘነጸራ*
*በትረ ሌዋዊ ያዕቆብ በአምሳለ በትር ጥሉል*
*ተጽሕፈ ቀለመ አርአያ ዘበግዕ ፊደል ፤*
*ወእምዕጽቀ ዝንቱ ነገር ለነሢአ ጽጌ አምሳል*
*ብሉየ መዋዕል ወለደት ድኀረ መዋዕል*
*አረጋዌ ዘርእየት ድንግል*

## ትርጉም

የሌዋዊ ያእቆብ
በትርን በጎች በአዩ በሽልምልም በትር አምሳያ
የበግ (ፊደል አርአያ) ቀለም ተፃፈ ፤
ከዚህም ነገር ቅርንጫፍ አበባ/ምሳሌን ለመውሰድ
ሽማግሌን ያየች ድንግል ከዘመን በሁዋላ
የዘመን ሽማግሌን ወለደች ።

## ምስጢር

የያእቆብ ሽልምልም በትርን ያዩ በጎች በበትሪቱ አምሳያ (እንደ በትሪቱ የተዥጎረጐሩ) ግልገሎችን እንደወለዱ ቅድስት ማርያምም

www.ethiopianorthodox.org

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልን በሽበታም ሽማግሌ አምሳል አይታና በርሱ ተበስራ (ከርሱ የምስራች ቃልን ሰምታ) ከአለም በፊት ያለ አምላክን ወለደች ይላሉ ባለቅኔው (ዘፍጥ·29–30) ።

*41· ዋዜማ (73)ኅ*

*ንግረነ ተክለ አሚን*
*ለእመ አንተሁ ክርስቶስ እማየ ሕይወትከ ገድል ፤*
*ዳግመ ተወልዶ እስመ ሰብእ ይክል ፣*
*ወእመ ተወለጥከ ለነ በርእየተ ኪሩብ አካል*
*እም ደመና ሰማይ ልብስከ መጽአ ቃል*
*ስብሐቲሁ ወልድየ ዘይብል ።*

## ትርጉም

ተክለ ሃይማኖት! አንተ
ክርስቶስ እንደሆንህ ንገረን ፤
ከህይወትህ ውሃ/ገድል ዳግመኛ መወለድን ሰው ይችላልና ።
በኪሩብ አካል አምሳልም በተለወጥህልን ጊዜ
ከሰማይ ደመና በምስጋናው ልጄ የሚል
ልብስህ/ቃል መጣ ።

## ምስጢር

አይሁድ መጥመቁ ዮሃንስ "አንተ ክርስቶስ እንደሆንህ ንገረን" እንዳሉት ፃድቅ ተክለ ሃይማኖትም የክርስቶስን ስራ ሰሩ ። ክርስቶስ የሰውን ከውሃ መወለድ እንደተናገረ እንዲሁም ፃድቅ ተክለ ሃይማኖት በተሰጣቸው ፀጋ የተማፀነባቸውን ህመምተኛ ሁሉ በፀበል ውሃ ጥምቀት እንደቀድሞው ጤነኛ አደረጉት ይላሉ ባለቅኔው ።

የክርስቶስ መልክ በደብረ ታቦር እንደተለወጠ ተክለ ሃይማኖትም ከሰው አምሳል የተለየ የመልአክን መልክ ያዙ (የፀጋ ክንፎች አበቀሉ) ። ክርስቶስ በደብረ ታቦር ሲገለጥ "ልጄ ይህ ነው" የሚል ቃል ከደመናው እንደተሰማ ከተክለ ሃይማኖት ልብስም የምስጋና ቃል ተሰማ በማለት ባለቅኔው የተክለ ሃይማኖትን ተአምራታዊ ሃይል በቅኔያቸው ገልጠዋል።



www.ethiopianorthodox.org

*፵2· ሥላሴ (523) አ*
*ዘአልታሰብ (አለቃ ፣ ዘደብረ ኀይል)*

*ቀዳሜ ጸጋ*
*ኀይሉ ለአብ ወጥበቢሁ!*
*ቤተ ክርስቲያን ቅድስት አሐቲ ትዌድሰከ ወትብል*
*ወልድየ ኀይሉ ወእትየ ቃል ፤*
*ከመኒ እምኄር ባሕርያ ባሕርየ ኂሩትከ ብዕል*
*ወአካል ጸጋከ ዘእም አካል*
*ተዘከር ሥጋ ሀብተ መዋዕል*
*ዘነሣእከ እም ቅድስት ድንግል ።*

## ትርጉም

የልግስና ደገኛ
(ቸር) የአባት ሃይሉና ጥበቡ!
"ልጄ ሃይሉ ወንድሜም ቃል" እያለች
የተቀደሰች አንዲት ቤተ ክርስቲያን ታወድስሃለች ፤
የቸርነትህ ባህርይ/ብልፅግናም ከቸር ባህርይዋ እንደተገኘና
አካል/ልግስናህ ከአካል የተገኘ እንደሆነ
ከቅድስት ድንግል የነሳኸውን
የዘመን ስጦታ/ስጋን አስብ ።

## ምስጢር

ክርስቶስን መፅሃፈ ኪዳን የአብ ሃይሉና ጥበቡ የሆንህ የልግስና ደገኛ (ቸር) ይለዋል ። ከንቲባ ሃይሉ የተባሉት የጎንደር ከተማ ሹም ስጦታ ታላቅ ነው ፤ ጥበበኛም ናቸው ይላሉ ባለቅኔው ።

አንዳንድ ሙሽሪት ሙሽራዋን (ባሏን) ወንድሜ እንደምትለው ቤተ ክርስቲያንም ከንቲባ ሃይሉን እንደ ወንድም ታመሰግናቸዋለች ። የእግዚአብሄር ወልድ ቀዳማዊ ልደቱ ከአካል ከተገኘ አካልና ከባህርይ ከተገኘ ባህርይ እንደሆነ ፡ የከንቲባ ሃይሉ የቸርነታቸው ብልፅግናም ከቤተ ክርስቲያን ልግስና የተገኘ ነው ። ካህናት በፀሎት ጊዜ "ከቅድስት እናትህ የነሳኸውን ስጋ አስብ" በማለት ክርስቶስን እንደሚማልዱት

ከንቲባው ሃይሉም በዘመናቸው ያገኙት ሃብት በቤተ ክርስቲያን ፀሎት የተገኘ መሆኑን ማስታወስ ይገባል በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

*43· ሥላሴ (521)አ*

*በዕለት ዘኢ·ተዐውቀ*
*እምይባእ ፈርዖን ብሔረ ባዕድ*
*ቀሊል ውእቱ በስቁረተ መርፍዕ ማዕበል*
*ይኅልፍ ዘምስለ ንዋዩ ብንያም ገመል ፤*
*ወኵሉ ዘፈትሐ ማኅፀነ ኤርትራ ድንግል*
*ቅዱስ ውእቱ ለእሥራኤል ፤*
*አምጣነ ሀየ ብንያም ወሬዛ በኀይል*
*ወትእምርቱ ሚካኤል መስቀል ።*

## ትርጉም

ባልታወቀ ቀን
ፈርአን ወደባእድ አገር ከሚገባ
ብንያም/ግመል ከነገንዘቡ በመርፌ ቀዳዳ/ማእበል
ያልፍ ዘንድ ቀላል ነው ።
የኤርትራ/ድንግል ማህፀንንም የፈታ ሁሉ
ለእስራኤል ቅዱስ ነው ፤
ብንያም በዚያ በሃይል ጎልማሳ ነውና
ምልክቱም ሚካኤል/መስቀል ነውና ።

## ምስጢር

ክርስቶስ "ባለፀጋ መንግስተ ሰማይ ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀላል" እንዳለ ብንያም ከነሃብቱ ኤርትራን ተሻግሮ ሲሄድ ፈርአን ኤርትራን ተሻግሮ አልሄደም በኤርትራ ሰጠመ ። በእስራኤል ዘንድ የእናቱን ማህፀን የፈታ ሁሉ (መጀመሪያ የተወለደ ሁሉ) ለእግዚአብሄር የተለየ (የተሰጠ) እንደሆነ የኤርትራን ባህር የተሻገረ እስራኤልን አመሰገነ ። ጎልማሳም በሃይሉ እንደሚመጣ ብንያም በተአምር ዳነ ። የባህታዊ በትርም በመስቀል ምልክትነት እንደሚታወቅ ለብንያም



የተደረገው ተአምርም በሚካኤል የተፈፀመ ነው ይላሉ ባለቅኔው ። ታሪኩ በአንደኛው መፅሃፍ በገፅ 108–109 ተተርኳል ።

*44· ሥላሴ (529)አ*

*ሰማዕትነ ገላውዴዎስ*
*ነዳየ ዘመን ወመዋዕል*
*እንዘ ይረውጽ አልጸቀ እስከ አንቀጸ ቄሣር ገድል'*
*ወተርኀወ ሎቱ ሙባኡ መስቀል*
*ኅበ ፍርፋረ ሞት ተርፈ ወስቴ መከራ ጥሉል*
*ዐፃዌ ኖኅት አማኑኤል*
*አኮኑ ቀዊሞ በዴዴ አካል*
*ዘርኀብከ ዘርኀብከ ይብል ።*

## ትርጉም

የዘመንና የወራት ችግረኛ
ሰማእታችን ገላውዴዎስ
እየሮጠ እስከ ቄሳር በር/ግድያ ድረስ ደረሰ ፤
መግቢያው/መስቀልም ተከፈተለት ፤
ሞት/ፍርፋሪ ፣ የሚያለመልም መጠጥ/ መከራም ከተረፈ ዘንድ
ደጃፍ ዘጊ/አማኑኤል
በአካል/ደጅ ቆሞ
የተራብህ! የተራብህ! ይላልና ።

## ምስጢር

ዘመን የጣለው ችግረኛ መብልና መጠጥ ለድሆች ወደተዘጋጀበት ቤት እየሮጠ ሄዶ በተከፈተለት በር እንደሚገባ ሰማእት ገላውዴዎስም የክርስቶስን ወንጌል እየሰበከ በቄሳር በር አደባባይ ተሰቃየ ፣ ሞተ ። የቸር ሰው መልእክተኛ በደጅ ቆሞ "የተራብህ! የተራብህ!ና እንደሚል እግዚአብሄር ወልድ (አማኑኤል) ሰው ሆኖ የተቀበለውን መከራ በስሚ አምኖ የተቀበለውን ሁሉ "ወደ እኔ ኑ" ይላል ማለት በቅኔው ተመስጥ ሯል (ገድለ ሃዋርያት) ።

www.ethiopianorthodox.org

*45· ሥላሴ (532)አ*

*ገላውዴዎስ ሊቀ ጉባኤ*
*አልቦ ዘይብል በጉባኤከ*
*አልቦ ለጽዮን አሐቲ እምሊቃውንቲሃ ዘይብል*
*ባዕል ሥጋ ወነዳይ ቃል*
*ለባዕል ቃል ፤ ወሥጋ ነዳየ ቀዋሚ አካል*
*እስመ ይሰአኖ ስኢነ ኀይል*
*ወኢይትከሃሎ ግብረ ኢከሂል*
*ተዋሕዶ ዘቀለም ፈትል ።*

## ትርጉም

የጉባኤ አለቃ ገላውዴዎስ!!
በጉባኤህ ስጋ (የሰው)
ባለፀጋ ነው ፤ ቃልም ችግረኛ ነው
የሚል ከአንዲት ፅዮን ሊቃውንት የለም ።
የቋሚ አካል ድሃ የሆነ ስጋ የሃይል መድከምን
ይደክመዋልና ፤ ለባለፀጋ/ቃልም
የቀለምና የፈትል መዋሃድን
ያለመቻል ስራ አይቻለውምና ።

## ምስጢር

ባለፀጋውን ድሃ ድሃውንም ባለፀጋ ብሎ መናገር ልክ እንዳይደለ ከተዋህዶ በፊት ስጋ በቅድምና ነበር ፤ ቃልም ፍጡር ነው ማለትን የአክሱም ፅዮን ሊቃውንት አይቀበሉም ። ምክንያቱም የቀለምና የፈትል ተዋህዶ (መጣማት) እንደማይለይ ከአለም በፊት ከአብ የተወለደው የእግዚአብሄር ቃል (እግዚአብሄር ወልድ) ከስጋ ጋር የተዋሀደው ተዋህዶ የማይለይ ሆነ በማለት ባለቅኔው በቅኔያቸው የእግዚአብሄር ወልድን ሰው የመሆን ምስጢር ያስረዳሉ ።

*46· ሥላሴ (517)አ*

*ተማለቀ*
*አርዌ ላዕለ አዳም*



www.ethiopianorthodox.org

*አመ እደ ፍትወት ሰፍሐ በምግበ አሐቲ አባል*
*ከመ ያጽግብ ነፍሶ እምኀርምት አስካል ፤*
*አእዳወ ክርስቶስ ፍዳ ተአስሩ በፈትል*
*ተአስረ ሞት በሰናስል ፤*
*ወመልአከ ስሕተት ወረደ ውስተ ግበ ሀጉል*
*ሶበ ርእዮ ጥብሉለ በቈጽል ።*

## ትርጉም

ከተከለከለች ፍሬ ሰውነቱን
ያጠግብ ዘንድ የአምሮት እጅን በአንዲት አካል/ምግብ
በዘረጋ ጊዜ አውሬ በአዳም ላይ ተሳለቀ(ተዘባበተ) ፤
የክርስቶስ እጆች ግን በፈትል በታሰሩ ብድራት
ሞት በሰንሰለት ታሰረ ፤
በቅጠል ተጠቅልሎ ባየው ጊዜም
የስህተት መልአክም ወደ ጥፋት ጉድጓድ ወረደ ።

## ምስጢር

አንድ ሰው ሲሰርቅ በተያዘ ጊዜ ጠላቶቹ ይዘባበቱበታል ። አዳምም በእጁ የበለስን ቅጠል በበላ ጊዜ የጠላቱ የዲያብሎስ ተገዢ ሆነ ። ንፁሁን ሰው በእሰት ያሳሰረ ወስላታ ሰው በእርሱ ገመድ እንደሚገባም የክርስቶስ የሁዋሊት (የፊጥኝ)መታሰርም ሞትን ድል ነሳው ። በጨለማ የሚሄድ ሰውም በጉድጓድ እንደሚወድቅ ዲያብሎስም መጥፋትን አደረገ (ጠፋ) ። ክርስቶስም በበረት ተወልዶ በቅጠል ተጠቅልሎ በታየ ጊዜ ለዲያብሎስ “ዕሩቅ ብእሲ ፡ ባዶ ሰው” መስለው ይላሉ ባለቅኔው ።

*47· ሥላሴ (519)አ*

*መልክአ ልደትኪ*
*ማርያም ምስብኢተ ሞአ ሕብረ ፀዳል*
*እም ብርሃናቲሁ ለሰማይ ልዑል ፤*
*ለበዓለ ዝንቱ ፋሲካ ዘኢቀደሞ አምሳል*

*ትሰነቁ ምድር መስንቆ ቃል*
*ባሕርኒ ትዘብጥ ከበሮ ማዕበል*
*በእዴሁ ለነፋስ ኀያል*

## ትርጉም

ማርያም! የውልደትሽ
መልክ ከከፍተኛ ሰማይ ብርሃኖች ይልቅ
በብርሃን አይነት ሰባት እጅ አሸነፈ ፤
አምሳያ ላልቀደመው ለባለዚሁ ፋሲካ
ምድር የቃል/መሰንቆን ትሰነቁታለችና (ትመታለችና)
በሃይለኛ ነፋስ እጅም
ባህር ከበሮ/ማእበልን ትመታለችና ።

## ምስጢር

ሃይለኛ ሰው ብዙዎቹን ሰዎች ይደመበሳቸዋል ። እንዲሁም የቅድስት ማርያም መልክ ብርሃን የሰማይ ብርሃኖችን በለጣቸው ። ደግሞ በአል ላደረገ (ድግስ ላደረገ) ባለፀጋ ሰው አንዷቱ በመስንቆ ፤ ሌላዪቱ በከበሮ እንደሚዘምሩ (እንደሚዘፍኑ) እንዲሁም ሞቶ ለተነሳው ክርስቶስ ምድር እልል እልል ትላለች ። ባህርም በነፋስ ማእበሏን ታጮኸለች በማለት ባለቅኔው ቅኔያቸውን አመስጥረዋል (ስንክ. ግን. 21) ።

ታሪኩ በአንደኛው ፤ መፅሃፍ በገፅ 207 ተተርጓል ።

*48 ሥላሴ (516) ለ*

*ጥምቀተ ኢየሱስ መድኀኒነ*
*መሃይምናነ ገዘረ በመጥባሕተ መንፈስ ስሑል ፤*
*ወቤተ ንዴት ሐነጸ በብዕል ።*
*ጥምቀተ አሪትሰ መንፈቀ አሐቲ አባል*
*ኢያድኀነት ሕዝበ ለእስራኤል ፤*
*እስመ አርዑታ ክቡድ ወአኮ ቀሊል ፤*
*ወአሥልጦ እምቅኔ ኢትክል ።*



www.ethiopianorthodox.org

## ትርጉም

የመድሃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት
አማኞችን በተሳለ በመንፈስ /ምላጭ ገረዘ ፤
ችግር/ ቤትንም በብልፅግና አነፀ ።
የአንዲት አካል ግማሽ /የኦሪት ጥምቀት ግን
ለእስራኤል ህዝብን አላዳነችም ፤
ቀንበሯ ቀላል ያልሆነ ከባድ ነውና
ከግዛትም ማምለጥን አትችልምና ።

## ምስጢር

አንድ ወጌሻ ጨቅሎች ልጆችን በምላጭ እንደሚገርዝ የክርስቶስ ጥምቀትም ሰዎችን በመንፈስ ቅዱስ አደሳቸው ። አናጢ ቤትን በድንጋይ እንደሚገነባ የክርስቶስም ጥምቀት ልጅነትን በማሰጠት ምእመናንን አከበረ ። ቅዳጅ (ቁራጭ) ልብስ አካልን ከመራቆት እንደማያድነው የኦሪታዊ ዮሃንስ ጥምቀት ልጅነትን አላሰጠችም ። ከባድ የሆነ ቀንበርም ለመሸከም እንደሚያቅት የኦሪት ህግ "ስለአይን አይን ይጥፋ" በማለት የምትደነግግ ስለሆነ አስቀቂ ናት ። የዘላለምንም ህይወት አታስገኝም በማለት ባለቅኔው ስለኦሪትና ስለክርስትና ጥምቀት ያላቸውን እምነት ገልጠዋል ።

ታሪኩ በአንደኛው መፅሀፍ በገፅ 105 ተተርጓል ።

*49 ሥላሴ (526)*
*ዘያምሮት (አለቃ)*

*አመ ኮነ ተጋእዞ*
*አሐዱ ይፈዲ ፍዳ አካሉ ፤*
*እስመ እመ ሰወረ ዮሴፍ ጽዋዖ በልብሰ ሕሳዌ አምሳል*
*ብንያምሃ ሐመዮ አሕባል ።*
*ወእንተ ዳዊት ዘርዐ በገራኅተ ሥጋ አካል*
*ለእመ ትበልዕ ሜልኮል*
*እንበለ ትትወከፍ ዘርዐ ወሊዶተ ቃል*
*በንጽሕና ፈደየት ድንግል*

## ትርጉም

ክርክር በሆነ ጊዜ
አንዱ የሌላውን ብድር ይከፍላል ፤
ወገኖች ብንያምን አምጥተዋልና ።
ዮሴፍ ፅዋውን በውሸት /ልብስ ቢሸሽግ
ዳዊትም በስጋ እርሻ አካል የዘራውን
ሜልኮል ብትበላ
ዘርን ሳትቀበል ቃልን መውለድን
ድንግል በንፅህና ከፈለች ።

## ምስጢር

አንድ ሰው ብድሩን ሳይከፍል ሲሞት ወይም አገር ጥሎ ሲሰደድ ዋሱ ይከፍላል ። እንዲሁም የዮሴፍ የወርቅ ፅዋ በወንድሙ በብንያም ስልቻ ተደብቆ በመገኘቱ ወንድሞቹ ብንያምን በሌብነት ጠረጠሩት ። የእስራኤል ንጉስ የዳዊት ሚስት ሜልኮል ዘረ ቆርጥም ብትሆንም ድንግል ማርያም የአብን ቃል ያለዘር ወለደች ይላሉ ባለቅኔው ።
ታሪኩ በአንደኛው መፅሃፍ በገፅ 119 እና 159 ተተርኳል ።

*50 ሥላሴ (74) ጎ*
*ዘሀብተ ድንግል (ራቅ ማሰሬ)*

*በጽዮን በዓልከ*
*ነዐ ዳዊት ! ውስተ ጽዮን*
*ወመሰንቆከ ኢትርሣዕ እግዚእ ፤ እስመ ዘይእዜ በዓል*
*ዚአከ ፅፃ ወዚአከ ክፍል ፤*
*ሐሜተ ሜልኮልኒ ለእመ እፈርሀ ትብል*
*እምአመ ተቀብረት ሜልኮል*
*ብዙኀ ውእቱ ኑኀ መዋዕል*
*ወኢያሁ ጐልቆ ኢንክል ።*



www.ethiopianorthodox.org

## ትርጉም

በፅዮን በአልህ
ዳዊት ! ወደ ፅዮን ና
አቤቱ ! ጌታ ሆይ ! መሰንቆህንም አትርሳ ፤ የዛሬ በአል
ያንተ እጣ ናትና ያንተም እድል ናትና ፤
የሜልኮልንም አሜት እፈራለሁ ብትል
ሜልኮል ከተቀበረች
የዘመን ርዝመት ብዙ ነው
እርሱንም መቁጠርን አንችልም ።

## ምስጢር

የእስራኤል ንጉስ ዳዊት በፅዮን በተባለ አምባ ላይ ከትሟል (ከተማ ሰርቷል) ። ለታቦተ ፅዮንም በበገናው ዘምሯል ። በዚህ ጊዜ ሚስቱ ሜልኮል ነቅፋዋለች ።

የጎንደሩ ንጉስ አፄ ዳዊት ግን ለታቦተ ፅዮን በአል በመሰንቆው ቢዘምር አይነወርም ። ምክንያቱም እንደ እስራኤል ንጉስ እንደ ዳዊት ነቃፊ ሜልኮል የለችበትምና ይላሉ ባለቅኔው ።
ታሪኩ በአንደኛው መፅሃፍ በገፅ 159 ተተርኳል ።

*51· መወድስ ስ*
*ዘሐዲስ ኪዳናት (ቄስ ገበዝ ፡ ዘጸላሎ)*
*እግዚእ ምድረ ግብጽ ዮሴፍ ለእመ አድለወ*
*አመ አኀዊሁ አንበረ በመንበረ መንግሥት ክፍል*
*በመንበረ ታሕት ሰወሮ ለመንበረ ብንያም ላዕል ፤*
*ታሕታዊሰ ምድረ እለ ነበሩ*
*ልሁላን አኀወ ዚአሁ ለዮሴፍ ድንግል ።*
*አንተሰ አማኑኤል*
*ጸረ አድልዎቱ ለዮሴፍ እመ ነቢከ ቀሊል*
*ፈቀድከ ከመ ይንበሩ ለምህሮ ሐዳስ ወንጌል*
*ላዕለ እስራኤል አሕዛብ ወላዕለ አሕዛብ እስራኤል ፤*
*ወዘፈነውከ ሕማም ሐዋርያ ሞት ኢይብል*
*ዝ ቤተ ነዳይ ወዝ ቤተ ባዕል ።*

## ትርጉም

የግብፅ ምድር ጌታ ዮሴፍ ቢያደላ
በመንግስት ዙፋን ክፍል ወንድሞቹን ባስቀመጠ ጊዜ
በታች ዙፋን የላይ ብንያም ዙፋንን ሸሸገው ፤
ታላላቅ የሆኑ የድንግል
ዮሴፍ ወንድሞች ግን በታችኛው ምድር ተቀመጡ ።
አማኑኤል ! አንተ ግን
የዮሴፍ ማድላቱ ሸክም ባንተ ዘንድ ቀላል ቢሆን
በእስራኤል ላይ አህዛብ ፡ በአህዛብም ላይ እስራኤል
አዲስ ወንጌልን ለማስተማር ይቀመጡ ዘንድ ፈቀድህ ፤
የላክኸው ህማም/ የሞት ሃዋርያም
ይህ የድህ ቤት ነው ፡ ይህም የሀብታም ቤት ነው አይልም ።

## ምስጢር

በግብፅ ምድር ተሾሞ የነበረ የያእቆብ ልጅ ዮሴፍ ቀንተውበት ለነጋዴዎች የሸጡት ወንድሞቹ እህል ለመግዛት ከከነአን ወደ ግብፅ ባሄዱ ጊዜ ለታናሽ ወንድሙ ለብንያም ከሌሎች ወንድሞቹ የተለየ ስጦታ ሰጠው ። አማኑኤል የምትባል ኢየሱስ ክርስቶስ ! አንተ ግን በተነገረው ትንቢትና በተቆጠረው ሱባኤ መሰረት ወገኖችህ እስራኤል ትምህርትህን አንቀበልም ቢሉህ ፤ ትንቢት ያልተነገረላቸው ፡ ሱባኤ ያልተቆጠረላቸው አህዛብን ወንጌልህን ተቀብለው እንዲያስተምሩ አደረግህ ።

ወንጌልን ለማስተማር የተላከ ሃዋርያ በትምህርቱ ሃብታምንና ድሃን እንደሚያስተካክል አንተ የፈጠርኸው ሞትም ሃብታምንና ድሃን አይለይም ይላሉ ባለቅኔው ።

## ታሪክ

ብንያም የዮሴፍ ታናሽ ወንድም ነው ። ዮሴፍና ብንያም የአንድ አባትና የአንዲት እናት ልጆች ናቸው ። አባታቸው ያእቆብ እናታቸውም ራሄል ይባላሉ ። እናታቸው ራሄል ብንያምን በጭንቅ እንደተገላገለች ቤንአን ብላ ሰየመችው ። ቤንአን ማለት የጭንቀቴ ልጅ ማለት ነው ። ራሄል ወዲያውኑ ሞተች ። አባቱ ያእቆብ ግን ስሙን ብንያም ብሎ



www.ethiopianorthodox.org

ለወጠው ። ብንያም ማለት የቀኝ እጄ ልጅ ማለት ነው ። ዮሴፍ ያለእናት ያደገ ታናሽ ወንድሙ ብንያምን በጣም ይወደው ነበር (ዘፍጥ.35፥16–20፤ 42–45) ።

*52. መወድስ (178) አ*

*ዘአድማሱ ጀንበሬ (መልአከ ብርሃን)*

*ጽውዓነ በዓል ወፅኡ እንዘ ይትባሀሉ*
*ሥርዐተ ቤቱ ለኔሮን ሥርዐተ ኢይትበሀል ፤*
*ሶበ ለአርድእት ተሠርዐ ማዕደ ሮምያ መስቀል*
*ሊቀ ካህናት ሐዋሳት አካል*
*እንዘ ታሕተ ይነብር*
*ዘይቴሐት እግር እስመ ነበረ በላዕል ።*
*ዘንተሰ ተዋርዶ ከመ ኢንበል*
*ተዋርዶ ጳውሎስ አረጋዊ ለተናግሮ ኢይትከሀል ።*
*እስመ ተጸውዐ ይብላዕ ዘአመ ኔሮን በዓል*
*ሕፃናት ድኅረ ፀግቡ ትራፈ ሕፃናት ሰይፈ በቀል ።*

## ትርጉም

የኔሮን የቤቱ ስርአት ስርአት አይባልም
እየተባባሉ የበአል ተጠሪዎች /እድምተኞች ወጡ ፤
የሮም ማእድ /መስቀል ለሃዋርያት በተሰራ ጊዜ ፤
የካህናት (ሰውነቶች አለቃ) አካል
እታች ሲቀመጥ
ዝቅ ያለ እግር ከላይ ተቀምጧልና ።
ይህን ግን ውርደት ነው እንዳንል
የጳውሎስ ሽማግሌ ውርደትን ለመናገር አይቻልም ፤
በኔሮን በአል ጊዜ ህፃናት ከጠገቡ በሁዋላ
የህፃናት ትራፊ /የበቀል ሰይፍን እንዲበላ ተጠርቷልና ።

## ምስጢር

በድግስ ጊዜ ትልቁ እታች ትንሹ እላይ ተቀምጠው ሲታዩ “የእገሌ ቤት ስርአት ስርአት አይባልም ፡ እግር በራስ ነው” እንደሚባል

እንዲሁም የኔሮን ጣኦት አምላክ አይደለም ይላሉ ባለቅኔው ። የማእድ ምሳሌ መስቀል (ስቅላት) በሃዋርያት (በነጴጥሮስ) በታዘዘ ጊዜ የትልቅ ሰው ምሳሌ የሆነው አካል (ራስ) ሲዘቀዘቅ እግር በራስ ስፍራ ሆነ ። የህፃናትን ትራፊ የበላ የሽማግሌ ውርደት አይነገርም እንዲሉ ጳውሎስ የገሊላ ህፃናት የተቆረጡትን መቆረጥ በኔሮን ሰይፍ ተቆረጠ በማለት ባለቅኔው በክርስትና እምነት ምክንያት በሃዋርያት ላይ የተፈፀመውን ስቃይና መከራ ያስረዳሉ (ስንክ. ሐምሌ 5) ።

*53 መወድስ (179) አ*

*ዘፈንታ ገብርየ (መልአከ ብርሃን)*

*መፍትው ውእቱ አመ ሆሣዕና*
*ጽኑዕ አነ ድኩም ከመ ይበል ፣*
*እንዘ በዓለ ክንፍ ኪሩብ ፈረሰ ርእየቱ ጽዱል*
*በሩጸተ ኃይሉ ለሐንካስ ዕዋል*
*ጸዊሮ አምላከ ኀይል*
*ምስለ ተውሳኩ ትስብእት ዘይትፈቀድ ለበዓል ።*
*አይሁድሂ አዘማዲሁ መጠነ ተውህቦሙ ኀይል*
*አመ ዕለተ ዐርብ ተካየዱ ያንግሥዎ በመስቀል ፣*
*እስከነ ደምሰሰ ሎሙ በዐስበ ፃማ ቀሊል*
*ጥንተ ዕዳሆሙ ተናግሮ ዘጽሑፍ በእብነ ሐቅል ።*

## ትርጉም

በሆሳእና ጊዜ ደካማ
ብርቱ ነኝ ይል ዘንድ አግባብ (ተገቢ) ነው ፣
የብሩህ መልኩ ፈረስ /ኪሩብ ባለክንፍ ሲሆን
ለበአል ከሚፈቀድ
ከመጣየው/ ሰውነት ጋር የሃይል አምላክን ተሸክሞ
በአንካሳ/ ውርንጫ
ሃይል ሩጫ መድረስን ተስኖታልና (አልቻለምና)!
ዘመዶቹ አይሁድም ሃይል የተሰጣቸውን ያህል
በአርብ ቀን በመስቀል ያነግሱት ዘንድ ተማማሉ ፣



www.ethiopianorthodox.org

በዱር ድንጋይ የተፃፈ የእዳቸው መጀመሪያ /መናገርን በቀላል ድካም ዋጋ (ምንዳ) እስከደመሰሰላቸው ድረስ ።

## ምስጢር

"ከአንድ ብርቱ ሁለት ደካማ" እንዲሉ አንዱን ብርቱ ሁለት ደካሞች በመረዳዳት ያሸንፋሉ ። እንዲሁም ኪሩቤል በርቀቱ የተሸከሙትን አምላክ የአህያ ውርንጫ ከእነእናቱ እየተፈራረቀ በግዘፈ ስጋ ተሸከመው ። ስለዚህ ከኪሩቤል ሸክም የውርንጫ ሸክም ይከብዳል ። ኪሩቤል ቢሸከሙትም ይዘውት አልሄዱም ።
ውርንጫና እናቱ ግን ከቢታንያ እስከ ቤተ መቅደስ አደረሱት ።

ከዚህም ሌላ የአንድ አገር ሰዎች ተሰብስበው አንዱን አዋቂ ሰው ለሹመት እንደሚመርጡት ሆሳእና የተባለ ክርስቶስን የእናቱ የቅድስት ማርያም ወገኖች እስራኤል ተማምለው በመስቀል ሰቀሉት ። ተሿሚውም ስልጣኑን በተረከበ ጊዜ በመራጮች ላይ ያለ አግባብ የተጣለባቸውን እዳ እንደሚፍቅላቸው ሆሳእናም በድንጋይ የተነገረውን ሰብአዊ ምስጋናን ከማመስገን አይሁድን ለያቸው ይላሉ ባለቅኔው ።

ታሪኩ በአንደኛው መፅሃፍ በገፅ 90 ተተርኳል ።

*54 መወድስ/ አ*

*አኮ በግብር ተጸውዖ ስም ፣*
*እመኒ ተሐንጸ አረፍተ ልማድ ቃለ አምሳል*
*እስመ ኢይሰመይ ላሕመ በበሊዐ ቈጽል*
*ዘበግብር እንስሳ ወእርዌ ዘሐቅል*
*ባሕታዊ ትሩፈ ገድል*
*ወትሩፈ ገድል መርቅየን ባሕታዌ ኢይትበሀል*
*ክርስቶስኒ ለእመ ርኅበ እንዘ ውእቱ ባዕል*
*ነዳየ ባሕርይ ኢይሰመይ እስመ ለዙሉ ዘየአክል ፣*
*እመኒ ሰሐበ አባግዐ ሜጥ በሐብል*
*ዐሳብ ዘውገ ሰረቅት ኢይትበሀል በወንጌል ።*

## ትርጉም

የስም ጥሪ (ስያሜ) በስራ አይደለም ፣
ምንም የምሳሌ ቃል የልማድ ግድግዳ ቢሰራ

በግብር እንስሳና የዱር አውሬ ቂሆን
የመጋደል አትራፊ ባህታዊ
ቅጠልን በመብላት ላምን አይባልምና ፡
ግድያን አትራፊ
መርቅያንም ባህታዊን አይባልምና ።
ክርስቶስም ባለፀጋ ሲሆን ቢራብ
የባህርይ ችግረኛን አይባልም ፡ ለሁሉ የሚበቃ ነውና ።
የዋጋ (ሽያጭ) በጎችንም በገመድ ቢስብ
ደሞዘኛ በወንጌል የሌቦች ወገንን አይባልምና ።

## ምስጢር

በአብዛኛው የሰው ስም አጠራር በስራው አይገለጥም ። ከዚህም የተነሳ ይህን አለም ንቆ በጫካ ውስጥ እንደ እንስሳና አውሬ እየኖረ ቅጠል የሚበላ ባህታዊ (መናኝ) ባህታዊ እንጂ በቅጠል መብልና በጫካ ኑሮው ምክንያት እንስሳ ወይም አውሬ ተብሎ አልተጠራም ። በብህትውና ተጋድሎ ትርፍ ስራን የሰራ ባህታዊ መርቅያን ግን በስንበት በመፆሙ ምክንያት የቤተ ክርስቲያንን ስርአት በማፍረሱ የባህታዊነቱን ዋጋ አልተቀበለም ። አንድ ባለፀጋ በፈቃዱ ቢራብ ድሃ እንደማይባል ክርስቶስም አምላክ ሲሆን ራሱን ቢያስቸግር ለሁሉ የሚበቃ ባለፀጋ እንጂ ድሃ አይባልም ። በደሞዝ የተቀጠረ የበግ እረኛ የሚጠብቀውን በግ በገመድ ቢስብ ቢጎኝ ከሌባ አይቆጠርምና በማለት ባለቅኔው ስምና ግብር የማይተባበሩ መሆናቸውን ይገልጣሉ ።

55 መወድስ (79)ኀ
መንክር ውእቱ ግብረ ሆማዕና ፡
እንዘ ዲበ ኪሩብ ይትረአይ ረቂቀ ግልሳዌ አካል
እስመ ተርእየ ግዙፈ በዘፈቀደ ዕዋል ።
ዝኒ ዕዋለ አድግ
መካሕ ይቤ በቃሉ ልዑል
በኪሩቤል እትሜሰል
ወእመ ንእስኩ አነ ኢይንእስ እምኪሩቤል ።
እምክህነትሂ ወእምቅዳሴ አመ ሆማዕና በአል


www.ethiopianorthodox.org

ምሁራነ ኦሪት ካህናት ለእመ ተከልአ በወንጌል
ዘኢተምህሩ አእባን ግብረ ቅዳሴ በቃል
ተደለዉ ለቅዳሴ ቅዳሴ እም ይትሀጕል ።

## ትርጉም

የሆሳእና ስራ ድንቅ ነው ፡
የሶስተኛ አካል ረቂቅ ሆኖ በኪሩብ ላይ ሲታይ
በፈቀደው ውርንጫ የገዘፈ ሆኖ ታይቷልና ።
ይህም ተመኪ
የአህያ ውርንጫ በከፍተኛ ቃሉ
በኪሩቤል እመሰላለሁ አለ ፡
ባንስ ባንስም እኔ ከኪሩቤል አላንስም አለ ።
ከክህነትና ከቅዳሴም በሆሳእና በአል ጊዜ
ኦሪትን የተማሩ ካህናት በወንጌል ቢከለከሉ
የቅዳሴን ስራ በቃል ያልተማሩ ድንጋዮች
ቅዳሴ ከሚታጎል ለቅዳሴ ተዘጋጁ

## ምስጢር

አንድ ጀግና ሲፎክር "እዳገት ታይቶ እዘብጥ አዳሪ" እንደሚል ከሶስቱ አካላት አንዱ አካል እግዚአብሄር ወልድ በኪሩቤል እንዳለ ሆኖ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ሳይለይ ወደዚህ አለም መጣና ከቅድስት ማርያም ሰው ሆኖ ተወለደ ፡ ገዝፎ ታየ ። በአህያም ላይ ተቀመጠ ። አንዳንድ ትምክህተኛ ሰው ከአቅሙ በላይ ተንጠራርቶ "ማን ከማን ያንሳል" እንደሚል የአህያው ውርንጫ "ከኪሩቤል አላንስም" አለ ። ኪሩቤል በርቀት የተሸከሙትን ሆሳእናንም በግዝፍ ተሸከመ ። በስራውም ከኪሩቤል ይወዳደራል በማለት ባለቅኔው አመስጥረዋል ።

56 መወድስ (95)ኀ
ሀየንተ ሥነ ራሔል ሰይፍ ከዓዊተ ደም
እስከነ ሰብዐቱ ተቀንየ ጊዮርጊስ ኖላዌ ሐቅል ፡
አምጣነ ጠባብ ሰይፍ ብእሲተ ገድል
አክሊል ለምታ ጊዮርጊስ ባዕል
ወፈትለ እእዳው ትፈትል

*ዲበ ዐሥርቱ አህጉር ተሰየም እንዘ ትብል ።*
*ሕያወሂ ተራከበቶ ለርእሰ ጊዮርጊስ ቃል*
*ዘስማ መግደላዊት ማርያም ሰይፈ በቀል ፤*
*ወትንሣኤሁ ሰበከ መልአከ ብርሃን አክሊል*
*ዘተፈጥረ በአርምሞ እምነፋስ ወነበልባል ።*

## ትርጉም

ስለደም አፍሳሽ ራሄል/ ሰይፍ ውበት
የዱር እረኛ/ጊዮርጊስ እስከ ሰባት አመት ድረስ ተገዛ ፤
ብልሃተኛ የገድል ቤት/ ሰይፍ
ለባለፀጋ ባሏ ጊዮርጊስ አክሊል (ክብር) ናተና ፤
በአስር አገሮችም ተሾም
እያለች የእጀቿንም ፈትል ትፈትላለችና ።
ስሟ መግደላዊት የሚባል ማርያም/ የበቀል ሰይፍም
የጊዮርጊስ ራስ/ ቃልን ደህናውን ተገናኘችው ፤
ከነፋስና ከነበልባል በዝምታ የተፈጠረ
የብርሃን መልአክ/ አክሊልም ትንሳኤውን ሰበከ ።

## ምስጢር

ያዕቆብ ስለራሄል ውበት ለአባቷ ለላባ ሰባት አመት እንደተገዛ ቅዱስ ጊዮርጊስም ሰባት አመት ሙሉ ተሰቃይቶ በሰይፍ ተቆረጠ። መልካም ሴት ለባሏ ክብሩ እንደሆነች ሰይፍም ለጊዮርጊስ ክብርን አሰጠችው። የሰማእትነት አክሊልንም አቀዳጀችው። ሴት ፈትልን ፈትላ ባሏን እንደምታለብሰው ሰይፍም ለጊዮርጊስ ፀጋን አሰጠችው። ቀድሞ ክርስቶስን ሽቶ የቀባችው ማርያም መግደላዊት ከትንሳኤው በሁዋላም እንዳገኘችው ሰይፍም የጊዮርጊስን አንገት ቆረጠችው። አንድ አስተዳዳሪ የብዙ አውራጃዎች ሃላፊ ሆኖ እንደሚሾም ጊዮርጊስም ለአስር ተቆራረጠ። የማርያም አገር መግደል እንደሚባል በሰይፍ የመቆረጥ ውጤትም ሞት ሆነ ። የመልአክ ተፈጥሮ ከነፋስና ከእሳት እንደሆነ ጊዮርጊስም በሰይፍ የተገደለው በእሳት ከተቃጠለና በነፋስ ከተዘራ በሁዋላ ነው ይላሉ ባለቅኔው ።



ታሪኩ በአንደኛው መፅሃፍ በገፅ 58 እና 191 ተተርኳል ።

*57 መወድስ (97)ኀ*
*ዘዮፍታሔ*
*ፍዳ ተባርዮ አግብአ ዲበ ርእሰ ዞሉ*
*ኖላዌ ርኅራኄ ፍትሕከ አግብአ ፍዳ ሰብእ ዘይክል ፤*
*እንዘ ዲበ አራት ይነብር መፃጉዓ ደዌ ቀሊል*
*እስመ ከመ ያጠይቅ ተባርዮ*
*ነበረት በመልዕልተ ርእሱ አራቱ አክሊል ፤*
*ወኢይደልወነ አንክሮዝ ፤*
*ርቱዕ ፍትሕከ እስመ ዲበ ርእስከ ይትሌዐል ።*
*ኪሩቤልኒ አመ ጾሩከ በዘእንቲአከ ኀይል*
*አባግዐ ኬፋ አምጣነ ጾርከ ፍዳ ዘጾሩከ ኪሩቤል*
*ወለእመ መስቀል ተጽዕነ ላዕለ መትከፍትከ በቅል*
*እስመ ተጽዕንከ መልዕልቴሁ ለፈረሰ ሐማ ዕፀ መስቀል ።*

## ትርጉም

የርህራሄ ጠባቂ! የሰውን ብድር መመለስን
የሚችል ፍርድህ የፍርርቅን ብድራት በሁሉ ራስ ላይ መለሰ ፤
ቀላል የደዌ በሽተኛ በአልጋ ላይ ሲቀመጥ
ፈረቃን ያስረዳ ዘንድ
አልጋው/ አክሊል በራሱ ላይ ተቀምጣለችና ፤
ይህንም ማድነቅ አይገባንም ፤
ቀጥተኛ ፍርድህ በራስህ ላይ ወጥቷልና ።
ኪሩቤልም በአንተው ሃይል በተሸከሙህ ጊዜ
ኪሩቤል ስለተሸከሙህ ብድር (ፈንታ) የኬፋን በጎች ተሸክመሃልና፡
መስቀልም በትከሻህ/ በቅሎ ላይ ቢቀመጥ
በሃማ ፈረስ/ የመስቀያ እንጨት ላይ ተቀምጠሃልና ።

## ምስጢር

እውነተኛ ዳኛ ፍርድ ሳያዳላ ብድሩን ሁሉ አንድም ሳይቀር ያስከፍላል ። እውነተኛ ጠባቂ ክርስቶስ የፈረቃ ብድርን አላስቀረም (ሁሉንም እንደስራው ከፈለው) ።

www.ethiopianorthodox.org

አልጋ መፃጒእን በተሸከመችው ፈንታ በመፃጒእ ራስ ላይ እንደ አክሊል ሆነችበት (አልጋን ተሸከማት)። የሌላው ይቅርና ክርስቶስን ኪሩቤል በተሸከሙት ልክ እርሱ ደግሞ ሰዎችን ታገሰ። ክርስቶስ መስቀልን በትከሻው ቢሸከም ብድራቱ እንዳይቀር መስቀልም ክርስቶስን ተሸከመ (በመሰቀል ክርስቶስ ተሰቀለ) በማለት ባለቅኔው ይዋል ይድር እንጂ ሰው የእጁን የማያጣ መሆኑን በቅኔያቸው ምሰጢር አስረድተዋል ።

*58 መወድስ (80)ኅ*

*አእዛነ ፈረስ ነዮሙ ሐዋርያቲከ*
*በዘወሀብኮሙ አንተ ቁመተ ጸጋ አካል ፤*
*ወእም አርዳኢከ ደቅ እለ እሞሙ ወንጌል*
*ነዳይ ሀሎ ወሀሎ ባዕል ፤*
*አድልዎ እንዘ ኢትክል*
*እግዚአብሔር ፀሐይ ለኵሉ ዘተአክል ።*
*ከመሂ ኢይበሉ ኢሀለወከ አምሳል*
*በአጻብኢሆሙ ይግሥሥዎ ለምሳሌሆሙ ነበልባል ፤*
*እስመ እምአፃብዕ አዕዋም እለ ውስተ እድ ሐቅል*
*ቦ ዘይቴሐት ወቦ ዘይትሌዐል ።*

## ትርጉም

አንተ በስጠሃቸው በአካል
ፀጋ/ ቁመት ሃዋርያት የፈረስ ጆሮዎች ናቸው ፤
ማድላትንም ሳትችል ለሁሉ የምትበቃ
እግዚአብሄር/ ፀሃይ! ወንጌል እናታቸው ከሆነች
ከደቀ መዛሙርትህ/ ልጆች
ችግረኛ አለ ፤ ባለፀጋም አለ ።
እነርሱም አምሳያ የለህም እንዳይሉ
ምሳሌያቸው/ ነበልባልን በጣቶቻቸው ይዳስሱት ፤
በእጅ/ ዱር ውስጥ ካሉት ከጣቶች/ ዛፎች
ዝቅ የሚል አለና ፤ ከፍም የሚል አለና ።



## ምስጢር

ከአንድ አባትና እናት የተወለዱ ልጆች እንደ ፈረስ ጆሮዎች በቁመት የሚተካከሉ አሉ ። ለስብከተ ወንጌል ክርስቶስ የመረጣቸው ሃዋርያትም "በፀጋ የተቀበላችሁትን በፀጋ ስጡ ፤ እንዲያው የወሰዳችሁትን እንዲያው ስጡ" የሚለውን ትእዛዝ በመፈፀም አንድ ናቸው ። ደግሞ ከአንድ አባትና ከአንድ እናት ከተወለዱ ልጆች በቁመት የሚበላለጡ እንዳሉ ክርስቶስ ከመረጣቸው አስራ ሁለት ሃዋርያትም ከመመረጣቸው በፊት በድህነትና በብልፅግና የነበሩ አሉ ። ከዚህም ሌላ ሃዋርያት በስብከተ ወንጌል ፀጋ ከፍተኛነትና ዝቅተኛነት አላቸው ። ይህም ሲሆን ፀሃይ ለሁሉ እንደሚሞቅና አድልዎ እንደሌለበት ሁሉ አምላክም ጉድለትና አድልዎ የሉበትም ። እሳትን በእጅ መዳሰስ እንደማይቻል ከፍና ዝቅ ማለት መገረም አይገባም ። የመበላለጥን ምሳሌ ግን በእጆች ጣቶች መረዳት ይቻላል ። ምክንያቱም ከእንጨቶች ከፍና ዝቅ የሚሉ እንዳሉ ከጣቶችም ከፍና ዝቅ የሚል አለና በማለት ባለቅኔው አስተያየታቸውን በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል ።

*59 ሕንፄ ሃ(118)ይ*
*ዘወርቅነሀ ዋሴ (መሪጌታ)*

*በዘርእ ዘፈነዎ ሰማዕተ ወንጌል ባዕል*
*ዐምደ ቤት ወዐሊ ተመይጠ በሰብል ።*

## ትርጉም

የወንጌል ሰማእት ጊዮርጊስ/ ባለፀጋ
በዘር የላከው የቤት ምሰሶ/ ሎሌ በዝርዝር ጊዜ ተመለሰ ።

## ምስጢር

በጢት የተላከው ሎሌ ማታ ሲመለስ "በዘር የወጣ በዝርዝር መጣ" ይባላል ። እንዲሁም ቅዱስ ጊዮርጊስ የታሰረበት ያንዲት መበለት ቤት ምሰሶ ለመለመ ፤ አፈራ ፤ የእህል ዘር ከመብቀሉ በፊት ደረቅ እንደሆነ ምሰሶውም በተአምር ከመለምለሙና ከማፍራቱ በፊት ደረቅ እንጨት ነበር ይላሉ ባለቅኔው (ስንክሳር ህዳር 7)፡

ታሪኩ በአንደኛው መፅሀፍ በገፅ 58 ተተርኳል ።

www.ethiopianorthodox.org

*60 ዕዝል ዕጣነ ሞገር (218) አ*

*ዘገብረ ሥላሴ (መምህር ፡ ዘኤልያስ)*

*በዕለተ ነገደ ኤሳው ለንዒወ አርዌ እም ሐቅል*
*ነሢአ በግዐ ዘመርጡል*
*ቀደመ ያዕቆብ ነሢአ በረከት በክፍል ።*
*ወከዊነ አመት ለድንግል*
*እንዘ ልበ ድንግል ይንዑ ከዊነ እግዝእት ኃያኒ*
*ቀደመ ረጊዘ ከርሣ በመና ስሑል ።*

## ትርጉም

ኤሳው አውሬን ከዱር ለማደን በሄደ ጊዜ
የቤት በግን ይዞ
ያእቆብ በክፍል በረከት መቀበልን ቀደመ ።
ለድንግልም አገልጋይን መሆንን
የድንግል ልብ ቢያድን እመቤትን መሆን/ሃይለኛ በተሳለ መና
ሆዷን መውጋትን ቀደመ ።

## ምስጢር

በጦርነት ድል ካደረጉ ሁለት አርበኞች መካከል አንዱ ሌላውን ሲያይ ጓደኛው ቀድሞ ምርኮውን ይወስድበታል ። የይስሃቅ ልጅ ኤሳውም የዱር እንስሳ አድኖ አባቱን አብልቶ ለመመረቅ አስቦ አደን በሄደበት ስለዘገየ ወንድሙ ያእቆብ ለአባቱ የበግ ስጋ አብልቶ በረከቱን ወሰደበት ። የቅድስት ማርያም ልብም ለሌላዪቱ ድንግል አገልጋይ መሆንን ሲመኝ ሃይለኛ በጦር ሆድን እንደሚወጋ ሁሉ እመቤትነት በመና ሆዷን አጠገበ (በክርስቶስ ሆዷን ቀደሰ) ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

ታሪኩ በአንደኛው መጽሃፍ በገፅ 127 እና 253 ተተርኳል ።

*61 ዕዝል ጉባኤ ቃና (229) አ*

*ተርፈ ሎጥ አሐዱ ቅድመ ቅድመ ይርአይ ኵሎ*
*ኵነታ ለሰዶም እመ እመ ሀሎ ኢሀሎ ።*

## ትርጉም

አንዱ ሎጥ ሁሉን የሰዶምን ሁኔታ
ቢኖር ባይኖር (ቢኖርም ባይኖርም) ሳያይ ቀረ ።

## ምስጢር

እገሌ ባገር ቢኖርም ባይኖርም የሆነውን ነገር ምንም ሊያውቅ አይችልም ወሬም አይጠይቅም ይባላል ። ሎጥ ለጊዜው ከሰዶም በመውጣቱ ከሰዶም ሰዎች ጋር አልተቃጠለም ። በሰዶም ቢኖርም አምላክ በኪነ ጥበቡ ይጠብቀው ነበር እንጂ አይቃጠልም ነበር ይላሉ ባለቅኔው ።

ታሪኩ በአንደኛው መፅሃፍ በገፅ 47 ተተርኳል ።

*62 ዕዝል ጉባኤ ቃና (23)አ*

*ማሕጼ መርድኡ ለኤልሣዕ ዘኢተረከበ መሰሎ*
*ለየማነ ብርሃን ዘኤልሣዕ ማሕጼሁ እስመ እንዘ የኀሥሥ ሀሎ ።*

## ትርጉም

ለየማነ ብርሃን የኤልሳእ የተማሪው ምሳር
ያልተገኘ መስለው ፤ የኤልሳእን ምሳር እየፈለገ አለና ።

## ምስጢር

የነቢዩ ኤልሳእ ተማሪ ለቤት ስራ የሚሆን እንጨትን ሲቆርጥ ምሳሩ ከእጀታው ወልቆ በባህር ውስጥ ስጥሞበት ነበር ። ከአባ ኡምስጣቴዎስ ተማሮች መካከልም አንዱ ተጠራጣሪና ቂመኛ የሆነው የማነ ብርሃን እንደ ነቢዩ ኤልሳእ ደቀ መዝሙር ምሳር በኢያሪኮ ባህር ውስጥ ሰጠመ በማለት የጥርጥር ውጤቱ ቅጣት መሆኑን ባለቅኔው ያስረዳሉ (2 ነገስ· 1—5) ።

ታሪኩ በአንደኛው መጽሀፍ በገፅ 380 ተተርኳል ።

www.ethiopianorthodox.org

 www.ethiopianorthodox.org 

*63 መወድስ (230)አ*

*ፈታሕነ ብኪ ኢየሩሳሌም ፤*
*እስመ እምርኁቅ ኅሠሥኪ ዐቀብተ ሥራይ ዙሉ*
*ሆማዕናኪ ክርስቶስ እንዘ በቅሩብኪ ሀሎ ።*
*ወለነገርኪ ክቡደ ኢንብሎ*
*ሶበ እመጻሕፍት ንሴአሎ*
*እስመ ዘርዕኪ ነፋስ ወማእረርኪ ዐውሎ ።*
*ለሕሙምኒ አይሁዳዊ ዘደመ አባግዕ አቁሰሎ*
*እንዘ ኀጢአቱ ከመ ጽቡር በሐራውያ ናስተማስሎ ፤*
*አኮኑ ደዌሁ ኦሪት ዘይትቤቀሎ*
*ምዕረ ያሐይዎ ወምዕረ ይቀትሎ ።*

## ትርጉም

ኢየሩሴሌም ! ፈረድንብሽ ፤
መድሃኒትሽ ክርስቶስ በቅርብሽ ሳለ
ሁሉን የመድሃኒት ቀማሚዎችን ከሩቅ ፈልገሻልና ።
ነገርሽንም ከባድ አንለውም ፤ ከመፃህፍት
በተጠያየቅነው ጊዜ (በመፃህፍት ከተፃፈው ጋር ባገናዘብነው ጊዜ)
ዘርሽ ነፋስ ነውና አዝመራሽም ኩርፊት ነፋስ ነውና ።
የበጎች ደም ያቆሰለው በሽተኛ/አይሁዳዊም

ሃጢአቱ እንደጭቃው ሲሆን በእርያ እንመስለዋለን ፤
የሚበቀለው ደዌው ኦሪት
አንድ ጊዜ ያድነዋልና አንድ ጊዜም ይገድለዋልና ።

## ምስጢር

ሽማግሌዎች ከባሏ ጋር በምክንያት ለመፋታት የምትፈልግን ሴት "የእረኛ ሰነፍ ከቅርብ ሲሉት ከሩቅ" እንደሚባል" አንቺም ያቀረብሽው ነገር ፍሬ ቢስ ነው ፤ ደግ አላደረግሽም አየንብሽ" ይሏታል ። ከዚህም አንፃር ኢየሩሳሌም! በስጋ የሚፈውስና በነፍስ የሚያፀድቅ ሆሳእና የተባለ ክርስቶስ ቢያስተምርሽ ከእርሱ ይልቅ ጣኦትን መርጠሽ እርሱን



www.ethiopianorthodox.org

ለቀልሽ ። ስለዚህ አእምሮ ቢስ መባል ተገባሽ ። በነፋስና በኩርፊት (በአውሎ ነፋስ) የተበተነ አመድ እንደማይጨበጥ ሁሉ ስራሽ ህገ ወጥ ነው ።

በቁስል በሽታ የሚሰቃይ ህመምተኛም የቁስሉ እዥ እንደጭቃ ሲሆን ያዩት ሰዎች የመዳን ተስፋ የሌለው መሆኑን እንደሚረዱ የክርስቶስ ደም የፈረደበት የአይሁድ ወገን በበደል ላይ በደል ሰራ ።

እርያም ታጥቦ በጭቃ ውስጥ እንደሚገባ ይሁዳም የክርስቶስ ደቀ መዝሙር ከሆነ በሁዋላ ክርስቶስን ከድቶ የሰይጣን ተገዥ ሆነ ። አንዳንድ ህመምተኛ አንድ ጊዜ ሲታመም አንድ ጊዜ ሲድን በመጨረሻው በዚያው በሽታ ይሞታል ።

አይሁዳዊም በኦሪት አምኛለሁ ቢል የኦሪትን ህግ ስለማይፈፅም በኦሪት ይፈረድበታል ማለት በቅኔው ምስጢር ተገልጧል ።

*64 መወድስ (256)አ*

*እግዚአብሔር አብ አመ አስተርአዮ*
*ለአብርሃም ወልድ በፈለገ ትንቢት እንዘ ሀሎ*
*ማርያምሃ ሀገረ አወርሰከ ይቤሎ ፤*
*ወታውኅዝ ሐሊበ ሥጋዌ ዘያጸግብ ዙሎ*
*ወሕገ አምላኩ መዐረ ሴሎ*
*እም ርእሰ መለኮት ሳኔር ወእም ዔርሞን ተሣህሎ ።*
*ሱራፌልሰ የዐቅብዎ ኀበ ገነተ ወልድ ተሰቅሎ*
*ኢይግባእ ዕጉለ አርዌ ይሁዳ በተሀብሎ ፤*
*ወለሥጋ ድንግል ኢዮብ በደመና መንፈስ ወዐውሎ*
*ገብርኤል ከመ አምላኩ እግዚአብሔር ተሰአሎ ።*

## ትርጉም

እግዚአብሄር አብ ለአብርሃም ወልድ
በትንቢት ወንዝ ሳለ በታየው ጊዜ
ማርያም/አገርን አወርስሃለሁ አለው ፤
እርሷም ሁሉን የሚያጠግብ ሰው መሆን/ወተትን ታፈሳለች ፤
የአምላኩ ህግ/የሴሎ ማርንም
ከመለኮት/ሳኔርና ከኤርሞን ይቅርታ ራስ ታፈሳለች ።

ሱራፌል ግን የአውሬ ልጅ/ይሁዳ በመደፋፈር እንዳይገባ
በወልድ ገነት/መስቀል ዘንድ ይጠብቁታል ፤
የድንግል ስጋ/ኢዮብንም በመንፈስና በአውሎ ነፋስ ደመና
ገብርኤል እንደ አምላኩ እግዚአብሄር ጠየቀው ።

## ምስጢር

እግዚአብሄር አምላክ ለአብርሃም በወንዞች መካከል በታየው ጊ "ወተትንና ማርን የምታፈስ አገርን አወርስሃለሁ" እንዳለው ሁ እግዚአብሄር አብ የባህርይ ልጁን እግዚአብሄር ወልድን በተነገረለ ትንቢት መሰረት የቅድስት ማርያምን ስጋ እንዲለብስ ላከው ። ከነአ ሁሉን የሚያጠግቡ ወተትንና ማርን ሳኔርና ኤርሞን ከሚባሉ ተራሮ ራስ እንደምታፈስ ሁሉ ፣ ቅድስት ማርያም የእግዚአብሄር ወልድ ሰ መሆንንና የአምላክን ህግ ከመለኮትና ከይቅርታ ስራ አስገኘች ። አዳ ተደፋፍሮ ወደ ኤደም ገነት እንዳይገባ ሱራፌልና ኪሩቤል የሚባ መላእክት የገነትን በር በእሳት ሰይፍ እንደጠበቁት እግዚአብሄ ወልድን ያሰቀለው ይሁዳ ከፅድቅ ውጭ ሆነ ። ከዚህም ሌላ እግዚአብሄ ኢዮብን በደመና እንደጠየቀው ቅዱስ ገብርኤል በአበሰራት ጊዜ የሚ ያም ስጋ በመንፈስ እግዚአብሄር ተቀደሰ ይላሉ ባለቅኔው (ዘፍጥ· —12 ፡፡3 ፥24) ።

*65 ሚበዝኁ (52)አ*

*እክለ አበሳሃ ለሔዋን*
*ከመ ተርእየ ኢኮነ በገራህተ ኤዶም ቅድመ ፤*
*ዝናመ ተሰቅሎ አምላክ እስመ በመስቀል ቆመ ፤*
*ዝኒ መስቀል ነገረ ጽድቁ ትሩፍ ለእረጋዊ ፈጸመ ።*

## ትርጉም

የሄዋን በደልዋ/እህል
በኤዶም እርሻ ቀድሞ እንደታየ አልሆነም ፤
የይቅርታ ዝናብ/አምላክ በመስቀል ቆሟልና ፤
ይህም መስቀል ለሽማግሌ የትርፍ ፅድቁ ነገርን ፈፀመ ።



www.ethiopianorthodox.org

## ምስጢር

የክረምቱ ዝናብ በመስቀል ስለቆመ የዘንድሮ ሰብል በእርሻው ላይ እንደታየው አልሆነም ይባላል ። ሄዋን የበደለችው በደልም በገነት እንደተሰራ አልታሰበም ። ምክንያቱም ክርስቶስ በደሏን ይቅር ብሎ በመስቀል ስለተሰቀለላት ነው ። ነገረ ፈጅ የወከለውን ሰው ነገር እንደራሱ ጉዳይ አስቦ እንደሚፈፅም መስቀልም አዳምን ነፃ አወጣው በማለት ባለቅኔው የክርስቶስን መሃሪነት በቅኔያቸው ምስጢር አስረድተዋል ።

*66 ሥላሴ (540)አ*

*አብርሃም ወይሁዳ*
*ዐስበ ኖላዊሆሙ ኢያትረፉ ፤*
*አኮኑ ትጉህ ኖላዊ በአባግዒሁ ዘደክመ*
*አውፅአ ሠላሳ ወአቀመ ላሕመ ፤*
*እምዝኒ ኢይርአይ ኖላዊ ዘአባግዒሁ ሕሰመ*
*በአንፃረ ላሕም እምድኅረ ቆመ*
*አፍራሰ እሳት ሎጥ በእግሩ ቀደመ ፤*
*ወነነዌ እሳተ ለጐመ ።*

## ትርጉም

አብርሃምና ይሁዳ
የጠባቂያቸውን ደሞዝ አላስቀሩም ፤
በበጎቹ የደከመ ትጉ እረኛ
ሰላሳ ብርን አውጥቷልና ፣ ላምን(በሬን)ም አቁሟልና
ከዚህም የተነሳ ጠባቂ የበጎቹን ክፋት እንዳያይ
በላም አንፃር ከቆመ በሁዋላ
ሎጥ የእሳት ፈረሶችን በእግሩ ቀደመ ፤
ነነዌም እሳትን ለጎመ ።

## ምስጢር

ሃቀኞች ሃብታሞች የከብት እረኞቻቸውን ደመወዝ አያስቀሩም ። አንዱ ሰላሳ ብር ሌላውም ወይፈን(ጊደር)ይሰጡታል ። በአንፃሩም

ባለቅኔው የአለም እረኛ (ጠባቂ)የሚባል እግዚአብሔር ወልድ በአብርሃም
ቤት የተሰዋለትን ወይፈን ማንሳቱንና በይሁዳ እጅ ለሰላሳ ብር መሸጡ
ጠቅሰዋል ። አያይዘውም የበጎች እረኛ (ጠባቂ) ከባለበጉ ደመወዝን ሲ
እግዚአብሔር ወልድ ግን አለምን የመጠበቁን ዋጋ ከአብርሃምና ከይሁ
አልፈለገም ። ለአብርሃም የሰዋለትን ወይፈን አነሳለት ። በማለ
ባለቅኔው ቅኔያቸውን አመስጥረዋል ።

ታሪኩ በአንደኛው መፅሀፍ በገፅ 302 ተተርኳል ።

*67 ሥላሴ(1006)ጎ*

*ኖላዊነ ፋሲለደስ*
*እስኩ ኢትኑም በወርኀ ጸብእ*
*እመ በወርኃ ጸብእ ደቀሰ ናዝራዊ ሰረቅተ አምጽአ ድካመ*
*እስመ ጸጉረ ርእሱ ላጸይዎ ቅድመ ፤*
*ወለዘአብዝኀ ሳእል አግዓዚ ንዋመ አግብርት ጥዑመ*
*ሰራቂ ይቅትሎ አስተሐመመ*
*ወጊዜ ተግባሩ አምላክ ሰረቀ ዐፅመ*
*እምገቦሁ ለአዳም ዘኖመ ።*

## ትርጉም

ጠባቂያችን ፋሲለደስ
እስኪ በጦብ ወራት አታንቀላፋ ፤
የናዝሬቱ ሶምሶን በጦብ ወራት ቢያንቀላፋ ድካምን የማምጣት ሌቦች
የራሱን ጠጉር በቅድሚያ ላጭተውታልና ፤
ጣፋጭ የሰራተኞች እንቅልፍን ያበዛ ሳኦል! ጌታንም
ሌባ ይገድለው ዘንድ ተግቷልና
አምላክም በሰራው ጊዜ አጥንትን
ከአንቀላፋ ከአዳም ጎን ሰርቋልና ።

## ምስጢር

ባለቤት እንቅልፋም ከሆነ ሌቦች አጥሩን ጥሰው ግድግዳውን
ምሰው ፣ እቤት ውስጥ ገብተው ሃብቱን ሙልጭ አድርገው ይወስዱበ
ታል። የበጎችም ጠባቂ ቸልተኛ ሲሆን በጎቹን አውሬ ይነጥቃቸዋል ።
ስለዚህም "እገሌ! እንደ እገሌ እንዳትሆን ተጠንቀቅ" በማለት ወዳጅ
ወዳጁን ይመክረዋል ። በአንፃሩም ሰማእቱ ቅዱስ ፋሲለደስ "በጦብ ጊዜ
አታንቀላፋ ፤ በጦርነትም ጊዜ እርዳን ቸል አትበለን" ይላሉ ባለቅኔው ።"
ያልጠረጠረ ተመነጠረ" እንዲሉ ሶምሶን በሚስቱ በደሊላ መጠጥ
ተታሎ ከተኛ በሁዋላ የሃይሉ ምንጭ የነበረው የራሱ ጠጉር በመቆረጡ
በጠላቶቹ ተሸነፈ ። ከባድ እንቅልፍ የያዘው ሳኦልም ፣ ጠላቱ ዳዊት
ከተኛበት ዋሻ ገብቶ ከራስጌው ጦሩንና እርኮቱን ሲወስድበት አልነቃም
(1ሳሙ·26፥11) ። የአዳምን አጥንት የነቀለው ሲያንቀላፋ ነውና ሰማእቱ
ፋሲለደስ! ጠላታችን በድንገት አደጋ እንዳይጥልብን ጠብቀን የሚል
ፀሎታዊ ምስጢር በቅኔው ተገልጧል (ዘፍጥ·2፥20 — 25) ። መሳ·16፥
4 — 22 ። 1ሳሙ·24 — 26 ። ገድለ ፋሲለደስ) ።

*68 መወድስ /ሰ*
*ዘካሳ(አለቃ)*

*መጽሐፈ ሕማም ጸሐፈ በአጻብዒሁ*
*ገብረ መርዓዊ ሕግ ሊቅ እንተ መነነ ዓለመ ፤*
*ወመጽሐፈ ሕማም ውእቱ ጊዜ ተርጎመ*
*ቅዱሳን አእጋሪሁ*
*በበፍኖቶሙ አስቆቀው ደመ ፤*
*አኮኑ ኢተፈጸመ*
*ሥርዓተ ዓለም ከብካቡ ብእሲ እስከ ተደመ ።*
*ዕፄያትሂ ደቂቀ ቤቱ እለ ኀደጉ ንዋመ*
*ለመጽሐፈ ሕማም አንበብዎ ልሳኖሙ እስከ ደከመ ፤*
*ገብረ መርዓዊ ሕግ ሊቅ እስመ በማእከሎሙ ቆመ*
*ይሰማዕ ሥቃያተ ንባበ ወቀለመ ።*

## ትርጉም

አለምን የናቀ የህግ ሊቅ/ገብረ ክርስቶስ
በጣቶቹ መፅሃፍ /ህማምን ፃፈ ፤
እርሱም መፅሃፍ/ህማምን በተረጎመ ጊዜ
ቅዱሳን/እግሮቹ
በእየመንገዳቸው ደምን አለቀሱ ፤
ሰው እስከተደነቀ ድረስ

የአለም ስርአት/ሰርጉ አልተፈፀመምና ።
እ/ንቅልፍን የተው የቤቱ ልጆች/ትሎችም
እንደበታቸው እስከደከመ ድረስ መፅሃፍ/ህማምን አነበቡት ፤
ስቃዮች/ንባብንና ቀለምን ሊሰማ
የህግ ሊቅ ሙሽራ ገብረ ክርስቶስ በመካከላቸው ቁሟልና ።

## ምስጢር

አን/ድ ሊቅ መፅሃፍን በብእር እንደሚፅፍ ገብረ ክርስቶስ በቁስል ህማም ጣቶቹን ተቆረጠ ። የሃይማኖት ሊቅ ሲሰብክ ምእመናኑ የበደላቸውን ብዛትና የእግዚአብሄርን ታጋሽነት እያመዛዘኑ እንደሚያዝኑና እንደሚያለቅሱ ገብረ ክርስቶስም በታመመ ጊዜ እግሮቹ ደሙ ።

በአንድ ሃገር የተለመደ ወግ በአንድ ችኩል ሰው ሲጣስ ያየ አስተዋይ ሰው በአድራጎቱ እንደሚገረም ፤ የገብረ ክርስቶስም ከሙሽሮች ግንኙት የተለየ ሆኖ አስደናቂ ታሪክን አተረፈ ። እንቅልፋሞች ያልሆኑ ልጆች አንደበታቸው እስኪደክም እንደሚያነቡና መምህራቸውም በመካከላቸው ሆኖ እንደሚሰማቸው በገብረ ክርስቶስ ቁስልም ትሎች ተፈጠሩበት ። ገብረ ክርስቶስም በእነሱ (በትሎች) ተሰቃየ። በማለት ባለቅኔው የገብረ ክርስቶስን ህማምና ስቃይ በቅኔያቸው ምስጢር አጉልተዋል ።

ታሪኩ በአንደኛው መፅሀፍ በገፅ 65 — 66 ተተርኳል ።

*69 አጭር ዞልክሙ (252) አ*

*መካናት አጽዋም እመ ኢይሬእያ ደመ*
*ተርፈ በከዊነ ዐፅም ባሕታዊ ዘደከመ ።*

## ትርጉም

መካኖች/ፆሞች ደምን ባያዩ
የደከመ ፅንስ/ባህታዊ አጥንት ሆኖ ቀረ ።

## ምስጢር

በእድሜ ገደብ ምክንያት መውለድ ያቋረጡ ሴቶች ፥ ወይም በዝሙትና በጤና ጉድለት ምክንያት መካኖች የሆኑ ሴቶች የወር አበባ እንደማያዩ የኢየሱስ ፆሞችም የእርድ ደምን አላስፈሰሱም ። አንዳንድ



www.ethiopianorthodox.org

ፅንስ በፀነሰችው ሴት ማህፀን ውስጥ አጥንት ሆኖ እንደሚቀር የባህታዊም አጥንት በፆምና በፀሎት ብዛት ገጠጠ በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

ታሪኩ በአንደኛው መፅሀፍ በገፅ 92 ተተርኳል ።

*70 ዕዝል ክብር ይእቲ (514) አ*

*ዕለተ ስቅለቱ ለወልድ ባሕታዊ ዘሱባዔሁ ፈጸመ*
*ውስተ ቤተ ጸሎት ወፅአ እንዘ ይከውን ጸሊመ ፤*
*አምጣነ በሰጊድ ወጾም እንበለ መጠን ደክመ ፤*
*ወእምነ ርትቅ መጽኡ ይሰአልዎ ከዋክብተ ሰማይ ሕልመ ።*

## ትርጉም

ሱባኤውን የጨረሰ የወልድ ስቅላት ቀን/ባህታዊ
ጥቁር ሆኖ ከፀሎት ቤት ወጣ ፤
በስግደትና በፆም ያለልክ ደክሟልና ፤
የሰማይ ከዋክብትም ህልምን ሊጠይቁት ከሩቅ መጡ ።

## ምስጢር

ባህታዊ በስግደትና በፆም ሱባኤውን ጨርሶ ከሱባኤው ሲወጣ ሰውነቱ ጠጧቁሮ ይታያል ። ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ቀንም ከመአልትነቱ ወደ ሌሊትነት ተለወጠ ። ባህታዊው ሱባኤ መግባቱን ያወቁ ሰዎችም ከሱባኤው ሲወጣ ያለሙትን ህልም እንደሚያስተረጉሙት ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ቀንም ሲለወጥ ከዋክብትም ረገፉ በማለት ባለቅኔው ያስረዳሉ (ማቴ·21 — 28) ።

*71 ዕዝል ዕጣነ ሞገር (560) አ*

*ዘወልደ ኢየሱስ (ሊቀ ጠበብት ፡ ዘመንበረ መንግስት)*
*በገራህተ አብርሃም ቃል አመ ተዘርዐ ፍጹመ*
*ሥጋ ማርያም በቈለ ወለምለመ ፤*
*መለኮት እንተ ያረዊ ዘገራህተ አብርሃም ትልመ*

*ኅዕሌሁ አምጣነ ዘንመ ፤*
*ወባሕርየ ሥጋ ጸገየ አሚሃ ጽጌ ተዋሕዶ አዳመ*
*ወትስብእተ ፍሬ አካላት ፈረየ ዳግመ ።*

## ትርጉም

የአብርሃም እርሻ/ቃል ፈፅሞ በተዘራ ጊዜ
የማርያም ስጋ በቀለና ለመለመ ፤
የአብርሃም እርሻ ትልምን የሚያረካ መለኮት
በላዩ ላይ ዘንቧልና ፤
የስጋ ባህርይም ያን ጊዜ መልካም አበባ/መዋሃድን አበበ
ሰው መሆን/የአካላት ፍሬንም ዳግመኛ አፈራ ።

## ምስጢር

ዝናብ ዘንቦ እርሻን ሲያረካ ዘር በእርሻው ይዘራል ፤ ዘሩም ይበቅልና ይለመልማል ። የእግዚአብሄር ቃልም በቅድስት ማርያም ማህፀን በአደረ ጊዜ (ከቅድስት ማርያም በተፀነሰ ጊዜ) ከማርያም የተገኘው ስጋ ክቡር ሆነ ፤ መለኮትንም ተዋሃደ ። የለመለመ ቡቃያ እንደሚያብብና ፍሬን እንደሚያፈራ የእግዚአብሄር ቃል ባህርይም የስጋን ውርደት ገንዘብ አደረገ ። ይህም የተፈፀመው የእግዚአብሄር ቃል ሰው ሆኖ ሰውን ለማዳን ስለወደደ ነው በማለት የተመሰጠረ የትስብእትና የመለኮት ተዋህዶ ምስጢር በቅኔው ተገልጧል ።

*72 ዕዝል ጉባኤ ቃና/ስ*
*ኢይሜህር ስምዖን ደቂቀ ቤቱ ዞሎሙ ።*
*ባዕል ስምኦን እስመ ለመደ ብርከሙ ።*

## ትርጉም

ስምኦን/ባለጠጋ መላውን የቤቱን ልጆች አያስተምርም ፤
ባለጠጋ/ስምኦን ጉልበታቸውን ለምዷልና ።

## ምስጢር

የልጆቹን ጉልበት የለመደ አባት ልጆቹን አያስተምርም ። ሰው በላ የሚባለው ስምኦን ልጆቹን እንኳ አልማራቸውም በላቸው ። "ኢይሜ



ህር" የተባለው ማሰሪያ ግስ ህብር ቃል ሆኖ በሰሙ በኩል በሃሌታ "ሀ" ሲፃፍ አለማስተማርን ሲገልጥ ፤ በወርቁ በኩል በሐመር "ሐ" ሲፃፍ ምህረት አለማድረግን(መብላትን) ይገልጣል ።
ታሪኩ በአንደኛው መፅሃፍ በገፅ 44 ተተርኳል ።

*73ዋዜማ(566)አ*
*ዘገብረ ሥላሴ(መምህር ፤ ዘኤልያስ)*
*አቅርንተ ብሂል ወብሂል*
*ወልደ ዮሴፍ ቃል ወብእሲተ ዮሴፍ እሙ*
*አሥረጹ አእዱገ ዜና መጻሕፍት ዞሎሙ*
*ኢብሂል እክለ አርድእተ ሰላም ቀሰሙ ፤*
*አኮኑ አውፅኡ እም ድንግል እሞሙ*
*ሠርዌ ሞት ለአይሁድ ብዕሎሙ ።*

## ትርጉም

ቃል የዮሴፍ ልጅ ነው
ማለትና እናቱ የዮሴፍ ሚስት ናት
የማለት ቀንዶችን የዜና አህዮች/መፅሃፎች አበቀሉ
አለማለት እህልን የሰላም ተማሮች ለቀሙ(አጣፈጡ)
የአይሁድ ብልፅግና የሆነ ጉድፍ/ሞትን
ከድንግል/አይናቸው አውጥተዋልና ።

## ምስጢር

አህዮች ቀንዶች አበቀሉ ማለት ፍፁም አሰት እንደሆነ በአንፃሩ ክርስቶስ የዮሴፍ ልጅ ነው ማለትንና እናቱ ቅድስት ማርያም የዮሴፍ ሚስት ናት ማለትን መፃህፍት አስረዱ ማለት ፍፁም ክህደት ነው ። እህልን አበጥሮ ፡ ለቅሞና አጣፍጦ እንደ መብላት የክርስቶስ ተማሮች ሃዋርያት ወንጌልን ሰበኩ ። ጉድፍን ከአይን አውጥቶ እንደመጣልም ሃዋርያት በአይሁድ መገደልን ከቅድስት ማርያም አራቁ በማለት ባለቅኔው አመስጥረዋል (ስንክ·ነሃሴ·16) ።

*74 ሥላሴ(120)ኀ*
*ሕሙም ገብረ መርዓዊ*

www.ethiopianorthodox.org

እዴሁ ይነፍሕ እንበለ ዕፅ ፤
ህየንተ ነዳዲ እሳት ደዌሁ አምጣነ ኮኖ ቀዲሙ
ወህየንተ ዕፅ እስመ ኮነ ዐፅሙ ።
ዓዲ ይሰብክ ምስሌሁ ዘያነቅሖ ሕማሙ ፤
ባሕቲቶ ኢይኩን ጊዜ ንዋሙ
እስመ በየማኑ ወበፀጋሙ
አኃዊሁ ዕፄያት ቆሙ ።

## ትርጉም

ገብረ መርአዊ/ህመምተኛ
እጁን ያለእንጨት እፍ እፍ ይላል ፤
ደዌው በቅድሚያ የሚነድ እሳት ፈንታ ሆኖታልና ።
አጥንቱም በእንጨት ፈንታ ሆኖታልና
ዳግመኛም የሚያነቃው ህመሙ ከርሱ ጋር ይተኛል ፤
በእንቅልፉ ጊዜ ብቻውን እንዳይሆን
ወንድሞቹ/ትሎች
በቀኙና በግራው ቆመዋልና ።

## ምስጢር

ሰው ለልማዱ እንጨቱን በእሳት አንድዶ እሳቱ እንዳይጠፋበት በአፉ እፍ እፍ ይለዋል ፡ ገብረ ክርስቶስ ግን ከዚህ ልማድ ውጭ ህመሙ እንደ እሳት አጥንቱ እንደ እንጨት ስለሆኑት ቁስሉን እፍ እፍ አለ ፡

በሽታውም እንደ እሳት አቃጠለው ። ከአባቱ ጋር የሚተኛ በእንቅልፍ ልቡ ሲወራጭ አባቱን እንደሚረግጠው ገብረ ክርስቶስንም የቁስል በሽታው ሲያንገበግበው እንቅልፍ አያስወስደውም ። ታናናሽ ወንድሞች ከታላላቅ ወንድሞቻቸው ጋር በቀኝና በግራ እንደሚቆሙ የገብረ ክርስቶስ ቀኙና ግራው አካሎቹ ተሉ በማለት ባለቅኔው የገብረ ክርስቶስን መከራና ስቃይ ፅናት ገልጠዋል ።
ታሪኩ በአንደኛው መፅሃፍ በገፅ 65 — 66 ተተርኳል ።
75 ሥላሴ(578)አ



www.ethiopianorthodox.org

አኅዘ ጥበ እሙ
ወጠበወ ሙሴ ሐሊበ ማይ
በትእዛዝከ አምላክ ሐፃኒ ከመ ኢይትከዐው ደሙ ፤
እስመ አጥባቲሃ አኅደገቶ እሙ ፤
ወኢይረክቦ ሕሰም ለሙሴ እንዘ ወልደ ማይ ስሙ ፤
ሰብአ ግብጽ በማይ አመ ተሰጥሙ
እስመ በየማኑ ወበፀጋሙ
አኅዊሁ ቀላያት ቆሙ ።

## ትርጉም

ሙሴ የእናቱን ጡት
ያዘና ወተት!ውሀን ጠባ ፤
አሳዳጊ አምላክ! በትእዛዝህ ደሙ እንዳይፈስ
እናቱ ጡቶቿን አስጥላዋለችና ።
ስሙ የውሃ ልጅ ሲሆን ሙሴንም አንዳች ነገር አያገኘውም ፤
የግብፅ ሰዎች በውሃ በሰጠሙ ጊዜ
በቀኙና በግራው
ወንድሞቹ/ወንዞች ቆመዋልና ።

## ምስጢር

ጨቅላ ልጅ የእናቱን ጡት ይዞ ወተቱን ይጠባል። ሙሴም የእናቱን ጡት ወተት እየጠባ በውሃ ዳር ተቀመጠ (ኖረ)። ለልማዱ ጨቅላ ልጅ ከእናቱ ከተነጠለ ጉዳት ያገኘው ነበር፣ ሙሴ ግን ከእናቱ መነጠሉ ለህይወቱ (ለደህንነቱ) ሆነለት። በወንዝ ዳር ተጥሎ ጉዳት ያላገኘውም ሙሴ ማለት የውሃ ልጅ ማለት በመሆኑ ወንዞች ወንድሞቹ እንደሆኑለት ወንድሞቹ በቀኙና በግራው የቆሙለት ሰው ኩራት እንደሚሰማው ሙሴም የኤርትራን ባህር ከፍሎ እስራኤልን ሲያሻግር፣ ውሃው በአባትነቱ ወንዞቹም በወንድምነታቸው በግራና በቀኝ እንደግድግዳ ሆኑለት በማለት ባለቅኔው በቅኔያቸው ምስጢር አስረድተዋል (ዘፀአ·2፡3 — 10)።

76 መወድስ ዞልክሙ(580)አ

ለብእሲ ፅሙዕ ኢ.የረውዮ
ቍሪረ ማየ እመ ይሰቲ በሕልሙ፣
ወኢይባልሖ እምጽምዕ ለሐሊበ ዕጎልት ጣዕሙ
ልምላሜ ጕርዔሁ ያየብስ ዳዕሙ
ከማሃ ተድላ ዓለሙ
ዘኢረከባ ይቴክዝ ወዘረከባ ይጻሙ።
እምዝኒ መንገለ ዝኒ ለለጌሠሙ ወዓሙ
ትትፋለስ ለለጊዜ ወለዐርካኒሃ ተኅድጎሙ፤
በእንተ ዝኒ ሐነጸ ሀገረ ነፍሱ በደሙ
ተክለ ሃይማኖት አንበሳ መስዕ ዘደብረ ሊባኖስ ክፍለ ገዳሙ፤
ወበቅድመ አምላክ ትቁም አስተሰነዐላ ለዐፅሙ
ተክለ ሃይማኖት አንበሳ መስዕ ዘደብረ ሊባኖስ ክፍለ ገዳሙ።

## ትርጉም

ቀዝቃዛ ውሃን በህልሙ ቢጠጣ
የተጠማ ሰውን አያረካውም፤
የጊደርም ወተት ጣም ከጥም አያድነውም
ልምላሜ ጉሮሮውን ያደርቃል እንጂ
እንዲሁም የአለምን ምቾት
ያላገኛት ይተክዛል፡ ያገኛትም ይደክማል።
ከዚህም ወደዚህ እየማግስቱና እያመቱ
በየጊዜው ትፋለሳለች፡ ወዳጆቿንም ትተዋቸዋለች፤
ስለዚህ ደብረ ሊባኖስ የገዳሙ ክፍል የሆነች
የመስእ አንበሳ/ተክለ ሃይማኖት ነፍሱ/መንደርን በደሙ አነፀ፤
አጥንቱንም በአምላክ ፊት ትቆም ዘንድ አሰናበታት።

## ምስጢር

ውሃ እንደጠማው የተኛ ሰው በህልሙ ውሃ ቢጠጣ ጉሮሮውን ከማድረቅ በቀር ሊያረካው አይችልም ። የዚህችን አለም ምቾትም ያገኛትም፡ ያላገኛትም በትካዜና በድካም አንድ ይሆናሉ ። ምክንያቱም ያገኛትም በቤተሰብ ሞትና በገንዘብ ወጪና ገቢ ጣጣ ሲብከነከን ያላገኛትም እርሷን ለማግኘት ይንከራተታል ። አለምም በተራ በተራ ሁሉንም የምታስተናግድ በመሆኗ ያገኛት እንዳላገኛት ፡ የዱር አንበሳም የከብቶችን አጥንት እንደሚሰብረው እግራቸውን በፀሎት ቁመት ብዛት የሰበረትና ወደአምላክ ያሳረጓት ተክለ ሃይማኖትም የከተማን ህንፃ በድንጋይ እንደመስራት ነፍሳቸውን በደማቸው አከበሩ በማለት ባለቅኔው የተክለ ሃይማኖትን ገዳማዊ ተጋድሎ በቅኔያቸው ምስጢር ያስረዳሉ ።

77 መወድስ (598) አ
ገዛኸኝ (ማራጌታ፡ ዘመርጡለ ማርያም)

ኦአንትሙ ደቂቀ አብርሃ
ሊቃላቲክሙ አነ ኢመጻእኩ እሥዐሮሙ ፡
ወንጌለ መንግሥት ዘይቤ ከመ እፈጽም ዳዕሙ
ወኅዳጠ ሕገ ተፋቅሮ ጸሐፍኩ ለክሙ
ከመ ትነስሑ ኵልክሙ
አምጣነ ይእቲ ፍቅር ነ.የ ማእከሌክሙ ።
ይቤሎሙሂ እግዚእነ ለሰብአ ዓለም ዘሐሙ
ሰዱሰ መዋዕለ ተገበሩ ግብረክሙ ፡
ወአመ ሳብዕት ዕለት ለኅሩያኒሁ ኵሎሙ
ዕለተ ሰንበት ምድረ ዋልድባ ዕረፍተ ትኩንክሙ ።

## ትርጉም

እናንተ የአብርሃ ልጆች ሆይ
እኔ ቃሎቻችሁን ልሽራቸው አልመጣሁም
የመንግስት ወንጌል ያለውን ልፈፅም ነው እንጂ ፡
ሁላችሁም ንስሃ እንድትገቡ
ጥቂት የመፈቃቀር ህግንም ፃፍሁላችሁ ፡
ያች ፍቅር በመካከላችሁ ናትና።
ጌታችንም የሚታመሙ የአለም ሰዎችን
ስድስት ቀን ስራችሁን ስሩ አላቸው፤


www.ethiopianorthodox.org

ለምርጦቹ ሁሉም በሰባተኛይቱ ቀን
የሰንበት ቀን/የዋልድባ ምድር እረፍት ትሁናችሁ አላቸው።

## ምስጢር

ክርስቶስ "ኦሪትንና ነቢያትን ልፈፅማቸው እንጂ ልሽራቸው አልመጣሁም" እንዳለ ባለቅኔው የጓደኞቻቸውን ምክርና ምልጃ አለማስተሃቀራቸውን አመልክተዋል ። ወደዋልድባ ገዳም መሄዳቸውም የጓደኞቻቸውን ምክር በመናቅ ሳይሆን የክርስቶስን ትእዛዝ ለመፈፀም መሆኑን እነርሱም (ጓደኞቻቸው) በመካከላቸው ባለው ፍቅር ወደ ክርስቶስ እንዲመለሱ መውደዳቸውን እግዚአብሄርም ስድስት ቀን መስራትንና በሰባተኛው ቀን ማረፍን እንዳዘዘ አለም በቃኝ ብሎ ወደ ዋልድባ ገዳም መግባትና በዚያው መሞት መንግስተ ሰማይ የመግባት ተስፋ ያለው መሆኑን ባለቅኔው በቅኔያቸው አመስጥረዋል ።

## ታሪክ

ባለቅኔው ግራጌታ ገዛኸኝ የመርጡለ ማርያም ካህን ናቸው። መንነው ወደ ዋልድባ ገዳም ለመሄድ ሲነሱ ማህበሩ (ካህናቱ) አትሂድብን ብለው ማልደዋቸው ለጊዜው እሽ ብለው ተመልሰውላቸዋል ። ይሁን እንጂ ቁርጥ አሳባቸውን ስላልለወጡ ሌሊቱን ተነስተው ሄደው ዋልድባ ገቡ ። ዋልድባም እንደገቡ ይህን ቅኔ ዕፈው ለማህበሩ ልከውላቸዋል እየተባለ ይተረካል ።

*78 መወድስ (581)አ*

*ኢትዮጲየ በባይ እምኢትዮጲየ*
*በጦማረ ወይሌ ወላህ ዘደመ ዕጉስታር ቀለሙ*
*መስቆቅዋተ ግብጽ ጸውዒ ከመ ይብክየ በስሙ*
*ለወልደ ጊዮርጊስ ፍትወ ሥን*
*ዐርዘ ሊባኖስ ዘይመስል ቆሙ ፡*
*ወወራዙትሂ ኢየርምሙ ፡*
*እስመ ዜና ሞቱ ተሰምዐ ቅድመ ይትአመር ሕማሙ ።*
*ኀድጊሰ ነባብየነ እለ ሀብተ ንባብ ቦሙ*
*አንብበ ሰቆቃው ዘኤርምያስ እስከነ አእባን ያዘንሙ*

*በወይሌ ወላህ ይትራድእዋ ለእሙ*
*ዖፍ በሰማይ ወአርዌ ውስተ ገዳሙ ።*

## ትርጉም

ከኢትዮጵያ የላቅሽ ኢትዮጵያ!
ቀለሙ የሬት ወለላ በሆነ በወዮታና በልቅሶ ደብዳቤ
አቋሙ ዝግባ ለመሰለ ፡ ውበቱ ላማረ ለወልደ ጊዮርጊስ
በስሙ እንዲያለቅሱ
የግብፅ ሙሾኞች/እስራኤልን ጥሪ ፡
ጎበዛዝትሽም ዝም አይበሉ ፡
ህመሙ ሳይታወቅ የሞቱ ወሬ ተሰምቷልና።
የነገር ስጦታ ያላቸውን ተናጋሪዎችንስ ተይና
የኤርምያስ ዋይታ (ሙሾ) እንባን ድንጋዮች እስኪያዘንቡ
ወፍ በሰማይ፣ አውሬም በጫካው ሆነው
እናቱን በዋይታና በሙሾ ይራዷት።

### ምስጢር

ደብዳቤ በቀለም እንደሚፃፍ ሁሉ ልቅሶው በእሬት ወለላ ተፃፈ ማለት መከራው እንደሬት መራራ ሆነ። በማናቸውም ፍጥረት መበላለጥ እንዳለ ባለቅኔው የእኛይቱን ኢትዮጵያን ከምድያም ኢትዮጵያ አልቀዋታል። ለደስታም ሆነ ለመከራ ቤተ ዘመዶች በደብዳቤ እንደሚጠሩና የግብፅ ምርኮኞች የሆኑት እስራኤላውያን እነራሄል ተንሰቅስቀው ለነፃነታቸው እንዳለቀሱ ሁሉ ኢትዮጵያም ረገደ መልካም ቁመተ ዝግባ ደመግቡ በነበሩት ጀግና በንጉስ ወልደ ጊዮርጊስ ሞት ለራሷ ታልቅስለት ይላሉ ባለቅኔው።
አንበሳ ልበሙሉ ሃይለኛ አውሬ እንደሆነ ሟቹ ንጉስ ልበ ሙሉ ጀግናና ደፋር ነበሩ። ስለዚህም የወላጅ እናታቸው ልቅሶ ኢያዜር ከምትባለው አልቃሽ ወፍ ልቅሶ ጋር ይመሳሰላል ። የየአብያተ ክርስቲያናቱ ደወሎችም እንደ ኤርምያስ ልቅሶ ድምፃቸውን ያስተጋቡ፤ ጎበዛዝቱም ሙያቸውን እያነሳሱ በህይወታቸው የነበራቸውን ወኔ በልቅሶው ይግለጡት በማለት ባለቅኔው ለንጉስ ወልደ


www.ethiopianorthodox.org

ጊዮርጊስ መልክ መልካምነትና ልበሙሉ ጀግንነት ያላቸውን አድናቆት በቅኔያቸው አመስጥረዋል።

## ታሪክ

እስራኤል ከከነአን ወደ ግብፅ በራብ ምክንያት ከወረዱ በሁዋላ ዮሴፍ በህይወት ባለበት ዘመን በደስታና በተድላ ኖሩ ። ዮሴፍ ከሞተ በሁዋላ በተከታታይ የነገሱት ፈርኦኖች በእስራኤል ላይ የእብሪት ስራ መስራት ጀመሩ ። የእስራኤል ህዝብ ቁጥር እየበዛ ስለሄደም ወንድ ሆኖ የተወለደ እስራኤላዊ ጨቅላ ሁሉ እንዲገደል ለግብፅ አዋላጆች ትእዛዝ ተላለፈ። እስራኤላዊ ደም ያላቸው ሁሉ በጡብ ስራ ላይ እንዲሰማሩ ተደረገ። ራሄል የምትባል እስራኤላዊት ነፍሰጡር ሴት በጡብ ረገጣ ስራ ላይ እንዳለች ምጥ ተሰማት። ይህንንም ለአሰሪዎች ብትናገር የሰው ደም ጡቡን ያጠነክረዋል እንጂ ምን ያደርገዋል ብለሽ ነው? አብረሽ ርገጪው አሏት። ወዲያውኑ መንታ አስወረዳትና ውርጃዎቹን ከጡቡ ጋር አብራ ረገጠቻቸው ። በዚያን ጊዜ "እስራኤልን የፈጠርካቸው አምላክ የለህምን'' ብላ ተንሰቅስቃ አለቀሰች። እንባዋንም በእፍኝዋ ተቀብላ ወደሰማይ ረጨችው። በዚህ ምክንያት ከግብፃውያን እጅ ከነወገኖቿ ወጥታ ነፃነትን አግኝታለች ተብሎ ይተረካል (ኤር·31፥15። ማቴ·2፥17 — 18)።

ነቢዩ ኤርምያስም ከእነወገኖቹ ተማርኮ ፋርስ ባቢሎን በወረደ ጊዜ ስለወገኖቹ ነፃነት ሰባ ዘመን አልቅሷል። በዚህ ምክንያት እስራኤል ነፃነትን አግኝተው ወደአገራቸው ገብተዋል ይባላል (ሰቆቃወ ኤር·6)።

*79· መወድስ ስ*

*ዘጥበቡ ካሣ(መሪጌታ፡ ዘቦገና ግራር ኢየሱስ)*

*ኦ አርድእት መስተጋድላን*
*ጥቡዐ ልብየ ወጥቡዐ ልብክሙ፡*
*ለሠናየ ፍሬ ማእረር ገድለ ዚአክሙ*
*እም ጉባኤ ቃና ደብረ ሴኬም*
*እስመ ቄሐ ምስጢረ ልቡና ቀንሞስ ለክሙ፡*
*ወእንዘ ጥበብ አክሊልክሙ*
*አምጣነ ባዝግና ዘወርቅ ምስጢረ መወድስ ሠርጎክሙ።*
*በወርኀሂ ወከዋክብት ዘተመሰልክሙ*
*ኪያየ ታበርሁ ወአበርህ ኪያክሙ፡*
*ወእንበለ ደዌ ፅኑዕ ብርሃነ ትንሣኤ ቀዲሙ*
*እግዚአብሔር መወድስ ያብጽሐኒ ያብጽሕክሙ ።*

## ትርጉም

ተጋዳዮች ተማሪዎች ሆይ
ልቤ ፅኑ ነው ፡ ልባችሁም ፅኑ ሆነ ፡
ፍሬው ለአማረ ለአዝመራ የእናንተ ገድል
ከሴኬም ተራራ/ጉባኤ ቃና
የልብ ምስጢር/ቀንሞስ ቀልቶላችሁዋልና፡
ጥበብም አክሊላችሁ ሲሆን
የመወድስ ምስጢር ሽልማታችሁ የወርቅ ዝርግፍ ነውና።
በጨረቃና በከዋክብት የተመሰላችሁ እናንተም
እኔን ታበራላችሁ፡ እኔም እናንተን አበራለሁ፡
ያለፅኑ በሽታም ለብርሃን ትንሳኤው አስቀድሞ
እግዚአብሄር መወድስ ያድርሰኝ፡ ያድርሳችሁ።

## ምስጢር

አንድ የጦር መሪ የሚመራቸውን ወታደሮች "ልባችሁ ይጠንክር፡ በእኛ መስዋእትነት የአገራችን አንድነቷ፡ ነፃነቷና ክብሯ ተጠብቆ ለትውልድ መተላለፍ አለባት "በማለት ያበረታታቸዋል። ባለቅኔውም እርሳቸው ለመምህርነት የበቁት ጠንክረው በመማራቸው መሆኑን አመልክተው ተማሪዎቻቸውም የእርሳቸውን ፈለግ እንዲከተሉ ይመክራሉ።
በመልካም የአዝመራ ወቅት ብዙ ፍሬን መሰብሰብ እንደሚቻል ተማሪዎ ችም ቅኔ ለመማር የሚያደርጉት ተጋድሎ የጠለቀ እውቀት ያስገኛል። ሴኬም በሚባለው ተራራ የተተከለው ቀንሞስ የሚባለው የሽቱ እንጨት እንደሚቀላም የተማሪዎች ልብ ጉባኤ ቃናን በመቁጠር ተጠበበ። በዝርግፍ ወርቅ የተንቆጠቆጠ ቀሚስና ካባ የለበሰ ሊቅ የወርቅ አክሊል


www.ethiopianorthodox.org

ሲቀዳጅ አምሮና ደምቆ እንደሚታይ የመሪጌታ ጥበቡ ካሳ አባሃጋር ተማሪዎችም ከእርሳቸው በመማራቸውና ቅኔ አዋቂዎች በመሆናቸው በሊቃውንቱና በህዝቡ ዘንድ ይከበራሉ።

ብርሃን ሰጭ የሆነ የፀሃይ ብርሃን ብርሃን ተቀብለው ብርሃን ከሚሰጡ ከጨረቃና ከከዋክብት ብርሃን እንደሚልቅ በጨረቃና በከዋከብት የተመሰሉት የባለቅኔው ተማሪዎች እውቀትም በፀሃይ ከተመሰሉት ከእርሳቸው እውቀት ያንሳል የፀሃይ ብርሃን በጨረቃና በከዋክብት ላይ ተንፀባርቆ ጨረቃና ከዋክብትም በበኩላቸው ብርሃን እንዲሰጡ ያደርጋል። ባለቅኔውም ተማሪዎቻቸውን ቅኔ አዋቂዎች በማድረጋቸው በተማሪዎቻቸው ብልህነት አገር እንዳወቃቸው ባለቅኔው ያስረዳሉ።

80 *ሕንጼሃ(603)አ*

*መዓልተ በደመና ለሐወርተ ግላ መርሐሙ*
*ኪዳነ መሐላ ሚካኤል ሊቆሙ።*

## ትርጉም

*ሊቃቸው የማላ ኪዳን/ሚካኤል*
*ቀን በደመና የጨለማ ሂያጆችን መራቸው።*

## ምስጢር

መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል እስራኤልን ቀን በደመና ፡ ሌሊት በእሳት ብርሃን ጋርዶ እንደመራቸው ወደ ጨለማ ቦታ የሚወርዱትን ነፍሳት ለቅድስት ማርያም የተሰጣት ቃል ኪዳን አዳናቸው ይላሉ ባለቅኔው (ስንክ.ህዳር ፡ 12 ፤ የካቲት 16)።

*81· ማእዝ ጉባኤ ቃና/ስ*
*ዘጌታሁን (አለቃ ፡ ዘሞጣ ጊዮርጊስ)*

*ሐና ትትፌሣሕ በዘተጸውዐ ስማ ፡*
*ድራረ ምሴት ትሕድስተ እስመ ረከበት በጻማ ።*

## ትርጉም

*ሃና ስሟ ስለተጠራ ትደሰታለች ፡*
*የማታ እንጀራ /እደሳን በድካም አግኝታለችና ።*



www.ethiopianorthodox.org

## ምስጢር

የማታ እንጀራ ያገኘች እናት ስሟ በተጠራ ቁጥር ትደሰታለች ። እንዲሁም የእናት ምሳሌ የሆነችው ሃና በስተርጅናዋ ማርያምን ወልዳ ታደሰች እየተባለ ሲተረክላት ስመጥር (ዝነኛ) ሆነች ። ታቦት ተቀርፆላት ቤተ መቅደስ ታንፆላት ትመሰገናለች በማለት ባለቅኔው ቅድስት ማርያምን በመውለዷ ምክንያት ለሃና የተሰጣትን ክብር በቅኔያቸው ገልጠዋል (ስንክ . ህዳር ፡ 11) ።

*82 ማእዝ ጉባኤ ቃና\ስ*
*ዘገላነሽ ሐዲስ (እማሆይ ፡ ዘጽላሎ አማኑኤል)*

*ትግህት ይእቲ አካለ ጊዮርጊስ ዘማ ፡*
*እስመ ኀበ ዕፅ ወፈረት ግብረ ማሕረጽ ፈጺማ።*

## ትርጉም

የጊዮርጊስ አካል/ ዘማ ትጉ ናት ፤
የወፍጮ ስራዋን ጨርሳ ወደእንጨት ለቀማ ተሰማርታለችና።

## ምስጢር

ትጉ የሆነች ሴት ሌሊት ስትፈጭ አድራ የወፍጮ ስራዋን ካጠናቀቀች በሁዋላ ሌሊቱ ሲነጋ እንጨት ለመልቀም ወደዱር ትሰማራለች ። የሰማእቱ የቅዱስ ጊዮርጊስ አካልም የክርስትና እምነትን በሚቃወሙ ሰዎች በወፍጮ እንደ እህል ከተፈጨ በሁዋላ በየእንጨቱ ላይ በነፋስ ሃይል ተበተነች ይላሉ ባለቅኔዋ (ስንክ. ሚያዝያ 23) ።

*8.3 መወድስ (618)አ*

*ዘዘገየ (ሊቀ ኅሩያን ፡ ዘደብረ መዊእ)*
*ምክዕቢተ ክብር ክፍሎሙ ለእለ ተቀንዩ*
*ውስተ ዐፀደ ወይን ጾም እንዘ ይጸንሑ ፍሬ ጻማ ፡*
*እስመ በየማና ጸሎት ወተፋቅሮ ዐጋማ*
*እሉ ኵሎሙ ይትጌበርዋ ፡*
*ይፍድዮሙ ዲናረተ ጽድቅ ሞገሰ ወግርማ*

*መጋቤ ጻድቃን በበስድሳ*
*ለእንጦንዮስ በቆብዕ ወለመቃርዮስ በአስኬማ ።*
*አድለውነሰ ዘበአድልዎ አዕይንተ ልብነ ጸልማ*
*ለዘቅብዐ ላሕም ያበርሆ ሲሳየ ፅለትነ ገጸ ዘማ*
*ኤልያስሰ ኢይቁም ውስተ ሐውዘ ዓለም ፍጽማ*
*ኀበ ደብረ ቀርሜሎስ ከመ ጐየ ጐየ ኀበ ራማ ።*

## ትርጉም

በወይን ቦታ/ፃም የድካም ፍሬን እየጠበቁ
ለተገዙ አገልጋዮች እድላቸው የክብር እጥፍ ድርብ ነው ፡
በቀኝዋ ፀሎት ፡ በግራዋም መፋቀር
እሊህ ሁሉ ያርሷታልና (ይኮተኩቷታልና) ።
የእውነተኞች መጋቢ ለእንጦንዮስ በቆብ
ለመቃርዮስም በአስኬማ ስልሳ ስልሳ
የፅድቅ ዲናሮች/ሞገስንና ግርማን ይከፍላቸው ዘንድ ።
የልባችን አይኖች በማድላት የጨለሙ እኛ ግን
የላም ቅቤ ለሚያበራው ለእለት ምግባችን የዘማ ፊት አደላን፡
በኤልያስ ግን በአለም አምሮት/ፊቷ እንዳይቆም
ቀርሜሎስ ወደሚባል ተራራ እንደሸሸ ወደሰማይ ሸሸ ።

## ምስጢር

የወይንን ቦታ እያረሱና እየኮተኮቱ ፍሬውንም እየጠበቁና እየሰበሰቡ የወይኑን ጌታ ያገለገሉ ሰራተኞች ደሞዛቸው በርካታ ይሆናል ። መንግስተ ሰማይንም ተስፋ በማድረግ በፆምና በፀሎት አምላክን ያስደሰቱ ቅዱሳን ዕድቃቸው ከፍተኛ ነው ። የወይኑን ቦታ የተንከባከቡት ሰራተኞች ደሞዛቸው ከፍተኛ እንደሆነ በፆምና በፀሎት ፡ በፍቅርም የተጠመዱ መናኞች ባለሚሎችና ተወዳጆች ናቸው ። አሰራው እንደየስራቸው መጠን ለሰራተኞች ደሞዝ እንደሚከፍላቸው አምላክም ለእንጦንስና ለመቃርስ በቆብና በአስኬማ ፍፁም ክብሩን አደላቸው ።

አይኖች በህመም እንደሚታወሩ የአለማውያንም ልቦች ደነቆሩ ። ስለዚህም መድሎኞች ሰዎች ለሰው ፊት እንደሚያደሉ የአለም ጉጉተኞች (ስግብግቦች) ከፆምና ከፀሎት ይልቅ በላም ቅቤ ለተቅለጠለጠ ምግብ አደሉ ።

አንዳንድ ሰው በተጣላት ሴት ፊት ለመቆም እንደማይፈልግ ነቢይ ኤልያስም በዚች አለም አምሮት አልተጠለፈም ። ችግር የገጠመው ሰው ወደዘመድ አገር እንደሚሸሽና እንደሚደበቅ ነቢይ ኤልያስም ከእስራኤል ንግስት ከኤልዛቤል ከተማ ወደ ቀርሜሎስ ተራራ ወጣ ፤ ከአለም አምሮትና ፍላጎትም ተለይቶ ወደ ሰማይ አረገ በማለት ባለቅኔው አመስጥረዋል ።

## ታሪክ

አስኬማ ከለስላሳ ነት እንደእንቢያጉስ ሆኖ የሚሰራ 12 ትእምርተ መስቀል ያለበት ነው ። ይህም ልብሰ ምንኩስና ከቀሚስ ከቅናትና ከቆብ በሁዋላ በመጨረሻ የሚለበስ የፍፃሜ ምንኩስና ምልክት ነው ። ከአስኬማ በሁዋላ ባህታዊ መሆን ፡ መዝጋትና አፅንኦ በአት እንጂ ከገዳም ወጥቶ አለማውያን ወደሚኖሩበት መግባት አይፈቀድም ። አስኬማን መልአኩ ለእንጦንዮስ እንደሰጠው ይተረካል ። በዚህም ምክንያት ምንኩስና ህገ መላእክት እንደሆነ ሲታመን ልብሱም አስኬማ መላእክት ይባላል ።

*84 ግእዝ ጉባኤ ቃና (624)አ*
*ኢያሱ ኃይልከ ዘተጋድሎ ሱላሜ*
*ቅጽረ ኑፋቄ ነሰተ ወልደ ኢየሉጣ ዘሮሜ ።*

## ትርጉም

የሮም ሰው የሆነች የኢየሉጣ ልጅ ቂርቆስ ! የመጋደል /ፍቅር ሰው የሆነ ሀይልህ ኢያሱ ቅጥር/ ጥርጥርን አፈረሰ ።

## ምስጢር

ኢያሱ የኢያሪኮን ቅጥር እንዳፈረሰ ሰማእቱ ቂርቆስ ያደረገው ተአምር ጥርጥርን አጠፋ ይላሉ ባለቅኔው (ስንክ. ጥር 15) ።

*85 ዕዝል ጉባኤ ቃና (625) አ*
*ተነሥሡ ሳዶቅ ወብእሲቱ ብዕለ ዘነደጉ ዕድሜ*


www.ethiopianorthodox.org

*አምጣነ በሕፃን በጽሖሙ ተጽናሰ ዕፀው ልምላሜ ።*

## ትርጉም

ሳዶቅና ሚስቱ እድሜን የተው ሰዎች ብልፅግናን ተፈላለጉ የእንጨቶች ችግር/ ልምላሜ በህፃን ደርሶባቸዋልና ።

## ምስጢር

በልጅ ምክንያት ችግር የደረሰባቸው ሰዎች ገንዘብ ይፈላልጋሉ ። እንዲሁም ህፃንን (ቅድስት ማርያምን) በመውሰድ እንደእንጨቶች መለምለምን ያገኙ ኢያቄምና ሃና የነኤልያስን ኑሮ አገኙ ይላሉ ባለቅኔው (ስንክ.ህዳር 11) ።

*86 ሚበዝኑ (127) ጎ*
*ሥጋ ዳግማዊ አዳም*
*ዘምድረ ለብሰ አሕጸረ ሰዓተ እድሜ*
*ወአስተርአየ ገሃደ በቅድመ ማርያም ወሰሎሜ ፤*
*ጥንተ ነገሩ ሕማመ ኅዲገነ ንብዳሕ ኀበ ትንሣኤሁ ፍጻሜ*

## ትርጉም

ምድርን የለበሰ
የሁለተኛ አዳም ስጋ የቀጠሮ ሰአትን አሳጠረ ፡
በማርያምና በሰሎሜ ፊትም በግልፅ ታየ ፤
ግን የነገሩ ጥንት ህማምን ትተን ወደመነሳቱ መጨረሻ እንድረስ ።

## ምስጢር

አንድ ሰው ስለአንድ የሚያጓጓ ድርጊት (በዝርዝር) ከስር ጀምሮ ሲያወራ አድማጮቹ ይቸኩሉና እስኪ መጨረሻውን ንገረን ይሉታል ። ከዚህም አንፃር ባለቅኔው የክርስቶስ በመቃብር ውስጥ ብዙ ጊዜ አለመቆየቱንና ወዲያው መነሳቱን በቅኔያቸው ምስጢር አስረድተዋል ።

*87 አጭር ዋዜማ (630) አ*
*ዘገብረ ሥላሴ (መምህር ፡ ዘኤልያስ)*
*ሀቀበ ጸዊረ ወሀበ ዘኤልያስ ዕድሜ*
*ሀርገት ዮሴፍ ዘይተልዋ ሰሎሜ ።*

## ትርጉም

የኤልያስ እድሜን ሰጪን መሸከም/ አቀበትን ዮሴፍ የተከተላት ሰሎሜ ወጣች ።

## ምስጢር

ብቻዋን መሄድ የፈራች መንገደኛ ጓደኛን አስከትላ አቀበትን እንደምትወጣ ቅድስት ማርያምን ያጨ ዮሴፍ የተጐዳኛት ሰሎሜም ለኤልያስ እድሜን የሰጠ አምላክን መሸከምን አዘወተረች በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

*88 ግእዝ ጉባኤ ቃና (132)ጎ*
*ሰመይናከ ታቦር መምህረ ዳዊት ሥዩም ፤*
*ድኅረ አንበባ ዳዊት እስመ ተርጎምካ ለዮም ።*

## ትርጉም

ታቦር ! የሹም ዳዊት መምህር አልንህ ፤
ዳዊት ከአነበባት በሁዋላ ፡ ዮምን ተርጉመሃታልና ።

## ምስጢር

አስተማሪው ተማሪው ያነበበለትን ይተረጉማል። እንዲሁም ዳዊት “ወአነ ዮም ወለድኩከ ፤ እኔ ዛሬ ወለድሁህ” ብሎ ስለስግው ቃል (ሰው ስለሆነው ስለእግዚአብሄር ወልድ) የተነባውን እግዚአብሄር አብ በደብረ ታቦር “ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ፤ ይህ ልጄ ነው” አለ በማለት ባለቅኔው የትንቢትንና በደብረ ታቦር ተፈፀመ የሚባለውን ተአምር ድንቅነት በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል ።


www.ethiopianorthodox.org

*89 ዕዝል ጉባኤ ቃና/ስ*
*ዕፄ ምድር ሔዋን ትረድኦ ለገብረ መርዓዊ አዳም ፡*
*እስመ እምገቦሁ ሐዳስ ፈጠራ ጥበበ አምላክ ሕማም ።*

## ትርጉም

የምድር ትል ሄዋን ገብረ ክርስቶስ አዳምን ትረዳዋለች ፡
የአምላክ ጥበብ / ህማም ከጎኑ ፈጥሯታልና ።

## ምስጢር

ሄዋን አዳምን ለመርዳት ከአዳም ጎን በአምላክ ኪነ ጥበብ እንደተፈጠረች ትል የገብረክርስቶስን ክብር ለማብዛት ከአካሉ ተፍለክለ ከች በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ( ዘፍጥ·2፡ 20-25) ።

*90· ዘአምላኪየ ስ*
*እፎ ወረደ በላዕለ ቶማስ ገዳም*
*አድግ ዘኢየገምሮ ተመትሮ ዝናም*
*እስከ ሥረዊሁ ተመልሐ በማዕበለ ሰይፍ ደም !*

## ትርጉም

አህያ የማይችለው መቆረጥ/ዝናብ
በሰይፍ ጎርፍ/ደም ስሮቹ እስኪነቃነቁ ድረስ
በቶማስ /ዱር ላይ እንዴት (ምንኛ) ዘነበ!

## ምስጢር

የዝናቡ ጎርፍ የእፀዋትን ስራስሮች እስኪነቃቅል ድረስ ጎርፉ ሲጐርፍ "አህያ የማይችለው ዝናብ ዘነበ" ይባላል ። ከዚህ አንፃር ባለቅኔው መርአስ የሚባል አገር ሰማእት ቶማስ ከነአህዮቹ መቆረጡን ፡ ጅማቶቹም መበጣጠሳቸውንና ደሙም መፍሰሱን በቅኔያቸው ምስጢር አስረድተዋል ።

ታሪኩ በአንደኛው መፅሀፍ በገጽ 52 ተተርኳል ።

*91 ዋዜማ (1.36) ጎ*
*ለመስተጋድላን በሕጎሙ*
*አምጣነ ተጋደሉ ገድለ መርዓተ ዘንበሪ ዓለም*



www.ethiopianorthodox.org

*ኢወደሰቶሙ ለያፌት ወሴም ፤*
*እስመ ለጊዮርጊስሰ ሲሩየ ዙለንታ በደም*
*ገዳሙ ወምድሩ ለስም*
*ትዌድሶ መርዓት ወትብሎ ወልድ እጐየ ቃልከ አዳም ።*

## ትርጉም

በተዋጊዎች ህግ
ውጊያን የተዋጉትን ያህል የዘንበሪ ሙሽራ/አለም
ያፌትንና ሴምን አላወደሰቻቸውም ።
ሁለንተናውን በደም የተበከለ ጊዮርጊስን ግን
ገዳሙና የስም ምድር ሙሽራ
"ወንድሜ ወልድ! ቃልህ መልካም ነው" ብላ ታወድሰዋለች ።

## ምስጢር

ተዋጊዎች አንድ ጊዜ ድል ሲያደርጉ አንድ ጊዜም ድል ሲሆኑ ይኖራሉ እንጅ ዘለአለማዊ ድል አያገኙም ። በመሆኑም "ወንድ ልጅ አንድ ቀን እንደ አባቱ አንድ ቀንም እንደ እናቱ የተሰኘውን ምሳሌያዊ አነጋገር እየጠቀሱ ድል ሲያደርጉ ሲደሰቱ ድል ሲሆኑም ሲያዝኑ ይኖራሉ ። ከዚህም የተነሳ የሚመሰገኑት ምስጋና ፍፁም አይሆንም ። ሰባት አመት የተጋደለ ሰማእቱ ጊዮርጊስ ግን የተሰቃየበትና ደሙን ያፈሰሰበት ምድር የሰማእትነቱ ምስክር ሆነችው ፡ ቅዱስ ሰማእት አሰኝታም ቃሉን በቤተ ክርስቲያን አፀደቀችለት ይላሉ ባለቅኔው (ስን·ሚያዝያ 27) ።

*92 ዋዜማ (35)ይ*
*ማየ አይኅ ተጋድሎ*
*አመ እንበለ አቅም ዘንመ ውስተ ደብረ መዊዕ ዓለም*
*ጠፍዐ ዘርኡ ለሰማዕት አዳም ፤*
*ወእንዘ በአፍአ የአርር ተቅራመ ሥጋ ወዐፅም*
*ኢተመይጠ ቋፅ ኀበ ኖኅ ገዳም*
*እስከ ነትገ ማየ አይኅ ደም ።*

## ትርጉም

የጥፋት ውሃ/መጋደል
በደብረ መዊእ/አለም ያለልክ በዘነበ ጊዜ
የሰማእት/አዳም ዘሩ ጠፋ ፤
በውጭም የስጋና የአጥንት ቃርሚያን እየለቀመ
የጥፋት ውሃ/ደም እስከጐደለ ድረስ
ቁራ ወደኖህ/ዱር አልተመለሰም ።

## ምስጢር

የጥፋት ውሃ በአለም በዘነበ ጊዜ የሰው ዘር እንደጠፋ ተጋድሎ በጎጃም ክ/ሀገር በባህር ዳር አውራጃ በምትገኘው በደብረ መዊእ በፀና ጊዜ የሰማእታት ወገን አለቀ ። ኖህ የላከው ቁራ ውዳቂውን ስጋ እየነጨ ወደኖህ እንዳልተመለሰ በደብረ መዊእም ሰማእታተ ኢትዮጵያን ደርቡሽ በሰይፍና በነፍጥ በፈጇቸው ጊዜ ስጋቸውን አሞራው በላው ። ደርቡሽም የሰማእታተ ደብረ መዊእን ስጋቸውን ከመቀርደድና አጥንታቸውን ከመከስከስ አልተቆጠበም ። ቁራው ያልተመለሰው የጥፋት ውሃ እስኪጎድል ድረስ እንደሆነ የደም ማፍሰስ ጊዜ እስኪያልፍ ደርቡሽ አልታገሰም በማለት ባለቅኔው በደብረ መዊእ ያለቁትን ሰማእታተ ኢትዮጵያ ገድል ፅናትና የደርቡሽንም ጭካኔ በቅኔያቸው ምስጢር አስረድተዋል ።

*93. ሥላሴ (142)ኀ*
*ዘክንፉ (አለቃ ፡ ዘራጉኤል)*

*እመ አቤል ቀዳማዊ*
*መቃብር ትበኪ ወትኀዝን ፤*
*አምጣነ ላቲ ኢኮኑ ውሉዳ ሕዋሳቲሃ ለእም ፤*
*ወተርፉ ትኩዛኒሆሙ ዕፄያት አዕዋም ።*
*ባሕቱ ትትፌሣሕ ደመና ወላዲተ ንጹሕ ዝናም ፤*
*አኮኑ ረከበት እንበለ ዓቅም*
*ሀብተ መላእክት ድንግለ ክፍለ ኖኀ ወሴም*
*እምኔሃ ለሃቲ ዓለም ።*

## ትርጉም

የቀድሞ ሰው አቤል እናት/
መቃብር ታለቅሳለች ታዝናለችም ፤
የእናት ማርያም ሰውነቶች/ልጆቿ ለርሷ አልሆኑምና ፤
ትሎች/ወገኖችም ያዘኑ ሆነው ቀሩ ።
የንፁህ ዝናም ወላጅ/ደመና ግን ትደሰታለች ፤
የመላእክት ስጦታ/ድንግልን እንደኖህና እንደሴም
ከዚያም አለም ያለልክ አግኝታለችና ።

## ምስጢር

ልጆቿ ስለሞቱባት ወልዳ እንዳልወለደች የሆነች እናት በሃዘን እንደምትንገበገብ የልጆች ምሳሌ የሆኑ የቅድስት ማርያም ሰውነቶች ያልፈረሱላት መቃብር ባዶዋን ቀረች ። በልጆች ሞትም የእናታቸው ወገኖች እንደሚያዝኑ እንዲሁም በቅድስት ማርያም ሰውነቶች ትሎች አልተፈጠሩም ።

ልጅ ያደገላት እናት እንደምትደሰት ዝናብን የምታዘንብ ደመና የምትባል ማርያም ወደላይ መጠቀች ። እናት ከልጅ ጋር ሃብትን ስታገኝ ደስታዋ ከመጠን ያልፋል ። ዝናብን የምትሸከም ደመና ማርያምን ለመሸከም አቅም ሳይኖራት መላእክት ባሳረጓት ጊዜ ተሸከመቻት ። የኖህ የቃል ኪዳኑ ምልክትና የሴም ክፍል የምትባል ማርያምም እጣ ሆነች (በደመና ተጋርዳ አረገች) በማለት ባለቅኔው አመስጥረዋል ስንክ·ነሃሴ 16) ።

*94 ሥላሴ (144)ኀ*
*በፈቃዱ (አቶ)*

*ይቤሉ ማዕበላት*
*ንሁ ንረድ ኀበ ፈርዖን*
*ወንክዐው ማየ ነገረ ሰብአ ግብጽ ዓለም*
*ይትሐጸባ ሠረገላቲሁ አዋልድ በደም ።*
*ወድኅረ እማኅተም ወፅአ በኀይሉ ፈረሰ ፈርዖን ጸሊም*
*ተመይጠ ይግባእ ኀበ ማኅተም ፤*
*አምጣነ በኀሳል ነፋስ ወማዕበል ልኅም*
*ይመይጦ እደ ሞት ግሩም ።*

## ትርጉም

ማእበሎች የፈርኦን
ሰረገላዎች /ቆነጃጅት በደም


www.ethiopianorthodox.org

ይታጠቡ ዘንድ "ኑ ወደፈርኦን እንውረድና
የግብፅ አለም ሰዎች ነገር/ውሃን እንበትን አሉ ፤
ጥቁር የፈርኦን ፈረስም ከዝግ በሃይሉ ከወጣ በሁዋላ
ወደዝግ ይገባ ዘንድ ተመለሰ፤
በልባብ / ነፋስና በማእበል ልጓም
የሚያስገርም የሞት እጅ ይመልሰዋልና ።

## ምስጢር

ስላሴ "ኑ እንውረድና የከለዳውያንን ቋንቋ እንለውጥባቸው" እንዳሉ የኤርትራ ባህር ማእበሎች በፈርኦን ራስ ላይ ፈሰሱበት ። ደግሞ ቤቶች በእስራኤል ንጉስ በአክአብ ሚስት በኤልዛቤል ደም እንደታጠቡ የፈርኦን ሰረገላዎችም በግብፃውያን ደም ተበከሉ ። ፈረስም ከተዘጋ ቤት ወጥቶ በውጭ ቆይቶ ተመልሶ በተዘጋ ቤት እንደሚያድር የፈርኦንም ፈረስ ከቤቱ ወጥቶ በኤርትራ ባህር ሰጥሞ ቀረ ። የፈረሰኛ እጅ ፈረሱን በልባብና በልጓም እንደሚገታው ሁሉ የፈርኦንን ፈረስ በነፋስና በማእበል ሞት አገኘው ይላሉ ባለቅኔው ።

ታሪኩ በአንደኛው መፅሀፍ በገፅ 38፡88 እና 190 ተተርኳል ።

*95 ሥላሴ(141)ኀ*
*ዘበሻህ(አለቃ፡ ዘሩጉኤል)*

*ኀድግዎ ወመንንዎ*
*ለአጼ ምኒልክ ዓለመ ሥጋ*
*ደዌ ወሞት ውሉደ ቀዳማይ አዳም!*
*ወኢትበልዎ ለመሬት ጌሠም ፤*
*አምጣነ ምኒልክ ንጉሥ በዊዐ ገነት ዳግም*
*በደሮ ለሄኖክ ዘይቀድም*
*አመ ወሰዶ መንፈስ መንገለ ገዳም ፤*
*ወአንበሮ በሐዲስ ዓለም ።*

## ትርጉም

ደዌና ሞት/የመጀመሪያ
አዳም ልጆች! የስጋ
አለም/አፄ ምኒልክን ተውት ናቁትም
ለመሬት/ነገም አትበሉት ፤
መንፈስ(ፈቃድ) ወደገዳም በወሰደው ጊዜ
ንጉስ ምኒልክ ዳግመኛ ገነትን መግባትን
የቀደመውን ሄኖክን ቀድሞታልና ፤
በአዲስ አለምም አስቀምጦታልና ።

## ምስጢር

መፅሃፍ ፃድቃን ሰዎችን "ይህን የስጋ አለምን ተውት ናቁት ፤ ምግብንም ለነገ አትበሉ" እንደሚላቸው ከአዳም የተገኙ ህማምና ሞት አፄ ምኒልክን አያግኟቸው ፤ ለመቃብርም አያድርጓቸው ። ወደመቃብር በመድረስ ሃዋርያው ዮሃንስም ጴጥሮስን እንደቀደመው አፄ ምኒልክም ወደገነት በመግባት ሄኖክን ቀደሙት ፤ ገነት የምትባለውንም ከተማ መሰረቱ ። ኢየሱስ መንፈሱ ወደገዳም እንደወሰደው ምኒልክም በጎ ፈቃዳቸው አዲስ አለምን አሰራቸው ይላሉ ባለቅኔው ።

*96· ሥላሴ/ስ*
*ዘነቅዐ ጥበብ(አለቃ)*

*መቃብር ድኅረ አሰረ*
*ዘጸሐፈ ሞት ልሳነ ሰብእ*
*ኢይተረጉማ እምድኅር ወኢያነብባ እምቅድም ፤*
*ጥቀ እስመ ተገድፈቶ ማርያም ቀለም ፤*
*ወድኅረ ቀረፀ ደርገ ብርዐ ቤተ ኤልያስ ዮም*
*በሰሌዳ አልዓዛር መተርጉም*
*ማርያምሃ ጸሐፉ ደመናት አዕዋም*
*ያንብብዋ በኵሉ ዓለም ።*

## ትርጉም

ሞት የፃፋትን ልሳነሰብ
መቃብር ከአሰረ በሁዋላ
ከሁዋላ አይተረጉማትም ከፊትም አያነባትም ፤
ማርያም /ቀለም በጣም ተገድፋዋለችና ፤
የኤልያስ ቤት ብእርንም ዛሬ በአንድነት ከቀረፀ በሁዋላ
በተርጓሚ /አልአዛር ሰሌዳ
ማርያም/ ቀለምን ፃፉ ።


www.ethiopianorthodox.org

## ምስጢር

ልሳነ ሰብእ የምትባለውን ክታብ አፅፎ ማይምን በአንገቱ ከአሰራት በሁዋላ አያነባትም ፤ አይተረጉማትም ። አንዳንዱ ሰው ፊደል ቢማርም ቀለም (የፊደል ንባብ) እንደሚገደፈው ሞት የገደለውን የሰውን አንደበት መቃብር ይበላዋል ። ቀለም እንደምትገደፍም ቅድስት ማርያምን መቃብር ውጦ አላስቀራትም ። ፀሃፊዎችም ብእርን ቀርፀው በሰሌዳ (በብራና) ቀለምን እንደሚፅፉበት ደመናዎች በአልአዛር መነሳት ቅድስት ማርያምን ወደሰማይ አወጧት ። የተፃፈችውም ቀለም በሁሉ ቦታ እንደምትነበብ እንዲሁም ቅድስት ማርያም በአለሙ ሁሉ ተሰበከች ይላሉ ባለቅኔው ።

*97 መወድስ(አ)*

*አፉሁ ለሰብእ ቀታሌ ርእሱ*
*እስመ በዘአርመመ አፍ ኢይበውዕ ዕፄ ገዳም ፤*
*ዝኒ ሐሰት ከመ ኢንበል ዮም*
*መካህ ወልደ ጌራ*
*ለእመ ሴረየ በጽርፈት ደም*
*ለዳዊት ልብሰ ሕማም*
*ላዕለ ሰሎሞን በቈለ አሜከላ ዳዊት ቂም ።*
*ተቀትለሂ ግብረ ሳኦል በፍትሐ ዳዊት ሥዩም*
*ገዘምኩ እመ ይቤ እንዘ ኪያሁ ኢይግዝም ፤*
*አመኒ አፉሁ ነበበ ሃይማኖተ ኬፋ በሮም*
*ለፋሲለደስ ረሲዓን ሰሐብዎ በልጓም ።*

## ትርጉም

የሰው አፉ ራሱን ገዳይ ነው ፤
ዝም ባለ አፍ የዱር ዝንብ አይገባምና፣
ይህንም አሁን ሃሰት ነው እንዳንል
ተመኪ የጌራ ልጅ
የህማም ልብስ/ዳዊትን
በስድብ/ቀለም ቢነክረው
የዳዊት ቂም/ደንደሮ የሚባል እሾህ በሰሎሞን ላይ በቀለ።
የሳኦል አገልጋይም እርሱን (ሳኦልን) ሳይቆርጥ
ቆርጥሁ ቢል በሹም ዳዊት ፍርድ ተገደለ ፤
የጴጥሮስ ሃይማኖትንም በሮም በተናገረ ጊዜ
ዝንጉዎች ፋሲለደስን በልጓም ሳቡት ።

## ምስጢር

"በአፍ ይጠፉ በለፈለፉ ፤ ዝም ባለ አፍ ዝንብ አይገባበትም" የሚባለው ምሳሌ አፍ አስገዳይ መሆኑን ያስረዳል ። ጥለኛ ሰው የጠላቱን ልብስ በደም እንደሚበክለው የልብስ ምሳሌ የሆነ ዳዊትን የጥለኛ ሰው ምሳሌ የሆነ ሳሚ ወልደ ጌራ የደም ምሳሌ በሆነ ስድብ ቢያስቀይመው በምድር ላይ እሾህ እንደሚበቅል የዳዊት ቂም በሰሎሞን ተወርሶ ሰሎሞን ሳሚን ተበቀለው ይላሉ ባለቅኔው ። የሳኦል አሽከር የነበረው አማሌቃዊ ሰው ሳኦልን በሰይፍ ሳይገድለው ፤ ገደልሁት ብሎ ለዳዊት ስለነገረው ፤ በዳዊት ፍርድ በገዛ አፉ መጥፋቱን በመግለጥ ሰማእቱ ፋሲለደስም ስለክርስቶስ ቢመሰክር አፉን በልጓም መለጎሙን ቅኔው ያስረዳል (2ሳሙ.1 ፥ 1–16)

*98 መወድስ (701) አ*

*ዘአካለ ወልድ (መምህር)*

*በኢትዮጵያ ሰማዕነ ጽዕለተ ሞዓብ*
*ኀበ ኮነት ሞዓብ ዕጕልተ ሠላስ አክራም ፤*
*እንዘ ዓዲሁ ማዕረር ኀልቀተ ዓለም*
*አኮኑ ተረክቡ እንበለ ጊዜ*
*ክርዳድ ጸላኢ ወዘሦከ ተቅራም*
*በኢትዮትጲየ ገራህተ ደም ።*
*ወእፎ አርመመ ኖላዌ አባግዕ ወላህም*
*አባግዒሁ እንዘ ይዘሩ ማዕከለ ተኲላት ዘሮም*
*ወእንዘ አኮ ኖላዌ ክልኤ ዕጓላተ ወርቅ ኢዮርብዓም*
*ባሕቱ ኖላዊ ይመስል እንተ ኢይሬኢ ዮም*
*አባግዒሁ እንዘ ይርዒ ወእንዘ ንቁሐ ይነውም ።*

## ትርጉም

ሞአብ የሶስት አመት ልጅ ከሆነች ዘንድ



www.ethiopianorthodox.org

የሞአብ ስድብን በኢትዮጵያ ሰማን፤
የአለም እልቂት /አዝመራ ገና ሲሆን
እንክርዳድ/ ጠላትና
የእሾህ ቃርሚያ በደም እርሻ/
ኢትዮጵያ ያለጊዜው ተገኝተዋልና።
ኢዮርብአምም የሁለት የወርቅ ጥጆች ጠባቂ ሳይሆን
በጎቹን በሮም ተኩላዎች መካከል ሲበትን
የበጎችና የላም ጠባቂ እንዴት ዝም አለ፤
ነገር ግን ጠባቂ (ክርስቶስ) በጎቹን ሲጠብቅ
የተኛም ንቁም ሲሆን ዛሬ የማያይ ይመስላል።

## ምስጢር

በሞአብ ላይ የተፈፀመው ጦርነት በኢትዮጵያ ላይ ስለደረሰ ኢትዮጵያ እንደሞአብ ሆነች። ምክንያቱም አለም የሚያልፍበት ጊዜው ሳይደርስ የተፈፀመባት የጠላት የባህል ወረራ እንዳለች አያስቀራትም።

የከብቶች እረኛ ከብቶቹ ከሰው አዝመራ ውስጥ ሲገቡበት ዝም ብሎ መመልከት እንደማይገባው የምእመናን መምህር ክርስቶስም ሮማውያን መምህራን ኢትዮጵያን በእምነት ባህላቸው ሲበክሏት ያላየና ያልሰማ መስሎ በትእግስት መመልከቱ በመጨረሻ ጊዜ የሚሰጠውን አምላካዊ ፍትህ የሚጠቁም መሆኑን በቅኔያቸው አስረድተዋል (መ·ሳ·3፡12 30)።

*99 መወድስ (157) ኀ*

*ሰላም አልብነ ምስለ ሰብአ ሮሜ*
*ወለሰብአ ሮሜ ምስሌነ ኢሀለዎሙ ሰላም፤*
*ኢየሱስ ክርስቶስ ዘመደ ሥጋ ወዐፅም።*
*እስመ ከተረነ ደምከ ቀለም*
*ኦ ዘትሠይም*
*ቀስተ ሕይወታ ለነፍስ በደመና ገቦ ንዝኀተ ደም።*
*አንተሰ ታስተዴሉ በውስተ ዛቲ ዓለም*
*ኪያሆሙ ለጥዒና ወኪያነ ለሕማም፤*
*ወእኅዘ እም ጥንተነ ጴጥሮስ በተዓድዎ ሕግ ፍጹም*
*ለዘተፃብዐከ ንፃብዖ ወለዘተቃወመከ ንትቃወም።*



## ትርጉም

የአጥንትና የስጋ ዘመድ ኢየሱስ ክርስቶስ!
ከሮም ሰዎች ጋር ሰላም የለንም
ለሮም ሰዎችም ሰላም የላቸውም፤
ደምህ/ቀለም ከትሮናልና (ለይቶናልና)፤
የነፍስ የህይወቷ
ቀስትን በጎን/ደመና የደም ርጭት የምትሾም
አንተ! ግን በዚች አለም
እነርሱን ለጤንነት እኛን ግን ለህማም ታዘጋጃለህ፤
ከጥንታችን/ጴጥሮስ ጀምረንም ፍፁም ህግን በመተላለፍ
የተጣላህን እንጣላዋለን፤ የተቃወመህንም እንቃወማለን።

## ምስጢር

አንዱ የአንዱን ወንድም በመግደሉ ምክንያት በደም የተለያዩ ሰዎች በማንኛውም ነገር አይገናኙም። ኢየሱስ ክርስቶስም ሰው ሆኖ በአፈሰሰው ደም እምነት የሮም ካህናትና የኢትዮጵያ ካህናት አይተባበሩም። ከዚህም የተነሳ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ካህናት አብረው ቀድሰው በአንድነት አይቆርቡም። ደግሞ አምላክ አለምን በጥፋት ውሃ ዳግመኛ እንደማያጠፋት ቀስትን በደመና ላይ (የቃል ኪዳንን ምልክት እንዳደረገ) የሰዎችን የነፍስ መዳንም በደሙ ፈሳሽነት አደረገ ይላሉ ባለቅኔው (ዘፍጥ·9፡8 17)።

"በክርስቶስ ሁለት ባህርይ፤ ሁለት ፈቃድ" በማለት የሃይማኖትን መንገድ የለወጡ የሮም ካህናትን ተቃዋሚዎች ሲሆኑ ኢትዮጵያውያን ለስጋዊ መከራ ተዳረጉ። "በክርስቶስ ሁለት ባህርይ ሁለት ፈቃድ" የሚሉ ሮማውያን ግን የስጋዊ ደስታ ባለቤት ሆኑ በማለት ቅኔው ተመስጥሯል።

ግዛትን ለማስፋት ሮማውያን (ጣሊያኖች) በኢትዮጵያ ላይ በተደጋጋሚ ያካሄዱት ወረራ መቅድም" የእንግሊዝ ቄስ በቀኝ እጁ መፅሃፍ ቅዱስ በግራ እጁ መትረየስ" እንዲሉ የሮም ካህናት ሃይማኖት እንስብካለን በማለት ያደረጉት የስለላ ተግባር መሆኑን የተረዱት ኢትዮጵያዊ " ሰላም አልብነ ምስለ ሰብአ ሮሜ፤ ከሮም ሰዎች ጋር ሰላም የለንም"



www.ethiopianorthodox.org

ብለዋል።

*100 መወድስ (158) ጎ*

*ዘወልደ አብ(አለቃ)*

*ትእምርተ ባሕርዩ ኅቡእ በሰውሮ ግብሩ*
*አርአየነ ለነ ሆሣዕና ዳዊት ዓለም፤*
*እስመ ገጸ ሙታን ከደነ በልብሰ ሕያዋን ንዋም፥*
*አመኒ ሰረቀ ሕዝበ ዮሴፍ*
*ወቅብዐ መንግሥቱ ለዳዊት ሥዩም*
*በእደ ሙሴ ወሳሙኤል*
*በአንጽሖ ፍርሃት ከዐወ ንጹሐ ደመ ላሕም።*
*ወቀበረ በኢያእምሮ መቃብረ ሥጋ ወዓፅም*
*መቃብረ አልዓዛር እንተ ሞተ በሕማመ አቤል*
*ወአዳም፤*
*ወርስሐተ ፅንስ ያንጽሕ በማየ ዘለፋ ዝናም*
*ተፋቅሮ ልብሰ አንስት ሠወራ ለማርያም።*

## ትርጉም

የዳዊት/አለም መድሃኒት የተደበቀ የባህርዩ
ምልክትን በስራው በመሰወር ለእኛ አሳየን፥
የሙቶችን ፊት በደህነኞቸ ልብስ /በእንቅልፍ ሸፍኗ
ልና፥
የዮሴፍ ሕዝብንና የሹም ዳዊት
የመንግስት ቅባትን በሰረቀም ጊዜ
በሙሴና በሳሙኤል እጅ
ፍርሃትን ለማንፃት ንፁህ የላም ደምን አፈሰሰ።
በአቤልና በአዳም ህማም የሞተ የአልአዛር መቃብር
ንም
ባለማወቅ በአጥንትና በስጋ መቃብር ቀበረ፥
የፅንስ እድፍንም በዘለፋ/ዝናም ውሃ ያነፃ ዘንድ
መታጨት/የሴቶች ልብስ ማርያምን ሸሸጋት።



www.ethiopianorthodox.org

## ምስጢር

ላለመታወቅ የፈለገ ሰው ራሱን በልብስ ተከናንቦ ፊቱንም ሸፍኖ ይቀመጣል። ሆሳእናም የተባለ ክርስቶስ የባህርዩን አለመመርመር በሚሰራው ስራ ርቀት አስረዳ። ፊትን በልብስ እንደመሸፈን ክርስቶስም የአልአዛርን ሞት በእንቅልፍ መስሎ ተናገረ (ዮሃ· 11፡11–14) ።

የሰውን ገንዘብ የሚሰርቅ ሰው ጨለማ ለብሶ እንደ ሚሄድ አምላክም የዮሴፍን ወገኖች እስራኤልን ከግብፅ ባርነት በሙሴ መሪነት ለማውጣት ፈቀደ፤"በምድረ በዳ መስዋእትን ሰውተውልኝ ይመለሳሉ" በማለትም ፈርኦን ንና አማካሪዎቹን ሸነገለ።

በጊደር መስዋእት ምክንያትም በነቢይ ሳሙኤል አማካይነት የመንግስትን ስልጣን ከሳኦል ወገን አወጣና ለዳዊት ሰጠ። የሞተ ሰውን በመቃብር እንደ መቅበርም "አልአዛርን ወዴት ነው የቀበራችሁት?" ማለቱን ባለማ ወቅ ሸፈነው። ሴትም በቀሚስዋ እጅጌ ፊቷን እንደምትሸ ፈን የሴቶች መታጨት ቅድስት ማርያምን አላለፋትም። ልብስም በውሃ ታጥቦ ከእድፉ እንደሚነፃ በዘለፋ ውሃ መጠጥ ፅንሱን አስፈተነ በማለት ባለቅኔው ያስረዳሉ (ዘዐኦ·7–10 ። 1ሳሙ·13–16 ። ማቴ·1፡24)።

*101 መወድስ(155)ጎ*

*ኢይበውእ ማይ ውሳጤ አፉሁ*
*ለዘ ኢይበውእ ሰብእ ውሳጤ አፉሁ ቀለም*
*ኀበ አእመረ ጥበበ ኢያእምሮ ጥበብ ፍጹም፥*
*ወይሰቲ ወይነ ለለዕለቱ*
*እንበለ መሥፈርት ወኀዳጥ ዓቅም*
*እስከነ ያተርፍ ለጌሠም*
*ወያሰጥሞ ቀላይ ዘአቤሜሌክ ንዋም።*

ሊተሰ ለዘአልብየ ንዋየ ኃላፊ ዓለም
በስትየ ቁሪር ማየ ፈለግ ኢይትዔረየኒ ሰሊሆም፤
ወእም አፉየ ርኁቅ ወይነ ቤተ ባዕል ጥዑም
ከመ ላህበ ነድ እም አስሐትያ ወከመ ዕዕዳዌ እምነ
ደም።

## ትርጉም

ፍፁም ጥበብን አለማወቅ
ጥበብን ካወቀ ዘንድ ቀለም በአፉ ውስጥ
በማይገባ ሰው አፍ ውስጥ ውሃ አይገባም፤
ያለመስፈሪያና ያለጥቂት
ልክም ለነገ እስኪያተርፍ
ድረስ ወይንን በየቀኑ ይጠጣል፤
የአቢሜሌክ እንቅልፍ/ ወንዝም ያስጥመዋል።
የወንዝ ቀዝቃዛ ውሃን በመጠጣት መስኖ አይስተካከለ
ኝም፤
የእሳት ሙቀት ከውርጭ፡ ንጣትም ከደም እንደራቀ
የባለፀጋ ቤት ጣፋጭ ወይንም ከአፌ የራቀ ነው።

## ምስጢር

ባልተማረ ሰው አፍ ቀለም (ትምህርት፣ እውቀት) አይነገ
ርም። ደግሞ አንዳንድ ዝምተኛ ሰው እንደበቱን ለንግግር
ከከፈተ ቶሎ ዝም እንደማይል ያልተማረው ሰውም እውቀትም
ባይኖረው ሀብት ስላለው ውሃ አይጠጣም፤ ሁል ጊዜ የወይን
ጠጅ ይጠጣል። በደራሽ ውሃ ጢም ብሎ የሞላ ወንዝም ደፍሮ
የሚገባበትን ሰው እንደሚያሰጥም ከባድ እንቅልፍም ሃብታ
ሙን ሰው ይጫጫነዋል። ለታወቀው ባለሙያ ተወዳዳሪ እንደማ
ይገኝለት ድሃው ባለቅኔ ከውሃ በስተቀር የወይን ጠጅ ሰለማያ
ገኙ በውሃ መጠጥ ከመስኖ በለጠ። በውርጭ ጊዜም ሙቀት፤
ንጣትም በደም ቀለም እንደሌለ በባለቅኔውም አፍ የወይን ጠጅ
አልገባም በማለት በቅኔው ምስጢር ተገልጧል።



www.ethiopianorthodox.org

102 መወድስ(704)አ
ዘዶሪ ( አለቃ፣ ዘጨለቆት ሥላሴ)

በእመተ መልአክ መጠነ ቆመ ድንግልና
መጠነ መልአክ ታእምር እደ የማነ አብ ማርያም
ዘኢገሠሣ ልማድ እደ ሜልኮል ፀጋም፤
ወከመ ኢትቅርፀ ዘበቁለ
ሥዕርተ ኑኅ ለወላድ ጽሕም
በመቅረፀ ሜልኮል እመ ሕልም
በመሥፈርተ ወላድ ሠፈረት ወሊዶተ ቃል ጽንፈ ዓለም።
ነገራኒ በስምዐ ክልኤ/ከመ ይቁም
ሰማይ ድንግልና ወምድር ከዊነ እም
በእደ አሐቲ ድንግል ለእመ ተሰሕበ ዮም
እርመመ ዳንኤል ወርዕደ ዕንባቆም።

## ትርጉም

የሜልኮል ግራ እጅ/ልማድ
ያልዳሰሳት ማርያም የመልአክን ልክ ታውቅ ዘንድ
የአብ ቀኝ እጅ ቁመት/ድንግልናን በመልአክ ክንድ ለካ፤
የበቀለ የወላድ/ጢም
ርዝመት ጠጉርንም በህልም እናት
በሜልኮል መቀስ እንዳትቆርጥ
በወላድ መስፈሪያ ቃልን መውለድ/የአለም ዳርቻን ሰፈ
ረች።
ነገሯም በሁለት ምስክርነት ይቆም ዘንድ
ሰማይ/ ድንግልነትና ምድር/ እናትን መሆን
በአንዲት ድንግል እጁ፡ ዛሬ ቢሳቡ
ዳንኤል ዝም አለ፤ እንባቆምም ተንቀጠቀጠ።

## ምስጢር

አንዲት ቤት የምትሰራ ሴት የምታሰራውን ቤት ስፋት
ለማወቅ መሬቱን የሜትር መጠን ባለው ገመድ ታስለካለች።

ቅድስት ማርያምም የመላእክትን ንፅህና ይዛ ስለተገኘች የአብ የባህርይ ልጅ እግዚአብሄር ወልድ ንፅህት መሆኗን ወደደው ።

እምነቷን ጠባቂ ሴት ከባሏ በቀር የሌላ ወንድ እጅ ቢነካት እንደማትወድ የሚልኮል ልማድ (የወንድ ዘርን መቀበል ያላስቀረው (ምክንትን) ማርያምን አላገኛትም።

የጢም ፀጉር በመቀስ እንደሚቀረጥ ድንግል ማርያም የወላድን መውለድ በሚልኮል ምክንት አላጠፋችም። በአንድ ግለሰብ የሚያዝ የከተማ ቦታ ከዳር እስከዳር እንደሚሰፈር ድንግል ማርያም የአብ ቃልን መውለድን በወላድ ደንብ ቻለች። አንድ አከራካሪ የሆነ ነገር በሁለት ሰዎች ምስክርነት እንደሚ

ፀና የድንግል ማርያም የድንግልነትና የመውለድ ፀጋ ልዩ ሆነ። ሰማይና ምድርም በአድማስ አንድ ናቸው ( ይገናኛሉ) እንደሚባለው፣ ድንግልነትና እናትነት በአንዲቱ ድንግል ቢገኙ፣ ስለክርስቶስ ትንቢት የተነበዩ ዳንኤልና እንባቆም አደነቁ በማለት ባለቅኔው ለማርያም ብቻ የተሰጠውን የድንግልነትና የእናትነት ፀጋ በቅኔያቸው ምሰጢር አስረድተዋል።

*103 መወድስ (739) አ*

*ዘምንደስይል (ደብተራ)*

*ሕንፃ ደብረ ብርሃን ማኅሌት ዘኢትዮጵያ*
*በስቡሕ ተወጥነ ወሐልቀ በሰላም፤*
*ወድኅረ ሕንጻ ዝ ዘመን አምላከ አዳም*
*ለጴጥሮስ ጠፈረ ቅድምና ይቤሎ በአቅም*
*ሑር እምድኅሬየ፥*
*እስመ ኮንከ አንተ ማዕቀፍየ ዘቅድም።*
*ለትዕማርሂ ጠፈረ ሕንጻ ዘተሜረየት በደም*
*በፍኖት ተበአሳ ዐይነ ብእሲ አቤሴሎም፤*
*እስመ በምኒልክ ቅድመ ወበኢያሱ ዳግም*
*እግዚአብሔር ደብረ ብርሃን ዐቢይ ዘለዓለም።*

## ትርጉም

የደብረ ብርሃን ህንፃ የኢትዮጵያ ማህሌት
በስቡህ ተጀመረና በሰላም ተፈፀመ ፤
ከዚህም ዘመን ህንፃ በሁዋላ የአዳም አምላክ
የቀድሞ ህንፃ/ጴጥሮስን በልክ
ከሁዋላዬ ሂድ አለው ፤
አንተ የቀድሞ መሰናክሌ ሆነሃልና ።
በደም የጠለቀች የህንፃ ጠፈር/ትእማርንም
የሰው አይን/አቤሴሎም በመንገድ ተጣላት ፤
ቀድሞ በምኒልክ ዳግመኛም በኢያሱ
እግዚአብሄር ደብረ ብርሃን ዘላለም ታላቅ ነውና ።

## ምስጢር

የኢትዮጵያ ማህሌት በቤተ ክርስቲያን ባህል ሲዘመር "ስቡሕ ወውዱስ" ፥ (ምስጉን) በሚል መዝሙር ይጀመርና "ሰላም" በሚባል ስለአገርና ስለአለም ሰላም በሚዘመር መዝሙር ይፈፀማል ። ሰላምን የሚነካው ድርሰትም ሰላም ይባላል ። "ስቡሕ ወውዱስ" ማለት የተመሰገነ ፥ የተለየ ማለት እንደሆነ የደብረ ብርሃን ስላሴ ቤተ ክርስቲያን ህንፃም ሲታነፅ መሰረቱ የተመሰገነ መሰረት ሆኖ ድምድማቱም ያለሁከት መፈፀምን አገኘ ። ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ነገረ መስቀሉን ሲናገር "ይህ አይሁንብህ" ያለው ጴጥሮስን "ከሁዋላዬ ወግድ" እንዳለው አዲሱ የደብረ ብርሃን ህንፃ የቀድሞውን ህንፃ አስናቀው ። ወንድሟ አምኖን ክብረ ድንግልናዋን ያሳጣትን ትእማርን ሌላው ወንድሟ አቤሴሎም በአድናቆት እንዳያት የህንፃውን ጠፈር (ጣራ) የተመልካቹ ሰው አይን አተኮረበት ። እግዚአብሄር አምላክ ከአለም በፊትም ከአለም በሁዋላም ዘለአለማዊና ገናና ነው እንደሚባል ፥ በአፄ ምኒልክ የተቆረቆረና በልጅ ኢያሱ የታደሰ የደብረ ብርሃን ስላሴ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ከተማ ይሆናል ይላሉ ባለቅኔው ።

## ታሪክ

ዳግማዊ አፄ ምኒልክ በዘመናቸው ያሰሩት የደብረ ብርሃን ስላሴ ቤተ ክርስቲያን በልጅ ኢያሱ ጊዜ ታድሷል ። ቤተ ክርስቲያኑ ከታደሰ በሁዋላ ከቀድሞው የበለጠ ውብ ሆኖ በመታየቱ ባለቅኔው ይህን ቅኔ አበርክተዋል ።

ታሪኩ በአንደኛው መፅሃፍ በገፅ 69 ተተርኳል ።


www.ethiopianorthodox.org

104 ዕዝል አሠረ ንጉሥ (791) አ

አሕሰምከ ሞት ሰራቂ አንተ አልብከ ንዋም
ዘኅለፈሰ ኅለፈ አምኃ ኢየሱስ ግሩም
እንከሰ ኢትሰርቅ ወኢትድግም
ቴዎድሮስሃ መሥዋዕተ ዘቤተ ልሔም
እስመ ቦቱ ይድኅን ዓለም ።

## ትርጉም

እንቅልፍ የሌለህ ሞት/ሌባ ! አክፋህ ፤
ያለፈውስ አለፈሪ አምሃ ኢየሱስ አለፈና !
የቤተ ልሄም መስዋእት/ቴዎድሮስን
እንግዲህ ወዲህ አትስረቅ አትድገምም ፤
አለም ይድንበታልና ።

## ምስጢር

አንድ ሌባ የዘመዶቹን ንብረት ሰርቆ ሲያዝ ደግ አልሰራህም ፤ ያለፈው አለፈ እንግዲህ ወዲህ አይድገምህ" ይባላል ። ባለቅኔው "ሞት ! አምሃኢየሱስን ገደልህ ይኸው ይብቃህ ፤ ወደ ቴዎድሮስም አትመለስ ፤ አገር ይረጋጋበታልና" ይላሉ ።

## ታሪክ

ከሸዋ መሳፍንት አንዱ አምሃ ኢየሱስ የተባሉት ናቸው ። አስፋወሰን የተባሉት ልጃቸው ቴዎድሮስም እየተባሉ ይጠሩ ነበር ። የሸዋው መስፍን አምሃ ኢየሱስ በሞቱ ጊዜ ባለቅኔው የአምሃኢየሱስን ልጅ ቴዎድሮስን በህይወት መኖር የሃዘን ማፅናኛ አድርገው ምኞታቸውን በቅኔያቸው ገልጠዋል ።

105 ዕዝል ዕጣነ ሞገር (908)አ

ይሥርዎ ግብተ አፈ ጳውሎስ ረገሞ
ዘጉንዱይ ዘመን ኢአደሞ
ለነሀቢ ብሩር እስክንድሮስ ፈድፋደ ዘተቃወሞ
በምሳሌ ነገር አስተሐሚሞ ።



www.ethiopianorthodox.org

ልብነ ድንግልኒ መከረ በወልዱ ከመ ይኩንን ዓለሞ
ወለአበ ደም ዘያገብእ ደሞ ።

## አሰረ ንጉሥ

ቤተ ክርስቲያን ይብለኪ ይእዜ መልአከ ረድኤት ቀዊሞ
ተሠርገዊ ጽድቀ ወተከደኒ ሰላሞ ፤
አንቲኒ ዐባይ መቅደሰ ዳሞ
ርእሰ አድባራት ኩኒ ጸዊረኪ ዐፅሞ
እስከ ዙሉ ይነቅህ ነዊሞ ።

## ትርጉም

የዘገየ ዘመን ያላማረው በነገር
ምሳሌ ተግቶ እጅግ
የተቃወመው ብር አንጣሪ/እስክንድሮስን በድንገት ያጠፋው
ዘንድ የጳውሎስ አፍ ረገመው ።
ልብነ ድንግልም በልጁ አለሙን ይገዛ ዘንድ መከረ ፤
ለባላጋራም ደሙን የሚመልስ ሆነ ።

## አሰረ ንጉስ

ቤተ ክርስቲያን ! የርዳታ መልአክ ቆሞ ዛሬ
"እውነትን ተሸለሚ ፤ ሰላሙንም ልበሺ" ይልሻል ፤
አንቺ ታላቅ የሆንሽ የዳሞ መቅደስም !
ሁሉ ተኝቶ እስኪነቃ ድረስ አፅሙን ተሸክመሽ
የአድባራት አለቃ ሁኚ ።

## ምስጢር

ቅዱስ ጳውሎስን በስብከተ ወንጌል የተቃወመው እስክንድሮስ በጳውሎስ አፍ ተረግሞ እንደጠፋ ሁሉ የአፄ ልብነ ድንግል ጠላት ግራኝ መሀመድ በአፄ ገላውዴዎስ ጠፋና የልብነ ድንግል ደም ተመለሰ ። ከዚህም የተነሳ ቤተ ክርስቲያን እውነትን አገኘች ተረጋጋች ፤ የአፄ ልብነ ድንግል አፅም ያረፈባት ደብረ ዳሞም የሞተው ሁሉ እስኪነሳ ድረስ ከአድባራት ልቃ ትኖራለች ይላሉ ባለቅኔው ።

## ታሪክ

እስክንድሮስ (ደሜጥሮስ) የሚባል አንጥረኛ የኤፌሶን ከተማ

አንጥረኞችን እየሰበሰበ የሀዋርያው የቅዱስ ጳውሎስን ትምህርት የሚቃወም ስራ ይሰራ ነበር ። ቅዱስ ጳውሎስም ለስራው መሰናክል በፈጠረበት በአንጥረኞች አስተባባሪ በእስክንድሮስ አዘነበት ። ከዚህም የተነሳ ከራስጌው የተሰቀለው መዶሻው ከተሰቀለበት ወድቆ ጭንቅላቱን ስለፈጠፈጠው እስክንድሮስ ሞተ ይባላል (የሀዋ. 19፥23–27)።

*106 ሚበዝኁ (812)አ*

*ዘአድማሱ ጀንበሬ (መልአከ ብርሃን)*

*ሕፁየ መንግሥት ቶማስ*
*ውስተ ቤተ ጸሎት ምትረት በአሌልዮ ገይሠ*
*እለ ተኀጉሉ አእዱገ እንዘ ይተግህ ኀሠሠ ፤*
*አኮኑ አእመረ እንዘ አእዱጊሁ የኀሥሥ ከመ ወልደ ቂስ ነግሠ ።*

## ትርጉም

ለመንግስት የታጨ ቶማስ
ወደፀሎት ቤት/መቆረጥ መገስገስን በመማለድ
የጠፉ አህዮችን ተግቶ ፈለገ ፤
የቂስ ልጅ ሳኦል አህዮቹን ሲፈልግ እንደነገሰ አውቋልና ።

## ምስጢር

ሳኦል የጠፉ አህዮችን ሲፈልግ ወደ ነቢይ ሳሙኤል ቢሄድ በነቢዩ እጅ ቅብአ መንግስት ተቀብቶ የእስራኤል የመጀመሪያው ንጉስ ሆኖ ነግሷል ። የመርአስ ኤጲስ ቆጶስ ቶማስም የተቆረጠውን መቆረጥ አህዮቹም ተቆረጡ ። የተቆረጡትን አህዮቹንም አዳናቸው ፤ እርሱም ለእግዚአብሄር መንግስት (ለመንግስተ ሰማይ) ተመረጠ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል (ስንክ. ህዳር 9) ።

ታሪኩ በአንደኛው መፅሀፍ በገፅ 133 ተተርኳል ።

*107 ዋዜማ (1209)አ*

*ለትድምርት ወተሌልዮ*
*እለ ብክሙ ሥርዓት ፈደላቲነ ሠወሰ*
*ዘበልየ ሕንፃ ቤትክሙ ለባዊ ሐደሰ ፤*
*እስመ እመ በግፍዕ አሐዱ ቤተ ካልኡ ወረሰ*
*ወእምነ ቤት ቤት እመ ተፋለሰ*
*ምሥጢራት ያነሥኡ ባዕሰ ።*

## ትርጉም

ለአንድነትና ለመለየት
ስርአት ያላችሁ ፊደሎቻችን ሠናስ !
ያረጀ የቤታችሁን ህንፃ ልበኛ አደሰ ፤
አንዱ በግፍ የሌላውን ቤት ቢወርስ
ከቤትም ቤት ቢፋለስ
ምስጢሮች ጠብን ያነሳሉና ።

## ምስጢር

በህብረት የሚሰሩ ማህበርተኞች ያረጀውን ቤት እንደሚያድሱ በዘፈቀደ ይፃፉ የነበሩት ንጉሱ "ሠእና እሳቱ" ሰ "በየስርአታቸውና በየመግቢያቸው መፃፍ አለባቸው ። ምክንያቱም በህገወጥ አፈፃፀም አንዱ ሰው ከሌላ ሰው ቤት ገብቶ አልወጣም ቢል ባለቤቶቹ እንደሚጣሉት ፡ እነዚህም ፊደሎች (ሠናሰ) አለቦታቸው ቢገቡ ታሪክ ይፋለሳል ፤ ምስጢርም ይበላሻል ይላሉ ባለቅኔው ።

*108 ሥላሴ (181)ነ*

*ዘድንቆ ማርቆስ*

*በፍናው አርባዕቱ*
*ይቤ መልአክ ዐቃቤ ርእሱ*
*ላዕለ መንኖ እክል ወማይ ክልኤቱ እስመ ገብረ ሕይወት ሐደሰ*
*መንኖ ዐራዝ መንክረ ሣልሰ ፡*
*ወራብዑ ዕፁብ ነገር ለቀራንብቲሁ ድቃሰ*
*ከመ እለ ኪሩቤል ኢኀሠሠ ፤*
*እመ ለብሰ ሥጋ ወእመ ኢለብሰ*
*ክዋኔሁ ኢየአምር አንሰ ።*


www.ethiopianorthodox.org

## ትርጉም

በሁለቱ እህልንና
ውሃን በመናቅ ላይ አስደናቂ
ሶስተኛ ልብስን መናቅን ገብረ ህይወት አድሷልና ፤
ያስደናቂ ነገር አራተኛ እንቅልፍንም ለቅንድቦቹ
እንደኪሩቤል አልፈለገምና ፤ በአራቱ መንገዶች (ነገሮች) ስጋን
ለብሶ እንደሆነ ፥
አለበሰም እንደሆነ ሁኔታውን እኔ አላውቅም
አለ ራሱን ጠባቂ መልአክ ።

## ምስጢር

አንድ ባለፀጋ ሰው በየጊዜው የተለዋወጠ ጠባይ ለአሽከሮቹ ሲያሳይ ጋሻጃግሬው ለጓደኞቹ "እኔ የጌታዬን ጠባይ ምን እንደሆነ ለማወቅ አልቻልሁም ፤ በየቀኑ ይለዋወጣል" ይላል ። እንዲሁም አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ (አቦ) ሰው ሲሆኑ ከሰው ጠባይ የተለየ ጠባይ ያላቸው መሰሉ ። የሰው ህይወቱ እህልና ውሃ ፥ ልብስና እንቅልፍ ሲሆኑ ፃድቁ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ከእነዚህ ከአራቱ አስፈላጊዎች ነገሮች ነፃ ሆነው ኖሩ ። ስለዚህ ፃድቁ ገብረ መንፈስ ቅዱስ መንፈሱ (ረቂቅ መልአክ) ይሆኑ ፥ ሰው ይሆኑ አልታወቀም ። ሰው ቢሆኑ ኖሮ ከአራቱ አስፈላጊ ነገሮች ነፃ ሊሆኑ ባልቻሉም ነበር ። በሰው አምሳል የሚታዩ ውስጠ መልአክ ቢሆኑ ነው እንጂ በማለት ባለቅኔው ቅኔያቸውን አመስጥረዋል ።

## ታሪክ

እኚህ ፃድቅ በገድላቸው ላይ ገብረ ህይወትም ፥ ገብረ መንፈስ ቅዱስም ይባላሉ ። ባልተማሩ ምእመናን ዘንድ ግን አቦ በመባል ይታወቃሉ ።

*109 ሥላሴ (182)ኑ*

*ተቀብረ መቃብር*
*ወሞት ሞተ በቅድመ ዕዝራ ፤*



*ድኅረ እሙታን ተንሥአ ባሕቱ ሞተ አልዓዛር ዘንእሰ*
*አስተርእየ ለሰማዕተ ልዳ ጊዜያተ ሥልሰ ።*
*ወሶበ ለዝ ሰማዕት ነጋሢ ዐቃቤ ሥራይ ኀሠሠ*
*እም ሕይወት ደዌሁ ኢተፈወሰ ፤*
*ወብሔረ ሕይወት ኤልያስ ዐፅሙ ፈለሰ*
*ተፅዒኖ ዘእሳት አፍራስ።*

## ትርጉም

መቃብር ተቀበረ ፥
ሞትም በእዝራ ፊት ሞተ ፤
ከሞቱ ሰዎች ተለይቶ ከተነሳ በሁዋላ ግን ያነሰ የአልአዛር ሞት
የልዳ ሰማእት ለሆነ ለጊዮርጊስ ሶስት ጊዜ ታየ ።
ንጉስም ለዚህ ሰማእት ጊዮርጊስ ባለመድሃኒትን በፈለገ ጊዜ
ከህይወት/ደዌው አልተፈወሰም ፤
ለአፅሙ ኤልያስም የህይወት ፈረሶችን ተቀምጦ
ወደህይወት/አገር ፈለሰ (ተሰደደ)።

## ምስጢር

የሞተ ሰው በመቃብር እንደሚቀበር መቃብር ሙታንን ይዞ ማስቀረቱ ቀረ ፥ በፅኑ የታመመ ህመምተኛም እንደሚሞት ሞት ገድሉ አልቀረም ። ግን ክርስቶስ ከሙታን ተነስቶ ለደቀመዝሙሮቹ ሶስት ጊዜ እንደታየ ሞት ሶስት ጊዜ እየሞተ ተነሳ በሚባል በጊዮርጊስ ሶስት ጊዜ ተሸነፈ ። ለታመመ ሰው ቤተሰቡ ባለመድሃኒትን እንደሚፈልግለት በወንጀለኛ ንጉስ የተሰቃየ ሰማእቱ ጊዮርጊስም ከህይወት አልተለየም ። ኤልያስም በእሳት ሰረገላ እንዳረገ የጊዮርጊስ አፅም በህይወት እንደነበረ ሆነ በማለት ቅኔው ተመስጥሯል (2ነገስ. 2፡1–12) ስንክ. ሚያዝያ 23) ።

*110 መወድስ (80)ይ*

*ሆማፅና ዳዊት ተቀብዐ ለአብርሆ ገጽ*
*ቅብዐ ተጸፍዖ በእድ ወፀሐየ ቀትር ኢኀሠሠ ፤*
*እስመ አንጸረ ፅፅ ቆመ እንዘ የኀድግ አልባሰ ፥*
*እመኒ ሠዐረ ሕገ መዋቲ*



www.ethiopianorthodox.org

*ብዕል ዘከይሲ እንዘ ባዕድ ወረሰ*
*ወብዕለ ዘብእሲ ፣*
*መጽሐፈ ዕዳሁ ቀኖተ በኪደተ እግሩ እስመ ደምሰሰ ።*
*ሥርዓትሂ ዘአናንያ ወዘአኀዊሁ ፈለሰ ፤*
*በጥንተ ቅዳሴ ዘኢነበረ እብነ ቢታንያ እስመ ቀደሰ ፣*
*ባሕቱ ረከበ በኀበ እግዚኡ ሞገሰ*
*ተረፈ ንባብ ምግበ ዕለቱ እስመ ለጌሠም ኢያግኀሠ ።*

## ትርጉም

የዳዊት ሆሳእና ፊትን ለማብራት
መፀፋት/ቅቤን በእጅ ተቀባ የቀትር ፀሃይንም አልፈለገም ፤
ልብስን ትቶ በእንጨት አንፃር ቆሟልና ፣
የሟችንም ህግ በሻረ ጊዜ
ባእድ ሲሆን የእባብን ብልፅግና (ሃብት)
የሰውንም ብልፅግና ወረሰ ፤
የእዳው መፅሃፍ/ችንካርን በእግሩ እርግጫ ደምስሷልና ።
የአናንያና የወንድሞቹም ስርአት ፈለሰ (ተወገደ) ፤
በቅዳሴ መጀመሪያ ያልነበረ ዲያቆን/የቢታንያ ድንጋይ ቀድሷልና ።

ነገርግን በጌታው ዘንድ ሞገስን (ባለሟልነትን) አገኘ ፤
የእለት ምግብ/የነገር ትራፊን ለነገ አላስቀረምና ።

## ምስጢር

ቅቤ ሲበሉትም ሲቀቡትም ፊትን ያበራል (ወዛም ያደርጋል)። ስለዚህም ሰው ፊቱን ለማብራት ቅቤ ይቀባል። በአንፃሩም ሆሳእና የሚባል ክርስቶስ በአይሁዳዊ እጅ ፊቱን ተፀፋ ( በጥፊ ተመታ)። ቅቤ የተቀባ ሰው ቅቤው ወዟያውኑ እንዳይቀልጥበት የሚያቃጥል የፀሃይ ሙቀትን አይሻም። ሆሳእናም ፊቱን በጥፊ ተመትቶ ሲሰቀል ፀሃይ ጨለመ ይላሉ ባለቅኔው። ቅቤ የተቀባ ሰው ፀሃይ እንዳይመታው ዛፍ ስር እንደሚቆም ክርስቶስ በእንጨት መስቀል ሲሰቀል ራቁቱን ሆነ።

አንዳንድ ተጋፊ ዳኛም በሕገወጥ አፈፃፀም የባእድን ሃብት እንደሚ



ወርስ ክርስቶስም የሟችን መፍረስ አስቀረ። ዲያብሎስ በስጋ ከይሲ (በእባብ አካል) ተሰውሮ አዳምን እንዳሸነፈው ክርስቶስም የአዳምን ስጋ ለብሶ ዲያብሎስን ድል ነሳው፤ በኖህ መርከብ ውስጥ እንደነበረው አባብም (ዘንዶም) ታገሰ። ክርስቶስ በእብነ ሩካም ተፅፎ ነበር የሚባል የአዳምን የእዳ ጽህፈት በዮርዳኖስ በተጠመቀ ጊዜ እንደደመሰሰው እንዲሁም በችንካር እግሩን ተቸነከረ።

በኪዳን ጊዜ ያልነበረ ካህን እንደማይቀድስ በአናንያና በአዛርያ ቅዳሴ (ምስጋና) መጀመሪያ ያልነበረው የቢታንያ ድንጋይ ክርስቶስ በአህያ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ ቀደሰ። እነአናንያ በባቢሎን በእሳት ጉድጓድ ውስጥ ፀለዩት በሚባለው ፀሎት “ ይባርክዎ ኵሉ ግብረ እግዚእ ለእግዚአብሔር፤ የጌታ ስራዎች ሁሉ እግዚአብሄርን ያመሰግኑታል” በማለት እያንዳንዱን ፍጥረት በየስሙ ዘርዝረው እግዚአብሄርን የሚያመሰግን መሆኑን ቢያስተውሉ“ ድንጋይ እግዚአብሄርን ያመሰግነዋል” አላሉም ነበርና ድንጋይ በሆሳእና በአል አፍ አውጥቶ ካመሰገነ የእነአናንያ ስርአት ተሻረ።

አንድ አማኝ ከእለት ምግቡ የተረፈውን ለነገ ሳያስቀር ለችግረኛ እንደሚሰጥ ክርስቶስን ያመሰገነው የቢታንያ ድንጋይ በሆሳእና በአል ጊዜ የተናገረውን ነገር ዳግመኛ አልተናገረም በማለት ባለቅኔው ቅኔያቸውን አመስጥረዋል።

### *111 ዕዝል ዕጣነ ሞገር (1226)አ*

*እንስተ ገሊላ ብክየ በወሊዶትክን ሮሰ*
*አርዌ ገሊላ ሄሮድስ እም አመ ነግሠ*
*ከመ ይብላዕ ሕፃናተ ዘአመ ፈርዖን አግነሠ፤*
*ወአመ ምክረ ሞት አስተኀየሰ*
*እምነ ድንግል ትጉይስ ኀቤሁ እስመ ረከበት ሞገሰ*
*ሚልኮል በኢወሊዶታ ሕፃነ ንኡሰ።*

### *አሠረ ንጉሥ*

*በወርኀ ምኒልክ ሰላም ዘአግበርክሙ መጥባሕተክሙ ማኅረሰ*

www.ethiopianorthodox.org

*ዙናተ ሐራ ግበሩ ይእዜ ማዕጸደክሙ ሐዲሰ*
*ማእረሩ ለዔሳው እምድኅረ የብሰ*
*ሐመልማለ ገመል ኢያውፅእ ወጽጌ ፈረሰ*
*በአትልዎ ዘነበ ወርእሰ*

## ትርጉም

በፈርኦን ጊዜ ያነሳቸውን ህፃናትን ይበላ ዘንድ
የገሊላ አውሬ ሄሮድስ ከነገሰ ጊዜ ጀምሮ
የገሊላ ሴቶች! ወንድ ልጅን በመውለዳችሁ አልቅሱ፣
የሞትንም ምክር በአሻሻለ ጊዜ
ሚልኮል ትንሽ ሕፃንን ባለመውለዷ በርሱ ዘንድ
ከድንግል ትሻላለች ፤ ሞገስን አግኝታለችና።

## አሰረ ንጉስ

በምኒልክ/ ሰላም ወራት ሾተላችሁን ማረሻ ያሰራችሁ!
የኤሳው አዝመራ ከደረቀ በሁዋላ ጅራትንና ራስን
በማስከተል ገመል/ ልምላሜን፡
አበባ/ ፈረስንም እንዳያወጣ አዲስ ማጭዳችሁን
የወታደሮች ጦር አድርጉ።

## ምስጢር

ውሻ ከሰው ፊት የወዳደቀውን ፍርፋሪ እንደሚለቃቅም ሁሉ የገሊላ ንጉስ ሄሮድስም አስራ አራት እልፍ ህፃናትን ከእናቶቻቸው እቅፍ ወስዶ ፈጀ። ፍርፋሪም ከተመጋቢ ሰው እጅ እንደሚወድቅ የግብፅ ንጉስ ፈርኦንም ወንዶች ሕፃናትን ከእናቶቻቸው ነጥሎ አስፈጅቷል። በሽፍታም ዘመን ከባለገንዘብ ይልቅ ገንዘብ የሌላት ድሃ ሰላም እንደምታገኝ በሄሮድስ ዘመን ስለልጅዋ ህይወት ከተሰደደች ከቅድስት ማርያም ይልቅ ያልወለደችው ሚልኮል ትደሰታለች ብለዋል ባለቅኔው።



በሰላም ዘመን ጦርነት ስለሌለ ሾተልን ማረሻ ማሰራት ይቻላል፤ በጠብ ዘመን ግን ማጭድን ጦር ለማሰራት ያስመኛል። እንዲሁም አፄ ምኒልክ በአድዋ ጦርነት ጣልያንን ድል ከነሱ ወዲህ ያለጦርነት ገበሬው በሰላም እያረሰ ኖረ። ጣልያኖች የአድዋን በቀል ለመበቀል ለጦርነት መንቀሳቀስ በጀመሩ ጊዜ ግን ገበሬው ያለአገር ነፃነት ማረስና ማዝመር ስለማይችል የውትድርና ተግባር ያከሂድ ነበር። አዝመራ ከደረቀ በሁዋላ እንደማያለመልምና እንደማያብብ ቢታወቅም፣ የኤሳውም ጠብ (የአረቦችም ጠብ) ደጀንና ፊታውራሪን በማከታተል የግመልን በቀልና በፈረስ የሚካሄድ ጦርነትን እንዳያመጣ በመስጋት ባለቅኔው በዘመናቸው የነበሩትን የኢትዮጵያን መሪዎች በቅኔያቸው አስጠንቅቀዋል ።

*112 ዘይእዜ (1248)አ*

*አይቴ ሀለው እለ ይቤሉ*
*ላዕለ ደብረ ወኸኒ ስቅልዎ ለሰብእናከ ኢያሱ?*
*ወእለ ፈቃዱ ካልአ ያንግሡ?*
*ይምጽኡኬ! ይርአዩ በዐፀደ መንግሥት እንዘ ታንሶሱ*
*ዳጋ ትብለከ ደብረ መቅደሱ*
*ለእስጢፋኖስ ሰማዕት ዘጸደሬ አእባን ልብሱ*
*ዳጋ ትብለከ ደብረ መቅደሱ።*

## ትርጉም

ኢያሱ! ሰውነትህን በወህኒ
ተራራ ስቀሉት ያሉት ሰዎች ወዴት አሉ?
ሌላ ሊያነግሱ ያሰቡትስ ወዴት አሉ?
በመንግስት ቦታ ስትመላለስ ያዩ ዘንድ
ልብሱ የድንጋዮች ግምጃ የሆነ የሰማእት እስጢፋኖስ
የመመስገኛው ደብር ዳጋ እንኪያ (እንግዲያውማ)! ይምጡ
አለችህ።
ልብሱ የድንጋዮች ግምጃ የሆነ የሰማእት እስጢፋኖስ

www.ethiopianorthodox.org

## ምስጢር

"በተራራ ላይ ቤት እንሰራለን ያሉት ሰዎች ወዴት ደረሱ? ካሉ·ማ! ወጥተው አይሰሩም ነበር? እስኪ እገሌ የሰራውን ቤት ይዩት" ይባላል። አፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ሊነግሱ ሲሉ ወህኒ በሚባለው አምባ ታሰሩ። በሁዋላ ከወህኒ አምባ ወጥተው በነገሱ ጊዜ እንዳይነግሱ የጣሩ ተቃዋሚ ዎች አፍረዋል። በጊዜው በኢያሱ ላይ የተፈፀመውን ደባ የተመለከቱት የቅኔ ሊቅ " ተቃዋሚዎች በመጡና አይናቸው ጉድ ባየ" በማለት በዲጋ እስጢፋኖስ ደብር የኢያሱን ድል አድራጊነት በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል።

*113 መወድስ (1251) አ*

*ከንቶ ፃመው እለ የሐንጹ*
*እመ ኢሐነጸ ቤተ እግዚአብሔር ለርእሱ*
*እመኒ ርስቶሙ በዠናቶሙ ወረሱ*
*ውስተ ፍናቶሙ ፍጡነ ሐንከሱ።*
*ዝንቱስ ፍሬ ከርሡ*
*ለመፍቀሬ ካህናት ዳዊት መፍቀሬ ካህናት ኢያሱ*
*ምንንተ ከመ ዕፄ ዘይሬስያ ለነፍሱ*
*ሐነጸ ወሣረረ በስመ ሥላሴ ቤተ መቅደሱ፣*
*ባሕቱ ለዝንቱ ንጉሥ ድኅረ ተፈጸመ ንግሡ*
*እም እለ የሐይዉ ካህናት እለ ይመውቱ ይኄይሱ።*

## ትርጉም

እግዚአብሄር ለራሱ ቤትን ካልሰራ በቀር
የሚያንፁ በከንቱ ደከሙ፣
ርስታቸውን በጦራቸው ቢወርሱም
በመንገዳቸው ፈጥነው አነከሱ።
ግን ይህ የካህናት
ወዳጅ የዳዊት የሆዱ ፍሬ የሆነ ሰውነቱን
እንደትል የተናቀች የሚያደርጋት የካህናት ወዳጅ ኢያሱ
በስላሴ ስም ቤተ መቅደሱን ፈፅሞ አነፀ፣


www.ethiopianorthodox.org

ነገር ግን የዚህ ንጉስ ንግስና ከተፈፀመች በሁዋላ
ከሚኖሩ ካህናት ይልቅ የሚሞቱት ካህናት ይሻላሉ።

## ምስጢር

ባለቅኔው የሰው ልጆች ስራ አምላክ ካልተጨመረበት ከንቱ እንደሚሆንና አምላክ ሲጨመርበት ግን መልካም ፍፃሜን እንደሚያገኝ ከመዝሙረ ዳዊት "እመ እግዚአብሔር ኢሐነጸ ቤተ ከንቶ ይጻምው እለ የሐንጹ፤ እግዚአብሄር ቤትን ካልሰራ ቤት ሰሪዎች በከንቱ ይድከሙበ ታል" የሚለውን ሃይለ ቃል ጠቅሰው የጦር አርበኞችም ቢሆኑ ያለእግዚ አብሄር ፈቃድ ያንዱን አገር ወርረው ቢይዙ ወዲያው ያጡታል ይላሉ ። አድያም ሰገድ ኢያሱም ለካህናት ምቹ የሆኑ ደገኛ ንጉስ ከመሆናቸው የተነሳ ምኞታቸው በጎንደር ከተማ በሚገኘው በደብረ ብርሃን ስላሴ ቤተ ክርስቲያን ስራ ተፈፀመላቸው ። የርሳቸው መንግስት ካለፈ በሁዋላ ለሚኖሩ ካህናትስ ከመኖር ይልቅ መሞት የሚሻል መሆኑን በማስረዳት ባለቅኔው ቅኔያቸውን አመስጥረዋል (መዝ·127፣ 1)።

*114 መወድስ ( 193)ጎ*

*በትረ ገቢረ ኀይል ኀቡረ ለእመ አንሥኡ*
*ኢያሱ ነቢይ ወሕዝቅያስ ዘኢይሔሱ*
*እፎኑ እምኮነት ፀሐየ ጸዋሚ እም ንእሱ!*
*አኮኑ ትቀውም በትእዛዙ*
*ለነቢይ እንተ አኅዊሁ ምድረ ርስት ወረሱ፣*
*ወአክሊለ ብርሃን ተቀጺላ*
*በትእዛዘ ሕዝቅያስ ሊቀ ዲበ ገጸ ሰማይ እስመ ታንሶሱ።*
*ባሕቱ ገቢረ ኃይል እመ ኀቡረ ኀሠሡ*
*ኢያሱ በገባዖን ወሕዝቅያስ በመቅደሱ*
*ለሊሁ ራጉኤል እምገብረ ለአርእዮተ ክብር እምልብሱ*
*ሚጠተ ፀሐይ ለሕዝቅያስ ወቆመተ ፀሐይ ለኢያሱ*

## ትርጉም

ነቢዩ ኢያሱና የማይዋሽ ህዝቅያስ
ተአምርን የማድረግ በትርን አንድነት ቢያነሱ

ከትንሽነቱ ጀምሮ የሁሞጊ ፀሃይ እንዴት በሆነች ነበር!
ወንድሞቹ የርስት ምድርን
በወረሱለት በኢያሱ ትእዛዝ ትቆግለችና ፣
የብርሃን አከሊልልንም ተቀዳጅታ
በሊቀ ህዝቅያስ ትእዛዝ በሰግይ ፊት ትመላለሳለችና ።
ነገር ግን ኢያሱ በገባአን ህዝቅያስም በመቅደሱ
ተአምርን ግድረግን አንድነት ቢሹ
የፀሃይን መመለስ ለህዝቅያስ ፣ የፀሃይን ቁመትም ለኢያሱ
እርሱ ራጉኤል ከልብሱ ክብርን ለግሳየት ባደረገ ነበር ።

## ምስጢር

ሁለት ሰዎች በበትር ያስፈራሯት ቤት ልጅ የምትሆነውን እንደም ታጣ ህዝቅያስና ኢያሱ በአንድ ጊዜ ተአምርን ግድረግ ቢችሉ ኖር ፀሃይ ለግንኛው እንደምትታዘዝ ትቸገር ነበር ። ምክንያቱም ልጇቱን አንዱ "ተቀመጭ" ቢላት ሌላው ደግሞ "ወደዚያ ሂጂ" ቢላት ለሁለቱም መታዘዝን እንደግትችል አንዷቱ ፀሃይ ለኢያሱ ብትቆም ለህዝቅያስ እስከ አስር ደረጃ ወደሁዋላ ልትመለስለት ስለግትችል ነው ። ነገር ግን ልጇቱ በየተራ ለሁለቱ ሰዎች እንደምትላክ ፀሃይም በተለያየ ጊዜ ለኢያሱ እንድትቆምና ለህዝቅያስም እግዚአብሄር እስከ አስር ደረጃ እንድትመለስ ለት ግድረግ ለመልአኩ ራጉኤል ለእስራኤል መስፍን የነዌ ልጅ ኢያሱና ለእስራኤል ንጉስ ህዝቅያስ ይቻለው ነበር በግለት ባለቅኔው በፀሃይ ላይ ተፈፅሟል የሚባለውን ተአምር በቅኔያቸው አስረድተዋል (ኢያ·10፡ 11–14 ። 2 ነገ·20፡11) ።

*115መወድስ(192)ኀ*

*ሰቆል ዐይንየ ዴበ ዐይኑ ሆሉ ፤*
*እንዘ ላዕለ ሞውት አኑ ወታሕተ ሕያዋን አንቦሱ*
*እምግኑ አልቦ ከግየ ዘያቴሕታ ለርእሱ*
*እም እለ አዝግን ቀደሙኒ*
*ወእለ አዝግን እምኔየ ንእሱ ።*
*ዓዲ ጊዜ ተጽናሱ*



*ዘይትዔረየኒ አልቦ ዘበሥጋዊት ግኀሡ ፤*
*ይትርፍስ ፍጥረተ ሰብእ ዘያከብራ ለነፍሱ*
*ዕፀው ወአዕዋፍ እምኔየ ይኄይሱ*
*እንዘ ኢይዘርእ ዖፍ እስመ ይመልዓ ለከርሡ*
*ወዕፀው በበዓመት እንዘ ኢየዐንሙ ይለብሱ ።*

## ትርጉም

አይኔ በሁሉ አይን ላይ የተሰቀለ ነው ።
እኔ ከሙት በላይና ከደሀነኞች በታች ስመላለስ
በዘመናች ከቀደሙኝ ሰዎችና
በዘመናች ከእኔ ከአነሱት
እንደእኔ ራሱን የሚያዋርዳት የለምና ፣
ዳግመኛም በችግሩ ጊዜ
በስጋዊት ፍላጎቱ የሚስተካከለኝ የለምና ።
ሰውነቱን የሚያከብራት የሰው ባህርይስ ይቅርና
እንጨቶችና ወፎች ከእኔ ይሻላሉ ፣
ወፍ ሳይዘራ ሆዱን ይሞላታልና
እንጨቶችም በያመቱ ሳይሸምኑ ይለብሳሉና ።

## ምስጢር

የተንጠለጠለ ነገር ከታችኞቹ በላይና ከላይኞቹ በታች ይወዛወዛል። ባለ ቅኔውም ከህያዋን በታችና ከሞቱት በላይ ሆነው ሲንጠራወዙ አይናቸው ይቀላውጣል ፣ ወደ ሀብታሞችም አይን እየተመለከተ ይቅበዘበዛል ።

ደካማ መንገደኛ የቀደሙትን መንገደኞች እንደማይደርስባቸውና ሁዋለኞችም እንደሚቀድሙት ፣ ባለቅኔውም በእድሜ ከቀደሟቸውና ከአነሷቸው በታች ሆነው ተዋርደው መኖራቸውን በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል ። በጣም ቁመታም የሆነውን ሰው በርዝመት የሚስተካከለው የለም እንደሚባል በጣም ችግረኞች ናቸው ከሚባሉት ድሆች እንኳን የባለቅኔው ችግር ባሰ ። እነዚያ (ችግረኞች) ለምነው ይጠግባሉ ይለብሳሉ። ባለቅኔው ግን እንዳይለምኑ ያፍራሉ ፤ ሲርባቸው እንዳይበሉና ሲበርዳቸው እንዳይለብሱ ሃብት የላቸውም ።



www.ethiopianorthodox.org

እንጨቶችም ለምለም ቅጠልን ይጎናፀፋሉ ፤ (ይለብሳሉ) ወፎችም ይጠግባሉ ። ባለቅኔው ግን ሰውነታቸው ደርቆ ፣ ሆዳቸው ተጣብቆ በችግር ሲማቅቁ መኖራቸውን ብቸኛ ሃብታቸው በሆነው በቅኔያቸው ምስጢር አስረድተዋል ።

## ታሪክ

ባለቅኔው ተምረው በሊቅነታቸው የእለት ጉርስ የአመት ልብስ ሳያገኙ የቀሩና ካልተማሩ ሰዎች በታች ሆነው በችግር ሲሰቃዩ የኖሩ መሆናቸው በቅኔያቸው ተገልጧል ።

*116 ግእዝ ጉባኤ ቃና/ስ*

*በምንት ቆመት ድንግለ ሙሴ ወዮሳ?*
*ሰማይ ወምድር እስመ ሀለው በከርሣ*

## ትርጉም

የሙሴና የዮሳ ድንግል በምን ቆመች?
ሰማይና ምድር በሆዷ አሉና ።

## ምስጢር

የፍጥረት ሁሉ መቆሚያው ምድር ሲሆን ምድርንና ሰማይን በመሃል እጇ የያዘ አምላክን የፀነሰች ድንግል ማርያም ምድርና ሰማይም በሆድ ውስጥ ስለሆኑ የምትቆምበት ምድር አላገኘችም ይላሉ ባለቅኔው ።

*117 ሥላሴ(1277)አ*

*ዘገብረ ሥላሴ(መምህር ፡ ዘኤልያስ)*

*ኢኮነት ምሳሌሃ*
*ዐጽቀ አቤሜሌክ ለድንግል ፤*
*እስመ ዘአቤሜሌክ ዕፅ ዐቃቢተ ርእሱ እንስሳ*
*በከየት ብካየተ ደም ክራማተ ስድሳ ።*
*ባሕቱ ድንግል ንጽሕተ ዙሉ አበሳ*
*ኢርእየት ደመ እም ቅድመ ፅንሳ ፤*
*እስከ አመ ወለደት ወልደ ፍሬ ከርሣ*
*ዐቃቢሁ እመኒ ለርእሳ ።*



## ትርጉም

የአቤሜሌክ አፅቀ በለስ (የበለስ ቅንጣት)
የድንግል ማርያም ምሳሌ አልሆነችም ፤
ራሱን/እንስሳ የምትጠብቅ የአቤሜሌክ እንጨት
ስድሳ ዘመን የደም ልቅሶዎችን አልቅሳለችና ።
ነገር ግን ከበደሉ ሁሉ የነፃች ድንግል
የሆድዋ ፍሬ ወልድን እስከወለደች ድረስ
ከፅንሷ በፊት ደምን አላየችም ፤
ምንም ራሷን ጠባቂ ቢሆን ።

## ምስጢር

"እገሊት የእገሊት ወደረኛ ልትሆን አትችልም ። ያቺ ሳሃ አታጣም፤ ይህች ግን እንከን የሌላት ናት" ይባላል ። የአቤሜሊክ በለስ ጫፍም የቅድስት ማርያም ምሳሌ ስትባል ምሳሌነቷ አልተሳካም ። ምክንያቱም ቅድስት ማርያም ከመፅነስም በፊት ፣ በመፅነስና በመውለድም ጊዜ ከደም የነፃች ናት ። የአቤሜሌክ በለስ ግን ስድሳ ዘመን ሙሉ ከደም አልተለየችም በማለት ባለቅኔው ስለቅድስት ማርያም ንፅህና ያላቸውን እምነት በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል ።

ታሪኩ በአንደኛው መፅሃፍ በገፅ 216 ተተርኳል ።

*118መወድስ (204)ኀ*

*ኢየሱስ ክርስቶስ ፈትለ ሜላት*
*ዘቀጥቀጡከ በዓርብ ጠበብተ እስራኤል ስሳ*
*ወሐዋርያዊት ዕፅ ዘፆረተከ በከርሣ!*
*ሐጸቡከ ሕዝብ በቅንዋት*
*ማያተ ሀልዎ በብዙኀ ኀሠሣ ፤*
*ወዳግመ ወሀቡከ*
*ለዋዕየ ፀሃይ ጽኑዕ ሞተ እለ አቤል ወአቢሳ ።*
*ድኅረሂ አመ ወፈርከ ምድረ አርባዕቱ እንስሳ*
*ኀይልከ ባሕታዊ ተፅዕነ በአንበሳ ፤*
*ስቅለተከ ሂ ዘመነ ለአውጽአ መጥቅዕ አበሳ*
*ካህን አስቆሮታዊ ገደፈ በሠላሳ ።*

www.ethiopianorthodox.org

## ትርጉም

ስላ የእስራኤል ጥበበኞች በአርብ
የቀጠቀጡህ ፣ መወርወሪያ እንጨትም በሆዱዋ የተሸከመችህ
ኢየሱስ ክርስቶስ/የሃር ፈትል!
በችንካሮች/ የመኖር ውሃዎች
ሕዝብ በብዙ አበሳ አጠቡህ ፤
ለፅኑ የፀሃይ ቃጠሎ /የእነአቤልና የእነአቢሳ ሞትም ዳግመኛ ሰጡህ።
በሁዋላም በአራቱ እንስሳዎች ምድር በተሰማራህ ጊዜ
ሃይልህ/ባህታዊ በእንበሳ ተጫነ (ተቀመጠ) ፤
ስቅላትህ ዘመንንም መጥቅእ/አበሳን ለማውጣት
ካህን/የአስቆሮት ሰው ይሁዳ በሰላሳ ገዷሬ ።

## ምስጢር

ልብስ የሚሆን ፈትል አርብ መስሪያ በሚባለው በሸማኔ (ይጸጠራል) በመወርወሪያም ሆድ ይደረጋል ፤ በውሃ ተነክሮ ለፀሃይ ሙቀት ይሰጣል ። ኢየሱስ ክርስቶስም በአርብ ቀን በአይሁድ እጅ ተሰቃየ ፤ በመስቀል ተሰቀለ ። ፈትሉ በሙቅ ውሃ ተነክሮ ለፀሃይ እንደሚሰጣ ኢየሱስ በችንካሮች ተቸንክሮ ሞተ ።

እረኛም ከብቶችን እየነዳ ከከብቶች ጋር እንደሚሰማራ ኢየሱስ ክርስቶስ በአራቱ ኪሩቤል ላይ ተመስገነ ። ባህታዊም የመንፈሳዊ አገልግሎቱ እንደ እሳት ለመፋጇት እንደሚያደርሰው ሰው ፤ በአንበሳም ላይ የመቀመጥ ፀጋ እንደሚሰጠው ክርስቶስም በአምላክነቱ አራቱን ኪሩቤል እንደአንበሳ ያስፈራቸዋል ። ካህን "መጥቅዕ" የሚባለውን ቁጥር ለማውጣት ዘመኑን በሰላሳ እንደሚገድፈው (እንደሚያከፋፍለውና ቀሪውን ለአፅዋማት ማውጫ እንደሚያደርገው) ይሁዳም ኢየሱስን አበሰኛ ተብሎ እንዲሰቀል በሰላሳ ብር ሸጠው ይላሉ ባለቅኔው ።

*1190ዘል ክ/ይእቲ/ስ*

*እፎኑመ መልአ ይሁዳ ውስተ ልብከ አበሳ*
*በዓለ መካልይ ትሢጥ በሤጠ ዮሴፍ ሠላሳ!*
*አምጣነ እኮ ሥርዐት ሤጠ ትንንያ ለዓሣ ፤*
*ወእኮ ልማድ ሤጠ ጣዕዋ ለዘየዐብዮ እንስሳ ።*



## ትርጉም

ይሁዳ ባለብዙ መክሊት ወልድን በዮሴፍ ሽያጭ ሰላሳ ብር
ትሸጥ ዘንድ እንዴት በደል በልብህ ሞላ!
የትንኝ ዋጋ ለአሳ እንዲሆን ስርአት አይደለምና ፤
የጥጃም ዋጋ ለሚበልጠው እንስሳ እንዲሆን ልማድ አይደለምና ።

## ምስጢር

የትንሽ ዋጋ ትንሽ ፡ የትልቅም ዋጋ ትልቅ ይሆናል እንጂ የትንሹ ብዙ የትልቁም ትንሽ ሊሆን አይችልም። አላዋቂ ባለከብት ግን ትልቁን በሬ በቀላል ዋጋ ይሸጠዋል ። ይሁዳ አእምሮ ጎደሎ በመሆኑ ወርቅ የተባለ ኢየሱስ ክርስቶስን ወንድሞቹ ለግብፅ ነጋዴዎች እንደሸጡት እንደያእቆብ ልጅ እንደ ዮሴፍ በሰላሳ ብር ሸጠው በማለት ባለቅኔው የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል ።

*120 ግእዝ ክብር ይእቲ (207)ጎ*

*አመ በዐለ ሞት ገብረ መልአከ ሐሰት ለአበሳ*
*ኢረከበት ሲኦል መርዓተ ብዙኅ ኅሠሣ*
*ቅብዐ ኀጥአን ሞተ ከመ ትቅብዖ ለርእሳ*
*ሤጠ ደመ ወልድ ቅብዕ እስመ ኮነ በሠላሳ ።*

## ትርጉም

የሃሰት መልአክ ለአበሳ የሞት በአልን ባደረገ ጊዜ
የብዙ ፍለጋ ሙሽራ /ሲኦል የሃጢአተኞች
ቅቤ/ ሞትን ራሷን ትቀባው ዘንድ አላገኘችም ፤
የወልድ ደም/ቅቤ ሽያጭ በሰላሳ ብር ሆኗልና ።

## ምስጢር

ቅቤ በተወደደ ጊዜ ዋጋው እስከ ሰላሳ ብር ይደርሳል ። የእግዚአብሄር ወልድ ደምም በሰላሳ ብር ሽያጭ ፈሰሰ ። ቅቤ ሲወደድ በበአል ጊዜ ሴት የምትቀባው አታገኝም ። የሃሰት መልአክ ሞትን ባመጣ ጊዜም ሲኦል የሃጢአተኞችን የነፍስ ሞት ለራሷ ገንዘብ አላደረገችም ።



www.ethiopianorthodox.org

ምክንያቱም ነፍሳት በወልድ ደም ነፃ አውጪነት ከሲኦል ውስጥ ስለወጡ ነው በማለት ባለቅኔው የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት በቅኔያቸው ምስጢር መስክረዋል ።

*121 ዘአምላኪየ /ስ*
*ዘመርሐ ጽድቅ (ግራ ጌታ)*

*መቅድመ ተአምር በታቦር አመ አንበቡ ሥላሴ*
*ይስማዕ ነቢሮ እንተ ደከመ ሙሴ*
*እስመ ቆመ ጴጥሮስ ለአብጽሖ ፍርሃት ቅዳሴ ።*

## ትርጉም

የተአምር መጀመሪያን ስላሴ በአነበቡ ጊዜ
የደከመ ሙሴ ተቀምጦ ይስማ !
ጴጥሮስ ፍርሃት/ቅዳሴን ለማድመጥ ቆሟልና።

## ምስጢር

የተአምር መቅድም ሲነበብ የደከመው ተቀምጦ ፣ የበረታው ቆሞ እንዲሰማ ተፈቅዷል ። የክርስቶስ ብርሃነ መለኮትም በደብረ ታቦር ሲገለፅ ሙሴ ወደነበረበት ተመለሰ ። ለማስቀደስ ማልዶ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሄደ ሰው ቅዳሴን ለማድመጥ ቀጥ ብሎ እንደሚቆም ጴጥሮስም ከመፍራቱ የተነሳ በድንጋጤ ድርቅ ብሎ ቀረ ይላሉ ባለ ቅኔው ።

*122 ዘአምላኪየ (1336) አ*
*ዘገብረ ሥላሴ (መምህር ፡ ዘኤልየስ)*

*ብርሃና ለገጽ እንዘ ጽልመታ ለልብስ*
*ቅብዐ ላሕም ፣ ዝኒ ደመ ወልድ ቅዱስ*
*ደዌሃ ውእቱ ለሥጋ እንዘ መድኃኒታ ለነፍስ ።*

## ትርጉም

የላም ቅቤ የልብስ ጥቁረት ሲሆን የፊት ብራት ነው ፣
ይህም የተቀደሰ የወልድ ደም
ለነፍስ መድሃኒቷ ሲሆን ለስጋ ደዌዋ ነው ።



## ምስጢር

የላም ቅቤ ልብስን ሲበክልና ሲያጠቁረው ፊትን ያበራዋል ፣ የኢየሱስ ክርስቶስም ደም ሃጢአተኛ ስጋን ሲያመነምን ነፍስን ያፀድቃታል በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

*123 ሚበዝኑ (1339) አ*
*ዘገብረ ሥላሴ (መምህር ዘኤልየስ)*

*ጠለ ደመና ዘክርም*
*ወዘርዐ ሐረስት ሀወለ ፣ እሉሰ ወርኃ የብስ*
*ወዘርዐ ሐረስት ሐወዘ ኀበ ቦሙ ግብረ ባእስ ፣*
*ዘኒ ዘፈትሐ በማኅተመ ጥበብ ይትዋነይ ምስለ ሰሎሞን ንጉሥ።*

## ትርጉም

የክረምት ደመና ጠልና
የገበሬዎች ዘር "ሀናለ" ፊደሎች ናቸው ፣ እነዚህ የድርቅ ወርና የገበሬዎች ዘር ግን የጠብ ስራ ካላቸው ዘንድ "ሐናዘ" ፊደሎች ናቸው ፣ ይህንንም በጥበብ/ቁልፍ የፈታ ከንጉስ ሰሎሞን ጋር ይጫወት ።

## ምስጢር

ሀሌታው "ሀናለ" የተባሉት ፊደሎች በቦታ የተቃረቡ እንደሆኑ የገበሬ ዘርና የደመና ጠል ተፈላላጊዎች ናቸው ። ዘር በዝናብ ጠል ይበቅላል ይለመልማል ። ደግሞ ሀመሩ "ሐናዘ" የተባሉት ፊደሎች የተራራቁ እንደሆኑ የገበሬ ዘርና የድርቅ ወራት አይተባበሩም ፣ በድርቅ ወራትም ዘር አይዘራም በማለት ባለቅኔው በፊደላት አደራደር ላይ የተመሰረተውን ቅኔያቸውን የሚፈታ (የሚተረጉም) የቅኔ ባለሙያ ከጠቢቡ የእስራኤል ንጉስ ሰሎሞን ጋር በጥበብ ሊወዳደር እንደሚችል አስረድተዋል ። ባለቅኔው "ሀወለ ፣ ቀላቀለ" እና "ሐወዘ ፣ አማረ" የተሰኙትን የግእዝ ግሶች በ"ወ ፣ እና" ላጫፈሩዋቸው "ሀ ፡ ለ ፡ ሐ ፡ ዘ" ፊደላት መሰወሪያ አድርገዋቸዋል ። ምክንያቱም ግእዝ ለተማረ ሰው



www.ethiopianorthodox.org

እስተድሞ ትዝ የሚለው የግሶቹ ያግርኛ ትርጉም እንጂ የፊደላቱ መጫፈር ስላልሆነ ነው ።

*124 ሚበዝኁ (338) አ*

*ዘእሼቴ (መልእክ ገነት)*

*ገዘፈ ሥጋ በእክል*
*ወገዘፈ ነፍስ በጾም እምጣነ ሥጋ ጽኑስ*
*ኢይቀውም ምንተ እንበለ መብልዕ ሐዲስ*
*ወእንበለ ጾም ብዙኀ አልባቲ በቁዔት ለባሕታዊት ነፍስ ።*

## ትርጉም

የስጋ ውፍረት በእህል
የነፍስ ውፍረትም በፆም ነው ፤ ችግረኛ ስጋ
ያለአዲስ መብል ምንም አይቆምምና ፤
ለብቸኛ ነፍስም ያለብዙ ፆም ጥቅም የላትምና ።

## ምስጢር

ግድግዳ ያለጣሪያ ጣሪያም ያለግድግዳ እንደማይፀኑ ፡ ስጋ ያለ እህል ነፍስም ያለፆም ህይወትን ሊያገኙ አይችሉም በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

*125 ዋዜማ (1342) አ*

*ዘክንፋ (አለቃ ፡ ዘሩፋኤል)*

*ተክለ ሃይማኖት ነጋዴ ባሕር*
*ንስቲተ ወርቀ ስብሐተ ሥጋ ወነፍስ*
*በዋሕድ እግሩ አትረፈ ለልብስ ፡*
*ወይቤ በቃል መከየደ እግሩ ቀሲስ*
*ስብሐት ይደሉ ለሥሉስ ቅዱስ*
*እንዘ ሀሎ በሰማይ መቅደስ ።*

## ትርጉም

የባህር ነጋዴ/ተክለ ሃይማኖት
ትንሽ ወርቅ/የስጋና የነፍስ ምስጋናን
በአንድ እግሩ ለልብስ አተረፈ ፤
የእግሩ መርገጫ /ቄስም በሰማይ/ መቅደስ
ሳለ በቃል ለሶስት ቅዱስ ፡
ምስጋና ይገባል አለ ።

## ምስጢር

የባህር ነጋዴ በአንድ እግር (በአንድ ጊዜ) ለልብስ የሚሆነውን ትርፍ እንደሚያተርፍ ፃድቁ ተክለ ሃይማኖትም በአንድ እግራቸው ቆመው በልብሳቸው የተነገሩ ምስጋናን አበዙ ። ቄስም በመቅደስ ውስጥ "ስብሐት ወክብር ለሥሉስ ቅዱስ ይደሉ ። ለሶስት ቅዱስ ምስጋናና ክብር ይገባል" እያለ እንደሚያመሰግን የፃድቁ ተክለ ሃይማኖት እግርም በሰማይ ስላሴን አመሰገነ በማለት ባለቅኔው በፃድቁ ተክለ ሃይማኖት እግርና ልብስ ተፈፅሟል የሚባለውን ተአምር በቅኔያቸው ምስጢር አረጋግጠዋል ።

*126 ሥላሴ (1365) አ*

*ዘእንግዳ ወርቅ ኃይሉ (አለቃ)*

*ወሀበ ፀባሕተ ወርቅ*
*ለዘነግሠ ፈትል ውስተ ገሊላ*
*አጽባዕተ ድንግል አምላክ ርእዮ መልክአ ዲናር ንጉሥ*
*ዘተጽሕፈ በሕልቀተ ስሙ ለቄሣር መቅደስ*
*በመጥባሕተ መኑ ትገብር ባሕቱ ኢይበልዎ አልባስ*
*እስመ ዐናሚሁ መንፈስ ቅዱስ ፡*
*ወያረውጾ ለወርቅ ሐመልሚል ፈረስ*
*ዘተዕዕነ ዲቤሁ መንፈስ ።*

## ትርጉም

የድንግል ጣት/አምላክ
የብር ንጉስ መልክን አይቶ
በገሊላ ለነገሰ ፈትል በስሙ/ቀለበት የተፃፈ
የወርቅ ግብርን በቄሳር/መቅደስ ሰጠ ፡


www.ethiopianorthodox.org

ነገር ግን ልብሶች "በማን ስልጣን ይህን ትሰራለህ" እንዳይ
ሉት ሰሪው መንፈስ ቅዱስ ነው እኮ ፤
መንፈስ በርሱ ላይ የተቀመጠ ዝጉርጉር
ፈረስ/ወርቅንም ያሮጠዋል ።

## ምስጢር

ኢየሱስ ክርስቶስ የንጉስ ቄሳር ስም የተፃፈበትን ዲናር አይቶ "የቄሳርን ለቄሳር ፡ የእግዚአብሄርን ለእግዚአብሄር ስጡ" እንዳ የቅድስት ማርያምም ጣት ወርቅንና ሃርን አዋህዶ ፈተለ ። በዲናሩ የቄሳር ስም እንደተፃፈበትና መልኩም እንደተቀረፀበት የተፈተለውም ፈትል ለቤተ መቅደስ አገልግሎት ሆነ ። አይሁድ "ይህን በማን ስልጣን ትሰራለህ" እንዳሉት የቅድስት ማርያምን ፈትልም የሌሎች ልብሶች እንዳይመስሉት በመንፈስ ቅዱስ የተሰራ ነው ። ፈረስንም ጋላቢው እንደሚያሮጠው በቅድስት ማርያም የሃርና የወርቅ ፈትል ስራም የመንፈስ ቅዱስ ተሳትፎ አለበት በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

*127 ሥላሴ/ስ*

*በዘመን ቀዳማዊ*
*ኢይሕሚ ቋዕ ኤልያስሃ*
*በተአዝዞቱ አክራመ ሠለስተ እንበለ መብልዕ ወልብስ*
*ለዕጓለ ቋዕ ዘዐቅሙ ንኡስ*
*እስመ ወሀብኮ ዐይነከ ማኅቶተ ሥጋ ግሡሥ*
*አድኅንኮ ሐሜተ ለኤልያስ*
*ገብረ መንፈስ ቅዱስ ዓለመ ሰማየ አፍራስ*
*ዘወረድከ ይእዜ በነፍስ ።*

## ትርጉም

የፈረሶች ሰማይ አለምን
ዛሬ በነፍስ የወረድህ
ገብረ መንፈስ ቅዱስ ! በቀድሞ ዘመን ቁራ ኤልያስን
እንዳያማ ያለ መብልና ያለ ልብስ ሶስት ዘመን በመታዘዝ



አቅሙ ትንሽ ለሆነ ለቁራ ግልገል
የተዳሳሽ ስጋ መብራት
የሆነ አይንህን ሰጥተኸዋልና
ኤልያስን ከሃሜት አዳንኸው ።

## ምስጢር

ያገለገለ ሰው ያገልግሎቱን ደመወዝ ሲያጣ ቀጣሪውን ይወቅሳል ። የተወቃሹም ወገን ስለበዳዩ ሆኖ ይከስለታል ። ከዚህ በሁዋላ ወቀሳው ይወገዳል ። ቁራ ስጋ እያመላለሰ ሶስት አመት ከመንፈቅ በነፃ የቀለበው ነቢዩ ኤልያስ እያለ ቁራ ምንም ያላገለገላቸው ፃድቁ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ለቁራ አይናቸውን አጠጡት ይላሉ ባለቅኔው (1 ነገስ ፡ 17 ፡ 2—7 ፡ ገድለ ገብረ መንፈስ ቅዱስ) ።

*128 ሥላሴ (1361) አ*

*በርቀት እለ ተፈጥሩ*
*መላእክት ረኃብ ወጽምዐ ማይ*
*ውስተ ባሕረ እሳት አንብዕ እንተ ይትረከብ እምርእስ*
*አስጠሙኪ እንበለ ርኅራኄ ማርያም ነፍስ ፤*
*ኢነጸርኪ ምንተ እመኒ ገጸ መልአከ ሞት ሄሮድስ*
*ወአመ በከርሥኪ ይትከወስ*
*እንተ ጊዜሁ ኀለፈ ረኀብ ፅንስ*
*ጼና እክል ጸላእኪ እምከርሥ ።*

## ትርጉም

በርቀት የተፈጠሩ
መላእክት/ራብና የውሃ ጥም
ከራስ በሚገኝ እሳት ባህር/እንባ ውስጥ
ማርያም/ነፍስ ! ያለ ርኅራሄ አሰጠሙሽ ፤
ምንም የሞት መልእክተኛ የሄሮድስ ፊትን ባታዩ
ጊዜው ያለፈ ራብ/ፅንስም
በሆድሽ በሚላወስ ጊዜ
የእህልን ሽታ ከሆድ ጠላሽ ።



www.ethiopianorthodox.org

## ምስጢር

የተኰነነችን ነፍስ በርቀት የተፈጠሩ (የሚዳሰስ ስጋዊ አካል የሌላቸው) መላእክት በእሳት ባህር ውስጥ ያሰጥሟታል ይባላል ይህም የሚሆነው ነፍስ ፊቱን በማታየው የሞት መልአክ ከስጋ ስትለይ ነው እየተባለ ይነገራል ። ሰውነትን የሚያቀጥኑ ራብና ጥምም ቅድስት ማርያምን በእንባ አጠቧት ፤ በማህፀን ውስጥ የተፀነሰ ፅንስ ሲላወስ ነፍሰጡሪቱ ሴት የእህልን ሽታ እንደምትጠላ ራብም በማርያም ሆድ ፀና ። ለሽታ እንኳን ምግብን አላገኘችም በማለት ባለቅኔው ቅኔያቸውን አመስጥረ ዋል ።

*129· መወድስ (235)ጎ*

*ዘከፍለ ዮሐንስ*

*ጥቀ ኄር እግዚአብሔር*
*ለሐዋርያ ግብጽ ዮሴፍ ዘበደዌ ሞቅሕ ሐንካስ*
*ወለዘፈተኖ ዳንኤል በጾመ ዕለታት ሠላስ ።*
*በጥቃ መዓቱስ እንዘ ሀሎ*
*ማእረረ ምናሴ ምሕረቱ ሐዲስ ፤*
*እስመ ያሜክረነ በተጽናስ*
*ወአርዌ ረኀብ ይነቁ ውስተ ጸላዕትየ ከርሥ ።*
*መብልዕየሂ ጼና መብልዕ ዘያመጽእ ነፋስ*
*ወስቴ አንብዕየ ተረፈ አንብዑ ለኤርምያስ ፤*
*ልብስየ ሂ ምንንት መንጠላዕተ ርኀቅት ነፍስ*
*እስመ አነ ከመ ዶርሆ እምላዕለ አብራክየ እለብስ ።*

### ትርጉም

በደዌ/እግር ብረት
አንካሳ ለሆነ ለግብፅ መንገደኛ ዮሴፍና በሶስት ቀናት
ፆም ለፈተነው ለዳንኤል እግዚአብሄር እጅግ ቸር ነው
በቁጣው አጠገብ ሳለ ግን
የምናሴ አዝመራ ይቅርታው አዲስ ነው ፤
በችግር ይፈትነናልና ፤
አውሬ/ራብም በዋሻ ሆዴ ይጮኽልና ።
መብሌም ነፋስ የሚያመጣው የመብል ሽታ ነው



መጠጤም የኤርምያስ የእንባው ትራፊ የሆነ እንባዬ ነው ፤
የተናቀች ልብሴም የራቀች ነፍስ መጋረጃ ናት ፤
እኔ እንደደሮ ከጉልበቴ በላይ እለብሳለሁና ።

## ምስጢር

ህመምተኛ ከበሽታው ፅናት የተነሳ እግሩ ያነክሳል ፤ ዮሴፍም ለግብፅ ሰዎች ከተሸጠ በሁዋላ እግሩ በእግር ብረት ታሰረ ። ተማሪ በትምህርቱ እንደሚፈተን ዳንኤል ሶስት ቀን በፆም ጊዜ አለቀሰ ። ህመምተኛው ከደዌው እንደሚፈወስና የተፈተነውም ተማሪ ፈተናውን በጥሩ ውጤት እንደሚያልፈው ዮሴፍንና ዳንኤልንም እግዚአብሄር አዳናቸውና አላቃቸው ።

አባት ሲቆጣ በልጁ ፊቱን እንደሚያዞርበት ባለቅኔውንም የስጋ ፍላጎትን በማሟላት እግዚአብሄር አልጎበኛቸውም ። አዝመራ በየጊዜው አዲስ እንደሚሆን ለምናሴ የሆነው ቸርነቱ ባለቅኔውን አስቸገራቸው ። ተማሪ በትምህርቱ እንደሚፈተን ባለቅኔው በችግር ተንገላቱ ፤ አውሬም በዋሻው እንደሚጮህ የባለቅኔው ሆድ በተራበ ጊዜ ያንጫርራል ።

ሃብታም ባለስልጣን ደጀጠኝ ያመጣለትን ምግብ እንደሚመገብ ባለቅኔው ነፋስ የሚያውደውን (የሚያመጣውን) የምግብ ሽታ እንደ እለት ምግብ አደረጉት ። አሽከርም የጌታውን ትራፊ እንደሚጠጣ ባለቅኔውም ከችግራቸው ጥናት የተነሳ የሚያነቡት እንባቸው በአፋቸው ውስጥ ገባ ።

አውራ ዶሮ ረዘም ያለ ጠጉር ያለው ከጉልበቱ በላይ እንጂ ከጉልበቱ በታች እንዳልሆነ የባለቅኔው ልብስ ለሙቀት ሳይሆን ለሰውነት መከለያ ያህል የተዘጋጀች ቁራጭ ጨርቅ ናት በማለት አኗኗራቸውን በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል ።

*130 መወድስ(459) አ*

*ዘገብረ ሥላሴ(መምህር ፡ ዘኤልያስ)*

*ይቤሎ ለሰይፍ መጋቤ ደቂቁ*
*በዐለ በለስ ሞት ፍሬ ኑፋቄ ዘየኀሥሥ*
*ግዝማ እንከ ለርእሰ ልዳዊ በለስ*
*ፍሬ ክህደተ ኀበ ኀጣእኩ ፤*
*ወለምጽአትየ ይእዜ ሣልስ ፤*
*አምጣነ ውእቱ ጊዮርጊስ*



www.ethiopianorthodox.org

*ያፀርዕ ምድረ አምልኮተ ባዕድ እምንእስ ።*
*ተጠምቀሂ ሰማዕተ ልዳ በኀዲገ ፍርሃት ልብሰ*
*ተመትሮ ጥምቀተ ማይ ዘሰበከ ዮሐንስ ፤*
*ወእም አጽናፈ ምድር መጽአት ንግሥተ አዜብ ነፋስ*
*ትስማዕ ጥበቢሁ ለዐፅመ ልዳዊ ወልደ ንጉሥ ።*

## ትርጉም

ፍሬ ጥርጥርን የሚሻ
ባለበለስ/ሞት የልጆቹ መጋቢ/ሰይፍን
ፍሬዋ ክህደትን ከአጣሁ ዘንድ
የልዳ ሰው ራስ/በለስን እንግዴህ ቁረጣት አለው ፤
ለመምጣቴም ዛሬ ሶስተኛ ነው ፤
እርሱ ጊዮርጊስ
ባእድን ማምለክ ምድርን ከልጅነት ጀምሮ ያቦዘናልና
ዮሃንስ የሰበከውን መቆረጥ/ የውሃ ጥምቀትንም
የልዳ ሰማእት ፍራት/ልብስን በመተው ተጠመቀ ፤
የጊዮርጊስ አጥንት/የንጉስ ልጅ ጥበብንም ትሰማ ዘንድ
የአዜብ ንግስት/ነፋስ ከምድር ዳርቻዎች መጣች ።

## ምስጢር

የበለስን ፍሬ የሚሻ የበለስ ጌታ በለሱ የማታፈራ መሆኗን በተረዳ ጊዜ የልጆቹ መጋቢ(የሰራተኞቹ አለቃ)በለሲቱን እንዲቆርጣትና ምድሩም በእርሷ አለማፍራት እንዳይቦዝን እንዲያደርግ ያዛል ። መጋቢው የበለስን ፍሬ እንደሚሻ ሞትም መወላወልን ያመጣል ። መጋቢው በለሲቱን እንደቆረጣት ሰይፍም የሰማእቱ ቅዱስ ጊዮርጊስን ራስ ከአንገቱ ለያት ። በበለሲቱ ፍሬ እንደታጣባት በሰማእቱ ቅዱስ ጊዮርጊስም ክህደት አልተገኘበትም ። መጋቢው ወደበለስ ሶስት ጊዜ እንደተመላለሰ ሞትም በጊዮርጊስ ሶስት ጊዜ ተፈፀመ ። ያላፈራችው በለስ ምድርን እንዳቦዘነች ጊዮርጊስም የባእድ አምልኮን አጠፋ ። በክርስትናም ሆነ በሌላ ህመም ምክንያት በውሃ የሚጠመቅ ሰው ልብሱን አውልቆ ይጠመቃል ። ጊዮርጊስም አንገቱን ሲቆረጥ ፍርሃትን አራቀ ። ዮሃንስ የንስሃ ጥምቀትን እንደሰበከ መቆረጥንም አስቀደመ ።



የአዜብ ንግስት ማክዳም የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት እንደመጣች አዜብ ከሚባለው አቅጣጫ የነፈሰች ነፋስም የጊዮርጊስን አጥንት በተነች ይላሉ ባለቅኔው(ክብረ ነገስት) ።

*131 መወድስ/ስ*
*ዘአፈወርቅ ትኩዬ(መሪጌታ ፣ ዘሰይፋጥራ ማርያም)*

*ምሉዓነ ጸጋ ነገሥት ባሕታውያን*
*ለቀሲስ እንብዕ አልበስዎ ልብሰ ንጉሥ ፤*
*አምጣነ ይመስጥ ልበ ድምፀ ሰቆቃው ቀሲስ ፤*
*ወይሰጥቅ ጠፈረ አሐቲ ዐይኖሙ ተስላስ*
*ወቀደሰ እንዘ ይብል*
*አምላከ ነዳያን ረኀብ ተዐቁረ ውስተ ከርሥ ።*
*ተሰምየትሂ ወተብህለት ምዕራገ ዘመሥዋዕት ጢስ*
*እንተ እብን ማዕጾሃ ገጸ ባሕታዊ ቤተ መቅደስ ፤*
*ወአመ በቀትር ተንሥአ ጾመ ኢየሱስ ነፋስ*
*አንቀልቀለ ሥረዊሃ ለግዘፈ ሥጋ ዕፀ በለስ ።*

## ትርጉም

ፀጋን የተሞሉ ነገስታት/ባህታውያን
ቄስ/እንባን የንጉስ ልብስን አለበሱት ፤
የቄስ/እንባ ድምፅ ልብን ይመስጣልና ፤
የአንድ አይናቸው/አዳራሽ ጣራንም ይሰነጥቃልና
የችግሮች አምላክ/
ራብም በሆድ ውስጥ ተፀነሰ እያለ ቀድሷልና ።
መዝጊያዋ ድንጋይ የሆነ የባህታዊ ፊት/ቤተ መቅደስም
የመስዋእት ጢስ ማሳረጊያን በፍፁም ተባለች ፤
ነፋስ/የኢየሱስ ፆምም በቀትር በተነሳ ጊዜ
የስጋ ውፍረት/የበለስ እንጨት ስር ተናወጠ ።

## ምስጢር

ጥንታውያን የኢትዮጵያ ነገስታት ድምፀ መልካም ቄስ ሲያገኙ ይሾሙትና ይሸልሙት እንደነበር ባህታውያንም በፆም ጊዜ ከመብልና ከመጠጥ

www.ethiopianorthodox.org

ተከልክለው ሃጢአታቸውን እያስታወሱ በማልቀስ እንደ ንጉስ ልብስ የነጣ እንባን አነቡ ።
በቀትር ጊዜ የተነሳ እውሎ ነፋስ ዛፉን ሁሉ ከስሩ እንደሚያናውጠውና እየነቃቀለ እንደሚጥለው በኢየሱስም ፆም ወቅት(በኩዳዬ) የወፈረው ሁሉ ከሳ ይላሉ ባለቅኔው ።

*132 መወድስ(1443)አ*

*ማኅሌተ ኀዘን አኀሊ ለተፈጥሮትየ ፡*
*እስመ ለለዕለት ይበውእ ውስተ ቤተ ሁከት መቅደስ*
*ሊቀ ካህናት ሥጋየ ጽዑነ ንዴት ፈረስ ፡*
*ወእምነ አዚብ ርእስየ*
*ለእመ ተንሥአ ደዌየ ነፋስ*
*እስመ ለተሐውሶ ኢየዐርፍ*
*ዘበጽንፈ ባሕር በቈለ ልብየ ብርዐ ባሕሩስ ።*
*ኢያዕረፍኩሂ ለአስቈቅዎ እስከ ይእዜ እም ንእስ*
*አድያመ ዮርዳኖስ እስከ ፆደ አንብዐ ዚአየ ዮሐንስ ፡*
*እስመ ዘባቲ ነበርኩ ዓለመ ተስናን ወባእስ*
*አኮ ዓለመ ሥጋ ወአኮ ዓለመ ነፍስ ።*

## ትርጉም

ለመፈጠሬ የሃዘን ማህሌትን እዘምራለሁ ፤
ችግር/ ፈረስን የጫነ የካህናት አለቃ/ስጋዬ
በእውከት መቅደስ ውስጥ እየቀኑ ይገባልና ፤
ከአዜብ/ራሴም
በሽታዬ/ነፋስ ቢነሳ
በባህር ዳር የበቀለ
ልቤ/የመቃ ብርእ ለመወዛወዝ አያርፍምና ።

እንባዬ/ዮሃንስ የዮርዳኖስን አቀልቋይ እስከ ዞረ ድረስ
ከልጅነት ጀምሮም እስካሁን ለማልቀስ አላረፍሁም ፤
የኖርሁባት የፍፁም ጠብ አለም ፤
የስጋ አለም አይደለችምና ፤ የነፍስንም አለም አይደለችምና ።



## ምስጢር

ካህን መዝሙርን እንደሚዘምር ባለቅኔው በመፈጠራቸው አዘንን አበዙ ፤ ሰሞነኛ(ተረኛ)ሊቀ ካህናት በየቀኑ ወደ ቤተ መቅደስ እንደሚገባ የባለቅኔውም ሰውነት በየቀኑ ይታወካል ። ከአዜብ በተነሳ ነፋስም የባህር ዳር መቃ ብርእ(የመቃ እንጨት) እንደሚወዛወዝ የባለቅኔው ልብም በራስ ምታት እንደውሃ ይፈስሳል ።
መጥምቁ ዮሃንስም የዮርዳኖስን ዙሪያ እንደዞረ የባለቅኔው እንባ እንደ ዮርዳኖስ ውሃ ከልጅነት እስከ እውቀት ያለማቋረጥ ወረደ ። ምክንያቱም አለማቸው የስጋም ፤ የነፍስም አለም ሳትሆን ከሁለቱም የወጣች ስለሆነች ነው በማለት የሀማምና የችግር እሮሮ በቅኔው ምስጢር ተገልጦበታል ።

*133 መወድስ ስ*

*ዞሉ ይመውት በዘኢሀለዮ ።*
*ጦማረ ዝኒ ንጽሕፍ በሰሌዳሁ ለሳዊሮስ ፡*
*እስመ እንዘ ይሔሊ ፈርዖን ሞተ እስራኤል አልባስ*
*በጽሐ በርእሱ ፍትሐ ሞት ሐዲስ ፡*
*ወያዕቆብ እንዘ ሀሎ*
*ተቀትለ ኤሳው ሞተ ዚአሁ ዘየነሥሥ ።*
*ጠቢባንሂ ከመ ይምትሩ ሥርወ ምሳሌ በለስ*
*ሐማ እስመ ተሰቅለ እንዘበ መርዶክዮስ ፡*
*ወእንዘ ሀሎ ሕያወ ድልወ መጥባሕት ክርስቶስ*
*ኅልቀተ ሕፃናት አስተዳለወ ልሳነ መጥባሕት አሚስያስ ።*

## ትርጉም

ሁሉ ባላሰበው ይሞታል ።
የዚህንም ፅሁፈት በሳዊሮስ ሰሌዳ እንፅፋለን ፡
ፈርኦን የወገኖች እስራኤልን ሞት ሲያስብ
አዲስ የሞት ፍርድ በራሱ ደርሷልና ፡
ያእቆብም ሳለ



www.ethiopianorthodox.org

የርሱን ሞት የሚሻ ኤሳው ተገድሏልና ።
ጥበበኞችም የምሳሌ/በለስ ስርን ይቆርጡ ዘንድ
መርዶክዮስ ሳለ ሃማ ተሰቅሏልና ፤
ለሰይፍ የተዘጋጀ ክርስቶስም ሳለ
የሰይፍ ስለት/አሜስያስ የህፃናት እልቂትን አዘጋጅቷልና ።

## ምስጢር

" ቆቅ ወዲያ ቅዝምዝምወዲህ" እንዲሉ የእያንዳንዱ ሰው አሳብ በታሰበበት ቀርቶ ባልታሰበበት ሲፈፀም ይገኛል ። ይህም ይታወቅ ዘንድ የግብፅ ንጉስ የነበረው ፈርኦን እስራኤልን ለመያዝ ሲገሰግስ እርሱ ራሱ በኤርትራ ባህር ውስጥ ቀልጦ ቀረ ። ታናሽ ወንድሙ ያእቆብንም ሊገድለው የሚሻ ኤሳው በሞት ቀዳሚ ሆነ ።

የበለስም ስር እንደሚቆረጥ የምሳሌውን እውነትነትም የቅኔ ሙያ አፍቃሪዎች እንዲረዱ እስራኤላዊ መርዶክዮስን ለማሰቀል መስቀያን ያዘጋጀ ሃማ ባዘጋጀው መስቀያ ተሰቅሎ ሞተ ። የገሊላ ንጉስ ሄሮድስም ለክርስቶስ ያሰበው በሰይፍ መገደል ለገሊላ ህፃናት ሆነ በማለት ባለቅኔው ያስረዳሉ ።

ታሪኩ በአንደኛው መፅሃፍ በገፅ 190እና 337 ተተርኳል ።

*134 መወድስ(229) ጎ*

*ዘናትናኤል*

*ቀሊል ውእቱ ዕፀበ ገዳም*
*ቅድመ ማፍዐ ዝንቱ ዓለም አርአያ ጽላሎት ወጢስ ፤*
*ወነዖ ይእቲ ባዕልተ ጥዒና ሐዳስ*
*ምስለ አራዊት ዘተነድር ነፍስ*
*እንዘ እምነ ሰብእ ትትገነሥ*
*እስመ ግዕዘ አርዌ ዐቢይ ወግዕዘ ሰብእ ንኡስ ።*
*በመብልዕሰ ነበ እከይ ዘያበጽሖ ለከርሥ*
*ጸላዔ ማርያም ወላዲትከ ምስለ ደቂቀ ኤዶም ይትባዐስ ፤*
*ወዘከህደ ኪያከ ይብል ንጉሡ አርያም ክርስቶስ*
*ምንተ እበልዕ ወምንተ እለብስ ።*



## ትርጉም

የጥላና የጢስ አምሳል በሆነ
በዚህ አለም ግፍ ፊት የዱር ጭንቅ ቀላል ነው ፤
ከሰው ተገልላ ከአራዊት ጋር
የምትኖር ነፍስም ባለአዲስ ጤና ናት ፤
የአውሬ ጠባይ(ባህርይ)
ታላቅ ነውና የሰውም ጠባይ ታናሽ ነውና ።
ሆድን ወደክፋት በሚያደርሰው መብል ግን
የእናትህ ማርያም ጠላት ከገነት ልጆችም ጋር ይጣላል ፤
የአርያም ንጉስ ክርስቶስ ! አንተንም የካደ
ምን እበላለሁ ፤ ምንስ እለብሳለሁ ይላል ።

## ምስጢር

ሁለት ነገሮች በግራና በቀኝ ሲመዘኑ ቀላሉን ከባዱ በክብደት እንደሚያመዝነው የዚህን አለም ግፍና የጫካን ጭንቅ (በጫካ ውስጥ በብቸኝነት የመኖርን ጭንቀት) ሲያመዛዝኑት የጫካ ጭንቅ ሳይሻል አይቀርም ። ከሰው ጋር ከመኖርም ከአራዊት ጋር መኖር ይሻላል ። ምክንያቱም ለፈጣሪው ለተገዛ ባህታዊ አራዊት ስለሚገዙለትና የአለም ሰው ለፈጣሪው ስለማይገዛ ነው ይላሉ ባለቅኔው ።

በመወለድ የቀደመ የበኩር ልጅ ከታናናሽ ወንድሞቹና እህቶቹ በእድሜ እንደሚበልጥ ከሰው ጠባይ የአራዊት ጠባይ ይሻላል ። አራዊት ለእነዳንኤል ተገዝተዋል ። ቅድስት ማርያምን የሚጠሉ ክፉዎች ሰዎች ግን ለገነት የታደሙ ፃድቃን ሰዎችን ያሰቃያሉ ። ህፃናት አባታቸው ታቅፎ ሲያጎርሳቸው የአባታቸውን ፍቅር ይረዳሉ ። ኢየሱስ ክርስቶስም ደቀ መዛሙርቱን "ፈልጉ ታገኛላችሁ" በማለት የስራን አስፈላጊነት ማስተማሩን ያላመኑ ሰነፎች በከንቱ አሳብ ብቻ ይዋኛሉ ይላሉ ባለቅ ኔው።

*135 መወድስ (240)ጎ*

*ፍኖተ አባግዕ ይመስል ፍኖተ መከራ ፤*
*እስመ እንዘ ያስቆቁ ኢዮብ በኀልቀተ ውሉድ አልባስ*
*ደዌ ጽኑዕ በዐለ ፈረሰ*



www.ethiopianorthodox.org

*በእግር ተለዎ ለኢዮብ ንጉሥ*
*እስከ አስተርአዮ በዮርዳኖስ*
*አቡሁ አካል እንተ አልሐቀ እምንእስ ።*
*ያዕቆብሂ እንዘ ያስቆቁ በሕፀፀ ዮሴፍ ከርሥ*
*ጸምዐ አዕይንተ ከመ ጸምዐ ጤሜዎስ ፤*
*ወእንዘ ዳዊት ያስቆቁ በተፈልጦ አምኖን ነፍስ*
*ለዳዊት አደንገፆ ርኅቀተ አቤሴሎም አድማስ ።*

## ትርጉም

የመከራ መንገድ የበጎች መንገድን ይመስላል ፤
ኢዮብ በልጆች/ልብሶች ማለቅ ሲያለቅስ
ባለፈረስ/ብርቱ ህመም
ኢዮብ/ንጉስን በእግር ተከታትሎታልና ፤
ከልጅነት ጀምሮ
ያሳደገው አካል/አባቱ በዮርዳኖስ እስከ ታየው ድረስ ።
ያእቆብም በዮሴፍ/ሆድ መጉደል ሲያለቅስ
ጤሜዎስ እንደተጠማ አይኖችን ተጠማ ፤
ዳዊትም በአምኖን/ነፍስ መለየት ሲያለቅስ
የአቤሴሎም/አድማስ ርቀት ዳዊትን አስደነገጠው ።

## ምስጢር

ባለቅኔው "የመከራ መንገድ የበጎችን መንገድ ይመስላል" በማለት በበጎች ተከታትሎና ተጠጋግቶ መሄድ የመከራን ተደራርቦ መምጣት ያስረዳሉ ። ልብሶች እንደሚያልቁ የኢዮብ ልጆቹ ሞቱበት ፣ ፈረስኛ ወራሪ በድንገት እንደሚደርስ የኢዮብ አካል በዮርዳኖስ ጥምቀት እስኪድን ድረስ በቁስል በሽታ ተሰቃየ ።

ውሃ የጠማውና የራበው ልጅ እንደሚያለቅስ ያእቆብም በዮሴፍ መታጣት ምክንያት ሲያለቅስ አይኖቹ እንደጤሜዎስ አይኖች ጠፉ በሞት ጊዜ ነፍስ ከስጋ እንደምትለይ ዳዊት ልጁ አምኖንን አጣ ። የምድርም ዳርቻ በቅርብ እንደማይገኝ ሁለተኛው ልጁ አቤሴሎምን ባለማግኘቱ የዳዊትም ድንጋጤ እፅፍ ድርብ ሆነ ይላሉ ባለቅኔው ።



*136 መወድስ(1417)አ*
*ዘተክሌ (መምህር ፡ ዘዋሸራ)*
*ተክለ ሃይማኖት ተክለ ለአስተጻንዖ*
*ዐጽቀ ደብረ ማርቆስ ዘይት በሥርወ ጽዮን ሐዳስ ፡*
*ወከመ ኢይሁክ ዘንተ ኃይለ ጸላኢ ነፋስ*
*አኮ ጊዜሁ ለኃያል በለስ ፡*
*እስመ በክብሩ ዘይኄይስ*
*ደብረ ማርቆስ ኮከብ እምከዋክብተ ኀይል ወየብስ ።*
*በተምኔትሂ እምድኅረ ኀልቀ ነገረ ጳውሎስ ልብስ*
*ለደብረ ማርቆስ እግረ ደብር ተውህቦ ከዊነ ርእስ ፡*
*እስመ በይነ ዝንቱ ዘይብል ተክለ ሃይማኖት ንጉሥ*
*እም ግብጽ ጸዋዕክዎ ለወልድየ ማርቆስ ።*

## ትርጉም

ተክለ ሃይማኖት የማርቆስ ደብር/
ዘይት ጫፍን ለማፅናት (ለማጠንከር) በአዲስ የፅዮን ስር ተከለ ፡
ይህንንም የጠላት/ነፋስ ሃይል እንዳያውክ
የሃይለኛ/በለስ ጊዜው አይደለም ፡
የማርቆስ ደብር/ኮከብ
ከባህርና ከደረቅ ኮከቦች በክብሩ የሚሻል ነውና ።
በምኞትም የጳውሎስ ነገር/ልብስ ካለቀ በሁዋላ
ለማርቆስ ደብር/የደብር እግር ራስን መሆን ተሰጠው ፡
ስለዚህ ንጉስ ተክለ ሃይማኖት
ልጄ/ማርቆስን ከግብፅ ጠራሁት የሚል ነውና ።

## ምስጢር

አትክልተኛው ዘይቱንና ወይራውን አጣምሮ እንደሚያዳቅላቸው ንጉስ ተክለ ሃይማኖት የደሃራዊውን (በሁዋላ የተተከለውን) የደብረ ማርቆስን ቤተ ክርስቲያን ህንፃ ከቀዳማዊት የአክሱም ፅዮን ቤተ ክርስቲያን ህንፃ እኩል አደረጉት ። ጠንካራ መሰረት ያለውን ህንፃም ነፋስ እንደማያናውጠው ንጉስ ያላቁትን ደብረ ማርቆስን ምቀኛ ሊቃወ



www.ethiopianorthodox.org

መው አይችልም ። በለስ ያለጊዜው እንደማያፈራ ምቀኛም ቢመቀኝ ከንጉስ ጋር መከራከር አይደፍርም ። ደግሞ ኮከብ ከኮከብ በክብር (በብርሃን) እንደሚበልጥ ከሌሎቹ አውራጃዎች የንጉስ ተክለ ሃይማኖት መዲና ደብረ ማርቆስ ይልቃል ።

ልብስ ሲያረጅ እንደሚያልቅ ቅዱስ ጳውሎስ "እግር ራስ አይሆንም" በማለት የተናገረው ነገር በደብረ ማርቆስ አልተፈፀመም ። ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ደብረ ፀሃይ የተባለው የደብረ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን በትክል ሁዋለኛ ሲሆን ከጎጃም አድባራት በላይ ሆነ ። ወደግብፅ የተሰደደው ክርስቶስ ወደናዝሬት እንደሚመለስ ነቢዩ ኢሳይያስ እንደተነባ ንጉስ ተክለ ሃይማኖትም ከግብፅ የመጣውን የቅዱስ ማርቆስን ዕላት በደብረ ማርቆስ ከተማቸው ባሰሩት አስደናቂ ቤተ ክርስቲያን አስገቡት በማለት ባለቅኔው አመስጥረዋል ።

*137 መወድስ (1396)አ*

*ጎለ እንስሳ ትትሜካህ ላዕለ ቀራንዮ ፤*
*እስመ በውስቴታ ተረክበ ለሆሣዕና ክርስቶስ*
*ትርሚተ ነዳይ ወርቅ ወቈጽለ በለስ*
*አመ ተሐደሰ መንግሥቱ ተጽናስ ፤*
*እምዡሉስ ትኄይስ*
*ዘከደነቶ ጽልመተ ፀሐይ ንግሥተ የብስ ።*
*ወርኀኒ ዘይውኅዛ ደመ ከዊነ ደም ሐዲስ*
*ለሆሣዕና ጊዜ ሕማሙ ምንተ ትገሥሥ ?*
*ዘፈረ ልብሱ ኢትልክፍ ለረኪበ ፈውስ*
*ለሆሣዕና በቀራንዮ እስመ ኢሀለዎ ዘፈረ ልብስ ።*

## ትርጉም

የእንስሳ በረት በቀራንዮ ላይ ትመካለች ፤
ችግር/መንግስቱ በታደሰ ጊዜ ሆሳእና
ለተባለ ክርስቶስ የድሃ ሽልማት የሆነ
ወርቅ ከበለስ ቅጠል ጋር ተገኝቷልና ፤
ጨለማን ያለበሰችው
የምድር ንግስት/ፀሃይ ግን ከሁሉ ትበልጣለች ።
አዲስ ደምን የመሆን ደም የሚፈሳት ጨረቃም
በሆሳእና ህማም ጊዜ ምንን ትዳስሳለች ?
መዳንን ለማግኘት የልብሱን ጫፍ እንዳትነካ
ለሆሳእና የልብስ ዘርፍ በቀራንዮ የለውምና ።

## ምስጢር

አዲስ ልብስ ያለው ትምክህተኛ ልጅ አዲስ ልብስ በሌለው ልጅ እንደሚመካበት ክርስቶስ በተወለደበት ቦታ በጨርቅና በበለሶን ቅጠል ተጠቀለለ ። በተሰቀለባት በቀራንዮ ግን ራቁቱን ሆነ ። በልዩ ልዩ ጌጥ ከምታጌጥ አንዲት ሴት ሌላ ከእርሷ የምትበልጥ ጌጠኛ እንደምትኖር ፀሃይም ጨለማ የክርስቶስን ራቁትነት በመሰወሯ ትደነቃለች ። "ጨረቃም ምንን ትዳስሳለች ?" በማለት ክርስቶስ በተሰቀለ ጊዜ ጨረቃ ደም መሆኗንና ክርስቶስም ራቁቱን መሰቀሉን ባለቅኔው ያስረዳሉ ።

*138 መወድስ (247)ኀ*
*ዘካሣ (ቈስገበዝ ፡ ዘጎንጅ)*
*ተመነይኩ እስማዕ ዜና ምዝባሪሃ*
*ለእንተ ሐነፅክዋ አነ ጥበበ ሢራክ መቅደስ*
*ዘባቲ እሄሉ ዘእንበለ ምግብ ወልብስ ፡*
*አምጣነ ንጹሕ ተአኀዘተኒ ፡*
*ወአምሰጠተኒ ብዕለ ወርቅ ነፋስ*
*እንዘ ልቡናየ ትገይሥ*
*በመንፈቀ ሌሊት ኀቤሁ ለምሥራቃዊ ቴዎድሮስ ።*
*ኮነኒ ብዕለ ዚአየ ብዕለ አልዓዛር ተጽናስ*
*ከመ እዝራዕ ተዋርዶ እንዘ ልብሰ አሐርስ ፡*
*ባሕቱ መነንኩ አነ ቃለ ሰሎሞን ንጉሥ*
*ዘይቤ እምነ ዙሉ ጥበብ ትኄይስ ።*

## ትርጉም

ያለምግብና ያለልብስ የምኖርባት
እኔ የሰራሁዋት የሲራክ ጥበብ መቅደስ



www.ethiopianorthodox.org

የመፍረስ ዜናን ልሰማ ተመኜሁ ፡
በሌሊት አጋማሽ
ልቤ ወደምስራቅ ሰው ቴዎድሮስ ስትገሰግስ
ችግር ተይዛኛለችና ፡
የወርቅ ብልፅግና/ነፋስም አምልጣኛለችና ።
በችግር እያረስሁ መዋረድን እዘራ ዘንድ
የአልአዛር ብልፅግና/ችግርም የእኔ ብልፅግናን ሆነ ፡
ነገር ግን እኔ "ከሁሉ ጥበብ ትበልጣለች"
የሚለውን የሰሎሞንን ቃል ናቅሁ ።

## ምስጢር

አንድ ሰው አዲስ ቤት ይሰራና በዚያ ቤት ውስጥ መኖር ገና ሲጀምር እርሱም ፡ ቤተሰቡም ጤና ያጣል ። ከዚህም የተነሳ ቤቱን አፍርሶ ወደሌላ ቦታ አዛውሮ ለመስራት ይመኛል ። የቅኔው ባለቤት የመፃህፍት ትርጓሜና የቅኔ ሊቅነታቸው በቂ የእለት ጉርስ ፡ የአመት ልብስ ሊያስገኝላቸው ባለመቻሉ የተማሩትን ትምህርት ጥፋት ተመኝተዋል ።

አንድ ገበሬ የተወሰነ መሬት ደጋግሞ በማረስና በማለስለስ ከእርሻው ከሚያገኘው ምርት የእለት ጉርሱን የአመት ልብሱን እንደሚያገኝ ሊቁም አላቂ ልብሳቸውን ደጋግመው በመደረት ስለሚኖሩ "ከሁሉ ጥበብ ትበልጣለች" በማለት ሰሎሞን የፃፈውን ቃል የማይቀበሉት መሆኑን በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል ።

## ታሪክ

ምስራቃዊ ቴዎድሮስ በአንፆኪያ ከተማ የተወለደና የተጋደለ ሰማእት ነው ። አባቱ ዮሃንስ ከላይኛው ግብፅ ወደ አንፆኪያ ሄዶ የሚኖር ክርስቲያን ነበር ። እናቱ ከአንፆኪያ ቤተ መንግስት ዘር የተወለደች ጣኦት አምላኪ ነበረች ።

ቴዎድሮስ ለትምህርት ሲደርስ እናቱ ወደጣኦት መምህራን ትምህርት ቤት ሄዶ እንዲማር ባሏ ዮሃንስን ጠየቀችው ። ዮሃንስም ልጄ ከጣኦት ትምህርት ቤት አይገባም ብሎ ስለተቃወማት ከአንፆኪያ አባረረችው ። ይሁን እንጂ ቴዎድሮስ ካደገ በሁዋላ የአባቱን ሃይማኖት (ክርስትናን) ከአንፆኪያው ጳጳስ ተምሮ ተጠመቀ ። ከዚህ በሁዋላ የሮማው ንጉሰ ነገሥት የዲዮቅልጥያኖስ የጦር ሰራዊት አለቃ ሆኖ ተሾመ ። ዲዮቅልጥያኖስ በጀግንነቱና በብልሃቱ ቴዎድሮስን ቢጣም ይወደው ነበር። ዲዮቅልጥያኖስ ከክርስትና እምነት ወደአምልኮተ ጣኦት በተመለሰ ጊዜ ግን ቴዎድሮስ ዲዮቅልጥያኖስን ነቀፈው ። በዚህም ምክንያት ቴዎድሮስ በዲዮቅልጥያኖስ ትእዛዝ በልዩ ልዩ ስቃይ ከተሰቃየ በሁዋላ በ304 አካባቢ አንገቱን በሰይፍ ተቆርጦ በሰማእትነት አረፈ (ስንክ· ሃምሌ 20) ።

*139. ዕዝል ክብር ይእቲ (1471)አ*
*ዘዮሐንስ ማምሻ (አጋፋሪ ፡ ዘመናገሻ ማርቆስ)*
*ፈትለ ዕለተ ዐርብ ሔዋን በቀራንዮ ዘሠርክ ዕለትልብስ ፡*
*እስመ ልብሰ ሌሊት ኮነ ዘፈተለቶ በለስ ፤*
*ወበዘፈቀደ ለብሰ ወልደ ባሕርየ አብ ክርስቶስ ፡*
*እንዘ መንፈቁ ብሉይ ልብሰ ወልድ እስመ መንፈቁ ሐዲስ ።*

## ትርጉም

የሄዋን/አርብ ቀን/ፈትል በቀራንዮ የሰርክ ቀን ልብስ ነው ፡
በለስ የፈተለችው የሌሊት ልብስ ሆኗልና ፡
የአብ የባህርይ ልጅ ክርስቶስም በዘፈቀደ ለበሰ ፡
የወልድ ልብስ እኩሌታው አሮጌ ሲሆን እኩሌታው አዲስ ነውና ።

## ምስጢር

አንዱ ልብስ የሰርክ (የዘወትር) ልብስ ሲሆን ሌላው የክት ልብስ ይሆናል ። የሌሊት ልብሱም ከሰርክና ከክት ልብሶች የተለየ ነው ። ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት የአርብ ቀን ብርሃንም በሰርክ ጊዜ (በአመሻሽ) በራ ። በለስን መብላትም በአዳምና በሄዋን ፡ በዘራቸውም ሁሉ በጨለማ ቦታ መውደቅን አመጣ ። በአንዳንዱ ሰው የበዘፈቀደ አለባበስም አሮጌ ልብስና አዲስ ልብስ ተቀላቅለው እንደሚታዩ የብሉይ ኪዳንና የሃዲስ ኪዳን ሀግጋትን የሰራ እግዚአብሄር ወልድም እንደወደደ ያደርጋል ይላሉ ባለቅኔው ።



www.ethiopianorthodox.org

*140 ዕዝል ዕጣነ ሞገር (1480)አ*
*ዘገብረ ሥላሴ (መምህር ፡ ዘኤልያስ)*

*ሀገረ ሰሎሞን ሖረት ንግሥተ አዜብ መቅደስ*

*እምነ ጉንደ ዕፀ ሕይወተ ከመ ትኅሥሥ ፡*
*እኅታሰ ቤተ እሙ ለሰማያዊ ንጉሥ*
*ለንሚሠ ዕፀ ኢትገይሥ*
*እንዘ እብን ውእቱ ክዳና ወመርዓዊሃ ክርስቶስ*
*ወተሐውር እምኪደተ ደብር ላዕለ እብን ፈረስ ።*

## አሠረ ንጉሥ

እመ ኢነላፊ ውእቱ መሥዋዕቱ ለቴስብያዊ ቀሲስ
እምኢሐነጸ በእብን መቅደሶ ንጉሠ ለባዊት ነፍስ
አምጣነ ውእቱ ኤልያስ
በእሳት ያውዒ እብነ አድማስ
ወውእቱ እሳተ ልቡስ

## ትርጉም

የአዜብ ንግስት/መቅደስ ከእንጨት ግንድ
ህይወትን ትሻ ዘንድ ወደሰሎሞን አገር ሄደች ።
የሰማይ ንጉስ የእናቱ ቤት/እህቷ ግን
ልብሷ ድንጋይ ሲሆንና
ሙሽራዋም ክርስቶስ ሲሆን እንጨትን ለመሻት አትገሰግስም ፤
ጭቃንም ከመርገጥ በድንጋይ/ፈረስ ላይ ትሄዳለች ።

## አሰረ ንጉስ

የቴስብያ ኤልያስ/ቄስ መስዋእት የማያልፍ ቢሆን
የልበኛ ነፍስ ንጉስ (ክርስቶስ) መቅደሱን በድንጋይ ባልሰራ ነበር ፤

እርሱ ኤልያስ
የአድማስን ድንጋይ በእሳት ያቃጥላልና ፤
እሳትንም የለበሰ ነውና ።



## ምስጢር

የአዜብ (የኢትዮጵያ) ንግስት ማክዳ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ወደ ኢየሩሳሌም በሄደች ጊዜ ሰሎሞን ቤተ መቅደስን ሲሰራ መቃን እንዳይሆን በማጠሩ፣ መድረክም እንዳይሆን በመርዘሙ ምክንያት ከቤተ መቅደስ ስራ የተረፈው እንጨት ሲያነቅፋት ከእግሯ በሽታ እንደዳነች ክርስቶስ የሰራት ቤተ መቅደስም በእንጨትና በሳር ከመሰራት ነፃ ሆነች። የማክዳ እህት ህንደኬ ግን ከእንጨት መዳንን ለመሻት ወደሰሎሞን አገር ወደኢየሩሳሌም እንዳልሄደች የክርስቶስ እናት የቅድስት ማርያም ቤተ መቅደስም በእንጨት አልተሰራችም ፤ ባጧም ፣ ግድግዳዋም ድንጋይ ሆነ እንጂ ይላሉ ባለቅኔው ። ቤት ሙሽራም ከወንድ ሙሽራ ጋር በጋብቻ አንድ እንደምትሆን የቅድስት ማርያም ቤተ መቅደስ በክርስቶስ ፀናች ። ሴት ወይዘሮም ጭቃ እንዳይነካት በፈረስ እንደምትሄድ የዚች ቤተ መቅደስ ስራም ያለጭቃ በድንጋይ ብቻ ተሟላ ።

ኤልያስ የሰዋው መስዋእት በክርስቶስ ጊዜ ቢኖር ክርስቶስ የሰራትን የድንጋይ መቅደስ ኤልያስ መስዋእቱን እንዲበላለት አወረደው የሚባለው እሳት ያቃጥላት ነበር ። የነቢዩ መስዋእት አላፊ በመሆኑ እሳቱም በእርሷ ምክንያት ባለመምጣቱ የማርያም ቤተ መቅደስ ልትሰራና ልትፀና ቻለች በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

*141 ዕዝል ጉባኤ ቃና (1483)አ*

*ቃለ ዐዋዲ አርሰየ ኀበ ክንፈ መልአክ መርሶ*
*ዘየሀውኮ ነፋስ ተመትሮ ሐመረ ተግሣጽ ርእሶ ።*

## ትርጉም

ዮሃንስ/መርከበኛ ነፋስ/መቆረጥ የሚያውከው
የተግሳፅ መርከብ/ራሱን በመልአክ ክንፍ/ወደብ ዘንድ አሳረፈ ።

## ምስጢር

መርከበኛ ነፋስ የሚያንጓልለውን መርከብ በወደብ ያሳርፋል ። መጥምቁ ዮሃንስም መቆረጥ ከአንገቱ በታች ካለ አካሉ የለየው ራሱን በመልአክ ክንፍ ወደአየር አወጣ በማለት ባለቅኔው በመጥምቁ ዮሃንስ ተፈፀመ የሚባለውን ተአምር በቅኔያቸው ምስጢር አስረድተዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

*142 ዘአምላኪየ(1484)አ*

*ለዘለዘ ለሞት ሰሎሞን ወልደ ቤርሳቤሕ አንገሦ*
*ዳዊት ይሁዳ መአብስ ጌሶ*
*ናታን ዕፀ ተግሣጸ ልቡና ሐንክሶ ።*

## ትርጉም

የቤርሳቤህ ልጅ የሆነ ሰሎሞን/ሞትን ያነገሰው
በዳይ ዳዊት/ይሁዳን አነቀፈው
ለናታን እንጨት የልብ ተግሳፅ/እንክስና ይገባል አለው ።

## ምስጢር

ሰሎሞንን አባቱ ዳዊት እንዳነገሰው በኢየሱስ ክርስቶስ የተፈፀመ የስቅላት ሞትን ይሁዳ አመጣው ። ነቢዩ ናታን ዳዊትን እንደነቀፈው እንጨት በሰው አንደበት ይሁዳ ራሱን ሊሰቅልበት ያዘጋጀው (እንደ ሰው) ተናገረ ይላሉ ባለቅኔው ። ናታንም ከብሉይ ኪዳን ህግጋት ውጭ የሆኑ ሰዎችን እንደሚገስፅ ይሁዳ የተሰቀለበት እንጨትም ወደአንድ ወገን ማዘንበል ታየበት በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

ታሪኩ በአንደኛው መፅሃፍ በገፅ 42 እና 142 ተተርኳል ።

*143 ግእዝ ጉባኤ ቃና/ስ*

*ኒቆዲሞስ ላሕም ዘበውስተ ምኩራብ ተአሰረ*
*መንጠላዕተ ብሉይ ምሖራበ እንዘ ይበልዕ ኀደረ ።*

## ትርጉም

በምኩራብ ውስጥ የታሰረ ኒቆዲሞስ/በሬ
የብሉይ ኪዳን/የቤት መጋረጃን ሲበላ አደረ ።

## ምስጢር

የተራበ በሬ በታሰረበት ቦታ አጠገብ የተሰቀለ ጨርቅን ሲበላ ያድራል ። ኒቆዲሞስም የብሉይን ምኩራብ ስርአት (የኦሪት ቤተ መቅደስን ህግና ስርአት) በአዲስ ኪዳን ህግ ለወጠ በማለት ባለቅኔው የኦሪት ህግ አለቅነቱን ትቶ ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት ማመኑን ገልጠዋል (ዮሃ· 3 ፥ 7 ፥ 45–52 ፥ 19 ፥ 39) ።



*144 ዋዜማ(1036)ኀ*

*በምንት ነዐድዎ?*
*ለባሕረ ልቡና ኀዘን እንተ ያሰጥም አእጋረ*
*ሐመር ሀብተ ካህናት አኮኑ ተሰብረ ፣*
*ወበምንት ንሬኢ? ገጸ መጻሕፍት ምሥጢረ*
*መጽሔተ አእምሮ ጎንደር እስመ ተመዝበረ*
*ወመሰለ ግብጻዌ ብሔረ ።*

## ትርጉም

እግሮችን የሚያሰጥም
የልብ ባህር/አዘንን በምን እንሻገረዋለን?
የካህናት ሃብት/መርከብ ተሰብሯልና ፣
የመፃህፍት ፊት/ምስጢርንስ በምን እናያለን?
የአእምሮ መስታወት/ጎንደር ተመዝብሯልና
የግብፅ አገርንም መስሏልና ።

## ምስጢር

በአገልግሎቱ ብቸኛ የሆነው መርከብ ከተሰበረ በሁዋላ እንደገና ተጠግኖ ስራ እስኪጀምር ድረስ ባህርን መሻገር አይቻልም ። በጎንደር መንግስት የገነነው የካህናት ሀብት (ክብር)ም በደርቡሽ ወረራ ስለጠፋ የባህር ምሳሌ የሆነው አዘን የማይገፋ ሆነ ። መስታወት ከተሰበረ ፊትን ማየት እንደማይቻል ቅዱሳት መፃህፍትን በትርጓሜ ማመስጠርና ማብራራት የመፃህፍት አንድምታ ትርጓሜ የተስፋፋበት ጎንደር ከጠፋ ይጠፋል በማለት ባለቅኔው የደርቡሽ ጦር ያደረሰው ጥፋት በጊዜው ብቻ ተወስኖ የማይቀር መሆኑን በቅኔያቸው ምስጢር አስረድተዋል ።

## ታሪክ

አፄ ዮሃንስ አራተኛ መተማ ላይ ከደርቡሾች ጋር ሲዋጉ በ1881 ዓ/ም ሞቱ ። ደርቡሽ ጎንደር ከተማ ገብቶ የቻለውን ያህል ዘርፎ ሲወስድ የቀረውን የኢትዮጵያ ቅርስና ንብረት አቃጥሏል ። ከሊቃውንቱም የገደለውን ገድሎ የተረፈውን ማርኮ ወደምድረ ሱዳን አውርዷል ።



www.ethiopianorthodox.org

ይህንም የሀገር ጥቃት የተመለከተ ባለቅኔ የጊዜውን ሁኔታ በቅኔው ቀርፆ አልፏል ።

*145· ዋዜማ ስ*

*ዘነቅዐ ጥበብ (አለቃ)*

*ለኪሩቤል ኢናንክሮሙ*

*እንዘ አርባዕቱ ነዮሙ ለእመ ጸሩ መንበረ ፤*

*እስመ ጾረ ማኅፀነ ሐና ሰማየ ወምድረ ፤*

*ባሕቱ ራጉኤል በይነ ኂሩቱ ፈጠረ*

*አርምሞ ለሰብእ ወለአድግ ነገረ*

*ወአርአየ ዲበ ምድር መንበረ ።*

## ትርጉም

አራት ሲሆኑ ዙፋንን

ቢሸከሙ ኪሩቤልን አናደንቃቸው ፤

የሃና ማህፀን ሰማይንና ምድርን ተሸክሚልና ፤

ነገር ግን ራጉኤል ስለቸርነቱ

ዝምታን ለሰው ፤ ለአህያም መናገርን ፈጠረ ፤

በምድርም ላይ ድንቅን አሳየ ።

## ምስጢር

ብዙ ሰዎች አንድ ሸክም የሳንሳ ቢሸከሙ ብርቱዎች ተብለው አይደነቁም ። አራቱ ኪሩቤልም የአምላክን ዙፋን ቢሸከሙ በቅድስት ማርያም እናት በሃና አንፃር አያስደንቅም ። ምክንያቱም አለምን በመሃል እጁ እንደያዘ አምላክን የፀነሰች ቅድስት ማርያምን ሃና ፀንሳለችና ። ቸር ሰው ገንዘቡን ለድሆች እንደሚያካፍል ራጉኤልም የማይናገረውን አህያን በተአምር አናገረ ፤ የሚናገረውን ሰውንም ዲዳ አደረገ በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

*146· ዋዜማ (847) አ*

*ርኁቀ መዓት አምላኪየ*

*ረኀበ ሥጋ ወጽምዕ አራዊተ ገዳም ኅቡረ*

*ዐገቱኒ በዐውደ ምንዳቤ ከመ ንህብ መዓረ ፤*



*ከርቤ ቱሱሐ ዘምስለ ሐሞት ድሙረ*

*አኮኑ ለነዳይ አፉየ አስተይዎ ወትረ ፤*

*ወፈቀዱ ያብልዕዎ ሣዕረ ።*

## ትርጉም

መአትህ የራቀ አምላኬ!

የስጋ ራብና ጥም/የዱር አውሬዎች አብረው

ንብ ማርን እንደሚከብ በችግር ዙሪያ ከበቡኝ ፤

ከሃሞት ጋር የተቀላቀለ ከርቤ ደምረው

ለችግረኛ አፌ ዘወትር አጠጥተውታልና ፤

ሳርንም ሊያበሉት ወደዋልና ።

## ምስጢር

ውሾች የከበቡት መንገደኛ የውሾችን ጌታ "አድነኝ አድነኝ" እያለ ይማፀናል ። የውሾች ምሳሌ በሆኑ በራብና በጥም ስለተጨነቁና የራቡና የጥሙ ስቃይም የማይቃለልላቸው ስለሆነ "አምላኬ! እባክህ አቃልልኝ" ብለዋል ። አይሁድ ከርቤንና አሞትን ቀላቅለው ኢየሱስን እንዳጠጡት የራቡና የጥሙ ስቃይ ብዛት ባለቅኔውን መረራቸው ። የሚበላ እህልም ሲታጣ ራብ ሳርን ለመብላት የሚያስገድድ መሆኑን ባለቅኔው በቅኔያቸው ምስጢር አስረድተዋል ።

*147 ዋዜማ ስ*

*ፈረሱ ለፈርዖን ይቤ ድኅረ ድኅረ ፤*

*እስመ እግሩ ኢለመደ ባሕረ*

## ትርጉም

የፈርኦን ፈረስ ወደሁዋላ ፤ ወደሁዋላ አለ ፤

እግሩ ባህርን አለመደምና ።

## ምስጢር

ወንዝ መሻገርን ያለመደ ፈረስ ወደሁዋላ ፤ ወደሁዋላ ይላል (ያፈገፍጋል) ። እንዲሁም የፈርኦን ፈረስም በኤርትራ ባህር ሰጥሞ ቀረ



www.ethiopianorthodox.org

ማለት በቅኔው ምስጢር ተገልጧል ። ተማሪው የህዳር ሚካኤል እለት በቤተ ክርስቲያን አጠገብ እመንገድ ዳር ተጋድሞ "ፈረሱ ለፈርያን ይቤ ድኅረ ድኅረ" እያለ የቅኔውን አራተኛ ቤት በዜማ ሲመላልስ ራስ ወልደ ገብርኤል ሰምተው "እስመ እግሩ ኢለመደ ባሕረ" አትለውምን? በማለት የመጨረሻውን ቤት ሞሉለት ይባላል ።

*148· ሥላሴ (1037)ኀ*

*ዘጾ.ጋ (አለ.ቃ)*

*መርዓት በኢ.የእምሮ*
*ሕይወታ ቀበረት ዘምስለ ሥጋ*
*በመካነ ፍትሕ ወርትዕ ገሊ.ላ ፍዳ ዮሐ'ንስ ጸዊረ*
*ታትርፍ ሀየ ወትግበር ሥዉ.ረ*
*ወበውስተ ምድር ኢ.ይርአይ ሥጋሁ ሙስና መ.ቃብር መሪረ*
*ንጉሠ ገሊ.ላ ዘተዛመረ*
*ሥጋሁ ምውተ በሥጋ ቀበረ ፤*
*ወምስሌሁ ሕገ ሰብእ ገብረ ።*

## ትርጉም

ሙሽራ ባለማወቅ
ህይወቷን ከስጋ ጋር ቀበረች
በፍርድና በቀጥታ ቦታ በገሊላ የዮሃንስ ፍዳ መሸከምን
በዚያ ታርፍ ዘንድ ፡ ትሸሽግም ዘንድ ፡
በምድርም ስጋው አሳዛኝ የመቃብርን ጥፋት እንዳያይ
የተመሳከረ የገሊላ ንጉስ
ሚች ስጋውን በስጋ ቀበረ
ከርሱም ጋር የስጠውን ህግ ሻረ ።

## ምስጢር

በአፈ ታሪክ እንደሚባለው አንዳንድ የድሮ ዘመን መኳንንትና ወይዘሮዎች ሞተው ሲቀበሩ አገልጋዮችም ከነህይወታቸው አብረው ይቀበሩ ነበር ። ስለዚህም ባለቅኔው ሙሽራ ህይወቷን ከስጋ ጋር ባለማወቅ ቀበረች በማለት መጥምቁ ዮሃንስን ስላሰቃየች ብድራት



ሄሮድያዳን ከእነህይወቷ ምድር የዋጣት መሆኑን አስረድተዋል ። ሄሮድስ የልቅናውን ያህል (ንጉስ እንደመሆኑ መጠን) ስጋው በመቃብር እንዳይበሰብስ "ስጋውን በስጋ ቀበረ" በማለት የገዛ አካሉን እየበላ ሞተ ፡ ስለዚህም እንደ ሰው የመቀበርን ልማድ አጠፋ ይላሉ ባለቅኔው ።

*149· መወድስ (893) አ*

*ለእለ አልቦሙ ሕግ ለሰብአ ትካት*
*አጥፍአሙ ማይ ወኢ.የትረፎሙ ድኅረ ፡*
*ወሀ.ቃቤ ሕግ ኖኅ ዘምስሌሆሙ ኢ.ነብረ*
*ማየ አይኅ ከመ ኢ.የጥፍአ ተንከተመ ገብረ*
*ዓዲ በሰማርያ*
*ዘይሰትይዎ ማይ እንተ ኮኖሙ መሪረ ።*
*ሕግስ ሰማ.የዊ ለእመ ሐወጾ ምድረ*
*ኮነት ማየ ባሕር ሐሊ.በ ወመዓረ ፡*
*ወበዐለ ሕግ አምላክ ለእመ ይከይድ ምድረ*
*ማየ ዮርዳኖስ እንተ ጐየ ወሐመረ ጌ.ጋይ ዘተሰብረ ።*

## ትርጉም

ለጥንት ሰዎች ህግ ባይኖራቸው

ውሃ አጠፋቸው ለሁዋላ አላስቀራቸውም ፡
ከእነርሱ ጋር ያላበረ ህግን ጠባቂ ኖህ ግን
የጥፋት ውሃ እንዳያጠፋው መርከብን ሰራ ፡
ዳግመኛም የሚጠጡት
ውሃ መራራ የሆነባቸው ሰዎች በሰማርያ ነበሩ ።
ሰማያዊ (የሰማይ) ህግ ግን ምድርን ቢጎበኝ
የባህር ውሃ ወተትንና ማርን ሆነች ፡
ባለህግ አምላክ ግን ባህርን ቢረግጥ
የባህር ውሃ የሸሸ ሆነ ፡ የበደልም መርከብ የተሰበረ ሆነ ።

## ምስጢር

አንድ አዲስ ቤት ተሰርቶ መዝጊያ ካልገባለትና አጥርም ካልታጠረለት መዝጊያና አጥርም ቢኖሩት ጠባቂ ከሌለው በውስጡ ያለው ንብረት ከሌባ አይድንም ። የተሰራላቸውን ህግ ያልጠበቁ ሰብአ ትካት (የቀድሞ



www.ethiopianorthodox.org

ሰዎች) ም በጥፋት ውሃ ሲደመሰሱ ህግ ጠባቂ ኖህ ከጥፋት ውሃ ዳነ ። የሰማርያም ሰዎች ህግን ቢጠሉና የህግን ባለቤት ቢያማርሩ የሚጠጡት ውሃ ጥምን በማርካት ፈንታ ምክነትንና ደዌን የሚፈጥር ሆነባቸው ።

ሹም ሽር ሲደረግ የላዩ ወደታች የታቹ ወደላይ እንደሚሆኑ ሰማያዊ አምላክ እግዚአብሄር ወልድም ምድራዊውን ስጋ ሲለብስ ፡ ውሃ ማጥፋቱ ቀረና ወተትንና ማርን ሆነ ። ሽፍታ ከገኘ ፊት እንደሚሸሽ የዮርዳኖስም ውሃ ስፍራውን ለቀቀ ፡ መርከብ በማእበል ሞገድ እንደሚሰበር በዮርዳኖስ ውስጥም የነበረው የአዳምና የሄዋን የእዳ ደብዳቤ በኢየሱስ ክርስቶስ እግር በተረገጠ ጊዜ ተደመሰሰ ይላሉ ባለቅኔው (ዘፍጥ· 7 ፡ 1—23 ። ዘፀአ· 15 ፡ 22—26 2ነገ· 2 ፡ 19—22 ። ማቴ· 3፡ 13) ።

*150· መወድስ (888) አ*

*ዘሮብዓም (መልአከ ፀሃይ)*

*መርጡለ ማርያም ለምንት ወሊዶትኪ*
*እምከመ ውሉደኪ እልፈ ዐይንኪ ኢነጸረ*
*ወእምከመ የዋሀ ልብኪ ሴስዮተ እሉ ኢሠምረ*
*ሀየል ጥቀ ለዘፀንሰቶ*
*ተዐውድ ሎቱ ዘቤቴል አድባረ ፤*
*መንፈቀ ሥጋሁ ድኅረ ወፈረ*
*ምስሌሃ ይሴሰይ ዘአድባረ ቤቴል ሣዕረ ።*
*ወተዐቅብ ዕጐሊሃ እንዘ ኢትኔጽር ድኅረ*
*ሰገኖ ዜማ ብካያ ኤርምያስ ዘተምህረ ፤*
*እስመ እመ ትኔጽር ባዕደ ወታስተሐይጽ ነኪረ*
*ከመ ለከንቱ ፃማ ሰገኖ መጽሐፍ ተናገረ ።*

## ትርጉም

እልፍ ልጆችሽን አይንሽ ካላየ
ገር ልብሽም እነዚህን መመገብን ካልወደደ
መርጡለ ማርያም! መውለድሽ ለምን ነው?
ዋሊያ እንኳን ለፀነሰችው
የቤቴል ተራራዎችን ትዞራለች፣
የስጋው እኩሌታ ከተሰራ በሁዋላ
የቤቴል ተራራዎች ሳርን ከርሷ ጋር አብሮ ይበላ ዘንድ።



የልቅሶዋ ድምፅን ኤርምያስ የተማረ ሰጎንም
ወደሁዋላ ሳትመለከት ገላግልቷን(ግልገሎቿን) ትጠብቃለች፤
ባእድን ብታይና ሌላንም ብተመለከት
የሰጎን ድካም ለብላሽ እንደሆነ መጽሃፍ ተናግሯልና።

## ምስጢር

እናት ወልዳ ልጆቿን ካላበላችና ካላለበሰች መውለዷ መውለድ አይባልም። በጎጃም ክፍለ ሀገር የምትገኘው መርጡለ ማርያም አገልጋዮቿ የሆኑትን ካህናት ካልጠበቀቻቸው በካህናት መገልገልዋ ለመቸ ሊሆን ነው? ዋሊያ እንኳን በአቅሟ የፀነሰችው ፅንስ ሲወለድ እኩል አካሉ ወጥቶ፣ እኩል አካሉም በማህፀኗ ውስጥ እንዳለ ምግቡን ወደሚያገኝበት ትሄድለታለች። መርጡለ ማርያምስ ከዋሊያ ታንሳለችን? ለምን ካህናትዋን አትመግባቸውም? ለምንስ ከመቅሰፍት አታድናቸውም? ይላሉ ባለቅኔው።

ሰጎን ግልገሎቿ በህይወት እንዲኖሩላት አስባ እንቁላሏን በትኩረት ትመለከተዋለች። መርጡለ ማርያምስ ካህናትዋን ለምን በእንክብካቤ አትይዛቸውም? በማለት ባለቅኔው በመርጡለ ማርያም ገዳም የኖሩ ካህናት “ የተከፉ ተደፉ ” እንዲሉ በሞት በመቀሰፋቸው የተሰማቸውን አዘን በቅኔያቸው ገልጠዋል።

## ታሪክ

የመልአከ ፀሃይ ሮብአም የትውልድ ቦታ መርጡለ ማርያም ነው። መልአከ ፀሃይ ሮብአም ተሾመው ከሚኖሩበት ከጎንደር ወደሸዋ ሲሄዱ ወደትውልድ አገራቸው ወደ መርጡለ ማርያም ደረሱ። ብደብሩ ቀድሞ ከሚያውቋቸው ሽማግሌዎች ሊቃውንት ሌላ ወጣቶች ሊቃውንት ተጨምረው አገኙና በጣም ተደሰቱ። ደስታቸውንም ለመግለጥ “ ናስተሐምም ንስተይ ማየ ፈለግኪ፣ የወንዝሽን ውሃ እንጠጣ ዘንድ እንተጋለን” የሚል ቅኔ ተቀኝተው ጉዟቸውን ወደሸዋ ቀጠሉ።

ከሸዋ ሲመለሱ ወደመርጡለ ማርያም ቢሄዱ እነዚያ ያዩአቸው ሊቃውንት ሁሉ አልቀው ስላገኙ ይህን የሐዘን መግለጫ ቅኔ ተቀኝተዋል።። ሊቃውንቱም ያለቁት በክፉ ቀን ራብና ራቡም ባስከተለው በሽታ እንደሆነ ይተረካል።



www.ethiopianorthodox.org

*151 መወድስ (270) ኀ*

*ንጉሠ እስራኤል ዅሎሙ እግዚአብሔር*
*ዘወሀቡከ ኪሩቤል ቃለ ቅዳሴ መዓረ*
*ወዘባንከ አሥረፀ ጥብጣቢ ሕዋሳት ፀጉረ!*
*ጢስ ብእሲ ዘዕጣን አንጸረ*
*ንዋየ መስቀልከ ዘተቀብረ፣*
*እሌኒ ንግሥት እመ ኀሠሠቶ ድኅረ ።*
*ኢይሑርኺ ፍና አጥፍአ ደቂቀ አዳም አብትረ*
*ውስተ ቀራንዮ ቤተ አግዓዚ አመ ቦአ ወኀደረ*
*በዕለተ ዐርብ ቀድሐ ማየ ደመ አካል ቈሪረ*
*ስቅለትከ ባሕታዊ ሰንበተ ዘአክበረ።*

## ትርጉም

ኪሩቤል የምስጋና ቃል መአርን የሰጡህ፡
ጀርባህም የሰውነቶች ግርፋት /ጠጉርን ያበቀለ
የሁሉዉ እስራኤል ንጉስ /እግዚአብሄር!
ንግስት እሌኒ በሁዋላ
ብትፈልገው የተቀበረ
መስቀልህ/ገንዘብን የእጣን ጢስ ሰው አመለከተ።
ወገኖች/የአዳም ልጆችን ማጥፋት መንገድን እንዳይሄድም
በጌታ ቤት/ ቀራንዮ በገባና ባደረ ጊዜ
ሰንበትን ያከበረ ስቅለት/ባህታዊ
በአርብ ቀን ቀዝቃዛ የአካል ደም/ውሃን ቀዳ።

## ምስጢር

የጥንት ገበሬዎች ለመንግስት ማር ይገብሩ ነበር። ኪሩቤልም ለክርስቶስ የምስጋና ቃልን ያሰሙታል። ብርድና ሙቀት የሚፈራረቁበት የሰው አካል ጠጉር እንደሚያበቅል የክርስቶስ ጀርባም ግርፋትን ተቀበለ። ብር ሲቀበር ያየ ሰውም ብሩ የተቀበረበትን ቦታ እንደሚያሳይ እሌኒ ያስጤሰችው የእጣን ጢስም የተቀበረውን የክርስቶስን መስቀል አመለከተ። የጠፋውን ገንዘብ ባለቤቱ እንደምትፈልገው እሌኒ የተባለችው



ንግስት መስቀሉን አስፈለገች (ስንክ·መስከረም 17)።

ሰንበትን አክባሪ ባህታዊው በሰንበት ቀን መንገድ እንደማይሄድና ለእሁድና ለቅዳሜ የሚሆነውን ውሃ በአርብ ቀን እንደሚቀዳ ክርስቶስም የአዳም ልጆች እንዳይኮነኑ ደሙን በአርብ ቀን አፈሰሰ። ባህታዊ ሰንበትን እንደሚያከብር የክርስቶስ ስቅላትም በሰንበት ቀን አልሆነም ይላሉ ባለቅኔው።

*152 መወድስ (273)ኀ*
*ዘዘዮሐንስ (አለቃ)*

*በአሠረ ማይ የሐውር መልአከ አድኅኖ*
*በዕለተ ገብረ ፀብአ ከመ ያስተኅፍር ፀረ፣*
*እስመ በኤርትራ ከረየ መቃብረ ፈርዖን ባሕረ*
*ወእንበለ ደዌ ውስተ ባሕር ቀበረ*
*ንጉሠ ምድረ ግብጽ ወሐራሁ*
*ለዐይነ ሙሴ ነቢይ ከመ ይክስት ተአምረ።*
*ለሞትኺ ወመቃብር እመ አስተፋጠነ እግረ*
*ፈርዖን በኤርትራ ደዌሁ ኢያእመረ።*
*እስመ ያረውፆ ለፈርዖን እምነ ሀገር ሀገረ*
*ተግሣጸ መልአክ ደዌ መከራ በርእሱ እኁተ ኀደረ ።*

## ትርጉም

የማዳን መልአክ በውሃ መንገድ ይሄዳል፡
ጠብን በአደረገ ቀን ጠላትን ያሳፍር ዘንድ
የፈርኦን መቃብር/ባህርን በኤርትራ ቆፍሯልና።
ለነቢይ ሙሴ አይንም ተአምርን ይገልጥ ዘንድ
የግብፅ ምድር ንጉስንና
ወታደሮቹንም ያለደዌ በባህር ውስጥ ቀብሯልና።
ለሞትና ለመቃብርም እግርን በአፋጠነ ጊዜ
ፈርኦን በኤርትራ በሽታውን አላወቀም፡
በራሱ ያደረ የመልአክ ቁጣ! የመከራ ደዌ
ፈርኦንን ከአገር ወደአገር ያሮጠዋልና።



www.ethiopianorthodox.org

## ምስጢር

አንድ ባላጋራ ያለው ሰው በድብቅ ይሄዳል። መልአኩ ቅዱስ ሚካኤልም የግብፅን ሰዎች በመከራ ሊመታ ሲያስብ ሃይሉን በውሃ ስም አደረገ። የሚች ወገንም መቃብር እንደሚቆፍር ሚካኤል የኤርትራን ባህር እንደመቃብር አደረገው። በተቆፈረው መቃብር ሙትን እንደመቅበር ሚካኤልም ፈርኦንን ከነሰራዊቱ በኤርትራ ባህር አሰጠመው። የሙቱን መቃብር በቀብር ላይ ላልነበሩ ዘመዶቹ በቀብር ላይ የነበሩ ጎረቤቶች እንደሚያሳዩ ሚካኤል የኤርትራን ባህር የመክፈል ተአምርን ለሙሴ ገለጠ ይላሉ ባለቅኔው(ዘፀአ·14፡1— 21)።

*153 መወድስ/ስ*

*ዘኪዳናት ወልደ ሩፋኤል(መምህር፡ ዘጽላሎ)*

*ሰብአ ተመክሖ ኢይፍቅድ ነቢረ ሀገሩ*
*ወምስለ ድኩማን ኢይስተይ ንብረተ ሀገሩ ማኅበረ*
*እስመ በይነ ርስቶሙ ሳሌም ዘረሰይዎ ማኅደረ*
*ዳዊት ወሠራዊቱ*
*ሶዱ ነዋ እምሀገር ሀገረ*
*እስከ ኀጥኡ ምስዋረ፥*
*ወፍኖተ ሳሌም ጸሩ ዘኢይትከሀል ኀሣረ።*
*ድኅረ ለብሰሂ በጊዜ ጸብዕ ፍቅረ ዐፀደ ወይን ፀምረ*
*ናቡቴ በዓለ ርስት ውስተ ብሔረ ባዕድ ዘኢሖረ*
*በዐፀደ ወይኑ መድሎት አመ ተለቅሐ ነውረ*
*አትረፈ ተዋርዶ ወአስተዳለወ መቃብረ።*

## ትርጉም

የመመካት ሰው በሃገሩ መኖርን አይውደድ
ከደካሞችም ጋር የሃገሩ መኖር /ማህበርን አይጠጣ፥
ማደሪያን ስላደረጓት ስለ ርስታቸው/ሳሌም
ዳዊትና ሰራዊቱ
መሸሸጊያን እስካጡ ድረስ
ከሃገር ወደ ሃገር እነሆ ዞረዋልና፥
የማይቻል አሳርንም በሳሌም መንገድ ተሸከመዋልና።



በጠብ ጊዜም የወይን ቦታ ፍቅር/ግምጃን ከለበሰ በሁዋላ
ወደባእድ ሃገር ያልሄደ ባለርስት/ናቡቴ
በወይኑ ቦታ/ሚዛን ነውርን በተበደረ ጊዜ
መዋረድን አተረፈ፤ መቃብርንም አዘጋጀ።

## ምስጢር

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በቀኖና ወስና ከምታከብራ ቸው ቅዱሳን መካከል በአንዱ ስም ማህበር የሚጠጡ ምእመናን በሃብታቸው መጠንና በፆታ የተመደቡ እንደሆኑ፥ ትምክህተኛ ሰውም ከደካሞች ወገኖቹ ጋር በአገሩ መኖርን አይፍቀድ። ምክንያቱም በአገራ ቸው በኢየሩሳሌም የተነሳ የእስራኤል ንጉስ የነበረው ዳዊትና ሰራዊቱ ከፍተኛ ችግር ደርሶባቸዋል።

በትውልድ አገሩ የሚኖር የመሬት ከበርቴ በጦርነት ጊዜ በወርቅ የተጎበጎበ ለምዱን ደርቦ እንደሚዋጋና በሰላምም ጊዜ ምርጥ ምርጥ ልብሱን ለብሶ የሃብቱን አያያዝ እንደሚቆጣጠር፥ ናቡቴም የወይን ተክል ቦታውን ለእስራኤል ንጉስ ለአክአብ ሚስት ለኤልዛቤል አልሰጥም ማለቱ እንደነውር ተቆጥሮበት በሞት ተቀጥቷልና “ ሰው በሀገሩ መኖርን አይፍቀድ” ይላሉ ባለቅኔው (1 ነገስ·20፡ 17–26 ። 22፡34–38)።

*154 ሕንጼሃ(275)ኀ*
*ሚካኤል መልአክ ለዘለፋ አይሁድ አንበረ*
*እብነ ሆሣዕና ዘመና ጎሞረ።*

## ትርጉም

የመና መስፈሪያ/የሆሳዕና ድንጋይን
መልአክ ሚካኤል ለአይሁድ ዘለፋ አኖረ ።

## ምስጢር

ቅዱስ ሚካኤል በጎሞር ( በመና መስፈሪያ ቁና) የተሰፈረ መናን ለእስራኤል ሲመግባቸው እንደርሱ ፈጣሪውን ያመሰገነ ድንጋይ ለእስራ ኤል ልጆች ለአይሁድ መፈራረጃን ሆነባቸው። ምክንያቱም አእምሮ ግእዛን (የተፈጥሮ እውቀት) የሌለው ድንጋይ በሆሳእና እለት ሲያመሰግን



www.ethiopianorthodox.org

እነርሱ(አይሁድ) ስላላመሰገኑ ነው ማለት በቅኔው ተመስጥሯል።

*155 ግእዝ ዕጣነ ሞገር (274)ኀ*

*ተክለ ሃይማኖት ጻድቅ*
*ምሳሌ ዚአሁ ለኤሳው ወምሳሌ ያዕቆብ ኢይመረ፡*
*እስመ ከመ ይጽልዖ ጽልዐ ወከመ ያፍቅሮ አፍቀረ*
*ለእግዚአብሔር ሕያው ዘበኢተፈጥሮ ፈጠረ*
*ላዕለ ባሕር ወላዕለ እሳት እሳተ ወባሕረ።*

## አሠረ ንጉሥ

*ኦ ኢዮአስ ንጉሠ ፈረስከ ዘተአስረ*
*በሐብረ ረዋጺ ነፋስ ሐዊረ ኢሐዊር ኢሖረ*
*ወረዊጸ ኢረዊጸ እግር ኢያብደረ ።*

## ትርጉም

ፃድቅ ተክለ ሃይማኖት
የኤሳውን ምሳሌና የያእቆብን ምሳሌ አንድ አላደረገም፡
እሳትን በባህር ላይ ባህርንም በእሳት ላይ
ያለተፈጥሮ ለፈጠረ ለህያው እግዚአብሄር
እንደሚጠላው ጠልቷልና፡ እንደሚወደውም ወዷልና።

## አሰረ ንጉስ

ንጉስ ኢዮአስ ሆይ! በሯጭ ነፋስ ገመድ
የታሰረ ፈረስህ ያለመሄድ መሄድን አልሄደም፡
የእግር ያለመሮጥ መሮጥንም አልመረጠም።

## ምስጢር

ብልህ መንገደኛ በመንታ መንገድ ላይ ጊዜው ሲመሽበት ወደመንደር የሚያደርሰውን መንገድ ይዞ ይሄድና በአንድ ሰው ቤት ያድራል። ፃድቅ ተክለ ሃይማኖትም እንደኤሳው መጣላትን ጠልተው እንደያእቆብ መወደድን ስለመረጡ፡ አለምን ንቀው ለአንድ አምላክ ብቻ ስላደሩ እንደያእቆብ መወደድን አተረፉ እንጂ እንደኤሳው መጠላትን አላተረፉም።



በገመድ የታሰረ ፈረስ ሊፈረጥጥ አይችልም። እንዲሁም በጎንደር ከተማ የነገሡት የአፄ ኢዮአስ ፈረስ በነፋስ ታሰረ በማለት ፈረሳቸው እንደነፋስ ፈጣን መሆኑን ባለቅኔው ገልጠዋል (ሮሜ·9፡10—13)።

## ታሪክ

በልጅነቱ በጎንደር የነገሰው የኢትዮጵያ ንጉስ አፄ ኢዮአስ በጦርነት የእርሱ ወገኖች በመሸነፋቸው ተማረከ። አፄ ኢዮአስ ተማርኮ በሄደበት አገር ከንጉሱና ከመኳንንቱ ልጆች ጋር ፈረስ ግልቢያ ሲጫወት “ ወደ አገሩ ሲጋልብ መጣ መጣ ወደእነርሱ ሲጋልብ ሄደ ሄደ” እንዲሉ በቅድሚያ ለልጆች አስጠና። ከዚህ በሁዋላ ከእለታት በአንዱ ቀን በድንጉላ ፈረስ ላይ ተቀምጦ ሽምጥ ሲጋልብ ፈረሱ እንደነፋስ ሽው ብሎ አገሩ አግብቶታል ተብሎ በቃል ይተረካል። ስለዚህም ባለቅኔው “ ፈረስከ ዘተአስረ በሐብለ ረዋጺ ነፋስ፤ በሯጭ ነፋስ ገመድ የታሰረ ፈረስህ” ብለዋል።

*156 ሥላሴ (929)አ*
*ዘቃማ (አባ)*

*አሐዱ ንጉሥ ይቤሎሙ*
*ሶበ ዐበዩ መጺአ*
*ለምሳሑ እለ ተዐሥሩ*
*ነዳያነ ወምስኪናነ ጸውዑ ወሑሩ፤*
*ወሐዊሮሙ ረከቡ በጽጕ ክልኤቲ ሀገሩ*
*ቶማስሃ እደ ዘመተሩ*
*ወተክለ ሃይማኖት ምስኪነ ዘተሰብረ እግሩ*
*ውስተ ጽርሑ በዐለ ይግበሩ።*

## ትርጉም

ለምሳው የታደሙት
መምጣትን እምቢ
ባሉ ጊዜ አንድ ንጉስ ሂዱና
ችግረኞችንና መፃተኞችን ጥሩ አላቸው።
ሄደውም በሁለተኛይቱ አገሩ ጥግ
እጁን የቆረጠውን ቶማስን

www.ethiopianorthodox.org

እግሩ የተሰበረ ተክለ ሃይማኖት/ምስኪንን አገኙ፣
በአዳራሹ ውስጥ በአልን ያደርጉ ዘንድ።

## ምስጢር

አንድ ንጉስ ለልጁ ሰርግ አስርጎ የታደሙትን ወደሰርጉ ይጠሩ ዘንድ አሽከሮቹን ቢልካቸው እድምተኞቹ ለሰርጉ ግብዣ ፈቃደኞች አልሆኑም። ከዚህም የተነሳ ድግሱ ተዘጋጅቶ ሳይበላ እንዳይቀር አሽከሮቹ ችግረኞችንና ምፃተኞችን እንዲሰበስቡ አደረገ ። ሃጢአተኞች ሰዎች ወደአምላክ አንመለስም ቢሉ ሰውንና እግዚአብሄርን ለማገናኘት ቶማስ መርአስ በሚባል አገር፣ ተክለ ሃይማኖትም በኢትዮጵያ ሰበኩ። በዚያም ጊዜ የቶማስ እግሮች በከሃዲዎች ሰይፍ ተቆረጡ፣ የተክለ ሃይማኖትም እግር በፀሎት ቁመት ብዛት ተሰበረ በማለት ባለቅኔው ቅኔያቸውን አመስጥረዋል።

ታሪኩ በአንደኛው መጽሃፍ በገፅ 77 ተተርኳል።

*157 ሥላሴ( 933) አ*

*ዓለም በጊዜሁ ብሔረ ባዕዳን የሐውር*
*ወከማሆሙ ይከውን ለባዕዳኒሁ በግብሩ*
*ለዝኒ ከዋኔ እምዕሙቅ ምስጢሩ*
*ገብረ መንፈስ ቅዱስ ኢወፅአ ለእመ ወፅአ እምድሩ*
*እስመ ለአናብስት ዘይጥኁሩ*
*አርአያ ማኅደሮሙ ኮነ ማኅደሩ*
*ወጸጉሮሙ ተመሰለ ጸጉሩ።*

## ትርጉም

አለም በጊዜው ፣
ወደባእዶች (ሌሎች) አገር ይሄዳል ፡
በስራውም እንደባእዶቹ ይሆናል ።
ከዚህም ሁኔታ ጥልቅ ምስጢር
ከምድሩ እንደወጣ ገብረ መንፈስ ቅዱስ አልወጣም ፡
ማደሪያው እንደሚያገሱ
አንበሶች ማደሪያ ይሆናል ፡
ጠጉሩም ጠጉራቸውን ተመስሏልና ።



## ምስጢር

ሰው ኑሮውን ይመስላል እንዲሉ "ወደባእድ አገር ብትሄድ እንደእነርሱ ሁን" እንደተባለው በባእድ አገር የሚኖር ሰው ሁሉ የሚኖርበትን አገር ሰዎች መስሎ መኖር ይገባዋል ። አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ከትውልድ አገራቸው ከግብፅ ወጥተው ከዘመድ ተለይተው በኢትዮጵያ ገዳማት ሲኖሩ አኗኗራቸው በሚኖሩበት ጫካ ውስጥ ከሚኖሩ አራዊት ልማድ አልወጣም ፡ እንደ አራዊት ጫካውን ማደሪያ ፡ ጠጉራቸውንም ልብስ አደረጉ በማለት የቅኔው ደራሲ የፃድቁን ሃይማኖታዊ ገድል በቅኔያቸው ገልጠዋል ።

ታሪኩ በአንደኛው መፅሀፍ በገጽ 75 ተተርኳል ።

*158 መወድስ (962) አ*
*ዘወልደ መስቀል (አለቃ ፡ ዘሁርኤል)*
*ለእመ ትእዛዝ ወፅአ እምኀበ ደመና*
*ቈፅለ ዕፀ ገዳም ዓለም ይጸሐፍ በበብሔሩ*
*ይቡሳነ ቈጽል ዕፀው ምሕረተ ዚአሁ አንከሩ ፤*
*እስመ ጽድቅ ቃሉ ወእሙን ነገሩ ፤*
*ወበይነ ዘወለደ ነጠብጣበ*
*ጸወርተ አእባን አፍላግ በዐለ ይገብሩ ።*
*ድቡረሂ ለእመ ቀብዖ ለዘተወልደ ዕውሩ*
*ሰብአ ዐይን ሐመልማል ሰገደ ታሕተ እግሩ ፤*
*ለእግዚአ ዝናም ክረምት ዘዲበ ኢዮር መንበሩ*
*እስመ እንዘ ማይ ጠፈረ ቤቱ ደመና መንኰራኵሩ ።*

## ትርጉም

የዱር እንጨት ቅጠል/ሰው በያገሩ
እንዲቆጠር ከደመና ዘንድ ትእዛዝ ቢወጣ
ቅጠላቸው የደረቀ እንጨቶች ምህረቱን አደነቁ ፤
ቃሉ እውነት ነውና ነገሩም የታመነ ነውና ፤
ነጠብጣብንም ስለወለደ
ድንጋዮችን ተሸካሚዎች ወንዞች በአልን ያደርጋሉ ።
እውር ሆኖ የተወለደውንም ጭቃን ቢቀባው



www.ethiopianorthodox.org

አይናማ/ልምላሜ ከእግሩ በታች ሰገደ ፤
መቀመጫው በሰማይ ላይ የሆነ የዝናብ ጌታ/ክረምት
የቤቱ ጣሪያ ውሃ ሲሆን ፥ ደመና መንኰራኩሩ ነውና ።

## ምስጢር

በግዛቱ ውስጥ የሚኖረው ሰው ሁሉ እንዲቆጠርና እንዲመዘገብ ከሮሙ ንጉሰ ነገስት ከአውግስጦስ ቄሳር ትእዛዝ እንደ ተሰጠ የዱር እንጨት ሁሉ ከደመና በሚዘንበው ዝናብ ለመለመ ፤ ቅጠሉም ተንሰራፋ። የክርስቶስን ምህረት ምእመናን እንደሚያደንቁ በበጋ ጠውልገው የነበሩት እንጨቶች የደመናን ዝናብ ተስፋ አደረጉ ። ኢየሱስ ክርስቶስ የማያደርገውን እንደማይናገርና የተናገረውንም እንደማያስቀር ሁሉ የክረምት ደመና ከዳመነ አያብልም ዝናብ ያዘንባል ።

ከእግዚአብሄር አብም ስለተወለደው ስለእግዚአብሄር ወልድ ምእመናንና ካህናት በአልን እንደሚያከብሩ ደመናም ዝናብን ሲያዘንብ ወንዞች ሞልተው ድንጋዮችን ያጥረገርጋሉ ። ኢየሱስ ክርስቶስ እውር ሆኖ የተወለደውን ጭቃ ቀብቶ አይን ሲፈጥርለት ከእግሩ ስር እንደሰገደለት ድፍኑን ደረቅ መሬት ዝናቡ ሲያጨቀየው ልምላሜ ያላቸው እፀዋት አትክልትና አዝርእት ሁሉ አደጉ ። አምላክ በሰማይ እንዳለና ጣሪያው ውሃማ መንኰራኩሩም ደመና እንደሆነ በክረምትም ደመና በሰማይ ያጉረመርማል ውሃውንም ያዘንባል ይላሉ ባለቅኔው ።

*159 መወድስ (941) አ*
*ዘበቃ (ቄሰ ገበዝ ፡ ዘጎንጅ)*
*ሠለስቱ አብያት ዘላዕለ ታቦር*
*ድኅረ በሕሊና ተሐንፀ ተነሥቱ ወተመዝበሩ ፡*
*መሠረተ ኰኵሕ ጴጥሮስ እመ ኢጸንዐ እምድሩ*
*ክልኤቱ ያዕቆብ ወዮሐንስ*
*አዕማደ ምስጢር አኮኑ ተሰብሩ ፤*
*ወዘታሕተ ጠፈር ሠረገላሁ*
*እስመ ወሰደ ኤልያስ ዘኢየሐውር በእግሩ ።*
*አዘዞሙሂ ወልደ ባሕርይ ለዘነለፉ ወሖሩ*
*በታቦር ዘተገብረ ለአብያጺሁ ኢይንግሩ ፤*
*እስመ ጽዋዐ ሞት ደገመ ወልደ እንበረም ፍቁሩ*



*እንዘ አሐደ ኢይጥዕም ኤልያስ በሀገሩ ።*

## ትርጉም

በታቦር ላይ ሶስት ቤቶች
በአሳብ ከተሰሩ በሁዋላ ፈረሱና ተመዘበሩ ፤
የአለት መሰረት የሆነ ጴጥሮስ አካቶ ሳይፀና
ሁለቱ ያእቆብና ዮሃንስ
የምስጢር ምሰሶዎች ተሰብረዋልና ፤
ከጠፈር በታች ያለውን ሰረገላውንም
በእግሩ የማይሄድ ኤልያስ ወስዷልና ።
በታቦር የተደረገውን ለጓደኞቻቸው እንዳይነግሩ
ያለፉትንና የሄዱትንም የባህርይ ልጅ አዘዛቸው ፤
ኤልያስ በአገሩ አንድ ሳይቀምስ
ወዳጁ የእንበረም ልጅ መጠጥ/ሞትን ደግሟልና ።

## ምስጢር

መሰረታቸው ያልጠና ቤቶች ከተሰሩ በሁዋላ ምሰሶዎቻቸው ከመሰበራቸው የተነሳ ይፈርሳሉ ፤ ሊቀ ሃዋርያት ጴጥሮስም በደብረ ታቦር እንዲሰሩ የተመኛቸው ሶስት ቤቶች ታስበው ሳይሰሩ ቀሩ ። መሰረት የተባለው ቅዱስ ጴጥሮስና አእማድ የተባሉ ያእቆብና ዮሃንስም ከመለኮት ግርማ የተነሳ ወደቁ ። ቤቶቹ ሲፈርሱ ጎረቤት በውስጣቸው ያለውን እቃ እንደሚያወጣ ነቢይ ኤልያስም በሰረገላው ሆኖ ወደነበረበት ቦታ ተመለሰ ።

አንዱ ሰው አንድ ዋንጫ ሳይቀምስ ሌላው ሁለት ዋንጫ ሲጠጣ "ያህስ ጉድ ነው" እንደሚባል ፡ አንድ ጊዜ ካልሞተ ነቢይ ኤልያስ ጋር የተናገረ ከመቃብር የወጣው ሟቹ ነቢይ ሙሴ ወደነበረበት መቃብር ተመለሰ በማለት ባለቅኔው አመስጥረዋል (ማቴ·17) ።

*160 መወድስ (947) አ*
*ዘውብሸት (ቄሰ ገበዝ)*
*ሕማም ወሞት ነገሥተ ሙስና*
*ሥጋ ምግቦሙ ወእንበለ ሥጋ ኢየኀድሩ ፤*
*መልዕልተ ኵሉ ዓለም ኀበ ተልዕሉ ወከብሩ*



www.ethiopianorthodox.org

*ለበሊዐ ስጋ አኮኑ ተፈጥሩ ።*
*ወአግብርተ ሥቃይ መቃብራት*
*ትራፋቲሆሙ በልዑ እንዘ እምኔሆሙ ይዴኀሩ ፤*
*እግዚአሙሂ በከመ ይቤ ትእዛዘ እግዚእ ይግበሩ*
*እምሀገር ውስተ ሀገር ለአጥፍኦ ሀገር የሐውሩ ፤*
*ወኵሎ ዓለመ እንዘ ይኔጽሩ*
*ምዕረ ይቀሥፉ ወምዕረ ይመትሩ ።*

## ትርጉም

ህማምና ሞት/የጥፋት ነገስታት
ምግባቸው ስጋ ነው ያለስጋም አያድሩም ፤
በአለም ሁሉ ላይ ከፍ ካሉና ከከበሩ ዘንድ
ስጋ ለመብላት ተፈጥረዋልና ።
የስቃይ አገልጋዮች/መቃብሮችም
ከእነርሱ ወደሁዋላ ብለው ትራፊዎቻቸውን በሉ ፤
ጌታቸውም እንዳለ የጌታን ትእዛዝ ይሰሩ ዘንድ
ከአገር ወደአገር ለማጥፋት ይሄዳሉ ፤
አለምን ሁሉም እያዩ
አንድ ጊዜ ይገርፋሉ ፤ አንድ ጊዜም ይቆርጣሉ ።

## ም ስ ጢ ር

ለስጋ መብል የታደሉ ነገስታት ያለ ስጋ መብል አያድሩም ። ለጥፋት የተዘጋጁ ህማምና ሞትም ስጋውያኑን እንጂ መንፈሳውያኑን (መላእክትንና እግዚአብሄርን) አያገኟቸውም ። ደግሞ በስቃይ የሚኖሩ የነገስታት አገልጋዮች ጌቶቻቸው ከበሉ በሁዋላ ትራፊዎቻቸውን እንደ ሚበሉ መቃብሮችም ከህማምና ከሞት በሁዋላ የሞቱ ሰዎች በድኖችን አፈረሱና አበሰበሱ ።

አሽከሮች ጌታቸው ያዘዛቸውን እንደሚፈፅሙ ህማም ፡ ሞትና መቃብርም የማይፈቱትና ባዶ የማያደርጉት ቤት የለም በማለት ስጋ የለበሰ ሁሉ ከሞት የማይቀር መሆኑን ባለቅኔው ያስረዳሉ ።



*161 መወድስ (950) አ*
*ዘለማ ኃይሉ (አለቃ)*
*ዲበ በዐለ ቤት ዐቢይ ሆሣዕና ኵሉ*
*ገባእተ ጽባሕ ኪሩቤል ብዙኀ አንጐርጐሩ*
*ወሕገ ተኀጥኦ እምዮናስ ከመ ይጠይቁ ሖሩ*
*እስመ ለአእዱግ ገባአተ ሠርክ*
*ምስሌሆሙ አስተዓረዮሙ ኪያሁ ይጹሩ*
*አእዱግሰ እለ ተድኀሩ*
*በገጽ ገጸ ምስለ ኪሩባዊ ኢይትናጸሩ ።*
*አእባንሰ ለሆሣዕና ተልዕሎቶሙ ይንግሩ*
*በላዕለ አይሁድ ለተመክሖ ከመ አናብስት ይጥኀሩ ፤*
*ለዘርኀበ ዮሴፍ አምጣነ ምሕረተ ገብሩ ፤*
*ወለእለ ደምፀ ሕዝበ ሙሴ መዓተ ያቈርሩ ።*

## ትርጉም

በታላቅ ባለቤት/የሁሉ ሆሳእና ላይ
የጧት ምንደኞች ኪሩቤል ብዙ አጉረመረሙ
የመኮብለል ህግንም ከዮናስ ይረዱ ዘንድ ሄዱ ፤
አህዮች/የምሽት ምንደኞችን
ከእነርሱ ጋር አስተካክሏቸዋልና ።
እርሱን ይሸከሙ ዘንድ
ወደሁዋላ ያሉ አህዮች ግን ከኪሩቤል ጋር ፊት ለፊት አይተያዩም ።
ድንጋዮችማ! ታላቅነታቸውን ለሆሳእና ይናገሩ ዘንድ
በአይሁድ ላይ ለመመካት እንደ አንበሶች ይጮኸሉ ፤
ለተራበ ዮሴፍ ምህረትን አድርገዋልና ፤
ለተጠሙ የሙሴ ወገኖችም ቁጣ/ጥማቸውን ያቀዘቅዛሉና ።

## ምስጢር

ከጥዋቱ አንድ ሰአት ጀምረው ሙሉ ቀን የሰሩትንና ከቀኑ አስራ አንድ ሰዓት ጀምረው የሰሩትን የቀን ሙያተኞች በደመወዝ ያስተካከላ ቸው አንድ ሃብታምን ቀዳሚዎቹ ሰራተኞች እንደተቃወሙት ፡ ሆሳእና የሚባል የክርስቶስን ዙፋን ተሸክመው የሚኖሩ አራቱ ኪሩቤልንና



www.ethiopianorthodox.org

አህዮችን ሆሳእናን በመሸከም ማስተካከል ከሰዎች ይልቅ የመላእክትን ክብር በማሳነስ ነው ። ዮናስ ከእግዚአብሄር ኮብልሎ ሲሄድ የእግዚአብሄር እጅ በአሳ ነባሪ ውጦት እንደያዘው ኪሩቤልም የእግዚአብሄርን ዙፋን ከመሸከም አይወጡም ይላሉ ባለቅኔው ።

በጦር ሜዳ ጀብዱ የሰሩ ወታደሮች በአውደልዳዮች ላይ እየተመኩ እንደሚኖሩ አይሁድ ሆሳእናን ማመስገንን ሲቃወሙ ፤ አእምሮ የሌላቸው ድንጋዮች እንደ መላእክት የሆሳእናን ምስጋና አበረከቱ ። ጀብዱ የሰሩም "እዚህ ገዳይ" በማለት ሙያቸውን እንደሚጠቃቅሱ ድንጋዮች ለዮሴፍ ዳቦ ፤ ለእስራኤል የውሃ መፍለቂያ ሆኑላቸው ፤ ራብና ጥምንም አስወገዱላቸው በማለት ባለቅኔው አመስጥረዋል ።

## ታሪክ

ዮሴፍን አባቱ ያእቆብ ለወንድሞቹ ስንቅ እንዲያቀብላቸው ላከው ። ቀድሞ ከነበሩበት ቦታ በጎቻቸውን ወደሌላ ይዘው ሄደው ወንድሞቹን አጣቸው ። ዮሴፍ ወንድሞቹን በመፈለግ ከአንዱ ቦታ ወደሌላው ቦታ ሲንከራተት በጣም ራበውና አዘነ መልአክ በሰው አምሳል መጥቶ "ምን ሆንህ?" አለው ። ዮሴፍም ለመልአኩ ችግሩን ነገረው ። "ምነው ከያዝከው ምግብ አትበላምን?" አለው ። "ይህንማ አባቴ ለወንድሞችህ ስጥ አለኝ እንጂ መቼ አንተ ብላው አለኝ!" በማለት መለሰለት ። መልአኩም "የአባትህን ህግ የምትጠብቅ ከሆንክስ የአባትህ አምላክ ድንጋዩን ዳቦ ያደርግልሃል!" ሲለው ወዲያውኑ ድንጋዩ ዳቦ ሆኖለት ተመግቧል ይባላል ።

እስራኤል በሙሴ አማካይነት በመልአክ መሪነት ከግብፅ ወጥተው በምድረ በዳ ሲጓዙ በውሃ ጥም ተጨነቁና ሙሴን ተጣሉት ፤ አንጎራጎሩበት (አጉረመረሙበት) ። ሙሴም ስለህዝቡ ውሃ ጥም ወደ እግዚአብሄር አመለከተ ። እግዚአብሄርም የኤርትራን ባህር በከፈለበት በትር የኮሬብን አለት ድንጋይ እንዲመታው ሙሴን አዘዘው ። ባትእዛዙም መሰረት ሙሴ አለቱን በበትሩ በመታው ጊዜ ከድንጋዩ ውሃ ፈልቆላቸው የእስራኤል ህዝብ ጠጥተዋል ተብሎ ተጽፏል (ዘፀአ·17፥1–7) ።

*162 መወድስ (953) አ*

*ማየተ ብርሃን ቀድሑ እምነቅዐ ገቦከ*
*አዕይንተ ዕውር ሕዝብ ዘገዳመ ጽልመት ወፈሩ ፤*



*ወሰገደ ለከ እንዘ ይመጽእ በእግሩ*
*ሐንካስ እንግዳ ዘርጉቅ ሀገሩ*
*እግዚአብሔር ካህነ ፍትሕ!*
*ቃላተ ዕውር መጽሐፍ ዘበቃልከ ተነግሩ ።*
*እስራኤልኒ ሕዝበ ዕሌኒ እለ ኪያከ አፍቀሩ*
*ኢየሱ ጢሰ ዕጣን ኀበ ሖረ የሐውሩ ፤*
*አኮኑ ተነጥአ ወኢተረክበ እምድሩ*
*ሙሴ ዕፀ መስቀል ዘተነብአ መቃብሩ ።*

## ትርጉም

የእውር/መፅሃፍ ቃሎች በቃልህ
የተነገሩ እግዚአብሄር/የፍርድ ካህን !
በዱር /ጨለማ የተሰማሩ የእውር አይኖች/ ህዝቦች
የብርሃንን ውሃዎች ከምንጭ/ወገብህ
ቀዱ ፤ አገሩ የራቀ
እንግዳ/አንካሳም በእግሩ መጥቶ ሰገደልህ ።
አንተን የወደዱ እስራኤል/የእሌኒ ህዝብም
ኢያሱ/የእጣን ጢስ ወደ ሄደበት ይሄዳሉ ፤
መቃብሩ የተሰወረ ሙሴ/የእንጨት መስቀል
ታጥቷልና አካቶም (በፍፁም) አልተገኘምና ።

## ምስጢር

የገጠር ኗሪዎች ከምንጭ ውሃ እንደሚቀዱ በጨለማ የኖሩ የእውር ሰው አይኖች ከክርስቶስ ጎን ከፈሰሰው ደም ርጭት (መረጨት) የተነሳ የብርሃን ምልክታን (ማየትን) አገኙ ። አገሩ የራቀ እንግዳ በእንግድነት እንዲያሳድረው ለፈለገው ሰው እጅ እንደሚነሳ በክርስቶስ ተአምር የአንካሶች እግሮች ረቱ (ተቃኑ) ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የመፃህፍት ትርጓሜ ሊቃውንት መፃህፍትን በቃል እንደሚተረጉሙ ክርስቶስም እውር ሆኖ ለተወለደው ሰው አይኖችን ፈጠረለት ፤ ከእውርነት የዳነውም ሰው የምስጋና ቃላትን አሰማ ። እስራኤል መስፍናቸው ኢያሱ ወደ ሄደበት እንደሄዱ የንግስት እሌኒ አሽከሮች የእጣን ጢስ በሰገደለትና በአነፀረበት (በአመለከተበት/በጎልጎታ) ተሰበ



www.ethiopianorthodox.org

ሰቡ ። እስራኤል ኢያሱን የተከተሉት መሪያቸው ሙሴ በመታጣቱ እንደሆነም የእጣኑም ጢስ በጎልጎታ የሰገደው የክርስቶስ መስቀል በዚያ ተቀብሮ መኖሩን ለማመልከት ነው ይላሉ ባለቅኔው ።

ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል የእውርን አይን ከማብራቱ፣ ድውይንም ከመፈወሱ የተነሳ አይሁድ ቀንተው በጎልጎታ ቀበሩት ይባላል ። ህዝቡም በነፍስ ወከፍ (አንድ በአንድ) የየቤቱን ጥራጊ በመቃብሩ ላይ እንዲጥሉበት ታዘዙና ፈፀሙበት ። ስለዚህ በመቃብሩ ላይ የተቆለለው ጥራጊ በቀን ብዛት አደገና ኮረብታ ሆነ ፤ የመስቀል መቃብርም እንደሆነ ሊታወቅ አልቻለም ። የሮማው ንጉሰ ነገስት የቆስጠንጢኖስ እናት ንግስት እሌኒ ክርስትናን ከተቀበለች በሁዋላ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል በመጥፋቱ ታዝንና ትቆረቆር ነበር ። በክርስቶስ ካላመነው ከሮሙ ንጉስ ከቁንስጣ የወለደችውን ቆስጠንጢኖስን እግዚአብሄር ለክርስትና ሃይማኖት ቢያበቃላት መስቀሉን ልትፈልግ ተሳለች ። ባሏም ሲሞት ልጇ የክርስትና ሃይማኖትን ተቀብሎ ነገሰላትና በስእለቷ መሰረት መስቀሉን ለመፈለግ ወደኢየሩሳልም ተጓዘች ። እዚያ ደርሳ የአይሁድን ሽማግሌዎች እያስያዘች ስለመስቀሉ መቃብር ብትጠይቅ እርግጡን የሚነግራት አጣች ።

በዚህ በሁዋላ የእንጨት ደመራ አስደምራና አቃጥላ በግመል የጫነችውን እጣን በፍሙ ውስጥ አስጨመረችው ፤ የእጣኑ ጢስ እንደቀስተ ደመና መስቀሉ በተቀበረበት ቦታ ላይ ተተክለላትና ያን ምልክት አድርጋ ኮረብታውን አስቆፍራ የክርስቶስን መስቀል አግኝታለች ።

ነቢዩ ሙሴ እስራኤልን ከግብፅ አውጥቶ ወደ ከነአን ሲጓዝ እስራኤል እርሱን እንደ አምላክ ያዩት ነበር ። ሲሞት ስጋውን እንዳያመልኩበት ለማድረግ የእግዚአብሄር መልአክ ቅዱስ ሚካኤል ሙሴን ናባው ወደሚባል ተራራ ወስዶ መቃብር አስቆፍሮ በህይወቱ ቀብሮታል ተብሎ ይተረካል ። ስለዚህም እስራእል የሙሴን መቃብር ሊያውቁ አልቻሉም ። ዲያብሎስ ግን የሙሴን መቃብር አሳያችሁዋለሁ ብሎ እስራኤልን ሲወስዳቸው መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል አይቶ ገስፆታል ይባላል (ይሁዳ 8–10 ። ስንክ·መስከረም 17) ።

*163 መወድስ (955) አ*



ርእሰ ዐውደ መንግሥት ዮሐንስ እለ ቀደስኮሙ
አምኃ መቅደሰከ ዐይነ በአንቃዕድዎ ይሰፍሩ ፤
እስመ ሥዕለ ማይ ወወርቅ ለደብረ ብርሃን ጠፈሩ ፤
ወእለ ምስሌከ በመልክእ ኀብሩ
አኀዊከ መንክራት
ዳግሚተ ዐይን ፀሐየ ለወለተ ዐይን ፈጠሩ ።
ወርቅሂ ወብሩር እለ ኢተምሀሩ
በከተማ ርእሳ ለመቅደስከ ምስለ ነፋሳት ይትናገሩ ፤
ወለዘአግባእኮ መልአክ ኀበ ራብዓዊት መንበሩ
ዐጸፍተ ብርሃናት አልባሲሁ ምስለ ከዋክብት ይትናጸሩ ።

## ትርጉም

የመንግስት አደባባይ ራስ! ዮሃንስ! የቀደስሃቸው
ሰዎች በመቅደስህ እጅ መንሻ/ አይንን በማንጋጠጥ ይሰፍራሉ ፤
የደብረ ብርሃን ጣሪያው የውሃና የወርቅ ስእል ነውና
ከአንተ ጋርም በመልክ አንድ የሆኑ
ወንድሞችህ/መደነቆች
የአይን ሁለተኛ ፀሃይን ለአይናማ ፈጥረዋልና ።
ያልተማሩ ወርቅና ብርም
በመቅደስህ ራስ ጫፍ ከነፋሳት ጋር ይናገራሉ ፤
ወደአራተኛ መንበሩ የመለስኸው መልአክም
ብርሃኖችን የተጎናፀፉ ልብሶቹ ከከዋክብት ጋር ይነፃፀራሉ ።

## ምስጢር

ለመንግስት ግብር እንዲያገቡ የተመረጡ ገባሮች እጅ መንሻ ማር እንደሚሰፍሩ የጎንደሩ ንጉስ ፃድቁ አፄ ዮሃንስ የሰሩት የደብረ ብርሃን ቤተ መቅደስ ጣራ በሰማያዊና በወርቃማ ቀለም ስለተሳለ በተመልካቾቹ አይን ታይቶ አይጠገብም ።
ጥበበኛውን በሙያው የመሰሉት ተራ ሰራተኞች የርሱን ስራ አስመስለው እንደሚሰሩ አፄ ዮሃንስ የሰሯቸው መደነቆችም ለአይናማይቱ ንግስት ፀሃይን መሰሏት ። የቅዳሴን ስርአት የማያውቁ አስቀዳሾች በቅዳሴ ጊዜ



www.ethiopianorthodox.org

ከሚመሳሰሉ ሰዎች ጋር እንደሚነጋገሩ በጎንደር ከተማ ያለው የደብረ ብርሃን ቤተ ክርስቲያን የብር ጉልላት ሻሁራ (መርገፍ) በነፋሶች ይንቧቧል ። አምላክ አዳምን ወደ ቀድሞ ቦታው እንደመለሰው ፣ ፃድቁ ንጉስ አፄ ዮሃንስ በደብረ ብርሃን የሾሙት አለቃ የለበሰው ካባ ኮከብ ይመስላል ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

*164 መወድስ (958)አ*

*ዘወርቅ አገኘሁ ተክሌ (አለቃ)*

*በጉሀሉት ወርቅ ንዋየ ዐመፃ*
*ኢትዮጵያ ሕዝብኪ አዕርክተ ረድኤት ይግበሩ ፣*
*አኮኑ ዐረዩ ወተማከሩ*
*ኤዶምያስ ወሞዐብ*
*ከመ በዋሕድና ክብረኪ ይሥዐሩ*
*ምስሌኪ እለ ኅብሩ*
*እንዘ በእንቲአኪ ዘልፈ ሰላመ ይትናገሩ ።*
*ሲሳዮሙሂ ሕዝበ ዚአኪ እምድኅረ ተደሩ*
*ርኁብ እንዘ ሀሎ እለ ጸግቡ አንጐርጐሩ ፣*
*አምጣነ ሕማሞሙ ረስዑ ፣ ወኢተዘከሩ*
*ዘገብረ እግዚአሙ መንክረ ዲበ ፀሩ ።*

## ትርጉም

ኢትዮጵያ! የአመፃ ገንዘብ በሆነ በሸንገላ/ወርቅ
ህዝብሽ የእርዳታ ወዳጆችን ያድርጉ (ያብጁ) ፣
ኤዶምያስና ሞአብ በአንድነት
ክብርሽን ይሽሩ ዘንድ
ተካክለው (አንድ ሆነው) ተማክረዋልና ፣
ከአንች ጋር የተባበሩት
ስላንች ዘወትር ሰላምን ሲናገሩ
ያንች ወገኖችም ምግባቸውን ከተመገቡ በሁዋላ
የተራበ ሳለ የጠገቡ አጉረመረሙ ፣
ህማማቸውን (መከራቸውን) ረስተዋልና ፣
ጌታቸው በጠላቱ ላይ ያደረገውን ድንቅም አላስቡምና ።



## ምስጢር

ሃይለኞች ደካማውን በሃይል ሊያጠፉ ሲሞክሩና ሲተባበሩ ደካማው በበኩሉ ረዳት የሚሆኑ ወዳጆችን በገንዘብ ማፍራት እንደሚችል ፣ የኢጣልያ ፋሽስቶች ኢትዮጵያን በወረሩ ጊዜ በአፍ ጣልያኖችን በልብ አገራቸውን መስለው የሰሩ ውስጠ አርበኞች አሉ ። እስራኤል ከግብፅ ሲወጡ መና ከደመና እየወረደላቸው ሲመገቡ እንዳልተመገቡ ሆነው በሙሴና በአምላካቸው ላይ እንዳንጎራጎሩ (እንዳጉረመረሙ) ፣ በኢጣሊያ ወረራ ዘመን ተሾመው የነበሩ ባንዳዎች ስለአገራቸው በራብና በጥም ሲሰቃዩ በነበሩት አርበኞች ላይ ከፋሽስቶች ጋር ሆነው መከሩባቸው ። ከዚህም ሌላ እስራኤል ያጉረመረሙት አምላካቸው ያደረገላቸውን ዘንግተው እንደሆነ ፣ ባንዳዎችም በኢጣልያ መንግስት ተደልለው በወገኖቻቸው የኢትዮጵያ አርበኞች ላይ ለፈፀሙት ማሳደድ የተደረገላቸውን ይቅርታ አላስታወሱም በማለት ባለቅኔው ባንዳዎችና ፋሽስቶች በአንድ ወገን ፣ በሌላ ወገንም አገር ወዳድ አርበኞች የሰሩትን በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል ።

*165 ግእዝ ክብር ይእቲ/ይ*

*ርኅቡ ሕዝብ ዘፍኖተ ሀጉል የሐውሩ*
*በኅብስት ዘነሥኡ አምጣነ ዕፄ ነጸሩ ።*
*ያነክርሂ ካህን እንተ ሥርናየ ይዘሩ*
*አምጣነ ምእመናን አዕዋፍ እለ ኢይዘርዑ የአርሩ ።*

## ትርጉም

የጥፋት መንገድን የሚሄዱ ህዝብ ተራቡ ፣
በያዙት ህብስት ትልን አይተዋልና ።
ስንዴን በመበተን የሚዘራ ካህንም ያደንቃል ፣
አማኞች/ወፎች ያልዘሩትን ይለቅማሉና ።

## ምስጢር

መንገደኞች ሰዎች ስንቃቸውን ይዘው ሲሄዱ በያዙት ዳቦ ውስጥ ትል ካገኙበት ምንም ቢራቡ አይበሉትም ። በአንፃሩ በስንዴ ህብስት የሚሰጠው የክርስቶስ ስጋ በሃጢአት ሆነው የተቀበሉትን ሰዎች እሳቱ



www.ethiopianorthodox.org

ወደማይጠፋበትና ትሉ ወደማያንቀላፋበት ገሃነመ እሳት ያወርዳቸዋል ይላሉ ባለቅኔው ።

ስንዴን የሚዘራ ገበሬ ያልዘሩትን ዘር በሚለቅሙ ወፎች እንደሚደነቅ በሚፀለየው የቅዳሴ ፀሎት የስንዴው ህብስት የክርስቶስ ስጋ የሚሆንለት ካህንም በህብስቱ የክርስቶስ ስጋነት መሆን ምስጢር ይገረማል ይላሉ ባለቅኔው ።

*166 ዕዝል ዕጣነ ሞገር (971)አ*

*ዘኀሹ አራት አይና*

*እመ ኢያእመሩ ሕዝብ ዐቅመ ትንንያ በግብሩ*
*ዘአካለ ነጌ ግዘፈ እምኢያንከሩ ፤*
*ወለኪሩባዊ በአዕይንት ተቀሥፎ ዘባኑ ወእግሩ*
*እመ ኢተወልደ ዘዕውሩ ፤*
*ወለእመ በሞት ኢኀጸረ ትንሣኤ አልዓዛር ገብሩ*
*እምኢኮነ ፍሉጠ ትንሣኤ ቃለ አብ በኩሩ ።*

## ትርጉም

ሰዎች የትንኝን አቅም በስራው ቢያውቁ ኖሮ
የዝሆን አካል ውፍረትን ባላደነቁ ነበር ፤
አይነ ስውሩም ባይወለድ ኖሮ የኪሩብን ጀርባና እግር
በአይኖች መገረፍን ባላደነቁ ነበር ።
የአገልጋዩ አልአዛር ትንሳኤም በሞት ባያጥር
የበኩር ልጁ የአብ ቃል በትንሳኤ የተለየን ባልሆነ ነበር

## ምስጢር

የአንድ ፍጡር ታናሽነት በአካል ግዝፈት ከእርሱ የበለጡ ፍጡራን በመኖራቸው ይታወቃል ። የጤንነት ጥቅም በታመሙ ጊዜ ፣ የነፃነትም ጥቅም ነፃነትን ተገፍፎ በጠላት እጅ በወደቁ ጊዜ በይበልጥ ይረጋገጣል። ባለቅኔውም ትንኝን ከዝሆን ፣ ታውሮ የተወለደውን ብዙ አይኖች አሏቸው ከሚባሉት ከኪሩቤል ፣ ዳግመኛ ሞትን ያስከተለ የአልአዛርን ትንሳኤም ሁለተኛ ሞትን በማያስከትል ከእግዚአብሄር ወልድ ትንሳኤ ጋር በማወዳደር ቅኔያቸውን አመስጥረዋል ።



*167 ዕዝል ጉባኤ ቃና (980)አ*

*ሰነ.ቃዊ ገብርኤል ለመሰንቆሁ ሰወራ*
*ዕፄ መቃብር ሕፃን ከመ ኢይብትክ አውታራ ።*

## ትርጉም

የመቃብር ትል/ህፃን ጅማቷን እንዳይቆርጣት
አዝማሪ/ገብርኤል መስንቆውን ደበቃት

## ምስጢር

አዝማሪ መስንቆውን ህፃን እንዳያበላሽበት ደብቆ ያኖራታል ። ቅድስት ማርያምንም የመቃብር ትል እንዳይበላት የአዝማሪ ምሳሌ መልአክ አሳረጋት (ወደሰማይ አወጣት) ማለት በቅኔው ምስጢር ተገልጧል ።

*168 ግእዝ ጉባኤ ቃና (981)አ*

*ኢጥሀለ ምንተ ወይነ እስራኤል ኤርትራ ፤*
*እስመ እስከ ታሕቱ ሰትይዎ ዘንጉሠ ግብጽ ሐራ*

## ትርጉም

የእስራኤል ወይን/ኤርትራ ምንም አላተለም ፤
የግብፅ ንጉስ ወታደሮች እስከ እንቃሪው ጠጥተውታልና ።

## ምስጢር

ጠላው ጥሩ ሲሆን ጠጪዎቹ እስከ እንቃሪው ድረስ ይጠጡታል ። በአንፃሩም ግብፃውያን የሰጠሙበት ኤርትራ እስከ እንጥፍጣፊው መጉደሉን ባለቅኔው አመስጥረዋል ።

*169 ግእዝ ጉባኤ ቃና/ስ*

*ካህን ጥርስነ ዘበትርጓሜሁ ደብተራ*
*ይጸነጽል ገብሰ ወያመረግድ ሽንብራ*



www.ethiopianorthodox.org

## ትርጉም

በትርጓሜው ደብተራ የሚባል ካህን/ጥርሳችን
ገብስን ይፀነፅላል ፤ ሽንብራንም ያመረግዳል ።

## ምስጢር

ካህን በንኡስ እንደሚፀነፅልና በአቢይ እንደሚያመረግድ እንዲሁም የሰዎች ጥርስ ገብስን ያመሽካል ፤ ሽንብራንም ያደቃል ይላሉ ባለቅኔው ። የተለያየ ደረጃ ያላቸው የዝማሬ አይነቶች ንኡስና አቢይ በተባለ ክፍል ተመድበው በፀናፅል ይፀነፀላሉ ።

*170 መበለት እኪት ባሕረ ኤርትራ*
*አስመጠመቶ ለፈርዖን ሽንብራ ።*

## ትርጉም

ክፉ መበለት/የኤርትራ ባህር
ፈርኦን/ሽንብራን አሰጠመችው ።

## ምስጢር

የኤርትራ ባህር ፈርኦንን እንዳሰጠመችው አንዲት መበለት አደራ አስቀምጭልኝ የተባለችውን ሽንብራ ጨርሳ በላቸው በማለት ባለቅኔው አደራ በላዋን ባልቴት በቅኔው ወቅሷል ።

## ታሪክ

አንድ የቅኔ ተማሪ በአንዲት መበለት ቤት በሰኔ ወር በልመና ያጠራቀመውን ሽንብራ በአደራ አስቀምጦ ወደ ትምህርት ቤቱ ሄደ ። በመስከረም ተመልሶ ቢጠይቃት ሽንብራውን ጨርሳ በልታው ተገኘች ። ስለዚህም አደራ ሰጪው ተማሪ ይህን ቅኔ ዘርፎባታል ይባላል ። ቅኔው የዋዜማ ቀጠፋ እንደሆነ ይነገራል ።

*171 ሥላሴ (989)አ*
*ዘአድማሱ ጀንበሬ (መልአክ ብርሃን)*



www.ethiopianorthodox.org

*ራብዓት እለ ሃ ሐ ኃ*
*ዘምስለ ኣ ዓ አኃቲሆን*
*አዋልደ ግእዝ ሔዋን በበአብያቲሆን ይንበራ*
*ኢይሑራ አብያተ እሞን ነገረ ይፍጥራ ፤*
*እንዘ ኢይሰምዓ ዘንተ እመ ከመዝሰ ገብራ*
*ወነገረ ሐሰት አስተሓወራ ፤*
*እስፍንቱ አብያት እለ ተመዝበራ?*
*ወእስፍንቱ ዘስሕተ ደብተራ?*

## ትርጉም

ፊደሎች እነ ሃ ሐ ኃ
እህታቸው ከሆኑት ከነ ኣ ዓ የሄዋን (ግእዝ) ልጆች ጋር
በየቤቶቻቸው ይቀመጡ ዘንድ
ነገርን ሊፈጥሩ ወደ እናታቸው ቤቶች አይሂዱ ፤
ይህን ሳይሰሙ እንደዚህ ቢያደርጉ ግን
የአሰት ነገርንም ቢያካሂዱ ፤
የተመዘበሩ ቤቶች ስንቶች ናቸው?
ደብተራስ የሳታቸው ስንት ናቸው?

## ምስጢር

ሴቶች የየቤታቸውን ስራ ትተው መንደር ለመንደር እየዞሩ ነገርን ቢያመላልሱ ትዳራቸው ይፈርሳል ስማቸውም ይጠፋል ። እንዲሁም ሶስቱ ራብእ "ሃሐኃ" እና ሁለቱ ራብእ "ኣዓ" ፊደላት ያለቤታቸው በግእዝ ግጥምና በቅኔ ቤት መምቻነት ገብተው ቢፃፉ የፅህፈት ታሪክ ይቃወሳል ፤ የድርሰቱም ምስጢር ይፋለሳል ። ስለዚህም ባለቅኔው ከላይ የተጠቀሱ ፊደላት ራብእና ግእዝ ሆሄ ስለማይለያይ ድምፃቸው ከጠፋ ብሎ በአንድ የግእዝ ግጥም እና በአንድ ቅኔ ግእዝና ራብእ እያደረጉ ቤት መምታት አይገባም ይላሉ ።

172 መወድስ (289)ኀ

*ይጸውዑ ሠርከ በጉባኤሆሙ*
*ኃያላነ ሰይፍ ነገሥተ እምቤተ ፋሬስ ወዛራ*

እለ ኢተቀጸሉ ሕዝብ ሰቆቃወ ኤርምያስ ጌራ ፤
አኮኑ ጎበ ተተክለ
ተግሣጸ ቃልከ ዘኢዮብ ደብተራ
እግዚአብሔር ጠለ ነከራ
ዘእሳተ ሰማይ አቈርከ በምድረ አማዒት ገሞራ!
ያስቆቅውሂ በእንቲአየ ምስለ መስቆቅዋን ሐራ
መኑ እምጸውዖሙ ለኤርምያስ ወለእዝራ
እስመ ለጸቃውዕ ሥጋየ ዕጉሥታረ ደዌ አምረራ
ወዕድሜ ዘወሀብከኒ ተፈጸመ በመከራ ።

## ትርጉም

በአመፀኛ የገሞራ ምድር የሰማይ
እሳትን የቋጠርህ እግዚአብሄር የድንቅ ጠል!
የኤርምያስ ልቅሶ /ጌራን (የራስ ቁር) ያልተቀዳጁ ህዝብ
የሰይፍ ሃይለኞች ነገስታትን
ከፋሬስና ከዛራ ቤት በሰርክ (ማታ) ጊዜ
በጉባኤያቸው ይጥሩ ፤
የኢዮብ ድንኳን/የቃልህ ተግሳፅ ከተተከለ ዘንድ ነውና ።
ስለኔም ከአልቃሾች ወታደሮች ጋር አብረው ያለቅሱ ዘንድ
ኤርምያስና እዝራን ማን በጠራቸው ፤
የማር ወለላ/ስጋዬን እሬት/ የስጋ ደዌ አምርሯታልና
የሰጠኸኝም እድሜ በፈተና ተፈፅሟልና ።

## ምስጢር

የሹመት አክሊልን ያላገኙ ወታደሮች አለቆቻቸውን በሚበልጧቸው ነገስታት ለማስጠራት የክስ ማመልከቻ ይዘው ይሄዳሉ ። ህዝቡም እየፀለዩና እያለቀሱ እንደኤርምያስ ካላዘኑላቸው በሰይፍ የሚሞቱ ነገስታት እግዚአብሄር የዛራንና የፋሬስን ጠብ ያዝዝባቸዋል ። ጠል በሳርና በቅጠል ጀሮ የሚንቆረዘዝ የውሃ ነጠብጣብ እንደሆነ እግዚአብሄርም የሰማይ እሳትን በአመፀኛዪቱ በገሞራ ምድር አዘነበ ። ድንኳን እንደሚተከልም በኢዮብ የስጋ ደዌ በሽታ የንብረትና የቤተሰብ እልቂት አመጣ



LAPSLEY / BROOKS FOUNDATION, INC.
N. GREENVILLE AVE. ST. 810
TEXAS 75081, USA

በት።

አዘንተኛ የቀጠሮ ልቅሶ ሲያስለቅስ ሙሾኞችን (አልቃሾችን) እንደሚጠራ ባለቅኔው ስለበሽታቸው የመላእክትንና የእነኤርምያስን ርዳታ ለማግኘት ተመኝተዋል ። እሬት የተቀላቀለበት የማር ወለላ እንደሚመር የባለቅኔው አካል በስጋ ደዌ ህማም ተለወጠ ። ልብስም እየተቀደደ እንደሚያልቅ የባለቅኔው ዘመን በፈተና አለፈ በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

*173 መወድስ (1005)አ*
*ዘተድላ (መምህር)*

ተድላ ዋሕዱ አምላክ አስተዋሐደነ ፥
አምጣነ ኵሎ ያጸግብ ደጃዝማች አበራ የማታ እንጀራ ፥
እዳመሆኔሰ ዘይት እመ ኢሐሰወት ግብራ
ደንገፀት አላጌ ፥ ወፈርሀት አረራ ፥
እስመ ጽድቀ ይነግራ
ሰማይ ወምድር አድያማቲሃ ለቦራ ።
እሳትሂ ነበልባላዊ የወገብህ ጥይት ገሞራ
ይሤለስ በወጨፎ ወይትዋሐድ በውጅግራ ፥
ወእስከ አፉሆን መልዓ ማያተ ምኒልክ ኤርትራ
መሳብክተ ፈረንጅ ሸጉጦችህ በበስድስቱ ያገምራ ።

## ትርጉም

አምላክ/ተድላ ዋህዱ አንድ አደረገን ፤
የማታ እንጀራ/ደጃዝማች አበራ ሁሉን ያጠግባልና ፥
ዘይት/እዳመሆኔ ግን ስራዋን ባታብል
አላጌ ደነገጠች አረራም ፈራች ፤
የቦራ ወረዳዎች/
ሰማይና ምድር እውነትን ይናገራሉና ።
ነበልባላሙ የገሞራ እሳት/የወገብህ ጥይትም
በወጨፎ ይሰለስና (ሶስት ይሆንና) በውጅግራ አንድ ይሆናል ፤
ስድስት ስድስቱን የሚችሉ የፈረንጅ ጋኖች/ሽጉጦችህም
የምኒልክ/ኤርትራ ውሃዎችን እስከ አፋቸው ሞሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ምስጢር

አምላክ ሁሉንም አዋህዶ (በአንድነት) እንደሚያስተዳድር ተድላ ዋህዱ ባእድንና ዘመድን ትንሽንና ትልቅን አይለዩም ። በአንድ መሶብ የተሰራ እንጀራ ተመጋቢዎችን ሁሉ በአንድነት ያጠግባቸዋል ፤ ደጃዝማች አበራም "ከፍትፍቱ ፊቱ" እንዲሉ በብሩህ ገፅታ ያስተናግዳሉ ። ዘይትም ዘይትነቱን እንደማያብል እዳመሆኔ ግብሯን ስትገብር ጊዜ አላጌ ልታመልጥ አልቻለችም ፤ አረራም ተብረከረከች ። ሰማይና ምድርም ተፈጥሯቸውን በተግባራቸው እንደሚመሰክሩ የቦራ አቆልቋዮች (ወረዳዎች) በደጃዝማች አበራ ትእዛዝ እማን ብለው ተዳደሩ ።

ሶስት ግብሮች (ነበልባል ፡ ፍም ፡ ብርሃን) እንዳሉት እንደገሞራ እሳት የሚንቀለቀለው ጥይታቸው በሶስት ጎራሽ ወጨፎና በአንድ ጎራሽ ውጅግራ ይተኮሳል ። የቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት ጋኖች ስድስት ፈጅ እንደሆኑና እስከ ከንፈራቸው በውሃ እንደተሞሉ ፤ በደጃዝማች አበራ እጅ ወደፈረንጅ የተተኮሱ የስድስት ጎራሽ ሽጉጣቸው ጥይቶችም ፋሽስቶችን በመግደል የአፄ ምኒልክን ፍላጎት አሟሉ ይላሉ ባለቅኔው ።

*174 መወድስ(295)ኅ*

*ካህን ቀላዋጭ ኢትናቅ ምጥዋ ነጋዴ ፤*
*ወኢትስደብ ካዕበ ገበራርተ አራሽ በበሬ ፤*
*አምጣነ ትትቀሰፍ አንተ በቀጠና ረኀብ ማሰሬ ፤*
*ወኢይኩን ሰማዕተ ሐሰት ኤልያስ ነገሬ*
*ናሁ እንበለ ፍሬ*
*በእሳተ ረኀብ ውዕዩ አኀዊከ ደቂቀ ቆሬ ።*
*አነሂ ሰማንያ አንድ መጻሕፍተ አበው ተምሬ*
*አመልክ በነጋዴ ወእሰግድ ለገበሬ ፤*
*እስመ እምዘደንቢያ አራሽ ወእምነጋድያን ዘትግሬ*
*እቀላውጥ አንድ እንጀራ ወእለምን ድርጎ ጥሬ ።*

### ትርጉም

ቀላዋጭ ካህን የምጥዋ ነጋዴን አትናቅ
ሁለተኛም በበሬ አራሽ ገበሬዎችን አትስደብ ፤
በራብ ቀጠና/ማሰሪያ አንተ ትገረፋለህና ፤
ኤልያስ/ነገሬም የአሰት ምስክርን እንዳይሆን
እነሆ (አሁን) ያለፍሬ
የቆሬ ልጆች/ወንድሞችህ በራብ/እሳት ተቃጠሉ ።
እኔም የአባቶች ሰማንያ አንድ መፃህፍትን ተምሬ
በነጋዴ አመልካሁ ለገበሬም እሰግዳለሁ ፤
ከደምቢያ አራሽና ከትግሬም ነጋዴዎች
አንድ እንጀራ እቀላውጣለሁና ፤ ድርጎ ጥሬም እለምናለሁና ።

## ምስጢር

ካህን ተምሬአለሁ በማለት በትምህርቱ ተመክቶ ነጋዴዎችንና ገበሬዎችን መናቅና መስደብ አይገባውም ። ነጋዴ የነገደውንና ገበሬ ያመረተውን ካላገኘ ወንጀለኛ በጅራፍ እንደሚገረፍ ካህንም በራብ ይሰቃያል ። የቆሬ ልጆች በእሳት እንደተቃጠሉ በራብ የሚንገበገቡ ካህናት ብዙዎች ናቸው ። የጎንደር ሊቅ እንኳን ሰማንያ አንድ መፃህፍትን አውቆ ከትግሬ ነጋዴና ከደንቢያ ገበሬ የእለት ጉርሱን የአመት ልብሱን ለማግኘት ከመከጀል አላመለጠም ። ስለዚህ ባለቅኔው "ካህናት ገበሬዎችን ማክበር ይገባቸዋል" ይላሉ(ዘሁል. 16፥1–35) ።

*175 ሣህልከ(296)ኅ*

*ዘድንቄ(አለቃ)*

*እፎኑመ ኮንኪ እንበለ ፍሬ*
*ደብረ ኀይል ወይንነ ምልዕተ ሐመልማል ዘማሬ !*
*እስመ አዕፁቅኪ ካህናት*
*ተመትሩ ከመ ኢይንግሩ ዘጻድቃን ፍካሬ ።*

### ትርጉም

ልምላሜ አዝመራን የተመላሽ
ደብረ ሃይል ወይናችን እንዴት ያለፍሬ ተገኘሽ !
ቅርንጫፎችሽ ካህናት
የፃድቃንን ምስጋና እንዳይነግሩ ተቆርጠዋልና

## ምስጢር

ቅጠሏ የተንሰራፋ ወይን ፍሬን የማያፈሩ ቅርንጫፎቿ ከተቆረጡ ልታፈራ አትችልም ። ደብረ ሃይል የተባለች የእንጦጦ ራጉኤል ቤተ


www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያን ካህናትም በሞት ስለተለዩ እነርሱ ይዘምሩ የነበረውን ዝማሬ ደብሪቱ አታገኘውም በማለት ባለቅኔው ጓደኞቻቸው መዘምራን በወጣትነት እድሜያቸው የተቀሰፉ መሆኑን ያስረዳሉ ።

*176 ግእዝ ጉባኤ ቃና ስ*

*ተከብቶ ኢክህለት ድንግለ ሙሴ ሀገር ፡*
*አኮኑ ተሐንጸት በመልዕልቴሃ ለደብር ።*

## ትርጉም

የሙሴ ድንግል መንደር መሰወርን
አልቻለችም ፡ በተራራ ላይ ተሰርታለችና ።

## ምስጢር

በተራራ ላይ የተሰራች መንደር መሰወርን እንደማትችል የቅድስት ማርያምም የዘር ሃረግ በዝቅተኛ ትውልድ የተገኘ አይደለም ፡ ነቢዩ እንባቆም ያያት የተራራም ምሳሌ ሆነች ። ተራራ ከፍተኛ ቦታ እንደሆነች ማርያምም በምእመናን ዘንድ ገነነች በማለት በቅኔው ተመሰጥሯል ።

*177 ግእዝ ጉባኤ ቃና(1022)አ*

*መና ክብር ርእስ ወዘካርያስ እግር*
*ሰማይ ሰልሞን ወዘርዐ ፍጡራን ምድር*

## ትርጉም

የክብር መና/ራስ ሰማይ/ ሰልሞን ነው ፡
ዘካርያስ/እግር ደግሞ የፍጡራን ዘርእ/ምድር ነው ።

## ምስጢር

እነሆ ራስና እግር እንደ ሰማይና እንደ ምድር ከፍተኛና ዝቅተኛ ሆነው በተፈጥሮ ተለይተዋል ። የእህል ዘርና በጣም ቅዝቃዜ የበዛበት በበረዶ የተሸፈነ ደጋማ ቦታም የተራራቁ ናቸው ። በአንፃሩም ለህፃኒቱ ለቅድስት ማርያም በመልአክ እጅ ከሰማይ የወረደው መናና የቤተ መቅደስ አስተዳዳሪው ዘካርያስ አልተገናኙም ። የእህል ዘር በበረዶ



በተሸፈነ ደጋማ ቦታ እንደማይዘራና ቢዘራም እንደማይበቅል መናው ለህፃኒቱ ለማርያም እንጂ ለዘካርያስ አልተሰጠም ። ራስ ከእግር ፣ ሰማይም ከምድር የራቁ እንደሆኑ መናም በመልአኩ እጅ ከዘካርያስ አጠገብ ወደላይ ሰቀቀ (ወደላይ ወጣ) ይላሉ ባለቅኔው (ስንክ. ታህሳስ 3) ።

*178 ዋዜማ (1037)አ*

*ዘአርአያ ወረታ (አቶ)*
*ለወለተ ንጉሥ ሐሴቦናዊ*
*ሕዋሳቲሃ ከረዩ ዐዘቅተ ቤተ ሄኖክ ደብር ፤*
*ወሰትዩ በሕፍነ አምሳል ዘኤልያስ ንስር ።*
*እንበይነ መብልዕሰ ከመ ኢትማስን ምድር*
*ኢይብላዕ ሥጋ መሐለ ዕፄ መቃብር ፡*
*ወፈቀደ ጸዊመ ለምዕር ።*

## ትርጉም

የእውነተኛ ንጉስ ልጅ
ሰውነቶች የሄኖክ/ተራራ ቤት ጉድጓድን ቆፈሩ ፤
በኤልያስ /አሞራ ምሳሌ/ እፍኝም ጠጡ ።
ስለመብል ምክንያት ግን ምድር እንዳትጠፋ
የመቃብር ትል ስጋ እንዳይበላ ማለ ፤
ለአንድ ጊዜም መፆምን ፈቀደ ።

## ምስጢር

ሰዎች የጉድጓድ ውሃን ለማውጣት በቤታቸው አጠገብ ያለች ምድርን እንደሚቆፍሩ የቅድስት ማርያም ሰውነቶች ሄኖክ ወደገባበት ቦታ ገቡ ። መንገደኞችም ውሃን በእፍኛቸው እንደሚጠጡ የማርያም ሰውነቶች እንደ ኤልያስ ሰውነት አረጉ ። አንድ ባለፀጋ ከስጋ መብል የተነሳ በሚሰራው ሃጢአት ነፍሱ እንዳትጠፋ "እንግዲህ በፆም ስጋ ብበላ እርም ያድርግብኝ" ብሎ በመፀፀት እንደሚፆም ፣ የሌሎቹን ሙቶች ስጋ የሚበላና የሚያጠፋ የመቃብር ትልም በማርያም አልተፈጠረም ፤ አካሏንም አላፈረሰውም ይላሉ ባለቅኔው (ስንክ. ነሃሴ 16) ።



www.ethiopianorthodox.org

*179 ዋዜማ (1042)ኅ*

*ተክለ ሃይማኖት እንበለ ሕግ*
*እፎኑ ወሰከ በዲበ ቆሙ ሐፂር*
*ክንፈ ለገቦ ወዕፀ ለእግር !*
*ባሕቱ ለይትርፍ እንተ ከመዝ ነገር*
*አምጣነ አልቦ ለስምዕ በኵሉ ብሔር*
*እምእግዚኡ ዘየዐቢ ግብር ።*

## ትርጉም

ተክለ ሃይማኖት ያለህግ
ክንፍን ለጎን ፡ እንጨትንም ለእግር
እንዴት ያለ ህግ በአጭር ቁመቱ ላይ ጨመረ !
ነገር ግን እንዲህ ያለው ነገር ይቅር ፤
ከጌታው የሚበልጥ አገልጋይ
በአገሩ ሁሉ ለምስክር የለምና ።

## ምስጢር

ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳለው "በአጭር ቁመቱ ላይ ትንሽ ቁመት መጨመር የሚችል" ሳይኖር ተክለ ሃይማኖት በፀሎት ቁመት ብዛት በተሰበረው እግራቸው ባእድ የእንጨት እግርን ፡ በግራና በቀኝ ጎናቸውም ክንፎችን አበቀሉ ። ክንፎችንም በማብቀላቸው "በአጭር ቁመቱ ላይ መጨመር የሚችል የለም በማለት ፈጣሪያቸው የተናገረውን ነገር አስተሃቀሩ (አቃለሉ) ይላሉ ባለቅኔው።

*180 ሥላሴ (1043)አ*

*ለልደተ ክርስቶስ ወማርያም*
*ስብሐተ ናዝልፍ ይሜህረነ መምህር*
*ወይመርሐነ መራሒ መዝሙር ።*
*ለአዳምሰ ዘተሠገወ እምድር*
*ዜናሁ ኅደጋነ በኅጺር ፤*
*ሶበሰ ይነውኅ አንቀጸ ነገር*
*በውስቴቱ እምተረክበ ነውር ።*



## ትርጉም

ለክርስቶስና ለማርያም ልደት
ምስጋናን እናዘወትር ዘንድ መምህር ያስተምረናል
መሪ/መዝሙርም ይመራናል ።
ከምድር ሰው የሆነ የአዳም ዜናን
ግን በአጭር ተውን ፤
የነገር አንቀፅ ቢረዝም ግን
በውስጡ ነውር በተገኝ ነበር ።

## ምስጢር

የዘፈን አቀንቃኝ ዘፈኑን እያቀነቀነ ተቀባዮቹን እንደሚመራቸው የኢየሱስ ክርስቶስ መወለድና የቅድስት ማርያም መወለድ አስቀድሞ በምሳሌና በትንቢት ተነግሮ ስለተፈፀመ እንከን የሌለበት ሆነ ። አንዳንድ አሳፋሪ ድርጊት ያለበትን ነገር አብራርቶ ከማቅረብ ይልቅ ሸፋፍኖ እንዲያልቅ ማድረግ በሽማግሌዎች ዘንድ የተለመደ ነው ። የሰው ዘር ሁሉ አባት የሆነው አዳምም አትብላ የተባለውን በለስን በልቶ ያመጣው ፍዳ(መከራ) ለልጆቹ ተረፋቸው ። ከዚህም የተነሳ የአባትነቱ ታሪክ የሚያስመሰግን አይደለም ። በማለት ባለቅኔው አዳምና ሄዋን የበለስን ፍሬ በመብላታቸው ምክንያት በሰው ልጆች ሁሉ ላይ ተወስኗል የሚባለውን የሞት ፍርድ በቅኔያቸው ምስጢር ያስረዳሉ ።

*181 ሥላሴ (1063)አ*

*ዘወልደ ማርያም ሀብቴ (አለቃ)*
*ሚጡ ንዋየክሙ*
*ወምጽዋተ ሀቡ ለነዳያን*
*ዜናዌ ተስፋ አብ ይብለነ በቃሉ ለደቂቀ ኅዘን መራር*
*የሀብክሙ መንግሥተ ዚአሁ አቡክሙ ኄር ።*
*ወአመ ተነደፍኩ በፍቅሩ ለንባበ ዝንቱ ምስጢር*
*ንዋይየ ሜጥኩ ለመቃብር*
*ወእምዘኒቦቱ ምጽዋተ እመ አበድር*
*ወሀብክዎ ምጽዋተ ለምድር ።*



www.ethiopianorthodox.org

## ትርጉም

የአብ አለኝታ ነጋሪ
በቃሉ ለመራራ አዘን ልጆች
"ቸር አባታችሁ የርሱን መንግስት ይሰጣችሁ ዘንድ
ጥሪታችሁን ሽጡና ለድሆች ምፅዋትን ስጡ" ይለናል ።

እኔም በዚህ ምስጢር ንባብ ፍቅር በተነደፍሁ ጊዜ
ገንዘቤን ለመቃብር ሸጥሁ ፤
ከመሰብሰቡም ምፅዋትን ብመርጥ
ምፅዋትን ለምድር ሰጠሁት ።

## ምስጢር

"ሃብታችሁን ሽጣችሁ ለድሆች መፅውቱ" ከተባለው ክርስቶሳዊ ቃል የተነሳ "ሲመፀውቱ አየሁ ብዬ ሌላ ባጣ ያለኝን ንዋይ ለምድር መፀወትሁ" በማለት ባለቅኔው ንዋይ የተባለ ልጃቸው ሞቶ መቀበሩን ለማስረዳት አዘናቸውን በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል።

*182 ሥላሴ (300)ጎ*

*ፀሐየ ዓለምነ ፈቅጦር*
*ዘይነዝኅ ለነ ፀዳለ ሰላም ወፍቅር*
*እስመ ምእራቢሁ አእመረ በቀትር ፡*
*ሎቱ ትብክዩ ታዖድራ በቃለ ሐዋዝ መዝሙር*
*ንሥኢ ቃለ እምኢያዜር*
*እንዘ ትብሊ አንቲ ብሂለ ነገር*
*ዋይ ! ዋይ ! ዋይ! የወርቁ ሚዛን ተሰበረ ወየው እኔ ልሰበር ።*

## ትርጉም

የአለማችን ፀሀይ ፈቅጦር
የሰላም የፍቅርን ብርሃን የሚፈነጥቅልን
መግቢያውን በቀትር አውቋልና ፡
ታአድራ በመልካም መዝሙር ለሱ ታለቅሽ ዘንድ
አንቺ ወየው ! ወየው ! ወየው ! በማለት ነገር
ከኢያዜር የልቅሶ ቃልን ተማሪ ።



## ምስጢር

የፀሃይ ብርሃን በአለም ላይ እንደሚሰራጭ የጎንደሩ ንጉስ ፈቅጦር በሰላምና በፍቅር ያስተዳድሩ ነበር ። ፀሃይ በምስራቅ ወጥቶ በምእራብ እንደሚገባም ንጉሱ በወጣትነት ዘመናቸው በሞት ተቀስፈው ወደመቃብር ወረዱ ። ስለዚህ ንግስቲቱ ታአድራ ኢያዜር በምትባል በአልቃሽ ወፍ ዜማ ልታለቅስላቸው ይገባል ። ወርቅ በሚዛን እንደሚመዘን "በወርቅ ልብስ የተንቆጠቆጠው ንጉስ አየ ጉድ ! አየ ጉድ ! ሞተ ? ምነው እኔ በሞትሁ !" በማለት ደራሲው በቅኔያቸው ምስጢር የአፄ ፈቅጦርን ሞት አሳዛኝነት ያመለክታሉ ።

*183 ሥላሴ (301) ጎ*
*በድንግል ድኅረ አመንከ*
*ኍልቍ ሰብአ እመ ትቀኒ*
*ፍቱነ ጊዜያት ሀብታት ሰብዓቱ ተክለ ጊዮርጊስ ብሩር*
*እስከነ ተዐውቀ ጽርየትከ ፍቅር ፤*
*እስመ እመ ይቤ ለይኩን ፈጣሪ መላእክተ ሰማይ ወምድር*
*ይትቀነዩ ለከ አርአያ ገብር ፡*
*ወለእመ ይቤ ኢይኩን እግዚአብሔር*
*ይዔምፁ አእዳው ወእግር ።*

## ትርጉም

ጥራትህ /ፍቅር እስከታወቀ
በሰባት ጊዜዎች/ ሃብቶች
የተፈተንህ ተክለ ጊዮርጊስ/ ብር ! በድንግል ካመንህ በሁዋላ
ብትገዛ ሰውን እንደ ከንቱ ቁጠር ፤
ፈጣሪ ይሁን ቢል የምድርና የሰማይ መላእክት
በአገልጋይ አምሳል ይገዙልሃልና
እግዚአብሄር አይሆንም ካለ ግን
እጆችና እግሮች ያምፃሉና ።

## ምስጢር



www.ethiopianorthodox.org

ወርቅ ጥሬ፡ እስኪታወቅ ድረስ በእሳት እንደሚፈተን መንግስታቸው እስኪደላደል ድረስ ፈተና የተቀበሉ ከአፄ ቴዎድሮስ ቀጥሎ የነገሡ አፄ ተክለ ጊዮርጊስ ናቸው ። ኢትዮጵያን ሲገዙ በቅድስት ማርያም ካለቻው እምነት የተነሳ ጠላታቸውንና ወዳጃቸውን ለይተው ከማወቅ ደረጃ መድረሳቸው በቅኔው ምስጢር ተገልጧል ። አምላክ ከፈቀደ የማይገዙለት ይገዛሉ ካልፈቀደም የሚገዙት እጅና እግር እንኳ አይታዘዙም ፤ (አይገዙም) በማለት ባለቅኔው በእምነታቸው እንዲፀኑ አፄ ተክለ ጊዮርጊስን ይመክራሉ ።

*184 ሥላሴ (303) ጎ*

*ኤልያስ በተአንግዶ*
*እሙሴ ኢትስአል ማየ ሕይወት*
*እስመ ለሙሴ ዕሙቅ ዐዘቅቱ ፡ ወህየንተ ኅብስት ሥሙር*
*ይሁበከ መቃብረ ዕፄ ፍሬሃ ለምድር ።*
*ወኢትኅየጥ ትድምርተ ዘኬፋ በዔጠ ጳውሎስ ፍቅር ፡*
*አመ ይየውሁከ ላዕለ ደብር*
*እስመ ቦ ለኬፋ ዘራዔ ምስጢር*
*ቁልቁሊተ ዘየወርድ ምክር ።*

## ትርጉም

ኤልያስ በእንግድነት
ከሙሴ የህይወት ውሃን አትለምን ፤
የሙሴ አዘቅቱ ጥልቅ ነውና ፡ ስለተወደደ እንጀራ ፈንታም
የምድር ፍሬ የሆነ የመቃብር ትልን ይሰጡሃልና ።
የጴጥሮስ አንድነትንም በጳውሎስ ዋጋ ፍቅር አትግዛ ፡
በተራራ ላይ ቢያሞኝህ
ምስጢርን ለሚዘራ ጴጥሮስ
ቁልቁል የሚያወርድ ምክር አለውና ።

## ምስጢር

ጠላት ያለበት ሰው በመብልና በመጠጥ ከሚደረግ መርዝ እንደሚጠበቅ ፡ ነቢይ ኤልያስ ከነቢይ ሙሴ ጋር ሲኖር የሙሴ መቃብር



እንዳያገኘውና በእንጀራ መስተንግዶም ፈንታ ሙሴ የመቃብር ትልን እንዳያቀርብለት መጠንቀቅ ይገባዋል ይላሉ ባለቅኔው ። ደግሞ አንዳንድ አታላይ ሰው ብረቱን ብር አስመስሎ እንደሚያሞኝና ምክሩም ቁልቁል እንደሚያወርድ ፡ ኤልያስም ከጴጥሮስ ጋር ቢኖር እንደ ጴጥሮስ ተዘቅዝቆ መስቀል ይመጣበት ነበር ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

*185 ዘይእዜ (1065) አ*
*ዘገብረ ማርያም (መምህር)*

*ዘመን ኀልቀ ወተፈጸመ ፡*
*ክልኤቱ ደቂቅ ልብሰ ተክለ አብ ወእግር*
*እስመ ይብሉ ቅድመ ዐበይቶሙ ሱራፌል ማኅበር*
*ንትናገር ንሕነ ፡ ንሕነ ንትናገር ፡*
*ወእንዘ ሀሎ እግዚእ በዐለ መንበር*
*ፍትሐ ቀራንዮስ ፈትሐ ልሳነ አይሁድ ገብር*
*ወእንዘ ሀሎ እግዚእ በዐለ መንበር ።*

## ትርጉም

ዘመን አለቀ ተጨረሰም ፡
የተክለ ሃይማኖት ሁለቱ ልብስና እግር /ልጆች
በሚበልጧቸው ሱራፌል/ ማህበር ፊት
"እኛ እንናገር ፡ እኛ እንናገር" ይላሉና ፡
ባለዙፋን ጌታም ሳለ
የቀራንዮ ፍርድን የአይሁድ አንደበት/ አገልጋይ ፈርዷልና ።
ባለዙፋን ጌታም ሳለ

## ምስጢር

"በስምንተኛው ሺህ ልጆች ሽማግሌዎችን አያናግሩም ዳኞቹንም አያስፈርዱም" እየተባለ እንደሚነገር የፃድቁ ተክለ ሃይማኖት ልብስና እግር ከመላእክት ፊት አመሰገኑ ። በፍጥረቱ ሁሉ ላይ በሚፈርድ ጌታ ላይም የፈጠራቸው አይሁድ መስቀልን ፈረዱበት ይላሉ ባለቅኔው ።

*186· መወድስ (1102)አ*

*ዘፈንታ ገብርዬ (መልአከ ብርሃን)*
*አአድባር ዘኢትዮጵያ*



www.ethiopianorthodox.org

*ዘእንዘ እምትካት አንትሙ ገጸ ቅድምናክሙ ነነፍር ፡*
*አዳም ማርቆስ ደኃራዩ ፍጥረት ምክር*
*ተመይጠ ላዕለ ዘቀዲሙ ፍጥረታት አድባር ፡*
*እስመ እመ ይቀድም ተነ ጢስ*
*እምአፍራሰ እሳት ወነድ ከመ ነድ ኢይትፈቀር ፡*
*ካዕበኒ እምአቅርንቲሁ እንዘ ቀዳሚ ፍጡር*
*ነጌ ነቢየ አፍአ ከመ አቅርንቲሁ ኢይከብር ።*
*ወእንዘ ብሩር ወወርቅ ቀደምተ ኪነት ወግብር*
*ወርቅ ደኃራዊ ላዕሌሆሙ ይነብር ።*

## ትርጉም

የጥንት ስትሆኑ ፊት
ቀዳሚነታችሁን የምናፍረው የኢትዮጵያ ደብሮች ሆይ !
የፍጥረት /ምክር ሁዋለኛ አዳም/ ማርቆስ
በቀድሞ ፍጥረቶች /ደብሮች ላይ ተሾመ ፡
የጢስ ብናኝ ከእሳትና
ከነዲድ ፈረሶች ቢቀድም እንደነዲድ አይወደድምና ።
ሁለተኛም ከቀንዶቹ የቀደመ ፍጡር ሲሆን
ዝሆን የውጭ ነቢይ እንደ ቀንዶቹ አይከብርምና ።
ብርና ብረትም የብልሃትና የስራ መጀመሪያዎች ሲሆኑ
ሁዋለኛ ወርቅ በላያቸው ላይ ይቀመጣልና ።

## ምስጢር

ፊታቸው የሚታፈርና ነገራቸው የስመረ አዛውንቶች ሳሉ የሁዋለኛው ፍጥረት (ልጅ) በሽንጎ ነገር "እኔ ልቅደም" እንደሚል የጎጃም ደብር የደብረ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን የተሰራና የተደበረ በሁዋላ ሲሆን ቀደም ብለው ከተሰሩትና ከተደበሩት ከጎጃም አድባራት በላይ ሆኖ ከበረ ። ቀድሞ የሮጠ ሁሉ የውድድሩ አሸናፊ ካልሆነ በተመልካቹ ዘንድ ከበሬታን አያገኝም ። የጢስ ብናኝ እንደ እሳቱ ፡ ባለቀንድ ዝሆንም እንደ ቀንዱ ስለማይከበሩና ብርና ብረትም በጥበበኛ በመሰራት ቢቀድሙ ፡ ወርቅ በሁዋላ መጥቶ በላያቸው ላይ ይፈስባቸውና ይሸፍናቸዋል ። የደብረ ማርቆስም ቤተ ክርስቲያን በሁዋላ መሰራቱ ከቀደሙት አድባራት በታች እንዲሆን አያደርገውም በማለት ባለቅኔው መከበር በመቅ



ደም አለመሆኑን በቅኔያቸው ያስረዳሉ ።

*187 መወድስ (1078)እ*

*ዘተክለ ጽዮን (አለቃ)*

*ለእመ ብሁላን አህጉር ደብረ ሊባኖስ*
*ሑረታቲሃ ነዮሙ ማዕከለ ሥጋዌ ምስጢር ፤*
*እሳተ እደ ቶማስ ቃል አምጣነ ምስለ ደም ድሙር ።*
*አንቲሰ ባቢሎን እኅተ ሞዓብ*
*ሰማየ እመ ተለዐልኪ እምራኅባ ለምድር*
*ኀፍረት ለነጊር*
*ሕገ ቤትኪ ገለዓድ ከንቶ ዘይትጌበር ።*
*በግብጽኒ በትረ ባሕሩስ ወወልታ ዕኑዕ ኀሳር*
*ሀለወኪ ትትኀፈሪ ከመ ተኀፈርኪ በአሦር ፡*
*አምጣነ ጽግብት አንቲ እምተዐብዮ መሪር*
*እንዘ ኢሀሎ ዘይጸግቦ ለቃለ መጽሐፍ መዓርዒር ።*

## ትርጉም

የባለፀጉች አገሮች እናት ደብረ ሊባኖስ
አካሄዶቿ በቃል ሰው መሆን /ምስጢር መካከል ናቸው ፤
የቶማስ እጅ እሳት /ቃል ከደም ጋር አንድ የሆነ ነውና ።
ግን አንች የሞአብ እህት /ባቢሎን!
ከምድር ስፋት ወደሰማይ ብትመጥቂ
ከንቱን የሚሰራ
የገለአድ /ቤትሽን ህግ ለመናገር ሃፍረት ነው (ያሳፍራል ) ።
የመቃ በትርና የፅኑ ውርደት ጋሻ በሆነ በግብፅም
በአሶር እንደአፈርሽ ታፍሪ ዘንድ አለሽ ፤
ጣፋጭ የመፅሃፍ ቃልን የሚጠግበው ሳይኖር
ከመራራ መታበይ የጠገብሽ ነሽና ።

## ምስጢር

የባለፀጎች እናት እርምጃዎች በዝግታ እንደሚፈፀሙ የሃገሮች እናት የሆነች የደብረ ሊባኖስ ትምህርቶች በክርስቶስ ሰው መሆን ላይ ያተኮሩ ናቸው ። የእግዚአብሄር ቃል እግዚአብሄር ወልድ የሰውን ስጋ እንደተዋ



www.ethiopianorthodox.org

ሀደ የቶማስን እጅ አቃጠለው የሚባለው እሳተ መለኮት የስጋውና የደሙ ባህርይ ነው ፡ ስለዚህ ከሃጢአት ሳይነፁ በድፍረት የሚቀበሉትን ያቃጥላቸዋል ። ባቢሎን ከተሰጣት ህግ ወጥታ ወደላይ ብትንጠራራ ወደታች ወርዳ እንድትንከታከተችና ታሪኳም አሳፋሪ እንደሆነ ፡ ከባለቅኔው ባህል ውጭ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን እርሷው ራሷ ብትሮክር ብትመፃደቅና ብትሞገስ ትምህርቷ ተጨባጭ አይደለም ።

አንዳንዱ ሰው "የእገሌ ነገር ቢከፋቱ ተልባ ነው" በመባል እንደሚታማ የሸሹ ሰዎች መደበቂያ በነበረች በገለአድ የተመሰለው ባለቅኔው የሚቃወሚት ቤተ ክርስቲያን ህግም ከንቱ ነው ። በዚህም ላይ በአሶር የተዋረደችው ባቢሎን አነስተኛና አሳረኛ በሆነች ግብፅም እንደተዋረደች ፡ እንዲሁም ይህቺው ቤተክርስቲያን በግብፅ ቤተ ክርስቲያን ህግና ስርአትም ትረታለች ። ምክንያቱም ገና የሚድህ ልጅ የማይጠግበውን ጣፋጩን ነገር አልፎ መራራውን እንደሚቀምሰው ፡ እርሷም ተጨባጩን ያመፅሃፍ ቃል በቀጥታው በመተርጎም ፈንታ በማጣመም ስለምትተረጉመው ነው በማለት በባቢሎን አንፃር በተመሰጠረው ቅኔያቸው ከእርሳቸው በባህል (በትምህርተ ሃይማኖት) የተለዩ ሊቃውንት የሚገኙባትን ቤተ ክርስቲያን ባለቅኔው ነቅፈዋል (ዘፍጥ11፡ 1-9) ።

*188 መወድስ (1079)አ*

*ዘተክለ ጻዮን (አለቃ)*

*መኑ የሀቁር ውስተ ከርሠ ሐፅኑ*
*እሳተ ገሞራ ረኀበ ዘበማይ ኢይቈርር*
*እንበሌየ ሊተ ለእክብዶ ንዴት ፆር?*
*ወሊተ እንበሌየ*
*ሐንካስ መኑ ወመኑ ዕውር ?*
*አምጣነ ፍና ኢየሐውር ፡*
*ወኢይሬኢ ብርሃነ እንዘ ሰብአ ዐይን ወእግር ።*
*ሊተሰ ይኄይሰኒ ከመ አልዓዛር*
*እምእንበር ኀበ አፍአ በዊአ ቤትየ መቃብር*
*ወመሬተ እባእ ከመ ወፃእኩ እምድር ፡*
*አምጣነ ዕቡረ እከውን ከመ ተፈጠርኩ እምዕቡር ።*



## ትርጉም

ለእኔ ችግር /ሽክምን ለማክበድ ከእኔ በቀር
በውሃ የማይቀዘቅዝ የገሞራ እሳት/ ራብን
በሆድ /ጭኑ ውስጥ ማን ይቋጥራል? (ይችላል?)
ለእኔ ያለእኔስ
አንካሳ ማነው? እውርስ ማነው?
መንገድን አልሄድምና ፡
የአይንና የእግር ሰው ስሆን ብርሃንን አላይምና ።
ለእኔ ግን በውጭ ከምኖር
እንደ አልአዛር ወደቤቴ/መቃብር መግባት ይሻለኛል
ከምድር እንደወጣሁም ወደመሬት ልመለስ ፤
በጭቃ እንደተፈጠርሁ ጭቃን እሆናለሁና ።

## ምስጢር

እሳትን በጭኑ ውስጥ መያዝ የሚቻለው እንደሌለ እንዲሁም ለማንኛውም ፍጡር እንደእሳት የሚያንገበግብ ራብን መታገስ አይቻልም። በቀትር ጊዜ የተነሳ የሰደድ እሳትን በውሃ ማጥፋት እንደሚያስቸግር ራብም ውሃ በመጠጣት ብቻ አይመለስም ። አንዳንድ ግምት የማያውቅ ተሸካሚ ከአቅሙ በላይ እንደሚሸከም ባለቅኔውም በችግር ላይ ችግርን በመቀበል ሲራቡ ኖሩ ። ባለቅኔው እግር ለመሄድ አይንም ለማየት እያላቸው እግርና አይን እንደሌላቸው እንደ አንካሳና እንደ እውር በአንድ ቦታ ሆነው ራቡን በል በለኝ ይሉታል ። ከዚህም የተነሳ "ውሎ ውሎ ከቤት ኖሮ ኖሮ ከሞት" እንዲሉ ባለቅኔው በቅኔያቸው ምስጢር በራብ አለንጋ ከመገረፍ ይልቅ የማይቀረውን ሞት ሞቶ መቀበርን ተመኝተዋል።

*189 መወድስ (1080)አ*

*ጸላኢ ይበኪ በከናፍሪሁ*
*ወበአፉሁ ያስቆቁ ፡ ሰይፈ ልቡና ነገር*
*ውስጠ ውስጠ እንዘ ይመትር*
*ፍቅረ ወሰላመ*
*ከመ ገብረ ልቡ ለኢዮአብ ፀር*
*ማእከለ አቢሳ ወአበኔር*



www.ethiopianorthodox.org

እንዘ በእዴሁ እትገዝ ሰይፈ ሐፃውንት በትር ፤
ወዳዊት ኤፍራታዊ እንዘ በልቡ ክቡር
ሞተ አቤሴሎም ይጸልእ ወሞተ አርዮ ያፈቅር
ነገረ ብካይ አርአየ ለዘሀለው ማኅበር
በይነ አቤሴሎም በልቡና ወበይነ አርዮ በከናፍር ።

## ትርጉም

ጠላት በከንፈሮቹ ያለቅሳል
በአፉም ይንሰቀሰቃል ፤ የልብ ሰይፍ/ ነገር
ውስጥ ውስጥን እየቆረጠ
የኢዮአብ /ጠላት ልብ
የብረቶች ሰይፍ/በትር በእጁ
የተያዘ ሲሆን በአበኔርና
በአቢሳ መሃል ፍቅርንና ሰላምን እንዳደረገ ፤
የኤፍራታ ሰው ዳዊትም በክበረ ልቡ
የአቤሴሎምን ሞት ሲጠላና የአርዮን ሞት ሲወድ
በልቡ ስለአቤሴሎም ፣ ስለአርዮም በከንፈሮቹ
የልቅሶን ነገር ለአሉት ማህበርተኞች እንዳሳየ ።

## ምስጢር

ቢላዎ ውስጥ ውስጡን እያረደ ላይ ላዩን ቆዳን ይገፋል ። “የጠላት መሳም ከመንከስ ቁጥር ነው” እንዲሉ አንዳንድ ሰው በስውር ጠላቱ ላይ ችግር ሲደርስበት በሁኔታው እየተደሰተ ፣ ለሰው ይምሰል ከንፈሩን እየመጠጠ ሳቅ አስተኔ ልቅሶ ያለቅሳል ። ይሄውም ይታወቅ ዘንድ የእስራኤል ንጉስ የነበረው የዳዊት የጦር አለቃ ኢዮአብ አቤሴሎምን ለመግደል ቁርጠኛ ሆኖ ሳለ ለታዛዦቹ ለአቢሳና ለአበኔር ይምሰል አምጡት አልነካውም አለ ። ዳዊትም በምስጢር አርዮ እንዲገደል ያዘዘ ሲሆን እንዳላዘዘ ሆኖ እንዳይገደል ያዘዘለት የልጁ የአቤሴሎምን ያህል ለአርዮም ከአንገት በላይ ለሰራዊቱ ይምሰል አልቅሷል ይላሉ ባለቅኔው (2 ሳሙ. 11–12፣18፣6–33) ።

*190 መወድስ/ስ*

*ዘኪዳናት ወልደ ሩፋኤል (መምህር ፣ ዘጽላሎ)*



ዘመዱ ለሰብእ እግዚእ ምናሴ
ወአልቦ ካልእ ዘመድ ወማኅፈር ፤
ተዘምዶተ ሰብእ ዘኬዎስ እስመ ውእቱ ኅጺር
ወምሉዕ አኮ ፍቅረ ሰብእ ባሕር
ለእመ ፍቅረ ሰብእ ንዜክር
ወእመ ናስተሐይጽ ንሕነ ገጸ ተዘምዶቱ ለሰብአ ምድር ።
ለሰብእሰ መሬታዊ ተዘምዶተ ሰብእ ፍጡር
አመ ውስተ ምድርነ ይበቁዖ ወያሐይዎ ጊዜ ኀሣር
ለበዓለ ዘመድ ሮቤል በኩረ ዘርዐ ያዕቆብ ኄር
እምኢተረክበቶ ሞተ ሥጋ ወኢበልዐቶ መቃብር ።

## ትርጉም

የሰው ዘመዱ የምናሴ ጌታ ነው
ሌላ ዘመድና ወዳጅም የለውም ፤
የሰው መዘመድ/ ዘኬዎስ አጭር ነውና ፣
የሰው ፍቅር/ ባህርም ሙሉ አይደለምና
የሰው ፍቅርን ብናስብ
የምድር ሰው መዘመድ/ፊትንም ብንመለከት ።
ለመሬታዊ ሰው ግን የፍጡር ሰው መዘመድ
በምድራችን ቢጠቅመው ፣ በመከራም ጊዜ ቢያድነው
የደገኛ ያእቆብ ዘር በኩር የሆነ ባለዘመድ ሮቤልን
የስጋ ሞት ባላገኘችው ነበር ፣ መቃብርም ባልበላችው ነበር ።

## ምስጢር

ዘኬዎስ የተባለ ሰው ቁመቱ በጣም አጭር (ድንክ) እንደነበረ ፡ ሰው በስጋ ትውልድ ቅርበት የሚመሰርተው ዝምድና ዘላቂ ባለመሆኑ የሰው የማይለወጥ ዘመዱ የእስራኤል ንጉስ የነበረው የምናሴ አምላክ ነው ።

አንዳንድ ባህር ወይም ሃይቅ በድርቅ ዘመን ሲጎድል በዝናብ ጊዜም ጢም ብሎ ሲሞላ በየወቅቱ የተለያየ ሁናቴ ይታይበታል ። እንዲሁም በመስታዎት መልክን ማየት እንደሚቻል የሰውን ዝምድና ብንመለከትና ብናስታውስ የሰው ዝምድናም በፍቅር ጊዜ የሚቀርብ በጥል ጊዜም የሚርቅ ይሆናል ።



www.ethiopianorthodox.org

ከሰው ጋር መዛመድ ለሰው የሚጠቅመው ቢሆን ኖሮ አስራ አንድ ወንድሞችና ብዙ ወገን የነበረው የያእቆብ ልጅ ሮቤል ሞትና መቃብር ባላገኙት ነበር በማለት ባለቅኔው በዘመድና በወገን ብዛት ከመመካት ይልቅ እግዚአብሄርን ዘመድ አድርጎ በእግዚአብሄር መመካት እንደሚገባ ብቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል (ዘፍጥ·29 ፥46) ።

191· መወድስ (1081) አ

ኢየሱስ ክርስቶስ ነግደ ተሠግዎ
ዘአብጽሐከ ዕለት ውስተ ቤተ ሥጋ ኀሡር
እንዘ ሕፁረ ነድ ምውቅ ቤተ አቡከ መንበር ፡
እፎ ኀደርከ ከመ ሰራቂ
በመስቀል አፍአ ዘአልቦ ሕፁር
ምስለ አራዊት ውሉደ ነውር?
ወእፎ ኀጣእከ ምጽላለ ጥዒና ምሉአ ስዝር?
እንዘ አንተ ታወርሶሙ ብሔረ ጥዒና መንክር
ዘይሔድም አርአያሁ ወልምላሜሁ ዘይትፌቀር
ለዕውረ እግር ሐንካስ ወለሐንካሰ ዐይን ዕውር
እምሐዊረ ፍና ገጸ ብእሲ ወእምነጽሮ እግር ፍና ብሔር ።

## ትርጉም

በጎስቋላ ስጋ ቤት ውስጥ ቀን ያደረሰህ
ሰው የመሆን እንግዳ ኢየሱስ ክርስቶስ
የአባትህ ቤት /ዙፋን በሞቀ ነዲድ የታጠረ ሲሆን ፡
እንዴት እንደ ሌባ አጥር
በሌለው መስቀል/ እዳሪ ከነውር
ልጆች/ አውሬዎች ጋር አደርህ?
ስንዝር ሙሉ የሆነ የጤና መጠለያንስ እንዴት አጣህ?
መንገድ የሰው ፊትን ከመሄድ እግሩ
ለታወረ አንካሳና ፡ እግር የእግር መንገድን
ከማየት አይኑ ለአነከሰ እውር
የሚያስደንቅ ጤና/ እግርን አንተ ስታወርሳቸው ።

## ምስጢር



**አንድ** ባለፀጋ ከሞቀ ቤቱ ወጥቶ በእንግድነት በውጭ ሲያድር **አሽከሮቹ** “**እዩ** ጉድ ቤትን ይዘውት አይሄዱ! እገሌ እንኳ ያን መሳይ ቤት **እያለው እውጭ** አደረ” ይባባላሉ ። እግዚአብሄር ወልድም በባህርዩ **እሳታዊ ሲሆንና** የዙፋኑ ተሸካሚዎች ኪሩቤልም እሳታውያን ሲሆኑ “**በአምስት ቀን** ተኩል” ተብሎ በእለት ምሳሌ በተነገረው ትንቢት **መሰረት አምስት** ሽህ ከአምስት መቶ ዘመን ሲሞላ ሰው ሆኖ ከቅድስት **ግርያም ተወለደ** ። ከሁለት ሽፍቶች ጋርም እንደወንጀለኛ በመስቀል **ተሰቀለ** ። **ያንድ** አገር መሪ ታማኞች አገልጋዮችን ያገር አስተዳዳሪዎች **እንደሚያደርጋቸው** ክርስቶስ ለእውሩ አይኑን ያበራለትና ለአንካሳውም **እግሩን ያረታለት** (ያቃናለት) ከሆነ እንደወንጀለኛ በመስቀል መሰቀል **አይገባውም** ነበር ይላሉ ባለቅኔው ።

192 መወድስ(1087) አ

**ቀቲል** ኦርዮ ግፉዐ ዕዐለተ ዳዊት
**መዘምር** ሕዝቡ ለሴት በአዋልደ ቃየል ነውር ፤
**እስመ** ከመ ይምሐሉ ሠምሩ በጸውዖ ኤርሞን ደብር ።
**ነባቢሰ** ቃል ሶበ ነበበ
**እግረ** ልብ ብእሲ ኢያዕቅፍ ነገር
**እስመ** ሆሴዕ በጎሜር
**ዘየ ዘመወ** መንገለ ዘመወት ምድር
**ኢኀደገት** ምትናሁ ብእሲተ ጻድቃን ምግባር ፤
**እምግን** ኵሉ ይትፌቀር በጊዜሁ ወኢበጊዜሁ ኢይትፌቀር ፤
**በረምኒ** ስሑል ቀቲለ አጋግ ነኪር
**ኢያስተዋደዮ** ለሳሙኤል መንገለ እግዚኡ እግዚአብሔር ።

## ትርጉም

**የተገፋ ኦርዮን** መግደል የዳዊት መሰደቢያ ነው
**በቃየል ልጆች** የሴት ህዝብ መሰሰንም ነውር ነው ፤
**ኤርሞን** የተባለ ተራራን በመጥራት ይምሉ ዘንድ ወደዋልና ።
**ተናጋሪ ቃል** ግን በተናገረ ጊዜ
**ነገር የሰው** ልብ እግርን እንዳያነቅፍ
**ሆሴእ ምድር** በሰሰነችበት



www.ethiopianorthodox.org

ወዚያ በትግሬ በለሰን ጊዜ
የፃድቃን ሴት ምግባር ባለቤቱን አላተወችም ፡
ሁሉ በጊዜው ይወደዳልና ፡ ያለጊዜውም አይወደድምና ፡
በተባለ ጦር ልዩ አጋግን መግደልም
ሳሙኤልን ከጌታው እግዚአብሔር ዘንድ አላላመውምና (አላማላውምና)።

## ምስጢር

ተሸክሸኮ የተሰራ ልብስ የሸማኔው መልደይ እንደሆነ መግደል የማይገባውን ንጉሥ ሰው አርዮን የፃዊት ግልጋል የንጉሥነቱ መነተፊያ ሆነበት ። ምክንያቱም የአርዮን ግልት በርካሽ ወደ በፈለ ዝሙት መግደል ያለበት ወንጀለኛው እርሱ ራሱ ዳዊት ሲሆን ፡ "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" እንዲሉ ሚስቱን ተቀማ ህይወቱን አስጠፍቶ በበደል ላይ በደል ስለፈፀመበት ነው ።

የእግዚአብሔር ልጆች የተባሉት የሴት (ሴት የአዳም ልጅ) ወገኖች መልከ መልካሞቹን የቃየልን ሴቶች ልጆች በማየት በዝሙት ተነድፈው አንዳንድ ሰዎች "ተራራ ተንዶ ይጫነን" ብለው እንደሚሉ ከአርሞን ወርደው ከቃየል ሴቶች ልጆች ጋር በዝሙት ስራ ተባበሩ ።

ደግሞ አንዳንድ ትእግስተኛ ሴት ባሏ በምትሰስን ሴት ቢታማ ትም ሐሜቱን (እውነት) ብላ ተቀብላ ባሏን እንደማትፈታው የአምላክ ቃል (ሲሰኛዩቱን) ትጫርን እንዲያገባት ለሆሴእ ነገረው ። እርሱም በታዘዘው መሰረት ቢያገባት የእውነተኛነት ስራ አልተለየችውም ፡ የፃድቅነቱም ዋጋ አልቀረችበትም ። የሚጠላው የሚወደድበትና የተወደደው የሚጠላበት ጊዜ ስላለ በተባለ ጦር የሳሙኤል አጋግን መግደልም በአምላክ ዘንድ ሳሙኤልን አስወደደው እንጂ አላስነተፈውም ይላሉ ባለቅኔው (1ሳሙ.15 ። ሆሴ. 1፡3-9 ፤ 3፡ 1-3) ።

193 መወድስ (1093) ሌ
ዘዘወልዱ (ለሲታ)
ሆሉ ይሰላሕ በስብሐተ ዕዝራ
ልሳነ ዘሰግዩ አዕዋፍ ወልሳነ አራዊት ዘምድር ፡
ሞተ ሕግንምአ ጸድቅ እስመ ተናገረ ንበር ፡
ወአግብአ ሎቱ ለኤርምያስ በኩር



መዋቲ እመ ታብር
ወበግዜ ናኅ ያፍ መጋቤ ኤልያስ መፈከር ።
ናላዊ ላሕምኒ እንበሳ ኀይል ወናላዊ በግዕ ነምር
እንዘ ለትዱላን እግዚአብሔር በከመ ፈቀደ ይትገበር ፡
ባሕረ አናንያ አሳት እስመ የውሕዝ ለባሕር
ወልሳነ ወርቅ ይፀልያ ለእሳት ከመ ግዕር ።

## ትርጉም

የሰማይ ወፎች ቢሆኑ ፡ የምድር
አራዊትም ቢሆኑ ሁሉ በዕዝራ ምስጋና ይመሰገናል ፡
የፃድቅ ህግንምእ ሞትን አሞራ ተናገሯልና ፡
ለበኩር ኤርምያስም ጊችን
ከመታብር መለሰለታልና
ናህን የሰደለ ወፍም ተርጓሚ ኤልያስን መጋቢ ነውና ።
የኃይል አንበሳ የላም እረኛ ነው ፡ ነብርም የበግ እረኛ ሆነ ፡
የንጉሦች ጌታቸው እንደወደደ ሲያደርግ
የአናንያ ባህር የሆነ እሳት ባህርን ያቃጥለዋልና
የወርቅ ሚዛንም እሳትን እንደሳር ይፀላዋልና ።

## ምስጢር

የተላኩትን መልእክት በትክክል የሚያደርሱ ሁሉ ይመሰገናሉ ፡ እንዲሁም ወፎችም ሆኑ አራዊት ጉዳይ ይፈፅማሉ ። ይሄውም ይታወቅ ዘንድ ህግንምእ የተባሉት ኢትዮጵያዊ ፃድቅ በፆመኛ (በብህትውና በዘጉበት) ቦታቸው ሲሞቱ ንስር የሚባል አሞራ ሞታቸውን ለመነኩሳቱ ግህበር ነገረ ይባላል ። ከዚያም በፊት ይሄው ንስር ለነቢዩ ኤርምያስ በመታብር ላይ በሜለው ወግር (ደብዳቤ) የሞተውን አስነሳው ፡ የናህን መልእክት ሳይመልስ በመቅረቱም ተፀፅቶ የነቢይ ኤልያስ መጋቢ ሆነ ።

ባለቅኔው ላምን የሚጠብቅ አንበሳ ላምን ጠበቀ በማለት አንበሳ የተባለ ክርስቶስ ከእንስሳት ጋር አደረ ፡ በግን የሚያንቅም ነብር በግን አልበላም ፡ ምክንያቱም የትዱሳን አምላክ እንደፈለገ ስለሚያደርግ ነው ይላሉ ። በተጨማሪም ለአናንያ እንደውሃ የቀዘቀዘው እሳት የባህርን ውሃ ለነቢዩ ኤልያስ በላለት (አቃጠለለት) ። ለበላኤ ሰብእ ስምኦንም



www.ethiopianorthodox.org

የወርቅ ሚዛን እሳትን (ገሃነመ እሳትን) አስቀረለት በማለት ቅኔው ተመስጥሯል (ዘፍጥ·7 ፡፡ 1 ነገስ· 17 ፡ 2 7 ገድለ አባ ሀግንሞእ) ፡፡

*194 መወድስ (1099) አ*

*ዘቀፀላ ኃይሉ (መምህር ፡ ዘዋሸራ)*

*አይቴ ውእቱ ምዕራፌ ዐይንየ?*
*በገዳምኑ ግሩም? ወሚመ ውስተ ደብር?*
*ወእምኀየሰኒ ሊተ እመ አሐውር*
*ኀበ ዘሀለወ ዐይንየ ስውር ፤*
*ባሕቱ ሐዊረ ፍና*
*ኢይትከሀሎ ለልብ ዘእንበለ ዐይን ወእግር ፡፡*
*አንሰሂ ሶበ ቆምኩ በጽንፈ ኀዘን ባሕር*
*ሐመረ ተስፋ ዘይፄዐኖ ለእመ ልብየ ይዜክር*
*ሚ ትርኅቅ ተሌልዮቱ ሀገር*
*ዘኮነ ፍጻሜሃ አድማስ መቃብር!*

## ትርጉም

የአይኔ ማረፊያ ወዴት ነው ?
በሚያስፈራ ዱር ነውን? ወይስ በተራራ ውስጥ?
ለእኔስ የተሰወረው አይኔ ወደአለበት
ብሄድ በተሻለኝ ነበር ፤
ያለአይንና ያለእግር
መንገድን መሄድ ለልብ አይቻለውም እንጂ ፡፡
እኔም /በአዘን ባህር ዳርቻ በቆምሁ ጊዜ
የሚቀመጥበት አለኝታ/ መርከብን ልቤ ቢያሳየው
መቃብር አድማስ መጨረሻዋ የሆነ
መለየቱ/ አገር ምን ትርቅ!

## ምስጢር

አንድ ልጅ ከአባትና ከእናቱ ኮብልሎ በሄደ ጊዜ “ኩቱ ያ ልጅ ወዴት ደርሶ ይሆን? አድራሻውን የሚነግረኝ ቢገኝ እኔም ወደሄድበት እሄድ ነበር ፤ ታዲያ ምን ይሆናል ! ያለመሪ መሄድ የህልም ሩጫ ነው” በማለት ከወላጆቹ አንዱ ይናገራል ፡፡ ባለቅኔውም አይናቸው ከታወረ በሁዋላ ያለአይን እሄዳለሁ ሲሉ እንቅፋቱ እግራቸውን እየመታቸው ፤ እሾህም እየወጋቸው ከመኖር እንደ አይናቸው የህይወታቸውን መጥፋት ተመኝተዋል ፡፡ መጨረሻዋ አድማስ የሆነ አገር ሩቅ እንደሆነችና ያለመርከብም ባህርን መሻገር እንደማይቻል ፤ ባለቅኔው በሃዘን ባህር ውስጥ እየዋኙ የመኖር ተስፋ ቆርጠው ወደመቃብር የሚወርዱ መሆናቸውን በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል ፡፡

*195 መወድስ (1127)አ*

*ዘገብረ ኢየሱስ (አለቃ ፡ ዘጠዳ)*

*አመ ሆሣዕና ይቤሉ ሕዝበ ሆሣዕና*
*እንተ ሠላሳ የአክል ክረምተ ሜጡ ብሩር*
*በጌጋየ መኑ ተወልደ ነሚአ ፍሬ ዕውር*
*ወለተዐቅቦ ተፈውሶቱ*
*ምክንየተ ኮኖ ዘገብሮ ዕቡር*
*ሆሣዕና ምውት አልዓዛር ፡፡*
*ወዘፈነዎ ትንቢት ጠማረ ብሂል ጠማር*
*ይበውኡ ዘኢፃመው ውስተ ፃማ ባዕዳን አብትር*
*ኢይምጻእ መንገሌነ በዐለ ትፍሥሕት ከመ ንግበር ፡፡*
*ወከመ ትንቢት ይትፈጸም ሆሣዕና እግዚእ ወገብር*
*ካልእ ዘይዘርእ ፡ ወካልእ ዘየአርር ፡፡*

## ትርጉም

የሺያጨ ክረምት/ብር ሰላሳ
የሚያህል የሆሳእና ወገኖች በሆሳእና ጊዜ ፍሬን መያዝ/እውር
በማን በደል ተወለደ አሉ ፤
ለመጠበቅ/መዳኑም
የሟች አልአዛር ሆሳእና የሰራው
ጭቃ ምክንያት ሆነው ፡፡
የላከውም “ያልደከሙት በሌሎች ወገኖች ድካም
ይገባሉ” የማለት/ደብዳቤ ትንቢት/ደብዳቤ
የደስታ በአልን እንድናደርግ ወደእኛ እንዳይመጣና
እንደ ትንቢትም ያገለጋይና የጌታ ሆሳእና እንዲፈፀም
የሚዘራው ሌላ ነው ፡ የሚለቅመውም ሌላ ነው ፡፡



www.ethiopianorthodox.org

## ምስጢር

በሶስት ወር ክረምት ጊዜ የተዘራው የእህል ፍሬ ሲመረት "ይህ ሁሉ ምርት በማን ጥረት ተገኘ? በእገሌ ጥረት አይደለምን? ደግሞስ እርሱ ለጥቢቃው አመቺ የሆነውን አጥር ባያጥር ኖሮ ይህ ሁሉ ፍሬ ባልተገኘም ነበር" በማለት ያምራቹ ወገኖች ይነጋገራሉ። እንዲሁም ሆሳእና የተባለው ክርስቶስ እውር ሆኖ የተወለደውን ሰው በምራቁ ያቦካውን ጭቃ ቀብቶ አይን ሲፈጥር ያዩ ሰዎች አደነቁ ፡ ክረምትም ሶስት ወር እንደሆነ ክርስቶስም ለሰላሳ ብር ተሸጠ ።

አድራሻ የሌለው ደብዳቤ ለትላከለት ሰው ሳይደርስ ሲቀር ላኪው መልስ ባለማግኘቱ ሁለተኛ ደብዳቤ ይፅፋል ፡ እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ አንዱ የደከመበት ንብረት ላልደከመበት ለሌላ ሰው እንደሚሆን "ያልደከሙት ሌሎቹ በደከሙበት ይገባሉ" በማለት የተነገረው ትንቢት በሁዋለኞች ሊቃውንት አልሆነም ፡ በዚህ አፈፃፀም ደስታቸው አልበዛም ። ምክንያቱም ጌታውንና ሎሌውን በእኩልነት የሚመለከት እግዚአብሄር ወልድ በተገለጠ ጊዜ ዘሪውም ፡ አጫጁም እየቅል በመሆናቸው ነቢያት ተነቡት (ስለመወለዱ ትንቢት ተናገሩ) ። ሃዋርያት አዩት ፡ እኛ ግን ሳናየው አመነው ይላሉ ባለቅኔው ።

*196 መወድስ (1100)አ*

*ዘዓለማየሁ ፈንታ (አለቃ)*

*መኑ የዐቢ እምክብረ እድግት*
*ወእምክብረ በቅል ሥርጉት በወርቅ ወበብሩር?*
*ወለእመ በቅል ያረቶ ለንጉሠ ነገሥት ፍጡር*
*ተዐቢ እምኔሃ*
*ዕዋለ እድግት ዘሥርጉት በበትር ፡*
*ጊዜ ሆሣዕና እስመ ፆረቶ*
*ለንጉሠ ነገሥት ፈጣሪ እንተ ኢይፀወር ፆር ፡*
*እድግትሂ ለሆሣዕና ጊዜ አስሐትያ ወቁር*
*አስተማወቀቶ እስትንፋሰ ውስተ ጎለ እብን እንዘ እሱር ።*
*ወአመ ነሥሦ ሄሮድስ ለሆሣዕና መንክር*



*እምገጸ ሄሮድስ አጉየየቶ ውስተ ብሔረ ግብጽ ከመ ይንበር ።*

## ትርጉም

በወርቅና በብር ከተሸለመች
ከበቅሎ ክብርና ከአህያ ክብር ማን ይበልጣል?
በቅሎም ፍጡር የሆነ ንጉስ ነገስትን ብትሸከም
በበትር የተሸለመች
የአህያ ውርንጫ ከርሷ ትበልጣለች ፡
የነገስታት ንጉስ የሆነ
የማይቻል ሸክም ፈጣሪን በሆሳእና ጊዜ ተሸክማለችና ።
አህያም በውርጭና በቅዝቃዜ ጊዜ በድንጋይ
በረት ውስጥ የታሰረ ሲሆን ሆሳእናን በትንፋሽ አሟሙቃዋለችና ፡
ሄሮድስም አስደናቂ ሆሳእናን በፈለገው ጊዜ
በግብፅ አገር ውስጥ ይኖር ዘንድ ከሄሮድስ ፊት አሸሽታዋለችና ።

## ምስጢር

የሃብታም በቅሎ በወርቅ በተዘመዘመ ግላስ ብታጌጥ ፡ አህያም ተጭና በበትር ብትመታ የአህያ አገልግሎት ከበቅሎ አገልግሎት አያንስም ። አንድ በጎ አድራጊ ለችግረኛ መልካም ስጦታን እንደሚሰጥ ሆሳእና የሚባል ኢየሱስ ክርስቶስም በከብቶች በረት ሲወለድ አህያ በትንፋሿ አሟሙቃዋለች ፡ በስደቱም ጊዜ ተሸክማዋለች ። ወደ ኢየሩሳሌምም በአህያ ላይ ተቀምጦ ገብቷል ። ስለዚህም ምድራዊውን ንጉስ ከተሸከመችው በቅሎ ይልቅ ሰማያዊውን ኢየሱስ ክርስቶስን በመሸከሚ አህያ ትበልጣለች ይላሉ ባለቅኔው (ማቴ. 21 ፡ 9—15)

*197 መወድስ (1103)አ*

*በርእሰ አድባር ለይንበር ከመ ጌራ ወርቅ*
*ደብረ ጊዮርጊስ መስቀል መልዕልተ ኵሉ ነገር ፡*
*እመኒ ዮሐንስ ፍቅደ ዘመኑ ኀዲር*
*እስመ ከመ ኢይረድ እምእሎንቱ*
*ከርሥ እብን ለወሊደ ወልድ በሕማም ወፃዕር*
*እስከነ ይትፈታሕ እማእሰር*
*አድባርኒ ይርኀቁ እምግብረ ተሀውኮ ብእሲት ነውር ።*



www.ethiopianorthodox.org

*ጉንደ ዕፀ መቅድመ ጽጌ ወበኩረ ፍሬ ሥሙር*
*ኢይትፈቀር ከመ ጽጌ ወከመ ፍሬ ኢይከብር ።*
*ወርእሰ አልሕምት ዘሎን እንዘ ቀዳማዊ ፍጡር ፤*
*ቀርን ደኃራዊ በርእሰ አልሕምት ይነብር ።*

## ትርጉም

የነገር ሁሉ የበላይ የሆነ የጊዮርጊስ ደብር/መስቀል
እንደ ወርቅ አክሊል በደብሮች ራስ ላይ ይቀመጥ ፤
ምንም ዮሃንስ/የዘመኑ ቁጥር አጭር ቢሆን
ከእሊህ እንዳይወርድ
ከማሰሪያ እስቲፈታ ድረስ የድንጋይ ሆድ ልጅን ለመውለድ
በምጥና በጭንቅ አለና ።
ደብሮችም ከመታወክ ድርጊት/የነገር ሴት
ይርቁ ዘንድ ከአበባ የቀደመ የእንጨት ግንድና የሰመረ የፍሬ በኸር
እንደ አበባ አይወደድምና ፡ እንደ ፍሬም አይከብርምና ፡
የሁሎች ላሞች ራስም መጀመሪያ ፍጡር ሲሆን
ሁዋለኛው ቀንድ በላሞች ራስ ይቀመጣልና ።

## ምስጢር

አክሊል በሰዎች ራስ ላይ እንደሚደረግ የዲማ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ከአድባራት በላይ ላቀ ፤ ዮሃንስ የሚባል አንድ ፃድቅ ሰው አጭር በሚል ቅፅል የሚታወቅ እንደሆነ የተተከለበትና የተደበረበት ዘመን ቅርብ ቢሆንም ሆድ ልጅን እንደሚወልድ የድንጋይ ህንፃ የወልድ ሰው መሆን መነገሪያ ሆነ ። ደናግል ወንዶችም ከሴት እንደሚርቁ ሌሎች አድባራት ከደብረ ድማህ በታች በመሆናቸው አይከራከሩ ። ምክንያቱም የዲማ ጊዮርጊስ ደብር ከእነርሱ በታች እንዳይሆን ከአበባና ከፍሬ የቀደመው የእንጨት ግንድ እንደ አበባው አይወደድም ፤ እንደፍሬውም አይከበርም ። የላሞችም ራስ ቀዳሚ ሳለ በሁዋላ የበቀለው ቀንድ ከራስ በላይ ስለሚሆን በሁዋላ መደበሩ ዲማ ጊዮርጊስን ከቀዳሚ ዎቹ አድባራት በታች አያደርገውም በማለት ባለቅኔው ስለዲማ ጊዮርጊስ ታላቅነት ያላቸውን አስተያየት በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል።



*198 መወድስ(1005)አ*
*ዘዘዮሐንስ (አለቃ)*
*ዕለተ ግብሩ ለወልድ ዕለተ ሰንበት*
*ባሕቱ ለምንት አዘዞ በርእሰ ደብር*
*ለሙሴ ሰንበተ ከመ ኢይሥዐር*
*ወያዕርፉ ባቲ አግዐዚ ወገብር ?*
*በሰንበት አምጣነ ገብረ*
*እንተ ኢይተርፍ ድኅረ ፍኖተ ሰማይ ወምድር ፡*
*በሰንበትሂ እምድኅረ ከልአ አንሥአተ እድ ወእግር*
*አርኅወ መቃብረ ፍኖተ ትንሣኤ ከመ ይሑር ።*
*ባሕቱ ለመኑ ይትከሀል መንኖተ ምክሩ ለኄር ?*
*ለሰብእ ዘይኄይሶ አምጣነ ውእቱ የአምር ።*

## ትርጉም

የወልድ የስራው ቀን የሰንበት ቀን ናት ፤
ነገር ግን ሰንበትን እንዳይሽር
ጌታና አገልጋይም እንዲያርፉባት
በተራራ ሙሴን ለምን አዘዘው ?
ወደሁዋላ የማይቀር
የሰማይና የምድር መንገድን በሰንበት አድርጓልና ፤
በሰንበትም እጅንና እግርን ማንሳትን ከከለከለ በሁዋላ
መንገድ/ትንሳኤን ሊሄድ መቃብርን ከፍቷልና ።
ነገር ግን የቸር ጌታ ምክርን መናቅ ለማን ይቻላል ?
ለሰው የሚሻለውን እርሱ ያውቃልና ።

## ምስጢር

አምላክ ከመፍጠር ስራው ያረፈባትን ቀን የሰንበት ቀን ብሎ ሰይሞ አክብሯታል ፤ በደብረ ሲናም ሰንበትን እንዲያከብር ሙሴን አዝዞታል ። ታዲያ “አምላክ ሰንበትን እንዳይሽራት ሙሴን ካዘዘ በሁዋላ እርሱ የሰራውን እርሱ ራሱ እንዴት አፈረሰው ? በሰንበትስ ለምን ትንሳኤውን አደረገ ?” በማለት ባለቅኔው ራሳቸውን ከጠየቁ በሁዋላ” የሚያለማውንና የሚያጠፋውን ለሰው ሁሉ የሚያውቅለት እርሱ (አምላክ) ስለሆነ ፡



www.ethiopianorthodox.org

አድራጎቱን ከጥፋት የሚቆጥረው የለም” የሚል መልስ በመስጠት ምርምራቸውን ገተዋል ።

## ታሪክ

እግዚአብሔር ፍጥረትን የጀመረውና ክርስቶስም ከሙታን የተነሳው እሁድ ቀን ነው ይባላል ። ስለዚህም የእረፍት ቀን እንድትሆን በቤተ ክርስቲያን ስርአት መፅሀፍ ተወስኖ ስትከበር ኖራለች ። ሙሴም አምላክ ከመፍጠር ስራው አረፈባት የምትባለውን ቀን ቀዳሚት ሰንበትን እንዲያከብራትና እንዳይሰራባት ተፅፏል (ዘፍጥ. 2 ፡ 1 4። ዘፀአ. 20፡ 8 11) ።

*199 መወድስ (1115)አ*

*ዘተክሌ (መምህር ፡ ዘዋሸራ)*

*ኢየእመረ ዮሴፍ ብእሴ ንጻሬ*
*ባሕርየ ድማኅ ዘለብሰት ብርሃነ ከመ ፀምር ፡*
*እስመ ለለዕለት ይትዌለጥ ሶበ ኅብረ ገጸ መንክር ፡*
*ወበእንተዝ ሶበ ውላጤ*
*ዐይነ ሰብእ ነዋ ዮሐንስ ዘንስር*
*ዘልዑለ ይሰርር ፡*
*አምጣነ ጠፈራ መጥባሕት ክሣደ ፍጡራን ዘይመትር ።*
*መላእክትሂ ተጋቢአሙ እምነ ርኁቅ ጠፈር*
*በሰፊሐ ክንፍ ከለልዋ ለድማኅ እመ አህጉር ፡*
*አምጣነ ድማኅ ድንግል ንጽሕተ አበሳ ወነውር*
*ትበርህ እምፀሐይ ወትትሌዓል እምአድባር ።*

## ትርጉም

ብርሃንን እንደ ግምጃ የለበሰች
የማየት ሰው ዮሴፍ የዲማን ባህርይ አላወቀም ፡
አስደናቂ የሆነ የፊቷ አይነት ውበት በየቀኑ ይለወጣልና።
ስለዚህም ለውጥ
የሰው አይን ከፍተኛ በረራን የሚበር
ባሞራ የተመሰለ ዮሃንስ ነው ፡



ጣሪያዋ/ሰይፍ የፍጡሮችን አንገት የሚቆርጥ ነውና ።
መላእክትም ከሩቅ ጠፈር (ሰማይ) ተሰብስበው
ያገሮች እናት/ዲማን ክንፍን በመዘርጋት ጋረድዋት ፡
ከበደልና ከነውር የነፃች ዲማ/ድንግል
ከፀሃይ ትበራለችና ፡ ከደብሮችም ከፍ ትላለችና ።

## ምስጢር

ቅድስት ማርያም የእግዚአብሔር አብን ቃል ፀንሳ ሳለች መልኳ ይለዋወጥ ስለነበር ጠባቂዋ ዮሴፍ በአንድ መልክ ሊያያት አልቻለም ። በጎጃም ክፍለ ሀገር የዲማ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ በሆነ ቀለም ስለተሳለች ተመልካቿ በአንድ ሁኔታ ሊያውቃት አልቻለም ። ደግሞ ዮሃንስ ወንጌላዊ የአሞራ ምሳሌ እንደሆነ የቤተ መቅደሲቱ ተመልካች አይን ጣሪያ ጣሪያውን በማየት እንደ አሞራ በረረ ። ሰይፍም አንገትን እንደሚቆርጥ ጣሪያዋ የመላእክትን ስእል ለመመልከት የሚያንጋጥጥ የተመልካች አንገትን የሚሰብር ሆነ ። መላእክት በክንፎቻቸው ቅድስት ማርያምንና ልጇን እንደጋረዷቸው የዲማ ጊዮርጊስን ቤተ ክርስቲያን ጠፈር (ጣሪያ) የመላእክት ስእሎች አሸበረቁት ። በተጨማሪም ድንግሊቱ ማርያም ከፀሃይ ይልቅ የምታበራና ከሴቶችም ሁሉ የምትበልጥ መሆኗ እንደተነገረ ይህችም ዲማ እንደ ፀሃይ የምታንፀባርቅና ከሌሎች አድባራትም የምትልቅ ሆነች ይላሉ ባለቅኔው ።

*200 መወድስ (1138) አ*

*ዘወልደ ሚካኤል (መምህር ፡ ዘዜና ማርቆስ)*

*እግዚአብሔር ይኄሥጽ አንተ ያፈቅር*
*ዘይቤ መጽሐፍ በቃለ መተርጉም መምህር*
*እሙን ውእቱ ለጻድቃን ገዳም ወደብር ፡*
*ወሕሰው በነቢየ ፡*
*እስመ አነ ዝንጉዐ ልቡና ወአነ እሱር*
*በነበለ ኀጢአት ዘይነውኅ*
*እንዘ ለለዕለት እትገሀ በግብረ ዐመፃ ወነውር ።*
*ሊተሰ ይደልወኒ ተግሣጸ አምላኪየ ኄር ፡*



www.ethiopianorthodox.org

ለልየ በእዴየ እስመ ጸዋዕክዎ ለነግር
እንዘ እብል እድኅን እምደዊ ክልኤቱ አእጋር
ወሰብእ መሬታዊ ዘይረክቦ ኢየአምር ።

## ትርጉም

እግዚአብሄር የሚወደውን ይቀጣል
ያለው መፅሃፍ ዐተርጓሚው መምህር ቃል
ለገዳምና ለደብር ፃድቃን እውነት ነው ፤
በእኔ ዘንድ ግን አሰት ሆነ ፡
በእየቀኑ በአመፅና በነውር ስራ እየተጋሁ
እኔ ልበ ዝንጉና
በረዘመ ገመድ/ሃጢአት አስረኛ ነኝና ።
ለእኔስ የቸር አምላኬ ቁጣ ይገባኛል ፤
ከሁለት እግሮች ህመም እድናለሁ ስል
እኔ በገዛ እጄ አሳርን ጠርቸዋለሁና
የመሬት ሰውም የሚያገኘውን አያውቅምና ።

## ምስጢር

"አባት ልጁን እንደሚገስፀው እግዚአብሄር ወዳጁን ይገስፀዋል" የተባለው ነገር በፃድቃን ዘንድ የታመነ ቢሆንም በእኔ ዘንድ ውሸት ነው በማለት ባለቅኔው ሁለት እግራቸውን ካመማቸው በሽታ እድናለሁ ሲሉ ከባሰ ችግር ላይ ወድቀው መከራ የፀናባቸው መሆኑን ገልጠዋል። በተጨማሪም "የአምላክ ወዳጅ ሳልሆን በመከራ ተፈተንሁ፣ መከራ የፅድቅ ሳይሆን የሃጢአት ነው" በማለትም ጥፋታቸውን አምነዋል።

እንስሳ እረኛ ወዴት እንደሚያሰማራው እንደማያውቅ ሰው ሁሉ በላዩ ላይ ምን እንደሚመጣበት ሊያውቅ አይችልም። ስለዚህ እኔም "እድናለሁ ስል የባሰ አገኘኝ" በማለት ባለቅኔው የደረሰባቸውን ስቃይ በቅኔያቸው ምስጢር አስረድተዋል።

*201 መወድስ(1145)*
*ዘተክሌ(መምህር፡ዘዋሸራ)*



**ሰማይ** ወምድር አመ ተፃብዓ
**እምቅሉ** ክልኤቲ አንስት ፀዋሪተ ምውት ምድር
**እፎ** ተኅዝነ በሞተ ሰሎሞን ኄር?
**እምጣነ** ተኅጥአ እምኵሉ ፍጡር
**ፍትሔ** ጽድቅ ዘየአምር፡
**እንዘ** ትፀውር ሕያወ ዘኢወለደት ጠፈር።
**ወእፎ** ያስተፌሥሓ ዜና ሞተ ሰሎሞን በኩር
**ለሰማይ** ሐሳዊት እንዘ ሕፃነ ባዕድ ትፀውር?
**እስመ** እመቦ ሰሎሞን በሰማያዊት መንበር
**ሕያወ** እምቀተለ ክፍለ ክልኤቱ ከመ ይግበር።

## ትርጉም

**በውሉት** ሴቶች አምሳል
**ሰማይና** ምድር ቢጣሉ በድን ተሸካሚ ምድር
**በቸር**/**ሰ**ሎሞን ሞት እንዴት ታዝን?
**የእውነት** ፍርድን የሚያውቅ
**ከፍጥረት** ሁሉ ታጥቷልና፡
**ያልወለደ**ችው ሴት ሰማይ ዘይወት ያለውን ስትሸከም
**ሰማይ**/**ው**ሸታሟንም የባእድ ህፃንን ስትሸከም
**የአልቃ** **ሰ**ሎሞን ሞት ወሬ እንዴት ያስደስታት!
**በሰማይ** **ዙ**ፋን ሰሎሞን ቢኖር ኖሮ
**ለውሉቱ** **ሴ**ቶች ያካፍል ዘንድ በህይወት ያለውን በገደለ ነበርና።

## ምስጢር

**በአንድ** ደህነኛና በአንድ ሙት ዘፃን የተጣሉ ሁለት እስራኢላውያት **ሴቶች** **በተ**ካሰሱ ጊዜ እውነቱን ለማወቅ ደህነኛውን ልጅ በሰይፍ **ከፍለው** **እንዲ**ካፈሉ ሰሎሞን አዝዟል። መጥምቁ ዮሃንስም አንገቱን **በሰይፍ** **በተቆረ**ጠ ጊዜ ራሱ በክንፍ ወደሰማይ በሮ ሲሄድ በድኑ በምድር **ቀርቷል**። **ስለዚ**ህ በዚያን ጊዜ ሰሎሞን ቢኖር ኖሮ ምድር በድኑን ብቻ **ሳይሆን** **ህይወት** ካለው ከዮሃንስ ራስም ድርሻ ታገኝ ነበረ በማለት **ባለቅኔው** **አመ**ስጥረዋል።



www.ethiopianorthodox.org

## ታሪክ

የእስራኤል ንጉሥ የዳዊትና የቤርሳቤህ ልጅ ሰሎሞን በአባቱ ዙፋን ተተክቶ እስራኤልን ሊያስተዳድር አምላኩ የፍርድ ጥበብን እንዲሰጠው ለመነ። በዘመነ መንግስቱ ሁለት ሴቶች በአንድ ቤት ውስጥ ሲኖሩ በሶስት ቀናት ልዩነት ተከታትለው ወለዱ። ሁለቱም ሌሊት እንደተኙ አንዲቱ ልጇን በእንቅልፍ ልቧ ስለተጫነችው ሕፃኑ ሞቶ አገኘችው። የርሷን ሬሳ ልጅ በጓደኛዋ ብብት አስጠግታ ደህናውን የጓደኛዋን ልጅ ወሰደች።

የደህነኛዋ ልጅ እናት ጧት ከእንቅልፏ ነቅታ ልጇን ለማጥባት ብታስብ የሞተውን የጓደኛዋን ልጅ አገኘች። እርሷንም "የሞተ ልጅሽን ውሰጂ የእኔንም ልጅ መልሺልኝ" ብትላት እምቢ አለቻት። ሁለቱም ሴቶች ተካሰው ወደሰሎሞን ሄዱና ሲጠየቁ "ደህነኛው ልጅ የእኔ ነው ተባባሉ"። በዚህ ጊዜ ሰሎሞን ሰይፍ አስመጥቶ "ደህነኛውን ልጅ በሰይፍ ለሁለት አካፍሏቸው" ብሎ አዘዘ። የደህናው ልጅ እናትም" አይቆረጥ ለእርሷ ስጧት፤ እኔ ይቅርብኝ" አለች። "ያልወለደ አንጀት አረደ" እንደሚባለው ያልወለደ ሆድ የዚያን ያህል ነው የሟቹ ልጅ እናት ግን "ይከፈል ፡ ለሁላችንም አይሁን" በማለት ተናገረች ።

በዚህም ጠቢቡ ሰሎሞን እውነተኛዋ ማን እንደሆነች ስለተረዳ ደህነኛውን ልጅ ለወላጅ እናቱ እንዲሰጥ ፈረደ (1ነገስ 3፡16 27 ፡ ስንክ·መስከረም 2)።

*202 መወድስ(11...)አ*
*ዘዘወልዱ(አለቃ)*

*ቅውልድ የነልፍ ወሰነ አበው*
*ወትውልድ ይተርፍ እምነ እሙሁ በግብር*
*ምሳሌ ዝኒ ሳሰሉከ ሣህለ ማርያም ይብር*
*ሐሰውከኒ ኢተዘለኒ*
*እምነ ዜናሁ ለሰሎሞን በከር*
*ጠይቅ ወተዘከር፡*
*እመ ነባቢሁ ተቀብረ አምባነ ንባቡ ኢይትቀበር ።*

*በይን ጽድቅኒ ወልደን ርትዕ ወልደን የውሻት መንክር*
*እለከን ትግሬ ይመርሐከ ስለሕተ የማንከ ፍዳ ዐር፡*
*አርቲዐከኒ ፍናተ ማእከለ ወሎ ሀገር*
*ተመራሕ ለትንና መንገሥ ዘየንደር።*

## ትርጉም

ያባቶቻችን ድንበር ትውልድ ያልፋል
ከአባቶቹም በስራ ይተርፋል ።
ሳህለ ማርያም/ተረፈ ! የዚህም ምሳሌ በአንተ ላይ ነው ፤
ጥበብም እንዳትለኝ
ከጠቢብ ሰሎሞን ነገር
ተረዳ አስታውሰም ፡
ተናጋሪው ቢቀበር ንግግሩ አይቀበርምና
ስለእውነትና ስለቀጥተኛነት ስለሚያስደንቅ የዋህነትም
የጠላት ፍዳ በቀኝህ ምክንያት እስከ ትግራይ ድረስ ይመራሃል ፤
በወሎ አገር መካከልም መንገዱን አቅንተህ
ለመግባት ተዘጋጅ ወንንደርም ንገስ ።

## ምስጢር

አንዳንድ ሰው ወሸን እንደሚገፋ አንዳንድ ጊዜም ከአባቱ የሚበልጥ ልጅ ይወለዳል ። ይህም በጥምቀት ስማቸው ሳህለ ማርያም በተባሉ በአፄ ምኒልክ ይታወቃል ። ከወላጅ አባታቸው ከሃይለ መለኮት ይልቅ አፄ ምኒልክ ግዛት አስፍተዋልና ባለቅኔው መላዋን ኢትዮጵያን አንድ አድርገህ ወሎና ትግሬን ትንደርንም ግዛ በማለት ለአፄ ምኒልክ ያላቸውን ፍቅር በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል ።

*203 መወድስ(108.3)አ*
*ዘአክሊል ወልደ(መምህር)*

*ምንትኑ ለከም ዘቲኣተ ዚአሁ?*
*እመ ተሰምዐ ዘርሃን ጽልመተ ሌሊት ገብር*





www.ethiopianorthodox.org

ወዓዲ ጥዑመ እመ ይሰመይ መሪር፣
ተሰምዮተ ወይን ወብርሃን
ኢበቊዐ አኮኑ ለአውናን ወኤር፣
ወበቅድመ ኢዮአብ ፍሬ ማዕር
ሐመልማለ ማዕር ኮነ አበኔር ወልደኔር።
ብርሃንሰ እመ ተሰምየ ወልደ ባሕርየ አብ ኄር
ኮነ መራሔ ፍና ለዕውር ወልደ ዕውር፣
ወለእመ ተሰምየ ወይነ ጥዑመ ነገር
ኮነ ሰማዕተ ጽድቅ ወይነ ቤተ ቃና ዘመደ ፍቅር።

## ትርጉም

የስም ጥቅሙ ምንድር ነው?
የሌሊት ጨለማ/አገልጋይ ብርሃን ቢባል
መራራም ጣፋጭ ቢባል፣
ወይንንና ብርሃንን መባል
ለአውናንና ለኤር አልጠቀመምና ፡
ዘኢዮአብ/የሳር ፍሬ ፊትም

የኔር ልጅ አበኔር የሳር ቅጠል ሆኗልና።
ቸር የአብ የባህርይ ልጅ ግን ብርሃን ቢባል
ለእውር ልጅ-እውር መንገድ መሪ ሆነው፣
የነገር ባፋጭ ወይንም ቢባል
የፍቅር ዘመድ የቃና ቤት ወይን የእውነትም ምስክር
ሆነው።

## ምስጢር

ማንኛውም ባለስም በጥሩ ቢጠራ ስሙና ግብሩ ካልተሟ በሩ በስም ብቻ መከበርን አያገኝም። ይህም ሊታወቅ ጨለማው በብርሃን መራራውም በጣፋጭ ስም ቢጠራ ጨለማው ብርሃንን፣ መራራውም ጣፋጭን ሊሆን አይች ልም። ስለዚህም በየስማቸው ትርጓሜ አውናን ወይንን ኤርም



ብርሃንን በግብር ሊሆኑ አልቻሉም። ግን የአንዳንዱ ሰው ስሙ ከግብሩ ጋር እንደሚተባበር የአብ የባህርይ ልጁ የእግዚአብሄር ወልድ ስያሜ በየስያሜው ልክኛ ሆኖ ተገኘ። ብርሃን ቢባል እውር በብርሃኑ እንዲሄድ አደረገ፣ ወይንም ቢባል በቃና ዘገሊላ በዶኪማስ ቤት በተደረገው የሰርግ በአል ውሃውን ወደወይን በመለወጡ ወይንነቱ ፀደቀ ይላሉ ባለቅ ኔው (ዮሃ·2፡1. — 9)።

204 መወድስ(1089)አ
ዘእንግዳ ወርቅ ኀይሉ(አለ.ቃ)

ዓለመ ተድላ ጎንደር እምድኅረ ኀለፈ
ዓለመ ተድላ ይፍጥሩ እምኅበ አልቦ ጎንደር
ሥላሴ እቀሙ በዘርዐ ዳዊት መንበር
ኪያከ ወሌ ጉግሣ
ዘትሠሪ ኀጢአተ ግብሩ ለኩሉ ብሔር፣
ባሕቱ በዘመንከ
ኢይትፈጠር ብነ እንተ ኢዘልው ግብር።
እምግብጽሂ ለተሐድሶ እመ ተጸውዐ ንስር
ይትቀሠፍ በኀይልከ ወበሰይፈ ቃልከ ይትመተር፣
እምከመ ኢጠፍአ ለነ እንዘ ዓዲሁ በምድር
ዘንስር ተሰርዎ እምጣነ ልዑለ ይሠርር

## ትርጉም

የምቾት አለም/ጎንደር ካለፈ በሁዋላ
የምቾት አለምን ከሌላው ጎንደር ይፈጥሩ ዘንድ
የሃገሩን ሁሉ ሃጢአት/ግብርን የምታስተሰርይ
ወሌ ጉግሳ! አንተን
ስላሴ በዳዊት ዘር ዙፋን አቆሙ(ተኩ)፣
ነገር ግን በዘመንህ
ነዋሪ ያልሆነ ግብር አይፈጠርብን።



www.ethiopianorthodox.org

ለመ ታደስም ንስር ከግብፅ በትጠራ ጊዜ
በሃይልህ ይቀሰፍ በሰይፍ ቃልህም ይመተር፤
በምድር ገና ሲሆን ካልጠፋልን
የአሞራ መነቀል ወደላይ ይበራልና

## ምስጢር

ስላሴ (አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ) ይህ አለም ካለፈ በሁዋላ አዲስ አለምን ይፈጥራሉ እንደሚባል የምቾት ከተማ ጎንደር በደርቡሾች ከፈረሰ በሁዋላ ከቀረው ጎንደር ምቾትን ለማስገኘት ራስ ጉግሳ ወሌን አስነሱ። ሃጢአት በንስሃ እንደሚስረይ ጉግሳ ወሌ የነበረውን ልማድ ለወጡ። የግብፅ ንስር በየአምስት መቶ ዘመን በሚያካፋ ካፊያ ይታደሳል ተብሎ እንደሚነገር የአሞራ ግብር አይሰራብን፣ ሃጢአተኛ በጅራፍ እንደሚገረፍና አመፀኛ አንገቱን በሰይፍ እንደሚቆረጥ በቅጣት መልክ የተሰራብን የአሞራ ግብር ይቅርልን። ካልቀረልን አሞራ ወደላይ እንደሚበር በአሞራ ግብር ምክንያት ወደበላይ ለአቤቱታ እንሄዳለን በማለት ባሰቅኔው አቤቱታቸውን አሰምተዋል ።

## ታሪክ

ራስ ጉግሳ ወሌ የተባሉት መስፍን በጎንደር በካህናቱ ርስት ላይ የአሞራ ጠባቂና የጭቃ ማር የሚባል ግብር ሰሩበት። በዚህም ምክንያት አለቃ እንግዳ ወርቅ ሃይሉ የጎንደርን ካህናት በመወከል የሚሞግቷቸው መሆኑን በመግለጥ ራስ ጉግሳ ወሌን በቅኔያቸው አስጠንቅቀዋል ።

*205 መወድስ (1047)ጎ*

*ጠፈረ ሐተታ ሰማይ ለእመ ርኢኩ*
*ኢያጸድቆ ለሰብእ ጸሎት እንበለ ፍቅር*
*ወኢይበቁዖ አሚን እምኀበ አልቦ ምግባር ፤*
*ዓዲ ኢይደልዎ*
*ትእቢት ፀሩ ለክርስቶስ በኩር*
*ፍና ትሕትና ዘየሐውር*
*እስመ ኀበ ሀሎ ትእቢት ሀየ ሀሎ ኀሣር ።*



*እኀውየሂ ከመ ታእምሩ ምሳሌ ዝንቱ ነገር*
*እእዳው ኢይበቁዑ እንበለ አጻብዕ ወአጽፋር ፤*
*ወኢይሜንዩ ከመ በኀበ ኵሉ ፍጡር*
*አስናን ባሕቲቶሙ እምኀበ አልቦሙ ከናፍር ።*

## ትርጉም

የምርምር ሰማይ ጠፈርን ብናይ
ፀሎት ያለፍቅር ሰውን አያፀድቀውም
ማመንም ምግባር ከሌለው አይጠቅመውም ፤
ዳግመኛም የትህትና
መንገድን የሚሄድ የበኩር ክርስቶስ ጠላት
የሆነ ትእቢት አይገባውም ፤
ትእቢት ከአለ ዘንድ በዚያ አሳር አለና ።
ወንድሞቼ! የዚህን ነገር ታውቁ ዘንድ
እጆች ያለጣቶችና ያለጥፍር አይጠቅሙም ፤
ጥርሶችም ከንፈሮች ከሌሏቸው ብቻቸውን
በፍጡር ሁሉ ዘንድ በፍፁም አያምሩም ።

## ምስጢር

የምርምርን ነገር ማራቀቅ የሰማይ ጠፈርን ቀና ብሎ እንደማየት ሲሆን ፤ እንጀራ ያለወጥ እንደማያጠግብ ፀሎትም ያለፍቅር ዋጋ አያስገኝም ። ግድግዳ ያለማገሪያ እንዳይጠቅም እውነትም ያለምግባር አይረባም ። መንገደኛ ሰው ጠላቱ በሸመቀበት መሄድ እንደማይገባውና ቢሄድም በዚያ አሳር እንደሚያገኘው ክርስቶስ የማይወደው ትእቢት ሰውን አዋርዶ በመከራ ላይ ይጥለዋል ። ይህንንም እጆች ያለጣቶችና ጥፍሮች ፤ ጥርሶችም ያለከንፈሮች አለመፈጠራቸው ያስረዳል በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

*206 መወድስ (328)ጎ*

*ዘገብረ ሚካኤል ዕውር*

*በአክናፈ ተምኔት ነዐርግ መልዕልተ ደመና*
*ፍትሐ መለኮት ዕቅፍት እንዘ በማእከሉ ንቡር ፤*



www.ethiopianorthodox.org

*ወወርቀ ፍትሐ ሞት ንሰርቅ እምንዋየ መንግሥት ክቡር ፤*
*ዘይሬኢ ዙሉ ዐይነ ሞት ፀር*
*እንዘ መንገሌነ ይኔጽር ፤*
*ወእንዘ ያንቦሉ ዝየ ተባርዮ ፍዳነ እግር ።*
*ንስሕብ ሐረገ ሞት ስቴየ ደመ ሔዋን ባሕር*
*እምአሥራወ አቤል ተዳግዊ ወእስከ ጽንፈ አቤል አንተ ድኀር*
*ወዘእምኔሁ ይትቀሰም ከዊነ መሬት ማእረር*
*ይመልእ በረከተ በምክያደ አልዓዛር መቃብር ።*

## ትርጉም

የመለኮት ፍርድ/መሰናክል በመካከሉ የተቀመጠ
ሲሆን በምኞት ክንፎች በደመና ላይ እንወጣለን ፤
ወርቅ የሞት ፍርድንም ከከበረ ከመንግስት ገንዘብ እንሰርቃለን ፤
ሁሉን የሚመለከት የሞት ጠላት/አይን
ወደኛ ሲመለከት ፤
የፍዳችን ፍርርት/ጠላትም ወደዚህ ሲመላለስ ።
ከቀድሞ ሰው ከአቤል በሮች እስከ የሁዋላ ሰው አቤል ዳርቻ
የሄዋን ደም/ባህርን የጠጣ ሃረግ/ ሞትንም እንስባለን ፤
ከርሱም የሚለቀመው አፈርን መሆን/አዝመራ
በአልአዛር ሐውድግ/መቃብር በረከትን ይሞላል ።

## ምስጢር

ወሮች በክንፎቻቸው ወደላይ እንደሚበሩ እኛ ሰዎች ትልቅነትን እንመኛለን ። ክንፈ ሰባሪ ወፍ ሊበር እንደማይችል እኛም ወደአሰብነው ሳንደርስ የአምላክ ፍርድ ያስቀረናል ። ሌቦችም ከመንግስት ካዝና ገንዘብ እንደሚሰርቁ በሌላው ላይ ሞትን ብናመጣበትም ጠላት ባላጋራውን በድብቅ እንደሚጠባበቀው በእኛም ላይ ሞት ይታዘዝብናል ። ባለጉዳይም ጉዳዩ ወደቀረበበት ሃላፊ እንደሚመላለስ መከራ ይፈራረቅብናል ።
ውሃ የጠጣ የወይን ሃረግም ከወዲያ ወዲህ እንደሚሳብ በሄዋን ደምን ያመጣ የነፍስ ሞትንም ከአዳም ልጅ ከአቤል ጀምሮ እስከመጨረሻው የአቤልን ሞት እንሞታለን ። ደግሞ አዝመራ በእርሻ እንደሚሰበሰ



ቁና በአውድማ እንደሚሞላ ከሞት የሚከተል አፈርና ትቢያን መሆን በመቃብር ይፈፀማል በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

*207 መወድስ/ስ*
*ዘምሥራቅ (አለቃ ፤ ዘኤልሻማ)*

*መሪረ ንብኪ በእንተ ርእስነ*
*መሽቶብናልና ጊዜው ከስጋው ገበያ ስንዞር*
*ዘማ ቤተ ነዌ ዓለም እያታለለችን በፍቅር*
*እንዘ ሕልም ንብረተ ዚአሃ ወሐውዛ መሪር*
*የስጋው አዛዥ መቃብር*
*ታላቅ ታናሹን ሳይለይ እስኪፈጀው ድረስ በምድር ።*
*ሞትሂ የሁሉ ጌታ የጉዞውን አዋጅ ሲነግር*
*አትልከስከሱ ከስጋው ተራ መሄዱ ላይቀር እግር በእግር ፤*
*ዳግመኛ ዳግም ልበል ኮርቻ አላጣም በክብር*
*ፈረስ ፈረስ ሲል የተዘጋጀ መርገፍ አለና ያለማፈር ።*

## የግእዙ ትርጉም

ስለራሳችን አምርረን እናልቅስ ፤
አኗኗሯ ህልም ፤ ውበቷም መራራ ሲሆን
የነዌ ቤት ሸርሙጣ/አለም እያታለለችን
ከስጋው ገበያ ስንዞር ጊዜው መሽቶብናልና ።

## ምስጢር

በስጋ ገበያ ሲዞር ውሎ ከመሸ የተነሳ ብቸኛ ሰው በጨለማ ሲሄድ አውሬ ሲመጣበት በጣም አምርሮ ይጮኸል ። እንዲሁም የስጋን ኑሮ እየዘው እይዘው ሲል አንዱን ሳይዘው ያረጀ ሰው ስለሃጢአቱ በንስሃ ማልቀስ አለበት ። ደግሞ በዘማ ሴት ፍቅር የተታለለ ጎበዝ ቤቱን እንደማያስብ በዚች አለም ተድላ የተያዘ ሰው ሞትን አያስታውሰውም ።
ህልም እንደማይጨበጥና የዘማ ሴት ነገርም ማታለል የሞላበት እንደሆነ የዚህች አለም ሁኔታ አጥፊና ጎጂ ነው ። አንዳንድ የስጋ ቤት አዛዥ የስጋ መልከኛው ገና ታናሹንና ታላቁን ለይቶ ሳያወጣ ጎምዥቶ ስጋውን እየቆረጠ እንደሚበላ መቃብር ትንሹንም ፤ ትልቁንም ሳይለይ



www.ethiopianorthodox.org

ይቀበላል ። አንድ የጦር አዛዥ የዘመቻ አዋጅ ሲያውጅ ግቴን ጨር ሳይሉ ወዲያውኑ እግር በእግር ተከትሎ መዝመት የወታደሮች ግደ ነው ። እንዲሁም ሞትን ያህል ግዴታ ያለበት ሰው በስጋዊ ነገር ተ ተጠምዶ መልከስከስ አይገባውም ። ፈረስ ያለው ኮርቻ ቢለ ከባለመርገፍ ግላስ ጋር እንደሚያገኝ በሞት መፍረስና መርገፍ ፡ አ ትቢያም መሆን የማይቀርለት ሰው መልካም ስራ በመስራት የህይወ ዘመኑን ማሳለፍ እንደሚገባው ባለቅኔው ያስረዳሉ ።

*208 መወድስ ስ*

*ዘየማን ብርሃን (ቄስ ገበዝ)*

*በደመ ቈዕለ ዕፅ ዘረብሐ ልብሰ ክዋኔሁ*
*ለአበ ብዙኃን አዳም ወለሔዋን ሕጽጸተ ክብር*
*በደመ ሥጋዌ ኀፀበ እግዚአብሔር ፤*
*ወበላዕለ ኵሉ ገጸ ዓለም*
*ሰወረ ዕርቃነ መሐላ በዘኖኅ ፀምር ፤*
*አምጣነ ኢክህለ ተሌልዮ*
*እምአፍራሰ እሳት ኪሩቤል አምሳለ እግዚእ ወገብር ።*
*ዓለመሂ አመ ሐወጸ በሩጸተ ሰሎሞን እግር*
*ሠምረ ዘኢሞዖ ለጽኑዕ አረፍተ ፀር ፤*
*አምጣነ ይኄይስ ሣህል እምነቢረ ልዑል መንበር*
*ወድንግል እብነ ምሳሌ በሥምረተ ነቢይ ታገምር ።*

## ትርጉም

የብዙዎች አባት የአዳምና ክብሯን ያላነሰች የሄዋን
በእንጨት ቅጠል ደም ያደፈ ልብስ/ሁኔታን
እግዚአብሄር በሰውነት ደም አጠበ ፤
በሁሉ የአለም ፊት ላይም
በኖህ ግምጃ መራቆት/መሀላን ሸፈነ ፤
የጌታና ያገልጋይ አምሳያ
ከእሳት ፈረሶች/ኪሩቤል
መለየትን አልቻለምና ።
በሰሎሞን/እግር ሩጫም አለምን በጐበኘ ጊዜ



የጠና የጠላትን ግድግዳ ያላሸነፈውን ወደደ ፤
በከፍተኛ ወንበር (ዙፋን) ከመቀመጥ ይቅርታ ይሻላልና
ድንግልም በነቢይ ፈቃድ የምሳሌ ድንጋይን ትችላለች ።

## ምስጢር

በደም የቆሸሸውን ልብስ አጣቢ በላሙና እንደሚያጥበው ክርስቶስ ዘበለስ ቅጠል ደም የተዋረደውን የአዳምንና የሄዋንን ባህርይ በደሙ ቀደሰው (አከበረው) ። ራቁትነትም በልብስ እንደሚሸፈን ለኖህ በመሀላ የገባውን ኪዳን ፈፀመ ። አገልጋይም ከፈረሶች በሁዋላ እንደሚከተል እግዚአብሄር ወልድም በሰውነቱ እንደ አገልጋይ ሲሆን በአምላክነቱ በኪሩቤል ላይ ይመሰገናል ። በሩጫም ካሰቡት ቦታ በፍጥነት እንደሚደ ረስ ሰሎሞን በቤተ ክርስቲያን ተገብቶ (ቤተክርስቲያንን አስመልክቶ) በተናገረው ምሳሌ መሰረት እግዚአብሄር ወልድ አለምን (ሰውን) በአዳነ ጊዜ የዲያብሎስን ተንኰል ያልተቃወመውን አዳምን ይቅር አለው ። በዙፋኑ ሆኖ መልእክን አዝዞ ከሚያድነው ይልቅ እርሱ ራሱ ሰው ሆኖ ፡ በመስቀል ተሰቅሎ ካሰለት ። ይህም የሆነው በደለኛ ድንጋይ "ተሸከሞ ይቅርታ እንደሚጠይቅ ቅድስት ማርያም የቅዱስ ገብርኤልን ብስራት በእምነት ተቀብላ በዳንኤል ድንጋይ የተመሰለውን እግዚአብሄር ወልድን ስለወለደች ነው ይላሉ ባለቅኔው ።

*209 መወድስ/ስ*

*ዘነበዚ (አለቃ ፡ ዘደብረ ወርቅ)*

*ኢናንክር ኀዳጠ ለመንፈስ ቅዱስ*
*ለንጽሕተ ባሕርይ ድንግል እመ እንጽሓ እምነውር ፤*
*መሐፒልኦ ይትኀሠሥ ለእንተ ጸዕደወ ፀምር*
*ለርሱሕ ዳዕሙ ይትኀሠሥ በግብር ፤*
*አንክሮሰ ናንክር*
*እመ አንጽሐ ኪያነ እምርስሐተ ጌጋይ ጽቡር ።*
*ርሱሕኒ እንዘ ሀሎ አጸዕድዎ ሜላት ሥሙር*
*ለነዌ ጸውዖ ነዌ እንዘ ኢይጼዋዕ አልዓዛር ፤*
*ባሕቱ ኢሀለወ ፍትሕ አምጣነ ኢይክል ፍጡር*
*በላዕለ ነጋሢ ፈቲሐ ፍትሕ ወአንድዶ እሳት በላዕለ ባሕር ።*



www.ethiopianorthodox.org

## ትርጉም

ባህሪዋ የነፃ ድንግልን ከነውር ቢያነፃት
መንፈስ ቅዱስን ጥቂት አናደንቀውም ፤
ለነፃችው ግምጃ ልብስ አጣቢ ይፈለጋልን ?
ለአዳፋው ልብስ ይፈልጋል እንጂ ፤
ከበደል/ጭቃ እድፍ
እኛን ቢያነፃ ማድነቅን እናደንቃለን ፤
እድፉም ሳለም የተወደደ ሃርን ማንጣት
አልአዛር ሳይጠራ ነዌን የነዌ መጥራት ነው ፤
ግን ፍርድ የለም ፤ በንጉስ ላይ ፍርድን መፍረድንና
በባህር ላይ እሳት ማንደድን ፍጡር አይችልምና ።

## ምስጢር

አንድ ልብስ አጣቢ አዲሱን ልብስ አጥቦ ቢያነፃ አያስደንቅም ፤ የሚያስደንቀው ያደፈውን ልብስ አጥቦ ሲያነጣው ነው ። መንፈስ ቅዱስም ጥንቱን በተፈጥሮ ባህርይዋ የተቀደሰችውን ቅድስት ድንግል ማርያምን ቢቀድሳት አይደነቅም ። የሚደነቀውስ በበለስ መብል ሃጢአት የተዋረዱትን አዳምና ሄዋንን ፣ ልጆቻቸውንም ከሃጢአት ማንፃቱ ነው ። ደግሞ አዳፋውን ልብስ ማጠብና ማጥራት የሚገባ ቢሆንም ያላደፈውን ልብስ ማጠብና ማንጣት የተለመደ እንዳይደለ እግዚአብሄር ወልድ ሰው የሆነው ሃጢአተኛውን እንጂ ፃድቁን ለማዳን አይደለም ። በባለፀጋው ነዌ ደጅ የወደቀውን ድሃውን አልአዛርን በመጥራትና በመርዳት ፈንታ "ነዌ ነዌን ጠራው" በማለት ባለፀጋ ባለፀጋን መጋበዙ የመንግስተ ሰማይ ዋጋን አያስጥም ። ድሃ በንጉስ ላይ መፍረድን እንደማይችል በባህር ላይም እሳት እንደማይነድ ፍጡርም በፈጣሪው ላይ መፍረድ አይችልም በማለት ባለቅኔው ቅኔያቸውን አመስጥረዋል ።

*210 መወድስ (325)ኀ*

*ፍትሐ ጽድቅ ወፅአ እምኢፈ ነጋሢ*
*በበትረ እዴሁ አዳም ርእሰ አርዌ ከመ ይሰብር ፤*
*በመዋዕለ ሙሴሰ ይፃእ እምነ ዝንቱ ጎሣር*



*ውእቱ አርዌ ወውእቱ በትር ።*
*ወኢይደልወነ ንትናገር*
*በቀለ አርዌ ዘቅድም በመዋዕለ ሰላም ወፍቅር ፤*
*አምኤዶም አረጋዊ አመ አውረዶ በምክር*
*እንተ ኢያውረደ አረጋዌ አምጣነ አዕረገ ላዕለ ደብር ፣*
*ወሰቃለ ኖኀ ይትአዘዝ ጊዜ ሕማሙ ነኪር*
*አፉሁ አርዌ ገዳም ኢከሠተ በሐመር ።*

## ትርጉም

አዳም በእጁ በትር የእባብ ራስን
ይሰብር ዘንድ የእውነት ፍርድ ከነጋሽ አፍ ወጣ ፤
በሙሴ ዘመን ግን ከዚህ መከራ ይወጣ ዘንድ
እርሱው እባብ ነበረ ፣ በትርም ራሱ ሆነ ።
ግን የቀድሞ እባብ በቀልን
በሰላምና በፍቅር በመን እንናገር ዘንድ አይገባንም ፤
ሽማግሌን ከገነት በምክር በአወረደ ጊዜ
ያላወረደውን ሽማግሌ ወደተራራ አውጥቷልና ፣
ለኖህ ቃልም ይታዘዝ ዘንድ በልዩ ህማሙ ጊዜ
የዱር እባብ አፉን በመርከብ አልከፈተምና ።

## ምስጢር

ይዋጣላቸው ብሎ ልጅና ልጅን እንደማታገል አይነት እባብ የአዳምን ሸሆና እንድትነድፍና አዳምም በበትር እርሷን እንዲቀጠቅጥ ተደርጎ ነበር ። ግን ከሁለት ጥለኞች አንዱ መብት ሲያገኝ ሌላውን ማጥቃት እንደሚችል እባብ በሙሴ ታምር እባብም ፣ በትርም በመሆኑ በአዳም በትር ራሱን ከመቀጥቀጥ ነፃ ሆነ ።

ሁለት ጥለኞች በሽማግሌ ከታረቁ በሁዋላ ጠበኞች ሆነው መኖራ ቸው ይረሳል ። እባብም ሽማግሌ አዳምን ከገነት ወደምድረ ፍዳ (ወደመከራ ምድር) ቢያወርደውም አቡነ አረጋዊን ወደ ደብረ ዳሞ ራስ ላይ ስላወጣቸው የአዳም ልጆች ዘንዶን ሊበቀሉት አይገባም ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።



www.ethiopianorthodox.org

## ታሪክ

አባብ በክፉ ምክር አዳምን ከገነት ስላስወጣችው አዳም የአባብን ራስ በበትር እንዲቀጠቅጥና አባብም የአዳምን ሰኰና (ተረከዝ) እንድትነድፍ እግዚአብሄር ተናግሯል ። ሙሴንም እስራኤልን ከግብፅ እንዲያወጣ ወደ ፈርኦን ሲልከው በትሩ እባብ እንድትሆንና የግብፅ አስማተኞችን በትሮች እንድትበላ ፣ ወደ በትርነቷም እንድትመለስ አድርጓታል (ዘፍ·3፡1–24፤ ዘፀአት 8–16) ።

ዘንዶ በኖህ ጊዜ ርግብ አፉ ውስጥ እንቁላሏን ብትጥልበት እስክትወጣ ድረስ አፉን አላንቀሳቀሰም ። ምክንያቱም ኖህ ከመርከብ አውጥቶ በንፍር ውሃ ውስጥ እንዳይጥለው ነው ይባላል (ዘፍጥ·7፡10)

የደብረ ዳሞን ተራራ የገደሙት ፃድቁ አቡነ አረጋዊ የደብረ ዳሞን ተራራ የሚወጡበት አጥተው ሲጨነቁ አንድ ታላቅ ዘንዶ ራሱን ወደተራራው ጫፍ ጅራቱን ወደተራራው ስር አድርጎ ሲንቀሳቀስ አዩ ። እርሳቸውም ሌላ አማራጭ ስላልነበራቸው የዘንዶውን ጅራት ጨብጠው በዘንዶው ጉልበት ተስበው በደብረ ዳሞ አንባ ላይ ወጥተዋል ተብሎ በገድላቸው ተጽፏል ።

*211· ሕንጻሃ ስ*

*እስራኤል ዘሞዕዎ ለጸላኢዘሙ ባሕር*
*አኮ በሆናት ዳዕሙ ዘበትር ።*

### ትርጉም

እስራኤል ጠላታቸው/ባህርን ያሸነፉት
በጦር አይደለም ፣ በበትር ነው እንጂ።

### ምስጢር

ባላገሮች ሲጣሉ በበትርም በድንጋይም ተደባድበው የበረቱት ያሸንፋሉ ። እስራኤልም ከግብፃውያን ጋር ጦርነት ሳይገጥሙ በሙሴ በትር ባህርን ከፍለው ግብፃውያንን አሰጠሙ ይላሉ ባለቅኔው ።



*212 ዕዝል ዕጣነ ሞገር (108)ዩ*
*ዘገብረ ሚካኤል (ባዜተዊ)*

*መቃብረ ድንግል ሐተተ አእዳወ ጴጥሮስ መምህር ፣*
*እንዘ በእፍኣ ጻድቅ መቃብር*
*አምጣነ ኃጥእ በውሳጤሁ ዘውስተ ልበ ሰብእ ምድር*
*ለእመ አልቦ ዘየእምር ።*
*ወንስሓ ዕፄ ቀሊል ፣ እስመ ለዕፄ ፍጡር*
*ጌጋዩ ሐልዮ ወአኮ ገቢር ።*

### እሠረ ንጉሥ

*እስኩ አኀው ተዘከርዋ ለብእሲተ ሎጥ ፍቅር ፤*
*ለእመ አምላክ አነመ ተሐውኮ ወተአጽፎቶ ብሔር*
*እስመ እምዐይነ ሰብእ ዘይኔጽር*
*ኢትክል ተከብቶ ሀገር*
*እንተ ተሐንጸት መልዕልተ ደብር ።*

### ትርጉም

የመምህር ጴጥሮስ እጆች የድንግልን መቃብር መረመሩ
በሰው ምድር ልብ ውስጥ ያለውን
የሚያውቅ ባይኖርም መቃብር በውጭ ፃድቅ ሲሆን
በውስጡ ሃጢአተኛ ነውና ፣
የትል ንስሃም በእርሱ ዘንድ ቀላል ነው ፣ ለፍጡር/ትል
በደሉ ማሰብ እንጂ ፣ ማድረግ አይደለም ።

### እስረ ንጉስ

እስኪ ወንድሞች ! የሎጥ ሚስት/ፍቅርን አስቧት ፣
አምላክ መታወክን ቢሰራና አገር ብትገነፀፈው
ከሚያይ የሰው አይን
በተራራ ላይ የተከተመች
ከተማ መሸሸግን አትችልምና ።



www.ethiopianorthodox.org

## ምስጢር

በውስጥ ሃጢአተኛ ሲሆን በውጭ ፃድቅ የሚመስለውን ሰውዳኞች በአደባባይ እንደሚመረምሩት በውስጡ የሰው ደምና አጥንት ያሉበት ሲሆን ውጪው በእብነ በረድ የሚለሰን መቃብርን የጴጥሮስ እጆች ቆፈሩት ። በሰው ልብ ያለውን አሳብ የሚያውቅ እንደሌለ በምድር ውስጥ ያለውን ልዩ ፍጥረት የሚያየው የለም ። በማድረግ ከተፈፀመ ሃጢአት በማሰብ የተፈፀመ ሃጢአት እንደሚቀል በቅድስት ማርያም መቃብር የሴላው ሬሳ ትል አልተፈጠረም ፡ ስጋዋንም ሊበላ አልቻለም ። የሎጥ ሚስት የጨው ሃውልት ሆና የቀረችበትን ነገር ማሰብ እንደሚገባ ፍቅርን ማጥናት ይገባል ። ሸማኔ የሰራውን ሸማ ያሰራችው ሴት እንደምትለብሰው እንዲሁም አምላክ ያዘዘውን መታወክ አገር ታወክች ። በተራራ የተከተመች ከተማ ከተመልካች አይን እንደማትሰወር ከወራሪ ልታመልጥ አልቻለችም በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

## ታሪክ

ባህታዊ ገብረ ሚካኤል አፄ ዮሃንስ አራተኛ ጎጃምን በ1870 በነሃሴ ወር ከመውረራቸውና ከመዝረፋቸው አስቀድሞ በህዝቡ ላይ የሚደርሰውን መከራ ስለተረዱ ጥር 21 ቀን 1870 ኢ.ም. በዋሸራ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ይህን ቅኔ ተቀኝተዋል ። በተከታዩም አመት ረሀብ የሚመጣ መሆኑን ስለተገነዘቡ "በሀፀደ ረኃብ ያንሶሱ እግረ ተዋርዶ ፡ በረሀብ የአትክልት ቦታ የመዋረድ እግር ይመላለሳል" የሚል መወድስ ቅኔ ተቀኝተው መንነዋል ። በዘረፋውም ምክንያት የአፄ ዮሃንስ ወታደሮች በዋሸራ ማርያም እቃ ቤት ብዙ ሀብት ስላገኙ አሸራ ማርያም ብለው ሰይመዋታል ተብሎ ይተረካል ።

*213 ዕዝል ዕጣነ ሞገር (1176)አ*

*ዘራስ ወርቅ (መምህር)*

*ለእመ ኢሞተት ቅድመ ኅጠተ ሥርናይ እግር*
*ባሕቲታ ትሄሉ ወትነብር ፡*
*ባሕቱ እመ ሞተት ወእመ ረከባ ኀሣር*



*ትፈሪ ክንፈ ክብር ።*

*ወቃለ ማዕነቅ ተሰምዐ በገቦ ተክለ አብ ምድር ፡*
*ለኀሚደ አምጣነ አልጸቀ ተክለ አብ ግእረር ።*

## አሠረ ንጉሥ

*ኢትዮጵያ ይእቲ እስክንድርያ መንበረ ማርቆስ በኤር*
*ርኅቀተ ሀገር ሀባይ አኮኑ አይከልአ ለፍትር ።*
*ወሀየንተ ማርቆስ መፈክር*
*ሀየ ሀሎ አብርሃም ምእመን ኄር ፡*
*ሕገጊሃ አኮኑ ማእምር ።*

## ትርጉም

የስንዴ ቅንጣት/እግር በመጀመሪያ ባትሞት
ብቻዋን ተቀምጣ ትኖራለች ፡
ግን ከፈረሰችና በጭቃ መለወስ ካገኛት
የክብር ክንፍን ታፈራለች ።
የቁርዬ አሞራ ቃልም በተክለ አብ ጎን/ምድር ተሰማ ፡
ተክለ አብ አዝመራ ለአጨዳ ደርሷልና ።

## አስረ ንጉስ

ኢትዮጵያ የታላቅ ማርቆስ ወንበር የሆነች እስክንድርያ ናት ፡
የታላቅ "አገር መራቅ ፍቅርን አይከለክላትምና" ።
ስለተርጓሚ ማርቆስም ፈንታ
ቸር ታማኝ አብርሃም በዚህ አለ ፡
ህጎቿን አዋቂ ነውና ።

## ምስጢር

የስንዴ ቅንጣት በእርሻ ጭቃ ውስጥ ካልበሰበሰች ልትበቅልና ፍሬ ልታፈራ አትችልም ። ከበሰበሰችና ከበቀለች በኋላ ግን ብዙ ፍሬን ልታፈራ ትችላለች ። እንዲሁም የአቡነ ተክለ ሃይማኖት እግር በመቆም ብዛት በመሰበሩ ስድስት የፀጋ ክንፎች ተሰጧቸው ። ደግሞ የቁርዬ



www.ethiopianorthodox.org

አሞራ ቃል በየአመቱ ሚፀደይ ወራት እንደሚሰማ ሁሉ በተክለ ሃይማኖት ጎን ክንፍ በቀለ ። አዝመራው ለአጨዳ እንደሚደርስ ተክለ ሃይማኖት እግራቸውን እስከ መሰበር ደረሱ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል።

ታሪኩ በአንደኛው መፅሃፍ በገፅ 77 ተተርኳል ።

214 ዕዝል ቱባኤ ቃና (177) አ

ለተራክቦ ሞት ላሕም ዘወለደቶ ለኖላዊሁ በደሮ
ዘበተከ ስምዖን ጣዕዋ ኑኀ መዋዕል ማእሰሮ ።

## ትርጉም

የዘመን ርዝመት ማሰሪያውን የበጠሰ ስምኦን/ ጥጃ
የወለደችው ላም ሞትን ለመገናኘት ጠባቂውን ቀደመው ።

## ምስጢር

ማሰሪያውን በጥሶ ከወለደችው ላም ጋር ለመገናኘት የሮጠ ጥጃ እረኛውን እንደሚቀድመው ፡ በእርጅና ምክንያት በአልጋው ላይ ተጣብቆ የኖረው ስምኦን አረጋዊ ከዚህ አለም በሞት እንዲያሰናብተው ክርስቶስን ለመነው ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

## ታሪክ

የአሪት ካህን የነበረው ስምኦን የነቢዩ ኢሳይያስን የትንቢት መፅሀፍ ሲፅፍ "እነሆ ! ድንግል በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ወንድ ልጅ ትወልዳለች" የሚል ቃል አገኘ ። ስምኦን ነገሩ በታሪክ ያልታየ አዲስ ስለሆነበት "ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ?" ብሎ ነበር ። ይሁን እንጂ እርሱ የእድሜ ባለፀጋ በመሆኑ ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመኑ ተወለደ ። እንደማንኛውም እብራዊ ህፃን በተወለደ በአርባ ቀኑ ዮሴፍና እናቱ ቅድስት ማርያም ኢየሱስ ክርስቶስን ወደቤተ መቅደስ ባስገቡት ጊዜ ካህኑ ስምኦን ታቀፈው ። በዚህም ጊዜ ስምኦን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደታቀፈ "እንግዲህስ ባሪያህን አሰናብተኝ" በማለት ለሰው ልጅ ሁሉ የማይቀረውን የሞት ፅዋ ለምኗል ተብሎ ተፅፏል (ስንክ. የካቲት 8) ።



215 ዘአምላኪየ (1181)አ
ዘደሴ (ማዕበል)

ማዕቀበ አልፋ መምህር በአነዳሁ ጠፈር
ለልሕሆት ባሕረ ኢያሪኮ ዘሙሴ ሰበሮ ፡
እስመ ልደተ ቃል ቄዳር ምዕላደ ሐሊብ ገብሮ ።

## ትርጉም

ሙሴ የሰበረውን የኢያሪኮ ባህር ሸክላን
መምህር ማአቀበ አልፋ በቁርበት ጠፈረው ፤
የክርስቶስ ልደት/ዘላን የወተት ማከማቻ አድርጎታልና ።

## ምስጢር

ባለላም የተናጋውን (የተሰበረውን) የወተት ማስቀመጫ በቁርበት ይፍረዋል ። ማአቀበ አልፋ የሚባሉት ኢትዮጵያዊ ፃድቅ አባ ስጣቴዎስም ተማሮቻቸውን ለማሻገር በኢያሪኮ ባህር ላይ አፅፋቸ ጫኑበት ። ተንቦው በቁርበት የሚጠፈረው የወተት ማጠራቀሚያ ሆነ ክርስቶስ በተወለደበት ቀንም ባህሩ ወተት ሆነ ይላሉ ባለቅ ።

216 ሥላሴ (1187)አ
ዘአድማሱ ጀንበሬ (መልአከ ብርሃን)

ኢትክሉ ተቀንዮተ
ለእግዚአብሔር ወለንዋይ
ለዘይብለከ አምላክ ሰማዒ መቅድመ ኵሉ ታፍቅሮ
ለገብርከ አፍቅሮ ንዋይ ይእዜ ሰዐሮ ፤
እመሰ ለወርቅ አፍቀርኮ ወአስተባዛኀከ ክብሮ
እንዘ በጥንቁቅ ታነብሮ
አእምሮ አእምሮ አእምሮ
ከመ ኮንከ ለንዋይ ገብሮ ።



www.ethiopianorthodox.org

## ትርጉም

ለእግዚአብሄርና ለገንዘብ
መገዛትን አትችሉም "ያለህን
እምላክ ለሚ ! ከሁሉ በፊት ታፈቅረው ዘንድ
አገልጋይህ/ገንዘብ መውደድን ዛሬ አስናብተው ፡
ወርቅን ብትወድ ክብሩንም ብታበዛ
በጥንቃቄ እያኖርኸው
የገንዘብ አገልጋዩ እንደሆንህ
ማወቅን እወቅ ፡ እወቅ ።

## ምስጢር

"አንድ አገልጋይ ለሁለት ጌቶች መገዛት አይቻለውም" እንደተባለ እግዚአብሄርን እወዳለሁ የሚል ሰው ገንዘብን በጣም የሚያፈቅር ከሆነ የእግዚአብሄር ወዳጅ ሊሆን አይችልም በማለት ለገንዘቡ ሲንሰፈሰፍ የእግዚአብሄርን ትእዛዝ መፈፀም የሚያዳግተው መሆኑን ባለቅኔው ያስገነዝባሉ ።

*217 መወድስ (1193)አ*

*ዘገብረ ሥላሴ (መምህር ፡ ዘኢልያስ)*

*ተራኅቆ ዘመድ ይኄይስ እምተቃርቦቱ ፡*
*ለዝኒ ነገር ከመ ንለቡ ምስጢሮ*
*በዋሕድ ከርሥ ሶበ ጊዜ ዕንሱ ነጸሮ*
*ያዕቆብ ለኤሳው*
*አእመረ ከመ ጸላኢሁ ወአዕቀፀ እግሮ ፡*
*ወለዘክልኤሆሙ ተግርሮ*
*እመጽሐፈ ዛራ ወፋሬስ ንሕነ ንዜክሮ ።*
*ፈቀደሰ ተራክቦቶ ከርሠ ወላዲቱ ሰቆሮ*
*ዮሐንስ ለእግዚኡ ውስተ ከርሠ እሙ ሶበ አእመሮ ፡*
*ርኅቀተ መካን ወከርሥ ኀበ ለዝንቱ አሥመሮ*
*ወንጌል ተራኅቆ አምጣነ ትሰብክ ተፋቅሮ ።*



## ትርጉም

ከመቀራረቡ ከዘመድ መራራቁ ይሻላል ፡
የዚህን ነገር ምስጢር ልብ እንድንል
ባንድ ሆድ በፅንሱ ጊዜ ቢመለከተው ፡
ያእቆብ ኤሳውን
ጠላቱ እንደሆነ አውቆ እግሩን አሰናከለው ፡
የሁለታቸውንም መፃረር (መጣላት)
ከዛራና ከፋሬስ መፅሃፍ እኛ እናስታውሰዋለን ።
ለዮሃንስ ግን ጌታውን በእናቱ ሆድ ባወቀው ጊዜ
የእናቱን ሆድ ቀዶ መገናኘቱን ወደደ ፡
የቦታና የሆድ መራራቅ ይህን ካሰመረው ዘንድ
መራራቅ/ወንጌል መፋቀርን ትሰብካለችና ።

## ምስጢር

ቤትና ቤት ተያይዞ (ተቀራርቦ) ሲሰራ መንቀሳቀሻ እንደሚታጣ ዘመድና ዘመድም ሲጠጋጋ ፍቅር ይጠፋል ፡ ይህም ሁኔታ በያእቆብና በኤሳው ፡ በዛራና በፋሬስ ቅራኔ ተገልጧል ። መራራቅ ፍቅርን እንደሚያጠና ዮሃንስ በእናቱ ሆድ ሳለ በቅድስት ማርያም ሆድ ለተፀነሰ ለኢየሱስ ክርስቶስ ባቀረበው ስግደት ይታወቃል በማለት ባለቅኔው አመስጥረዋል ።

## ታሪክ

ያእቆብና ኤሳው መንታ ሆነው የተወለዱ የይስሃቅና የርብቃ ልጆች ናቸው ። በምጥ ጊዜ በእናታቸው ሆድ ውስጥ ይገፋፉ ነበር ። ኤሳው አስቀድሞ ብቅ ካለ በሁዋላ ያእቆብ በእጁ የወንድሙን እግር ይዞ አሰናከለና ራሱ ቀድሞ ተወለደ ። በዚህም ምክንያት ያእቆብ ተብሎ ተሰየመ ። ያእቆብም ማለት ተረከዝ አሰናካይ ማለት ነው (ዘፍጥ. 25፡ 19—26) ።

የያዕቆብ ልጅ ይሁዳ ለልጁ ለኤር ትእማር የተባለች ሚስት አጋባው ። ኤር ሞተ ፡ ሚስቱንም በኦሪቱ ህግ መሰረት ወንድሙ አውናን ወረሳት ። አውናን ሳይወልድ የሞተ የወንድሙ የኤር ስም መጠሪያ



www.ethiopianorthodox.org

የሚሆን ልጅ መውለድ ስላልፈለገ የወንድሙን ሚስት በሩካቤ ስጋ ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ ዘሩን ከማህፀን ውጭ ያፈስ ነበር ። እርሱም እንደ ወንድሙ ሞተ ። ከዚህ በሁዋላ ይሁዳ ትእማርን "ልጄ ሴሎም እስኪያድግ ድረስ ሂጅና በብቸኝነት ኑሪ" ብሎ አሰናበታት ። በዚያን ጊዜ የይሁዳ ሚስት ሞተች ፤ ይሁዳም ከሞተችው ሚስቱ አዘን ከተፅናና በሁዋላ በጎቹን የሚሸልቱት ሰዎች ወደአሉበት ወደቴምናታ ሄደ ። ትእማርም መሄዱን ሰማችና ሌላ ጋለሞታ መስላ ተሸፋፍና በመንገዱ ዳር ጠበቀችውና አታለለችው ። ይሁዳም ደረሰባትና መንታ ፀነሰች ። በምጥዋም ጊዜ አንዱ እጁን አወጣና ቀይ ፈትል አሰረችበት ። እርሱም ዛራ ነው ዛራም እጁን መለሰና ወንድሙ ወጣ ፤ እሱም ፋሬስ ነው ። ከርሱም በሁዋላ ባለቀይ ፈትል ዛራ ተወለደ ፡ (ዘፍጥ. 38፥ 1—30) ።

የአሪቱ ሊቀ ካህናት የዘካርያስ ሚስት ኤልሳቤጥ ዮሃንስን በፀነሰች በስድስተኛው ወር ገብርኤል የተባለው መልአክ ወደድንግል ማርያም ተልኮ አበሰራት ። ቅድስት ማርያም በተበሰረችው ብስራት ካመነች በሁዋላ የእግዚአብሄርን ቃል በመንፈስ ቅዱስ ፀነሰች ። በዚያው ወራትም ወደ ይሁዳ ከተማ ሄደችና ወደዘካርያስ ቤት ገባች ፤ ኤልሳቤጥ ንም ሰላም አለቻት ። በዚህም ጊዜ በኤልሳቤጥ ሆድ ውስጥ ያለው የስድስት ወር ፅንስ ዮሃንስ በድንግል ማርያም ሆድ ውስጥ ላለው ፅንስ ኢየሱስ ክርስቶስ መፈንደቁ ፡ ብድግ ብድግ ማለቱ ተፅፏል (ሉቃ.1፥1— 80)።

*218 መወድስ /ስ*

*ናሁ መሐለ እግዚአብሔር*
*ለዳዊት ወይን ዘኑሡሠ ማኀደሮ*
*ከመ ለፍሬሁ ሥሙር ዲበ መንበሩ ያንብሮ ፤*
*ለሳዖል ዘመነ ክረምት አኮኑ ሰሀሮ ፡*
*ወይን ዘአፍቀሮ*
*ድኅረ ኮነ መርሐ ለጽጌ ገዳም ዘምሮ ።*
*ወቀንሞስ ጸናጽል ምስለ ናርዶስ ከበሮ*
*ለመዝሙር ዘመነ ጽጌ ፈድፋደ ያሠምሮ*
*ለአዳም ወይን አምጣነ የአምር ግብሮ*
*እግዚአብሔር ዘብርሃናት በአርአያ ደሙ ከመ ይፍጥሮ ።*



## ትርጉም

የተወደደ ፍሬውን /ልጁ ሰሎሞንን/
በዙፋኑ ያስቀምጠው ዘንድ ማደሪያውን
ሰፈለገ ለዳዊት ወይን እነሆ እግዚአብሄር ማለ ፤
የወደደው ወይን ለዱር አበባ/መዘመር
መሪ ከሆነ በሁዋላ
ሳኦል/የክረምት ዘመንን ሽሮታልና ።
ቀንሞስ /ፀናፅልም ከናርዶስ/ ከበሮ ጋር
መዝሙር/የፅጌ ዘመንን በጣም ያሳምረዋል ፤
የብርሃናች አምላክ እግዚአብሄር በደሙ አምሳል
ሳይፈጥረው የአዳም/ወይን ግብርን ያውቃልና ።

## ምስጢር

እግዚአብሄር ለዳዊት ልጁን ሰሎሞንን በዙፋኑ እንደሚያነግስለት ምሎለታል ። ለወይንም ልምላሜን አደረገለት (ወይንን አለመለመው) ። ዳዊት የአምላክን ቤተ መቅደስ ለመስራት እንደተመኘ ወይንም ለቤተ ክርስቲያን ለቅዳሴ አገልግሎት ጠቃሚ ሆነ ። የዳዊት ልጅ ሰሎሞንን በአባቱ ዙፋን እንዳነገሰውም የወይን ፍሬን በአልጋው ላይ አንዠረገገው። ከዳዊት በፊት የእስራኤል ንጉስ የነበረ ሳኦልንም ከመንግስቱ እንደሻረው ክረምትን በጊዜው አሳለፈው ። ዳዊት መዝሙርን ለመዘመር መሪ እንደሆነ ወይንም "በወርሃ ፅጌ (ከመስከረም 26 እስከ ህዳር 6 ቀን) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚቀርበው ዝማሬ ማኀፀባረቂያ ሆነ ። ፀናፅልም ከከበሮ ጋር የሰንበትን መዝሙር እንደሚያደምቀው ቀንሞስ የተባለው የሽቶ እንጨት ናርዶስ ከሚባለው እፅ ጋር የፅጌን ወራት አደመቀው ። እግዚአብሄርም አዳምን በአምሳያው ከመፍጠሩ በፊት ስራውን እንደሚያውቀው ወይንን በተግባር ሊያውለው ወደደ ። የልጁ የእግዚአብሄር ወልድ ደምን በወይን ፍሬ ጭማቂ አምሳል እንዲሰጥ አደረገ በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

*219 መወድስ (1204)አ*
*ዘበቃ (ቄሰገበዝ ፡ ዘጎንጅ)*

www.ethiopianorthodox.org

*ግብታዊት ጸብእ አመ በጽሐተኒ*
*ድኅረ ሰማንያ ዘመን ስእንኩ ተናግሮ ፤*
*ለልሳንየ ዘውስጥ እስመ አሰሮ*
*ርስዐነ ሥጋ ወለዐይንየ*
*ጽልመት መንጦላዕተ ግብጽ ፍጹመ ሰወሮ*
*ኢይጕየይ በነጽሮ*
*ጸላኤ ሥጋ ዘመጽአ እንዘ ያስተፋጥን አግሮ ።*
*ተነሥተኒ ወተመዝበረ ቤተ ልብየ ዘውቅሮ*
*በፍርሃት ወበድንጋፄ ሞተ እለ ኢዮዓብ ተዘኪሮ ፤*
*ወበዝ ኢትፍትሑ ብየ ደቂቀ አእምሮ*
*ጴጥሮስ አመ ፈርሀ እስመ ክሀደ ዘፈጠሮ*

## ትርጉም

ድንገተኛ ጠብ በደረሰችብኝ ጊዜ
ከሰማኒያ ዘመን በሁዋላ መናገር ተሳነኝ ፤
የውስጥ ምላሴን የስጋ እርጅና
አሰሮታልና ፣ አይኔንም
እግሩን እያፋጠነ የመጣ የስጋ
ጠላትን በማየት
እንዳይሸሽ ጨለማ/የግብፅ መጋረጃ በፍፁም ሰውሮታልና ።
በፍርሃትና በድንጋጤም የእነኢዮአብን
ሞት አስቦ የገንዘብ ቤት/ልቤ ፈረሰና ተመዘበረ ፤
በዚህም የእውቀት ልጆች! አትፍረዱብኝ ፤
ጴጥሮስ በፈራ ጊዜ የፈጠረውን ክዷልና ።

## ምስጢር

አምባገሮ በተፈጠረ ጊዜ የደነገጠ ሰው ምላሱ ይተሳሰራል ፤ ሰውነቱ ይርዳል ። ድንገተኛ ሞትም ሲደርስ የሰማንያ አመት ሽማግሌ መናገር ያቅተዋል ። እርጅና ምላሱን ይይዘዋል ፤ ሰውነቱን ያብረከርከዋል ። ደግሞ አልጋ በመጋረጃ እንደሚጋረድ ጨለማ አይኑን ይሸፍነዋል፤ በድንገት ከደረሰ ሃይሰኛ ጠላት ማምለጥ እንደማይቻልም ከእርጅና መታደስ አይቻልም ። የግንብ ቤት እንደሚናድና እንደሚፈርስ ልብም በእርጅና ሃይል ፍስስ (ቅልጥ) ይላል ። ዳዊት ለሰሎሞን ያስተላለፈው በቀል መቼ እንደሚፈፀምባቸው በማሰብ የፈሩ የእነኢዮአብ ፍራትና ድንጋጤ ይሰለጥኑበታል ። ባለቅኔውም ከሰማንያ ዘመን በሁዋላ ይህ ሁሉ ነገር ቢሆንባቸውም መቼም የሊቅ ልብ እስከሞት ህቅታ ድረስ ስለሚሰራ ይህን ቅኔ ዘርፈዋል ። ለፍራታቸውም መከታ ሲያበጁለት ሃዋርያው ጴጥሮስን ጠቅሰዋል (1 ነገስ· 2፡ 5 – 34) ።

*220 መወድስ (1199)አ*
*ዘአስበ ፃድቅ*

*ስምዑ ዘንተ በእዝነ ልቡና*
*ዘብክሙ እዝን ፣ ወዘብክሙ አእምሮ ፤*
*ወትጉሃነ ልብ ኩኑ ከመ ትለብው ምክሮ*
*ለመጽሐፍ ዘይምዕደነ ሠናየ ምስጢሮ*
*ከመ አማኑኤል ዘአንከሮ*
*ብእሲ ምእመን ዘለእግዚኡ አሥመሮ ።*
*ወርቀሂ ኢታፍቅሩ ወኢትኅሥሡ አሁሮ ፡*
*እስመ ወርቅ ዘየኀልፍ ይስኪ ዘአፍቀሮ ፤*
*ወለእመ በወርቅ ኮነ እንተ አብርሃም ተምሕሮ*
*ለኪራም በዐለ ወርቅ እልቦ ዘያከብሮ ።*

## ትርጉም

ጆሮ ያላችሁ ፣ አእምሮም
ያላችሁ ሰዎች! ይህን በጆሮ ልቡና ስሙ
አማኑኤል እንዳደነቀው ጌታውን እንዳገለገለ
ታማኝ ሰው ጥሩ ምስጢርን የሚመክረን
የመፅሀፍንም ምክሩን
ልብ ትሉ ዘንድ የልብ ትጉዎች ሁኑ ።
ወርቅንም አትውደዱ ዱካውንም አትፈልጉ ፤
የሚያልፍ ወርቅ የወደደውን ይከሳልና ፣
የአብርሃም መማር (መፅደቅ) በወርቅ ቢሆን ኖሮ
ባለወርቅ ኪራምን የሚያከብረው አይኖርምና ።


www.ethiopianorthodox.org

## ምስጢር

"በጎ ምክር ለሚፈፅማት ሁሉ መልካም ናት" በተባለው መሰረት በመፃህፍት ምክር የሚኖር ሰው የአምላክ ታማኝ ነው ይላሉ ባለቅኔው ። የጢሮስ ንጉስ የነበረ ኪራም የከበረበት ወርቅም ቢያደልቡት ፣ በሁዋ ጊዜ (በአምላክ ፍርድ ቀን) አድላቢውን ይከለዋልና ወርቅን አታድል በማለት ደራሲው በቅኔያቸው ምስጢር በጎ ምግባርን ያስተምራሉ ( ላሙ· 5 ፡ 11) ።

*221 ግእዝ ጉባኤ ቃና (1495)አ*

*ሕሙም ይስሐቅ ሶበ ለመዊት አልጸቀ*
*ዘመደ ሥጋሁ መጥባሕት በአንብበ ደም ተጠምቀ ።*

## ትርጉም

የታመመ ይስሃቅ ለሞት በደረሰ ጊዜ
የስጋ ዘመዱ /ሰይፍ በደም/ እንባ ተጠመቀ ።

## ምስጢር

አንድ ሰው ታሞ ለሞት ሲያጣጥር ወዳጅ ዘመዱ እንባ በእንባ እንደሚራጭ ፣ ይስሃቅም ሊሰዋ በቀረበ ጊዜ የአባቱ የአብርሃም ሰይፍ በተአምራት ደም ተቀብቶ ተገኘ ይላሉ ባለቅኔው (ስንክ·ሃምሌ 7) ።

*222 ግእዝ ጉባኤ ቃና (1493)አ*
*ዘወርቅ አገኘሁ (አለቃ)*

*ዕውር ኅጥእ ውስተ ግበ ሲኦል ወድቀ*
*መንግሥተ ሰማይ በርሀ ሶበ ለጻድቃን ሠረቀ ።*

## ትርጉም

መንግስተ ሰማይ/ብርሃን ለፃድቃን በወጣ ጊዜ
እውር/ሃጢአተኛ በሲኦል/ጉድጓድ ወደቀ ።

## ምስጢር

ብርሃን ቢወጣም መሪ የሌለው እውር በጉድጓድ ከመውደቅ እንደማይድን መንግስተ ሰማይ ለፃድቃን ሲሰጥ ሃጢአተኛ ወደሲኦል ገባ በማለት ባለቅኔው ወደ መንግስተ ሰማይ ለመግባት መልካም ምግባር



አስፈላጊ መሆኑን በቅኔያቸው አስረድተዋል ።

*223 ዕዝል ጉባኤ ቃና (1494)አ*

*ለቤዝወ አዳም ጳውሎስ እምሐቌ ኢያቄም ሠረቀ*
*ዘበውስተ ሕፅኑ ለስምዖን ማኅየዊ ተሐድሶ አካል ረፈቀ ።*

## ትርጉም

በስምኦን ጭን የተቀመጠ አዳኝ/የአካል መታደስ
አዳም/ጳውሎስን ለማዳን ከኢያቄም ወገብ ወጣ ።

## ምስጢር

እግዚአብሄር ወልድ አዳምን ለማዳን ከኢያቄም ልጅ እንደተወለደ እንዲሁም ለጳውሎስ የሆነ የመንፈስ መታደስ ለኢያቄም ሆነ ። ክርስቶስ በስምኦን አረጋዊ ጭን እንደተቀመጠ መታደስም ለስምኦን አረጋዊው ተሰጠ ይላሉ ባለቅኔው (ስንክ· የካቲት 8) ።

*224 ግእዝ ጉባኤ ቃና /ስ*

*ይሁዳ ይመስል ከመ ቃለ መጽሐፍ ዘጸድቀ ፤*
*ውስተ ቤተ መቅደስ ለሕዝብ አምጣነ ዘረወ ወርቀ ።*

## ትርጉም

እንደ መፅሃፍ ቃል ይሁዳ የፀደቀ ይመስላል ፣
በቤተ መቅደስ ውስጥ ወርቁን ለህዝብ በትኗልና ።

## ምስጢር

ዳዊት በመፅሃፉ "ወርቁን ለችግረኞች በተነ" ብሏል ። ከዚህም አንፃር ይሁዳ መምህሩ ኢየሱስ ክርስቶስን የሸጠበትን ወርቅ በትኖ መታነቁንና መሞቱን ለማስረዳት ባለቅኔው አመስጥረዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

225 ዕዝል ጉባኤ ቃና/ስ
ዘይትባረከ ቂርቆስ (መሪጌታ ፣ ዘደብረ ፅሙና)

ነጋዲ ረኀብ ኢትፈጽም ባሕታዌ ገዳም ሥንቀ
ፍኖትከ ጾም እስመ ኢኮነ መንፈቀ ።

## ትርጉም

ነጋዴ/ራብ! የገዳም ባህታዊ/ ስንቅህን አትጨርስ ፤
መንገድህ/ፆም ግማሽ አልሆነምና ።

## ምስጢር

የሚነግድ ነገዴ ካሰበው ቦታ ሳይደርስ ስንቁን ሲያዋግደው ጓደኛው "ጉዞህ ገና አልተጋመሰም ፤ ስንቅህን ቆጥብ" ይለዋል ። ራ ፆመ ኢየሱስ (ኩዳዴ) ሳይጋመስ ባህታዊን አታመንምነው ይ ባለቅኔው ።

226 ዋዜማ (1498)አ
ወርቅ ሰማያዊ
ጥብሉለ ንስቲት ፀርቅ አመ ውስተ ምድር ወድቀ
አይሁድ ለነሢእ ኢያሁ ተሐየዩ ጥቀ
ጠቢባንሰ ነሥእዎ ወአእመርዎ ጥዩቀ ፤
አምጣነ ረሢአን አይሁድ ነጸሩ ፀርቀ
ወነጸሩ ጠቢባን ወርቀ ።

## ትርጉም

በትንሽ ወርቅ
የተጠቀለለ የሰማይ ወርቅ በምድር ቢወድቅ
አይሁድ እርሱን ለመውሰድ በጣም ቸለል አሉ
ጥበበኞች ግን በግልጥ አውቀውት ወደዱት ፤
ዝንጉዎች አይሁድ ጨርቅን አይተዋልና
ጥበበኞችም ወርቅን አይተዋልና ።



## ምስጢር

የድሮ ሰው ወርቅን (ገንዘብን) በጨርቅ ጠቅልሎ ስለሚይዘው ወርቁ በጨርቅ እንደተጠቀለለ ይወድቃል ። አንዳንድ ሰዎች አይተውት ጨርቅ ብቻ መስሏቸው ሳያነሱት ያልፉታል ። ሌሎች ጥበበኞች ግን አንስተው ያዩትና ወርቅ የጠፋህ ማነህ? እያሉ በቤተ ክርስቲያንም ፤ በሌላ ህዝብ በሚሰበሰብበት ቦታም ይለፍፋሉ ። ባለቤቱ ቢገኝ ገንዘቡን በምልክቱ መሰረት ይሰጡታል ። የወርቁ ምሳሌ የሆነ እግዚአብሄር ወልድ በኃለ እንስሳ (በእንስሳት በረት) ተወልዶ በጨርቅ ተጠቀለለ ። አይሁድ በአምላክነቱ ባያምኑበትም አምላክነቱን በተአምራቱ የተረዱት አምነው ተጠቀሙበት ። አይሁድ ያላመኑበት ሰው ሆኖ ቢያዩት ("ዕሩቅ ብእሲ ባዶ ሰው ፡ ሰው ብቻ)" ስለመሰላቸው ነው ። ሌሎችም ሰዎች ያመኑበት ስራው አምላካዊ መሆኑን ስለተረዱ ነው በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

227 ዋዜማ (1503)አ
ዘአርአያ ወረታ (አቶ)

በድምፀ ነጐድጓድ ድንግልና
ላዕለ እብነ ሀገር ፅንስ ከርሠ ድንግለ ዮሴፍ ወድቀ
ወዘንጽሕ ጸዳለ ተፍሕሮ ላዕሌሃ በረቀ ፤
ንጽሐ ድንጋሌሃሰ በርሀ እምርደተ መልአክ ተዐውቀ ፤
እኮኑ እምልብሱ ልማድ ማሕፀና ተዐርቀ ፡
ወበማይ ድንጋሌ ተጠምቀ ።

## ትርጉም

በነጐድጓድ ድምፅ/ድንግልና
የዮሴፍ ድንግል ሆድ በአገር ድንጋይ ፅንስ ላይ ወደቀ ።
የንፅህና ፀዳል መታጨትም በእርሷ በረቀ
የድንግልናዋ ጥራት ብርሃን ግን ከመልአክ መውረድ የተነሳ ታወቀ፡
ከልብሱ/ልማድ ማህፀኗ ተራቁቷልና ፤
በውሃ/ድንግልናም ተጠምቋልና ።

www.ethiopianorthodox.org

## ምስጢር

የነጐድጓድ ድምፅ በድንገት ሲሰማና መብረቅ ሲበርቅ መንገደኛው ደንግጦ በድንጋይ ላይ እንደሚወድቅ የንፅህና መታጨትን ከታጨች በሁዋላ የቅድስት ማርያም ሆድ በድንግልና ፅንስን ፀነሰ ። ብርሃንም ከመልአክ መውረድ የተነሳ ወገግ እንዲል እንዲሁም የማርያም የድንግል ናዋ ጥራት ተገለጠ ። ራሱን በውሃ መጠመቅ የሚሻ ሰውም ልብሱን እንደማያወልቅ የማርያም ድንግልናዊ ንፅህና ከሴቶች ልማድ ተለየ (ራቀ)፣ በድንግልናም ጠና በማለት ባለቅኔው አስገንዝበዋል ።

*228 ዋዜማ (1501)አ*
*ዘይርጉ (አለቃ)*

*ገብርኤል ተፈናዊ*
*ይትዐጸፍ ምንተ ጊዜ ወርኀ ጥምቀት አልጸቀ*
*እስመ ነድ ልብሱ በሕፅበት ኀልቀ ።*
*ተሐጽቦተ ልብሱሰ ነድ ኢያስተዋረዶ ጥንቁቀ ፤*
*እስመ እግዝእቱ ድንግል ትፈትል ወርቀ*
*ወእግዚኡ ይትአጸፍ መብረቀ ።*

## ትርጉም

የጥምቀት ወር በደረሰ ጊዜ
ተላላኪ ገብርኤል ምንን ይለብሳል?
ነዲድ/ልብሱ በመታጠብ አልቋልና ፤
የነዲድ/ልብሱ ማለቅስ በፍፁም አላዋረደውም ፤
ድንግል/እመቤቱ ወርቅን ትፈትላለችና
ጌታውም መብረቅን ይለብሳልና ።

## ምስጢር

አንድ ልብስ ብቻ ያለው አሽከር ያው አንድ ልብሱን በእጥበት እንደ ጨረሰ የተመለከቱት ሰዎች "ይህ ሰው በክረምት ምን ሊለብስ ነው" ይላሉ ። ይህን የሰሙ ሌሎች ሰዎች ደግሞ "እመቤቱ ልብስ



www.ethiopianorthodox.org

ሞልቷታል ጌታውም ሞልቶታል ፤ ውራጃቸውን ይሰጡታል" በማለት ያስረዳሉ ። ልብስ በውሃ እየታጠበ እንደሚያልቅ የመልአኩ የቅዱስ ገብርኤል የተፈጥሮ ባህርይ የሆነ እሳት ለእነቂርቆስ እንደውሃ ቀዘቀዘ ። ብዙ ሃብት ያላት ሴት ከወርቅ በተሰሩ የተለያዩ ጌጣ ጌጥ እንደምታጌጥ ቅድስት ማርያምም በወርቅ ተመሰሎ መሶበ ወርቅ ያሰኛት ወልድን ወለደች ። አንድ አርበኛ የተሸለመው የወርቅ መዳሊያ እንደመብረቅ ብልጭ እንደሚል ክርስቶስም መብረቅን ያወርዳል በማለት ባለቅኔው በገብርኤል መልእክተኛነት ተፈፀመ ስለሚባለው ተአምር በቅኔያቸው አስረድተዋል ።

*229፡ ሥላሴ (345) ጎ*

*ሶበ ሰምዐ ድምፀ እሳት*
*ጕየ ሎጥ ውስተ ገዳም*
*መሥዋዕተ ኀጢአት ሰብአ መዋቲ እስከ ይሠውዕ ጥንቁቀ*
*እሳት በላዒ ዘበሰዶም ጸድቀ ፤*
*አመ እግረ ሕፃን ቂርቆስ ባሕቱ ብሔረ ነነዌ አልጸቀ*
*እሳት ጕየ እስከነ ርኅቀ ፤*
*እስመ ለበላዒ እሳት ኃምሳ ደቂቀ*
*ፋሲካሁ በኤልያስ ኀልቀ ።*

## ትርጉም

በሰዶም የፀደቀ በላተኛ/
እሳት ሟች ሰው/የሃጢአት
መስዋእትን በጥንቃቄ እስኪሰዋ ድረስ ፤ የእሳት ድምፅን
በሰማ ጊዜ ሎጥ ወደዱር ሸሸ ፤
የህፃን ቂርቆስ እግር ግን ነነዌ በደረሰ ጊዜ
እሳት እስኪርቅ ሸሸ ፤
እምሳ ልጆችን የበላ እሳት
ፋሲካው በኤልያስ ጊዜ አልቋልና ።

## ምስጢር

አንድ ሰው የጠላቱን ድምፅ ከሩቅ በሰማ ጊዜ ይሸሻል ፤ ሎጥም ሰዶምና ገሞራን ካቃጠላቸው እሳት ለመዳን በዋሻ ተሸሸገ ። አሪታዊ የሃጢአት ማስተስረያ መስዋእትን እንደሚሰዋ ከሰማይ የወረደ እሳትም በኤልያስ ጊዜ ሃጢአተኛውን ሰው አቃጠለው ። የሸሸ ሃይለኛ ሰውን ሌላ ሃይለኛ ሯጭ ሰው ቢከተለውም እንደማይደርስበት እሳት ነነዌንና ቂርቆስን አላቃጠላቸውም ። በተጨማሪም ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን ከአርባ ቀን ፆም በሁዋላ የስጋ መብያውን ጊዜ በአምሳ ቀኖች እንደሚጨርስ ፣ እሳትም በነቢይ ኤልያስ ቃል ታዝዞ አምሳ ሰዎችን አቃጠለ ይላሉ ባለቅኔው ።

## ታሪክ

ሎጥ የአብርሃም የወንድም ልጅ ነው ። የሰዶምና የገሞራ ሰዎች በእሳት ሲቃጠሉ ሎጥ ከእነልጆቹ ሸሽቶ ከእሳት ቃጠሎ ድኗል ።

አካዝያስ ወድቆ በታመመ ጊዜ ብኤልዜቡል የሚባለውን ጣኦት ከህመሙ ስለሚድንበት ጉዳይ እንዲጠይቁለት መላክተኞችን ላከ ። መላክተኞቹንም ነቢዩ ኤልያስ በመንገድ ተገናኛቸውና "ጌታችሁን አትድንም ትሞታለህ በሉት" አላቸው ። እነርሱም ተመልሰው ይህንን ለአካዝያስ ነገሩት ። አካዝያስም ኤልያስ መሆኑን በነገሩት በምልክቱ አውቆ ሁለት የአምሳ አለቆችን ከመቶ ሰዎች ጋር በተራ ወደኤልያስ ላከ ። ኤልያስ ግን በሰማይ እሳት መቶውን ጭፍሮች ከሁለት አለቆች ጋር አቃጥሏቸዋል ።

የሶስት አመቱ ህፃን ቂርቆስና እናቱ ኢየሉጣ በእሳት ላይ በተጣደ የብረት ጋን በፈላ ውሃ ውስጥ ተጥለው ለሰማእትነት ተጋድለዋል ። ንፍር ውሃውም አላቃጠላቸውም ተብሎ ይተረካል (2 ነገስ·1 ፣ 1 — 18 ። ገድለ ቂርቆስ)

*230 ሥላሴ (1511) አ*

*ዘመርሻ (አለቃ)*

*በደማስቆ*

*ወድቀ ሳውል እመባርቅት*



*አንተሰ ኀሩይ ሶበ ደማስቆ አልጸቀ*

*ግብተ እምነ መብረቅ ገጽከ በረቀ ፤*

*ወሥሙረ በቀልት ስምከ እምነ ቆምከ ልህቀ ፤*

*እስመ ለስምከ ዘኢርኀቀ*

*ነፋስ አእምሮ ረቂቅ እምዠሉ ዘረቀ*

*ኀበ ላዕል ሰሐበ ጥዩቀ ።*

## ትርጉም

በደማስቆ

ከመብረቆች የተነሳ ሳውል ወደቀ ፤

ግን አንተ ህሩይ! ደማስቆ በደረስህ ጊዜ

ከመብረቆች ይልቅ ፊትህ ድንገት በረቀ (በሰጨ)

ከሰሌን ግንድ ያማረ ስምህም ከቁመትህ ይልቅ አደገ ፤

ያልራቀ ስምህን ከሁሉ

የረቀቀ የረቂቅ እውቀት/ነፋስ

በተረዳ ነገር ወደላይ ስቦታልና ።

## ምስጢር

ጳውሎስ የተባለው ሳውል ደማስቆ በደረሰ ጊዜ የብርሃን መብረቅ በርቆበት ነበር እንጂ እርሱ ራሱ አልበረቀም (ብርሃን አልሆነም) ። ብላቴን ጌታ ህሩይ የተባሉት ኢትዮጵያዊ ሊቅ ግን አውሮፓን ጎብኝተው በተመለሱ ጊዜ ፊታቸው አንፀባረቀ ። በስመጥርነታቸውም የገነኑ ሆኑ በማለት ባለቅኔው አመስጥረዋል ።

*231 ሥላሴ(1507) አ*

*ዘታመነ (አለቃ)*

*ልደት ቀዳማዊ*

*ዘበአረጋይት ወአረጋዊ*

*በደኃራዊ ልደት ተሐድሶ አካል ተዐውቀ ፤*

*እስመ በርሀ ተሐድሶ ሥጋ ለጻድቃን ሠረቀ ።*



www.ethiopianorthodox.org

*ምሳሌ ዝኒ አብርሃም አለብዎተ ጠየቀ ፤*
*አኮኑ ወለደ እምድኅረ ልህቀ*
*በርሥእናሁ ሕፃነ ፣ ወቃሎ አጽደቀ*
*ወእምቃሉ አሐዱ ኢወድቀ ።*

## ትርጉም

በባልቴት ሃናና
በሽማግሌ ኢያቄም የሆነ
መጀመሪያው ልደት በሁዋለኛው ልደት/የአካል መታደስ ታወቀ ፤
ብርሃን የአካል መታደስ ለፃድቃን ወጥቷልና ።
የዚህንም ምሳሌ ማስገንዘብን አብርሃም ተረዳ ፤ ካረጀ በሁዋላ
በእርጅናው
ህፃንን ወልዷልና ፣ ቃሉንም አፅድቋልና
ከቃሉም አንዱ አልወደቀምና ።

## ምስጢር

ፊተኛው የወልድ ከአብ መወለድ በሁዋለኛው ልደቱ ከቅድስት ማርያም በመወለዱ እንደታወቀ የኢያቄምና የሃና ጉልምስና ካረጁ በሁዋላ ቅድስት ማርያምን በመውለድ በአገኙት መታደስ ፀና ። ብርሃን የተባለ ክርስቶስም ለፃድቃን እንደተገለጠ መታደስ ለኢያቄምና ለሃና ተሰጠ ። ክርክር በምስክር እንደሚፈፀም የእነርሱም መታደስ በአብርሃም ተረዳ ። አብርሃም በመቶ ዘመን እድሜው ይስሃቅን እንደወለደ እነርሱም በስተርጅና ማርያምን ወልደው ታደሱ ። በዚህም "ልጅ ትወልዳላችሁ" ብሎ የነገራቸው የመልአኩ ብስራት (የምስራች ቃል) አልታበለም ይላሉ ባለቅኔው (ስንክ·ማንቦት ፣ 1)።

*232 ሥላሴ (1509) አ*
*ዘበቀለ ኅበና (አለ.ቃ)*

*እምአ.ክሀለ ኒቆዲሞስ*
*ተዋሥአቶ ለኢየሱስ ፣*
*መንግሥተ እለ ጠበብት ሥጣዌ ከመ ኢትትናፈቅ ሕቀ*



*እስመ ሎሙ ልደተ ድንግል ፈታሒ አልጸቀ ፤*
*ወአዕበየ ሳዶቅ ከላሀ ከልኤሆሙ ዕርቀ ፤*
*አኮኑ ተወልደ እምድኅረ ልህቀ ፤*
*እምከርሠ እሙሰ ይትርፍ በከመ ተዐውቀ*
*እምወለቱ ወላዲ ሠረቀ ።*

## ትርጉም

ከኢየሱስ መወያየትን
ኒቆዲሞስ ባልቻለ ነበር ፤
የእነዚሁ ጠበብት መንግስት/መልስ ጥቂት እንዳትለያይ
የድንግል ልደት/ፈራጅ ለእነርሱ ደርሷልና ፣
ሳዶቅም የሁለቱን ጩኸት/እርቅን ዘለግ አደረገ
ከአረጀ በሁዋላ ተወልዷልና ፣
ከእናቱ ሆድስ እንደታወቀው ይቅርና
ከሴት ልጁ ወላጅ ሰረቀ ።

## ምስጢር

መንግስት እርስ በራሷ ከተለያየች እንደማትፀና የኒቆዲሞስና የኢየሱስ "የሁለተኛ መወለድ" ንግግር ካልተግባባ የኒቆዲሞስ እምነት ስለማይፀና ፣ ክርክር በፈራጅ እንደሚወሰን እንዲሁም በቅድስት ማርያም መወለድ የኢየሱስን ነገር ኒቆዲሞስ አመነ ፥ እውር ሆኖ የተወለደ ጤሜዎስ ወደኢየሱስ ድምፁን ዘለግ አድርጎ እንደጮኸ ኢየሱስንና ኒቆዲሞስን የሚያግባባቸው ሁኔታም በሳዶቅ ተፈፀመ ። ምክንያቱም ሳዶቅ የተባለው የማርያም አባት ኢያቄም ካረጀ በሁዋላ እንደገና ወጣት ሆኗልና ። ሰው ካደገ በሁዋላ ወደእናቱ ሆድ የመግባትስ ጉዳይ "ሰው ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ ወደእግዚአብሄር መንግስት ይገባ ዘንድ አይችልም" ብሎ ኢየሱስ ክርስቶስ በተናገረው ቃል ታውቋል ። ወላጅ አዳም ግን ከግራ ጎኑ ከተፈጠረች ከሄዋን ሰረቀ (ልጁ ሄዋንን አስወለደ) ሎጥም ከሴት ልጆቹ ወለደ በማለት ባለቅኔው አመስጥረዋል (ዘፍጥ። 2 ፣ 20 —25 ፣ 19 ፣ 30 — 38። ዮሃ·3 ፣ 1 — 7) ።

www.ethiopianorthodox.org

*233 ሥላሴ (1510) አ*

*ዘበቀለ ጎበና (አለቃ)*

*ደለዎሙ ለመላእክት*
*ከመ ሰብአ ዓለም ሐሜተ ግብር ፤*
*አምጣነ በዐይን ዐይነ አመ ሩፋኤል ሰረቀ*
*ለድንግል ከመ ያስተፍሥሓ ገብርኤል ሰሐቀ ፤*
*ሚካኤልኒ ዘኮነ በስመ ይዋሂ ዕውቀ*
*ቤቶ ለፈርዖን እስመ ሠጠቀ*
*እምክረ እሉስ ይርኀቅ በከዊን ጥንቁቀ*
*ቀውስጦስ ተገድፈ ወወድቀ ።*

## ትርጉም

እንደአለም ሰዎች
የስራ አሜት ለመላእክት ተገባቸው ፤
ሩፋኤል አይን በአይን ቢሰርቅ
ድንግልን ሊያስደስታት ገብርኤል ስቋልና ፤
በርህራሄ ስም ታዋቂ የሆነ ሚካኤልም
የፈርዖንን ቤት ሰንጥቋልና ።
ከእኒህ ምክር ግን ጠንቃቃ በመሆን ይርቅ ዘንድ
ቀውስጦስ ተጣለና ወደቀ ።

## ምስጢር

የዚህ አለም ሰዎች በሚሰሩት ስራ ገሚሱ ሲታማ ገሚሱ ይመሰገናል ። ከአለም ስራ ነፃ የሆኑ መላእክትም በስራ ምክንያት ከሚነሳ አሜት አልራቁም ።

ሌባ ሲሰለጥን አይን በአይን እንደሚሰርቅ ሩፋኤልም የጠፋውን የጦቢትን አይን እንደደህነኛው አይን አደረገው ። ገብርኤልም ቅድስት ማርያምን በብስራቱ አስደሰታት ። "ሌባውን ሌባ ቢሰርቀው ምን ይደንቀው?" እንዲሉ ሌባ የሌላውን ሌባ ቤት ግድግዳ እንደሚቀድ ሚካኤል በርህራሄ የታወቀ ሲሆን ፈርኦንን አሰጠመው ። የሌባውን



ቀጣት ያየ ሰውም እንደሚጠነቀቅ ቀውስጦስ የተባለው መልአክ እንደነርሱ (ሩፋኤል ፣ ገብርኤልና ሚካኤል).ሳይሆን ቀረ በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

## ታሪክ

ገምኑዲ በተባለ ቦታ የተወለዱት ህፃናት በቅዳሴ ጊዜ ውር ውር (ወዲያና ወዲህ) እያሉ ስለአስቸገሩ ቀውስጦስ የተባለው መልአክ እንዲቀስፋቸው ከአምላክ ታዘዘ ። በትእዛዙ መሰረት ህፃናቱን ሲቀስፍ አንድ መልከ መልካም የሆነ አሳዛኝ ህፃንን አየና "ይህንስ የፈጠረው ይግደለው" ብሎ በርህራሄው አለፈው ። በዚህ ምክንያት አምላክ ቀቆጣበትና የፀጋውን ክንፍ ነሳው (እንዳይበር አደረገው) ። እንደምንም ቀንገባግቦ ደብረ ቀልሞን በሚባል ቦታ በተሰራች ቤተ ክርስቲያን ቤተልሄም አጠገብ ወደቀ ። በቀትር ጊዜ ዲያቆን ለተልእኮ ቢመጣ እይኑ ሲንቀለቀል አየውና "ምንድር ነህ? ሰማያዊ ነህን? ወይስ ምድራዊ? ቢለው" በግብሬ ምድራዊ ሆኛለሁ እንጂ በተፈጥሮየስ ሰማያዊ ነኝ ፤ ለአባ ሳሙኤል ንገርልኝ" አለው ። ዲያቆኑም ነገረለት ። አባ ሳሙኤልም መጥቶ እንደ ዲያቆኑ ቢጠይቀው ለዲያቆኑ የተረከለትን መልሶለታል ። ከዚያም መልአኩ ቀውስጦስ አባ ሳሙኤልን "ለእመቤታችን ለቅድስት ማርያም እመልክትልኝ ፤ ከልጇ ታማልደኛለች" አለውና እመልክቶለት (ፀልዮለት) የቀድሞው ክንፈ ፀጋው ተመልሶለት ወደሰማይ አርጓል ተብሎ ተፅፏል (ተአምረ ማርያም ) ።

*234 መወድስ/ስ*

*ዘሐዲስ ኪዳናት (ቄስገበዝ ፣ ዘጽላሎ)*

*እብነ ቢታንያ ይበሊ በውስተ ምግባሩ*
*ወከዊኖቱ ብሉየ ቅድመ ሆሣዕና ተዐውቀ ፤*
*ምስለ አእሩግ ኪሩቤል አምጣነ ረፈቀ ፤*
*ለተሴስዮ ጣዕመ ዝማሬ*
*ኀብስተ ጣዕማዌ ዘየጸግብ ጥቀ*
*አእሩገ ወደቂቀ*
*ወበህላዌሁ ንባብ እምነ ዙሉ ኢርኀቀ ።*



www.ethiopianorthodox.org

*ሐንካሰሂ አስቆሮታዊ ዘኢረሰየ ሰዋቀ*
*በትረ ሃይማኖት ሆሣዕና ጴጥሮስ ዘናፈቀ*
*እንዘ ፍኖተ ካሀድ የሐውር በመካነ አብን ወድቀ*
*ሆሣዕና ዳዊት ጸላኢሁ ሶመ በጽሐ ወአልጸቀ ።*

## ትርጉም

የቢታንያ ድንጋይ በምግባሩ ያረጃል
ያረጀ መሆኑም በሆሳእና ፊት ታወቀ ፤
ሽማግሌዎችንና ልጆችን ፈፅሞ የሚያጠግብ
ጣፋጭ እንጀራ/የምስጋና
ጣምን ለመብላት ከሽማግሎች/
ኪሩቤል ጋር ተቀምጧልና
በአኗኗሩ/ነገርም ከእነርሱ አልራቀምና ።
ጴጥሮስ የጠረጠረው የሃይማኖት በትር/ሆሳእናን
ድጋፍ ያላደረገ አንካሳ/የአስቆሮት ሰው ይሁዳም
የዳዊት ሆሳእና/ጠላቱ በደረሰበት ጊዜ
መንገድ/ ክህደትን ሲሄድ በድንጋይ ቦታ ወደቀ ።

## ምስጢር

አንድ ጎልማሳ ሰው ከሽማግሌዎች ጋር ተቀምጦ ሲያወጋ ፤ በምግብ ጊዜ ከእነርሱ ጋር ሲበላና በአኗኗሩም እነርሱን ሲመስል ይህ ሰው በእድሜው ባያረጅም በሚያደርገው ድርጊት ሸምግሏል ይባላል ። በእስራኤል አገር የሚገኘው የቢታንያ ድንጋይም ኢየሱስ በአህያይቱና በውርንጫዋ ላይ በየተራ እየተቀመጠ ወደኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ ከኢየሩሳሌም ሽማግሌዎችና ህፃናት ጋር ኢየሱስን እንደኪሩቤል አመሰገነ ።

ያለምርኩዝ መንቀሳቀስ የሚችለው አንካሳ ንቆ የተወውን ምርኩዝ ያልተደገፈ ደካማው አንካሳ ጠላቱ በድንገት በመንገድ በደረሰበት ጊዜ ፤ ሮጦ ለማምለጥ ቢሞክር በድንጋይ ላይ እንደሚወድቅ ኢየሱስን የካደ የአስቆሮት ሰው ይሁዳ በክህደቱ ፀና ። ኢየሱስን ክዶ የነበረ የሃዋርያት አለቃ ጴጥሮስንም በንስሃ አልመሰለውም ይላሉ ባለቅኔው ።



*235 ግእዝ ጉባኤ ቃና/ሰ*

*ስምዖን አብ ያኀዝነኒ በሕቁ ፤*
*እክለ እክለ እስመ ይብልዎ ደቂቁ ።*

## ትርጉም

ስምኦን አባት በጣም ያሳዝነኛል ፤
ልጆቹ እህል እህል ይሉታልና ።

## ምስጢር

ልጆቹ እህል እህል ሲሉት የሚያበላቸው ያጣ የልጆች አባት በጣም ያሳዝናል ። በአንፃሩም እህል ይመስል ልጆቹን የበላ በላኤ ሰብእ ስምኦን በጣም ያስገርመኛል ይላሉ ባለቅኔው ።

*236 ግእዝ ጉባኤ ቃና (152) ሰ*

*ተዝካሮ ግበሩ ባሕታውያን ደቂቁ ፤*
*ለምውት ጾም እስመ ደብረ ዘይት መንፈቁ ።*

## ትርጉም

ልጆቹ ባህታውያን ተዝካሩን አድርጉ (አውጡ) ፤
ለሙት /ፆም መንፈቁ ደብረ ዘይት ነውና ።

## ምስጢር

የሞተ ሰው መንፈቁ (ስድስተኛ ወሩ) ሲደርስ ልጆቹ ለተዝካሩ (ለመታሰቢያው) ድግስ እንደሚያደርጉለት የኢየሱስ ፆም እኩሌታው ደብረ ዘይት ተብሎ የሚጠራው የአራተኛው ሳምንት እሁድ መሆኑንና ባህታውያንም ኢየሱስን በማሰብ መፆማቸውን የቅኔው ምስጢር ያስገነዝባል ።

*237 መወድስ (352) ጎ*
*ዘዶሪ (አሰቃ)*

*መንጦላዕተ ፍትሕ ትሰፍሕ በገጸ ፈጣሪ*
*መርዓዌ ተውላጥ ክርስቶስ ግፉዕ እንዘ ዕራቁ*
*ወእመ አኮ ርቱዕ ለቤተ ምኩናንከ ንድቁ*



www.ethiopianorthodox.org

*ዳዊት ወአክዓብ*
*እለ ትእዛዘከ መዝገበ ሰረቁ*
*ውስተ ግበ ኀዘን ለእመ ወድቁ*
*ለዳዊት ተኀዝን ወለአክዓብ ታሰቆቁ ።*
*አንተሰ ወዳዊት እመ ትትዓረቁ*
*ዳዊት ወእርዮ ነገረ ቤርሳቤህ ኢያኀለቁ ፤*
*አኮኑ ልቃሐሙ ፍትሐ ኢፈደይኮሙ በሕቁ*
*ለዳዊት ከመ ጌጋዩ ወለእርዮ በከመ ጽድቁ ።*

## ትርጉም

የለውጥ ሙሽራ/ክርስቶስ ! የተበደለ ሰው
ራቁቱን ሲሆን መጋረጃ /ፍርድን በፈጣሪ ፊት ትዘረጋለህ
የፍርድህ/ቤት ስራም ቀጥተኛ ባይሆን

ትእዛዝ/ሳጥንን
የሰረቁ ዳዊትና አክአብ
በመከራ/ጉድጓድ ውስጥ በወደቁ ጊዜ
ለዳዊት ታዝናለህ ፤ ለአክአብም ታለቅሳለህ ።
አንተና ዳዊት ግን ብትታረቁ
ዳዊትና እርዮ የቤርሳቤህን ነገር አልጨረሱም ፤
ለዳዊት እንደ በደሉ ለእርዮም እንደ ፅድቁ
ብድራቸው/ፍርድን በፍፁም አልከፈልሃቸውምና ።

## ምስጢር

ችግረኛው ራቁቱን ሳለ ለሙሽራ ከሰው ፊት የሚለይ መጋረ
እንደሚጋረድለት ክርስቶስም ተገፊው ሳለ ፍርዱን ለገፊው አደረገ ፤
ሳጥን ሙሉ ወርቅ የሰረቀ ሌባ እጅ ተፍንጅ ተይዞ በታሰረ ጊዜ እንዳንድ
ዘበኛ የትም ውሎ እንዲመጣ ይለቀዋል ። ፈጣሪም ጣኦትን በማምለክ
ናቡቴንም በማስገደል ትእዛዙን ለጣሰ ለእስራኤል ንጉስ ለአክአብ
ይቅርታ አደረገለት ።

ሁለት ጥለኞች (ጠበኞች) ሲታረቁ ከእነርሱ ጋር በብድር ገንዘብ
የተጣሉ ሌሎች ተባባሪ ሰዎች ብድሩ ካልተከፈለና እብረዋቸው ካልታ
ረቁ ጠቡ አይደርቅም ። እምላክም በእርዮ ሚስት በቤርሳቤህ የበደለውን



ዳዊትን በንስሃ ይቅር ሲለው የእርዮ መበደል በዳዊት መቀጣት አልተመለ
ሰም ። የእርዮ ደም የሚመለሰው "ወደ ጎልማሳ ሚስት አትሂድ ፤
አትግደል" የተሰኙትን የአሪትን ትእዛዛት በድፍረት ተላልፎ የበደል
በደል የፈፀመ ዳዊት ቢቀጣና ቢገደል ነበር ይላሉ ባለቅኔው ።

ታሪኩ በአንደኛው መፅሃፍ በገፅ 42 ተተርኳል ።

*238 መወድስ (1534) አ*
*ዘዐወቀ (አለቃ ፤ ዘወቄጣ ማርያም)*

*ወላዴ ሕፃናት ወይን ሰብአ ተዋርዶ*
*ልብሰ ዘባኑ ከፈለ በሰማርያ ቤተ ምርፋቁ ፤*
*በጽንፈ እሳት ወነድ አምጣነ ያስቆቁ*
*ዐረቁ እንዘ ይብል*
*ልብሰ ዘኢያቀውም ሰኪኖን ደቂቁ ፤*
*ወይትሜነይ መቃብረ ፤*
*ንዋያቲሁ አቁጽል እስመ በበሕቅ ኀልቁ ።*
*እግዚእነሂ ወይነ ዕብራስዲ አመ ተአኀዘ በሕቁ*
*አቁጽለ በለስ አርዳኢሁ እኀዙ ይሰረቁ ፤*
*ወአልበስዎ ሜላተ እንዘ ይሣለቁ*
*አይሁድ ደመናት ምራቀ ዘወረቁ ።*

## ትርጉም

ህፃናትን ወላጅ ወይን/የመዋረድ ሰው
በመኖሪያ ቤቱ/በሰማርያ የጀርባውን ልብስ ከፈለ ፤
ልብስ የማያቆመው አንዶድ/ልጁ
በእሳትና በነዲድ
ዳር ተራቆትሁ እያለ ያለቅሳልና ፤
መቃብርንም ይመኛል ፤
ቅጠሎች /ገንዘቦቹ ጥቂት በጥቂት አልቀዋልና ።
የእብራስዲ ወይን/ጌታችንም በተያዘ ጊዜ
የበለስ ቅጠሎች ተማሮቹ ሊሰረቁ (ሊሾልኩ) ጀመሩ ፤
ምራቅን የተፉ ደመናዎች አይሁድም
እየተዘባበቱ ግምጃን አለበሱት ።



www.ethiopianorthodox.org

## ምስጢር

የብዙ ልጆች አባት የተራቆተ ልጁ በእሳት ዳር ሆኖ ተራቆ
(በረደኝ) እያለ ሲያለቅስበት ልብሱን ከፍሎ ከፋዩን ያለብሰዋል
ገንዘቡም ሲያልቅበት ሞትን ይመኛል ፣ የአባት ምሳሌ የሆነው የሰማ
ወይን ቅጠልም በክረምት ጊዜ እሳትን መሰለ ረገፈ ። የልጁ ምሳ
የሆነው እንዶድም እንደ ወይን ሆነ ። እንደገንዘቡም ማለቅ የእንዶ
ቅጠሎች ደረቁ።

አይሁድ ክርስቶስን በያዙት ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ እንደተበ
አብራስዲ የሚባል አገር (ቦታ) ወይን በዝናብ በተመታ ጊዜ ቅጠሉ
ረገፉ። አይሁድም ክርስቶስን ግምጃ እንዳለበሱትና እንደተዘባበቱበት
ምራቅንም እንደተፉበት የክረምትም ደመናዎች አጉረምርመው ዝናብ
አዘነቡ ። ወይንንም አቀሉት በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

*239 መወድስ (1533) ለ*
*ዛአድማሱ ጀንበሬ (መልአከ ብርሃን)*
*አበሳ ይከውን ትሩፋተ ሥጋ*
*ምሳሌ ዝኒ ነገር እምአበው ይጠይቁ*
*በብሂለ እፎ ዕቅፍት እለ ተዐቅፉ ወወድቁ*
*አኮኑ ለአጋግ ጽንዐ ጌጋዩ ቀቲለ ብእሲ ለሳሙኤል ጽድ*
*ወጌጋየ አዳም በሊዐ ቈጽል*
*ትሩፋተ ኮነ በኀበ ምእመናን ደቂቁ ።*
*በጾምሂ ወበርኀራኄ እምገጸ ትሩፋት ርኁቁ*
*መርቅያን ወሳኦል በቤተ ትሩፋት እለ ልህቁ ፤*
*ወእምነውረ ሰረቅት ይንጽሑ በማየ ትሩፋት ተጠምቁ*
*ዘኢደለዎሙ ለበሊዕ ኅባውዘ ቁርባን እለ ሰረቁ ።*

## ትርጉም

የስጋ ትሩፋት በደልን ይሆናል ።
እንዴት በማለት እንቅፋትም የተሰናከሉና የወደቁ
የዚህን ነገር ምሳሌ ከአባቶች ይረዱ ፤
የአጋግ የበደሉ ጥናት የሆነ



ሰውን መግደል ለሳሙኤል ፅድቅ ሆኗልና ፣
የአዳም በደል የሆነ ቅጠልን መብላትም
በአማኞች ልጆቹ ዘንድ ትሩፋትን ሆኗልና ።
በትሩፋት ቤት ያደጉ መርቅያንና ሳኦል
በጦምና በርህራሄ ከትሩፋት ፊት ርቀዋልና ፣
ለመብላት የማይገባቸውን የቁርባንን እንጀራ የሰረቁም
ከሌቦች ነውር ሊነፁ በትሩፋት/ውሃ ተጠምቀዋልና ።

## ምስጢር

አንዳንድ ሰው በበጎ ስራው ፈንታ ክፉ ሲፈፀምበት "ለበጎ ስራ መልሱ ክፉ ስራ ይሆናልን?" በማለት ይገረማል ። ለአንዱ ሃጢአት የሆነበት በደል ለሌላው እንደ ፅድቅ ስራ ጠቃሚ እንደሆነው የሚያስረዱ ታሪኮችን በመጥቀስ" በእንቅፋት የተሰናከሉ እንደሚወድቁ ይህንንም ነገር የተጠራጠሩ ተቃዋሚዎች ቢኖሩ በሚከተሉት መረጃዎች ይረ ታሉ" ይላሉ ባለቅኔው ።

ለአንዱ የተስማማው መድሃኒት ሌላውን እንደሚጎዳው ሁሉ ሰውን መግደል አጋግን አስኰነነው ፤ ሳሙኤልን ግን አጋግን መግደሉ አፀደቀው ። የበለስን ቅጠል መብላት አዳምን ከኤዶም ገነት አስወጥቶ በሲኦል አስጣለው ። ለመናኞች ግን በፆምና በፀሎት ተወስነው ቅጠልን የመብላት ትሩፋት (በሃይማኖት መፃህፍት ከታዘዘው የስነ ምግባር ስራ በተጨማሪ አትርፎ መስራት) የነፍስ ክብርን (ለመንግስተ ሰማይ የሚበቃ ዋጋን) አስጣቸው ።

የእስራኤል ንጉስ የነበረ ሳኦልን ለአጋግ መራራቱ ከስልጣኑ እንደሻረው መርቅያንንም በሰንበት ቀኖች መፆሙ እስጎዳው እንጂ አላስጠቀመውም ። በውሃ የታጠቡ ከእድፍ እንደሚነፁ ለካህናት እንጂ ለእነርሱ የማይገባቸውን የቁርባንን እንጀራ የፀሉ ዳዊትና አሽከሮቹም ነውረኞች ከመሆን ነፃ ሆኑ በማለት ባለቅኔው ያስረዳሉ ።

*240 መወድስ*
*ዘቀፀላ (ሊቁ)*
*በመጠን ዘምር እብነ ቢታንያ*
*ወኢትክላሀ እንከ እምአኀዊከ በሕቁ ፤*

www.ethiopianorthodox.org

*ከመ ኢይርሥዑ ቃለ ስሆሣዕና ደቂቁ*
*እስመ እሙንቱ መተርጉማን*
*ቃለ ሆሣዕና በአሚን ያጽድቁ ፤*
*በከመ ነበበ ጳውሎስ*
*ከመ እምንባብ ይሄይስ ትርጓሜ መፃህፍት እለ ተፀውቁ ።*
*ለአድግሂ ብዝኃ ንባቡ ከመ ይጠይቁ*
*አእሩገ እስራኤል በአርምሞ ወበብዙኀ ትዕግሥት ይረፍቁ ፤*
*ዘምስለ ባዕዳን አይሁድ ኢትደመሩ ረኀቁ*
*አምጣነ ይቤሎሙ ሆሣዕና ለእለ በአሚን ይትላሀቁ ።*

## ትርጉም

የቢታንያ ድንጋይ በልክ አመስግን እንጂ
ከእንግዲህ ወዲህ ከወንድሞችህ ይልቅ በጣም አትጩህ ፤
የሆሳእና ልጆቹ ቃልን እንዳይረሱ
የሆሳእና ቃልን በእምነት
ያፀድቁ ዘንድ እነርሱ ተርጓሚዎች ናቸውና ፤
የታወቁ የመፃህፍት ትርጓሜ
ከንባብ እንደሚሻል ጳውሎስ እንደተናገረ ።
የአህያንም የንግግሩን ብዛት ይረዱ ዘንድ
በዝምታና በትእግስት ብዛት የእስራኤል ሽማግሎች ይቀመጣሉ ፤
ሆሳእና በእምነት የላቁትን
ከሌሎች አይሁድ ጋር አንድ እንዳትሆኑ ራቁ ብሏቸዋልና ።

## ምስጢር

አንድ ልጅ በጣም እየጮኸ መዝሙረ ዳዊት ሲደግም "ቀስ ብለህ ድገም ፥ሌሎችን ደጋሚዎች የመዝሙረ ዳዊትን ቃል ታስገድፋቸዋለህ" እንደሚባል የቢታንያ ድንጋይና የኢየሩሳሌም ህፃናት በአህያ ላይ ተቀምጦ ወደቤተ መቅደስ የገባውን ሆሳእናን (ኢየሱስ ክርስቶስን) አመሰገኑ ።

አንዱ ሲያነብ ሁለተኛው እንደሚተረጉም ፤ ከንባብም ትርጓሜ እንደሚሻል በድንጋይና በህፃናት ምስጋና የክርስቶስ አምላክነት ተመሰከረ ። የንባቡን ትርጓሜ ለመስማት ምእመናን እንደሚቀመጡም ትልል ቆቹ የእስራኤል መምህራን እንደ አህያ ዝም አሉ ። የሃይማኖት መምህር ተማሪዎቹን በሃይማኖት ከነርሱ ከሚለዩ ሰዎች ጋር አትቀላቀሉ እንደሚ ላቸው ያመሰገኑት ክርስቶስም ሽማግሌዎችን ካላመሰገኑት አይሁድ በሃይማኖት ለያቸው ይላሉ ባለቅኔው ።

*241 ሚበዝኁ (1535) አ*
*ዘወርቅ አገኘሁ (አስቃ)*

*በዓለ መዛግብት አብድ*
*ለባዕድ ይዘግብ እንዘ ለርእሱ ይቄቂ ፤*
*እስመ ኢያእመረ ምንተ ምጽአተ ሞቱ ሰራቂ ፤*
*ወመልአከ ሞት መራድ ከመ ኪያሁ ይጸንሕ ወአስናኒሁ የሐቂ ።*

## ትርጉም

ባለመዛግብት ሰነፍ
ራሱን እየነፈገ ለሌላ ያከማቻል ፤
የሞቱ/ሌባ አመጣጥን ምንም አላወቀምና ፤
ወራሪ/የሞት መልአክም እርሱን እንደሚጠባበቀውና ጥርሶቹን እንደሚያፋጭ አላወቀምና ።

## ምስጢር

አንዳንድ ንፉግ ባለፀጋ እርሱ ራሱ አይበላ ቤተሰቡን አያስበላ የቆጠበው እየመሰለው ገንዘብ በመሰብሰብ ብቻ ይደከማል ። ሌባ ሲያደባ ቆይቶ በአጋጠመው ቀን ገንዘቡን ይሞልጨውና ባዶውን ያስቀረዋል ። ምክንያቱም "ያልጠረጠረ ተመነጠረ" እንዲሉ ባለገንዘቡ ሳይጠረጥርና ሳይጠነቀቅ እንደተዘለለ ስለሚገኝ ነው ። ሰነፍ ሃጢአተኛም በሃጢአት ላይ ሃጢአትን ያደልባል ። ራሱን ሳይመረምር ሞት እንዳለበትና መልአከ ሞት እንደሚቀስፈው ሳያስብ በድንቁርና ይኖራል በማለት ባለቅኔው ሰው በህይወት እያለ እለተ ሞቱን ማሰብ እንዳለበት ያስረዳሉ ።

*242 ሚበዝኁ (355) ጎ*
*ዘድንቄ (አለ.ቃ)*

*መስተገብረ ኀይል ቂርቆስ*
*ለምእመናኒሁ አትክልት ማየ ተአምኖ ይሰቂ*



www.ethiopianorthodox.org

*እኅዝ ሐቋ ልቡ ንጹሕ ቅናተ ወንጌል አጣቂ*
*ወኢ.ተሀበለ ይሰርቅ ንዋየ ዚአሁ እምነተ ባሀለ ንስጥሮስ ሰራቂ*

## ትርጉም

የሃይል ገበሬ/ቂርቆስ
ንፁህ የሆነ ወገብ (መታጠቂያ) ወንጌልን ታጥቆ
ለአማኞቹ /ተክሎች ውሃ /ማመንን ያጠጣል ፤
የንስጥሮስ ባህል/ሌባም የርሱ ገንዘብ/ እምነትን ሊሰርቅ አልደፈ
ረም ።

## ምስጢር

ገበሬ አትክልቶቹን ውሃ እንደሚያጠጣ ሰማእቱ ቅዱስ ቂርቆስ ለምእመናን እምነትን አፀና ። ሌባ ከተነቃበት ገንዘብ ሊሰርቅ እንደማ ችል የንስጥሮስ ባህልም የሰማእቱ ቂርቆስ ሃይማኖትን ሊለውጥ አል ለም ይላሉ ባለቅኔው ።

*243 ዋዜማ/ስ*

*ጽድቅ ወዓመፃ*
*እስመ ቤተ ዕውቅ ፀርኪ ወቤተ ክርስቶስ ዐራቂ*
*ነፍስየ ! እምግብረ ዓመፃ ፍጹመ ረኀቂ !*
*እንዘ ተኀድጊስ ጽድቀ እመ በዓመፃ ረፈቂ*
*ከመ ይደልዎ መቅሠፍት እምአበው ጠይቂ*
*ለዘቦአ ቤተ ባዕድ ሰራቂ ።*

## ትርጉም

አመፅና ፅድቅ
የታወቀ የጠላትሽ ቤትና ያስታራቂ የክርስቶስ ቤት ናቸውና
ነፍሴ ! ከአመፅ ስራ ፈፅመሽ ራቂ ፤
ፅድቅንም ትተሽ በአመፅ ብትቀመጪ
በሌላ ቤት ለገባ ሌባ
ጅራፍ እንደሚገባው ከአባቶች ተረጂ ።



## ምስጢር

በሌላ ሰው ቤት ገብቶ ሲሰርቅ የተያዘ ሌባ ግርፋት ተፈርዶበት ይገረፋል ። አመፅ የሰይጣን ቤት ሲሆን በዚያ ገብቶ መገኘት ነፍስን ያስኮንናታል ። ፅድቅ ግን የክርስቶስ ቤት ስለሆነ በዚያ ገብቶ መገኘት በጌታው ቤት እንደሚኖር ታማኝ አሽከር ያስቆጥራል በማለት ባለቅኔው ያስረዳሉ ።

*244 ዕዝል ጉባኤ ቃና (1543)አ*
*ዘአድማሱ ጀንበሬ (መልአከ ብርሃን)*

*ውስተ ልበ ምድር ተኀብአት ሄሮድያዳ አርዌ ስሕተት መርቄ*
*ለእመ በሰማይ ሶደ ከሣደ ዮሐንስ አንቄ ።*

## ትርጉም

የዮሃንስ አንገት/ጭልፊት በሰማይ ቢዞር
የስህተት /ቆላ አባብ/ ሄሮድያዳ በምድር ውስጥ ተሸሸገች ።

## ምስጢር

ጭልፊት በሰማይ ሲዞር አባብ በመሬት ውስጥ ይገባል ። እንዲሁም የዮሃንስ ራስ ወደሰማይ ሲወጣ ያስቆረጠችው ሄሮድያዳ በምድር ውስጥ ሰጠመች በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ። (ስንክ.መስከረም ፡ 2) ።

*245 ዕዝል ጉባኤ ቃና (1548)አ*

*ላሕይ ንጽሐ ሱራፌ ረቂቅ*
*በፍትው ገጽ ተከለ ሃይማኖት ጻድቅ ።*

## ትርጉም

የረቂቅ ሱራፌ ወዝ
በተወደደ ፊት/ተክለ ሃይማኖት አለ ።

## ምስጢር

ወዝ በፊት እንደሚኖር ሱራፌ የሚባለው መልአክ ንፅህናም በተክለ ሃይማኖት አለ በማለት ባለቅኔው የተክለ ሃይማኖትን ንፁህነትና

www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስነት በቅኔያቸው ገልጠዋል።

*246 ዘአምላኪየ (1552)አ*

*ሐልዮ ሥርዓት በዘሌዋውያን ምርፋቅ ፡*
*ታሕተ ነቢሮ እስጢፋ ልሂቅ*
*አምጣነ ነበሩ ላዕለ አእባነ አፍአ ደቂቅ ።*

## ትርጉም

በካህናት መቀመጫ ስርአት የለም ፡
ሽማግሌ/እስጢፋኖስ ከታች ተቀምጦ
የውጭ ድንጋዮች/ልጆች ከላይ ተቀምጠዋልና ።

## ምስጢር

እንደ ወጉ ሽማግሌ ከላይ ወጣቶች ከታች መቀመጥ ይገባቸዋል ወጣቶች ከላይ ሽማግሌዎቹ ከታች ተቀምጠው ሲታዩ "በነዚህ ካህና ቦታ ስርአት የለም" ይባላል ።

በአይሁድ ዘንድ ጭካኔ እንጂ ምህረት ባለመኖሩ አይሁድ ሰማእ እስጢፋኖስን በድንጋዮች ወግረው በገደሉት ጊዜ የእስጢፋኖስ አካ በስር ድንጋዮቹ በላይ መሆናቸውን የቅኔው ምስጢር ያስረዳል ።

## ታሪክ

አስራ ሁለቱ ሃዋርያት የክርስቶስን ወንጌል እየሰበኩ ያሳመኗቸ ክርስቲያኖች እየበዙ ሲሄዱ በማህበሩ አስተዳደር (ማጉረምረም) ተ ጠረ። ስለዚህም ሃዋርያት ክርስቲያኖችን ሰብስበው "እኛ ለስብከ ወንጌልና ለፀሎት ስለምንፋጠን ፡ ይህን ትተን በማህበሩ አስተዳደ ልንሰራ አንችልምና በዚህ ስራ ላይ የምንሾምላችሁን ሰባት ሰዎ ምረጡልን" አሏቸው ። እነርሱም ሃዋርያት በነገሯቸው ተደስተው ሰባ ሰዎች መረጡና አቀረቡላቸው ሃዋርያትም በሰባቱ ተመራጮች ራስ ላ እጆቻቸውን በመጫን ዲያቆናት አድርገው ሾሙላቸው ።

ከሰባቱ ሰዎች መካከል አንዱ የመጀመሪያው ሰማእት ቅዱ እስጢፋኖስ ነበር ። እርሱ በኢየሩሳሌም ስለክርስቶስ ሲሰብክ ብዙ ሰዎች



ተቃወሙት ። ይሁን እንጂ በሚከራከሩት ጊዜ በተሰጠው የክርክር ጥበብ ተከራካሪዎቹን ምላሽ ያሳጣቸዋል ። ከእለታት በአንዱ ቀን "እነሆ ሰማይ ተከፍቶ ኢየሱስ በአብ ቀኝ ተቀምጦ አየሁ" አለ ። አይሁድ ይህን በሰሙ ጊዜ "ዛሬስ! አለ አለና ለሰማይ ደጃፍ ለእግዚአብሄር ልጅ አወጣለትን?" ብለው ተናደዱ ። "የሙሴን ህግ ሲነቅፍና እግዚአብሄርን ሲሰድብ ሰምተነዋል" የሚሉ የሐሰት ምስክሮችን አስመሰከሩበት ። በአሪት ህግ መሰረት በድንጋይ ተወግሮ መሞት ተፈረደበት ። ተቃዋሚዎቹ አይሁድ ከከተማ ወደውጭ አውጥተው በድንጋይ ሲወግሩት "ኢየሱስ ሆይ አቤቱ ነፍሴን ተቀበል" በማለት ፀለየ ። በመጨረሻም በጉልበቱ ተንበርክኮ "አቤቱ ይህችን ሃጢአት አትቁጠርባቸው" ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸና ሞተ (የሃዋ. 6—7) ።

*247 ዋዜማ/ስ*

*አመ ኀልቀ በሀቢይ*
*ድኅረ በንኡስ ተብህለ መልክአ ኢየሱስ ረቂቅ*
*ፍጡነ አውረዶ ለኮከብ ዚቅ*
*መዘምር ስቅለት ምሁረ ቤተ ጴጥሮስ ሊቅ ፤*
*ወፀሐይ ወወርኀ ካህናት ደቂቅ*
*ወለጥዎ በልሳን ዕውቅ ።*

## ትርጉም

የረቀቀ የኢየሱስ
መልክ በንኡስ ከተባለ በሁዋላ በአቢይ በአለቀ ጊዜ
የጴጥሮስ ሊቅ ቤት ምሁር የሆነ
መዘምር ስቅለት ኮከብ ዚቅን ፈጥኖ አወረደው ፤
ልጆች የሆኑ ካህናት/ፀሃይና ጨረቃም
በታወቀ አንደበት ለወጡት (ወረቡት) ።

## ምስጢር

በማህሌት ጊዜ ማህሌት የተቆመለት መልአክ ፡ ፃድቅ ፡ ወይም ሰማእት መልክአ በንኡስ (ዝቅ ባለ የመዘምራን ድምፅ ፡ ዝግ ባለ የከበሮ



www.ethiopianorthodox.org

ሙቅና ባልፈጠነ የፀናፅል ፯፯ታ የሚዘም የአዚያዚያም አይነት) ተብሎ በአቢይ (ንኡስ ከተባለው የዝማሬ አይነት ከፍ ያለ ፡ የመዘምራን ድምፅ ክፍ ብሎ የከበሮው ምትና የፀናፅሉ ፯፯ታ ደምቆ የሚዜም የአዚያዚያም አይነት) ይባላል ። ዚቅ የሚባለው የመዝሙር ክፍል በመዘምር ቃል ይወርዳል (ይባላል) ። እንዲሁም የኢየሱስ ሰውነት ትልቁንና ትንሹን ጥፊና ግርፋት ተቀበለ ።የኢየሱስ ክርስቶስ ስቅላት ኮከብን አወደቀው ። ሁለት ሶስት መዘምራን በህብረት ዚቁን እንደሚለውጡት (እንደሚወርቡት) ፀሃይና ጨረቃም ህብራቸውን ለወጡ ። ፀሃይ ጨለመ ፤ ጨረቃ ደም ሆነ ይላሉ ባለቅኔው (ማቴ. 27) ።

*248 ዋዜማ (357)ጎ*

*ውሕዘ እምላዕሉ*
*ፈለገ ብርሃን ገጽኪ በላዕለ ምውታን አዕጹቅ*
*ማርያም ዐይነ እንቲአኪ ዘልብሱ መብረቅ ፤*
*ወኮከበ ብርሃን ሠረቀ እምደብረ ምጥማቅ ልሂቅ ፤*
*እስመ ቈጽለ ብርሃን እዴኪ ሐመልማለ ወርቅ*
*ከደነቶ ለሕያው ምጥማቅ ።*

## ትርጉም

አይንሽ መብረቅ
ልብሱ የሆነ ማርያም የብርሃን ወንዝ/ፊትሽ
በሙቶች/ጫፎች ላይ ከላይ ፈሰሰ ፤
የብርሃን ኮከብም ከትልቅ ደብረ ምጥማቅ ወጣ ፤
የወርቅ አመልማሎ እጅሽ ብርሃን ቅጠልን
ለህያው/ደብረ ምጥማቅ አልብሳዋለችና ።

## ምስጢር

ከተራራ ላይ የሚወርድ ወንዝ በእፀዋት ላይ እንደሚፈስ ብርሃን የሚታይበት የቅድስት ማርያም ፊት በሰዎች ዘንድ ተገለጠ ። ደግሞ ኮከብ ከሰማይ እንደሚወጣ በደብረ ምጥማቅ ብርሃን ከማርያም ፊት ፈለቀ ። ማርያም ልጇ ክርስቶስን ከከብቶች በረት በወለደች ጊዜ ቅጠል እንዳለበሰ



ው ፡ የወርቅ አመልማሎን የፈተለች እጇ ደብረ ምጥማቅን በብርሃን ለቀለቀችው በማለት ባለቅኔው በደብረ ምጥማቅ ተፈፅሟል የሚባለ ን ተአምር አመስጥረዋል።

## ታሪክ

ደብረ ምጥማቅ በግብፅ ምድር በቅድስት ማርያም ስም የተገደመች ናት ። በዚችም ገዳም በያመቱ ማርያም በቤተ ክርስቲያኒቱ ጉልላት ሆና እንደፀሃይ እያበራች አምስት ቀን ለክርስቲያኖችም ለእስላሞችም ይ ነበር ። እያንዳንዱም ሰው እንደ ፍላጎቱ የሞተውን ዘመዱን ሌን አምጪልኝ" ሲላት አምጥታ አሳይታዋለች በማለት ተተርኳል ምረ ማርያም) ።

*249 ዋዜማ (1554)አ*
*ዘምን ደስይል (ለባ)*

*ለማርቆስ ተርጕምዎ*
*ለነበ ብዙኀ ፍኖት ዘአሚስያስ ደቂቅ*
*እስከ ወፅአ ስሙዓተ ደሙ እምሀረብ ወሠርቅ ፤*
*ወከመ ይኩኑ ስምዐ ለሞተ ማርቆስ ሊቅ*
*ነጐድጓደ ሰማይ ኤልያስ ወሙሴ መብረቅ*
*ተጸውዑ እምራማ ምርፋቅ ።*

## ትርጉም

የአሚስያስ ልጆች
ማርቆስን በብዙ መንገድ ስልት ተረጐሙት ፤
የደሙ ስሚ በምእራብና በምስራቅ እስኪወጣ ድረስ ።
ለማርቆስ ሞት/ሊቅም ምስክርን ይሆኑ ዘንድ
የሰማይ ነጎድጓድ /ኤልያስና ሙሴ/ መብረቅ
ከሰማይ/መቀመጫ ተጠሩ ።

## ምስጢር

የአይሁድ ንጉስ የነበረ የአሚስያስ በድን በፈረስ ተጭኖ ወደኢየሩ ም እንደተጓዘ ፡ ወንጌላዊ ማርቆስን ያሰቃዩትም መንገድ ለመንገድ



www.ethiopianorthodox.org

በበሬዎች አስጎተቱት ። የተማሩ ሊቃውንት የሚተረጉሟቸው የመዛዘ
ፍት ትርጓሜን ብዙ ሰዎች እንደሚያዳምጡ የማርቆስ ደምም በየስፍራው
ፈሰሰ ። ከዚህም ከሳሽ ምስክሮችን እንደሚጠራ በማርቆስ ሞት ጊዜም
መብረቅና ነጎድጓድ ተሰሙ በማለት ባለቅኔው አመስጥረዋል ። (2 ነገስ.
14 ፥ 1—22 ። ስንክ. ሚያዝያ 30) ።

*250 ሥላሴ (1561)አ*

*ዘአድማሱ ጀንበሬ (መልአከብርሃን)*

*ጊዮርጊስ መስተበቅል !*
*ዝርዋን ቃላት/አዕፅምቲከ*
*ዘውስተ ዐየር ተከዕው እስከነ ዐረብ ወሠርቅ*
*ይባኡ ውስተ እዝነ ዙሉ ዘዕፀው ዐጽቅ*
*ከመ ልማድከ አዝዝ ሮምያ ዕርቅተ መልበስ ጽድቅ ፥*
*ወጽምእተ ልሳን እማየ ዕርቅ*
*ጽዋዐ ባቢሎን ትስተይ ዘእንበለ ወርቅ*
*ከማሆሙ ለሰብዓ ደቂቅ ።*

## ትርጉም

ተበቃይ ጊዮርጊስ !
እስከ ምእራብና እስከ ምስራቅ
በአየር ውስጥ የፈሰሱ ብትኖች ቃላት /አጥንቶችህ
ከሁሉ ጆሮ/ የእንጨቶች ቅርንጫፍ ውስጥ ይገቡ ዘንድ
ከእውነት/ልብስ የተራቆተች ፥ ምላሷም ከእርቅ/ውሃ
የተጠማች ሮምያ እንደሰባ ልጆች
የባቢሎንን መጠጥ ያለወርቅ
እንድትጠጣ እንደልማድህ እዝዝ ።

## ምስጢር

በአደባባይ የተነገሩ ቃላት በሁሉ ጆሮ ይሰማሉ ፥ የሰማእቱ የቅዱስ
ጊዮርጊስ አጥንቶችም በነፋስ ሲበተኑ በጫካ ውስጥ ባሉ እንጨቶች
ቅርንጫፍ ሁሉ ተረጩ ። ባለቅኔው ጊዮርጊስ ! የተራቆተችና የተጠማች
ለማኝን ልብስን ማልበስና ውሃን ማጠጣት እንደሚገባም ከእውነት



ቆችና እርቅን የማትፈልግ ሮምያን ቀድሞ በእሳት እንዳጋየዘቸው
ደሰባው ነገስት የባቢሎን ቃጠሎ አቃጥላት ይላል (ገድለ ጊዮርጊስ) ።

*251 ሥላሴ (1557)አ*

*እምቅሩብ ተአኅዎ*
*ዘአምኖን በኩር ወዘትዕማር*
*እምከመ ዘትዕማር ወድቀ ሕሊና ኃይለ አምኖን መብረቅ*
*ይኄይስ ተዘምዶ ዘዮሴፍ ርኁቅ ፥*
*አኮኑ ጽሩየ ድንጋሌ ማኅተመ ኢሳይያስ ወርቅ*
*ኢሰበረ ዮሴፍ በእንተ ጽድቅ*
*እስከነ ኢሰምዐ ቃለ በእዝነ ምሥራቅ*
*ጽባሐዊ ገብርኤል ማዕነቅ ።*

## ትርጉም

በኵር ልጅ አምኖንና
ትእማር ቅርብ ወንድምነትና እህትነት
ምኖን /መብረቅ ሃይል/ አሳብ በትእማር ከወደቀ በሁዋላ
ሴፍ ሩቅ ዝምድና ይሻላል ፥
ራ የወርቅ /ኢሳይያስ ቁልፍ/ ድንግልናን
ፍ ስለእውነት አልሰበረምና ፥
ስራቃዊ ገብርኤል /ሽመላ አሞራ በምስራቅ/ ጆሮ
ልን እስከአሰማ ድረስ ።

## ምስጢር

የቅርብ ዝምድና ያላቸው ሰዎች በየምክንያቱ ሲጣሉና ሳይስማሙ
"ከነርሱ ዝምድና የባእድ ወዳጅነት ይሻላል" ይባላል ። አምኖንና
ርም የእስራኤል ንጉስ የዳዊት ልጆች ሲሆኑ አምኖን በትእማር
ተነድፎ የታናሽ እህቱ የትእማርን ክብረ ንፅህና ገሰሰ ። ዮሴፍ ግን
እንኳን ከቅድስት ማርያም ጋር ያለው ዝምድና ራቅ ያለ ቢሆንም
ቁልፍን እንዳለመስበር የቅድስት ማርያምን ድንግልና አልደፈ



www.ethiopianorthodox.org

ሽመላ የሚባለው አሞራ በጥቅምት ወራት ከምስራቅ በኩል ድምፁን እንደሚያሰማ ቅዱስ ገብርኤል "ድንግል ትፀንሳለች ፤ ወንድ ልጅንም ትወልዳለች" በማለት እስከ አበሰራት ድረስና ከዚያም በሁዋላ ዮሴፍ ቅድስት ማርያምን በግብር አላወቃትም ይላሉ ባለቅኔው ።

*252 ዘይእዜ (1566)አ*
*ዘናሁዳ (አሊቃ)*

*ወርቅኪ ዐርገ በክንፈ ሕንፃ*
*መንገለ ዳግሚት ሰማይ እንዘ ንሬእዮ ደቂቅ ፤*
*ወእመ እምዝንቱ ልብኪ ርኁቅ*
*ወለተ ጊዮርጊስ አጥረይኪ በምሥያጠ ሰሎሞን ቃለ ጽድቅ*
*ሠናየ ስመ ዘኢየኃልቅ ፤*
*እስመ ኢየኃልቅ ስም ለእመ የኅልቅ ወርቅ*
*ሠናየ ስመ ዘኢየኅልቅ ።*

## ትርጉም

ልጆች እያየነው
ወርቅሽ በክንፍ ህንፃ ወደሁለተኛዪቱ ሰማይ አረገ ፤
ልብሽም ከዚህ የራቀ ቢሆን
ወለተ ጊዮርጊስ! በሰሎሞን ገበያ የእውነት ቃል
የማያልቅ መልካም ስምን ገዛሽ
ወርቅ ቢያልቅ ስም አያልቅምና
የማያልቅ መልካም ስምን ገዛሽ ።

## ምስጢር

በራሪ አሞራ በክንፍ ወደ አየር ሲበር እንደሚታይ በክርስትና ስማቸው ወለተ ጊዮርጊስ የተባሉ የእቴጌ ምንትዋብ ገንዘብ በጎንደር ከተማ በምትገኘው በቁስቋም ቤተ መቅደስ ስራ ላይ ስለዋለ ዳግሚት ሰማይ የተባለች የቅድስት ማርያም ገንዘብ ሆነ ። አንዱ አሞራ ከሌላው አሞራ በበረራ ይመጥቃል ፤ ይልቃልም ። "ከአገርም ልብ ይሰፋል" እንደሚባል የእቴጌ ምንትዋብም ልብ አርቆ አሳቢ ሆነ ። ሴት ነጋዴ



ገበያ ጥሩ ጥሩ እቃ መርጣ እንደምትገዛ እቴጌዪቱ እንደጠቢቡ ሰሎሞን ማያልቅ ወርቅ ለብዙ ዘመናት ሲጠራ የሚኖር ስም አገኙ በማለት ለቅኔው ለእቴጌዪቱ ቅኔያቸውን አበርክተዋል ።

*253 ዘይእዜ (71)ይ*
*ዘበቃ (ቄስገበዝ ፡ ዘጎንጅ)*

*ሜመ አብ ላዕለ ታቦር*
*በአንብሮተ እድ ጴጥሮስ ወልደ ባሕርዩ ረቂቅ ፤*
*ለውእቱ ወልድ በቂሣርያ*
*እስመ ተሐዘቦ ልበ ጴጥሮስ ሊቅ*
*ከመ ሥጋዊ ውእቱ እንዘ እመንበሩ ኢየዐርቅ ።*
*ወእምይሁዳ ሠወረ ምሥጢራተ ጽድቅ ፤*
*ልበ ይሁዳ ታቦት አምጣነ ልቡጥ በወርቅ*
*ወእምይሁዳ ሠወረ ምሥጢራተ ጽድቅ ።*

## ትርጉም

ጴጥሮስ እጅን በመጫን
የረቀቀ የባህርዩ ልጅን አብ በታቦር ላይ ሾመ ፤
እርሱን ወልድን
ከመንበሩ ሳይለይ ስጋ የለበሰ ሰው እንደሆነ
በቂሳርያ የሊቅ ጴጥሮስ ልብ ታዝቦታልና (ተጠራጥሮታልና) ፤
የእውነት ምስጢሮችንም ከይሁዳ ሸሸገ ፡
የይሁዳ ልብ ታቦት በወርቅ የተለበጠ ነው ፤
የእውነት ምስጢሮችንም ከይሁዳ ሸሸገ ።

## ምስጢር

እንደ አክሱም ፅዮን አስተዳዳሪ ስም እጅን በራስ ላይ በመጫን ሰጥ መንፈሳዊ ሹመት አለ ። በዚህ አንፃር እግዚአብሄር አብ የባህርይ ን በደብረ ታቦር ገለጠው ፤ ጴጥሮስንም በቃሉ ጣለው ። አንድ የቤት ልጋይ የማይገባ ስራ ባሰራ ጊዜ "እንዴት ያደርገኝ ይሆን?" በማለት



www.ethiopianorthodox.org

ጌታውን እንደሚጠራጠረው ጴጥሮስም መሞቱን ያወሳለትን እግዚአብሄር ወልድን "ይህ ሞት ለአንተ አይደለም" አለው ። ለታማኝ ሰው የተነገረ ምስጢርም እንደማይገለጥ በፀሎተ ሀሙስ በተደረገው የእራት ግብዣ ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ "አስቀድሞ ወደወጪቱ ወጥ እጁን ያወረደው ያስይዘኛል" አሊእንጂ "ይሁዳ ያስይዘኛል" አላለም ። ፅላት በወርቅ እንደሚለበጥ ይሁዳም ሰላሳ ብር ተቀብሎ ወልድን አስያዘው በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

*254 ዘይእዜ (359)ኀ*

*እዝንከ ይስተይ ማየ ዘለፉ*
*ኅበ ነቅዐ ማይ ግፍዕ እምድኅረ ኀለፍከ ሊቅ*
*ወፅአት በትር ዘእዴሆሙ*
*ለእለ ገፍዑከ ነፋሳት ደቂቅ*
*ተኰርዖተ ርእስከ ትዕማር በበትረ ይሁዳ ከመ ትጽደቅ ፤*
*ወምስፍና ልብስከ ወፅአት እምአባለ ዕርቅ*
*ከመ ትትናገር ዕርቃነ እንበለ ምክንያት ፀርቅ*
*ወምስፍና ልብስከ ወፅአት እምአባለ ዕርቅ ።*

## ትርጉም

ጆሮህ የዘለፋ ውሃን ይጠጣ ዘንድ
ሊቅ! ወደ ውሃ ምንጭ /ግፍ ከሄድህ በሁዋላ
የገፉህ የነፋሶች/ልጆች
የእጃቸው በትር ወጣች ፤
የራስህ መገመስ/ትእማር በይሁዳ በትር ትረታ ዘንድ ።
ምስፍና/ልብስህም ከእራቁትነት አካል ወጣች
ያለ ምክንያት/ጨርቅ ራቁትነትን ትናገር ዘንድ
ምስፍና/ልብስህም ከራቁትነት አካል ወጣች ።

## ምስጢር

ውሃ የሚጠጣ ፍጡር ወደ ምንጭ ቦታ ይሄዳል ፤ እንዲሁም የክርስቶስ ጆሮ የአይሁድን ዘለፋ ሰማ ። አውሎ ነፋስ ያገኘውን ሁሉ



ያነሳ እንደሚጥለው አይሁድም ክርስቶስን በአመፅ ገፉት ፤ ራሱንም በትር መቱት ። ትእማር ይሁዳን በበትሩ ምልክትነት እንደረታችው ክርስቶስ ራስም በአይሁድ በትር ተገመሰች ። ምስፍና (መስፍንነት) ያእቆብ ልጅ ከይሁዳ እንደወጣች የክርስቶስ ልብስም ራቁትነትን ልሸፈነችም ይላሉ ባለቅኔው ።

*255 መወድስ (1591)እ*
*ዘፍሥሓ ክርስቶስ (አባ)*

*እፎኑመ ኀልቀ ልብሰ ሃይማኖት*
*ድልዋንሂ ኵልነ ለሰሐቅ ወለሥላቅ ፤*
*አምጣነ ኢመልዐ ልብ ዘኢሳይያስ ማዕምቅ*
*ድኅረ አገሪሁ እንተ ትተሉ*
*ዘበእዝነ ሥጋ ኢተኀልፍ ጽድቅ*
*ወለምንት ያድለቀልቅ*
*መሠረተ አሚን ልብነ ከመ ሕንጻ ኵሉ ደቂቅ?*
*አኮኑ ጸብዐ ንጉሢ ናቡከደነፆር ወርቅ*
*በዕርቀ ዳንኤል እብነ ደብር ኀሉቅ ወድቁቅ ፤*
*ዴገናሂ ለፍቅር ወተደለወ ለዕርቅ*
*ሐመልማለ ሲና በደብረ ሲና ምስለ ነደ ሲና ዘይመውቅ ።*

## ትርጉም

ልብሰ ሃይማኖት እንዴት አለቀ?
ሁላችንም ለሳቅና ለዝብብት ዝግጁዎች ነን ፤
በስጋ ጆሮ የማታልፍ ፅድቅ(እውነት)
ከእግሩ በሁዋላ እየተከተለች
የኢሳይያስ ጥልቅ ልብ አልመላምና ፤
የእምነት መሰረት/ልባችንስ
እንደ ሁሉ ልጆች ህንፃ ለምን ይነዋወጣል?
የንጉስ ናቡከደነፆር ጠብ/ወርቅ
በዳንኤል እርቅ/የተራራ ድንጋይ ያለቀና የደቀቀ ነውና ።
የሲና ልምላሜ ከሚሞቅ የሲና ነዲድ ጋር
በደብረ ሲና ፍቅርን ተከተላት ፤ ለእርቅም ተዘጋጀ ።



www.ethiopianorthodox.org

## ምስጢር

ልብስ ደረጃ በደረጃ እንደሚያልቅ ሃይማኖት ተለያየ ። የተቀዳ
ልብስ በለበሰ ሰው ህፃናት እንደሚስቁ የሃይማኖት መለያየትም መነ
ፊያ ሆነ ። ባዶ ጉድጓድ ጥልቀቱ እንደሚታይ የተነቃቃፊዎች ል
እውቀትን አልተመላም ። ኢሳይያስ "ጉድጓድ ሁሉ ይሙላ" እን
ልብም እውቀትን መምላት ነበረበት ። ነገር በጀሮ ብቻ ተሰ
አይቀርም ፤ በሰሚው ሰው ልብም ይታሰባል ፤ ይገመገማል ።

ጥንካሬ ያለው መሰረት እንደማይናወጥ በእምነት የፀና ል
መባባት አይገባውም ። ልጆችም የካቡት የድንጋይ ካብ እንደሚና
የአማኝ ልብም በፍርሃት መካድ የለበትም ። ናቡከደነፆር በህልሙ ያየ
የወርቅ ምስል ከተራራ ላይ በወረደ ድንጋይ እንደ ደቀቀ የናቡከደነ
ጣብም ነቢዩ ዳንኤል በመሰረተው እርቅ ሰላም ሆነ ። ከዚህም
የተጣሉ ሁለት ሰዎች በእርቅ እንደሚስማሙ የማይስማሙት እርጥ
ቅጠልና የእሳት ነዲድ በደብረ ሲና ተዋህደው ሳይጠፋፉ ቀሩ ይላ
ባለቅኔው (ዘፀአ·3—4 ። ዳን 2· ፣ 1—49) ።

*356 ሕንጼሃ (1597)አ*

*አንስት እለ ተሐፅና ውስተ ቤተ እሳት ምውቅ*
*ይጸንዓ እምነ ዕደው ሠለስቱ ደቂቅ ።*

## ትርጉም

በሞቀ የእሳት ቤት ውስጥ ያደጉ ሴቶች
ከሰለስቱ ደቂቅ ወንዶች ይጠነከራሉ ።

## ምስጢር

ሃይልን በሚያጠነክር ምግብ ያደጉ ሴቶች እንደነገሩ ካደጉ ወንዶች
ይጠነክራሉ ። በእሳት ካልተቃጠሉት ከሰለስቱ ደቂቅ (አናንያ ፣ አዛርያ
ሚሳኤል) በእሳት ተቃጥለው የሞቱት ሰማእት ሴቶች ይደነቃሉ በማለ
ቅኔው ተመሰጥሯል (ገድለ ፡ ሰማእታት) ።



*257 ዕዝል ክብር ይእቲ (371)ጎ*
*ዘኃይለ ሥላሴ (አለቃ)*

*ለዘዕርቃነ ማይ ከደነ ጊዜ ከብካብ በልብሰ ይሁዳ ረቂቅ*
*አጽርቅተ ኤፍራጥስ ከልዕም ዘይትከልው ደቂቅ ፤*
*ወዘጥምቀተ ማይ ኢይኩን ትእምርተ ያዕቆብ ሊቅ*
*ለከሣደ ድምፁ ክርስቶስ ኢረከበ ፈትለ ማየ ዝናም ዘአስቅ ።*

## ትርጉም

የውሃ ራቁትን በሰርግ ጊዜ በቀጭን የይሁዳ ልብስ የሸፈነ ወልድን
የሚከለክሉ አሽከሮች የኤፍራጥስ ጨርቆችን ከለከሉት ፡
የሊቅ ያእቆብ ምልክትም በውሃ ጥምቀት እንዳይሆን
ክርስቶስ ለአንገት/ድምፁ የዝናብ ውሃ/ የአሸብ ፈትልን አላገኘም።

## ምስጢር

አንዳንድ ደግ ሰው ለታረዘው ሲያለብስ ፤ ለተራበው ሲያበላ ይኖርና
እርሱ ባጣ ጊዜ የእጁን አያገኝም ። ክርስቶስም በቃና ሰርግ ቤት የጋኖችን
ውሃ ወይን አድርጎ ያጠጣቸው አይሁድ ውሃ ነሱት ። "ልብሱን በወይን
ያጥባል በፍሬውም ደም በፍታውን ያጥባል " ተብሎ ለይሁዳ ተነግሮለ
ታል ። ስለዚህም ባለቅኔው "በልብሰ ይሁዳ " ብለዋል ። ደግሞ ህፃን
ሲጠመቅ ሶስት አይነት ቀለም ያለው ክር (ማተብ) በስላሴ አምሳል
ይፈተልና በአንገቱ ይደረጋል ። ይህም የሚደረግበት ምክንያት ያእቆብ
ዘእልበረዳኢ የተባለው የአንፆኪያ ቤተ ክርስቲያን መምህር በጨለማ
ብዙ ሰዎችን ሲያጠምቅ ለተጠመቁትና ላልተጠመቁት መለያ እንዲሆ
ነው በተጠመቁት ሰዎች አንገቶች ላይ ክር ማድረግ ስለጀመረ ነው
ይባላል ። አንዳንድ ክርስቲያኖች ግን በአንገታቸው ማተብ ሳያደርጉ
እንደሚገኙ ክርስቶስም ዝናብን የሚሰጥ ሲሆን "ተጠማሁ" ባለ ጊዜ
የዝናብ ጠብታ ውሃን አላገኘም ይላሉ ባለቅኔው ።

*258 ሚበዝኑ (1606)አ*

*ቤተ ክርስቲያን ዕቀቢ*
*ሕሙመ ሥጋ ዓለመ ዘሕማመ ሥጋ ያጠውቆ ፤*



www.ethiopianorthodox.org

*አኮኑ ያፈርሀ ከመ ውስተ እሳት ኢያውድቆ ፤*
*ወእመ ለክፎ እሳት አልቦ ሐዪው ወፍጻሜሁ ተጽዕቆ ።*

## ትርጉም

ቤተ ክርስቲያን!ህመም/ በደል
ያስጨነቀው የስጋ በሽተኛ/አለምን ጠብቂው ፤
በእሳት ውስጥ እንዳይጥለው ያስፈራልና ፤
እሳትም ከነካው መዳን የለውምና ፤ ፍፃሜውም መጨነቅ ነውና ።

## ምስጢር

የሚጥል በሽታ የያዘውን ልጇን በእሳት ላይ እንዳይወድቅና እንዳይቃጠል እናት መጠበቅ አለባት ። በሃጢአት የጠለቀ አለም (ሰው) ከገቡ በሁዋላ መውጣት በሌለበት በገሃነመ እሳት ውስጥ እንዳይገባ እንዳይቀጣ ቤተ ክርስቲያን ማስተማር አለባት በማለት ባለቅኔው ስለፅድቅና ስለኩነኔ ያላቸውን አስተያየት በቅኔያቸው ገልጠዋል ።

*259 ሣህልከ (1610)አ*
*ዘአካለ ወልድ (መምሀር)*

*ኢትንግሩ ጌት ወደማስቆ*
*ለኢትዮጵያ ኅዘንት ድምፀ ኀለይተ ብርት መሰንቆ ፤*
*አኮኑ ነገሥሥ ለምኒልክ*
*እስከነ ፍጻሜ መንግሥቶ ወጽድቆ ።*

## ትርጉም

ጌትና ደማስቆ!
ለኢትዮጵያ/ሃዘንተኛ
የናስ/መሰንቆ ዘፋኞች ድምፅን አትንገሩ ፤
የምኒልክ መንግስቱንና
ፅድቁን እስከመጨረሻ እንሻለንና ።

## ምስጢር

ለሃዘንተኛ ሴት በሀዘኗ ጊዜ የሙዚቃ ድምፅ አያስፈልጋትም ።



በእስራኤል ንጉስ በዳዊት ድል የተመቱ የጎልያድ አገር የጌትና የሶርያ ዋና ከተማ የደማስቆ አጋጣሚ ለኢትዮጵያ አይሁንባት ። ምክንያቱም የአፄ ምኒልክ መንግስት ከእውነተኛ ፍትሁ ጋር እስከ መጨረሻው ፀንቶ እንዲኖር ስለሚፈለግ ነው በማለት ባለቅኔው ለአፄ ምኒልክ መንግስት የነበራቸውን አክብሮት አስረድተዋል ።

## ታሪክ

ደማስቆ ከሁለት ሺህ አመት ከክርስቶስ ልደት በፊት የተሰራ የሶርያ ዋና ከተማ ነው ። ከምስራቅ ወደታላቁ ባህር ከሰሜንም ወደ ግብፅ የሚያደርሱ መንገዶች የሚገናኙበት የአያሌ ነጋዴዎች መናኸሪያ ነበር ። ዳዊት ደማስቆን ወሮ ሀያ ሁለት ሺህ ሰዎች ገድሏል ። የሶርያንም ሰዎች አስገብሯል ። (ዘፍጥ· 14፣ 15፣ ። 2 ሳሙ· 8 ፤ 5—6 ። የሃዋ· 9 ፤ 11) ።

ጌት ከአምስቱ የፍልስጥኤም ከተሞች አንዱ ነበረ ። ዳዊት በወንጭፍ ድንጋይ የገደለው ፍልስጥኤማዊ ጀግና ጎልያድ የተወለደው በዚሁ ከተማ ነው ።

(1 ሳሙ· 17 ፤ 4—53 ፤ 2 ሳሙ2 15 ፤ 18) ።

*260 ግእዝ ጉባኤ ቃና/ስ*
*ከበሮ ጻድቅ ትእዛዘ ወንጌል ዐቀበ ፤*
*ክልኤተ ገጸተ እስመ ለተጸፍዖ ወሀበ ።*

## ተርጉም

እውነተኛ/ከበሮ የወንጌልን ትእዛዝ ጠበቀ ፤
ሁለት ፊቶቹን ለጥፊ ሰጥቷልና ።

## ምስጢር

መናኝ ፃድቅ “ቀኝ ጉንጭህን ቢመታህ ግራህን አዙርለት” የሚለውን የወንጌል ትእዛዝ ስለሚከተል ፣ አንዱን ፊቱን በጥፊ ለመታው ግፈኛ ሁለተኛውን ፊቱን አዙሮ ይሰጣል ። ከበሮም ትልቁን ደባዩን (ሰፊውን ክፍል) በቀኝ እጅ ሲመታ ትንሹን ደባዩን (አማሪቱን ፣ ጠባቡን ክፍል) በግራ እጅ ይመታል ማለት በቅኔው ተመስጥሯል



www.ethiopianorthodox.org

261 ዕዝል ጉባኤ ቃና /ስ

ደዌሁ ለጾም ያፈርሀ እለ ይበዝኍ ሕዝበ
እስመ ኢይጥዕም እክለ ወኢይሰቲ ሐሊበ ።

## ትርጉም

የፆም ብሽታ የበዙ ሰዎችን ያስፈራል ፤
እህልን አይቀምስምና ፤ ወተትንም አይጠጣምና ።

## ምስጢር

እህል የማያስቀምስና ወተት የማያስጠጣ በሽታ ብዙዎችን ሰዎ ያሰፈራል። የፆም ስርአት ቁርስ አያስበላም ፤ ወተትንም ያስከለክላ በማለት ባለቅኔው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቀኖ የተደነገገውን ያፁዋፁዋም ስርአት ያስረዳሉ ።

262 ሥላሴ(380) ጎ
ዘድንቄ(አለቃ)

ሰማዕት ምስለ ሰማዕት
በበይናቲሆሙ ተናበቡ ፤
እስመ እመ ረሰየ ቶማስ ደመ አካሉ አስራበ
ቂርቆስ ወልደ ኢየሉጣ ጽሕርተ ሐፀበ ።
ወሕሙም ሉቃስ እመ ኀሠሠ ሐሊበ
ጊዮርጊስ ላህመ አስተራከበ ፤
ፋሲለደስኒ ልጓመ ለእመ ነሀበ
ቴዎድሮስ ሐፂነ አቅረበ ።

## ትርጉም

ሰማእታት ከሰማእታት ጋር
እርስ በራሳቸው ተነጋገሩ ፤
ቶማስ የአካሉን ደም ፍፍቴን ቢያደርግ
የኢየሉጣ ልጅ ቂርቆስ ጋንን አጥቧልና ፣
ህመምተኛ/ሉቃስም ወተትን ቢፈልግ
ጊዮርጊስ ላምን አገናኘ ፤



ፋሲለደስም ልጓምን ቢሰራ
ቴዎድሮስ ብረትን አቀረበ ።

## ምስጢር

በአንድ ገዳም የሚኖሩ ሰዎች እየተመካከሩ ይተዳደራሉ ። አንዱ ውሃ ሲያመጣ ሌላው ጋን ያጥባል ። የሰማእቱ ቶማስ ደም እንደውሃ ሲፈስ ሰማእቱ ቂርቆስ በፈላ የብረት ጋን ውሃ ውስጥ ተጥሎ ተሰቃየ ። በሽተኛ “ወተት አማረኝ” ሲል የሚወደው ዘመዱ ላምን ያመጣለታል ። ሰማእቱ ጊዮርጊስም እንደ ላም ወተትን ከአንገቱ አፈሰሰ ። ገበሬ ከብረት የተሰሩ መሳሪያዎቹን ለብረት ሰራተኛ እንደሚሰጥ ሰማእቱ ፋሲለደስም እንደፈረስና እንደበቅሎ አፉን በልጓም ተለጎመ። ሰማእቱ ቴዎድሮስም በብረት ችንካሮች ሰውነቶቹን ሁሉ ተቸንከሮ ተሰቃየ በማለት ባለቅኔው የሰማእታትን ስቃይ በቅኔያቸው ምስጢር አስገንዝበዋል ።

263 ሥላሴ/ስ
ዘወልደ ኪዳን ጀንበሬ(መምህር ፤ ዘደብረ ታቦር)

ፍጹመ እመ ሐለየ
እግዚአብሔር ከመ ይግበር
ለወልዱ የዋሀ መርዓዊ ስቅለተ ሐማ ከብካበ
ከዐወ በምኩራበ ኤሊ እክለ ምድር ኮከበ ፤
ወትቤ ፀሐይ መርዓተ ማኒ ዘቀርበ
ኢይክውን ሊተ እመ ነበበ
በዋሕድ ዐርብ ከመ አጽግብ ሕዝበ
መና ክብር ብርሃነ ዕጹበ ።

## ትርጉም

እግዚአብሄር ለየዋህ
ሙሽራ/ልጁ የሃማ
ስቅላት/ ስርግን ሊያደርግ በፍፁም ባሰበ ጊዜ
በኤሊ ቤት የምድር እህል/ኮከብን አፈሰሰ ፤
የቀረበ የጨለማ ሙሽራ/ፀሃይም
የሚያስደንቅ የክብር እንጀራ/ብርሃንን
ህዝብን አጠግብ ዘንድ በአንድ አርብ



www.ethiopianorthodox.org

ቢናገር አይሆንልኝም አለች ።

## ምስጢር

ልጇን ለመዳር የተዘጋጀ አንድ ባለፀጋ ለድግሱ እንጀራ የሚሆነውን ጤፍ ከሰርጉ ቀን በፊት ቢያንስ አስራምስት ቀን ቀደም ብሎ ወደሚወዳቸው ጎረቤቶቹና ዘመዶቹ ቤት እየወሰደ ፡ ቁና ቁና ጤፍ ያፈሳል(ያካፍላል) ሴቶችም ፈጭተው ጋግረው ለሰርጉ ጊዜ እንጀራውን በመሶባቸው አድርገው ወስደው ያስረክባሉ ። ለቤቷ ስራ እንኳን ጊዜ ያጠራት ሴትም “ በአንድ አርብ ስንቱን ልሰራ ነው?” በማለት ትጨነቃለች ። እግዚአብሄር አብ ልጁ እግዚአብሄር ወልድ አዳምንና ሄዋንን ፡ ልጆቻቸውንም ለማዳን በእለተ አርብ በቀራንዮ በተሰቀለ ጊዘ ከዋክብት ረገፉ ፡ ፀሃይም ጨለመች ይላሉ ባለቅኔው ።

*264 ዥልክሙ/ስ*
*ዘገብረ ኢየሱስ(መምህር ፡ ዘደብረ ሊባኖስ)*
*ይነብብ አፍ ተረፈ ልቡና ።*
*እብነ ቢታንያስ ዮም ተረፈ መኑ ነበበ?*
*ሆሣዕና ዳዊት ቡሩክ እስመ እንዘ ይፈጥር ሕዝበ*
*ቀዳሚ በአርአያሁ*
*ለእብን በእንተ አእምሮ ኢፈጠረ ልበ ፡*
*ወበእንተ ካልእ ተናግሮ*
*ስብሐተ መላእክት ወሰብእ አፈ ወጥበበ ።*
*ለዮሴፍ እምከመ ኮነ እብነ ምድረ ከነዓን ምግበ*
*ውሂቦተ እብን ለቅዳሴ መኑመ ተሐዘበ?*
*እንዘ ጸቀውዕ ይውሕዝ እምከናፍረ እብን ንህበ*
*አኮኑ ሞገስ ቃሉ ወጣዕመ ነገሩ አስተዓፀበ*
*ሆሣዕና ዳዊት ዘበአ ምሡራበ አይሁድ ጸባበ*
*አኮኑ ሞገሰ ቃሉ ወጣዕመ ነገሩ አስተዓፀበ ።*

## ትርጉም

አፍ የልብን ትራፊ ይናገራል ።
የቢታንያ ድንጋይ ግን የማንን ትራፊ ተናገረ?
ምስጉን የዳዊት ሆሳእና ህዝብን ሲፈጥር



ቀድሞ በአምሳያው
ለድንጋይ ስለእውቀት ልብን አልፈጠረምና ፡
ስለሁለተኛ የመላእክትንና
የሰዎችን ምስጋና መናገርም አፍንና ጥበብን አልፈጠረምና ።
ለዮሴፍ ግን የከነአን ምድር ድንጋይ ምግብን ከሆነ
ለቅዳሴ ድንጋይን መስጠትን ማን ጠረጠረ?
ከድንጋይ ከንፈሮች ወለላ ንብኛን ሲፈስ
የቃሉን ሞገስና የነገሩን ጣም አድንቋልና
የጠበበች የአይሁድ ምሡራብን የገባ የዳዊት ሆሳእና
የቃሉን ሞገስና የነገሩን ጣም አድንቋልና ።

## ምስጢ.

ሰው ቢናገር ማሰቢያ አእምሮ ፡ መናገሪያ አንደበቱ ባላለው ነው ። ንጋይ ግን የሚያስብበት አእምሮ ፡ የሚናገርበት አንደበት ሳይኖረው ናገሩ ሳይዘሩ እንደሚያምረት ይቆጠራል ። በቅዳሴ ጊዜ የቁርባኑ ህብስት ሚዘጋጀው ከስንዴ ነው ። ድንጋይም በተአምር ለያእቆብ ልጅ ለዮሴፍ ብ ሆኖለት ከተመገበው ለሆሳእና ቅዳሴ መስዋእት ሊሆን ይገባዋል ። ብም ማር እንደሚሰራ የድንጋይን ነገር ሆሳእና ወደደው በማለት ለቅኔው አመስጥረዋል ።

*265ዋዜማ (383) ጎ*
*ዘድንቄ (አለቃ)*
*ሰላመ እምአብዝኁ*
*ሙሴ ወዮናስ እመ ኅቡረ ተረክቡ ፡*
*ክልኤሆሙ እስመ በውስቴታ ለቀላይ ተዐቅቡ ።*
*ሎጥስ ወቂርቆስ ለገቢረ በቀል እምቀርቡ ፡*
*እስመ ፈርሀ ነደ ሎጥ ማእከለ ሕዝቡ*
*ወጥቡዕ ለሕፃን ልቡ ።*

## ትርጉም

ሙሴና ዮናስ በአንድነት
ቢገኙ ኖሮ ሰላምን በአበዙ ነበር ፡



www.ethiopianorthodox.org

ሁለታቸው በወንዝ ውስጥ ተጠብቀዋልና ።
ሎጥና ቂርቆስ ግን በቀልን ለማድረግ በቀረቡ ነበር ፤
በህዝቡ መካከል ሎጥ እሳትን ፈርቷልና ፣
የህፃን ቂርቆስ ልብም ጨካኝ ነውና ።

## ምስጢር

ያንድ ገበሬ የቀኝና የግራ በሬዎች በእርሻ ጊዜ ተስማምተው ቀንበሩን ፣ ሞፈሩንና ማረሻውን ይስባሉ ። የእስራኤል መሪ ሙሴና ነቢዩ ዮናስ በውሃ ሰጥሞ ከመሞት ዳኑ ። ሳይጠመዱ የሚዋጉ በሬዎች በአንድነት ቢጠመዱ በቀንበሩ ስር ለጠብ እየተያዩ ሲጓተቱ ይውላሉ እንጂ የእርሻውን ስራ በመግባባት አያከናውኑም። ቂርቆስና ሎጥም በእሳት ነገር አንድ አልሆኑም ። ሎጥ የገሞራን እሳት ፈርቶ ሲሸሽ ህፃኑ ቂርቆስ በድፍረት በእሳት በፈላ ብረት ጋን ውሃ ውስጥ ገባ በማለት ባለቅኔው በሙሴ ፣ በነቢዩ ዮናስ ፣ በሎጥና በቂርቆስ የደረሰውን በቅኔያቸው ምስጢር አስረድተዋል ።

*266 ዋዜማ (388) ጎ*
*ዘወልደ ሥላሴ(አለቃ)*

*አመ ወርኀ ስቅለት ተሰእላከ*
*ሐዋርያተ ማይ መሪር ሐሞተ ነጌ ወከርቤ*
*ወይነ ማየ መሳብክት ለይኩን ዘትቤ ፤*
*ወታሕተ መትከፍትከ ኮኑ ጊዜ ፈቀድከ ምንዳቤ*
*ደቂቀ እስራኤል ዕርቃን ወጥብጣቤ*
*እንዘ አንተ ለዕርቃን ግልባቤ ።*

## ትርጉም

የጋኖች ውሃ ወይንን ይሁን
ያልህ ክርስቶስ! የመራራ ውሃ ቀጂዎች/የዝሆን
አሞትና ከርቤ በስቅለት ጊዜ ጠየቁህ ፤
የእስራኤል ልጆች/ራቁትነትና ግርፋትም ችግርን
በፈቀድህ ጊዜ ከትከሻህ በታች ሆኑ ፤
አንተ ለራቁትነት መሸፈኛ ስትሆን ።



## ምስጢር

በድግስ ጊዜ ወይንን(የወይን ጠጅን ፣ ጠላን) በየጋኑ እንዲሾሙ የሚያዝዝ ባለቤትን ውሃ ቀጂዎች እንደሚያነጋግሩት ሁሉ ውሃውን የወይን ጠጅ ያደረገ ክርስቶስን አይሁድ ያጠጡት የዝሆን አሞትና ከርቤ ነመዘዙት ።

የእስራኤልም ልጆች በቁመት ከንጉሳቸው ከሳኦል ትከሻ በታች (ከስልጣኑ ስር) እንደሆኑ ራቁትነትና ግርፋትም በክርስቶስ ጀርባ ተፈፀሙ ። እርሱ የተራቆቱትን አልባሽ ሲሆን ችግረኛን መሰለ በማለት ባለቅኔው የክርስቶስን ከሃሊነትና ታጋሽነት በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል ።

*267 ዘአምላኪየ/ስ*
*ዘገብረ ሥላሴ( መምህር ፣ ዘኤልያስ)*

*አልቦ ለወልድ ውስተ ገጸ ምድር አብ*
*ወእም አልቦ በሰማይ ርሑብ*
*ከመ በሰማይ ገዳም ወበገጸ ምድር ኮከብ ።*

## ትርጉም

በሰማይ ገዳም ፣ በምድር ፊትም
ኮከብ እንደሌለ ለወልድ በምድር ፊት
አባት የለውም ፤ በሰፊ ሰማይም እናት የለችውም ።

## ምስጢር

ኮከብ በሰማይ እንጂ በምድር የለም ፤ እንዲሁም እግዚአብሄር ልድ ከእግዚአብሄር አብ በሰማይ ሲወለድ ያለእናት ነው ። በሰማይም ካ እንደ ሌለ ወልድም በምድር ከቅድስት ማርያም ያለአባት ተወለደ ላሉ ባለቅኔው ።

*268 ሥላሴ/ስ*
*ዘወልደ ጊዮርጊስ(አለቃ)*

*ወልድ ወላዲትከ*
*ዐባይ ይእቲ እመሠረታ*



www.ethiopianorthodox.org

*እመኒ በግብጽ አስተዋረዳ ረኀብ*
*እንዘ መሠረታ ውእቱ መክብብ ፤*
*ትውልደ አቡከ ጌር ባሕቱ ከመ ኢንንግር ለሕዝብ*
*መሠረት ሎቱ ኢይትረከብ ፤*
*ወሐረገ ትውልድ ለከ ከመ ኢንስሐብ*
*ኢሀለዎ ለአቡከ አብ ።*

## ትርጉም

ወልድ! መሰረቷ
መክብብ/የሹም ዘር/ ሲሆን
ምንም በግብፅ ራብ ቢያዋርዳት
እናትህ ከመሰረቷ ታላቅ ናት ፤
የቸር አባትህን ትውልድ ግን ለህዝብ አንዳንናገር
ለእርሱ መሰረት አይገኝም ፤
የትውልድንም ሃረግ ለአንተ እንዳንስብ
ለአባትህ አባት የለውም ።

## ምስጢር

ግድግዳ በመሰረት ላይ ይመሰረታል ፤ በግድግዳም ላይ ጣሪያ ይሰራል ። መሰረቱ ጠንካራ ከሆነ ቤቱም ጠንካራ ይሆናል ። የቅድስት ማርያምም ልደት ከከበረ ትውልድ(ዘር) ስለሆነ የእግዚአብሄር ወልድ ከእርሷ መወለድ ከአብርሃም ጀምሮ ይቆጠርለታል ። ግን ግድግዳና ጣሪያ ያለመሰረት እንደማይቆሙ ከአለም መፈጠር በፊት ከአብ የእግዚአብሄር ወልድ መወለዱ አያትና ቅድመ አያት አይነገሩለትም ። ምክንያቱም መሰረቱ አብ ስለሆነ ነው በማለት ባለቅኔው አመስጥረዋል ።

*269 መወድስ/ስ*
*ዘተጠምቆ(አለቃ)*

*ዓለም ትሰርሕ በወሊደ መንታ*
*እንዘ ለይሁዳ ጎሣር ወለማትያስ ከብካብ ፤*
*ዓለመ ተፈጥሮሰ ንፍታሕ እማኅተመ ፍጥረት መዝገብ*
*እለ ተጋባዕነ በምስጢር መርህብ ፤*



*እመኒ አፈ ጥበብ*
*ይነብብ ቃለ ዘአስተዳለወ ልብ ።*
*ደመናትሂ ያወርዱ በምድረ አሕዛብ ወሕዝብ*
*ዝናመ ለሐራሲ ወመና ለያዕቆብ ፤*
*እስመ ዘጸሐፈ ዮናስ መጽሐፈ ነበልባል ዕጹብ*
*ይጸሐፍ በነነዌ ወበሰዶም ይትነበብ ።*

## ትርጉም

አለም ለይሁዳ አሳር ፣ ለማትያስም
ሰርግ ስትሆን መንታን በመውለድ ትደክማለች ፤
ግን በምስጢር/መስክ የተሰበሰብን የተፈጥሮ አለምን
ከፍጥረት ማህተም መዝገብ እንፍታ ፤
ልብ ያዘጋጀውን ቃል ምንም ቢናገር ።
ደመናዎችም ዝናምን ለአራሽ ለያእቆብም መናን
በአህዛብና በህዝቦች(በእስራኤል) ምድር ያወርዳሉ ፤
ዮናስ የፃፈው የሚያስደንቅ መፅሃፍ/ነበልባል
በነነዌ ተፅፎ በሰዶም ይነበባልና ።

*270 ዥ ልክሙ /ስ*
*ዘጎበና (አለቃ)*

*እስራኤል ኢይብላዕ ጽፉቀ ስኰና*
*ወዘጥረሲሁ ክልኤቱ እንስሳ ገዳም ቅሩብ*
*ዘባነ ፈቃዱ ቀጥቀጠ ኃይለ አንበሳ ንባብ ፤*
*እስመ ቆመ ዘእንበለ በትር መደልው ልብ*
*ሀፀደ አሪት በየዐቅብ*
*ጽጌ ትእዛዛ ኢትቅሥም ሕልመ ራእየ ጴጥሮስ ንህብ ።*
*ንሕነሰ እመ ዘላዕነ እምጽንዐ በለስ ረኃብ*
*ጽፉቀ ባሕርይ ወዘክልኤቱ ልደታቲሁ በግዐ ዐርብ*
*መንጽሔ አበሳ ውእቱ ወዘዐዘቅተ ክብር ማሕየብ ፤*
*ነፋስ ሕይወቱ ኀበ መልዕልተ እስከ ቈመተነ ይስሕብ*
*አምጣነ ዕሙቅ ልደት ብዕለ ጸጋሁ ለአብ*
*ነፋስ ሕይወቱ ኀበ መልዕልተ እስከ ቈመተነ ይስሕብ ።*



www.ethiopianorthodox.org

## ትርጉም

እስራኤል ሸሆናው የተደፈነውንና
ጥርሱ በላይና በታች ሁለት ወገን የሆነውን እንስሳ እንዳይበላ
የአንበሳ ሃይል /ንባብ ጀርባ/ ፈቃዱን ቀጠቀጠ ፤
የጴጥሮስ ራእይ ህልም /ንብ አበባ/ ትእዛዟን
እንዳትቀስም አሪት/ቦታን
የሚጠብቅ መፅሃፍ/ልብ ያለ በትር ቆሟልና ።
ግን ባህርዩ አንድ የሆነውንና ልደቶቹ የሆኑትን
የእርብን በግ ከበለስ/ራብ ጥናት የተነሳ እኛ ብንበላ
አበሳን የሚያነፃ ነው ፤ የክብር ጉድጓድ መቅጃም ነው ፤
ነፋስ/ሕይወቱ ቁመታችንን ወደላይ እስኪስብ ድረስ
የአብ የስጦታው ብልፅግና ልደት ጥልቅ ነውና
ነፋስ/ህይወቱ ቁመታችንን ወደ ላይ እስኪስብ ድረስ ።

## ምስጢር

እንስሳ ሳሩን እየበላ ሳለ አንበሳ እንደሚሰብረው እስራኤል ሸሆናው ድፍን የሆነውንና ጥርሱ ሁለት ወገን የሆነውን (የላይና የታች ጥርስ ያለውን እንስሳ) እንዳይበሉ የአሪት ትእዛዝ ከልክሏቸው ነበር ። አንበሳ እንስሳውን የሚሰብረው እረኛው ያለመከላከያ መሳሪያ ስለቆመ እንደሆነ የእስራኤል ልብም አሪትን ባለመድፈር እንደፀና ነው ። ንብ አበባን እንደሚቀስም የጴጥሮስ የራእዩ ህልም የአሪትን ትእዛዝ አፀደቀ ። ይኸውም የተራበ ያገኘውን ሁሉ ሳይመርጥ እንደሚበላ ከሁለት ባህርያት አንድ ባህርይ የሆነውንና ሁለት ልደቶቹ የሚታመኑለት የእርብ መስዋእትን (የክርስቶስን ስጋና ደም) መብላት ለምእመናን የሃጢአት ማስተስረያንና የልጅነት ማግኛን ሆነ ። ጥልቅ ባህርም መሰረቱ እንደማይገኝ ወልድም ከአብ የተወለደው መወለድ ተመርምሮ አይደረስበትም በማለት ባለቅኔው አመስጥረዋል ።

## ታሪክ

በቂሳርያ ቆርነሌዎስ የተባለ ከአህዛብ ወገን የሆነ አንድ መቶ አለቃ ነበር ። የእርሱም ፀሎቱና ምፅዋቱ በአምላክ ስለተወደዱለት ጥምቀተ



ርስትናን እንዲቀበል ቅዱስ ጴጥሮስ በስድስት ሰአት ከፎቅ ላይ ይፀልይ
በር ፤ በዚያም እንቅልፍ መጣበት ። ሰማይ ተከፍቶ በአራት ማእዘን
ተያዘ መጋረጃ መሳይ እቃ ካሰማይ ወደ ምድር ሲወርድ አየ ።
ውስጡም አራት እግር ያላቸው እንስሳት እሪያዎችም ነበሩበት ።
ልአክ ወደ እሪያው እያመለከተ "ይህን እረድና ብላ" ቢለው እርሱም
"ርኩስ ነገርን በልቼም አላውቅ" አለው ። መጋረጃው ከእነንዙ
ተሸምልሎ (ተጠቅልሎ) ወደላይ ተመልሷል ። ጴጥሮስም በእሪያ
ተመሰለውን ቆርነሌዎስን አጥምቋል (የሀዋ· 10)

271 ሥላሴ /ስ

*ዘገብረ ሥላሴ (መምህር ፡ ዘኤልየስ)*

*ዐቀበ ለእግዚኡ*
*ስደተ ሄሮድስ ዝናመ ጊዜ*
*ከመ እምዐላዊ አክዐብ ሠለስተ ሱባዔ አውራኅ መዝገቦ*
*ኤልያስ ሶበ ሱዐላዊ አክአብ ረከቦ*
*ምስለ ዘማዊት ስጊድ ለሥዕለ ፀሐይ ስኪቦ ፡*
*አምጣነ በፀሐይ አመንደቦ*
*መዋዕለ ፀሐይ ወወርኀ ብዙኀ ዐስቦ*
*ለነቢዩ እግዚኡ የሀቦ ።*

## ትርጉም

የጊዜ ዝናብ
በወሮች ሶስት ሱባኤ
ከወንጀለኛ አክአብ እንደሸሸ ከሄሮድስ መሸሽ ሳጥኑን
ኤልያስ ለጌታው ጠበቀ ፡ ወንጀለኛ አክአብን
ለፀሃይ ስእል ከመስገድ/ ዘማዊት ጋር ተኝቶ ባገኘው ጊዜ
በፀሃይ አስቸግሮታልና ፡
የፀሃይና የጨረቃ ዘመን/ብዙ ደመወዙን
ለነቢይ ኤልያስ ጌታው ይሰጠው ዘንድ ።

## ምስጢር

አሽከር የጌታውን ንብረት እንዲጠብቅ ነቢይ ኤልያስ በዘመኑ
ዝናብ ሶስት አመት ከመንፈቅ እንዳይዘንብ ማድረጉን ኢየሱስ ተሰዶ



www.ethiopianorthodox.org

በ ብዕ ሶስት አመት ከስድስት ወር ለመኖሩ ምሳሌ አደረገው ። ከዘማዊት ሴት ጋር ተኝቶ የተገኘ የጎልማሳ ሚስት ደፋሪ በህግ እንደሚቀጣ ለሰሃዪ ስእል ከመስገድ ጋር ነግሶ የኖረ የእስራኤል ንጉስ አክአብ የሀሃይ ሃሩር በፈጠረው ድርቅ ተጨነቀ ። ከዚህም ሌላ የጌታውን ንብረት የጠበቀ ሎሌ ደመወዙን ከጌታው እንዲያገኝ ነቢይ ኤልያስ ንጉስ አክአብን ሳይፈራ በመገሰፁ የፀሃይንና የጨረቃን ያህል እድሜን ከፈጣሪው በመቀደሉ ፀሃይና ጨረቃ በሚያልፉበት ጊዜ የሚያልፍ ሆነ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

*272 ግእዝ ጉባኤ ቃና /ስ*

*ዘወልደ ሰንበት (ሊቀ ኅሩያን)*

*አፈቅር አነ ጉባኤ ቃና በግዕተ ፤*

*ጉባኤ ቃና በግዕት አምጣነ ትመልእ ቤተ ።*

## ትርጉም

እኔ ጉባኤ ቃና/በግን እወዳለሁ ፤

ጉባኤ ቃና/በግ ቤትን ትሞላለችና ።

## ምስጢር

ወልዳ ወልዳ ቤት ሙሉ የሆነች ወላድ በግ በጣም ትወደዳለች ። እንዲሁም ባለሁለት ቤት የሆነች ጉባኤ ቃና ከሁለት ቤት አንስታ በሀረግ እየተራዘመች አስራ አንድ ቤት እስካለው እስከ እጣነ ሞገር ስለምትዘምት በቅድሚያ እርሷን በጥሩ ሁኔታ ማጥናት ይገባል ይላሉ ባለቅኔው ።

273 ግእዝ ጉባኤ ቃና /ስ

ነነዌ አእመርነ ዘከመ ኮንኪ ሕምምተ ፤

ኵሉ ርእስኪ አምጣነ ኮነ እሳተ ።

## ትርጉም

ነነዌ ! ህመምተኛ እንደሆንሽ አወቅን ፤

ራስሽ ሁሉ እሳት ሆኗልና ።



## ምስጢር

አንዲት ታማ የተኛች ሴት ራሷ ሁሉ እሳት ሲሆን (ሲፋጅ) ራሷን የዳሰሳት ዘመዷ "በጣም ታመሻል ሁለንተናሽ እሳት ሆኗል" ይላታል ። ከሰማይ የወረደ እሳት በነነዌ ከተማ ራስ ላይ አንዣቦ ሳያቃጥላት ወደላይ መመለሱ በቅኔው ተኳሽቷል ።

*274 ዘአምላኪየ /ስ*

*ዘጥሩነህ (አለቃ ፡ ዘቦረና)*

*አመተ እግዚእ መቅደስ እንተ ትጸውር ልሕኵተ*

*ትኩን እምነ ሰማይ ወትኩን መሬተ*

*ጊዜ ጽምዐ ማይ ኢያቀት ፤ እስመ ረወየት ሠለስተ ።*

## ትርጉም

ገንቦን የምትሸከም የጌታ አገልጋይ/መቅደስ

እሰማይ ትሆን ፡ እመሬትም ትሆን

በውሃ ጥም ጊዜ አላወቀችም ፤ ሶስቱን ዋንጫ ጠላ ከልብሳለችና ።

## ምስጢር

በውሃ ጥም ጊዜ ሶስቱን ዋንጫ ጠላ ከልብሳ (ጠጥታ) የሰከረች ገንቦኛ ሴት እሰማይ ትሆን እመሬት ትሆን አታውቅም ይዞርባታል ። ክርስቶስ ሰራት የምትባል ቤተ መቅደስ ሰማያዊት እንዳትባል በሶስት ድንጋይ ብቻ ፀናች ። ምድራዊት እንዳትባልም በውሃ የቦካ ጭቃና እንጨት ሳይኖሩባት በሶስት ድንጋይ ብቻ ተሰራች ። አገልጋይቱም ገንቦን እንደምትሸከም ይህች መቅደስ የገንቦ ምሳሌ የሆነችውን ቅድስት ማርያምን አስመሰገነች በማለት የቅኔው ደራሲ አስገንዝበዋል (ስንክ· ግንቦት 20) ።

*275 አጭር ዋዜማ /ስ*

*ዘጥሩነህ (አለቃ ፡ ዘቦረና)*

*እሳት ሐንካስ ነነዌ ዘየዐቅብ ቤተ*

*በሠግረ በትረ ኃይል ኀለፈ ደቂቀ ባቢል ሠለስተ ።*



www.ethiopianorthodox.org

## ትርጉም

በትን የሚጠብቅ የነነዌ አንካሳ/እሳት
በሃይል በትር ርምጃ ሶስቱን የባቢሎንን ልጆች አለፈ ።

## ምስጢር

በትን የሚጠብቅ አንካሳ ዘበኛ በበትር እየተወረወረ (በትሩን ተደግፎ እየዘለለ) ልጆችን አልፎ ይሄዳል ። እሳትም በባቢሎን ሶስቱን ልጆች (አናንያን ፡ አዛርያንና ሚሳኤልን) ሳያቃጥል በገብርኤል በትር ተደረገ በሚባለው ተአምር ቀዝቅዞ ሌሎቹን አቃጠለ ። አንዳንድ አንካሳ በቤት ጥበቃ እንደሚውል እሳትም በቤት ውስጥ መልካም አገልግሎት አለው ። ያነከሰ እግር ከመሬት በላይ እንደሚንጠለጠል እሳትም በነነዌ ከላይ ተንጠልጥሎ ታየ እንጂ መሬትን አልነካም ይላሉ ባለቅኔው (ዳን. 3፡ ዮና. 3)

*276 ዋዜማ (417) ጎ*

*ዘገብረ መድኅን (ዘሌመን ሥላሴ)*

*ለወልድከ ባሕረ ኤርትራ*
*ሙሴ ገሥፆ ከመ ይትመሀር ትሥልስተ*
*ወበበትር እመ ዘበጥኮሁ ኢይመውት ሞተ ።*
*ወእመ ጸለየ ፈርዖን ጸሎተ ዮናስ ስጥመተ*
*እኁከ አሮን ማዕበል ስሕተ*
*ወሕዝብከ አበሱ ማየተ ።*

## ትርጉም

ሙሴ ! ልጅህ /የኤርትራ
ባህርን ሶስትነትን ይማር ዘንድ ገስፀው ፡
በበትርም ብትመታው ሞትን አይሞትም ።
ፈርኦንም የዮናስ ፀሎት/ ስጥመትን በፀለየ ጊዜ
ወንድምህ አሮን ማእበልን ሳተ ፡
ወገኖችህም ውሃዎችን በደሉ ።



## ምስጢር

"ወንድሜ ሆይ ! ይህን ልጅህን ቅጣው ፡ በበትር ብትመታው የሚሞት አይምስልህ" በማለት ወንድም ወንድሙን እንደሚመክረው ሙሴም የኤርትራ ባህርን በበትሩ ከሶስት ላይ ከፈለውና እስራኤል ምንም ውሃ ሳይነካቸው ተሻገሩ ። በግብፃውያን ግን እንደ ቀድሞው ባህር ስለሆነባቸው በስላም አልተሻገሩም ። ካህኑ አሮን ጣኦትን ለእስራኤል በመስራት እንደሳተና እስራኤልም ጣኦቱን በማምለክ አምላካቸውን እንደበደሉ ፈርኦን ግብፃውያንን እየመራ በኤርትራ ባህር ሲሰጥም ማእበሉ ተደፋበት በማለት ባለቅኔው ሙሴና አሮን ይመሯቸው ለነበሩ እስራኤላውያን ተፈፅሟል የሚባለውን ተአምር በቅኔያቸው አስረድተዋል (ዘፀአ. 3 15) ።

*277 ዋዜማ ስ.*

*ዘተክልኝ (ቀኛዝማች ፡ ዘየነጃ)*

*ለሕሙም ሰማዕተ ልዳ*
*ዘእሲተ ቤቱ ወንጌል እንዘ ታነድድ እሳተ*
*አሕመመቶ ነዋ ሰብዐተ ዓመተ ፡*
*ዘእንበሌሃ ካልእተ እስመ ኢየአምር ምንተ ፡*
*ወእሙ ክግድ በከየት ግብተ*
*ጊዜ ሞቱ ጸዊራ መጥባሕተ ።*

## ትርጉም

በሽተኛ /የልዳ ሰማእትን
የቤቱ ሴት/ ወንጌል እሳትን እያነደደች
እነሆ ሰባት አመት አስታመመችው ፡
ከእርሷ በቀር ሌላ አያውቅምና ።
እናቱ/ አንገትም በሞቱ ጊዜ ሰይፍ ተሸክማ አለቀሰች ።

## ምስጢር

ክርስቲያን ባል ከሀግ ሚስቱ በቀር ሌላ ሴት በሩካቤ አያውቅም ። ስለዚህ በታመመ ጊዜ እስከሞቱ ድረስ እሳቱን እያነደደች ፡ ውሃ



www.ethiopianorthodox.org

እየቀዳች፡ የጠየቀትን ሁሉ እየሚላች ታስታምመዋለች ። በሞተም
እናቱ መሳሪያውን ይዛ ታለቅስለታለች ። በወንጌል ስብከት ከምት
የክርስትና ሃይማኖት በቀር አምልኮ ባእድን የተወ ሰማእቱ ቅ
ጊዮርጊስንም ወንጌል በእሳት ውስጥ እንዲገባና ለባት አመት
ስቃይን እንዲቀበል አደረገችው ። አንገቱም በሰይፍ ተከለለች (ተ
ጠች) በማለት ባለቅኔው አመስጥረዋል ።

*278 መወድስ ስ*

*ዘገብረ ሥላሴ (መምህር ፡ ዘኤልያስ)*

*ኦ ሀገር ዘኢይትበጸው*

*ኖኅተ ጸሎት እዝንከ መዓልተ ወሌሊተ ?*

*ዑረተ ዐይንየ ረሲ ዘዐይነ ቂርቆስ ዑረተ*

*ኢይሖር እምነ ጽልመት ዳግመ ጽልመተ ፤*

*ኀዘነ ወትፍሥሕተ*

*በኵሉ አዝማን እስመ ዘታስተባሪ አንተ ።*

*ፀሐይሰ ወማኅቶት ኢይኤድሙኒ ሊተ*

*ጽርሐ ትሥልስትከ ዋሕዳዊ ክልልተ መለኮተ ፤*

*አኮኑ አእመርኩ ከመ ኢተኀሥሥ ምንተ*

*ፀሐየ ጊዜ ንግህ ወበፍና ሠርክ ማኅቶተ ።*

## ትርጉም

የፀሎት ደጃፍ /ጆሮህ በቀንና በሌሊት የማይዘጋ አገር ሆ
ከጨለማ ወደሁለተኛ ጨለማ እንዳልሄድ
የአይኔን እውረት የቂርቆስ አይን እውረትን አድርግ ፤
ሃዘንና ደስታን
በዘመኖች ሁሉ የምታፈራርቅ አንተ ነህና ።
ፀሃይና መብራት ግን እኔን አያምሩኝም ፤
አንድነት ያላት የሶስትነትህ አዳራሽ መለኮትን ተከልላ
በነግህ ፀሃይን ፡ በሰርክም ጊዜ መብራትን
ምንም እንደማትሻ አውቂያለሁና ።



## ምስጢር

በተከፈተ ደጃፍ በቀንም በሌሊትም ይገባበታል ይፀባበታልም ፤ በአምላክ ጆሮም በቀንና በሌሊት የተፀለየው ፀሎት ይሰማበታል ። ደግሞ የውጪው በር ተዘግቶ የውስጡ እንደሚከፈት የውጪው አይን ቢጠፋ የልብ አይን ከበራ ጉዳት የለም ። የሶስት አመት ዘፃን ቂርቆስ አይኖቹን በከሃዲዎች ችንካር ቢቸነከርም የክርስቶስን አገር (መንግስተ ሰማይን) ከማየት አለመታወሩን በመጥቀስ አይነ ስውርነታቸው እንደ እርሱ እውርነት እንዲሆንላቸው ተመኝተዋል ።

በጨለማ የሚሄድ ሰው እንደሚሰናከልም በስጋ አይን እውርነት ብርሃንን ሳያዩ ኖሮ በአካለ ነፍስ ወደ ገሃነም ጨለማ መግባት እጥፍ ድርብ ቅጣት ነው ። ቀንና ሌሊት እንደሚፈራረቁ ያዘነውን ማስደሰትና የተሰደሰተውን ማሳዘን በእግዚአብሄር ትእዛዝ ይፈፀማል ። በቢት ፀሃይን፡ በማታ ጊዜም መብራትን መሻት ብርድንና ጨለማን ለማራቅ ነው ። የክርስቶስ አዳራሽም ፀሃይዋም ፡ መብራቷም እርሱ ራሱ ሆነ በማለት የተቀኙትን ባለቅኔ በእውርነታቸው ምክንያት የዚህን አለም ብርሃን አለማየታቸው አላስፀፀታቸውም ። ምክንያቱም በተስፋ በሚመኙት በክርስቶስ አዳራሽ ከገቡ ብርሃን መጐናፀፍ የሚችሉ መሆኑን በእምነት ስለተቀበሉ በማለት ባለቅኔው ያስረዳሉ ።

*279 መወድስ /ስ*

*በዐቢይ ግፍዕ መሥፈርተ ናዘቴ*

*ወዘአርዮ መድሎት እግዚአ ገቢር ምሕረተ*

*እምእደ አይሁድ ይትሌቃሕ ሊቃሐ ፍጡራን ሞተ*

*ለአይሁድ ዘይሌቅሖሙ አሐተ ሰዓተ ፤*

*ወሰምዐ ጽዕለታተ*

*አእዛኒሁ ዘሰምዐ ቅዳሴ ወአኰቴተ ።*

*ይለብሳሂ ወይትከደና በእደ ይሁዳ ዘስሕተ*

*ተጸፍዖ መላትሒሁ እለ ኮና ለሩቃተ ፤*

*ወገቦ ዚአሁ ጽሙለ እምቅድመ ይስተይ ዙናተ*

*እለ ርኀቡ አእጋሪሁ ይበልዑ ቅንዋተ ።*

www.ethiopianorthodox.org

## ትርጉም

በታላቅ ግፍ /የናቡቴ መስፈሪያና
በኦርዮ ሚዛን ምህረትን የማድረግ ጌታ
ለአይሁድ በአንድ ሰአት የሚያበድራቸውን
የፍጡሮች ብድር/ ሞትን ከአይሁድ እጅ ይበደራል ፤
ቅዳሴንና ምስጋናን
የሰሙ ጆሮዎቹም ስድቦቹን ሰሙ ።
ራቁታቸውን የሆኑ ጉንጮቹም
በሳተ በይሁዳ እጅ ጥፊን ይለብሱና ይሸፈናሉ ፤
የተጠማ ጎኑም ጦርን ሳይጠጣ
የተራቡ እግሮቹ ችንካሮችን ይበላሉ ።

## ምስጢር

ተበዳሪ ሰው በትልቅ መስፈሪያም ፤ በሚዛንም ብድር ይበደራል ። እንዲሁም ለፍጥረቱ ምህረት የሚያደርግ እግዚአብሄር ወልድ እን[illegible] ናቡቴና እንደ ኦርዮ በግፍ ከአይሁድ እጅ ሞትን ተቀበለ ። ተበዳሪው[illegible] የተበደረው ብድር ባለፀጋ በነበረበት ጊዜ ለሌሎች ሊያበድራቸው[illegible] የሚቻለው እንደነበር አምላክም በአይሁድ እጅ የሞተው አይሁድ[illegible] በአንድ ጊዜ ሊገድላቸው ሲቻለው ነው ።

መልካም ነገር በሰሙበት ጆሮ ክፉ እንደመስማት ፍፁም ምስጋና[illegible] የሰሙ የክርስቶስ ጆሮዎች ስድቦችን አዳመጡ ። የታረዙ ሰዎች ልብሶች[illegible] እንደሚለብሱ የክርስቶስ ጉንጮችም በአይሁድ እጅ በጥፊ ተመቱ ። አንዳንዱ ችግረኛ ውሃ እንኳን አጥቶ ሲቸገር ሌሎች ሰዎች ከሚያስፈል[illegible] ቸው በላይ መብልና መጠጥ አግኝተው ይደሰታሉ ። ከዚህም አንፃር[illegible] የክርስቶስ ጎን ገና በጦር ሳይወጋ እግሮቹ በችንካሮች ተቸነከሩ በማለት[illegible] ቅኔው ተመስጥሯል ።

*280 ዕዝል ክብር ይእቲ (3.14) ን*
*ዘአድማሱ ጌትየ (ንቡረ እድ)*
*ምዕረ ሃሀ ርእሶ ዘተአገሠ ጸእለተ*
*ለኬፋ ወሳውል እንዘ ይሜህር ሥርሀተ ፤*



*ሰማዕተ ልዳለ ኄር ከመ ይትመካህ ድኅሪተ*
*ልቃሐ ሞቱ ፈደየ ለአግዓዚሁ ህየንተ አሐዱ ትርብዕተ ።*

## ትርጉም

ለጴጥሮስና ለጳውሎስ ስርአትን ሲያስተምር
ስድብን የታገሰ ክርስቶስ ራሱን አንድ ጊዜ ሰዋ ፤
ቸር /የልዳ ሰማእት ግን በሁዋላ ይመካ ዘንድ
ብድር/ ሞቱን ለጌታው በአንዱ ፋንታ አራትን ከፈለ ።

## ምስጢር

መስዋእት አንድ ጊዜ ከተሰዋ በሁዋላ በዚያው ቀን ሁለተኛ አይሰዋም ። ክርስቶስም በመስቀል ላይ አንድ ጊዜ ከተሰቀለ ሁለተኛ አይሰቀልም ። በወለድ የተበደረ ሰውም ብድሩን በአንድ ፈንታ አራት አድርጎ ይከፍላል ። ጊዮርጊስም በመንግስተ ሰማይ እንዲደሰት ሶስት ጊዜ ስለጌታው ክርስቶስ ሞቶ ተነሳና በአራተኛው ጊዜ አንገቱን በሰይፍ ተቆርጦ ሞተ ይላሉ ባለቅኔው ።

*281 ማእዝ ጉባኤ ቃና /ስ*
*ለውርዝው ቶማስ ወድሶተ ሰብእ ድልወቱ ፤*
*እምነ ጌጋያት አእጋር እምጣነ ንጹሕ ውእቱ ።*

## ትርጉም

ለጎበዝ /ቶማስ የሰው ምስጋና ተገቢው ነው ፤
ከበደሎች/ እግሮች የነፃ ነውና ።

## ምስጢር

ማንንም ሰው ያልበደለና አገሩን ወዳድ የሆነ ሰው በሰዎች ዘንድ ይመሰገናል ። ቶማስም ወንጌልን ሲሰብክ በትምህርቱ ተቃዋሚዎች እግሮቹን ስለተቆረጠ በክርስቶስ ዘንድ የገድሉን ዋጋ ሊያገኝ ይገባዋል በማለት ባለቅኔው የሰማእቱ ቶማስን ስቃይ በቅኔያቸው ገልጠዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

*282 ዕዝል ጉባኤ ቃና /ስ*
*ኮነ ወይን ምቱረ አጻብዕ ዐሥሩ*
*ደዌሁ ዝናም እስመ እንተ ዘርዕ ውእቱ ።*

## ትርጉም

ወይን /ሰው አስር ጣቶቹን የተቆረጠን ሆነ ፤
ደዌው/ ዝናብ የዘር ነውና ።

## ምስጢር

ከዘር የወረደ ደዌ ስጋ (የቁምጥና በሽታ) የሰውየውን ጣቶች እንደሚቆርጣቸው የወይን ቅጠል በክረምት መርገፉን ለመግለጥ ያህል ዘርን ለማብቀልና ለማሳደግ የሚዘንብ ዝናብ ወይንን ጐንደለው በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

*283 ግእዝ ጉባኤ ቃና /ስ*
*መኮንን ይፈትሕ ላዕለ ፍጡራን እስፍንቱ ፤*
*ዙሉ ፍጥረት እስመ ቀታሌ ነፍስ ውእቱ ።*

## ትርጉም

ፈራጅ በስንቶች ፍጥረቶች ላይ ይፈርዳል ፤
ፍጥረት ሁሉ ነፍስ ገዳይ ነውና ።

## ምስጢር

ሁሉም ጥፋተኛ ከሆነ ማንም በማንም ላይ ሊፈርድ አይችልም ። ሰው ሁሉ ነፍስ ገዳይ ከሆነ "ነፍስን አትግደል" ያለ አምላክ ስንቱን ይኰንነዋል በማለት የጥፋተኞችን መብዛት በቅኔያቸው ያስረዳሉ ።

*284 ዕዝል ጉባኤ ቃና /ስ*
*መፍትው ለቶማስ ያፍቅርዎ ሕዝበ ኑፋቄ ጻላእቱ ፤*
*እስመ ለወልዶሙ ሰይፍ አንሥአ በአጻብዒሁ ዐሥሩ ።*



## ትርጉም

ቶማስን የጥርጥር ሕዝብ /ጠላቶቹ ይወዱት ዘንድ ተገቢ ነው፤
ልጃቸው/ ሰይፍን በአስር ጣቶቹ አንስቶታልና ።

## ምስጢር

በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ስርአት መሰረት ያንዱን ክርስቲያን ወንድ ልጅ ክርስትና ያነሳ ሰው ወደ ክርስትና ልጁ እያመለከተ "ይህ በአስር ጣቴ ያነሳሁት ልጄ ነው" ይላል ። የክርስትና አባት ምሳሌ የሆነው ቶማስ የልጁ ምሳሌ በሆነው በከሃዲዎች ሰይፍ አስሩን የእጆቹን ጣቶች አስቆረጠ ። የቆረጡትን ጠላቶቹንም በጠላት መልክ አልተመለከታቸውም ይላሉ ባለቅኔው ።

*285 ግዕዝ ጉባኤ ቃና /ስ*
*ሐካይ ቶማስ ሀላዌ ዚአከ ከንቱ ፤*
*ለቤትከ አፍ አምጣነ ማዕጾ አልቦቱ ።*

## ትርጉም

ሰነፍ /ቶማስ ! የአንተ ኑሮ ብላሽ ነው ፤
ለቤትህ/ አፍ መዝጊያ የለውምና ።

## ምስጢር

ለኑሮው የማያውቅ ሰነፍ ሰው ለቤቱ መዝጊያ መግጠም ሲያቅተው፡ "የእገሌ ኑሮ ኑሮ አይባልም ከንቱ ነው" ይባላል ። የዚህን አለም ክብር ከንቱ ያደረገው የመርአስ ኤጲስ ቆጶስ ሰማእቱ ቶማስ ከንፈሮቹን በከሃዲዎች ሰይፍ ሲቆረጥ ጊዜ አፉ ክፍቱን ቀረ ማለት በቅኔው ተገልጧል ።

*286 ዘአምላኪየ ስ*
*ዘምሥራቅ (አለቃ ፡ ዘኤልሻማ)*
*ምሳሌ አበዊነ በጽሐ በዘካርያስ ዘታሕቱ ፤*



www.ethiopianorthodox.org

*ማእደ ተመትሮ እንተ ቀርበ ሎቱ ፤*
*አኮኑ ተደረ በወልዱ እንዘ ያመከኒ ቦቱ ።*

## ትርጉም

በታችኛው ዘካርያስ የአባቶቻችን ምሳሌ ደረስ ፤
የቀረበለትን ማእድ/መቆረጥን
በልጁ አመካኝቶ በልቷልና ።

## ምስጢር

"በልጅ አመካኝቶ ይበሏል አንጉቶ" እንዲሉ እናት በልጇ ስም
አንጉታ ትበላለች ። አባትም ለልጁ ሊያጎርሰው ያሰበውን ይጎርሳል ።
አባት ዘካርያስ በልጁ በዮሃንስ ምክንያት ተቆርጦ የተሰቀየውን ስቃይ
ልጁ ዮሃንስም እንዳባቱ ተቀበለው በማለት ባለቅኔው አመስጥረዋል ።

*287 ዘአምላኪየ /ስ*
*ዘምሥራቅ (አሊቃ ፡ ዘሌልሻማ)*
*አካለ መርዓዊ ገራህት ከመ ይገፍትዕ ይፈቱ*
*ሕማም ሐራሲ ዘዕረፍት አልቦቱ ፤*
*ዋሕድ ዘርዕ እስመ ኢሠረፀ ሎቱ ።*

## ትርጉም

እረፍት የሌለው ሕማም/አራሽ
የገብረ ክርስቶስ እርሻ አካልን ሊገለብጥ ይወዳል ፤
አንድም ዘር አልበቀለለትምና ።

## ምስጢር

አራሽ ዘር የማታበቅል እርሻን ይገለብጣታል ። እንዲሁም የገብረ
ክርስቶስን አካል ደዌ ስጋ ገለባበጣት ። እርሻይቱ ዘርን እንደማታበቅል
የገብረ ክርስቶስም አካል ከሩካቤ ስጋ ተጠበቀች ። ትጉህ ገበሬ የግብርና
ስራን ከማከናወን እንደማያርፍ የገብረ ክርስቶስ ደዌ ከማቃጠል አል.ታገ



ሰለትም በማለት ባለቅኔው የገብረ ክርስቶስን ህማም ፅናት በቅኔያቸው
ምስጢር አስረድተዋል ።

288 ዘአምላኪየ ስ
*ዶርሆ ገብርኤል በዐቃቤ ሰዓት ውእቱ*
*ነቀወ እምድኅረ ጊዜሁ በሰዓት ሠለስቱ ፤*
*ሠናዩ ቃል እምጣነ ተውህበ ሎቱ ።*

## ትርጉም

ሰአት ጠባቂ የሆነ ዶሮ/ገብርኤል
ከጊዜው በሁዋላ በሶስት ሰአት ጮኸ ፤
መልካም ቃል ለእርሱ ተሰጥቶታልና ።

## ምስጢር

ዶሮ በሌሊት ከጮኸ በሁዋላ ከጧቱ በሶስት ሰአት ይጮኸል ።
"ሂድና የኢያቄምን ልጅ አብስራት" የተባለውን ያወቀ መልአኩ ቅዱስ
ገብርኤልም የእግዚአብሄር አብ ቃል እግዚአብሄር ወልድ በሶስት ሰአት
ከእርሷ እንዲፀነስ ማርያምን አበሰራት ይላሉ ባለቅኔው ።

*289 ዋዜማ ስ*
*ዘዮርጊ (አሊቃ)*
*ለአብ ኢነጸርዎ*
*ምሉዓነ ዐይን ኪሩቤል እንዘ ቅሩባን እሙንቱ ፤*
*አካሎሙ እስመ ይከድኑ በአክናፍ ስድስቱ ።*
*እስጢፋኖስሰ ርኁቅ በጸርየተ አሚን መጽሔቱ*
*ነጸረ አበ ምስለ ክልኤቱ ፤*
*እስመ ዐይኑ ሃይማኖት ውእቱ ።*

## ትርጉም

አይንን የተሞሉ
ኪሩቤል ቅርቦች ሲሆኑ አብን አላዩትም ፤



www.ethiopianorthodox.org

አካላቸውን በስድስት ክንፎች ይጋርዳሉና ።
የራቀ እስጢፋኖስ ግን በማመን /መስታዎቱ ጥራት
ከሁለቱ/ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አብን አየ ፤
አይኑ ሃይማኖት ነውና ።

## ምስጢር

"ልብ ካላየ አይን አያይም" እንዲሉ ብዙ አይን ያላቸው ኪሩቤል ለእግዚአብሄር አብ ቅርቦቹ ሲሆኑ በልባቸው ፍራት የተነሳ ፊታቸውን በክንፎቻቸው ይጋርዳሉ ፤ አብንና ወልድን መንፈስ ቅዱስንም ሊያዩ አይችሉም ። የራቀ ሰው ግን በመነፅር ከሩቅ ቦታ ያለውን እንደሚያይ እስጢፋኖስም በምድር ሆኖ እግዚአብሄር በሰማይ በዙፋኑ በኪሩቤል ላይ ሆኖ ሲመሰገን አየ ። የባለ መነፅር አይን በመነፅር ረዳትነት እንደሚያይም እስጢፋኖስ ከሃይማኖቱ ፅናት የተነሳ የሰማይን ምስጢር ለማየት ቻለ በማለት ባለቅኔው ቅኔያቸውን አመስጥረዋል ።

*290 ዋዜማ ስ*

*ዘምስራቅ (አለቃ ፡ ዘኤልሻማ)*

*ማዕበለ ክረምት መሀትም*
*በብዝኃ ግሣጼ አንሥአ አእባነ ላዕለ ወታሕቱ*
*ኀያል ማዕቀበ አልፋ ዘቆጽሮስ ቤቱ ፤*
*ብሂሎ ዘሞተ እስመ ዘለፎ ለዝንቱ ፡*
*ወፈቀደ ካዕበ በመንኖቱ*
*አነዳሁ ከመ ይንጽፍ ሎቱ ።*

## ትርጉም

የክረምት ማእበል /ቁጡ
በቁጣ ብዛት የላይና የታች ድንጋዮችን አነሳ ፡
ቆጵሮስ ቤቱ የሆነ ሃይለኛ ማእቀበ አልፋ
ይህን ቁጡ የሞተ ብሎ ሰድቦታልና ፤
በመናቁም ዳግመኛ ዳባውን
ሊያነጥፍለት ወዷልና ።



## ምስጢር

አንድ ሃይለኛ ሰው ሌላውን ቁጡ ሰው "የሞተ" ሲለውና ዳባውን በላዩ ላይ ሲጥልበት ቁጡ ሰው ሊመታው ድንጋዮችን ያነሳል ። በአንፃሩም በክረምት ዝናብ የተፈጠረ ማእበል ከላይና ከታች ድንጋዮችን እንደሚያገለባብጥ ኢትዮጵያዊው ፃድቅ አቡነ ኤዎስጣቴዎስም በኢያሪኮ ባህር ማእበል ላይ አፅፋቸውን ጭነው ባህሩን እንደ ሌለ አደረጉት በማለት ቅኔው ተመስጥሯል (ስንክ· መስከረም 18)

*291 ዋዜማ (443) ጎ*

*ለአዳም እብነ ገሊላ*
*ገቦሁ ኅቱም ወኢይትዐወቅ ስቁረቱ ፤*
*ሔዋን አርምሞ እስመ ወፅአት ቦቱ ፤*
*ወለእብነ ገዳም አዳም እንዘ እመሬት ፍጥረቱ*
*መንፈስ ሕይወት አኅደረ በውስቴቱ*
*ሆሳዕና ዘመሐለ ሎቱ ።*

## ትርጉም

የገሊላ ድንጋይ /አዳም
ጎኑ ግጥም ነው ፡ ቀዳዳውም አይታወቅም ፤
ሄዋን/ ዝምታ ወጥታበታለችና ።
የገዳም ድንጋይ/አዳምም ፍጥረቱ ከመሬት ሲሆን ፤
የማለለት እግዚአብሄር ሆሳእና
የህይወት መንፈስን በውስጡ አሳደረ ።

## ምስጢር

ከአዳም ጎን ሄዋን ስትፈጠር የተፈጠረችበት ጎኑ ድፍን ነው እንጂ ክፍት አልሆነም ። የሆሳእና ድንጋይም ዝምታ ስትለየው የተናገረበት አፍ አልተገኘም ። ደግሞ አዳም ከመሬት ሲፈጠር ፈጣሪው የህይወትን መንፈስ እንዳሳደረበት ሆሳእና የሚባል ክርስቶስ ግእዝ ፍጥረት የሆነ ድንጋይን በሰብአዊ መንፈስ አናገረው ይላሉ ባለቅኔው ።

*292 መወድስ (479) ጎ*

*ዘጎበዜ (አለቃ ፡ ዘደብረ ወርቅ)*

*ጌራ ወርቅ ድንግል ዘበርእሰ ዙሉ*



www.ethiopianorthodox.org

*አሐደ ረሰየት እንዘ ተዘምዶ አልቦቱ*
*መርዓዌ ወሊደ ምስለ ድንግልና መርዓቱ*
*ወተቃርቦ እንዘ አልቦሙ*
*መንግሥት ምስለ ተዋርዶ አንበረ በሞቱ*
*ወልደ አብ ዘባሕቲቱ*
*እንዘ ከመ እግዚእ በላዕሉ ወዘከመ ገብር በታሕቱ ።*
*ሰሎሞንሰ ዘተሰእኖ አሲረ ክልኤቱ*
*ሰኢለ ወውሂበ ኢያኀበረ በመንግሥቱ ፤*
*ኢዮብኒ ኀቡረ ኢረከቦሙ በቤቱ*
*ለንዴት ጊዜ ብዕሉ ወለብዕል ጊዜ ንዴቱ ።*

## ትርጉም

በሁሉ ራስ ላይ ያለች የወርቅ ዘውድ /ማርያም
መውለድ/ ወንድ ሙሽራን ከድንግልና/ቤት ሙሽራ ጋር
ዝምድና ሳይኖርበት አንድ አደረገች ።
መቃረብም ሳይኖራቸው
ብቸኛው የአብ ልጅ መንግስትን ከመዋረድ ጋር
በሞቱ አስቀመጠ ፤
በላይኛው እንደ ጌታ ሲሆንና በታችኛው እንዳገልጋይ
ሲሆን።
ሁለቱን አንድ ማድረግ የተሳነው ሰሎሞን ግን
መለመንንና መስጠትን በመንግስቱ አላስተባበረም ፤
ኢዮብም ችግርን በብልፅግናው ጊዜ
ብልፅግናንም በችግሩ ጊዜ በአንድነት በቤቱ አላገኛቸውም ።

## ምስጢር

ዘውድ በንጉስ ራስ ላይ እንደሚውል ቅድስት ማርያምም ከሁሉ በላይ ትከበራለች ታስከብራለችም ። እናት ወንድ ልጇን ሙሽራን እንደምታጋባው ቅድስት ማርያም እግዚአብሄር ወልድን መውለድን ከድንግልናት ጋር አስተባበረች ። በቅርብ የማይተዋወቁትን ሁለት ሰዎች አማካያቸው ወዳጅ እንደሚያስተዋውቃቸው የአብ የባህርይ ልጅ ቃል እግዚአብሄር ወልድ ከማርያም ከተወለደ በሁዋላ መንግስትንና ትህትናን በአንድነት ያዘ ። በሰውነቱ ሲሞት በመለኮቱ አለምን እንደያዘ ህያው ሆነ። ስለዚህ በአባቱ በእግዚአብሄር አብ በኩል በጌትነቱ ሳለ በእናቱ



በቅድስት ማርያም በኩል በአገልጋይነት ተመላለሰ ።

ሁለቱን ጠበኞች ሰዎች ማስታረቅ ያልቻለ ሰው እንደማያስተባብራቸው ሰሎሞንም መለመንንና መስጠትን በአንድነት አላገኘም ። በሰይጣን ተንኮል ከቤተ መንግስቱ ወጥቶ ሶስት ቀን ያህል በገዛ ከተማው ሲለምን ድህነት እንጂ ብልፅግና አልነበረውም ። ወደዙፋኑ በተመለሰ ጊዜ ግን ጌትነት እንጂ ድህነት አልተገኘበትም ። ሙቀትና ቅዝቃዜ አብረው እንደማይገኙ ኢዮብም በብልፅግናው ጊዜ የችግርን መኖር አላወቀም ፤ በሀብቱ ማለቅ ጊዜም በብልፅግና እንደኖረ አልተገነዘበም በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

ታሪኩ በአንደኛው መፅሃፍ በገጽ 369—370 ተተርኳል ።

*293 መወድስ (480) ጎ*

*ነበልባለ እሳት አብርሃም ለዘይኔጽሮ ፤*
*ዙሉ ዘመጽአ እስመ ይትዌከፍ ውእቱ ፤*
*ወአናግዲሁ ነዮሙ ሰብአ ነነዌ ለዝንቱ*
*እሉ ሰብአ ነነዌ*
*ከመ አናግድ እመ ተርፉ ቦቱ*
*ተወካፌ ነግድ ነበልባል*
*እስመ ዘሥጋ መብልዐ ኢሐለየ ለባሕቲቱ ።*
*ድኅረ ተርፉሂ ሰብአ ነነዌ ከመ ይጸንዕ ትሕርምቱ*
*ሠለስቱ አስተርአይዎ ለእሳት ውሳጤ ቤቱ*
*ወአመ እሳት ነጸረ ምጽአተ ሠለስቱ*
*ቀዲሐ ማየ ባሕር አስተፋጠነ ከመ ይሕፅቦሙ ለእሎንቱ ።*

## ትርጉም

አብርሃም ለሚመለከተው የእሳት ነበልባል ነው ፤
የመጣውን ሁሉ እርሱ ይቀበላልና ፤
ለዚሁም የነነዌ ሰዎች እንግዶቹ ናቸው ፤
እኒህ የነነዌ ሰዎች
እንደ እንግዶች ቢቀሩበት
እንግዳን ተቀባይ ነበልባል
የሲጋን መብል ለብቻው አላሰበምና ።
የነነዌም ሰዎች ከቀሩ በሁዋላ ለትህርምቱ (መከልከሉ) እንዲፀና



www.ethiopianorthodox.org

ሶስቱ እሳትን በቤቱ ውስጥ ታዩት ፤
እሳትም የሶስቱን አመጣጥ ባየ ጊዜ
እሊህን ያጥባቸው ዘንድ የባህርን ውሃ መቅዳትን እፋጠነ ።

## ምስጢር

አብርሃም ወደርሱ የሚመጣውን እንግዳ ሁሉ እንደሚቀበለው የእሳት ነበልባል በእምላክ ያመነውን ያሰቃያል ። አብርሃም እንግዶች ሲቀሩበት ጠሙን እንዳደረ እሳትም የነነዌን ሰዎች አላቃጠላቸውም ። በራብም እንዳይሞት ሰላሴ በእንግዶች አምሳል በአብርሃም ቤት አደሩ ። እሳትም የነነዌን ሰዎች ባያቃጥል ሶስቱ የመንግስት ልጆች (አናንያ ፡ አዛርያና ሚሳኤል) በባቢሎን በእሳት ውስጥ ተመላለሱ ። አብርሃም የስላሴን እግር ለማጠብ ውሃን እንዳቀረበ ሶስቱ የመንግስት ልጆች የተጣሉበት የባቢሎን እሳት እንደ ውሃ ቀዘቀዘ ይላሉ ባለቅኔው ።

*294 መወድስ (483) ጎ*
*እምከብካበ አዳም አትረፉ ስቴ ሆሣዕና*
*ወይነ ቤተ ቃና ጽሩየ እለ ከዐው በከንቱ ፤*
*እስመ ሆሣዕና አክበደ ጽድቀ ብሂሎቱ*
*ምናሴ ሀብተ ዚአየ*
*ወገለዓድ ከርቤ ዚአየ ውእቱ ፤*
*ዝኒ ጸዋዐ ሞቱ*
*እስከ የዓም ኢኀልቀ ፡ አምጣነ ምሉዕ ቅድሐቱ ።*
*እመሰ ለሆሣዕና አዋልደ እም ቦቱ*
*እምኢሞተ ሆሣዕና በገቢረ ሠናይ ኀጢአቱ ፤*
*በምክረ አዋልድ ሠላስ እስመ አምሰጡ ክልኤቱ*
*በርባን እማእሰሩ ወአልዓዛር እምግነዙ ።*

## ትርጉም

ጥሩ የቃና ቤት የወይን ጠጅን በብላሽ
ያፈሰሱ ሰዎች ከአዳም ሰርግ የሆሳእናን መጠጥ አተረፉ ፤
ምናሴ አሞት የእኔ ሀብት ነው
ገለአድ ከርቤም የእኔ ነው
የማለት እውነትን አክብዷልና ፤
ይህም የሞቱ ፅዋ



እስከዛሬ ድረስ አላለቀም ፤ ቅጁ ሙሉ ነውና ።
ለሆሳእና ግን የእናት ልጆች እኅቶች ቢኖሩት
ሆሳእና ሃጢአቱ በሆነ መልካምን በመስራት ባልሞተ ነበር ፤
በርባን ከማሰሪያ ፡ አልአዛርም ከመግነዙ
ሁለቱ በሶስት ሴቶች ልጆች ምክር አምልጠዋልና ።

## ምስጢር

የሰርጉን ቤት ወይን አደፋፍተው የጨረሱ አሳላፊዎች ከሰርጉ ባለቤት ደብቀው ለራሳቸው የሚሆን መጠጥ ያስቀራሉ ። በቃና ሰርግ ቤት በኢየሱስ ደገኛ ተአምር የተለወጠውን ወይን አይተው ያላመኑ አይሁድም አዳም ሊቀበለው የሚገባውን መከራ በሆሳእና (በክርስቶስ) ፈረዱበት ። የሰርጉ ባለቤት "በገዛ ዳቦዬ ልብ ልቡን አጣሁት" እንደሚል "ምናሴና ገለአድ የእኔ ናቸው" ያለው ሆሳእና የሚባል ክርስቶስ አሞትንና ከርቤን ጠጣ ። ባለ ሰርጉም መጠጡን ቅዳ እንዲል የክርስቶስም የግል አሟሟት በየጊዜው እርሱን በመሰሉ ተከታዮች ላይ ይፈፀማል ። "እገሌ እኮ ቢወልድ ኖሮ ስሙ ባልጠፋ ነበር" እንደሚባል የሆሳእና እናት ቅድስት ማርያም ከእርሱ በቀር ሌላ አልወለደችም ። ሃጢአተኛው በሃጢአት እንደሚሞት መልካም ስራው እንደ ሃጢአት ተቆጥሮበት ሆሳእናን ሰሞት አደረሰው ። እስረኞችም ከእስራት በወገን ምልጃ እንደሚድኑ ሆሳእናም ማርያና ማርታ በሚባሉ በእህቶቹ ልመና አልአዛርን ከመቃብር አስነሳው ። በርባንም በአንዲት ሴት ምክንያት ከእስራት ተፈታ ማለት በቅኔው ተገልጧል ።

*295 ማእዝ ጉባኤ ቃና /ስ*
*ዘክፍሌ ፈለቀ (አሊቃ)*
*ዮነዝን ስብአ ሞተ መክሊተ ገብር አሐቲ ፤*
*ለእማ ረባሕ አምጣነ አሐቲ ይእቲ ።*

## ትርጉም

ያንዲት ያገልጋይ ብር ሞት ሰውን ያሳዝናል ፤
ለእናቷ/ትርፍ አንዲት ናትና ።

## ምስጢር

ለእናቷ አንዲት የሆነች ልጅ ስትሞት ታሳዝናለች ። ለሰነፍ



www.ethiopianorthodox.org

አገልጋይ የተሰጠች ብርም አንዲት እንደሆነች ያለትርፍ ቀረች በማለት ባለቅኔው ያስረዳሉ (ማቴ· 25 ፥ 15 — 29) ።

*296 ግእዝ ጉባኤ ቃና /ስ*

*ክርሡ ለስምዖን ቤተ ክርስቲያን ይእቲ ፡*
*ብዙኃን ሰብእ አምጣነ ተቀብሩ ባቲ ።*

## ትርጉም

የስምኦን ሆድ ቤተ ክርስቲያን ናት ፤
ብዙ ሰዎች ተቀብረውባታልና ።

## ምስጢር

በቤተ ክርስቲያን ብዙ የሞቱ ሰዎች እንደሚቀበሩባት ስሞኦንም ብዙ ሰዎችን እየበላ በሆዱ ከተታቸው ይላሉ ባለቅኔው (ስንክ· የካቲት 16) ።

*297 ግእዝ ጉባኤ ቃና /ስ*
*በረከተ ኀጥአ ማእረረ ምናሴ ቀኖት ፤*
*አኮኑ አተወ በእዝነ ቁርቆስ መሥነቅት ።*

## ትርጉም

የምናሴ አዝመራ /ቸንካር በረከትን አጣ ፤
በቂርቆስ/ አቅማዳ ጆሮ ገብቷልና ።

## ምስጢር

ዘመኑ ዘመነ ድርቅ ይሆንና ምርት በጣም ሲያንስ ሰዎች "በአቅማዳ ጆሮ የገባ አዝመራ አይበረክትም" ይላሉ ። የእስራኤል ንጉስ ምናሴ የተቸነከረበት ችንካር በቂርቆስ ጆሮ ገባ በማለት ባለቅኔው በሰማእቱ ቂርቆስ የደረሰውን ስቃይ በንፅፅር ያስረዳሉ ።

*298 ግእዝ ጉባኤ ቃና /ስ*

*ኢየዐቁር እክለ ገብረ መንፈስ ቅዱስ መሥነቅት ፤*
*አኮኑ ተሠጠ በመንፈስ ቅዱስ መጥባሕት ።*



## ትርጉም

ገብረ መንፈስ ቀዱስ /አቅማዳ እህልን አይቋጥርም ፤
በመንፈስ ቅዱስ/ ካራ ተቀዷልና ።

## ምስጢር

በቢላዋ የተቀደደ አቅማዳ እህልን እንደማይቋጥር በመንፈስ ቅዱስ የታደሰ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እህልን ተወ በማለት ባለቅኔው አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ (አቦ) "የእናታቸውን ጡት አልጠቡም ፥ እህል አልበሉም፤ ውሃም አልጠጡም" ተብሎ በገድላቸው የተፃፈውን በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል ።

*299 ዘአምላኪየ /ስ*
*ዘገብረ ሥላሴ (መምህር ፥ ዘኤልያስ)*
*እስፍንተ ዕለተ ትጸውሪዮ ዓመት*
*ለወልድኪ ነቢየ ቴስብያ ዘአልቦ ዕረፍት ፤*
*እስመ ይብል ዘልፈ ኢይልክፈኒ መሬት ።*

## ትርጉም

አመት (አገልጋይ) እረፍት የሌለው የቴስብያ
ነቢይ /ልጅሽን ስንት ቀን ትሸከሚዋለሽ ?
ዘወትር መሬት አይንካኝ ይላልና ።

## ምስጢር

የአንዲት አገልጋይ( የቤት ሰራተኛ) ልጅ ህመምተኛ ይሆንና እያለቀሰ እናቱን አለቅም ብሎ ስራ አያሰራትም። ስለዚህ ችግሯን የተመለከተ ሰው " እገሊት ይህን ልጅሽን ስንት ቀን አዝለሽ ትዘልቂያለሽ?! ዘወትር ከጀርባሽ አይወርድም፤ መሬት አይንካኝ ይላል" በማለት ያዋያታል። ዘመንም ነቢዩ ኤልያስን በህይወት ታሸጋግረዋለች፤ ሞትም የለበትም በማለት ባለቅኔው አስረድተዋል።

*300 ሚበዝኑ /ስ*
*ምኩራበ ቅድምና ክርስቶስ*
*ምዑዘ ተሐንጸ በደብር መስቀለ ሮምያ ዕፍረት*
*ወጥሉለ ከዊን ማኅደር ለነግደ መከራ ሐረገ ዘይት*
*ናሁ ተነሥተ ማዕከለ አእላፍ ሕዝብ በነፋስ ኀዒን ቀኖት።*



www.ethiopianorthodox.org

## ትርጉም

በሮሜ/መስቀል ተራራ ላይ
መታነፅ/ሽቶው የጣፈጠ፣ ለመከራ እንግዳ ማደሪያን
መሆን/የዘይቱ ሃረግም የለመለመ የቀድሞ ቤት/ክርስቶስ
በእልፍ ሕዝብ መካከል በብረት ነፋስ/ችንካር አሁን ፈረሰ።

## ምስጢር

ሽቶ ከሩቅ እንደሚሸትና በተራራ ላይ የተሰራ ቤት ከሩቅ እንደሚታይ ክርስቶስም በሮም መስቀል ላይ መሰቀሉ ተሰበከለት። ዘይት የሚባል ተክል ሐረግ ሲለመልም ብዙ ቅጠልን እንደሚሸከም ክርስቶስም ብዙ መከራን ተቀበለ። የሰዎች መኖሪያ ቤትም በነፋስ ሃይል እንደሚፈርስ ክርስቶስም በአይሁድ ፊት በብረት ችንካር ተቸነከረ በማለት ቅኔው ተመስጥሯል።

*301 ዋዜማ*
*ዘአፈ ወርቅ ትኩየ(መሪጌታ፣ ዘሰይፋጥራ ማርያም)*

*አልዓዛር ዘይንዕሶ*
*አመ ገደፎ መሬተ ለዕፄ መቃብር ትሑት*
*ይብል ዕፄ መቃብር ይኄይስ መዊት*
*ወይቤ ዮሐንስ እምነ መዊት ሕይወት*
*እስመ ሥጋ ድንግል ካህን ምሉዐ ፍርሃት*
*ይከውና ለእሙ ገነት።*

## ትርጉም

ትሁት የሆነ የመቃብር ትልን
ታናሹ አልአዛር ከመሬት ላይ በጣለው ጊዜ
የመቃብር ትል መሞት ይሻላል አለ፤
ዮሃንስ ግን ከመሞት ህይወት ይሻላል አለ፤
ፍርሃትን የተሞላ ካህን/የድንግል ስጋ
ለእናቱ/ገነት ይሆናልና።



## ምስጢር

ከአንድ አባትና እናት የተወለዱ ወንድማማቾች ጕረምሶች በተጣሉ ጊዜ ታናሹ ከታላቁ በጉልበት ያይልና ታላቅ ወንድሙን ወደላይ አንስቶ ከመሬት አውርዶ ይጥለዋል። ይህን ሁኔታ ከተመለከቱት ጓደኞቻቸው መካከልም አንዱ " ታናሽ ወንድሜ ከሚያሸንፈኝ ሞት ይሻለኛል" ሲል፣ ሌላው ደግሞ በበኩሉ" አባቶች እንዳሉት ከመሞት መሰንበት ይሻላል፤ ፈሪ ለእናቱ ደፋር ለሞቱ የተባለውን አልሰማህም? " ይለዋል። በአራተኛው ቀን በክርስቶስ ኃይል ተነሳ የሚባለው አልአዛር ከመቃብር ውስጥ በመታጣቱ የመቃብር ትል የሚበላው አጥቶ በራብ ሞተ። እንደሃዋርያው እንደ ቅዱስ ዮሃንስ በድን ሳይቀበር የቀረ የቅድስት ማርያም በድንም የመቃብር ትል ሳይበላው ገነት ገባ ይላሉ ባለቅኔው (ስንክ·ጥር፡21)።

*302 ሥላሴ(576)ኀ*
*ዘዘዮሐንስ(አለቃ)*

*አብ እምደመናሁ*
*ቃሎ በታቦር እመ ወሀበ*
*እንዘ ተአምሮ ለወልድ ቀዳሚ በደብረ ሲና ቅድስት*
*ነግደ ታቦር ሙሴ አፍርሀከ ምንት?*
*ለእመ ደንገጸ ጴጥሮስ ባሕቱ በሰሚዐ ቃሉ ግርምት*
*አልቦቱ ለጴጥሮስ ግብረ ሐሜት፡*
*እኮኑ ያፈርህ ገጸ መለኮት*
*ወልማዱ ላጴጥሮስ ፍርሀት።*

## ትርጉም

አባት ከደመናው
ቃሉን በታቦር በሰጠ ጊዜ
ወልድን ቀድሞ በደብረ ሲና ስታውቀው
የታቦር እንግዳ ሙሴ! ምን አስፈራህ?
ጴጥሮስ ግን አሰፈሪ ቃሉን በመስማት ቢደነግጥ
ለጴጥሮስ የሃሜት ስራ የለበትም፤
የመለኮት ፊት ያስፈራልና፣
ለጴጥሮስም ፍርሃት ልማዱ ነውና።



www.ethiopianorthodox.org

## ምስጢር

አንድ ሰው ቀደም ሲል የሚያውቀውን ወዳጁን ቢያየው ይደሰታል እንጂ አይፈራም፣ አይደነግጥም። ነቢይ ሙሴ ሰባት የእሳት መጋረጃ በተጋረደበት በደብረ ሲና አምላክን ባየው ጊዜ ቢፈራ አይፈረድበትም ነበር። ነገር ግን ያን ጊዜ ያልፈራ በደብረ ታቦር የደመና ድምፅን ቢሰማ መሸሹ ምን አይቶ ይሆን! እግዚአብሄር ወልድ እንደሆነ ያው በደብረ ሲና ያየው ነው። ይልቁንስ የሚያስፈራው ዘመዱ የሆነበትን ስጋን ሳይለብስ በእሳት መጋረጃ ውስጥ ሲታይ ነበር። ጴጥሮስ ግን ቢፈራ በደብረ ታቦር ያየውን እግዚአብሄር ወልድን በደብረ ሲና አላየውምና ፍርድ የለበትም በማለት ባለቅኔው በደብረ ሲናና በደብረ ታቦር በተለያየ ጊዜ ተገልጧል የሚባለውን የመለኮት ምስጢር ታሪክ በቅኔያቸው አስረድተዋል።

*303 መወድስ /ስ*

*ፍትሐ ሆሣእና ይደሉ ለዘተዋረደ፤*
*እመ ከመዝሰ ኮነ ንጻሬ ንጹሕ መጽሔት*
*እምተንሥአ ሊተ ሀብተ ብዕልየ ምውት፤*
*ዘምሰለ ዕዋላ አኮኑ ዕድግት*
*ሀብታተ ኪሩቤል ወሰደት*
*እንዘ ትብል ኪሩቤል የዐብዩኒ በምንት።*
*እብንሂ ዘመነንዎ ሕዝበ ሆሣዕና ነደቅት*
*ኮነ ለዝማሬ ውስተ ርእሰ አይሁድ መአዝንት፤*
*ወይብልዎ ለእብን እለ በጥቃሁ አርድእት*
*ዘምር በመጠን ከመ ኢይዘንግዑ መላእክት።*

## ትርጉም

የሆሳእና ፍርድ ለተዋረደ ያደላል፤
የንፁህ መስታዎት ምልከታስ እንደዚህ ከሆነ
የብልፅግና ሀብት ሙት በተነሳልኝ ነበር፤
አህያ ከነውርንጫዋ
ኪሩቤል በምን ይበልጡኛል እያለች
የኪሩቤልን ስጦታዎች ወሰዳለችና።
የሆሳእና ሕዝብ/ገንቢዎች የናቁት ድንጋይም
ለምስጋና በአይሁድ/ማእዘኖች ራስ ሆነ፤
በአጠገቡ ያሉት ሃዋርያትም መላእክት
እንዳይዘነጉ ድንጋይን በልክ ዘምር አሉት።

## ምስጢር

አንድ እቃ በሚዛን ሲመዘን አንደኛው የሚዛን ክፍል ወደላይ ከፍ ሲል ሌላው ክፍል ወደታች እንደሚመዝን ሁሉ የሆሳእና ፍርድ ዝቅተኞችን ከፍ ያደርጋል። ስለዚህም የሞተ ሰው አልአዛር በተአምር ከመቃብር ተነሳ እንደሚባል የተቀበረው ሃብታቸው(እድላቸው)እንደሚ ቃና ባለቅኔው ገልጠዋል። መልካም አገልጋይ የጌታውን ሃብት እንደሚወ ርስ ወደኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ የገባች አህያም ከነውርንጫዋ እንደኪ ሩቤል አምላክን ተሸከመች። ስለዚህም ኪሩቤል በምንም አልበለጧ ትም። በመናገር እንዳይበልጧት የበለአም አህያ የቅዱስ ሚካኤልን ግርማ ተናግራለች። የተናቀ ሰው በሹመት ከበላዮቹ በላይ እንደሚሆን እንዲ ሁም አእምሮ ግእዛን (እውቀት፣ የማሰብ ችሎታ) ካላቸው ከአይሁድ በልጦ አእምሮ ግእዛን የሌለው ድንጋይ የኢየሱስ ክርስቶስን መድሃኒት "ሆሳእና" በማለት እየጮኸ ተናገረ። ድምፃዊ የሆነ ባለሙያ ሲያዜም አድማጮቹን እንደሚያስደንቃቸው የድንጋይም ነገር ሃዋርያትንና መላእ ክትን አስገረማቸው በማለት ባለቅኔው ኢየሱስ ክርስቶስ በእናቲቱ አህያና በውርንጫዋ ላይ ተራ በተራ እየተቀመጠ ወደቤተ መቅደስ በገባ ጊዜ ተፈፅሟል የሚባለውን በቅኔያቸው ተርከዋል (ዘሁል·22፥28። ማቴ·21፥9--15)።

*304 መወድስ/ስ*

*ዘተሰማ(አለቃ፡ዘቀራንዮ)*

*ሐመልማላዊት ገነት ደብረ ቀራንዮ*
*ታዘነግዕ ልበ በመዓዛሃ ሥርዓት፤*
*እመ ኢበቊለ ባቲ ሦከ አልዓዛር ንዴት*
*ወተከሥተ በውስቴታ*





www.ethiopianorthodox.org

*ለአብርሃም እንተ ኢመነኖ መልከ ጼዴቅ ሀብት፤*
*እመ ነሐትታ ሰብአ ትፍሥሕት*
*ዘአሰረነ ኢንሑር ፍቅረ ዚአሃ መሥገርት።*
*አእመርናሂ ከመ ሀሎ በቀራንዮ ገነት*
*ያሬድ ዘወለዶ ሄኖክ ማኅሌት፤*
*እስመ ለጥበብ አድለው እምነ ኃላፌ ንብረት*
*እለ ዘአዕናቍ ተመሰሉ መዘምራኒሃ ሐዋርያት።*

## ትርጉም

የልምላሜ ቦታ የሆነች ገነት/የቀራንዮ ደብር
በመአዛዋ/ስርአት ልብን ታዘነጋለች፤
እንዳንሄድ የእርሷ/ፍቅር ወጥመድ
ያሰረን የደስታ
ለዎችም ብንመረምር አብርሃምን
ያልናቀው መልከ ጼዴቅ/
ሃብት በውስጧ ተገለጠ(ተገኘ)።
ያሬድ የወለደው ሄኖክ/ማህሌትም
በቀራንዮ/ገነት እንዳለ አወቅን፤
በእንቁዎች የተመሰሉ ዘማሪዎቿ/ሃዋርያት
ከአላፊ ንብረት ይልቅ ለጥበብ አድልተዋልና።

## ምስጢር

መልካም መአዛ ያላት የአትክልት ቦታ በመዓዛዋ ልብን ትመስጣለች። የቀራንዮ መድሃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያንም በስነ ስርአቷ ልብን ታስደስታለች። እሾህም ያልበቀለባት ምድር ገበሬዋን እንደማታስቸግር የቀራንዮ መድሃኔ አለም ደብርም ችግር ስለሌለባት አገልጋዮዋን አታሳዝንም። መልከ ጼዴቅም ለአብርሃም እንደተገለጠለት(ወይንና ኅብስትን ይዞ አብርሃምን እንደተቀበለው) ሀብት በውስጧ ይስጣል። ወጥመድም እግርን ይዞ እንደማያስሄድ የቀራንዮ ደብር ፍቅር ወደሌላ አያስመኝም ።



የመላልኤል ልጅ ያሬድ የወለደው ሄኖክም በገነት እንደተሰወረ ኢትዮጵያዊው ያሬድም የደረሰው ማህሌት በቀራንዮ ደብር ይደምቃል። ሃዋርያትም ከስጋዊ ንብረት ይልቅ ለመንፈሳዊ ፀጋ እንዳደሉ የቀራንዮ ካህናት እንደእንቍ እያበሩ በመንፈስ ተመስጡ ይላሉ ባለቅኔው።

## ታሪክ

መልከ ጼዴቅ በአብርሃም ዘመን የኖረ ንጉስ ሳሌም(የሰላም ንጉስ) ነበር። መልከ ጼዴቅ ማለት የፅድቅ ንጉስ ማለት ነው። መልከ ጼዴቅ የእግዚአብሄር ካህን በመሆኑ ክህነቱ ከነቢዩ ሙሴ ወንድም ከአሮን ክህነት እንደሚበልጥ ተገልጧል።

አብርሃም ነገስተ ኮሎዶጎሞርን( የኮሎዶጎሞርን ነገስታት) ወግቶ፤ በወርነት ድል አድርጎ ሲመለስ መልከ ጼዴቅ ህብስትንና ወይንን ይዞ ተቀበለው፤ ባረከው። አብርሃምም ከሃብቱ ሁሉ አስራትን(ከአስር አንድ) ሰጠው (ዘፍጥ·14፡18 20። እብ 5—7)።

ሄኖክ በትውልድ ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ ሰው ነው። ሄኖክ በእግዚአብሄር በማመኑና ትእዛዛቱን በመጠበቁ እግዚአብሄርን ደስ አሰኘ። ከዚህም የተነሳ ሄኖክ ስጋዊ ሞትን አልሞተም። በህይወቱ እንዳለ እግዚአብሄር ወሰደው ተብሎ ይተረካል። ሄኖክ ስለ ፀሃይና ጨረቃ ኡደት(አዚዚር) የሚተርክ መጽሃፍ ጽፏል። ይህም መጽሃፍ በደራሲው ስም ሄኖክ በመባል ይታወቃል (ዘፍጥ።5፡21—24። ሄኖክ 1፡9። እብ·11፡15። ይሁዳ14)።

*305 መወድስ/ስ*
*ዘሀስራት(ድማኅ ገነት ፡ ዘኤልያስ)*
*በላዒ እሳት ዕጓለ አንበሳ*
*አመ ርኅበ ነግሀ ዘእምአከዓብ መሥዋዕት*
*ለበሊዐ ሥጋ ይጥሕር ቅድመ ኤልያስ ዳዊት*
*ዘለመደ ሥጋ አርዌ ምድር እሳት፤*
*እስመ ሠርከ ተውህበት*
*ለካልአ ሕግ ኤልያስ መሥዋዕተ አቤል መንግሥት።*



www.ethiopianorthodox.org

*ዕርገትሂ ጽዋሀ ዕዝራ እመ ተቀድሐት*
*ለኤልያስ ጸውዕዎ መገብተ መዋዕል ሠረገላት፤*
*አኮኑ ይትሜጦ ጽዋዐ ሕይወት*
*ለኤልያስ እንተ ዖደ አድኃመ ዮርዳኖስ ደብረ ገነት።*

## ትርጉም

በላተኛ እሳት/የአንበሳ ልጅ
ከአክአብ መስዋእት በጢት በተራበ ጊዜ
ስጋን የለመደ የምድር አውሬ/እሳት
በኤልያስ/ዳዊት ፊት ስጋን ለመብላት ይጮኽል(ያገሳል)፤
የአቤል መስዋእት/መንግስት
ለህግ ሁለተኛ ኤልያስ በሰርክ ተሰጥታለችና።
የእዝራ ፅዋ/እርገትም በተቀዳች ጊዜ
የዘመን መጋቢዎች/ሰረገሎች ኤልያስን ጠሩት፤
የዮርዳኖስ/ደብረ ገነት ዙሪያን
ለዞረ ኤልያስ የህይወት ፅዋ ይሰጣልና

## ምስጢር

አንበሳ በጢት ሲራብ መብላት መፈለጉን በጩኸት ይገልጣል። እሳትም የአክአብን መስዋእት ትቶ የኤልያስን መስዋእት አቃጠለ። ግማሽ ቀን የነገሰ የእስራኤል ንጉስ የዳዊት ልጅ የአዶንያስ መንግስትም በሰርክ (ወደማታ) ለሌላው ልጁ ለሰሎሞን እንደተሰጠች የኤልያስ መስዋእት የአቤል መስዋእት በሰርክ ጊዜ አረገች። የማህበር ፅዋ በተራው የሚሰጠው ማህበርተኛን የማህበሩ ሙሴ ወይም ባለማህበሩ ፅዋውን አንስቶ " ማን ነህ ባለሳምንት?" እንደሚለው የእሳት ሰረገሎችም በህይወት መኖር ወዳለበት( ሞት ወደሌለበት) ገነት ኤልያስን አወጡት። መጥምቁ ዮሃንስም የዮርዳኖስን ዙሪያ እየዞረ እንደሰበከ ነቢዩ ኤልያስ በጎጃም ክፍለ ሀገር በሚገኘው በደብረ ገነት ተመስገን በማለት ባለቅኔው አመስጥረዋል።

*306 መወድስ(1066)ኀ*
*ተፈጸመ ቅብዐ ዘመነ ሥጋዌ*



*እንዘ እቴሁና ታገምር በበሠለስቱ መሥፈርት*
*ወተረፈ ሥጋ ትበልዕ ውሳጤ ግሩም ማጀት፤*
*አኮኑ ኢመጽአ አላምነህ ገብሩ*
*እምነ ሀገሩ ለንጉሥ ዳዊት፤*
*ዘኒ ከመ ይክሥት*
*ሃይማኖተ ገብሩ ድልሀ ተዋሐደ ምስለ ቅብዐት።*
*ዮሐንስሂ እደ ዚአሃ ሰባኬ ድልሀ ጥምቀት፤*
*በቅቤ ወበድልሀ አምጣነ ይሠረይ ኀጢአት፤*
*ወእመ እዴሃ የዐርግ ላዕለ ደብረ ኤልያስ ዘይት*
*ምንት ሥላጤሃ ለቅቤ ሕገ ግዝረት?*

## ትርጉም

እቴሁና ሶስት ሶስት መስፈሪያ እየቻለች
የስጋንም ትራፊ በሚያስገርም ማጀት እየበላች
የስጋ ዘመን/ ቅቤ ተፈፀመ(አለቀ)፤
ከንጉስ ዳዊት አገር
አላምነህ ገብሩ እልመጣምና።
ይህንንም ይገልጥ ዘንድ
የገብሩ ሃይማኖት/ድልህ ከቅባት ጋር ተዋሃደ።
ዮሃንስ የእርሷ እጅም ድልህ/ ጥምቀትን ሰባኪ ሆነ፤
በቅቤና በድልህ ሃጢአት ይሰረያልና፤
እጅዋም በዘይት/ኤልያስ ተራራ ላይ በወጣ ጊዜ
የቅቤ/የመገረዝ ህግ ጉዳይን መፈፀም ምንድር ነው?

## ምስጢር

ወልድ ሰው በመሆኑ ስጋን የመልበስ ዘመን እንደተፈፀመ በስጋ የሚበላ ቅቤ በእቴሁና ሶስት ሶስት ጊዜ በቀን እተየተበላ አለቀ። የእንግዶችንም ትራፊ እቴሁና ባልዋ አላምነህ ገብሩ ሳይመጣባት በማጀት ተደብቃ በልታ ጨረሰችው። ያንዳንድ ሰዎች ሃይማኖት ቅባት እንደሆነ እንዲሁም ያላምነህ ገብሩ ድልህ ከቅቤ ጋር ይዋሃዳል። ዮሃንስም የክርስቶስን ጥምቀት እንደሰበከ የእቴሁናም እጅ ድልሁን በቅቤ ያዋህ



www.ethiopianorthodox.org

ዳል። በፆምና በፀሎት ሃጢአት እንደሚሰረይ የተዋሃደው ቅቤና ድልህም እየተበላ ግብረ ስጋ ይፈፀምበታል። ከረጅም ተራራ ላይ ሆኖ ከታቹ ያለውን ሲመለከቱት ትልቁ ነገር ጥቃቅን መስሎ እንደሚታይ፡ ለፆም ጊዜ የታዘዘውን ዘይቱን የእቴሁና እጅ አዘጋጀ። የወንጌል ህግ ከተሰበከ በሁዋላ የኦሪት ህግ ጉዳይ እንደማትፈፀም በፆም ጊዜም ቅቤ እንዳልተበላች ሆነች ይላሉ ባለቅኔው።

*307 መወድስ(596)ኀ*

*ዘግእዛን(ቄስ ገበዝ)*

*ጊዮርጊስ ግዮን ፈለገ ሐሊብ!*

*ከመ ሕንጻ ደቂቅ ኮነ ሕንጸ አካልከ ቤት፤*

*እስመ ተማሰጠ ነፋስ ኀላፊ ፍኖት*

*ወሥልስ ጊዜያተ*

*አግብአት ቃላ ኀበ ኖኀ ሞት*

*ርግብ ስጋ ዚአከ*

*ለመንግስትከ ሥቃይ እስመ አልባቲ ኀልፈት።*

*ለርእስከኺ ንጉሠ ገድል ዕለተ መርዓሁ ምትረት*

*አስተቀጸለቶ በአክሊል እምከ ሃይማኖት፤*

*እስመ ክሣድከ ዮሴፍ ሥርግወ ተመትሮ ሜላት*

*ኢፈርሀ ነሚአታ ለድንግል ሰይፈ እሳት።*

## ትርጉም

የወተት ወንዝ ጊዮርጊስ/ግዮን!

የአካልህ/ ቤት ህንፃ እንደልጆች ካብ ሆነ፤

መንገደኛ /ነፋስ ተ' ጣጥቆታልና።

ርግብ/ያንተ ስጋም

በሶስት ጊዜዎች ወደኖህ/ሞት

ቃሏን አገባች(መለሰች)፤

ለመንግስትህ/ስቃይ እልፈት የለውምና

የግድያ ንጉስ/ራስህንም በሰርጉ/ መቆረጥ ቀን

እናትህ/ሃይማኖት አክሊልን አቀዳጀችው፤



መቆረጥ/ሃርን የተሸለመ አንገትህ/ዮሴፍ

ድንግል/የእሳት ሰይፍን መውሰድን አልፈራምና።

## ምስጢር

ግዮን የወተት ወንዝ እንደሆነ ጊዮርጊስም ከአንገቱ ቁራጭ ወተትን አፈሰሰ። ልጆች በጨዋታ ጊዜ የሚክቡት ካብ ወዲያውኑ እንደሚፈርስ የጊዮርጊስ አካልም እንደ ጥጥ ባዘተ። የመንገድ ዳር እሸትን ከየማእዘኑ የሚመጣው መንገደኛ እንደሚነጣጠቀው የጊዮርጊስን አጥንት ነፋስ በተነው። ርግብም ሶስት ጊዜ የጥፋት ውሃን ሁኔታ ለኖህ እንደነገረች የጊዮርጊስ ስጋም ሶስት ጊዜ ሞተ። የእምላክ መንግስት እልፈት እንደሌለው የጊዮርጊስ ስቃይም በረከተ። ሰሎሞንን በንግስናው ቀን እናቱ የወርቅ አክሊልን ሃይማኖትም ለጊዮርጊስ በመቆረጡ ቀን የሀጋና የክብር አክሊልን አወረደችለት። ሃርን የተሸለመ ዮሴፍ ቅድስት ማርያ ምን ወደህዝብ ቆጠራ ይዞ መሄድን እንዳልፈራ የጊዮርጊስ አንገትም የእሳት ሰይፍን ተቀበለ(እንደ እሳት በሚያቃጥል ሰይፍ ተቆረጠ)ይላሉ ባለቅኔው( ገድለ ጊዮርጊስ)።

*308 መወድስ(601)ኀ*

*ስሕተኒ አዕርፍ እምፃማ ተፈጥሮ*

*እንበለ እሑር ገብርከ ኀበ ዘኢይገብእ ሞት*

*ኦስዱቅ በኮለ ምሕረት!*

*እስመ አንተ ለሐዞሁ*

*አምልሕዞት ሥጋ ለሥጋ ልሕዞት*

*እግዚአብሔር ከመ ምጣሕት*

*ዘትዌልጦ ለዙሉ ወትሬስዮ ከመ ትካት።*

*እመኒ ኀጣውእየ አድባረ ሐፂን ወብርት*

*መጠነ አሐቲ ኅጠተ ሆፃ በቅድመ ዐይንከ መሐሪት፤*

*ወከመ ኢይበልከ አንሰ ክቡደ ቀኖና መዝራእት*

*ፈተንኩከ በምናሴ ወአመከርኩከ በዳዊት።*

## ትርጉም

በሎሚ/ምህረት የተኮላሀ



www.ethiopianorthodox.org

ሁሉን እንደመጋረጃ የምትሰውጥና እንደድሮው
የምታደርገው እግዚአብሄር!
እኔ ወደማልመለስበት ሳልሄድ ከተፈጥሮ ድካም
አርፍ ዘንድ/አሳርፈኝ/፤
ሸክላ/ስጋን ከሸክላ ስጋ የሰራኸው አንተ ነህና።
ሃጢአቶቼም የብረትና የናስ ተራራዎች ቢሆኑ
በይቅር ባይ እይንህ ፊት እንዲት የእሸዋ ቅንጣት ያህል ናቸው፤
እኔም ቀኖና/ክንድህን ያከበድህ ነህ እንዳልልህ
በምናሴ ፈትኜሃለሁ፤ በዳዊትም ሞክሬሃለሁ።

## ምስጢር

እነሆ ቀለበትና መስቀል አንባርም ተሰርተው በሎሚ ውሃ እንደሚ ኮሉ እግዚአብሄርም በትዕግስት የታመነ ነው። መጋረጃም በመጠቅለያው እንደሚጠቀለል እምላክም ሰውን ሁሉ በሞት ሰውጦ ሲያበቃ በትንሳኤ እንደነበረ ያደርገዋል። ሸክላ ሰሪ ከአፈር የሰራውን ሸክላ ከስክሶ እንደገና አዲስ የሸክላ እቃ እድርጎ እንደሚሰራው አምላክም ሰውን ከመሬት ፈጥሮታል። ከሞትም በሁዋላ አስነስቶ ያኖረዋል። ብረቶችና ናሶች ቢጠራቀሙም በመዶሻ እንደሚቀጠቀጡና እንደሚጠቀለሉ የሰው ሃጢአ ቶችም ቢበረክቱ በአምላክ ይቅርታ ይደመሰሳሉ። ክንደ ከባድ( ሃይለኛ፣ ጉልበታም) ሰው በክንዱ እንደሚያደቅ እምላክ ብዙ ቀኖናን(የቅጣት ህግን) ይሻል አይባልም። ክንደ ቀላል ሰው ቢማታም እንደማይጎዳ አምላክም ብዙውን የእስራኤል ነገስታት የነበሩ የምናሴንና የዳዊትን ሃጢአት አቃለሰው በማለት የአምላክን ይቅር ባይነትና የሰውን ሃጢአተኛ ነት በቅኔያቸው ምስጢር አስገንዝበዋል።

## ታሪክ

ምናሴ የእስራኤል ንጉስ የነበረው የህዝቅያስ ልጅ ነው። በአስራ ሁለት አመቱ ነግሶ በአባቱ ዙፋን ተተካ። ጣኦታትን በማምለኩ እግዚአብሄር ተቆጣ። የአሶርንም ንጉስ አስነስቶ አስማረከው። ምናሴም ተማርኮ በሄደበት በባቢሎን ንስሃ ገባ፤ ፀለየም። እግዚአብሄርም የንስሃ ውን ፀሎት ተቀብሎ ይቅርታ አደረገለት። ወደኢየሩሳሌምም ተመልሶ



በዙፋኑ ላይ ተቀመጠ ተብሎ ተፅፏል።(2ነገስ·21፡1—18። 2 ዜና – 33፡1—20)።

*309 መወድስ(606)ጎ*

*ማርያም ደከምኪ ድካመ ባሕርዩ*
*ለመልአክ ሰማይ ገብርኤል ሐዋርያ ርኑቅ ፍኖት*
*በውደተ ሀገር ስፉሕ ንጽሐ መንፈስ ቅዱስ እሳት*
*እምድካመ ሥጋ ዘአቡኪ ርስት*
*ድኅረ ሐወፁኪ መላእክት*
*ወአንበሩኪ ፍጹመ ማእከለ ንጽሕና ገነት።*
*ከመሂ ኢትባኢ ጊዜ ተመስሎ ምሴት*
*ምስሰ አንስተ ቤቴል ወገሊላ አብያተ ካልኣን ምሳሌያት*
*ከልዐኪ አሮን በበትረ እዴሁ ጥልልት*
*ወሕዝቅኤል ጽባሐዊ አቀመኪ በኆኅት።*

## ትርጉም

ከአባትሽ ርስት/የስጋ ድካም ወጥተሽ
የእሳት/መንፈስ ቅዱስ ንጽህና/ሰፊ አገርን በመዞር
የሩቅ መንገድ ሂያጅ/ የሰማይ መልእከተኛ የሆነ የገብርኤልን
የባህርዩ ድካምን ማርያም! ደከምሽ፤
መላእክት ከጎበኙሽና
በንፅህና/ገነት መካከል በፍፁም ከእኖሩሽ በሁዋላ።
በመመሰል/ምሽት ጊዜም ከቤቴልና ከገሊላ ሴቶች ጋር
አብረሽ ወደሌሎች ምሳሌዎች/ቤቶች እንዳትገቢ
አሮን በለመለመች በእጁ በትር ከለከለሽ፤
የምስራቅ ሰው ህዝቅኤልም በደጃፍ አቆመሽ።

## ምስጢር

ስደተኛ ከአባቷ ርስት ወጥታ ከአገር ወዳገር ስትዞር ሌላው መንገደኛ የሚደክመውን ድካም ትደክማለች። ቅድስት ማርያም እንደእ ናቷ የወንድ ዘርን ተቀብሎ ከመፅነስና ከመውለድ ልማድ ራቀች፤ በመንፈስ ቅዱስ መንፃትን ገንዘብ አደረገች። ግን ስደተኛዋን ሴት አንድ



www.ethiopianorthodox.org

ደግ ሰው ወደቤቱ እንደሚያስገባትና ከድካም እንደምታርፍ ማርያምም በመላእክት ንፅህና ፀናች፤ የመልአኩ የቅዱስ ገብርኤልን የባህርይ ፀጋ አገኘች። ደግሞ ስደተኛዋ ቀኑ ሲመሽ" የእግዚአብሄር እንግዳ" ብላ መጠጊያ በመለመን በሌሎች ሰዎች ቤቶች እንዳታድር አንዱ ዘበኛ በበትሩ ይከለክላታል፤ ሌላውም በደጃፍ ያቆማታል።

የሙሴ ወንድም የካህኑ የአሮን በትር ከሌሎች ሰዎች በትሮች እንደተለየች ማርያምም በመመሰል ጊዜ በሌሎች ሴቶች አትመሰልም። የአሮን በትር ያለምንም ምክንያት(ያለውሃና ያለአፈር)አፍርታ እንደተገኘች ማርያምም ያለወንድ ዘር ምክንያትነት አምላክን በስጋ ወለደችው።። ነቢዩ ህዝቅኤልም በራእዩ ባያት ዝግ በሆነች ደጃፍ ከአንድ የሃያላን ጌታ ከእግዚአብሄር በቀር ማንም እንዳልገባና እዳልወጣ፣ በማርያም ማህፀንም ከእግዚአብሄር ቃል በቀር የተፀነሰና የተወለደ ሌላ የለም በማለት ባለቅኔው ስለቅድስት ማርያም ንፅህናና ቅድስና ያላቸውን እምነት በቅኔያቸው ገልጠዋል(ዘሁል·17)።

*310 መወድስ/ስ*

*ዘጥሩነህ(አለቃ፥ ዘቦታ ኪዳነ ምህረት)*

*በይምን ወፅግም እለ ይቀውሙ*
*ቅውማኒሃ ለገጽ አዕይንተ ባሕታዊ ካህናት*
*ለአስተሐዝሎ አንብዐ መዝሙረ ዳዊት፥*
*አብጽሐ ሎቱ ለብርሃን ምውት*
*ቀዊሞሙ በመቅበርት*
*ጸሎተ ዳዊት አንብዐ ዘየአምርዎ ሕፃናት።*
*ወሰዳሂ በአደንግፆ ለልበ ባሕታዊ ሕምምት*
*ለአውፅኦ ነፍስ እንተ መጽአ ረኃበ ሥጋ መልአከ ሞት፥*
*ወእስከ አውረዳ ዳግመ ውስተ መቃብራ ድክመት፥*
*እምነ መቃብር ኢተሌለዩ መላእከተ ብርሃን አዕይንት።*

## ትርጉም

የዳዊት መዝሙር/እንባን
ለማስተዛዘል በቀኝና በግራ የሚቆሙ
የገፅ ቋሚዎች የባህታዊ አይኖች/ካህናት
በመቃብር ቆመው
ካህናት የሚያውቁት
የዳዊት ፀሎት/እንባን ለብርሃን/ሟች አደረሱለት።
ነፍስንም ለማውጣት የመጣ የስጋ ራብ/የሞት መልአክ
ደካማ የባህታዊ ልብ/ታማሚን በማስደንገጥ ወሰዳት፥
ዳግመኛም ወደመቃብር/ድክመት እስካወረዳት ድረስ
የብርሃን መላእከት/አይኖች ከመቃብር አልተለዩም።



## ምስጢር

ካህናት የዳዊትን መዝሙር ለማስተዛዘል(ለመድገም) ተራ በተራ እየተቀባበሉ በቀኝና በግራ ይቆማሉ። በመቃብርም ቆመው ለህፃናት የትምህርት መጀመሪያ የሆነውን የዳዊትን መዝሙር ለሟቹ ያደርሱለታል ። የባህታዊ አይኖችም እንደካህናት ዘቀኝና በግራ መቆም በቀኝና በግራ ተፈጥረዋል ። የዳዊትን መዝሙር በቀኝና በግራ እንደማስተዛዘል ህፃናት በእድሜ ምክንያት ፥ ዳዊትም ሃጢአቱን በንስሃ ለማስተስረይ ያነባውን እንባ የባህታዊ አይኖች አዥጎደጎዱት(ዱብ ዱብ አደረጉት) ። በልቅሶም ብዛት የባህታዊ አይኖች እንደመቃብር ጎደጎዱ ፥ ብርሃናቸውም ደከመ ።

ነፍስን ከስጋ ለመለየት የሚመጣ መልአከ ሞት(የሞት መልእክተኛ) የታመመን አስደንግጦ ይገድላል እንደሚባል ሞትን የሚያመጣና ነፍስን ከስጋ የሚለይ የስጋ ራብ የባህታዊን ልብ አፈሰሳት። የሟች በድንም ወደመቃብር እስኪወርድ የብርሃን መላ እክትከመቃብር አይለዩም ተብሎ እንደሚነገር፡ የባህታዊ ልብ እስክትፈነዳ ድረስ መድከሟን ያዩ የባህታዊ አይኖች እንደመቃብር ከመሰርጎድ አልዳኑም። ይላሉ ባለቅኔው።

*311 መወድስ/ስ*

*ዘመራሒ(አለቃ፥ ዘጉና ሚካኤል)*

*ኦአዳም ኀይለ ማርየም*
*አይቴ ሀሎከ ወነበርከ በሕይወት*
*በዓመተ ውሁእ ኮንከ እምደብረ ገነት*



www.ethiopianorthodox.org

*ሰሚዐከ ቃለ አስሕቶታ ለሔዋን ትምህርት?*
*ባሕቱ ዜና ሞትከ*
*ለሰሚዕ ዕፁብ ፤ አምጣነ ሐዲስ ለለዕለት ።*
*አንሰሂ እንዘ ሀሎኩ ለእብሬተ ውእቱ ሞት፡*
*መኑመ ጸውዐከ እንበለ እብሬትከ በቅጽበት።*
*ወእንዘ በስም አነ መራሔ ፍኖት፤*
*ፍና ሞት ቀደሙኒ ወልድ ወብእሲት።*

## ትርጉም

አዳም ሃይለ ማርያም !
ወዴት አለህ ? ወዴትስ በህይወት ኖርህ?
የሄዋን /ትምህርት የማሳቷ ቃልን ስምተህ
ከደብረ ገነት ወጪን በሆንህ ጊዜ
ወዴት ኖርህ? በህይወትስ ወዴት ነበርህ?
ነገር ግን የሞትህ ወሬ
ለመስማት አስደናቂ ሆነ ፤ እየቀኑ አዲስ ነውና።
እኔም ለዚያ ሞት ፈረቃ ሳለሁ
ያለተራህ በፍጥነት ማን ጠራህ ?
እኔም በስም መንገድን መሪ ስሆን
የሞትን መንገድ ልጅና ሚስት ቀደሙኝ

## ምስጢር

አዳምን አምላኩ "ወዴት አለህ?" እንዳለው ባለቅኔው የጉና ሚካኤል አስተዳዳሪ አለቃ መራሂ ልጃቸው ሃይለ ማርያም በትምህርት ቤት እንደተለያቸው በዚያው መሞቱን በቅኔያቸው አስረድተዋል ። የሄዋንን ቃልም በመቀበሉና የተደነገገለትን ህግ በማፍረሱ አዳም ከገነት እንደወጣ ሃይለ ማርያምም በትምህርት ምክንያት ከደብሩ ወጣ ። አዲስ ነገርም እንደሚያስደንቅ እንዲሁም ሃይለ ማርያም እንደወጣ መቅረቱ ያሳዝናል ። ባለተራው ሳለ ባለተራ ያልሆነው መጠራቱ አግባብ እንዳይደለ ሽማግሌው አባቱ መቅደም ሲገባቸው ወጣቱ ልጃቸው በሞት መለየቱ ይገርማል ። መንገዱን የሚያውቅ መሪም እየመራቸው ሳለ



ተመሪዎቹ ከመሪው በፊት አይሄዱም ። "መራሒ" ማለትም መሪ ማለት በመሆኑ አለቃ መራሂ እንደስማቸው መቅደም ሲገባቸው ፡ ልጃቸውና ባልተቤታቸው ቀድመዋቸው ስለሞቱ ይህንን የሃዘን መግለጫ ቅኔ ተቀኝተዋል ።

## ታሪክ

ባለቅኔው አለቃ መራሂ የህግ ባልተቤታቸው ወ/ሮ ዘውዲቱ ያለውና ልጃቸው ደቀ መዝሙር ሃይለ ማርያም በአንድ አመት ተከታትለው ስለሞቱባቸው ይህን የሃዘን መግለጫ ቅኔ በደብራቸው በጉና ቅዱስ ሚካኤል ተቀኝተውላቸዋል ።

*312መወድስ ስ*
*ዘአስፋው (መሪ ጌታ ፡ ዘተድባበ ማርያም)*
*እምሕገ ሙሴ አዘዘ ፍትሐ ሆሣዕና*
*ከመ በአእባን ትትወገር ዘማ ኪሩቤል ሰብሐት ፤*
*እኮኑ ተረክበት ምስለ ሕፃናት*
*ወምስለ አእሩግ ዘስሳ ክረምት ፤*
*ድኅረ ፈኀርዋ መላእክት*
*በእንተ ልደታ ለዛቲ እምነ ሥላሴ ነገሥት ።*
*አግሐሡሂ ተናግሮ ተረፈ አእባን ቀደምት*
*መርቆሬዎስ በፈረሱ ወበለዓም በእድግት ፤*
*ወእንዘ ይዘርዑ ልብሰ ዘርዐ ሕዋሳት*
*ቦ እመልበስቶሙ ዘወድቀ በፍኖት ።*

## ትርጉም

ከሙሴ ህግ የተነሳ የኪሩቤል ዘማ
ምስጋና በድንጋይ ትወገር ዘንድ የሆሳእና ፍርድ አዘዘ፡
ከስላሴ ነገስታት ስለመወለዷ
መላእክት ከአጨዋት በሁዋላ
ከስልሳ አመት
ሽማግሌዎችና ከህፃናት ጋር ተገኝታለችና ።
የቀዳሚዎች ድንጋዮች ትራፊ / መናገርንም



www.ethiopianorthodox.org

መርቆሬዎስ በፈረሱ በለአምም በአህያው አነሱ ፤
የሰውነቶች ዘር /ልብስንም ሲዘሩ
ከልብሳቸው በመንገድ የወደቀ አለ ።

## ምስጢር

በአሪት ህግ አንዲት ሴት ስትሰስን ከተገኘች በድንጋይ ተወግራ መሞት እንደነበረባት ኪሩቤል የሚያመሰግኗት ምስጋናም በድንጋዮች ተነገረች ። ዘማዊቲቱም ከማንም ጋር እንደምትዋደቅ ሆሳእና የሚባል ኢየሱስ ክርስቶስ የተመሰገነባት ምስጋናም በህፃናትና በሽማግሎች እንደበት ተገለጠች ። ዘማዊቷ ሴት ከነገስታት ዘር የተወለደች ከሆነች በዚሁ ተግባሯ ታላላቅ ሰዎች እንደሚያሽሚጥጧት መላእከትም ስላሴን ባከበሩባት ምስጋና ሆሳእና ተመሰገነባት ። የባለጉዳዮቹ ረዳቶች የቆሎ ተማሪዎች ከድግስ የተረፈውን ምግብ ሰብስበው ወደየቤታቸው እንደሚ ሄዱ በሆሳእና እለት በድንጋዮች የተነገረው ምስጋናም በመርቆሬዎስ ፈረስና በበለአም አህያ አንደበት ሲነገር ተሰማ ። ገበሬዎች ዘር ሲዘሩ ፍንጣሪው በመንገድ እንደሚወድቅ ከሆሳእና አመስጋኞችም ልብሳቸ ውን በመንገድ ያነጠፉለት አሉ በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

*313 መወድስ (591)ጎ*

*ግብረ ሆሣዕና ነገር ለእመ ተወጥነ*
*አንሥአት ጸብአ ምስለ ሰሎሜ እድግት*
*እንዘ ትብል ኢይኅድር ውስተ ልብኪ ትምክህት ፤*
*ለእመ ተሐዝቢ ሆሣዕና*
*አምጣነ ውእቱ ሀብትኪ ስደት ፤*
*ወእንዘ ተሐውሪ በፍኖት*
*አዕቀፁኪ እእባን ወእኀቱኪ ፈያት ።*
*ሊተሰ እመ ሐዘልኩ ሆሣዕና ኵሉ ፍጥረት*
*በስብሐት ተቀበሉኒ እእሩግ ወሕፃናት ፤*
*ወተንሥኡ ሊተ እእባነ ገዳም ዐበይት*
*እንዘ ይብሉ ሆሣዕና መጽአ በትፍሥሕት ።*



## ትርጉም

የሆሳእና ነገር ቢጀመር
ትምክህት በልብሽ ውስጥ አይደር እያለች
አህያ ከሰሎሜ ጋር ጠብን አነሳች ፤
ሆሳእናን ብታዝይ
ሃብትሽ (ስጦታሽ) ስደት ነውና ፤
በመንገድም ስትሄጂ
ድንጋዮች አሰነካከለውሻልና ፤ ሽፍቶችም ከበውሻልና ።
እኔ ግን የፍጥረት ሁሉ መድሃኒትን ባዘልሁኝ ጊዜ
ህፃናትና ሽማግሎችም በምስጋና ተቀበሉኝ ፤
ታላላቅ የዱር ድንጋዮችም
ሆሳእና በደስታ መጣ እያሉ ተነሱልኝ ።

## ምስጢር

ክርክር ሲጀመር ሁለቱ ተከራካሪዎች እንደሚጣሉና እንደሚነቃቀፉ አህያና ሰሎሜ በሆሳእና ምክንያት ተጣሉ ማለት ሰሎሜ ክርስቶስን በህፃንነቱ አዝላው መሰደዷንና በእንቅፋት መመታቷን በሽፍቶችም መጨነቋን መናገር ነው ። አህያ ግን ሆሳእና የሚባል ኢየሱስ ክርስቶስን ስትሸከመው ልብስና ቅጠል እየተነጠፈላት ህፃናትና ሽማግሌዎች ፡ ድንጋዮችም እየዘመሩላት መሄዷን የቅኔው ምስጢር ይገልጣል ።

*314 አጭር ዦልክሎ/ ስ*
*ዘገብረ ሚካኤል (አለቃ)*

*ሀዊዳ ትጸርሕ ዘግዕተ ዐላዊ መጥባሕት ፡*
*እስመ ተርፈ ውስተ አስፈሬዳ ዕጓላ ሰማእት ።*

## ትርጉም

የወንጀለኛ በግ /ሰይፍ ዞራ ትጮኸለች ፡
ግልገሏ ሰማእት (ቶማስ) በቅርጫት ውስጥ ቀርቷልና ።

## ምስጢር

ግልገሏ በቅርጫት ውስጥ የዋለባት በግ ወደሁዋላ ዘወር እያለች ትጮኸለች ። የቶማስ ትምህርት ተቃዋሚ ሰይፍም ስለት ለማውጣት



www.ethiopianorthodox.org

ተፋጨች ። መላልሳ የቆረጠችው ሰማእቱ ቶማስም በቅርጫት ውስጥ ሆኖ እየሄደ ወንጌልን ሰበከ በማለት ባለቅኔው ሰማእቱ ቶማስ የፈፀመውን ተጋድሎ አስረድተዋል ።

*315 አጭር ዙልክሙ /ሰ*
*ዘተካልኝ (ቀኛዝማች ፣ ዘየነጃ ሚካኤል)*

*ይርዳእከ መጽአ መፃጉዐ ደዌ ምውት ፤*
*እሳተ ለቢሶ ወልድከ አጽባዕት ።*

## ትርጉም

የህማም በሽተኛ ! ልጅህ/ ጣት
እሳት ለብሶ ሊረዳህ መጣ ።

## ምስጢር

አባትየው እንድ ነገር ሲሆን በእጠገቡ የቆመው ሰው አባትየውን "ያውልህ ልጅህ እሳት ለብሶ መጣ" ይለዋል ። ሰላሳ ስምንት እመት የታመመው በሽተኛ መፃጉእ ያዳነውን ክርስቶስን በጥፊ ሲመታው ጣቱ እንደጡዋፍ ነደደ ። ስለዚህም ሞተ ነፍስ (የነፍስ ሞት) ይፈረድበታል ይላሉ ባለቅኔው ።

*316 ሕንጼሃ(119)ይ*
*ዘወልደ ትንሣኤ (መሪጌታ)*

*ኢይቀውም አይሁዳዊ ቅድመ ሥላሴ ለጸሎት ፤*
*እስመ ምስለ ደም ብእሲቱ ዙናት ።*

## ትርጉም

አይሁዳዊ በስላሴ ፊት ለፀሎት እይቆምም ፣
ሚስቱ /ጦር ከደም ጋር (በእደፍ) ናትና ።

## ምስጢር

በአሪት ህግ ፀሎተኛ ሰው ከአደፍ (ከወር አበባዋ) ካልነፃችው ሚስቱ ጋር ከተኛ እርሱም ንፁህ ሊሆን አይችልም ። በዚህም ምክንያት



በስላሴ ፊት ቆሞ አይፀልይም ። የሰናእርን ግንብ ይሰሩ የነበሩት የአይሁድ ወገንም የሰናአር ግንብ ሲወድቅ አብሮ በስላሴ መአት ወደቀ ። ግንበኞቹም ወደሰማይ የወረወሩት ጦር ደም እየተቀባ ወደምድር ተመለሰ በማለት ባለቅኔው ያስረዳሉ (ስንክ· ጥር ፤ ሃምሌ 7) ።

*317 መወድስ (ጉርድ) ሰ*
*ዘጥሩነህ (አለቃ)*

*ቀርበሂ ለአንሥኦ እንዘ ይሰፍሕ አጽባዕቶ*
*ሕፃነ ገሞራ ነደ እሳት ነነዌ ዘሐዘለቶ*
*ወበእዴሃ ሰሎሜ ዘሐቀፈቶ*
*ቶማስ ፣ በአርብዓ እስመ ገብረ አንሥአቶ ።*

## ትርጉም

ነነዌ ያዘለችውን ፣ ሰሎሜም በእጁዋ
ያቀፈችውን የገሞራ ህፃን / የእሳት ነዲድንም
ለማንሳት ጣቶቹን ዘርግቶ ቶማስ ቀረበ ፤
ማንሳቱን በእርባ ቀን አድርጓልና ።

## ምስጢር

ህፃንን ክርስትና የሚያነሳ የክርስትና አባት እጁን ዘርግቶ ወደህፃኑ ይቀርባል ። ሃዋርያው ዲዲሞስ የሚባለው ቶማስም በጦር የተወጋውን የክርስቶስን ጎን በእጁ ቢዳስስ እጁ በእሳት ውስጥ እንደተጣለ ጅማት ተኮማተረ ። ክርስትና የሚነሳውንም ህፃን አንዲቱ ሴት ስታዝለው ሌላዩቱ ሴት ደግሞ በክንዱዋ ታቅፈዋለች ። ገሞራን ያቃጠለ እሳትም በጀርባ እንደመታዘል በነነዌ ላይ አንዣበበ ፤ በክንድ እንደመታቀፍም የቅድስት ማርያምን ሆድ የዳሰሰ የሰሎሜን እጅ አቃጠለ ። ያታው ወንድ የሆነ ህፃን በአርባ ቀን ክርስትና እንደሚነሳ የቶማስ እጅ በእሳት መቃጠልም ክርስቶስ ከሙታን በተነሳ በእርባኛው ቀን ሆነ በማለት ባለቅኔው በእሳት የተፈፀሙትን ድርጊቶች በቅኔያቸው ምስጢር አብራር ተዋል ። (ይህ መወድስ ቅኔ የመጀመሪያዎቹ አራት ቤቶች ስለተጎረዱ "ቀጠፉ" ቅኔ ይባላል ።)



www.ethiopianorthodox.org

*318 ግእዝ ጉባኤ ቃና /ስ*

*ዘአድማሱ ጀንበሬ (መልአከ ብርሃን)*

*ኢየሐፍር አንሰ እብነ አድማስ ከዊነ ፤*

*እብነ አድማስ ኃያል እስመ የሐርጽ አእባነ ።*

## ትርጉም

እኔ የአድማስ ድንጋይ መሆንን አላፍርም ፤

ሃይለኛ (ጠንካራ) የአድማስ ድንጋይ ድንጋዮችን ይፈጫልና።

## ምስጢር

ብርቱ የሆነ የአድማስ ድንጋይ ሌሎችን ድንጋዮች የሚያቀልጣቸው እንደሆነ ይነገራል ። እንዲሁም የመልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ደቀ መዝሙር የአድማስ ድንጋይ ቢባል ምስጋና እንጂ ስድብ አይሆንበትም ። ምክንያቱም የአድማስ ድንጋይ ሌሎችን ድንጋዮች የሚፈጫቸው (የሚያቀልጣቸው) ሃይለኛ እንደሆነ እንዲሁም የመልአከ ብርሃን አድማሱ ግርፍ (መልአከ ብርሃን አድማሱ ያስተማሩት) ደቀ መዝሙርም አላዋቂዎችን ያሰለጥናቸዋል በማለት ባለቅኔው ራሳቸውንና ደቀ መዝሙሮቻቸውን በቅኔያቸው ምስጢር አሞግሰዋል ።

*319 ዘአምላኪየ*

*ዘተክለ ማርያም (አለቃ)*

*መጻሕፍተ ጥበብ ናንብብ እንዘ ንለብስ ብርሃነ ፤*

*መጽአ መዓልተ አእምሮ ወኀለፈ ለነ*

*ሌሊተ ጽልመት ክቡድ እምድኅረ ከብደ ላዕሌነ ።*

## ትርጉም

ብርሃንን ለብሰን የጥበብ መፃህፍትን እናነብ

ዘንድ መአልት / እውቀት መጣ ፤

የከባድ ጨለማ ሌሊትም በእኛ ላይ ከከበደ በሁዋላ አለፈ

ልን።

## ምስጢር



መፃህፍትን ማንበብ በመአልት (በቀን) በብርሃን እንጂ በጨለማ እንደማይቻል በድንቁርና ተሸፍኖ ማወቅ የለምና ጥበብን ለማስፋፋት የእውቀት ፍልስፍና (ዘመናዊ ትምህርት) ተገለፀልን በማለት ባለቅኔው እውቀትን ከቀን ብርሃን ድንቁርናንም ከጨለማ ጋር አነፃፅረዋል ።

*320 መወድስ (635)ኀ*

*አኀፍር ኢንሰ በተፋኅሮትኪ*

*ለአረጋዌ ኀይል ዮሴፍ ማርያም እመ ኵልነ*

*እኅተ መላእክት ኵሎሙ እንዘ ንሰምየኪ ንሕነ ፤*

*ባሕቱ በኀበ ኵሉ*

*ወርቀ ንጽሕናኪ በዮሴፍ ተፈትነ ፤*

*እስመ ኢኀሠሠ ልቡናኪ*

*ኀበ ዮሴፍ ይሑር ሐልዮ ኃጢአት ሣዕነ*

*ነገርኪኒ ጽሩየ ኵሉ መንገለ ጽሩየ ኮነ*

*በብሂለ ዕፁብ አድማስ ፍጹመ ተወስነ*

*እስመ እንዘ ላህም ትነብር ምስለ አንበሳ እሙነ*

*እምአንበሳ ኀይል ዘአምሰጠት ላህመ ርኢነ ።*

## ትርጉም

የሁላችን እናት ማርያም !

እኛ የሁሎች መላእክት እህት ስንልሽ

ለሃይል ሽማግሌ ዮሴፍ በመታጨትሽ እኔ አፍራለሁ ፤

ነገር ግን በሁሉ ዘንድ

ወርቅ /ንፅህናሽ በዮሴፍ ተፈተነ ፤

ወደዮሴፍ ይሄድ ዘንድ

ሃጢአትን ማሰብ /ጫማን ልብሽ አልፈለገምና ።

ከሁሉ የጠራ ነገርሽም ጥሩ ከሆነ ዘንድ

ድንቅ በማለት/ አድማስ ፈፅሞ ተወሰነ ፤

ላም በእውነት ከአንበሳ ጋር ስትኖር

ከሃይል አንበሳ ያመለጠች ላምን አላየንምና ።

## ምስጢር

አንድ ልጅ የታዘዘውን ሳይፈፅም ውሎ ማታ ወደቤቱ ሲገባ እናቱን



www.ethiopianorthodox.org

ይፈራል ። ባለቅኔው ቅድስት ማርያም የዘመዱዋ የዮሴፍ እጮኛ መባሏን አልደፈሩም። ልጁ የሚፈራው እናቱ ስለምትቆጣው እንደሆነ ባለቅኔውም ያልደፈሩት ማርያም በንፅህናዋ እንደመላእክት ናት ስለሚባል ነው። ነገር ግን ወርቅ በእሳት እንደሚፈተንና ጥሩነቱ እንደሚታወቅ የማርያም ንፅህና በዮሴፍ ታወቀ ። የድሮ ሰው መንገድ ሲሄድ ጫማን ከእግሩ እንደማይሻ የማርያምም ልብ ዮሴፍን ለሰው ልጅ ልማድ (ለሩካቤ) አልተመኘውም። የገበሬ እርሻ በድንበር እንደሚወሰን የማርያምም ነገር በአድናቆት ይነገራል ። ላም ወደ አንበሳ ከቀረበች በአንበሳው ከመበላት የማትድን ስትሆን ማርያም ግን ከዮሴፍ ጋር ስትኖር በንፅህና ተጠብቃ አምላክን በድንግልና ፀንሳ ወለደችው በማለት ባለቅኔው ስለቅድስት ማርያም ያላቸውን እምነት ገልጠዋል።

*321 ዘአምላኪየ/ስ*

*ዘጥሩነህ (አለቃ)*

*እምአርባዕቱ አፍራስ ዘበተታልዎ ተፈትኑ*
*ፈረስ አሐዱ ይከውን ለመኑ?*
*ሠለስቱ አፍራስ እስመ ለሠለስቱ ተጽዕኑ ።*

## ትርጉም

በመከታተል ከተፈተኑ ከአራቱ ፈረሶች
አንደኛው ፈረስ ለማን ይሆናል?
ሶስቱ ፈረሶች ለሶስቱ ጋላቢዎች ተጭነዋልና ።

## ምስጢር

በመከታተል የተፈተኑ አራት ፈረሶች ተጭነው ሲሳቡና ከፈረሶች ጋር የሚሄዱት ሰዎች ሶስት ሲሆኑ "ሶስቱ ፈረሶች ለሶስቱ ሰዎች ይሆናሉ፤ አንዱ ፈረስስ ለማን ይሆናል ?" ይባላል ። ከዚህም አንፃር ባለቅኔው ገፀ ሰብእ (ሰው ፊት)፤ ገፀ እንስሳ (ላም ፊት) ገፀ አንበሳ (አንበሳ ፊት)፤ ገፀ ንስር (ንስር ፊት) የተባሉት አራቱ ኪሩቤልን ከአራቱ ፈረሶች አብን ወልድንና መንፈስ ቅዱስንም ከሶስቱ ፈረሰኞች ጋር አነፃፅረዋል ። ፈረሰኞች ፈረሶችን እንደሚጋልቡም አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አራቱ ኪሩቤል በተሸከሙት ዙፋን ላይ ሆነው ይመሰገናሉ እየተባለ ይነገራል ።



ሶስቱ ፈረሶች በሶስት ሰዎች እንደሚጋለቡ ሶስቱ ኪሩቤል ለአብ ፤ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ ይበቃሉ ። አራተኛው ኪሩብ ግን ትርፍ ነው በማለት ባለቅኔው ቅኔያቸውን አመስጥረዋል ።

*322 ግእዝ ጉባኤ ቃና (656)ጎ*
*መና ዝናም ለከርሠ እስራኤል ደመና*
*ወደመና ሰማይ ከርሥ ለዝናመ ክረምት መና ።*

## ትርጉም

መና ለእስራኤል ሆድ/ደመና ዝናብ ነው ፤
የሰማይ ደመና/ሆድም ለክረምት ዝናብ መና ነው ።

## ምስጢር

ዝናብ በደመና ውስጥ እንደሚቋጠር መናም በደመና ከሰማይ ወርዶ ለእስራኤል ምግብ ሆነ ። ደመና ዝናብን እንደሚሸከመው የእስራኤል ሆድም ደመና የተሸከመውን መና ጠገበው በማለት ባለቅኔው አስረድተዋል ።

*323 ግእዝ ጉባኤ ቃና/ስ*

*ተዐቀብ በትር ብእሴ ብዙኅ ልዕልና ፤*
*ከበሮ ፀርከ እስመ የኀሥሥ ሆሣዕና ።*

## ትርጉም

የብዙ ከፍታ ሰው/በትር ተጠበቅ ፤
ከበሮ/ጠላትህ መድሃኒትን ይፈልጋልና ።

## ምስጢር

ጠላቱ መርዝ ሊያበላው የሚዘጋጅበት ሰው መጠንቀቅ እንደሚገባው በአቢይ ፆም (በኩዳዴ) በማህሌት ጊዜ መቋሚያ ከከበሮ ራቀ (ተለየ)። ከበሮም በሆሳእና በአል ምክንያት እስኪመታ ድረስ ዝም በማለት ባለ ቅኔው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በተለይ በአቢይ ፆም የሚደረሰው ማህሌት ያለከበሮና ያለፀናፅል በመቋሚያ ብቻ እንዲዘመር የተሰራውን ስርአት በቅኔያቸው ምስጢር ያስገነዝባሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

*324 ዋዜማ/ስ*

*ዘሳሙኤል (አለ.ቃ ፡ ዘግሸን ማርያም)*

*ፈድፈደ ብዕለ ሥላሴ ፡*
*እንተ ለሥላሴ ተውህበ ላህመ አብርሃም አቡነ*
*ምስለ ሉቃስ ቢጹ እስመ ጽምደ ኮነ ፤*
*እስመ ከመዝሰ ብዕል ውስተ ሰማያት ተወጥነ*
*እንዘ ርስተ ሰማይ ንትካፈል በበመጠንነ*
*ሰማያተ ንሐርስ ኵልነ ።*

## ትርጉም

የስላሴ ብልፅግና በረከት ፡
ለስላሴ የተሰጠ የአባታችን አብርሃም ላም
ከጓደኛው ሉቃስ ጋር ጥምድ ሆኗልና ።
ብልፅግናስ በሰማዮች ውስጥ እንደዚህ ከተወጠነ
የሰማይ ርስትን በየልካችን እየተካፈልን
ሁላችንም ሰማዮችን እናርሳለን ።

## ምስጢር

ገበሬ ሃብት ሲያገኝ ቀንጃውን ጥምድ ያደርግና ያርሳል ። እንዲሁም ለስላሴ የታረደው የአብርሃም በሬ ተነስቶ እንደወንጌላዊው ሉቃስ እጅ ደህና ሆነ ። ገበሬው ጥምድ በሬ ከጠመደ በሁዋላ ርስቱን ከዘመዶቹ ጋር እየተካፈለ ድርሻውን እንደሚያርስ የስላሴም ስጦታ በመንግስተ ሰማይ ይሰጣል ። ስለዚህም መንግስተ ሰማይን በደረጃ ሁላችንም እንወርሳለን በማለት ባለቅኔው ምኞታቸውን በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል ።

*325 ዋዜማ(658)ን*

*አይድዕዎ ለመቃብር*
*ዜና ላእከ ኤልያስ ንስር ወላእከ ሙሴ ደመና*
*መላእክት እለ ይዜንው ዘድንግል ዜና ፤*
*እምጣነ ድንግል ዘርኀበት መብልዐ መሬት ሙስና*
*በልሀት ሥጋ ዘተርፈ ውስተ ፍና*
*ወዘኀልቀ በፈንቆን መና ።*



## ትርጉም

የድንግልን ዝና የሚናገሩ
መላእክት የኤልያስ መልእክተኛ/የንስርንና የሙሴ
መልእክተኛ/የደመናን ወሬ ለመቃብር ነገሩት ፤
የመሬት መብል/ጥፋትን የተራበች ድንግል
በመንገድ ውስጥ የቀረ ስጋን በልታለችና ፤
በፈንቆንም ያለቀውን መና በልታለችና ።

## ምስጢር

ወሬኞች ሰዎች የእገሌ መልእክተኛ እንዲህ ሰራ ፡ የእገሌም መልእክተኛ እንዲህ አደረገ እያሉ ላገኙት ሰው ሁሉ ያወራሉ ። ቅድስት ማርያምን ወደሰማይ አሳረጉ (አወጡ) የሚባሉ መላእክትም የኤልያስን ንስር ወሬና የሙሴን ደመና ወሬ ለመቃብር ነገሩት ማለት ንስር ለኤልያስ የሚያመላልሰውን ስጋ አስቀረ ፤ የሙሴም ደመና መና ማቅረቡን ፈንቆን በሚባል ቦታ አቆመ ። መላእክት የማርያምን ስጋ አላስቀበሩትም ። ሴት መንገደኛ እንደምትራብ ማርያምም እንደሙታን በመቃብር ውስጥ አልፈረሰችም ፡ አልበሰበሰችም ። መንገደኛይቱ ከደረሰችበት ቦታ እያደረችና ያገኘችውን እየበላች እንደምትጓዝ ማርያምም በፈንቆን እንደቀረው መና በስማይ ቀረች ይላሉ ባለቅኔው ።

*326 ዋዜማ (1075)ን*

*ዘእንግዳ (አለ.ቃ)*

*ዕፁብ ለሰማዒሁ*
*ነገረ ጠማር ድንግል እንተ አልባቲ ሙስና ፤*
*ጽንሰተ አምጣነ ርክብት ይእቲ በዜና*
*እምድምፀ መልአክ ፍንው እንተ አብሠራ በፍና ፤*
*ወእንዘ ኀትምት ይእቲ በድንግልና*
*ወለደቶ ለባሕራን ሕፃና ።*

## ትርጉም

ጥፋት የሌለባት



www.ethiopianorthodox.org

የደብዳቤ ድንግል ነገር ለሰሚው ድንቅ ነው ፤
በመንገድ ከእበሰራት ከመልአክ ድምፅ
በወሬ የበነሰች ሆና የተገኘች ናትና ፤
እርሷም በድንግልና የታተመች (የተቆለፈች)
ልጇ ባሀራንን ወለደችው ።

## ምስጢር

ቅድስት ማርያም የመልአኩ የቅዱስ ገብርኤልን ድምፅ ለምታ እግዚአብሄር ቃልን ስትፀንሰውና በድንግልና ስትወልደው አወላለዱ አስደናቂ ነው ። እንዲሁም የድንግሊቱ ምሳሌ የሆነችው የባህራን የሞቱ ደብዳቤ (ባህራንን ግደሉት የምትል ደብዳቤ) በመልአኩ በቅዱስ ሚካኤል ቃል "ለባህራን ሴት ልጄን አጋቡት" ወደማለት መለወጧ ተአምር ነው በማለት በቅኔው ተመስጥሯል (ስንክ. ሰኔ 12) ።

*327 ዘይእዜ ስ*

*ዘደስታ (እሊት ፡ ዘተድባበ ማርያም)*
*ሙሴ ኢትዕርግ ላዕለ ታቦር ፤*
*ዘመ ደብረ ሲና በታቦር እስመ ኢይትረከብ መና*
*ወበታቦር እልቦ ዘሀሎ በሲና ፡*
*ወእመ ሀየ ተዐርግ ኢይምሰልከ ለጥዒና ፤*
*ስቴ ዘታቦር ምስጢረ ዋሕድና*
*አምጣነ አእምሮ ያጠፍዕ ፡ ወያዘነግዕ ልቡና*
*ስቴ ዘታቦር ምስጢረ ዋሕድና ።*

## ትርጉም

ሙሴ ! በታቦር ላይ አትውጣ ፡
በታቦር እንደ ደብረሲና መና አይገኝምና
በሲና ያለውም በታቦር የለምና ፡
ወደዚያም ብትወጣ ለጤና አይምሰልህ ፡
የታቦር መጠጥ/የአንድነት ምስጢር
እውቀትን ያጠፋልና ፡ ልብንም ያዘነጋልና
የታቦር መጠጥ/የአንድነት ምስጢር ።



## ምስጢር

ለአንደ ወዳጅ ወዳጁን ሲመክረው "ወደእገሌ ቦታ አትሂድ ፤ ሁልጊዜ የአማን ቀን አይገኝም ፤ ብትሄድ ግን ለጤንነትህ አይደለም" ይለዋል ። ሙሴ በደብረ ሲና መና ከደመና ወርዶለት ተመግቧል ፤ ከአምላክ ጋር በእሳት መጋረጃ ውስጥ ተነጋግሯል ይባላል ። በደብረ ታቦር ግን ሙሴ ያየው ደመና እነጴጥሮስን አስደንግጦ የጣለ ስለሆነ ወደነበረበት መመለሱን ባለቅኔው በቅኔያቸው ምስጢር አስረድተዋል (ማቴ. 17) ።

*328 መወድስ/ስ*

*ሕሊና ይሔሊ ዘኢይፌጽም*
*ወእምሕሊና ይተርፍ ሐዋርያ ፍኖት ልቡና ፡*
*ወእምረበናት ንስማዕ ምሳሌ ውእቱ ዜና*
*ሞተ ሀገረ አሕዛብ ኢበጽሐት ሶስና ፤*
*ወእንዘ ምውት በሕሊና*
*ምስለ እግዚኡ ኢይሙት ጐየ ወልደ ዮና ።*
*በሕሊናሂ ለኤልያብ እንዘ ትደለው ምልክና*
*ተውህበት ለዳዊት ዘኢተሐለየ በልቡና ፤*
*ዘካርያስሂ ንዋየ እንዘ ይሬስዮ ለመና*
*መና ዘተሰፈዎ ተሰወረ በደመና ።*

## ትርጉም

ሀሊና የማይፈፅመውን ያስባል
መንገድን ሂያጅ ልብም ከሀሊና ይተርፋል ፡
የዚያንም ወሬ ምሳሌ ከአይሁድ መምህራን እንሰማ ዘንድ
የአህዛብ አገር/ሞትን ሶሰና አልደረሰችም ፤
በሀሊና የሞተ ሲሆን
ከጌታው ጋር እንዳይሞት የዮና ልጅ ሸሸ ፤
ግዛትም በሀሊና ለኤልያብ ስትዘጋጅ
በልብ ላልታሰበው ለዳዊት ተሰጠች ፤
ዘካርያስም መናን ገንዘብ ሲያደርገው
ተስፋ ያደረገው መና በደመና ውስጥ ተደበቀ ።



www.ethiopianorthodox.org

## ምስጢር

ሁለት መንገደኞች በፊትና በሁዋላ እንደሚሄዱ ሁሉ አሳብና ልብም ተባባሪዎች ሲሆኑ አሳብ ከልብ አልፎ ይሄዳል ። መንገደኞቹ በመንገድ ደክመው እንደሚያርፉ የልብ አሳብም እንደታሰበ አይፈፀምም። ወደሩቅ አገር ለመሄድ የተነሱ ሰዎች ቀኑ ከመሸ በሁዋላ መንገድ ቢጀምሩ ካሰቡት ቦታ ሳይደርሱ እንደሚጨልምባቸው ረበናትም (የአይሁድ መምህራን) ሶስናን በአሰት ለማስገደል ሲያስቡ የሶስና ሞት ለእነርሱ ሆነ ። ሃዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም ከመምህሩ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ለመሞት ሲያስብ ፤ እንኳን ሊሞትለትና "አንተ ደግሞ ከናዝሬቱ ከኢየሱስ ጋር ነበርህ" በማለት ለቀረበለት ጥያቄ "የምትሉትን አላውቀውም" ብሎ ካደው (ማር. 14 ፥ 66–72) ።

የሳኦልም መንግስት ለኤልያብ ሲታሰብ ያልታሰበው ዳዊት ለንጉስነት ተቀባ ። የኦሪቱ ሊቀ ካህናት ዘካርያስም ለእርሱ እንደወረደ ሲያስብ ይኸው መና ለኢያቄምና ለሃና ልጅ ለቅድስት ማርያም ተሰጠ በማለት የቅኔው ደራሲ አመስጥረዋል (ሳሙ. 16፥23) ።

*329 መወድስ(669)ጎ*

*ዘገብረ ማርያም ቡሬ (መልአከ ሰላም ፡ ዘደምበጫ ሚካኤል)*

*ጽዕለተ አይሁድ ትስማዕ በፍትሐ ኦሪት*
*ዕፁተ ማሕፀን ይእቲ እንተ ኢወለደት ሐና ፤*
*እመኒ ተወከፈት በረከተ መልአክ ዜና*
*ዕፁተ ማሕፀን ጊዜ ወሊድ*
*ዘበልበ ሰብእ ማርያም ሕሊና*
*እምጣነ ትትናጸር በልዕልና*
*ኢየሩሳሌም መካን ምስለ ወላዲት ደብረ ሲና ።*
*ዮሴፍሂ ኢፈለጠ በነጽሮ ገጸ ወሥና*
*ዘእግዚአብሔር አስተፃመረ ወሊደ ወንጽሕና ፤*
*እንዘ ቦሙ ጋዕዘ በጥንተ ነገር ሰብእና*
*ለሄሮድስ ግብረ ወሊድ ወለጲላጦስ ድንግልና ።*

## ትርጉም

የአይሁድን ስድብ በኦሪት ፍርድ
ትሰማ ዘንድ ያልወለደች ሃና ማህፀነ ዝግ ሆነች ፤
የመልአክ ስብከት ዜናን ብትቀበልም
በሰው ልብ ያለች ማርያም አሳብ
በመውለድ ጊዜ ማህፀነ ዝግ ናት ፡
ኢየሩሳሌም/መካን
ከወላጅ/ደብረ ሲና ጋር በከፍታ ትታያለችና ።
ዮሴፍም ፊቷንና ውበቷን በመመልከት
እግዚአብሄር ያጣመራቸውን መውለድንና ንፅህናን አለየም ፡
ለሄሮድስ/የመውለድ ስራና ለጲላጦስ/ድንግልና
በነገር ጥንት/ሰውነት ክርክር ሲኖራቸው ።

## ምስጢር

አንዳንድ ሴት ደጇን ዘግታ የሌለች መስላ የጎረቤቷን አሜት ታዳምጣለች ። እንዲሁም አግብተው ያልወለዱ ሴቶች በኦሪቱ ስርአት ማህፀነ ዝግ እየተባሉ ይሰደቡ ነበር ። ከዚህም የተነሳ የቅድስት ማርያም እናት ሃና በመምከኗ ማህፀነ ዝግ ተብላለች ።

የሰውም አሳብ መውጫውና መግቢያው እንደማይታወቅ በሰው ልብ የምትታሰብ ቅድስት ማርያም አምላክን በመፅነስና በመውለድ ጊዜ ማህፀኗ አልተፈታም ። ኢየሩሳሌምና ደብረ ሲናም እንደሚነፃፀሩ መካን ሴት ባለመውለዷ ፤ የወለደች ማርያምም ከወለደች በሁዋላ ማህተመ ድንግልናዋ ባለመለወጡ ማህፀነ ዝግ በመባል አንድ ሆኑ ።

እግዚአብሄር በጋብቻ ምስጢር ያጣመራቸውን ባልንና ሚስትን መለየት እንደማይገባ እምላክም በኪነ ጥበቡ ያጣመራቸውን መውለድንና መደንገልን ዮሴፍ በቅድስት ማርያም መልክ ውበት ተስቦ አላስቀረም። የእስራኤል አገር ገዥዎች የነበሩ ሄሮድስና ጲላጦስም በግዛት ወሰን ይጣሉ እንደነበረ መውለድና መደንገልም አይተባበሩም ። በተጨማሪም ባለቅኔው "መውለድ ባለበት መደንገል አይገኝም ፤ መደንገልም ባለበት መውለድ የለም" በማለት በቅድስት ማርያም የእናትነትና የድንግልነት ፀጋ ስጦታ ላይ ያላቸውን አድናቆት በቅኔያቸው ምስጢር አስረድተዋል።

*330 መወድስ (675) ጎ*

*ንዋየ ፋዳ ሰብእ ተዐውረ መልዕልተ ርእስከ*
*አግብኦተ ፋዳ ለሰብእ ዘተአምር ሆሣዕና!*





www.ethiopianorthodox.org

እስመ ዘተአምር አንተ እምቅድመ ያእምር ሕሊና
ለአዳም አቡነ ፍዳ ከላዕከ
ኢይብላዕ በለስ ገነት ወኢይርአይ ስና

ጊዜ ረኀብከ ሕገ ሲና
ፍሬ ዕፀ በለስ ኀጣእከ እንዘ ለካልእን ወሀቤ መና ።
ወኀጣእከ ግማደ ልብስ ቅድመ ቀያፋ ወሐና
ታሕተ እግረ ዕዋል ፍዳ ነጸፍከ አልባሰ ደቂቅ በውስተ ፍና ፤
ወፍዳ ተዋነይከ አንተ በወይነ ዚአሃ ለቃና
በቀራንዮ ሰኢለ ማይ አስተዋረደከ እምልዕልና ።

## ትርጉም

ለሰው ፍዳን መመለስ የምታውቅ ሆሳእና!
የሰው ፍዳ ገንዘብ በራስህ ላይ ሆነ ፤
ህሊና ሳያውቅ የምታውቅ አንተ አባታችን አዳምን
የገነት በለስን እንዳይበላና
መልኳን እንዳያይ ስለከለከልኸው ፈንታ
የሲና ህግ በሚሆን በራብህ ጊዜ
ለሌሎች መናን ለጪን ስትሆን የበለስ እንጨት ፍሬን አይተሃልና ።
የልጆችን ልብሶች ከውርንጫ እግር በታች በመንገድ ስላነጠፍህ
ፈንታም
በቀያፋና በሃና ፊት የልብስ ቁራጭን አጥተሃልና ፤
አንተም በቃና ወይን ስለተጫወትህ ፈንታ
በቀራንዮ ውሃን መለመን ከከፍታ (ከክብር) አዋርዶሃልና ።

## ምስጢር

"ብድር ውሎ አያድር" እንዲሉ መቸም ሰው ክፋም ሆነ በጎ የሰራውን ብድራት ያገኛል ። ሆሳእና የተባለው ክርስቶስም በመንገድ ሲራብ የበለስን ፍሬ ሳያገኝ የቀረው አዳምን በለስን እንዳይበላ ስለከለከለው ብድራት ነው በመስቀልም ላይ ከልብስ የተራቆተው የልጆችን ልብስ በመንገድ አስነጥፎ በአህያ እግር ስላስረገጠ ሲሆን በመስቀል ላይ የተጠማውም በቃና ውሃውን ወይን ስላደረገው ነው ይላሉ ባለቅኔው ።



331 ዕዝል ዕጣነ ሞገር /ስ
ዘጥፋነህ (አሰቃ ፣ ዘቦታ ኪዳነ ምሕረት)

ዐንበረ ጸርጋሞን ሞት ሐንካሰ ዮርዳኖስ ፍና
መስቄ አውስግንዮስ አሶር ቀስተ ደመና
እስመ ወልደ ቂርቆስ ምስዋራ ለመልእክተ ሞት ዮና
ለብእሲተ ግብጽ በአምጣና
ጽላሎተ ሞት እሞጽ ሙራደ ሥጋ አቤል መና
ኑኀሚን ደብረ ማርያም ተመይጠት ዕርቃና ።

## ትርጉም

የሽማኔ መወርወርያ የሆነ የዮርዳኖስ መንገድ አንካሳ
የወንዝ /ሞት አሳ አንበሪ የሆነ መቃብር/ ቀስተ ደመና
የአቤል ስጋ /መና መውረጃ እንደሆነ እንደሞት/ አሞን
በግብፅ ሴት ልክ
የሞት /ዮና መልእክት መሰወሪያ ወልደ ቂርቆስ ነውና
ኑሃሚን /ደብረ ማርያም ባዶዋን (ብቻዋን) ተመለሰች ።

## ምስጢር

የሽማኔ መውገሪያ ማጉን ለድሩ (ለዝሀው) እንደሚያጠጣው ዮርዳኖስ የሚባለው ወንዝ ፈሳሽ ውሃ የህፃናት መጠመቂያ ነው ። አሳ አንበሪ ከባህሩ ውጪ ለብዙ ጊዜ መኖር እንደማይችል ለሞት ያደረሰው የኢዮብ ህማም በዮርዳኖስ ውሃ ሲታጠብ ተወገደ ። ደመና የዝናብ ውሃን እንደሚቋጥር አሳ አንበሪ ነቢይ ዮናስን ውጧል ። ሞትም መቃብርን ያስከትላል ። ደመና የብርሃን መሰወሪያ እንደሆነ መቃብርም በሞት ሃይል የወልደ ቂርቆስ መደምደሚያ ሆነ ። ሁኔታውም በግብፅ አገር በኖረች እስራኤላዊት ሴት በራሄል ልቅሶ ተፈፀመ ። አሞንም የመና መውረጃ እንደሆነ ሞት የአቤል ስጋ መጥፊያ ሆነ ። ልጆቿ የሞቱባት ሴት ኑሃሚን ወደ አገሯ ባዶዋን እንደገባች ወልደ ቂርቆስ በተባሉት በመምህር ጩፋ ሞት ደብረ ማርያም ተፈታች ይላሉ ባለቅኔው። የቅኔው መንገድ ቅጥልጥል (ሐረግ) መንገድ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

## ታሪክ

ወልደ ቂርቆስ የተባሉት መምህር ጩፋ በአማራ ሳይንት በበሮ ቅዱስ ሚካኤል ደብር ተወለዱ ። በስመ ጥሩዋ ደብር በአትሮንስ ማርያም ተምረው ስመጥር የቅኔና የአቡሻህር መምህር ለመሆን በቅተዋል ። በአፄ ዮሃንስ ዘመነ መንግስት በአማራ ሳይንትና በቦረና አውራጃ ውስጥ የምትገኘውን የአደሬ ማርያምን ቤተ ክርስቲያን ተክለው ቅኔና አቡሻህር እያስተማሩ ይኖሩ ነበር ። በዚህም ጊዜ አያሌ ደቀ መዛሙርትን አስተምረው በመምህርነት መርቀዋል ። በሞቱ ጊዜም የአቡሻህር ትምህርት ደቀ መዝሙራቸው የሆኑት የቅኔ መምህር አለቃ ጥሩነህ ይህን ቅኔ ተቀኝተዋል ።

*332 ግእዝ ጉባኤ ቃና /ስ*
*ዘገብረ ጊዮርጊስ (መምህር ፡ ዘአክሱም)*
*ይሜንን ስብእ እብነ ቢታንየ ዲያቆን ፡*
*እስመ ቅዳሴ ተምሀረ እምነ ሱራፌ ካህን ።*

### ትርጉም

የቢታንያ/ዲያቆን ድንጋይ ሰውን ይንቃል ፤
ከሱራፌ/ካህን ቅዳሴን ተምሯልና ።

### ምስጢር

አንዳንድ ዲያቆን ከቅዳሴ ትምህርት ቤት ቅዳሴ ተምሮ ሲመለስ የቀድሞ ጓደኞቹንም ሆነ ሌላውን ሰው ይንቃል ። የቢታንያ ድንጋይም ሱራፌል የሚባሉት መላእክት የሚያመሰግኑትን ምስጋና ሲናገር ጊዜ አይሁድን አስናቀ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

*333 ዋዜማ 681 ን*
*ዘመርሻ/መጋቢ ፡ ዘዲማ ጊዮርጊስ/*
*ጤሜዎስ ወተክለ እልፋ*
*ኀቡራን ስም ነዩሙ እንዘ ፍሉጣን በሥን ፡*
*ለጤሜዎስ ገጹ አኮኑ ዘባን ።*
*ወለተክለ እልፋ ዘባኑ ልዑለ ብርሃን ቀርን ፤*
*እስመ ለገጸ ዝ ጤሜዎስ ድንግለ ብርሃን*



*ኢያእመራ ልበ ዮሴፍ ዐይን ።*

### ትርጉም

ጤሜዎስና ተክለ አልፋ
በመልክ የተለዩ ሲሆን የስም ተባባሪዎች ናቸው ።
የጤሜዎስ ፊት ጀርባ ነውና
የተክለ አልፋ ጀርባም ብርሃን /ቀንዱ ከፍ ያለ ነው ፤
የዚህ የጤሜዎስ ፊት/ የብርሃን ድንግልን
የዮሴፍ ልብ/አይን አላወቃትምና ።

### ምስጢር

በመልክ የማይመሳሰሉ ሁለት ሰዎች በስም አጠራር ብቻ አንድ ይሆናሉ ። ጤሜዎስና ኢትዮጵያዊው ፃድቅ አባ ተክለ አልፋም በተፈጥሮ ፀጋ (በአይን በማየት) አንድ አልሆኑም ። ምክንያቱም ጤሜዎስ ጥንቱን አይን ያልተፈጠረለት ሲሆን ተክለ አልፋ ባለአይን ሆነው ተፈጥረዋል። በተጨማሪም ተክለ አልፋ በስተሁዋላቸው ከጫንቃቸው ላይ የፀጋ አይን የተሰጣቸው ነበሩ ሲባል ጤሜዎስ በስተፊቱም የተፈውጥሮውን አይን እንኳ አላገኘም ። የበሬ ፊትም ቀንዳም እንደሆነ የተክለ አልፋ ፊትም አይናማ ሆነ ። ቅድስት ማርያምን የጠባቂዋ የዮሴፍ ልብ እንዳልተመኛት የጤሜዎስ ፊትም ብርሃን አልበራላትም ማለት በቅኔው ተገልጧል ።

*334 ዋዜማ ስ*
*ጸገየ ወፈረየ*
*ዘበምእት ምእተ በዘመነ ሐጋይ መስፍን*
*ዘበቈለ በርእሰ መቅደላ ቴዎድሮስ ወይን ፤*
*እምዘዚአሁ አስካል አምጣነ ጸግቡ በዐይን*
*እለ ጸዋምያነ ኮኑ አውሮፓውያን*
*እመቅደላ ከመ ይጹም እዝን ።*

### ትርጉም

በመቅደላ ራስ
የበቀለ ቴዎድሮስ /ወይን በበጋ/ መስፍን
ዘመን አበበና መቶ በመቶ አፈራ ፤



www.ethiopianorthodox.org

ከመቅደላ ጆሮ ይገም ዘንድ
ጴዋሚዎችን የሆኑ የአውሮጳ ሰዎች
ከእርሱ ፍሬ በአይን ጠግበዋልና ።

## ምስጢር

በመልካም መሬት ላይ የበቀለ ወይን ብዙ ፍሬን እንደሚያፈራና በፍሬውም ብዙ ሰዎች እንደሚጠግቡ በመቅደላ ራስ ላይ የሚያስደንቅ ጀግንነትን የፈፀሙ አፄ ቴዎድሮስም የሰሩት ስራ ከሌሎቹ ነገስታት ስራ መቶ በመቶ ይበልጣል ። ፆመኞች የሆኑ ሰዎች ከወይኑ ፍሬ እንደሚበሉ አፄ ቴዎድሮስን በመግደል ያልተሳተፉ የአውሮጳ ወታደሮች ለአፄ ቴዎድሮስ የጀግንነት ስራ የአይን ምስክር ሆኑ ። በመቅደላም የተፈፀመውን የጀግንነት ስራ የአውሮፓውያን ጆሮ ሰምቶ እንዳይቀር አይናቸውም አየ በማለት ባለቅኔው የአፄ ቴዎድሮስን የጀግንነት ስራ በቅኔያቸው ምስጢር አድንቀዋል ።

*335 ሥላሴ ስ*
*ዘገብረ ሥላሴ (መምህር ፡ ዘኤልያስ)*
*ማርያም ዘማርያም*
*እኅተ ሰሎሜ ወማርያም*
*እኅቱ ለአሮን ሠዋዒ መሥዋዕተ ብሉይ ኪዳን*
*አኮ ወአኮ እምዮሴፍ ምእመን*
*ወለደት ቃለ ኀታሜ ዓለመ ተድላ ወደይን*
*ብሂል ብሂል ከመ ኵሎን*
*አንስተ እስራኤል ክህለት ወሊደ ሕፃን*
*እምዳዊት ሜልኮል መካን ።*

## ትርጉም

የሰሎሜ እህት
የሆነች ማርያም ያይደለች ፡
የብሉይ ኪዳን መስዋእትንም የሰዋ የአሮን እህት የሆነች
ማርያም ያይደለች ማርያም ከታማኝ
ዮሴፍ የምቾትና የቅጣት አለምን የሚያሳልፍ



www.ethiopianorthodox.org

ቃልን ወለደች ማለት ፡
እንደሁሉች የእስራኤል ሴቶች መካን ሜልኮል
ከዳዊት ልጅን መውለድን ቻለች ማለት ነው ።

## ምስጢር

ቅድስት ማርያም ፡ ማርያም በመባል የሚመስሏት የሰሎሜ እህትንና የአሮን እህትን አልሆነችም ። እነርሱ ከወለዱ በሁዋላ መደንገልን አልቻሉም ። እርሷ ግን ያለወንድ ወልዳ ተደንግለች ። የወለደችውን ኢየሱስንም "ዕሩቅ ብእሲ ወልደ ዮሴፍ ፡ (ተራ ሰው የዮሴፍ ልጅ) ማለት፡ መካኒቱ የእስራኤል ንጉስ የዳዊት ሚስት ሜልኮል ወልዳለች እንደማለት ያለ ነው ። ሜልኮል መውለድን እንዳልቻለች ቅድስት ማርያምም የእግዚአብሄር ቃል የሚባል እግዚአብሄር ወልድን በሩካቤ ፡ በዘር አልወለደችም ይላሉ ባለቅኔው ።

*336 ዘይእዜ ስ*
*ዘገብረ ሥላሴ (መምህር ፡ ዘኤልያስ)*
*ለዘማ ታዴዎስ እንተ ማቀያ*
*ወለዘማዊት ዮሐንስ ዘተናበባ ጽድቆን*
*እመ ስብእ ደለወ ጽድቀ ዘማ*
*ዘታዴዎስ ዘማ እልቦቱ መጠን ፡*
*እስመ ዜናሃ ነገረ በዜና ዕርገቱ ጸራግሞን*
*ወወረደት ትርእይ ገነተ ዳታን*
*ሄሮድያዳ ዘለብሰት ድርዐ ኤልዛቤል ኀጺን ።*
*ወወረደት ትርአይ ገነተ ዳታን ።*

## ትርጉም

ታዴዎስ ያስቃያት ዘማና
ዮሃንስ የተናገራት ዘማ ፅድቃቸውን
ሰው ቢመዝን የሃዋርያ ታዴዎስ
ዘማ የሆነች የዘማ ፅድቅ ልክ የለውም ፡
ጸራግሞን በእርገቱ ዜና ዜናዋን ነግሯልና ፡

የዳታንን ገንትም ልታይ ወርዳለችና
የኤልዛቤል ብረት ጥሩርን የለበሰች ሄሮድያዳም
የዳታንን ገንት ልታይ ወርዳለችና ።

## ምስጢር

አንድ ሰው ሁለት ነገሮችን በሁለት የሚዛን ጫፎች ሲመዝን በአንድ በኩል ያለው ተመዛኝ ይደፋል (በሌላ በኩል ያለውን ይመዝን ዋል) ። ታደዎስ በነፋስ የሰቀላት የዘማ (በዝሙት አዳሪ)ሴት ስራም ዮሃንስ ከገስፃት ከሄሮድያዳ ስራ ጋር ሲነፃፀር የታደዎስ ዘማ ዕድቅ አመዝኗል ። የተፈጥሮን ውበት ተመልክታ ማድነቅ የምትፈልግ ሴት የተክል ቦታን ለመጎብኘት እንደምትወርድ ሄሮድያዳም የዳታንን ዱካ ተከትላ በመሬት ተዋጠች ። ታደዎስ በነፋስ አውታር የሰቀላት ዘማ ጴጥሮስና ጳውሎስ በነፋስ አውታር እንደሰቀሉት እንደ ንጉስ ጸራግሞን ሆነች ።

## ታሪክ

ሊቀ ሃዋርያት ጴጥሮስና ጳውሎስ የክርስቶስን ወንጌል እያስተማሩ ጸራግሞን ከሚባል ንጉስ ቤተ መንግስት ገቡ ። ንጉሱ ጸራግሞን ትምህርታቸውን ካዳመጠ በሁዋላ “ወፍ አይናን ያጠፋት አንዲት ሴት ልጅ አለችኝ ፡ እርሷን አድኑልኝና በአምላካችሁ አምናለሁ” አላቸው ። እነርሱም የጠየቃቸውን ፈፅመውለት ወደፈልጳስ “አገር ለማስተማር እንደሄዱ እንዶሁን የተባለ አገር ንጉስ መጥቶ ጸራግሞንን” ስለሁለቱ ጠንቋዮች ለምን ዝም ትላለህ? ምድርን በመድሃኒታቸው ሳያጠፉ ለምን አናጠፋቸውም?” አለው ። በዚህ ጊዜ ንጉሱ ጸራግሞን ጴጥሮስንና ጳውሎስን ይዘው እንዲያመጡለት አስር ሺህ ሁለት መቶ ፈረሰኞች ወታደሮቹን ላከ ። ሰራዊቱም በጴጥሮስና በጳውሎስ አምላክ አምነው ጴጥሮስና ጳውሎስንም ሳይዙ ወደ ጸራግሞን ተመልሰው የጦር መሳሪያቸውን አስረከቡት ። ከዚያም ጊዜ ጀምሮ ንጉሳቸው ያመኑበት ኢየሱስ ክርስቶስ እንጂ እርሱ (ጸራግሞን) አለመሆኑን ገለጡለት ። እርሱም ይህን ሲሰማ ተናዶ በክርስቶስ ያመኑት አስር ሺህ ሁለት መቶ ወታደሮች ታስረው በልዩ ልዩ ስቃይ እንዲሰቃዩ አደረገ ።

ከዚህ በሁዋላ ጸራግሞን አስር ሺህ አራት መቶ አግረኛ ወታደሮች ዘምተው ጴጥሮስና ጳውሎስ የሚሰብኩባትን የፊልጳስን አገር ያፈራርሷት ዘንድ አወጀ ። ሰራዊቱ ከመዝመቱ በፊት ጴጥሮስና ጳውሎስ ወደ



ንጉሱ ወደ ጸራግሞን ቤተ መንግስት ተመልሰው ፡ “ንጉስ ሆይ በእኛ ምክንያት አገር አታጥፋ ። ከፊትህ አለን” አሉት። ጸራግሞንም ወዲያውኑ በጴጥሮስና በጳውሎስ ራስ ላይ የጋለ የብረት አክሊል እንዲደፋባቸውና ቁልቁልም ተሰቅለው እንዲሰቃዩ አደረገ ። በዚህ ምክንያት ጸራግሞን ከነተከታዮቹ በነፋስ አውታር ቁልቁል ተሰቅሎ የስቅላት ስቃይን ከቀመሰ በሁዋላ ከስቅላቱ ወርዶ በጴጥሮስና በጳውሎስ አምላክ ከነሰራዊቱ ማመኑ ተፅፏል (ስንክ· ሐምሌ 15) ።

*337 መወድስ/ስ*
*ዘመኰንን (አለቃ)*

*ኵሉ ይትዌለጥ በኍን ዘመን*
*ፍዳ ዘሠጠጠ ሳዖል አልባሰ ዳዊት ገርዜን*
*አምጣነ ዳዊት ሰበረ መጽሔተ ሳዖል ብርሃን ።*
*ወማየ ብሔራ ለሰማርያ*
*ሰናክሬም ፍዳ ዘአንቅዐ እምሕዝቅያስ ዐይን*
*እስመ ያማስኑ ንኡሳን*
*ቈናጽለ ሕዝቅያስ ባዕድ ዐፀደ ሰናክሬም ወይን ።*
*ጸሐፉሂ መራዳኒሁ ለኢዮርብዓም ካህን*
*ፍዳ ምድረ ባቢሎን በነነዌ ወፍዳ ነነዌ በባቢሎን ፡*
*ዝኒ ነገር ሕሰወ ከመ ኢይኩን*
*መንበረ መፃጉዕ እስመ ተረክበ በርእሰ መፃጉዕ ከላውዴዎን ።*

## ትርጉም

ሁሉ በዘመን ርዝመት ይለወጣል ፤
ሳኦል የዳዊት ግምጃ ልብሶችን ስለመቅደዱ ፈንታ
የሳኦል/ብርሃን መስታዎትን ዳዊት ስብሯልና ፤
የሰማርያ አገር ውሃንም
ሰናክሬም ከህዝቅያስ/ምንጭ ስለማመንጨቱ ፈንታ
ታናናሾች የባእድ ህዝቅያስ
ቀበሮዎች የሰናክሬም ወይን ቦታን አጥፍተዋልና ።
የካህን ኢዮርብአም ወራሪዎችም የባቢሎን



www.ethiopianorthodox.org

ምድር ብድርን በነነዌ ፡ የነነዌን ብድርም በባቢሎን ፅፈዋልና ፤
ይህም ነገር እሰትን እንዳይሆን
የመፃጉእ አልጋ በመፃጉእ ራስ/ከላውዴዎን ተገኝቷልና ።

## ምስጢር

በዘመን ብዛት ብረትና ብር ይዝጋሉ ፤ ወርቅም ቢሆን ይዝጋል ። ሰውም የሰራው ስራ ይዘዋወራል (ይለወጣል) ። ጋሬጣ ልብስን እንደሚቀደው የእስራኤል ንጉስ ሳኦልም ከርሱ ቀጥሎ የነገሰ ዳዊትን ቢያጠቃውም መስታዎትን እንደመሰበር ዳዊት የሳኦልን ስልጣን ያዘ ። ምድርን ቆፍሮ ውሃን እንደማፍለቅ ሰናከሬም ሰማርያ የምትባለውን አገር ከህዝቅያስ ለመቀማት ሲዘምት ፡ ቀበሮዎች የወይንን ቦታ እንደሚያጠፉ የህዝቅያስ ረዳቶች የሰናከሬምን አገር አጠፉ ። ፀሃፊዎችም በትንሹ መዝገብ የመዘገቡትን በትልቅ እንደሚፅፉ የኢዮርብአም ወራሪዎችም የባቢሎንን ፍዳ (በቀል) በነነዌ ፡ የነነዌንም ፍዳ በባቢሎን አደረጉ ። ከፍዳ መዘዋወርም የተነሳ መፃጉእ ተኝቶበት የኖረውን አልጋ በራሱ ላይ ተሸከመው በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

*338 መወድስ (707)ኀ*
*ኀጢአተ ሕዝብከ ርኢ ከመ ዘኢርእየ*
*ወድልወተ ዚአከ እኮ እሞተ ርኅራኄ ድኂን ፤*
*እስመ ለከሂል ደዌከ ኢይፈውሶ ሰኢን*
*እምርእሰ አርምሞ ቀዳማይ ኪን*
*እስከ ተናግሮ እግረ ብርሃን*
*አንተ ትድኅክ መዓተ እግዚአብሔር ሕፃን ።*
*ትዌልጥሂ በበዘመኑ በዘይትዌለጥ ዘመን*
*ኀዘነ በትፍሥሕት ወትፍሥሕተ በኀዘን ፤*
*እስመ ብርዐ መዓት አንተ በኀበ ምናሴ ሐፂን*
*ወቀሊል በኀቤከ ክቡደ ኀጢአት ሰሎሞን ።*

## ትርጉም

ቀዳማዊ ጥበብ ከሆነ ከራስ/ዝምታ
እስከ መናገር/የብርሃን እግር መእትን የምትድህ
እግዚአብሄር/ህፃን! መቻል/ደዌህን
መሳን (ማቃት) አይፈውሰውምና
የህዝብን ሃጢአት እንዳላየ እይ ፤
ከርህራሄ/ደዌ መዳንም አግባብህ አይደለም ።
በሚለወጥ ዘመንም በእየዘመኑ አዘንን
በደስታ ፡ ደስታንም በአዘን ትለውጣለህ ፤
በምናሴ/ብረት ዘንድ የቁጣ ብር (ገለባ) ነህና
ሃጢአቱ የከበደ ሰሎሞንም በአንተ ዘንድ ቀላል ነውና ።

## ምስጢር

አንዳንድ ብልህ አባት ልጆቹን ሲመክር "ልጆቼ! አይቶ እንዳላዩ ፡ ሰምቶ እንዳልሰሙ መሆን ነው ፤ ሁሉንም ማውራት አይገባም" ይላቸዋል። ባለቅኔውም አምላክ ሆይ ሁሉን የምታይና የምታውቅ አምላክ ስትሆን ሃጢአታችንን እንዳልታየና እንዳልታወቀ ነገር ተውልን። ደዌው የፀናበትም ህመምተኛ ከሞት እንደማይድን አንተም ርህራሄህን አትተውብን ። ምክንያቱም የሚገድልን በሽታ መድሃኒት እንደማይፈውሰው ችሎታህንም ማቃት ስለማያስቀረው ነው ። ህፃንም አጎንብሶ በእግሩና በእጁ እንደሚድህ እንዲሁም አንተ አምላካችን በእውቀትም ፡ በመናገርም መእትን ታርቃለህ ። ባለፀጋም ልብሶችን እየለዋወጠ እንደሚለብስ አንተም ሃዘንንና ደስታን ታፈራርቃለህ ። ብር (ገለባ)ና ብረት ቢመዘኑ የብረቱ ክብደት እንደሚበልጥ የእስራኤል ንጉስ የነበረውን የምናሴን ከባድ ሃጢአትም ያንተ ቸርነት አስተሰረየው (አቃለለው) ። አንዱ ከባድ እቃ በሚበልጠው ሌላ ከባድ እቃ ዘንድ ቀላል እንደሆነ ከባዱን የሰሎሞንን ሃጢአትም አቃለልኸው በማለት ባለቅኔው የአምላካቸውን ይቅር ባይነት በቅኔያቸው ገልጠዋል ።

*339 ሥላሴ (724)ኀ*
*ዘገብረ መድኀን (አለቃ ፡ ዘሴመን ሥላሴ)*

*ደምሰሰ አሠረ ፍና*
*ትዕይርተ አርዌ ወእሕማር ፡*



www.ethiopianorthodox.org

*እስመ ለሐመር መካህ ሑረቱ እንዘ ይፄዐን ዘባኖ ፤*
*ወበክንፍ ዘበእንግድዓሁ አርዌ ምድር ይትፌኖ ።*
*ዮሐንስሰ ሑረተ ዘአርዌ ወዘአሕማር መኒኖ*
*በአዝኑ የዐርግ ደብረ አድኅኖ ፤*
*ወለእመ ሄሮድስ ይትጌየል ለአማስኖ*
*በፈረሱ ኢቀደመ እዝኖ ።*

## ትርጉም

የእባብና የመርከቦች
ተግዳሮት የመንገድ ፍለጋን አጠፋ
የትምክህተኛ መርከብ አካሄዱ ጀርባውን እየተጫነ ነውና ፤
የምድር እባብም በደረቱ ባለ ክንፍ ይላካልና ።
መጥምቁ ዮሃንስ ግን የእባብንና የመርከቦችን አካሄድ ንቆ
በጆሮው የማዳን ተራራን ይወጣል ፤
ሄሮድስም ለማጥፋት ቢበረታታ
በፈረሱ ጆሮውን አልቀደመም ።

## ምስጢር

እባብ በመንገድ ሲንሻለልና መርከብም በባህር ላይ ሲሄድ ፤ ለመንገዳቸው ፍለጋ የለውም ። መጥምቁ ዮሃንስ ግን እነርሱ ፍለጋቸውን እንዳጠፉ ፍለጋውን አላጠፋም ። እባብ በልቡ ፡ መርከብም በሆዱ እንደሚሄዱ ሳይሄድ ዮሃንስ ከእንገቱ በላይ ወደ ሰማይ ወጣ ። እባብን መንገደኛ እንደሚገድለውና መርከብን የባህሩ ማእበል እንደሚያሰጥመው ፈረሰኛው የገሊላ ንጉስ ሄሮድስም በአየር (በህዋ) ላይ እየተመላለሰ "ዋርላ አትውረስ ፤ ድንበር አታፍርስ" እያለ የገሰፀውን የመጥምቁ ዮሃንስን ራስ ሊደርስበትና ሊያጠፋው አልቻለም ይላሉ ባለቅኔው (ስን·መስከረም 2) ።

*340 ጉባኤ ቃና*
*ዘገላነሽ ሐዲስ (እማሆይ ፤ ዘጽላሎ/ስ*
*አዖደት ይስሐቅ ሕማመ ሥጋ ዘጻንዐ*
*ባቲ ዕቤርት ሰይፈ አብርሃም በግዐ ።*



## ትርጉም

የስጋ ህመም/ይስሃቅ የፀናባት
ባልቴት/የአብርሃም ሰይፍ በግን አዞረች ።

## ምስጢር

እንድ የአምልኮ ባእድ ተገዥ የሆነች ሴት በታመመች ጊዜ የህመሟን መነሻ ከማይታወቅ ከረቂቅ መንፈስ ቁጣ ጋር ስለምታያይዘው፤ ለምታምንበት ረቂቅ መንፈስ መስዋእት የምታደርገውን በግ ዙሪያውን ታዞራለች ። የይስሃቅ እንገት ያልተቆረጠባት የአብርሃም ሰይፍም ለይስሃቅ ቤዛ ሊሆን የቀረበውን በግ አረደች በማለት ባለቅኔዋ እመስጥረዋል ።

*341 ዘአምላኪየ /ስ*
*በማእደ ርእሱ ሰፉሕ ወበበትረ ልቡ ዘጻንዐ*
*ዐቀበ ተክለ ሃይማኖት ወአምላክ ሠርዐ ፡*
*ማእደ ሮሜ መስቀለ ወእሚነ ኬፋ በግዐ ።*

## ትርጉም

በራሱ/ማእድ የሮም ማእድ/ መስቀልን
አምላክ ሰራ ፤ ተክለ ሃይማኖትም
የጴጥሮስ እምነት/በግን በጠና በትር/ ልቡ ጠበቀ ።

## ምስጢር

ባለቤት ምግብን በማእዱ (በመሶቡ) እንደሚሰራ እግዚአብሄር ወልድም በሮማውያን ህግ መሰረት በመስቀል ተሰቅሎ መሞት ተፈረደበት ። እረኛ በግን በበትር እንደሚጠብቅ ተክለ ሃይማኖትም የጴጥሮስን እምነት በልቡ እፀና በማለት ባለቅኔው የኢየሱስ ክርስቶስን በመስቀል ላይ መሞትና የተክለ ሃይማኖትን የእምነት ፅናት በቅኔያቸው ምስጢር ተርከዋል ።

*342 ዋዜማ (1086)ን*
*ዘተጠምቆ (መምህር)*



www.ethiopianorthodox.org

ስምዖን መፍቀሬ ሰብእ
መሠግራነ ሰብእ ረሰይከ ከናፍሪከ አርዳእ ፤
ሕኑጸ መቃብረ ሥጋ ይሰመይ በአፍአ
ነገደ ፋሬስ ሥጋከ ዘበሊዐ እክለ ረስዐ
እንዘ በአፍአሁ ይመስል ሠናየ ሰብእ
እስመ ውስጡ አፅፅምተ መልዐ ።

## ትርጉም

ሰውን ወዳጅ/ስምኦን!
ከንፈሮችህ/ተማሪዎችን ሰዎችን አጥማጆችን አደረግህ ፤
እህልን መብላት የረሳ ስጋህ/የፋሬስ ነገድ
የተገነባ የስጋ መቃብርን በውጭ ይባል ዘንድ
በውጩ ያማረ ሰውን ሲመስል
ውስጡ በአጥንቶች ሞልቷልና ።

## ምስጢር

መፍቀሬ ሰብእ (ሰውን ወዳጅ) የሚባል ኢየሱስ ክርስቶስ አሳ አጥማጆች የነበሩ ተማሪዎች ሃዋርያትን "አሳ ማጥመዳችሁን ትታችሁ ተከተሉኝ ። እኔ ሰው አጥማጆችን (አስተማሪዎችን) አደርጋችሁዋለሁ" እያለ ከየባህሩ እንደጠራቸው በላኤሰብእ የሚባለው የስምኦን ከንፈሮች የሰውን ስጋ ጎረሱ ። ትምህርቱን የተቃወሙትን ፈሪሳውያንንም "እናንተ ግብዞች ፃፎችና ፈሪሳውያን በውጭ አምረው የሚታዩ በውስጥ ግን የሙታን አጥንት ፣ ርኩሰትንም ሁሉ የተሞሉ በኖራ የተለሰኑ መቃብሮችን ስለምትመስሉ ወዮላችሁ" በማለት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ወቀሳቸው ሰውን እንደ እህል ምግቡ ያደረገ በላኤሰብእ ስምኦንም በተፈጥሮው ሰው ሆኖ ሳለ በውስጡ የበላቸው የሰዎች አጥንት ሞልቶበታል በማለት ባለቅኔው አመስጥረዋል (ስንክ· የካቲት 16) ።

## ታሪክ

ፈሪሳውያን "ሰው የሚፀድቀው በግል ህይወቱ መልካም አካሄድና ህግን በመፈፀም ነው" በማለት ያስተማሩ የአይሁድ ሃይማኖት መምህራን ናቸው ። በኦሪት ህግ ላይ የአባቶችን ወግና የራሳቸውን ትእዛዝ ጨመሩ ። ለህዝቡም ከባድ ሸክም የሆነ ስርአት ሰሩ ። በዚህም ምክንያት ኢየሱስ ክርስቶስ በትምህርቱ "ግብዞች" እያለ ነቀፋቸው) ማቴ·15 ፤ 1—4 ፤ 23 ። ሉቃ· 11 ፤ 37—44 ። የሃዋ·15 ፤ 5) ።

343 ሥላሴ (730)ኀ
ዘደስታ(መምህር ፡ ዘዋሸራ)
ወለጠተ ርግዘ ኖኀ
በይነ በላዔ ሰብእ ሕገ ልማድ ፡
ሕፀፀ ማየ ባሕር ኢትንግር ይእዜ ለበላዔ ሰብእ ዘፀምዐ
እስመ ትብል ውስተ መድሎትከ ማየ ባሕር መልዐ ፡
ወእንዘ አርዌ ምድር ይትሜሀር በግብሩ የዋሃተ ርግብ ካልአ
በላዔ ሥጋ ሰብእ ዘተጸውዐ
በጽላሎታ ለዕፅ ረከበ ጽንዐ
ወድካመ ዘኄጋይ መዊዐ

## ትርጉም

የኖህ ርግብ ሰለበላኤ ሰብእ
የልማዱን ህግ ለወጠች ፡
የባህር ጉድለትን ስተጠማ በላኤ ሰብእ ዛሬ እንዳትነግር
በሚዛንህ ውስጥ የባህር ውሃ ሞላ ትላለችና ፡
የምድር አባብም ሌላ የርግብ የዋህነትን በስራው ሲማር
የተጠራ የሰው ስጋ በላተኛ
በእንጨት ጥላ ጥንካሬን አገኘ
የበደል ድካምን መሸነፍንም አገኘ ።

## ምስጢር

አንዳንድ ደግ ሰው ለወዳጅ ብሎ ልማዱን ይተውና የወዳጁን ፈቃድ ያፈፅማል ። በኖህ ርግብ የተመሰለች ቅድስት ማርያምም እንደኖህ ርግብ አልሆነችም ። የኖህ ርግብ የጥፋት ውሃን ጉድለት ለኖህ ነግራ ነበር ። ቅድስት ማርያም ግን በላኤ ሰብእ ስምኦን ለድሃው ያጠጣው አንድ እፍኝ ውሃ በሚዛን የሰባ ስምንት ሰዎች ነፍሳትን እንዲመዝን አደረገችው ።





www.ethiopianorthodox.org

አንዱ ሰው ከሌላው ትምህርትን እንደሚያገኝ የምድር እባብም የርግብ የዋህነትን በስራው አሳየ ። እርሷ በየዋህነት እንቁላሏን በአፉ ውስጥ ጣለች ። እርሱም ኖህ ከመርከቡ አውጥቶ በጥፋት ውሃ ውስጥ እንዳይጥለው እንቁላሏን አልበላም ። ከዚህም ሌላ ለአንዱ በሽተኛ የማይስማማው ነገር ለሌላው እንደሚስማማው ደኸው እባብ ዘዌ በምትባል እንጨት ጥላ ይደክማል ። የሰውን ስጋ በመብላት አውሬ የሆነው በላኤ ሰብእ ስምአን ግን የእንጨት ምሳሌ በሆነቸው ማርያም ጥላ ህይወትን አገኘ በማለት ባለቅኔው ስለማርያም አማላጅነት በተአምረ ማርያም የተፃፈውን በቅኔያቸው አስረድተዋል ።

*344 ሥላሴ (728)ኅ*

*ዘደንቁ (አሊቃ)*

*ለአሪት አረፋቲሃ*

*በኀይሉ ነሥተ መልአከ ኃይል ፡*

*ሰማዕተ ሐሰት ጠማረ አምጣነ በባዕል አንሥአ*

*ወባሕራን በውስተ ሃማሁ ለባዕል ቦአ ፡*

*ተናግሮዝ ሐሰት ባሕቱ እመ መልአከ ኀይል ሠርዐ*

*ለምንት ዳንኤል ነቢየ አፍአ*

*ማእከለ ረበናት አይሁድ ሐሰተ ከልአ?*

*ወተከፍሎ ኀቡዘሙ መጽአ?*

## ትርጉም

የአሪትን ግድግዳዎች

የሃይል መልአክ በሃይሉ አፈረሰ ፡

የአሰት ምስክር ደብዳቤን በባለፀጋ አንስቷልና

ባህራንም በባለፀጋ ድካም ሃብት ገብቷልና ።

ግን ይህን አሰት መናገርን የሃይል መልአክ ከሰራ ፡

የውጭ ነቢይ ዳንኤል በአስተማሪዎች

አይሁድ መካከል አሰትን ለምን ከለከለ?

መከፈልስ ወደእነርሱ ለምን መጣ?

## ምስጢር

አንዳንድ ሃይለኛ ሰው በተጋፊነት የሌላውን ቤት ግድግዳ ያፈር



ሳል። ተአምረኛ የሚባለው መልአክ ቅዱስ ሚካኤልም የኦሪትን ትእዛዛት አልጠበቀም ። ምክንያቱም አሪት "በአሰት ምስክር አትሁን" ብትል እርሱ በባለፀጋው ላይ የአሰት ደብዳቤን ፃፈበት ። የሌላውንም ገንዘብ መውሰድ በኦሪት የተከለከለ ሲሆን የባለፀጋውን ሃብት ለባህራን አወረሰው ። ባለፀጋውም "ባህራንን እንደደረሰ ግደሉት" በማለት የፃፈውን ደብዳቤ በተአምር ለውጦ የሞቱን ቃል የጋብቻ ቃል አድርጓል ። ባለቅኔው አሰት ከተፈቀደም ዳንኤል ሁለቱን የአይሁድ መምህራንን በአሰት ነገራቸው? ለምን እንደግራምጣ ሰነጠቃቸው በማለት ራሳቸውን ጠይቀዋል (መፅሃፈ ሶስና) ።

*345 መወድስ (734)ኅ*

*ሆሣዕና ሰማይ በምድር አመ አንሶሰወ*

*በሞተ ሰብእና ሕይወተ ዘይዌልጦ አንሥአ ፡*

*ባሕቱ አብርሃም ሶበ አካለ ይስሐቅ ሦዐ*

*ይስሐቅ ዝንቱ አሐደ በግዐ*

*ረከበ ወአምጽአ*

*እምሆሣዕናሁ ለይስሐቅ መንገለ ይስሐቅ መጽአ ።*

*ኤርምያስሂ ነቢየ ጽድቅ ሶበ በእንተ ጽድቅ ተገፍዐ*

*ለኤርምያስ ተገፍዖቶ ተመጠወ እብነ አፍአ ፡*

*ወደዌ ነጋዢ ዖዝያን ሐሜለተ ዖዝያን ኀብአ*

*ሥርዓት ቀዳማዊ በዖዝያን ኀበ ጠፍአ ።*

## ትርጉም

የሰማይ ሆሳእና በምድር በተመላለሰ ጊዜ

በሰውነት ሞት የሚለውጠው ህይወትን አነሳ ፡

ነገር ግን አብርሃም የይስሃቅን አካል በሰዋ ጊዜ

ከይስሃቅ ሆሳእና

ወደይስሃቅ ከመጣ ዘንድ

ይህ ይስሃቅ አንድ በግን አገኘ ።

የእውነት ነቢይ ኤርምያስም ስለፅድቅ በተነገረ ጊዜ

የኤርምያስን መገፋት የውጭ ድንጋይ ተቀበለ ፡

የቀድሞው ስርአት በአዝያን ከጠፋ ዘንድም

የንጉስ አዝያን ደዌን የአዝያን መጠምጠሚያ ሸሸገ ።



www.ethiopianorthodox.org

## ምስጢር

በጥንት ጊዜ አንድ ሰው ወደገበያ ሄዶ በአንድ እቃ ሌላውን እቃ ለውጦ ይመለስ ነበር ። እግዚአብሄር ወልድም በዚህ አለም ሰው ከሆነ በሁዋላ በስጋው ሞት ህይወትን አስገኘ ። የስጋ ነጋዴ አንዱን በግ አርዶ ስጋውን ይሸጥና ሌላ በግ ይገዛል ። አብርሃምም ልጁን ይስሃቅን በአሳቡ (በቁርጥ ውሳኔው) ከሰዋው በሁዋላ ለልጁ ቤዛ የሆነ በግን ሰዋ ። ባለቤት እንግዳን እንደሚጋብዝ የአብርሃም ልጅ የይስሃቅ ቤዛ የሆነው በግም የሆሳእና (የክርስቶስ) ምሳሌ ሆነ ። በጠብ ጊዜ ለዘመዱ እንደሚጋረድለት ድንጋይ የነቢይ ኤርምያስን መገረፍ ተቀበለ ። ሌላው ዘመድም በደለኛ ዘመዱን እንደሚሸሽገው የአዝያንን ለምጥ መጠምጠሚያው ሰወረው ። መብራትም በነፋስ እንደሚጠፋ የቤተ ክህነት ስርአት በአዝያን ቤተ መቅደስ ውስጥ መግባት ተለወጠ ይላሉ ባለቅኔው ።

*346 ዋዜማ (7.38)ኀ*

*ለእመ አይሁድ ዘተዐውሩ*
*ለከብካበ ኪሩብ ስብሐት ኀበ ሆሣዕና ኢመጽኡ*
*አእባነ ዘኢተዐሡሩ መንክራት ጸውዑ*
*በግብር ስብሐተ ቤተ ሆሣዕና ይምልዑ ፡*
*ወመርገመ ኤልሣዕ ነደ ሕፃናት ያጥፍኡ*
*ተሣልቆ ፍኖቶሙ ኀጥኡ ።*

### ትርጉም

ለኪሩብ ሰርግ/ምስጋና
የታደሙ (የተጠሩ) አይሁድ ወደሆሳእና ባይመጡ
በግብር/ምስጋና የሆሳእና ቤትን ይሞሉ ዘንድ
ያልታደሙ ድንጋዮችን ተአምሮች ጠሩ ፤
ህፃናትም የኤልሳእ ርግማን/እሳትን ያጠፉ ዘንድ
መዘባበት መንገዳቸውን አጡ ።

## ምስጢር

በወንጌል ምሳሌ አነጋገር እንደተባለው ለሰርግ የታደሙት እድምተኞች (ተጠሪዎች) ሳይመጡ ቢቀሩ የባለሰርጉ አሽከሮች በሜዳ ያገኟቸውን ሰዎች አምጥተው የሰርጉን ቤት ሞልተውታል ። ፈጣሪያቸውን



አውቀው እንዲያመሰግኑ በነባቢት ነፍስ እውቀት የተፈጠሩ አይሁድም ሆሳእና የተባለ ክርስቶስን አናመሰግንም ቢሉ ፡ አእምሮ ማእዛን የሌላቸው ድንጋዮች ፈጣሪያቸው ሆሳእናን አውቀው እንደመላእክት አመሰገኑት ይላሉ ባለቅኔው ። ህፃናት የእሳት ቃጠሎ ሲነሳ እሳቱን ማጥፋት ባለመቻላቸው ተጨንቀው መሄጃ መድረሻ እንደሚያጡ ኤልሳእ የረገማቸው የቤቴል ህፃናትም በነቢዩ በኤልሳእ ላይ የተዘባበቁትን መዘባበት በምስጋና ለወጠባቸው በማለት ቅኔው ተመስጥሯል (2ነገስ·2፡23-24) ።

*347 ዋዜማ ስ*
*ዘሞገስ (መምህር ፡ ዘግጼን)*

*ክበበ ፀሐይ ደብረ ክርቤ*
*ፈለገ ብርሃናት መስቀለ እመ ውስተ ዓለም ትክሁ*
*ተነፅበ በማየ ምሳሌ ዘኪሩብ መልክኡ ፤*
*ወለባሲያን መስቀለ በአክናፈ እሳት መጽኡ ፤*
*እስመ ውስተ ጸባብ አንቀጽ ኀቤሃ ይባኡ*
*ደብረ ክርቤ ትቤሎሙ ንዑ ።*

### ትርጉም

የፀሃይ ክበብ/ደብረ ክርቤ
የብርሃናት ወንዝ/መስቀልን በአለም ስታፈስ
መልኩ የኪሩብ መልክ የሆነ በምሳሌ ውሃ ታጠበ ።
መስቀልንም ለባሾች በእሳት ክንፎች ወጡ ፤
ያን ጊዜ በጠባብ በር ይገቡ ዘንድ
ደብረ ክርቤ ኑ ትላቸዋለችና ።

## ምስጢር

ወንዝ ከላይ ሲፈስ በታች ያለው በውሃው ይታጠባል ። የፀሃይ አምሳያ የሆነች ደብረ ክርቤ የምትባል የግሸን ማርያም ደብር ብርሃንን ያበራ መስቀልን ስታገኝ የኪሩብ አምሳያን አገኘች ። ልብሳቸውን መስቀለኛ አጣፍተው የሰበሱ ካህናትም ይዘምሩባታል ። በክርስቶስ መስቀል ያማተቡ ሁሉም ከእሳት በወንጌሉ ይድኑ ዘንድ ደብረ ክርቤን ይማጠናሉ በማለት ባለቅኔው ያስረዳሉ ።



www.ethiopianorthodox.org

*348 ዕዝል ጉባኤ ቃና/ስ*

*ዘምሥራቅ (አለቃ ፡ ዘኤልሻማ)*

*መአንዝር ኢያፎር አመ ሰንቀወ መሰንቆ ዳዊት ብጹዕ*
*በክሣድ ወረደት ወለተ ዳዊት አንብዕ ።*

## ትርጉም

አዝማሪ/ባህታዊ የምስጉን ዳዊት መሰንቆን በመታ ጊዜ
የዳዊት ልጅ/እንባ በአንገት ወረደች ።

## ምስጢር

ወንድ አዝማሪ መሰንቆውን እየመታ ሲዘፍን ሴት አዝማሪ በአንገቷ እስክስታ እየመታች ወደታች ትወርዳለች ። ባህታዊም እንደ ዳዊት ሲያዝንና ሲያለቅስ እንባው በአንገቱ ተንኳለለች በማለት በፆምና በፀሎት ተወስነው የብቸኝነት አለማቸውኝ የሚገፉ መናኞችን አኗኗር ባለቅኔው ገልጠዋል ።

*349 ዕዝል ጉባኤ ቃና/ስ*

*ዘምሥራቅ (አለቃ ፡ ዘኤልሻማ)*

*ጸግቡ ዮሴፍ ወሰሎሜ ማዕደ ራሄል ተገፍዖ ፡*
*እስመ ቀርበ ሎሙ በመሶበ ወርቅ መሊኦ ።*

## ትርጉም

ዮሴፍና ሰሎሜ የራሄል ማእድ/መገፋትን ጠገቡ ፡
በወርቅ መሶብ ሞልቶ ቀርቦላቸዋልና ።

## ምስጢር

በመሶብ ሞልቶ የቀረበ ምግብን የተራቡ ሰዎች ብልተው ይጠግባሉ በመሶበ ወርቅ በተመሰለች ፡ የንፁህ ወርቅ መሶብ አንቺ ነሽ እየተባለች በምትመሰገን በማርያም ላይ የደረሰ መገፋትም አብረዋት ወደግብፅ በተሰደዱ በዮሴፍና በሰሎሜም ተፈፀመ ይላሉ ባለቅኔው ።

*350 መወድስ/ስ*

*ዘጥፋነህ (አለቃ ፡ ዘቦታ ኪዳነ ምህረት)*

*ቀተሎሙ ለእለ ኬፋ በዐውደ አርዮ ተገፍዖ*
*መዓዛ ስቅለት ኮለ ናርዱ ዘማ ዘትትቀብዖ ፡*
*ጎበ ላዕል ወታሕት ከመ ይዝርዖ*
*ላእከ አርባዕቱ ገቦ ዓለም ነፋስ እስመ አምጽአ ።*



## ትርጉም

ዘማ የምትቀባው የስቅላት/ሽቶ መአዛም
በአርዮ አደባባይ/ግፍ እነጴጥሮስን ገደላቸው ፡
ወደላይና ወደታች ይበትነው ዘንድ
የአራቱ የአለም ጎን አገልጋይ/ነፋስ አምጥቶታልና ።

## ምስጢር

በአራቱ ማእዝነ አለም የሚነፍስ ነፋስ ያመጣው ሽታ በአደባባይ ያሉትን ሰዎች ያውዳቸዋል ። በአርዮ የተፈፀመው ግፍም በእነጴጥሮስ በስቅላት ተፈፀመባቸው። ሽቶን ዘማዊት ሴት እንደምትቀባው ሃዋርያው ታዴዎስም በአንዲት ዘማዊት ሴት እንዲፈፀም አደረገ። ሽቶን ነፋስ እንደሚያመጣው ዘማዊቲቱም የተሰቀለችው በነፋስ አውታር ነው። መአዛ ወዳላይና ወደታች እንደሚሰራጭ ስቅላትም ከምድር በላይ ከሆነ በሁዋላ ዘማዊቲቱ ከተሰቀለችበት ወደምድር ወረደች ማለት በቅኔው ተመስጥሮበታል ።

*351 ዕዝል ጉባኤ ቃና ስ*

*ዘጥበቡ ካሣ (አለቃ ፡ ዘቦገና ግራር ኢየሱስ)*

*አንክሮ ይደሉ ለአረጋዊ/ዘሕገ ተሰዶ ሰበከ ፡*
*ዳግሚት ሰማይ አምጣነ አብቈለት ሦከ ።*

## ትርጉም

የመሰደድ ህግን የሰበከ ሽማግሌን ማድነቅ ይገባል ፡
ሁለተኛ ሰማይ እሾህን አብቅላለችና ።

## ምስጢር

እሾህን ማብቀል የምድር ባህርይ ነው እንጂ የሰማይ ባህርይ አይደለም ። በመሆኑም በምድር ፈንታ የተገላቢጦሽ ሰማይ እሾህን



www.ethiopianorthodox.org

ብታበቅል ያስደንቃል ። በሰማይ የተመሰለች (የብርሃን መብራትን የተሸከምሽ ሁለተኛይቱ ሰማይ አንቺ ነሽ ተብላ የምትመሰገን) ቅድስት ማርያምንም ከዮሴፍ ጋር ወደ ግብፅ በተሰደደች ጊዜ እሾህ ወጋት ። ሰማይ እሾህን ስታበቅል ያየ ሽማግሌ ሊደነቅ እንደሚችል ከማርያም ጋር ወደ ግብፅ የተሰደደ ሽማግሌ ዮሴፍም እንደማርያም እሾህ ወጋው ይላሉ ባለቅኔው ።

*352 ዋዜማ (750)ኀ*

*ዛተክለ ሥላሴ (አለቃ)*

*ግብርናተ ዘካልኡ*
*መድኃኔ ዓለም አግዓዚ ዲበ ግዕዛኑ ወሰከ*
*ወረገመ ርእሶ ከመ ያብቁል ሦከ ፡*
*እስመ ፈነዎ አቡሁ እሰከ ኀቤነ ተልእከ*
*እንዘ ይብል ብላዕ በሐፈ ገጽከ*
*ተጸፍዖተ ዘድልው ለከ ።*

## ትርጉም

የሌላውን አገልጋይነት
መድሃኔ አለም በነፃነቱ ላይ ጨመረ
እሾህን ያበቅል ዘንድም ራሱን ረገመ ፡
ለአንተ ዝግጁ የሆነውን በጥፊ መመታትን
በፊትህ ላብ ብላ እያለ ፡ በእኛ ዘንድ
እስካገለገለ ድረስ አባቱ ልኮታልና ።

## ምስጢር

አንዳንዱ ተሸካሚ በራሱ ሸክም ላይ የሌላውን ደካማ ሸክም ጨምሮ ይሸከማል ። መድሃኔ አለምም አምላክም ሰውም ሲሆን የሰውን ጣጣ በሰውነቱ ከፈለ። እግዚአብሄር "እሾህ ይብቀልብህ" ብሎ የረገመውን የአዳምን "የእሾህ አክሊል" ለራሱ አደረገ። ልጅ ለአባቱ እንዲታዘዝ መድሃኔ አለም በባህርይ አባቱ በእግዚአብሄር አብ ፈቃድ ሰው ሆኖ ከሃጢአት በቀር የሰውነትን ስራ ሰራ ። እግዚአብሄር አዳምን በፊቱ ላብ እንዲበላ (ላቡ እየተንጠፈጠፈ ሰርቶ እንዲበላ) እንዳዘዘውም ፡ መድሃኔ አለም ፊቱን በጥፊ ተመታ በማለት ቅኔው ጣመስጥሯል።



*353 ሥላሴ /ስ*

*ዘመራሒ (አለቃ ፡ ዘጉና ሚካኤል)*

*ሞተ ለይፍርሁ*
*መላእከት እንከ በሰማያት*
*እስመ እንተ ሞተ ሰብእ ገብረ ዮሐንስ ምሁክ*
*ሰብእ አኮ ዳዕሙ መልአክ ።*
*ወሙሰናሃ ለሳሌም ማኅሌቱ ከመ ኢይርአይ በሀውክ ፡*
*ወልደ ሐዋርያት አቤሜሌክ*
*ታሕተ ዕፀ ክንቱ በለስ እንዘ ያሰምክ ፡*
*በጥበቡ ሰወሮ አምላክ ።*

## ትርጉም

እንግዲህ መላእክት
በሰማዮች ሞትን ይፍሩ ፤
የሞተው ሰው ርህሩህ ገብረ ዮሃንስ
መልአክ ነው እንጂ ሰው አይደለምና ።
የማህሌቱ /ሳሌም ጥፋትንም በእውከት እንዳያይ
ወልደ ሃዋርያት/አቤሜሌክ
በከንቱ በለስ እንጨት በታች ሲጠጋ
አምላክ በጥበቡ ሰወረው።

## ምስጢር

መላእክት የማይሞቱ ረቂቆች ስለሆኑ ሞትን አይፈሩም ነበር ፤ አሁን ግን ሊፈሩ ይገባቸዋል ። የሞቱት መሪ ጌታ ገብረ ዮሃንስ በተፈጥሮአቸው ሰው ቢሆኑ በግብራቸው መልአክ ስለሆኑ የእርሳቸው ሞት መላእክትን ያስጋል ። አቤሜሌክም የኢየሩሳሌምን ጥፋት እንዳያይ አምላክ በኪነ ጥበቡ በእፀ በለስ ስር እንደሰወረው የመሪጌታ ገብረ ዮሃንስ ጓደኛ መሪጌታ ወልደ ሃዋርያትም የማህሌቱን ጉድለት አላዩም ፤ እንደጓደኛቸው ሞቱ ። አምላክም በሞት አከታተላቸው በማለት ባለቅኔው የሁለቱን መሪጌቶች አሟሟት በቅኔያቸው ምስጢር አስረድተዋል ።

## ታሪክ

በጎንደር ክፍለ ሀገር በጋይንት አውራጃ ድጓ እያስተማሩ የሚኖሩ በሙያቸውና በመንፈሳዊ ስራቸው ምስጉኖች የነበሩ መሪጌታ በላይ



www.ethiopianorthodox.org

(በክርስትና ስማቸው ገብረ ዮሃንስ) እና መሪጌታ መንግስቱ(በክርስትና ስማቸው ወልደ ሃዋርያት) በአንድ ወር ውስጥ ተከታትለው ስለሞቱ ባለቅኔው ይህን የኀዘን መግለጫ ቅኔ በፀሎተ ፍትሃታቸው ላይ ተቀኝተውላቸዋል ።

354 ዋዜማ(771)ጎ
ዘድንቂ (እሲ.ቃ)

ለአልዓዛር መድሎተ ነፍስ
አንሥአ እግዚእ ኪዳነ ድንግል ናዝራዊ ፤
በፍትሕ ምድረ ቢታንያ አኮኑ ይደዊ ።
ወለአሐቲ ብእሲት ነፍሰ በላዔ ሰብእ ዐላዊ
ይቢላ ቤተኪ በሰላም እትዊ ፤
እስመ አነ ዘኵሉ ማኅየዊ።

## ትርጉም

የነፍስ ሚዛን/አልአዛርን
የናዝሬት ሰው የሆነ የድንግል ቃል ኪዳን/ጌታ አነሳው ፤
በፍርድ/የቢታንያ ምድር ታሚልና ።
ወንጀለኛ የሆነ የበላኤ ሰብእ ነፍስ/አንዲት ሴትንም
ወደቤትሽ በሰላም ግቢ አላት ፤
እኔ የሁሉ አዳኝ ነኝና ።

## ምስጢር

ኢየሱስ ክርስቶስ አልአዛርን በቢታንያ ከመቃብር እንዳስነሳው የቅድስት ማርያም ቃል ኪዳንም በእምላክ ፍርድ የነፍስን ሚዛን ወደላይ እንዲነሳ አደረገው ። ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲቱን ሴት ከሀመሚ አድኖ በሰላም ወደቤቷ እንድትገባ እንዳደረገ ለማርያም የተሰጣት ቃል ኪዳንም የበላኤ ሰብእን ነፍስ ወደ ገነት አገባት ይላሉ ባለቅኔው ።

355 ዋዜማ (772) ጎ
ዘአድማሱ ጌትዬ (ንቡረ እድ)
አናብስተ ገዳም እንዘ በላዕት
በሥርዓተ መጽሐፍ ኅብሩ ምስለ ዳንኤል ባሕታዊ ፤
ለጾም አምጣነ እድለው እመብልዕ ምድራዊ
ጾመ እሉሰ ኢክህሉ ቅድመ ገጸ ንጉሥ ዐላዊ
ነገደ ገሞራ ወሰይፍ ሠርጐ ሐራዊ
እንዘ ሀሎ ጊዮርጊስ መርዓዊ



## ትርጉም

የዱር አንበሶች በላተኞች ሲሆኑ
በመፅሃፍ ስርአት ከብቸኛ ዳንኤል ጋር ተባበሩ ፤
ከምድራዊ መብል ይልቅ ለፆም አድልተዋልና ።
የገሞራ እሳትና የወታደር ሽልማት ሰይፍ ግን
ጊዮርጊስ/ሙሽራ ሳለ በወንጀለኛ ንጉስ ፊት
የእነዚህን ፆም አልቻሉም ።

## ምስጢር

በፍስክ ጊዜ (ቅቤ ስጋና እንቁላል በሚበላበት ወቅት) ስጋ ሲበሉ የኖሩ ሰዎች ባህታዊ ሲፆም አይተው ይፆማሉ። የዱር አንበሶችም ሰውንና እንስሳን ሰብሮ መብላት ልማዳቸው ሲሆን ነቢይ ዳንኤል አብሯቸው ሲያድር አልነኩትም ። ሚዜዎች ከሙሽራው ጋር ሳሉ መፆምን አይችሉም ። እሳትና ሰይፍም በስቃይ ጊዜ ጊዮርጊስን አልፆሙም በማለት ባለቅኔው የጊዮርጊስን ስጋ እሳት ያቃጠለው ፡ ሰይፍም የቆጠረው መሆኑን በቅኔያቸው ምስጢር አስረድተዋል ።

356 ዋዜማ (774)ጎ
ዘፍሥሃ ጊዮርጊስ (ቄሰ ገበዝ ፡ ዘዳሞ)
አምኖን ገብረ መርዓዊ
እመ ተመስጠ ወነደ በፍቅረ ሥጋ ብሕታዌ
ለትእማር መንግሥተ ሰማይ ረከባ በደዌ ፤
እምዝኒ ኢይኩን ልማደ እራዊት ጉህላዌ
እንዘ በትሕትና ይረድእ አረጋዌ
ተባረከ ዘተረግመ አርዌ ።

## ትርጉም

አምኖን/ገብረ ክርስቶስ
በስጋ ፍቅር/ብቸኝነት ቢመሰጥና ቢቃጠል
ትእማር/መንግስተ ሰማይን በደዌ አገኛት ፤



www.ethiopianorthodox.org

ከዚህም ይልቅ የአራዊት ልማድ ሽንገላን እንዳይሆን
አባ አረጋዊን በትህትና እየረዳ
የተረገመው አውሬ (ዘንዶ) ተመረቀ ።

## ምስጢር

አምኖን የተባለው የዳዊት ልጅ በፍትወታዊ ፍቅር ተመስጦና ተቃጥሎ ታመምሁ በማለት ዘዴ የአባቱ ልጅ የእህቱ ትእማርን ክብረ ንፅህና እንደገሰሰ ገብረ ክርስቶስም ከአለም ርቆ መኖርን ከልቡ መረጠና በደዌ ስጋ ተሰቃየ ፤ በዚህ ምክንያት መንግስተ ሰማይን ለማግኘት ቻለ ።

አንዳንድ ባለጌ ሁልጊዜ መጥፎ እንዳይባል ጠባዩን አሻሽሎ ቅን ታዛዥ ይሆናል ፤ ሽማግሌዎችንም ይረዳል ። እባብም አዳምን ያሳተበትን ተንኮሉን ትቶ አቡነ አረጋዊን ወደ ዳሞ ተራራ አወጣ ። ክፉው ሰው በክፋቱ ቢነቀፍም እልፎ አልፎ በሚሰራው መልካም ስራ እንደሚመረቅ እባብም በአዳምና በሄዋን ምክንያት በተረገመው ርግማን ፈንታ የአቡነ አረጋዊን በረከት አገኘ በማለት ቅኔው ተመስጥሯል (ስንክ· ጥቅምት· 14)።

*357 መወድስ(785)ጎ*
*ዘገብረ ሥላሴ (ንቡረ እድ)*

*አዕርከተ ምኒልክ ብዙኀ ወይነ ፍቅርክሙ*
*ወለፍቅርክሙ ወይን ብዙኃን ይስትይዎ፤*
*እመኒ የኀልቅ ወይነ ተአኅዎ*
*ለቀሱተ ምግባር ሕሊናክሙ*
*ማየ ፍቅር እስከነ አፉሁ ወላዕሉ ምልዕዎ ፤*
*እስመ ለዘቦ ይዌስክዎ*
*ወለዘአልቦ ብዙኀ ዘቦ የኀይድዎ ።*
*ለባሕርይሂ ጸሎትክሙ ኢትደይዎ*
*ማእከለ አኀርው ጽኑዓን ጽልሑት ወሐስዎ፤*
*ገሕቱ ለጸሎት ማይ እምአዘቅተ ዳዊት ቀድሕዎ ፤*
*ለዐቃቤ ሥራይ ጸሎትክሙ አምጣነ ሕሙማን ይፈቅድዎ ።*



## ትርጉም

የምኒልክ ባለሟሎች! ወይን/ ፍቅራችሁ
ብዙ ነው ፤ ወይን/ፍቅራችሁንም ብዙዎች ይጠጡታል ፤
ወይን /ወንድማማችነትም ቢያልቅ (ያለቀ እንደሆን)
የምግባር እንስራ/እሳባችሁን
ውሃ/ፍቅርን እስከ አፉ ሙሉት ፤
ለአለው ይጨምሩለታልና
ብዙ የሌለውንም ያለውን ይቀሙታልና ።
በጠነከሩ እሪያዎች ሽንገላና ውሸት መካከልም
እንቁ/ፀሎታችሁን አትጨምሩት ፤
ፀሎት/ውሃን ከዳዊት ጉድጓድ ቅዱት እንጂ
ባለመድሃኒት/ፀሎታችሁን ሕመምተኞች ይፈቅዱታልና ።

## ምስጢር

ብዙ ወይን ብዙ ሰዎች ቢጠጡት ፣ ቢጠጡት አያልቅም ፡ በፈገግታ የሚያስተናግዱ የአፄ ምኒልክ ባለሟሎች ፍቅርም በብዙዎች ዘንድ የተመሰገነ ሆነ ። ወይን ሲያልቅ ሌላ ወይን በየእንስራው እንደሚሞላ የአንዳንድ ሰዎች ፍቅርም እየታደሰ ይኖራል ። ወይኑ እስከ እንስራው አፍ ጢም እንደሚል የልብ ፍቅር በአፍ ይገለጣል ። ኢየሱስ "ለአለው ይጨምሩለታል ፡ የሌለውን ግን ያለውን ቅሉ ይቀሙታል" እንዳለ እንዲሁም ሰውን በፈገግታ ለሚያስተናግድ ለአፄ ምኒልክ ባለሟል በክብር ላይ ክብር ይሰጠዋል ። ሰውን የሚጠላ ባለሟል ግን ከያዘው ሹመት ይሻራል ። በእሪያዎች መካከል የተኖረ እንቁ እንደሚሰበር ከአንገት በላይ የሆነው የማታለልና የውሸት ፍቅር የክፉ እለት (ከፍቅረ ኞች መካከል አንዱ ችግር በደረሰበት ጊዜ) አይገኝም ። ውሃ ከጉድጓድ እንደሚቀዳ ፍቅርም ከማታለልና ከውሸት የራቀ መሆን ያለበት መሆኑን ዳዊት ተናግሯል ። ባለመድሃኒቱን በሽተኞች እንደሚፈልጉት በፍቅር የተፀለየው ፀሎትም ድውያ ይፈውሳል በማለት ባለቅኔው የፍቅርንና የፀሎትን ጥቅም በቅኔያቸው ምስጢር አብራርተዋል ።

*መወድስ (786) ጎ*
*358 ዘገብረ ሥላሴ (መምህር ፣ ዘኤልያስ)*



www.ethiopianorthodox.org

*ለልበ ምኒልከ አልዓዛር አርከ እግዚእነ*
*ባሕርያተ ሥጋ አዝማድ አይቴ ቀበርከምዎ?*
*እስመ ኢየእምር አነ ኀበ ወሰድዎ*
*እለ በንቡዕ ከመ ሰራቂ*
*እመንበረ ክብሩ ሌሊተ ነሥእዎ*
*ወይደልወነ አስቆቅዎ*
*ለወሀቤ መንግሥት ዝናም ማየ መቃብር እስመ ከልዕዎ ።*
*ኀሠሥክዎሂ ጊዜ ምንዳቤ ወኢረከብክዎ*
*ወኢተሰጥወኒ ምኒልክ ሶበ ለምኒልክ ጸዋእክዎ ፤*
*ወእልክቱሰ በግፍዕ እለ ወግዕዎ*
*በንጥረ መባርቅት ምስለ አእላፍ ሀለዎሙ ይርአይዎ ።*

## ትርጉም

የስጋ ባህርዮች (ዘመዶች) የጌታችን ወዳጅ የሆነ
የምኒልክ ልብ/ አልአዛርን ወዴት ቀበራችሁት?
በድብቅም እንደ ሌባ ከክብሩ
ዙፋን ሌሊት የያዙት
የወሰዱበትን ቦታ እኔ አላውቅምና ።
ማልቀስም ይገባናል ፤
መንግስት /ዝናም ሰጪን ውሃ/ መቃብርን ከልክለውታልና ።
እኔም በችግር ጊዜ ፈለግሁትና አላገኘሁትም ፤
ምኒልክንም ብጠራው ምኒልክ አልመለሰልኝም ።
በግፍ የወጉት እነርሱ ግን
በመብረቆች ብልጭታ ከሺእላፍ ጋር ያዩት ዘንድ አላቸው ።

## ምስጢር

ኢየሱስ ክርስቶስ አልአዛርን ወዴት ቀበራችሁት ብሎ የአልአዛርን ቤተሰቦች እንደጠየቃቸው ሁሉ አፄ ምኒልክ በስጋ ባህርያት በሚመጣ ሞት ምክንያት ያ አሳቢና አዋቂ የነበረው ልባቸው በድን ሆነ ። ሌባም



በሌሊት እንደሚሰርቅ የአፄ ምኒልክም ሞት ድብቅ ሆነ ። ለሁሉም ዝናብን የሚሰጥ እግዚአብሄር ወልድ ተጠማሁ ቢል አይሁድ ውሃን እንደከለከሉት የኢትዮጵያን መንግስት የመሩ አፄ ምኒልክን የቤተ መንግሰት ሰዎች በግልፅ አልቀበሯቸውም ።

ከዚህም ሌላ "አውቆ የተደበቀ ቢጠሩት አይሰማም" እንደሚባል የምኒልክ ሞት ቢደበቅም እንደቀድሞው በአደባባይ ባለመታየታቸውና የህዝቡን ችግር ባለማቃለላቸው ተገለጠ ። ክርስቶስን በግፍ የወጉት አይሁድ ከመላእክት ጋር በመብረቅ ብልጭታ ታጅቦ ዳግመኛ ሲመጣ እንደሚያዩት ፤ ምኒልክም በህዝብና በሰራዊት ታጅበው በእንቢልታና በመለከት መቀበራቸው አይቀርም በማለት ባለቅኔው በዘመናቸው የተፈፀመውን የምኒልክን ሞት መደበቅ በቅኔያቸው ምስጢር ቀርፀዋል ።

## ታሪክ

የኢትዮጵያ ንጉስ ነገስት አፄ ምኒልክ በ1906 ዓ/ም ሲሞቱ ለጊዜው ሞታቸው ተደብቆ ነበር ። ባለቅኔው ይህን አድራጎት በዘመኑ ተገኝተው በማየታቸው አድራጎቱ ትክክል አለመሆኑን አመልክተው ወደፊት መገለጡ የማይቀር መሆኑን በቅኔያቸው አስረድተዋል ።

*359 መወድስ (787)ኅ*
*ዘተክሌ (መምህር ፤ ዘዋሸራ)*
*በግእዘ ሕፃናት በከይከ ሰማዕተ ድማኅ*
*ወዘበከይኮ መጥባሕት እስከ ክሳድከ ውኅዘ*
*ወለከዊነ እግር አእዳው ለእመ አንሥኡ ጋዕዘ*
*አስተዓረይኮሙ ጊዮርጊስ*
*ክልኤሆሙ ከመ ይትዋረሱ ምድረ ርስት ሐዋዘ ፤*
*ነበልባለ እሳት ልብሰትከ*
*ከመ አናንያ ዕፍረት እስከ ጼነወ ወምዕዘ ።*
*ሩፋኤልኒ ለአሰስሎ ዘእመ ናፆስ ትካዘ*
*ፀባሕተ አይዕንት ለመጥዎ ታሕተ እግረ ጠቢት ተአዘዘ ፤*
*ወእምተቀንዮ መጽሐፍ ለእመ ኮነ ግዑዘ*
*ምስለ አንበሪ ቤተ ዮናስ ቤተ መቅደሱ አስተአኀዘ ።*



www.ethiopianorthodox.org

## ትርጉም

የዲማ ሰማእት ጊዮርጊስ! በህፃናት ጠባይ አለቀስህ
ያለቀስኸውም ሰይፍ እስከ አንገትህ ፈሰሰ ፤
እጆችም እግርን ለመሆን ከርክርን ቢያነሱ
ጊዮርጊስ፤ ሁለቱም መልካም
የርስት ምድርን ይዋረሱ ዘንድ አስተካከልሃቸው ፤
የእሳት ነበልባልን አለባበስህ
እንደ አናንያ/ሽቶ እስከ አወደ ድረስ ።
ሩፋኤልም በናኦስ ጊዜ የነበረውን ትካዜ ለማስወገድ
የአይኖችን ግብር ለመስጠት ከጦቢት እግር በታች ታዘዘ ፤
ከመገዛት/መፅሀፍም ነፃ ቢሆን
ከዮናስ ቤት/አሳ አንበሪ ጋር ቤተ መቅደሱን አያያዘ ።

## ምስጢር

ህፃን እንባው በእንገቱ እሰኪፈስስ ያለቅሳል ። ሰይፍም የህፃኑ ምሳሌ የሆነው የሰማእቱ ጊዮርጊስን አንገት ከለለው። ሁለት ባላጋሮችም በአንድ መሬት ሲጣሉ ሃቀኛ ዳኛ መሬቱን ትክክል እንደሚያካፍላቸው ጊዮርጊስም እጆቹን ከእግሮቹ ጋር በጉንብስ እንደ ከብት አስሄዳቸው ። በልብስ ላይ የተርከፈከፈ ሽቶ እንደሚያውድ (እንደሚሸት) ጊዮርጊስ የተሰቃየበት እሳት አናንያ ፣ አዛርያና ሚሳኤል በባቢሎን እንደተጣሉበት እሳት ሆነ ፣ አላቃጠለውም ። ከዚህም ሌላ ሃዘን በደስታ እንደሚለወጥ የአሞን ንጉስ ናኦስ የእስራኤልን አይኖች እያስወጣ በማስገበር ስለሰራው ግፍ አፀፋ መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል የጠፉትን አይኖች ለጦቢት ገፀ በረከት አደረገለት ፤ አበራለት ።

ነፃ የወጣ ተገዥ በወደደው ቦታ ቤት የመስራት ነፃነት አለው ። ከመፃህፍት ትእዛዝ የወጣ ሰውም ከሃይማኖቱ ቀኖና ውጭ ይኖራል ። ዮናስ በአሳ አንበሪ ሆድ ውስጥ ሶስት መአልትና ሶስት ሌሊት እንዳደረ የመልአኩ ሩፋኤል ቤተ መቅደስም በአሳ አንበሪ ጀርባ ላይ ኖረ በማለት ባለቅኔው አመስጥረዋል ።



*360 ሣሀልከ (791)ኀ*
*ዘዳኼ (አሊቃ)*
*ለምንት እግርከ ወለማእዜ*
*ፈጻሜ ፈቃድ ራጉኤል አምጣነ አልብከ ጊዜ*
*ዘእንበለ ክንፍ ከመ ትሑር*
*ወሚመ ከመ ንሣየጥከ ሀበነ ይእዜ ።*

## ትርጉም

ፈቃድ ፈፃሚ ራጉኤል!
እግርህ ለምን ስራ ነው? ለመቸስ ጊዜ ነው?
ያለ ክንፍ ትሄድ ዘንድ ጊዜ የለህምና ፤
ወይም እንድንወዳጅህ ዛሬውኑ እድለን ።

## ምስጢር

እንድ ሰው ዘመዱን በደስታም በመከራም የማይጠይቅ ሲሆን ዘመዶች "ዝምድናህ ሲመችህ ብቻ ነው? ይደከምሃል እንዳይባል የምትሄደው በበቅሎ ነው፣ በቅሎ እንዳንገዛልህ በቅሎ አለህ' ይሉታል ። ባለቅኔው "መልአኩ ቅዱስ ራጉኤል! እርዳን ፤ የምናከብርህ ረዳት ልትሆነን ነው ። መምጣቱ ያቅትሃል እንዳንል የምትበረው በክንፍ ነው ፤ ያለክንፍ የሄድህበት ጊዜም የለም ። እለዚያ ደጅ ጥናቱን እንድንቀጥል ንገረን" በማለት በቅኔያቸው ምስጢር ተማፅነዋል ።

*361 መወድስ/ስ*
*ዘገሥሥ (መምህር ፡ ዘይስማላ ጊዮርጊስ)*
*ርኀቀተ እኑሁ ብንያም ለእመ አኀዘኖ*
*ቀድሐ ዮሴፍ ሞቅሐተ ስምዖን ማየ ፤*
*እስመ በዝንቱ ጥበብ ተራክቦቶ ሐለየ ፤*
*ወእመ ተዘክረ ተፈልጦቶ*
*ለብንያም በውስተ መሥነቅቱ ጽዋዖ ወደየ ፤*
*ዘኒ ዘአመክነየ*
*እስመ ሰራቂ ብንያም ከመ ኢይርኀቅ እምዘየ ።*



www.ethiopianorthodox.org

*ለአዳምሂ ተራኀቆቱ ለእመ ኮኖ እኩየ*
*ቅድመ ገጸ አዳም አስተዳለወ በለሰ ገነት መሠንየ ፤*
*ለፈያታዊ አዳም ከመ ያዕርጎ ለማየ*
*መኰንነ ፈያት ምስለ ፈያት እስመ ኮነ ፈያታየ ።*

## ትርጉም

የወንድሙ ብንያም ርቀት ቢያሳዝነው
ዮሴፍ ስምኦንን ማሰር/ውሃን ቀዳ ፤
በዚህ ጥበብ መገናኘቱን አስቧልና ፤
መለየቱንም ባሰበ ጊዜ
በብንያም አቅማዳ ውስጥ ፅዋውን ጨመረ ፤
ይህንንም ያመከኘው
ሌባ ብንያም በዚያ እንዳይቀር ነው እኮ ።
የአዳምም መራቁ ክፉን ቢሆንበት
በአዳም ፊት ያማረ የገነት በለስን አዘጋጀ ፤
ሽፍታ አዳምን ወደ ሰማይ ያወጣው ዘንድ
የሽፍቶች ጌታ ከሽፍቶች ጋር ሽፍታን ሆኗልና ።

## ምስጢር

የእናቱ የራሄልና የአባቱ የያእቆብ ልጅ ወንድሙ ብንያም የናፈቀው ዮሴፍ በተሾመበት አገር በግብፅ ከሌሎች ወንድሞቹ ለይቶ የአባቱን ልጅ ስምኦንን አሰረው ። በዚህም ምክንያት ወንድሙ ብንያም ከመጣለት በሁዋላ ፤ እንዳይለየው አስቦ የሚጠጣበትን የወርቅ ፅዋ በብንያም አቅማዳ ውስጥ በምስጢር አስጨመረ ። "የወርቅ ፅዋየን ሰረቃችሁኝ" በማለት ወንድሞቹን ሲያስመረምር ፅዋው በብንያም አቅማዳ ውስጥ በመገኘቱ ብንያም በሌባ ስም ታስሮ በግብፅ እንዲቀር አደረገ ። ኢየሱስ ክርስቶስም አዳም አትብላ" የተባለውን እፀበለስን በመብላቱ ከፈጣሪው ተጣልቶ ከገነት እንደወጣ እንዳይቀር ከሽፍቶች ጋር እንደ ሽፍታ ተሰቀለለት ። ወደቀድሞው ክብሩም መለሰው በማለት ቅኔው ተመስጥሯል (ዘፍጥ· 42—46 ። ማቴ· 27 ፡ 15—26) ።



*362 ማህሌት (809)ን*
*አግዓዚት አርምሚ ወተሐሠዪ ፡*
*አምጣነ ሰንበት ሀብትኪ ዕረፍተ ኵሉ ቀናዪ*
*ዘበእንቲአኪ ተነበዩ*
*ወለትየ እስከ ይቤለኪ ምኒልክ ርእዪ ።*

## ትርጉም

ንግስት! ዝም በይና ተደሰቺ ፤
ሰንበት/ህብትሽ የገዢ ማረፊያ ነውና ።
ስለአንቺ የተነቡትን
ምኒልክ "ልጄ! ተመልከቺ" እስኪልሽ ድረስ ።

## ምስጢር

ሰንበት የክርስቲያኖች ሁሉ ማረፊያ ቀን እንደሆነች የንግስት ዘውዲቱ ስጦታ የመኳንንቱ ሁሉ መደላደያ ነው ። ነቢዩ የእስራኤል ንጉስ ዳዊት ስለቅድስት ማርያም ሲተነባ ፤ "ልጄ ሆይ ስሚ! ተመልከቺም" ብሏል ። በአንፃሩም ንግስት ዘውዲቱን አባታቸው አፄ ምኒልክ አዋቂ አደረጓቸው ይላሉ ባለቅኔው ።

*363 ዕዝል ጉባኤ ቃና/ሰ*
*ዘምሥራቅ (አለቃ ፡ ዘኤልሻማ)*
*ሰረቂ ምንተ ነደ ገሞራ እንተ አልብኪ ሲሳይ ፤*
*መአትም ገብርኤል እስመ ይቤለኪ ማይ ።*

## ትርጉም

ምግብ የሌለሽ የገሞራ ነዲድ ሴት! ምን ሰረቅሽ?
ቁጡ/ገብርኤል ማይ ይልሻልና ።

## ምስጢር

በስርቆት የተከሰሰች ሴትን የሚመረምር ሹም "የጠፋውን እቃ ላለመስረቅሽ ማይ" እንደሚላት የመርማሪው ምሳሌ ቅዱስ ገብርኤል ገሞራን ያቃጠለች እሳትን ለእነአናንያ እንደ ውሃ አቀዘቀዘላቸው ይላሉ ባለቅኔው ።



www.ethiopianorthodox.org

*364 ዋዜማ/ስ*

*ዘገብረ ሥላሴ (መምህር ፡ ዘኤልያስ)*

*አ ዘሥርቀትኪ*
*እምክልልተ ወይሌ ወላህ ከዋክብተ ዳዊት ሰማይ*
*ሰማይ ሐና ማርያም ፀሐይ*
*ወይንኪ ንጽሕ ፡ ወበረድኪ ጌጋይ ፤*
*አኮኑ በንጽሕ ብርሃነ ዕበይ*
*መትሕቴኪ ኤልያስ ባሕርይ ።*

## ትርጉም

አወጣጥሽ የዳዊት/ሰማይ
ኮከቦች/ወዮታና ልቅሶን ከተጋረደች
ከሃና/ሰማይ የሆነ ማርያም ፀሃይ ሆይ!
ወይንሽ ንፅህና ነው ፣ በረድሽም በደል ነው ፤
በንፅህና /የከፍታ ብርሃን
ኤልያስ/እንቁ ከበታችሽ ነውና ።

## ምስጢር

ሰማይ በኮከቦች እንደምትከለል ሃና ወዮታና ለቅሶን አበዛች ። የፀሃይ አወጣጥ ከሰማይ እንደሆነ የቅድስት ማርያምም መወለድ ከሃና ሆነ ወይን በፀሃይ እንደሚለመልም ንፅህናም በማርያም ተገለጠ ። በረዶ በፀሃይ እንደሚሟሟ በደልም በማርያም ጠፋ ። እንቁ በብርሃን ከፀሃይ በታች እንደ ሆነ በድንግልና ንፁህ የሚባል ኤልያስ በንፅህናው ከማርያም ጋር አይወዳደርም በማለት ባለቅኔው አመስጥረዋል ።

*365 ግእዝ አሥረ ንግሥ (835)ኀ*

*ዘኅሩይ ወ/ሥላሴ (ብላታ)*

*ኢትደይ ብነ እግዚአ ዙሉ ምኒልክሃ ሰንቈ ባሕርይ*
*በቅድመ አሕርው ሞት ወመቃብር ሕፁፃነ መልክእ ሠናይ*
*ለዙልነ ጸዳለ መንግሥቱ ይትረአይ ።*

## ትርጉም

የሁሉ ጌታ! ምኒልክ/ባህርይ የተባለ እንቁን



መልካም መልክ በጎደላቸው በእሪያዎች/ሞትና መቃብር ፊት አትጣልብን ፣
ብርሃን/መንግስቱ ለሁላችን ይታይ ዘንድ ።

## ምስጢር

በእሪያዎች ፊት የተጣለ እንቁ በእሪያዎች እርግጫ መሰበሩ አይቀርም ። ስለዚህም ባለእንቁ እንቁን በእሪያዎች ፊት ማስቀመጥ የለበትም ። የእንቁ ባለቤት ለእንቁ ጥንቃቄ እንደሚያደርግ ፣ አምላክም አፄ ምኒልክን ለሞትና ለመቃብር አሳልፎ አይስጥብን ። እንቁ በከፍተኛ ቦታ ላይ ተደርጎ ለሌሊት ሰራተኞች እንደሚያበራም የአፄ ምኒልክ የመንግስታቸው አስተዳደር በኢትዮጵያ ተወዳጅ ሆኖ ይኑር በማለት ባለቅኔው ስለምኒልክ መንግስት አስተዳደር ያላቸውን አስተያየት በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል ።

*366 ዘአምላኪየ/ስ*

*ዘገብረ ጊዮርጊስ (መምህር ፡ ዘአክሱም)*

*ይቤ እሳት እንተ ኀዘኑ ፈድፈደ*
*እምደቂቅ ሠለስቱ ኀጣእኩ ዋሕደ ፤*
*ገብርኤልሰ ጸልአኒ ወኢኮነኒ ዘመደ ።*

## ትርጉም

አዘኑ የበዛ ሰው/እሳት
ከሶስት ልጆች አንድን አጣሁ አለ ፤
ገብርኤልም ጠላኝ ፡ ዘመድም አልሆነኝም አለ ።

## ምስጢር

በልጆቹ ሞት ያዘነ አባት "ከሶስቱ ልጆቼ አንዱን እንኳን አጣሁ እገሌም ጠላኝ ፡፡ ዘመድም አልሆነኝም" እንደሚል እሳት ከሶስቱ ልጆች (አናንያ ፡ አዛርያና ሚሳኤል) አንዱንም አላቃጠለም ። አዘንተኛውን ጠላቱ እንደሚያሰጠላውና ዘመድም እንደማይሆነው መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልም እነአናንያን ለማቃጠል የነደደውን እሳት አቀዘቀዘው በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

*367 ዋዜማ (840)ኀ*

*ዘደስታ (አለቃ)*



www.ethiopianorthodox.org

*ዲበ ርእሰ ሞሥርት ዘይዌሥሮ*
*ተንሥአ ጉንድ እንዘ ድኩመ ኃይል ገሀደ ፤*
*ወአርመመ ማኅፄ ዘይመትር ጕንደ ።*
*ትእምርተ ዝኒ አምሳል ከመ ኢይትመሰል ባዕደ*
*ቀቲለ ሥላሴ ነገሥት መዋቲ ፈቀደ*
*እንዘ ርእሱ ይከውን ሐመደ ።*

## ትርጉም

በግልጥ ደካማ ሲሆን
በሚገዘግዘው መጋዝ ላይ ግንድ ተነሳ ፤
ግንድንም የሚቆርጥ ምሳር ዝም አለ ።
የዚህም ምሳሌ ምልክት ሌላ እንዳይመስል
እርሱ ራሱ አመድ ሲሆን ነገስት/ ስላሴን
መግደል ሟች ሰው ወደደ ።

## ምስጢር

መጋዝ ቈራጭ ፥ ግንድ ተቈራጭ ሲሆን ግንድ መጋዙን ለመቁረጥ ተነሳሳ። ይህን የተገነዘበ ግንድን ቆራጭ ምሳርም በግንድ መቆረጥ ስለሚመጣበት ዝም አለ ። በሞት አፈር ትቢያ የሚሆነው ፍጡር በፈጣሪው ላይ አመፀ በባቢሎንም የሰናአር ሰዎች ጉዞውን ወደሰማይ ያደረገ ግንብ ሰርተው ታበዩ ። ስላሴንም በጦር ለመውጋት ሞከሩ በማለት ባለቅኔው የሰውን ደካማነት በቅኔያቸው ምስጢር አስረድተዋል (ስንክ· ጥር፡7ቀን) ።

*368 ሥላሴ /ስ*
*ዘገሠሡ(መምህር ፡ ዘይስማላ ጊዮርጊስ)*
*ስምዖን እንተ ደንፀወ*
*ለንጉሠ ነገሥት አፈ መላፂ*
*ሥእርተ ርእሱ ኀዳጠ ከልኤተ አዕይንቲሁ ለደደ ፤*
*ወዘንተ ሰሚዖ ቃለ አብ ኢፀሕደ ፤*
*ለአፈ መላፂ ንጉሥ ሠላሳ እመ አስትዐ ፀጉር አውሀደ*
*ግፍዐ መላፂ እስመ አውረደ ፤*



*በዐለ አክሊል ዘኮነ ሦከ ሐቅል ባዕደ*
*ወከሣደ ምስለ እግር አስገደ ።*

## ትርጉም

ጥቂት የራሱ ጠጉርን
ለነገስታት ንጉስ/ የምላጭ አፍ
የነፈገ ሶምሶን ሁለት አይኖቹን ሰደደ ፤

ይህንንም ሰምቶ የአብ ቃል አልተሳሳተም ፤
ለምላጭ አፍ/ ንጉስ ሰላሳ ጊዜ ግብር/ ጠጉርን ቢያጎድል
የምላጭ ግፍ ባለአክሊል የሆነ
የዱር እሾህ/ባእድን አውርዷልና ።
አንገትንም ከእግር ጋር አሰግዷልና ።

## ምስጢር

የስእለት ልጅና ናዝራዊ ከመሆኑ የተነሳ የነገስታት ራስ ጠጉር በሚላጭ በት በምላጭ ስለት የራሱን ጠጉር ያልተላጨ የማኑሄ ልጅ ሶምሶን መላጨት ለሚገባው ለጠጉሩ ሲሰስት ፍልስጥኤማውያን ሁለት አይኖ ቹን አሳወሩት ። የእግዚአብሄር አብ ቃል የሚባል እግዚአብሄር ወልድም ከቅድስት ማርያም ከተወለደ በሁዋላ በአሪት ህግ መሰረት ሊገረዝበት የቀረበውን ምላጭ እንደውሃ አሟሟው እንጅ አልተገረዘበትም ናዝራዊ በመሆኑም ጠጉሩን አልተላጨበትም ።
ይህንንም በማድረጉ በሶምሶን የደረሰውን የሁለት አይኖች መታወር አልፈራም ።
የመንግስት ግብርን በጊዜው ያልከፈለ ሰው ከነመቀጫው ይከፍላል። እግዚአብሄር ወልድም በምላጭ የፈፀመው ግፍ ከእናቱ ከቅድስት ማርያም ከዮሴፍና ከሰሎሜ ጋር ወደግብፅ በተሰደደ ጊዜ እግርን የሚወጋ ፤በአይሁድ ስቅላት በተፈረደበትም ጊዜ ለራሱ ዘውድ ያደረጉለት እሾህን ተቀዳጀ ይላሉ ባለቅኔው (ስንክ·ጥር 6 ፤ መጋቢት 27) ።

*369 ግእዝ ጉባኤ ቃና /ስ*
*ክልኤቱ አኀው አመ ውስተ ቀላይ ወረዱ*
*አሐዱ ተመይጠ ወኢተመይጠ አሐዱ ።*



www.ethiopianorthodox.org

## ትርጉም

ሁለቱ ወንድሞች ወደወንዝ በወረዱ ጊዜ
አንዱ ተመለሰ ፤ አንዱ ግን አልተመለሰም ።

## ምስጢር

ሁለት ጓደኞች በክረምት ውሃ የሞላ ወንዝን ሲሻገሩ ፤ አንዱን ደራሽ ውሃ ይወስደውና አንደኛው ብቻውን ይመለሳል ። የልብስ ማጠቢያ እንዶድም በገበታ ሆኖ ወደልብስ ማጠቢያ ወደወንዝ ይወርዳል ። ልብስ የታጠበበት እንዶድ ከውሃው ተቀላቅሎ ከወንዝ ሲቀር ገበታው ወደመጣበት ይመለሳል ። እንዶድና ገበታ የእንጨት ዘሮች ስለሆኑ በቅኔው ወንድማማቾች ተብለዋል ።

*370 ዕዝል ጉባኤ ቃና ስ*
*ዘጥፉነሀ (አለቃ)*
*ኢይኀዝን ሳዶቅ በመልአክ በይነ ኀልቀተ ወይን ዘጋዲ ፤*
*በበረሴሁ ለሳዶቅ ቅድሐቱ እምጣነ ይትቀዳሕ ዓዲ ።*

## ትርጉም

ሳዶቅ ስለጋዲ ወይን ማለቅ በመልአክ አይዘን ፤
ቅጁ በሳዶቅ ብርሌ ገና ይቀዳልና ።

## ምስጢር

"እገሌ! የወይኑ ጠጅ አለቀ ብለህ በአሳላፊው አትዘን ቅጁ ገና ነው፤ በብርሌህ ይቀዳልሃል" ይባላል ። አንዳንድ ስስታም ሰው በማንቆርቆሪያ የቀረበው መጠጥ ሲያልቅ ሌላ የሌለ መስሎት ያዝናል ። ይህን የተገነዘቡ ሰዎችም "እገሌ የወይን ጠጅ አለቀ ብለህ በአሳላፊው አትዘን ቅጁ ገና ነው ፤ በብርሌህ ይቀዳልሃል" ይሉታል ። በአንፃሩም መልአኩ ቅዱስ ፋኑኤል ለቅድስት ማርያም ሰማያዊ መናን መግቦ ፤ ሰማያዊ ወይንንም ሲያጠጣት ሳዶቅ የሚባለው አባቷ ምንም አልቀመሰም ። የወይኑ መጠጥ የብርሌ ምሳሌ ለሆነችው ለማርያም አስራ ሁለት አመታት ሙሉ አልተጓደለባትም በማለት ባለቅኔው አመስጥረዋል (ስንኩታህሳስ 3) ።



*371 ግእዝ ጉባኤ ቃና /ስ*
*በማይ ኀፀበት ዐይነ ማርያም እንግዳ*
*ወለተ ኤርምያስ ግፍዕ ዘተዋርዶ ልማዳ ።*

## ትርጉም

ውርደት ልምዷ የሆነ የኤርምያስ ልጅ/ግፍ
የማርያም አይን/እንግዳን በውሃ አጠበች ።

## ምስጢር

ትህትና ያላት ልጅ የእንግዳን እግር በውሃ እንደምታጥብ እንዲሁም በነቢዩ ኤርምያስ ላይ የደረሰች (የተፈፀመች) ግፍ የቅድስት ማርያምን አይን አስለቀሰች ይላሉ ባለቅኔው ።

*372 ዋዜማ(864)ኀ*
*ዘሀብቴ (ደብተራ)*

*ኀደረ ከመ ነገሩ*
*ውስተ ቤተ ነዳይ ቶማስ በዐለ ብዙኀ ፍዳ*
*ኀዳጥ ዘኢየአክሎ መቃብር እንግዳ ፤*
*ውስተደብረ አሰቦስ ይግበር ምልዐተ ክርሡ ሰሴዳ*
*ነሥአ ሥጋ ቀይሐ ወጸዓዳ*
*መቃብር ዘኢፈርሀ ዕዳ ።*

## ትርጉም

ጥቂት የማይበቃው
መቃብር/እንግዳ በባለ ብዙ ፍዳ
በችግረኛ/ቶማስ ቤት እንደነገሩ አደረ ፤
በደብረ አሰቦ ግን የሆዱ/ስሴዳ ሙላትን ያደርግ ዘንድ
እዳን ያልፈራ መቃብር
ቀይና ነጭ ስጋን ወሰደ ።

## ምስጢር

ጥቂት የማይበቃውና ብዙ የለመደ እንግዳ በድሃ ቤት እንደነገሩ ያድራል። ብዙውን ሰው የሚያፈርስና የሚያበስብስ መቃብርም የተቆራረጠ የቶማ



www.ethiopianorthodox.org

ስን ስጋ አበሰበሰ ። እንግዳው በሃብታም ቤት ሲያድር እንደሚጠግብ መቃብር ደብረ አሰቦ በሚባለው በተክለ ሃይማኖት ገዳም አልተቸገረም ። ድሃውም ሃብታሙም፣ ፃድቁም ሃጢአተኛውም ይቀበርበታል በማለት ባለቅኔው ሞትና መቃብር ለፃድቁም ለሃጥኡም የማይቀሩ መሆኑን በቅኔያቸው ምስጢር አስገንዝበዋል ።

*373 ግእዝ ጉባኤ ቃና(876)ኀ*

*ከንቶ ጻመወ እግረ ተክለ አብ ነግድ ፤*
*እስመ ኢያትረፈ ምንተ በምሥያጠ ኪሩብ ዋሕድ ።*

## ትርጉም

የተክለ አብ እግር/ነጋዴ በከንቱ ደከመ ፤
በአንድ ኪሩብ/ገበያ ምንም አላተረፈምና ።

## ምስጢር

ነጋዴ በገበያ ምንም ነገር ሳያተርፍ ሲቀር ድካሙ ከንቱ ይሆናል ። የተክለ ሃይማኖት እግርም እንደ እንጨት ተሰብሮ የኪሩብ ክንፍ አልተተካለትም። ተክለ ሃይማኖት ክንፈ ፀጋ አበቀሉ የሚባለው በጎናቸው ነው እንጂ በእግራቸው አይደለም በማለት ባለቅኔው ያስረዳሉ ።

*374 ዕዝል ጉባኤ.ቃና/ስ*

*ሞት ታቦተ ሕጉ ለወልድ*
*እፎ ተቀርፀ በዘቴዎድሮስ እድ!*

## ትርጉም

የወልድ የህጉ ታቦት/ሞት
በቴዎድሮስ እጅ እንዴት ተቀረፀ!

## ምስጢር

የእንጨት ቅርፃ ቅርፅ ስራ አዋቂ በሆነ በካህን እጅ ታቦት እንደሚቀረፅ፣ ራስን መግደል በአፄ ቴዎድሮስ እጅ እንዴት ተፈፀመ! በማለት የቅኔው ደራሲ የቴዎድሮስን ጀግንነት በማድነቅ የተሰማቸውን ጥልቅ ሃዘን በቅኔያቸው አመስጥረዋል ።



*375 መወድስ (895)ኀ*
*ዘተክለ ጽዮን(አለቃ)*

*ውስተ ቤተ አብርሃም ይጽናዕ ሥርዓተ ብኩርና*
*እጓለ መንፈስ ይስሐቅ ለእጓለ ሥጋ ሰደዶ ፤*
*ወያዕቆብ ይግበር አምሳለ ይስሐቅ ፈቃዶ*
*ኢኮነ እግዚአ ብኩርና እምካልእ ሐይዶ ፤*
*ዳዕሙ ቅድመ ተወልዶ*
*ድኅረ በነብለ ፍቅር ተስሕበ እንዘ ያቴሕት ክሣዶ ።*
*ንሕነሰ እምከመ ብነ ምስለ ሆሣዕና ተዘምዶ*
*ንርአይ ከመ ጣዕም ለምረረ ስደት ወተዋርዶ ፤*
*እስመ ሆሣዕና አልዐለ ትዕይርተ መስቀል ማዕጸዶ*
*እንዘቦ ምስለ አቡሁ በመንበረ ትሥልስት ወተዋሕዶ ።*

## ትርጉም

የብኩርና ስርአት በአብርሃም ቤት ይፀና ዘንድ
የመንፈስ ልጅ ይስሃቅ የስጋን ልጅ አባረረው ፤
ያእቆብም በይስሃቅ አምሳል ፈቃዱን ያደርግ ዘንድ
ከሌላ ቀምቶ የብኩርና ጌታ አልሆነም ፤
ከመወለድ ፊት
አንገቱን ዝቅ አድርጎ በፍቅር/ገመድ ከተሳበ በሁዋላ ነው እንጂ ።
እኛ ግን ከሆሳእና ጋር ዝምድና ካለን ዘንድ
የመሰደድና የመዋረድ ምሬትን እንደ ጥፍጥና እንያት ፤
በሶስትነትና በአንድነት ዙፋን ከአባቱ ጋር ሳለ
ሆሳእና የመስቀል ቅጥጥብ/ ማጭዱን ከፍ አድርጎልና ።

## ምስጢር

ህግ በህግ እንደሚሻርና ተተኪው ህግ እንደሚፀና የሳራ ልጅ ይስሃቅ የአጋር ልጅ የእስማኤልን ብኩርና አስለቀቀው ። አንድ ህብረተሰብ በታገገለት ህግ እንደሚተዳደር ያእቆብም በኤሳው አምሳል አባቱ ይስሃቅን አታለለው ። ሃቀኛ ሰው ከሌላ ቀምቶ እንደማይበለፅግና በራሱ ድካም ባገኘው ሃብት እንደሚተዳደር ያእቆብም የኤሳውን ብኩርና



www.ethiopianorthodox.org

ያገኘው በራሱ ሃይል አይደለም ። ያእቆብና ኤሳው ከመወለዳቸው በፊት "ኤሳውን ጠላሁ ፡ ያእቆብን ግን ወደድሁ" ብሎ አምላክ በተናገረበት ኪነ ጥበብ ነው እንጂ ።
ኮሶኛም ኮሶውን በአንድ ትንፋሽ ሲጨልጠው ምረቱን እንደማያስታው ሰው ፡ ባለቅኔውና መሰሎቻቸው በሃይማኖት ጭቅጭቅ ምክንያት የመሰደዳቸውንና የመዋረዳቸውን እንግልት እንደምቾት ገመቷት ። ኮሶ ከጠጡት በሁዋላ ሲያሽር እንደሚያስደስት የመሰደድና የመዋረድን እንግልትም ክርስቶስ ስለተቀበላት አልተሰቀቃትም ።
አጫጅ ገበሬ አዝመራውን ለማጨድ ማጭዱን እንደሚያነሳ ክርስቶስ በአንድነትና በሶስትነት ዙፋን ሳለ ፡ በሰውነቱ በተሰቀለበት መስቀል ላይ ሆኖ የአይሁድን መዘባበት መታገሱ ለባለቅኔውና ለመሰሎቻቸው መልካም አርአያ መሆኑ በቅኔው ምስጢር ተገልጧል ።

376 ዘአምላኪየ(898) ጎ

*መንክራተ መልአክ ማያት ዘእንበለ መጠን ሐመት፡*
*እስመ አኬዶሙ በለዓም በአድጉ*
*ወበላዕሌሆሙ ውኅዘ ለደመ ገጸ ወርኅ ፈለጉ ።*

## ትርጉም

የመልአክ ድንቆች/ውሃዎች ያለልክ ደፈረሱ ፡
በለአም በአህያው አስረግጧቸዋልና ፡
የጨረቃ ፊት ደም ወንዝም በእነሱ ላይ ፈሷልና ።

## ምስጢር

ወራጅ ውሃ የነጋዴ አህዮች በውስጡ ሲገቡበት ይደፈርሳል ። የአምላክ ተአምሮችም በበለአም አህያ ተገለጡ ፡ አህያውንም አናገሩ ። በወንዞች ላይ ውሃዎች እንደሚጎርፉባቸው በአምላክ ተአምሮችም የጨረቃ ክበብ (ክብነት) ደም መሰለ በማለት ባለቅኔው ያስረዳሉ ።

377 ዘይእዜ (899)ጎ

*አ ልብየ ሐቅለ ኑፋቄ !*
*ጽጌ ግብረ ጽድቅ አዳም ቅድመ በላዕሌከ ይጽጊ*
*ፈረይከ ሦከ ወአሜከላ*



*በምክረ ይሁዳ ቃለ ጽድቅ ኅዳጊ ፡*
*ወመኑ ላዕሌከ ምሥዋዐ ኀዘን አዕራጊ ?*
*እንዘ ፍና ጌጋይ ትረውጽ ወእንዘ ታንጌጊ*
*ዘይረክበከ ሞት አምጣነ ይመጽእ ዮጊ ።*
*እንዘ ፍና ጌጋይ ትረውጽ ወእንዘ ታንጌጊ }*

## ትርጉም

የጥርጥር ጫካ /ልቤ ሆይ !
መልካም የፅድቅ ስራ/ አበባ በአንተ ላይ ሳያብብ
የእውነት ቃልን በተወ
በይሁዳ ምክር እሾህንና አሜከላን አፈራህ ፡
በአንተስ ላይ የሃዘን መስዋእትን አሳራጊ ማን ነው ?
በበደል /መንገድ ስትሮጥና ስትቅበዘበዝ
ከአንተ የሚከበር ሞት አሁን ይመጣልና ።
በበደል/ መንገድ ስትሮጥና ስትቅበዘበዝ

## ምስጢር

እንዳንድ ጫካ አበባ ሳይኖርበት እሾህንና ደንደሮን ያበቅላል ። እንዲሁም ባለቅኔው ልቤ መልካም ስራን ሳይሰራ ሃጢአትንና ወንጀልን አበረከተ ይላሉ ። ጫካ በተፈጥሮው እፀዋትን እንደሚያበቅል የባለቅኔውም ልብ የገባ ሀሊናው ባመነጨለት ምክር እንደይሁዳ መሄዱን ቅኔው ያስገነዝባል ።
በሃጢአት አድፎ ያቀረቡት መስዋእት ወደሰማይ አያርግም ፡ የሃጢአተኛ ሀሎትም ተቀባይ የለውም ። በጫካ ውስጥ ባለ መንገድ የሃጢአተኛ ህሎትም ተቀባይ የለውም ። በጫካ ውስጥ ባለ መንገድ ብቻውን የሚጎሰግሰውን መንገደኛ ሽፍታ እንደሚቀማው የእኔም ልብ ሁልጊዜ አመፅን ሲያስብ ድንገተኛው ሞት ይመጣበታል ብለው ባለቅኔው ራሳቸውን በመውቀስ የፀፀት ምስጢር ያዘለ ቅኔ ተቀኝተዋል ።

378 ዘአምላኪየ (900)ጎ

*ተሰምዮተ አምላክ ወሰብእ መብልዐ ባሕርይ ወጸጋ*
*በልዐ ጊዜ ተጸውዖ ቅድመ ሕዝብ እንግልጋ*
*እንበለ ሥጋ ገብርኤል ወአማኑኤል በሥጋ ።*



www.ethiopianorthodox.org

## ትርጉም

አምላክና ሰው መባል የባህርይና የፀጋ መብልን
ገብርኤል ያለስጋ ፣ አማኑኤል ግን በስጋ
በመጠራት ጊዜ በህዝብ ፊት በአንድነት በሉ ።

## ምስጢር

ሁለት ሰዎች ለድግስ ተጠርተው ሲሄዱ አንዱ ፆመኛ ሆኖ ስጋ አልበላም ሲል ፣ ሁለተኛው ደግሞ የማይፆም ይሆንና ስጋ ይበላል ። መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልም የስሙ ትርጉም አምላክና ሰው ሲባል ሰው በመባሉ ስጋን አለበሰም ፤ በአምላክነትም ሰውን አላዳነም ። አማኑኤል ግን አምላክም ሰውም ሲሆን ሰው መባሉ ስጋን ቢለብስ ነው ፣ ሰው የሆነ አምላክ በመሆኑም ሰውን አዳነ ማለት በቅኔው ተመስጥሮበታል ።

*379 ዋዜማ (901)ኀ*

*ዘገብረ ሥላሴ (ንቡረእድ)*

*መላእክት ዘይነ በዐል*
*በአስተሐምሞ ይቤሉ ማእከለ ቅንዐት እንግሊጋ*
*ቅንው ለእንተ ተዐቢ ምልክና ወጸጋ ፤*
*እስመ ክብረ ድንግል ነፍስ ወበዐለ ራጉኤል ሥጋ*
*በተዋሕዶ አክበረ እንበለ ንትጋ*
*ለሰላም ሥርዐታ ወሕጋ ።*

## ትርጉም

መላእክት ስለበአል
በቅንአት /ሽንጎ መካከል በትጋት
ለምትበልጠው ግዛትና ስጦታ ቅኑ አሉ ፤
የድንግል ክብር /ነፍስንና የራጉኤል በአል/ ስጋን
በመዋሃድ ያለጉድለት የሰላም
ስርአትንና ህግን አከብሯልና ።

## ምስጢር



ሃዋርያት "ታላቅ ለሆነችው የፀጋ ፍቅር ቅኑ" ብለዋል ። መላአክትም (አነራጉኤል) የአፄ ምኒልክን ግዛት አፀኑ ። ተፈጥሮ ነፍስንና ስጋን በማዋሃድ ፀንቶ እንዲኖር ፣ የአፄ ምኒልክ የመንግስት ስርአትም የቅድስት ማርያምን በአለ ልደትና የመልአክ ራጉኤልን በአል በህብረት አስከበረ ይላሉ ባለቅኔው ።

*380 ዕዝል ክብር ይእቲ (904)ኀ*

*ተድላ ቀራንዮ ይነብር እንበለ ሕፀፅ ወንትጋ ፤*
*አምጣነ ዘለሄ ትበልዕ እምዘ ሰቀለቶ ሥጋ ፤*
*ወትሰቲ ወይነ እምአዘቅተ ገቦ ፈሊጋ ።*
*ተድላ ይሁዳሰ ጾም በቅንዐት እስመ ኢይትረከብ ጸጋ ።*

## ትርጉም

የቀራንዮ ተድላ ያለምንም ጉድለት ለዘላለም ይኖራል ፤
ከሰቀለችው ስጋ ሁልጊዜ ትበላለችና ፣
ከጎን /ወንዚ ጉድጓድም ወይንን ትጠጣለችና ።
የይሁዳ ተድላ ግን ጾም ነው ፤ በቅናት ፀጋ አይገኝምና ።

## ምስጢር

የሰቀለችውን እያወረደች የምትበላ ባለፀጋ ሴት ምቾቷ የሁልጊዜ እንደሆነ ወገኖቿ አይሁድ የሰቀሉትን የኢየሱስ ክርስቶስን ስጋና ደም የተቀበለች የአይሁዳዊት ክርስቲያን ሴት ፅድቅ ዘለአለማዊ ነው ። ለችግረኛ ሰው ፋሲካም ፆሙ እንደሚሆን ፣ ይሁዳ በአሰቀለው ክርስቶስ ስጋና ደም ሌሎች ሲድኑ እርሱ ግን አልፀደቀም ይላሉ ባለቅኔው ።

*381 መወድስ /ሲ*
*ዘገሠሠ (መምህር ዘይስማላ ጊዮርጊስ)*

*ለትንሣኤ ክርስቶስ ኅቡረ ያስተበጽዕዋ*
*ትውልደ ጻድቃን ዘተርፈ ወእንተ ኀለፈ ዐማፂ ሕግ*
*በከመ ይቤ ያዕቆብ ዘሥሩግ ፤*
*ድኅረ ትንሣኤሰ ሶበ ሞተ*
*አልዓዛር ምሕረተ ክርስቶስ ውእቱ ጸዋግ*
*ኩነኔ ኃጥእን ሞተ እጋግ ።*



www.ethiopianorthodox.org

*ወእምሰቅለ አሪት ተስሕበ ምሳሌሆሙ ሐረግ ፤*
*እስመ በጽሑ በገይሥ ኀበ ደብረ ሲና በደርግ ፤*
*እንተ ኢየዐርግ ወልደ ነዌ ወወልደ እንበረም ዘየዐርግ ፤*
*ወእምግብጽ ኅቡራነ ቆሙ በጽንፈ ምድረ ርስት ፈለግ*
*ውሉድ ዘይበውኡ ወዘኢይበውኡ አእሩግ ።*

## ትርጉም

የስሩግ ሰው ያእቆብ እንዳለ
የተረፈ የፃድቃን ትውልድና ያለፈ በደለኛ
የክርስቶስን ትንሳኤ በአንድነት ያደንቋታል ፤
ግን ከትንሳኤ በሁዋላ
አልአዛር /የክርስቶስ ምህረት በሞተ ጊዜ
የሃጥአን ፍርድ/ የአጋግ ሞት አስከፊ ነው ።
ምሳሌያቸው /አረግም ከዱር/ አሪት ተሳበ (ተመዘዘ) ፤
የማይወጣ የነዌ ልጅና የሚወጣ የእንበረም ልጅ
ወደደብረ ሲና በመገስገስ በአንድነት ደርሰዋልና ፤
የሚገቡ ልጆችና የማይገቡ ሽማግሌዎችም
ከግብፅ በአንድነት ወጥተው በርስት ምድር /ወንዝ ዳር
ቆመዋልና ።

## ምስጢር

የአማሌቅ ንጉስ አጋግ ከእስራኤል ጋር ባደረገው ጦርነት ድል ሆኖ በእስራኤል ንጉስ በሳኦል እጅ በተማረከ ጊዜ ነቢዩ ሳሙኤል በጦር ወግቶ ሲገድለው “ሞት እንዲህ መራራ ነውን?” እንዳለ ፤ አልአዛር ከሙታን ተለይቶ ከተነሳ በሁዋላ ቢሞት ከትንሳኤ ቀጥሎ የሚመጣ ሞት አስከፊና ወደር የለውም ። የስሩግ ሊቅ ያእቆብ ቀድመው የሞቱ ፤ በሁዋላም የሞቱ ሰዎች ክርስቶስ የተነሳውን ትንሳኤ በአንድነት ይነሳሉ በማለት እንዳስተማረ ፤ የሞቱ ሰዎች ሁሉ በአንድነት ሲነሱ ክርስቶስ ያለምንም ምህረት በሃጥአን ላይ የሚፈርደው ፍርድ እጅግ የሚዘገንን ይሆናል ።

ቤት ለመስራት የሚዘጋጅ ጎልማሳ ከደን ውስጥ ገብቶ አረግ እንደሚመዝ የፃድቃንና የሃጥአን ታሪክም በአሪት (በብሉይ ኪዳን) ከተፃፈ ታሪክ ጋር ይነፃፀራል ። በብሉይ ኪዳን ዘመን ወደሲና ተራራ የሚወጣ የእንበረም ልጅ ሙሴና ከተራራው ግርጌ የሚቀር የነዌ ልጅ ኢያሱ እስከ ሲና ተራራ ስር ድረስ አብረው ሄደዋል ። “ወተትና ማርን የምታፈስ ምድርን አወርስሃለሁ” ተብሎ ለአብርሃም በተሰጠው ቃል ኪዳን መሰረት ወደከነአን ምድር የሚገቡ ወጣቶችና የማይገቡ ሽማግሌ ዎች እስራኤላውያንም ከግብፅ በአንድነት ወጥተዋል ። ከዚህም አንፃር መንግስተ ሰማይን የሚወርሱ ፃድቃንና የማይወርሱ ሃጥአን በእለተ ምፅአት (ክርስቶስ ዳግመኛ ለፍርድ በሚመጣበት ጊዜ) አብረው ይነሳሉ በማለት ባለቅኔው እምነታቸውን በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል ።

## ታሪክ

ያዕቆብ ዘስሩግ ከሶርያ ሊቀ ካህናት ተወልዷል ። በተወለደ በሶስት አመቱ እናቱ ይዛው ከቤተ ክርስቲያን ገባች ። በእርገተ ቁርባን ጊዜ (ቁርባን ተቆርቦ ሲፈፀም) ከእናቱ ጭን ወርዶ ቤተ መቅደስ ገባ ። ሊቀ ጳጳሱ ደሙን በፅዋው ሶስት ጊዜ ጋተው ። በዚህም ጊዜ ምስጢር ተገልጦለት “ስጋህን ፤ ደምህን የሰጠኸን” እያለ ክርስቶስን አመሰገነ ። በሰባት አመቱ ብሉይና ሃዲስ አጠና ። በአስራ ሁለት አመቱ አዳዲስ ድርሰት ይደርስ ጀመር ።

ያእቆብ ጤግሮስና ኤፍራጥስ በሚባሉ ወንዞች መካከል በምትገኝ አገር የስሩግ ኤጲስ ቆጰስ ሆኖ ተሾመ ። በ451 በኬልቄዶን በተደረገው ጉባኤ ከእስክንድርያ ፓትርያርክ ከቅዱስ ዲዮስቆሮስ ጋር በመሆን በክርስቶስ ሁለት ባህርያት አሉ የሚለውን የሮሙን ፓፓ የልዮንን መልእክትና ይህንንም መልእክት የተቀበሉ 636ቱን ኤጲስ ቆጶሳት ተቃውመው ከጉባኤው ከተለዩት ኤጲስ ቆጶሳት መካከል አንዱ የስሩግ ኤጲስ ቆጰስ ያእቆብ ነበር ።

የስሩግ ኤጲስ ቆጰስ ያእቆብ ብዙ ድርሰት ደርሷል ፤ ተግሳፅም (ምክር) ፅፏል ። ከአያሌ ድርሰቶቹም መካከል ስለሙታን ትንሳኤ የሚናገረው በስሙ የሚጠራው ቅዳሴ ይገኝበታል ። ኤጲስ ቆጰስ ያእቆብ መንፈሳዊ ስራውን ሳያቋርጥ ሰኔ 27 ቀን አርፏል (መፅሐፈ ቅዳሴ 1918 ፤ ገፅ 432–433) ።

*382 ሚበዝኑ (91.3)ን*





www.ethiopianorthodox.org

*በጸንፈ መቃብር ባሕር*
*ለነዘን ዘብዴዎስ ሐዋርያ ወንጌል ነደነ ፡*
*ትንሣኤ ሥጋ ይምሀሩ ወከመ ይሰብኩ ሕነ*
*እስመ ለደመናት አርድእት ጸውዖሙ ኀይል ዲበ ሠረገላ ዐረነ።*

## ትርጉም

በመቃብር ባህር ዳር
ሃዘን ዘብዴዎስን የወንጌል ሃዋርያ ዮሃንስ ተወው ፡
የስጋ ትንሳኤን እንዲያስተምሩና ህጉን እንዲሰብኩ
ደመናዎች ተማሪዎችን ሃይል በሰረገላ ወጥቶ ጠርቷቸዋልና።

## ምስጢር

ኢየሱስ በባህር ዳር ሲሄድ ያገኘው ዮሃንስ ወልደ ነጐድጓድ አባቱ ዘብዴዎስን በባህር ዳር ትቶት ኢየሱስን ተከትሎ ሄደ ። ኢየሱስ የስጋውን ትንሳኤና ህጉን እንዲያስተምሩ ሃዋርያትን ላካቸው ። ወልደ ነጐድጓድ ዮሃንስም በመቃብር ዳር ማልቀስንና ማዘንን አስቀርቶ ደመናዎች ስጋውን እንዲያስነሱና እንዲያሳርጉ አደረገ በማለት ሃዋርያው ዮሃንስ እንደመምህሩ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ማረጉንና በመቃብር ውስጥም አለመቅረቱን በቅኔያቸው ምስጢር አስረድተዋል ።

*383 መወድስ (918)ኀ*

*መኑ አብዐኪ ውስተ ቁም ነገር*
*ለቤተ ምናምን ኪያኪ ? እንዘ ከመ ኑግ ትቅለጠለጢ*
*በክርኑ እንዳገኘ ጎበዝ ዘበደረቱ መጠጢ*
*መልክአ ጉባኤ ወአርኬ ገልባጢ*
*አንቲ ቀላዋጢ*
*ምስለ ቀባጣሪት አጣሪ ወምስለ ቅሬ አንቀራባጢ*
*ሙጨ ዘቤት ለቤት ወዘቤተ ልሔም ቀሳጢ !*
*ደንደስኪ ወሻኛኪ እንዘ ከመ ወይፈን ታሳብጢ?*
*ወድጎረ ተሸከምኪ ጉደ ቀንበረ ሀንቅርት ወሀጢ*
*እንዘ ግርግሪተ ትትአሰሪ ወእንዘ በጅራፍ ትትመለጢ ።*



## ትርጉም

መልክአ ጉባኤንና አርኬን
ገልባጭ ፤ በደረቱ መጠጢ በሆነ በእንዳገኘ
ክንድ እንደ ኑግ ስትቅለጠለጢ
ከቀባጣሪ አጣሪና ከአንቀራባጭ ጋር
ቤት ለቤት የምትውይ ፡
የቤተልሄም ቀሳጭ (ሌባ) የሆንሽ አንቺ ቀላዋጭ ሙጨ !
ደንደስሽንና ሻኛሽን እንደ ወይፈን ስታሳብጭ
አንቺን የምናምን ወገንን ማን ከቁም ነገር አገባሽ ?
የአጢና የአንቅርት ቀንበር /ጉድንም ከተሸከምሽ በሁዋላ
የፊጥኝ እየታሰርሽና በጅራፍ እየተገጠብሽ ትኖሪያለሽ ።

## ምስጢር

በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት (በማህሌት) ጊዜ ሳይማር እንዳገኘ የሚያዜም መልኩንና አርኬውን ያለስልቱ ያዜመዋል ። ሙጨ የሚባለው ሰው ደግሞ የቤት ለቤት አውደልዳይና የቤተልሄም ሌባ ስለሆነ እንዳገኘ ከሚባል ሰው ቤት እየቀላወጠ እንደአጣሪና እንደ ቅሬ ቢወፍርና ቢቅለጠለጥ ፤ ሻኛም ቢያወጣ ፤ እንደምናምን እንጂ እንደቁም ነገረኛ አይታይም ማለት በቅኔው ተገልጧል ።

*384 መወድስ (920)ኀ*

*ዘዘዮሐንስ (አለቃ)*

*ዞሉ ይትዌለጥ በኑኀ ዘመን ።*
*ባሕቱ ኀጣእኩ ለሕማምየ ውላጤ ፤*
*እስመ ይትኀሠሠኒ ሊተ ለዘኀጣእኩ መያጤ*
*ተሐውኮ ተኩላ ዐረብ*
*በዐጸደ ሥጋ ዘኮነ መሣጤ*
*ኀበ ኮነ በአመፃ*
*ልቡና ዚአየ ኅአል ልብሰ ትእዛዝ ሠጣጤ ።*
*ለነፍስየሂ ኢረከብክዋ ዕረፍተ ኀዳጥ ሥላጤ ፤*



www.ethiopianorthodox.org

*እስመ በአፍአ ተገፍዖ ሥጋ ወተገፍዖ ነፍስ በውሣጤ ፡*
*እመኒ እስከ ግብጽ አሐውር እንዘ እመስል ሡያጤ*
*ውስተ ፍኖትየ የማናዊት ሐሣር ወቅጥቃጤ ።*

## ትርጉም

ሁሉ በዘመን ርዝማን ይለወጣል ።
እኔ ግን ለህማሜ እረፍትን አጣሁ ፤
በስጋ/ቦታ ነጣቂ የሆነ
መታወክ/የአረብ ተኩላ
መላሽን ያጣሁ እኔን ይፈላለገኛልና ፤
በአመፃ ልቤ/ሳኦል
ልብስ/ትእዛዝ ቀዳጅ ከሆነ ዘንድ
ለነፍሴም የጥቂት ጉዳይ ፍፃሜ እረፍትን አላገኘሁላትም ፡
የስጋ መገፋት በውጭ የነፍስም መገፋት በውስጥ አሉብኝና ፡
እስከ ግብፅም ሻጭን መስዬ ብሄድ
በቀኝ መንገዴ አሳርና ቅጥቃጤ አሉና ።

## ምስጢር

ለሌሎች ሰዎች በዘመን ብዛት መከራና ደስታ ፡ ህመምና ጤና የሚፈራረቁ ሲሆኑ ለእኔስ የመከራ ለውጥ አልሆነልኝም (መከራየ አልቀለለልኝም) ይላሉ ባለቅኔው ። በአረብ አገር ያለ ተኩላ ነጣቂ እንደሆነ ባለቅኔውም መታወክ ያላጣቸው መሆኑን ያስረዳሉ ። የእንስሶች ጠባቂ ተኩላውን እንደሚያባርረው መታወክንም ከባለቅኔው የሚያር ቀው አልተገኘም ። የእስራኤል ንጉስ የነበረው ሳኦል የእስራኤል መስፍንና ካህን የሆነ የሳሙኤልን ልብስ እንደቀደደ ባለቅኔውም ልባቸው የአምላክን ትእዛዝ አለመፈፀሙን ገልጠዋል ። ስራ የበዛበት ሰው እረፍትን እንደማያገኝ ባለቅኔውም ለነፍሳቸው የመንግስተ ሰማይ ተስ ፋን ቆረጡ ። በቤት የቤተሰብ ብጥብጥ ያለበት ሰው በውጭም ብስጭት እንደማያጣው ባለቅኔውም በስጋም በነፍስም ተስፋ ቢስ መሆናቸውን በቅኔያቸው ምስጢር አረጋግጠዋል ።



*385 መወድስ /ስ*
*ዘበቀለ ኅበና (አለቃ)*

*እምኮኖ ጌጋየ በመዋዕሊነ*
*ለዳዊት ንጉሥ ቃለ ብሂሎቱ ፍሉጥ*
*ይለብሱ ጽድቀ ካህናተ አፍአ ወውስጥ ፤*
*እንዘ እምነቶሙ በመክፈልት ኅዳጥ*
*እስመ ብኩርናሆሙ ያመስጥ*
*ወታቦተ ሕግ ልቦሙ በወርቀ ዕበድ ልቡጥ ።*
*ቀሊለሰ ኢይኩንነ ወርቀ ሀመዓሆሙ ሜጥ*
*በእደ ቢጹ ወኢያሶን ኀለፍተ እከይ ይትመያየጥ ፡*
*እንዘ መድሎቱ ሐሰት በዐውደ ይሁዳ ተውላጥ*
*አምጣነ ንባቡ በቃለ ጽርዕ ወትርጓሜሁ በዕብራይስጥ ።*

## ትርጉም

የውስጥና የውጭ ካህናት
ፅድቅን ይለብሳሉ የንጉስ ዳዊት የተለየ
የማለቱ ቃል በዘመናችን በደል በሆነበት ነበር ፤
እምነታቸው በጥቂት መክፈልት (ዘኬ) ሲሆን
ልቅናቸው ያመልጣልና ፡
የህግ ታቦት /ልባቸውም በስንፍና/ ወርቅ የተለበጠ ነውና ።
የሽያጭ /አመፃቸው ወርቅ ግን ቀላል እንዳይሆንልን
ክፋትን ባለፉ በኢያሶንና በወንድሙ እጅ ይመላለሳል ፡
በይሁዳ አደባባይ /መለወጥ ሚዛኑ አሰት ሲሆን
ንባቡ በግሪክ ቃል ፡ ትርጌሜውም በእብራይስጥ ነውና ።

## ምስጢር

የእስራኤል ንጉስ ዳዊት በመዝሙሩ ‘‘ካህናትህ ፅድቅን ይለብሳሉ’’ ብሎ እንደዘመረላቸው እንደእውነተኞች ካህናት ያይደሉ ካህናት እምነታ ቸው በመብልና በመጠጥ ፤ በሹመትና በገንዘብ ስለሆነ ዳዊት ይህን መዝሙር የዘመረው በዘመናቸው ለነበሩ ካህናት ቢሆን ያስነቅፈው ነበር



www.ethiopianorthodox.org

ይላሉ ባለቅኔው ። ወርቅ ከብረትና ከብር የላቀ ዋጋ እንዳለው የአዋቂ አጥፊዎች የሆኑ ካህናትም በደል ቀላል አይደለም ።

በተሰሎንቄ በኢያሶን ቤት ውስጥ ሃዋርያው ቅዱስ ጳውሎስና ደቀ መዝሙሩ ሲላስ ወንጌልን እየሰበኩ ብዙ ሰዎችን አሳመኑ ። አይሁድም "ኢየሱስ የሚባል ሌላ ንጉስ አለን በማለት የቄሳርን ትእዛዝ ይቃወማሉ" ብለው ጳውሎስን ፡ ደቀመዝሙሩንና አዲሶችንም ክርስቲያኖች ቢወነጅሏቸው ኢያሶንና ወንድሞቹ ዋሶች ሆነው እንዳስፈቷቸው የካህናቱም በደል በየእለቱ የሚፈፀም ሆነ ።

ሚዛን እቃን በገንዘብ ለመግዛት ፡ ወይም እቃን ለመለወጥ መለኪያ በመሆን እንደሚያገለግል ፡ የካህናቱም አመፅ በአደባባይ መምህሩ ኢየሱስን አሳልፎ ከሰጠ ከይሁዳ ተንኮል ጋር አንድነት አለው ። የአመፃቸውም መሰረቱ ስሙ በግሪክኛ ዲያብሎስ ፡ በእብራይስጥ ሰይጣን የሚባለው የጨለማ መልአክ ስለሆነ ከእውነት ይልቅ እሰት ይቀናቸዋል በማለት ባለቅኔው አመስጥረዋል (የሃዋ· 17፡5–9)

*386 መወድስ(922)ን*
*ዘናሁዳ (አሊቃ)*

*ሞተ ሰብአ ምኩራብ ኢይንብብ በልሳነ ሰይፍ*
*አመ ከላዕኮ በምዕር ለመልአከ ራማ ሥሉጥ*

*ሆሣዕና ዓለም ጥዑይ እምደዌ ተዐቅቦ ተውላጥ!*
*አይሁድ ርእዩ ከመ ዘረወ*
*ብእሲ መሐሪ መንጦላዕት ስጡጥ*
*ለንዳየ አፍአ ንዋየ ውስጥ ፡*
*ወእንዘ ለአሚን የአክል በረከተ ዓሣ ኀዳጥ*
*ተወለጠኒ ከበበ ወርኅ ብእሲተ ሰማይ ሎጥ ፡*
*ወእጓለ ሌሊት አንፈርሀ በከርሠ መዓልት ኤልሣቤጥ ።*
*ለመጽሐፍኒ ማፍዕከ ኅሩመ ተውላጥ ሜጥ*
*መተርጉም ልበ ቀያፋ ኀበ ጽንዐቱ ይትመየየጥ ።*

## ትርጉም

የምኩራብ ሰዎች ሞትን በሰይፍ ምላስ እንዳይናገር
ስልጡን የሰማይ መልአክን በአንድ አፍታ በክለከልኸው ጊዜ
ከመጠበቅ ደዌ/መለወጥ የዳንህ የአለም ሆሳእና!
መፅዋች ሰው / ቀዳዳ መጋረጃ
የውስጥ ገንዘብን ለውጭ ድሃ
እንደበተነ አየ ፡
የጥቂት አሳ ብርካቴም ለማመን ሲበቃ
የሰማይ /ሎጥ ሚስት የጨረቃ ዙሪያ ተለወጠች ፡
የሌሊት ልጅ ጨለማም በቀን /ኤልሳቤጥ ሆድ ፈነደቀ ።
ልዋጭ (ዋጋ) ወደሌለው ወደመፅሃፍ/ ግፍዘ
ጥናትም ተርጓሚ /የቀያፋ ልብ ይመላለሳል ። }

## ምስጢር

አባት ልጁን ሲመክር "በምላስዘ ክፉን አትናገር" እያለ ይከለክለዋል ። ሆሳእና የሚባል ክርስቶስም መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል የምኩራቡን ሰዎች ትቶ የምኩራቡን መጋረጃ በሰይፍ እንዲቀደው አደረገ ። ልብስ ሲያልቅ አካል እንደሚራቆት የምኩራቡ መጋረጃ ሲቀደድ የውስጡ እንደውጪው ተገለጠ ። ለተጠሩት ሰዎች ጥቂት በቂ ሲሆን ብዙ እንደሚዘጋጅ የጥቂቱ አሳ ብርካቴ የሚያሳምን ሆነ ። የሎጥ ሚስት የጨው ሀውልት ወደመሆን እንደተለወጠች የጨረቃም ክበብ(የክብነት ቅርፅ) ደም ሆነች ። ዮሃንስ በእናቱ በኤልሳቤጥ ሆድ እንደፈነደቀ የሌሊት ጨለማም በቀን ብርሃን ሰፈነበት ። ተርጓሚም ከመፅሃፉ ሃይለ ቃል ዕናት (ክብደት) የተነሳ ወደዘናው ቃል እንደሚመላለስ ፡ የአይሁድ ሊቀ ካህናት የቀያፋ ልብም ክርስቶስን መበደሉን ደጋገመው በማለት ባለቅኔው ቅኔያቸውን አመስጥረዋል ።

*387 ዘአምላኪየ(926)ን*
*መንገለ ነነዌ ገነት ፈቃደ አምላክ ሜጠ*
*ለዮናስ መኰንነ ሔዋ ባሕረ ነድ ዘውኀጠ ፡*
*አኮኑ ኢክህለ እምእደ አምላክ አምሥጠ ።*

## ትርጉም

የእሳት ባህር የዋጠው የሄዋን ጌታ /ዮናስን
የአምላክ ፈቃድ ወደነነዌ/ገነት መለሰው ፡
ከአምላክ እጅ ማምለጥን አልቻለምና ።



www.ethiopianorthodox.org

## ምስጢር

የአምላክ ፈቃድ ዮናስን ወደነነዌ እንዳደረሰው አዳምን ወደገነት መለሰው ። ዮናስን ባህር እንደዋጠው አዳምንም እሳት ከበበው ። ዮናስ ከአምላክ እጅ ሊያመልጥ እንዳልቻለ አዳምም በሲኦል ሳለ በእደ እግዚአብሄር ተጠበቀ ይላሉ ባለቅኔው ።

*388 ሥላሴ (927) ጎ*

*ዘመዝሙር ካሣ*

*ራጉኤል ኀበ አምላክ*
*በእንተ ምኒልክ እንዘ ትጼሊ*
*ግብራተ ሐዲስ ዓለም በኀይሉ ለጸሎትከ ሠሊጠ*
*ይገብእ ኀበ ዘትካት መንበሩ እንጦጦ ፤*
*ወለጽንዐ ፍቅርከ ወይን ከራሚ ውስተ ልቡናሁ ዘሦጠ*
*በሐዲስ ዓለም ኢይዌልጠ*
*ወለአጽድቆዝ አብዝኃ ተመያይጠ*
*ኀበ ጸንዐ ፍቅርከ ዘኄጠ ።*

## ትርጉም

ራጉኤል! ወደአምላክ
ስለምኒልክ ስትፀልይ
የአዲስ አለም ሰራዎችን በፀሎትህ ኃይል ጨርሶ
ወደቀድሞ መቀመጫው እንጦጦ ይገባል (ይመለሳል) ፤
በልቡ ውስጥ የጨመረው የፍቅርህ ጥናት /ከራሚ ወይንንም
በአዲስ አለም አይለውጠውም ፤
የሸነገለው ፍቅርህም ከፀና ዘንድ
ይህንም ለማፅደቅ መመላለስን አዘዛ ።

## ምስጢር

ብልሀ አሰሪ ሰራተኛውን በወቅቱ ወደስራው ያስማራዋል ። ታዛዡም ሰራተኛ ስራውን ፈፅሞ ማታ ወደቤቱ ይገባል ። የኢትዮጵያ መሪ የነበሩት አፄ ምኒልክም በመጀመሪያ በእንጦጦ ቤተ መንግስታቸውን ሰርተው የእንጦጦ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያንን ተክለው ደብረዋል ።



በሁዋላም አዲስ አለም በተባለው ቦታ የቅድስት ማርያምን ቤተ ክርስቲያን ሰርተዋል ። የነተረ የወይን ጠጅ በጉሽ ጠጅ እንደማይለወጥ አፄ ምኒልክ የአዲስ አለም ማርያም ቤተ ክርስቲያንን በንቡረ እድ መአርግ ቢደብሩም ቅሉ ፤ "የቀድሞውን ወዳጅህን በምን ቀበርኸው? በሻሽ ፤ መጪው እንዳይሸሽ" እንዲሉ የመጀመሪያውን ስራቸውን የራጉኤልን ቤተ ክርስቲያን አልዘነጉትም በማለት ባለቅኔው አመስጥረዋል ።

*389 ዕዝል ጉባኤ ቃና (931)ጎ*

*ይትቀረጽ በጸመ ቀኖና መላዒ*
*ጌጋየ ዙሉ ዓለም ሥዕርቱ ለአቤሴሎም አማዒ ።*

## ትርጉም

የአመፀኛ አቤሴሎም ጠጉር /የአለም ሁሉ በደል
በቀኖና በጉደነገገ ፆም /ምላጭ ይከርከም ።

## ምስጢር

የራስ ጠጉር በምላጭ ይከረከማል ፤ የአለም ሰው በደልም በፆም ይሰረያል ። ጠጉር በራስ ላይ እንደሚበቅል በደልም የአባቱን መንግስት በገለበጠ በአቤሴሎም ላይ በዛ ። በማለት ባለቅኔው ያስረዳሉ ።

*390 ሥላሴ(836)ጎ*

*ዘጎፋይ (አለቃ)*

*ማእምር ወለባዊ*
*በማየ ብሔሩ ኢይትመከሀ ፤*
*ከመ ይጽብዕዎ ሐሩ አኮኑ በወልጦ ጎብሮሙ ገጸ*
*ኀያላን ማያተ ብሔሩ ለማኔዎስ ዕዕ ።*
*ይትራከብሰ ማእረር ግብጻዊ ምስለ ንባበ ንዕማን ሠርጸ*
*ዮርዳኖስኑ ማየ ተግሣጽ?*
*አው ሶርያ ፈለገ ሕፀፅ*
*ዘሰጠጦ ለመጽሐፍ ለምጽ?*



www.ethiopianorthodox.org

## ትርጉም

አዋቂና አስተዋይ
ሰው በአገሩ ውሃ አይመካ ፤
ሃይለኞች /ያገሩ ውሆች ሀብራቸው/ ሬትን በመለወጥ
ፈርኦን እንጨትን ሊወጉት ሄደዋልና ።
ግን አዝመራ /የግብፅ ሰው ከንእማን ነገር/ ቡቃያ ጋር ይገናኝ ዘንድ
መፅሃፍ ለምፅን የቀደደው
የተግሳፅ ውሃ የሆነ ዮርዳኖስ ነውን?
ወይም የጉድለት ወንዝ የሆነ ሶርያ ነው?

## ምስጢር

እንዳንድ ሰው ያላግባብ ሰው በድሎ በወገኑ ቢመካ ፡ አስተዋይ የሆነ ወገኑ ድጋፍ አያደርግለትም ። ስለዚዘም ማንም ሰው በተግባሩ እንጂ በወገኑ መመካት አይገባውም ። የግብፅ ንጉስ ፈርኦንም በአገሩ ውሃዎች እንዳይተማመን የአገሩ ውሃዎች ሊያስጥሙት ተሰበሰቡ ። በአንዳንድ አገሮች በአንድ በኩል መከር ሲሆን በሌላው በኩል ቡቃያ እንደሚሆን የፈርኦን ነገር ከንእማን ነገር ጋር ተባበረ ። የሶርያ ሰራዊት አለቃ ንእማን ከለምፁ የነፃው በአገሩ በሶርያ ወንዝ ሳይሆን በእስራኤል አገር ወንዝ በዮርዳኖስ ነውና ። መፅሃፍ በእንግልት ብዛት እንደሚቀደድ የንእማን ለምፅም በውሃ እጥበት ነፃ ማለት በቅኔው ተገልጧል (2ነገስ· 5 ፤ ሉቃ· 4 ፡ 27) ።

*391 ዋዜማ (1096)ኀ*

*ጲላጦስ ለዘዓል*
*አሐደ ያሐዩ እምነ ሙቁሓን ዘልፈ ፤*
*እስመ ሕግ ዘኀበ አይሁድ ከመዝ ተጽሕፈ ።*
*ተክለ አብሰ መካሀ እምዓቅመ ጲላጦስ ኀለፈ ፤*
*እስመ ለለበዓል ያሐዩ እልፈ እልፈ*
*ወአሐዱ እምእልፍ ኢተርፈ ።*



## ትርጉም

ጲላጦስ ለበአል
ከእስረኞች አንዱን ዘወትር ያድን ነበር ፡
ሀግ በአይሁድ ዘንድ እንደዚህ ተፅፏልና ።
መመኪያ ተክለ ሃይማኖት ግን ከጲላጦስ ልክ አለፈ ፡
ለየበአል እልፍ እልፍ ያድናልና
ከእልፍም አንዱ አልቀረምና ።

## ምስጢር

ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰቀለ ጊዜ የአይሁድ አገር ገዥ የነበረ ጲላጦስ በአይሁድ ህግ መሰረት ከእስረኞች አንዱን እስረኛ የማዳን ልማድ ነበረው ። አቡነ ተክለ ሃይማኖት ግን ከእርሱ (ከጲላጦስ) መጠን ያለፈ ስራን ሰሩ ። ይኸውም ይታወቅ ዘንድ በተአምር በየበአል ቀናቸው የፈወሷቸው በሽተኞች በእልፍ የሚቆጠሩ ሆኑ በማለት ባለቅኔው ለኢትዮጵያዊው ፃድቅ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ተሰጥቷቸዋል የሚባለውን የአማላጅነት ክብር በቅኔያቸው ምስጢር አረጋግጠዋል ።

*392 ዕዝል አሠረ ንጉሥ (959) ኀ*
*ዘወልደ ዮሐንስ (መልአከ ብርሃን)*

*ምኒልክ ኢበልዐ ኃፍረተ ቀትል እምነ ይሁዳ ዘተርፈ*
*ወበበትረ እድ ዘኮነት ለከንቱ ዘባነ ፀሩ ቀሠፈ ፤*
*እስመ ፀር ስመ ዘተሳተፈ*
*ትምክህተ ሰናክሬም ቈጽለ ጊዜ ነግሀ ተዐጽፈ ፤*
*ወበሰርክ ፍሬሁ ተነግፈ ።*

## ትርጉም

ምኒልክ ከይሁዳ የተረፈውን የውጊያ እፍረትን አልበላም
ለከንቱ በሆነች የእጁ በትርም የጠላቱን ጀርባ ገረፈ ፤
በስም የተሳተፈ (አንድ የሆነ) ጠላት
የሰናክሬም ትምክህት /ቅጠልን በነግህ ጊዜ ተጎናፀፏልና ፤
በምሽትም ፍሬው ረግፏልና ።



www.ethiopianorthodox.org

## ምስጢር

ከአንድ በእድሜና በማእረግ ዝቅተኛ ሰው የተረፈውን ፍርፋሪ ከርሱ የሚልቅ ሰው አይበላም ። አፄ ምኒልክም በጦርነት አፍረው አልተመለሱም (ድል አልሆኑም) ። ይሁዳ አባቱንና እናቱን ማርኮ አሳፋሪ ነገር ፈፅሟል ። አፄ ምኒልክ ግን የአህያ ጀርባ በበትር እንደመዝበጥ ጠላታቸውን በስልጣናቸው በማስወገድ የፈፀሙት ድርጊት ህዝባቸውን የሚያኮራና የጠላታቸውን ህዝብ የሚያሳፍር ነው ። የአንዳንድ ሰዎች ስም እንደሚሞካሽ በሰመ ንጉስ (ንጉስ ነኝ ብሎ) አፄ ምኒልክን ጦርነት የገጠማቸው ጠላት መጀመሪያ አብቦ በሁዋላ ፍሬው እንደሚረግፍ እንጨት ፍሬ ቢስ ሆነ ። በእስራኤል ንጉስ በህዝቅያስ ላይ የተመካ የአሶር ንጉስ ሰናክሬም የጦርነት እቅድ ከንቱ ሆኖ እንደቀረ የአፄ ምኒልክ ጠላት ድንፋታም ዋጋ ቢስ ነው ይላሉ ባለቅኔው (2 ነገስ· 19፡35) ።

*393 መወድስ*

*ዘገሠሠ (መምህር ፡ ዘይስማላ ጊዮርጊስ)*

*ኮሉ ውእቱ ክብረ ሆሣዕና*
*እመ ለኢሳይያስ ኮነ ኃሣሜ አእዱግ እለ ተገድፉ*
*እንዘ ልዑላን ኪሩቤል ታሕተ ተጽዕኖ መትከፉ*
*እስመ ለእስራኤል በአእዱግ*
*ኢሳይያስ ሶበ አኬዶሙ እስራኤል ተሀቅፉ*
*በይነ ሆሣዕና እስከ ተጽሕፉ*
*እለ ተገድፉ አእዱግ ውስተ ርእሰ ልደት መጽሐፉ።*
*አይሁድሂ በጥንቃቄ ትምህርተ አእዱግ ተወክፉ*
*ኀበ ቤተ ጸሎት አእዱግ አፍአ ከመ ቤተ ምስየጥ አመ ኃለፉ ፡*
*አምግነ አእዱግ ፈርሁ ወሆሣዕና ቀሠፉ ፡*
*ወከመ ፀረፉ ሆሣዕና አእዱግ ኢፀረፉ ።*

### ትርጉም

የጠፉ አህዮችን ፈላጊ (ሳኦል)
ለኢሳይያስ ቢሆን ሁሉ የሆሳእና ክብር ነው ፡
ከፍተኞች ኪሩቤል ከመጫን /ትከሻው በታች ሲሆኑ
እስራኤልን በአህዮች



ኢሳይያስ ባስረገጣቸው ጊዜ እስራኤል ተሰናክለዋልና ፡
የተገደፉ አህዮች
ስለሆሳእና በልደት /መፅሃፉ ራስ እስከተፃፉ ድረስ ።
የሚዳ አህዮችም እንደገበያ ቤት ወደፀሎት ቤት በሄዱ ጊዜ
አይሁድ በጥንቃቄ የአህዮችን ትምህርት ተቀበሉ ፡
አህዮችን ፈርተው ሆሳእናን ገርፈዋልና ፡
ሆሳእናንም እንደሰደቡ ፡ አህዮችን አልሰደቡምና ።

## ምስጢር

በዘመኑ ከነበሩ እስራኤላውያን ይልቅ በመልኩና በቁመቱ የላቀ ሳኦል የጠፉ የአባቱን አህዮች ሲፈልግ በነቢዩ በሳሙኤል ተመርጦ የእስራኤል ንጉስ ሲሆን የንጉስነት ዘይትን እንደተቀባ ፡ ሆሳእና የሚባል ክርስቶስም በአህያ ላይ ተቀምጦ ወደ ቤተ መቅደስ የገባው "እስራኤል ዘሥጋንና እስራኤል ዘነፍስን ፡ እስራኤልንና አህዛብን" ለማዳን ሲሆን ፡ የስሙ ትርጉም እግዚአብሄር ደህንነት ነው ማለት የሆነ ነቢዩ ኢሳይያስ "አህያ የገዥውን በሬም የጌታውን ጋጣ አወቀ እስራኤል ግን አላወቀም ፡ ህዝቤም አላስተዋለም" በማለት ትንቢት የተናገረባቸው እስራኤል በሆሳእና አላመኑም ።

የተገደፉ ቃላት በመፅሃፉ አርእስት ላይ እንደሚፃፉ አህዮችም ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ በበረት ውስጥ በትንፋሻቸው አሟሟቁት ። በሆሳእናም እለት በአህያይቱና በውርንጫዋ ላይ ተቀምጦ ወደኢየሩሳሌም ገባ ።

አንዳንድ ሰው በሃብትና በጉልበት ከእርሱ ከሚያይል ሰው ጋር ሲጣላና ያም ሰው በሃብቱና በጉልበቱ ሲመካበት እርሱም በበኩሉ በእርሱ ደረጃ ያሉትን ለማጥቃት ቢሞክር "አህያውን ፈርቶ ዳውላውን" የተሰኘው የአባቶች ምሳሌ ይመስልበታል ። አይሁድም ከወገናቸው ከቅድስት ማርያም የተወለደ ኢየሱስ ክርስቶስ በሽማግሌዎችና በህፃናት እየተመሰገነ በአህያይቱና በውርንጫዋ ላይ በየተራ እየተቀመጠ ወደቤተ መቅደስ በገባ ጊዜ ተቃወሙት ። አህዮችን ግን አልተቃወሙም ይላሉ ባለቅኔው (ማቴ· 21 ፡ 9-15) ።

*394 ዋዜማ (962)ኀ*
*ባዕል በዕበዱ*



www.ethiopianorthodox.org

*ይቤ ነፍስየ እምድካመ ሥጋ አዕርፊ ፤*
*ለኪ አምጣነ ዘገብኪ ወርቀ ክብር ኃላፊ ።*
*ልብሰ ባዕልሰ ነገረ እመ መርዓዊ ይስፊ*
*ይቤላ ለነፍሱ ወርቀኪ ግድፊ*
*እሙስና ዘሀሎ ትትርፊ ።*

## ትርጉም

ባለፀጋ በስንፍናው
ነፍሴ ከስጋ ድካም እረፊ ይላል ፤
ያላፊ ክብር ወርቅን ለአንቺ ሰብስቤያለሁና ።
ግን የባለፀጋ ልብስ /ነገርን መርአዊ/ ገብረ ክርስቶስ ቢሰፋ ፡
ከአለጥፋት ትተርፊ ዘንድ
ነፍሱን ወርቅን ጣዪ አላት ።

## ምስጢር

አንዳንድ ሰነፍ ባለፀጋ ሞትን ዘንግቶ "እንግዴህ ምን አለብኝ ፡ ብዙ ገንዘብ ሰብስቤያለሁ ፡ መደሰት አለብኝ" ይላል ። ገብረ ክርስቶስ ግን የአባቱን መንግስት ትቶ ከወርቅ ይልቅ ክርስቶስን በመከተሉ የሚመጣበትን መከራ መረጠ በማለት ባለቅኔው የገብረ ክርስቶስን አማኝነት በቅኔያቸው ምስጢር አስረድተዋል ።

*395 ዘእምላኪየ (19)ይ*

*ዘቸኮል (ባሕታዊ ፡ ዘወይዘይኝ ማርያም)*

*ሠሪዐ ቤቱ ነዓስ እንተ ኢየአምር ኬፋ*
*የስተሐምም አፎ አብየተ ዘአልፋ?*
*ወለተዘምዶቱ ድቀት እስከነ ሠለስቱ ጸሐፋ ።*

## ትርጉም

ትንሽ ቤቱን መስራት የማያውቅ ጴጥሮስ
ለክርስቶስ ቤቶች እንዴት ያስባል?
ዝምድናው /አወዳደቅንም እስከ ሶስት ቤት ቆጠራት ።



## ምስጢር

"የራሱን ቤተ ሰብ ማስተዳደር የማይችል ቤተ ክርስቲያንን ማስተዳደር አይችልም " በማለት ሃዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አስተምሯል። በደብረ ታቦር ለራሱ ቤት ለመስራት ያላሰበ ጴጥሮስ "ለክርስቶስና ለኤልያስ ፡ ለሙሴም ሶስት ቤቶችን እንስራ" ብሎ ቢናገርም ፡ ይህን ማድረግ እንዴት ይችላል? በማለት ባለቅኔው ቅኔያቸውን አመስጥረዋል ።

*396ዘእምላኪየ ስ*

*ሰማዕተ ልዳ ረከበ ምስለ ኤልያስ ሱታፌ*
*የፍቅር ሀላዌ ወይጽላዕ ኃላፌ ፤*
*አምጣነ እምለፌ ኀየል ወመስተዓግሥ እምለፌ ።*

## ትርጉም

የሚኖርን ይወድና ያለፈን ይጠላ ዘንድ
የልዳ ሰማእት ከኤልያስ ጋር አንድነትን አገኘ ፤
ከዚያ ብርቱ ሰው ነውና ፤ ከዚህም ታጋሽ ነውና ።

## ምስጢር

አንዳንድ ሰው ጓደኛውን ከልቡ ሲያፈቅር ጓደኛው የወደደውን ይወዳል ፡ የጠላውንም ይጠላል ። የሚያልፈውን አለም መከራ በመታገስ የማያልፈውን አለም ተስፋ ያደረገ የልዳ ሰማእት ቅዱስ ጊዮርጊስም እንደ ኤልያስ በተጋድሎው ፀና ይላሉ ባለቅኔው ።

*397 ግእዝ ጉባኤ ቃና ስ*

*ዘጥፉነዘ (አለቃ)*

*ተሐልበት ደመ ላህመ ቤተ ጳውሎስ ሰይፍ ፡*
*ነዳይ ቶማስ እስመ እንሥአ በአፍ ።*

## ትርጉም

የጳውሎስ ቤት ላም /ሰይፍ ደምን ታለበች ፤
ችግረኛ /ቶማስ በአፍ አንስቷታልና ።



www.ethiopianorthodox.org

## ምስጢር

ከቤቱ አርፎ የማይቀመጥ አንዳንድ አግረኛ ሰው ወደሌላው ሰው ቤት ሲሄድ ላሞች ሲታሰቡ ይደርሳል ፤ እንደ እግሩም እንደበቱ አያርፍምና "አቤት! የዚች ላም ጡቷ ምን ያክላል?" ብሎ ይናገራል ፤ በየደረሰበትም ያነሳታል ። ያችም ላም በወተት ፈንታ ደም ትታለባለች ። ሃዋርያው ጳውሎስ የተቆረጠባት ሰይፍም የቶማስን ከንፈሮች በቆረጠች ጊዜ ደሙን አፈሰሰችው ይላሉ ባለቅኔው ።

*398 ዋዜማ (967)ኅ*

*ዘፈቃዴ (አቶ)*

*በዓመተ ሞት ማእረረ ዘሉ*
*ፈለገ ሐሊብ ይውሕዝ እምከናፍሪሁ ለሰይፍ*
*ማየ ዕራቆ ኢይስተይ መትከፍ ፤*
*ወኢዘከረ እክናፈ ሰማዕተ ገሊላ መጽሐፍ*
*እስመ ኀልቆ ሳብዕ አክሊል ፍጹም ክንፍ*
*ነበ ርእሱ ዘየዐርግ ዖፍ ።*

## ትርጉም

በሞት /የሁሉ አዝመራ አመት
ባዶ ውሃን እንዳይጠጣ

ከሰይፍ ከንፈሮች የወተት ወንዝ ይፈሳል ፤
የገሊላ ሰማእት /መፅሃፍ ከንፈሮችን አላስታወሰም፣
የሰባተኛ አክሊል ቁጥር /ፍፁም ክንፍ
ወደራሱ የሚወጣ ወፍ ነውና ።

## ምስጢር

ለመስኖ ልማት አመች የሆነ ወንዝ ከምንጩ ጀምሮ አዝመራ ወዳለበት እንዲፈስ ይደረጋል ። በሰይፍ ከተቆረጠ ከቅዱስ ጊዮርጊስ አንገትም ወተትና ውሃ መነጩ ። አንዳንድ ሀመምተኛ ሰው ውሃና የአትክልት ጭማቂ እየቀላቀለ እንደሚጠጣ በጊዮርጊስ ትከሻ ላይም ውሃም ፤ ወተትም ፈሰሰ ። ሁሉም ነገር በመፅሃፍ ተፅፎ እንደማይገኝ ጊዮርጊስም እንደ መጥምቁ ዮሃንስ አንገቱን ሲቆረጥ ከንፎችን አላወ



ጣም። በእብራውያን የቁጥር ስርአት ሰባት ፍፁም ቁጥር (ሙሉ ቁጥር) እንደሆነ ለጊዮርጊስም በሰባተኛው የስቃይ አመት አክሊል ቢወርድለት፣ ክንፍ ለዮሃንስ ሆነ በማለት ባለቅኔው ቅኔያቸውን አመስጥረዋል ።

*399 ዋዜማ(968)ኅ*

*ዘወልደ ሥላሴ (አለ.ቃ)*

*ተክለ ሃይማኖት አመ ተሰቅለ*
*ዲበ ዕፀ መስቀል ኪሩብ ለቤዛ መንክራት አእላፍ*
*ተረግዘ ገቦሁ በዙናት ክንፍ ፤*
*ወሶበ እምላዕሉ ወረደ መንፈስ አእምሮ ዘዘልፍ*
*ሐዋርያቲሁ አልባሰ አርድእተ መትክፍ*
*ተናገሩ በልሳን ወአፍ ።*

## ትርጉም

በእንጨት መስቀል /ኪሩብ ላይ
ለድንቆች /ወገኖች ቤዛ ተክለ ሃይማኖት በተሰቀለ ጊዜ
በጦር /ክንፍ ጎኑን ተወጋ ፤
የዘወትር እውቀት መንፈስም ከላይ በወረደ ጊዜ
የትክሻ ረዳቶች ሃዋርያቱ /ልብሶች
በምላስና በአፍ ተናገሩ ።

## ምስጢር

ክርስቶስ በእንጨት መስቀል ላይ ለብዙዎች ቤዛ በተሰቀለ ጊዜ ጎኑን በጦር ተወጋ ፤ ኢትዮጵያዊው ፃድቅ አቡነ ተክለ ሃይማኖትም በኪሩብ አምሳል በጎናቸው በሰረፁ ክንፎች በረሩ ። ሃዋርያትም በመንፈስ ቅዱስ ሃይል ልዩ ልዩ ቋንቋን እንደተናገሩ የተክለ ሃይማኖት ልብሶችም አምላክን አመሰገኑ በማለት ባለቅኔው ለተክለ ሃይማኖት ተፈፅሟል የሚባለውን ተአምራዊ ድርጊት አመስጥረዋል ።

*400 ሥላሴ /ስ*

*ኤዎስጣቴዎስ*
*ማእዜ ተኃፍር በእርቃንከ?*
*ዖፍ ጥቀ እንተ ሠረፀት እምዖፍ*



www.ethiopianorthodox.org

*ዕርቃነ እጓላ ትከድን በክንፍ ።*
*ወእንበለ ዛቲ ዐጽፍከ እመ አልብከ ተረፍ ፡*
*እስመ አንተ አብ ኰናኔ ጽንፍ ፡*
*ስዝረ ስዝረ ለይእቲ ዐጽፍ*
*ንትካፈላ ውሉድከ እልፍ ።*

## ትርጉም

ኤዎስጣቴዎስ!
በራቁትነታችን መቼ ታፍራለህ?
ከወፍ የተወለደች ወፍ እንኳን
የልጇን ራቁትነት በክንፍ ትሸፍናለች ፤
ያለዚች አፅፍህም ትርፍ ከሌለህ
ጠረፍ ገዢ አባት ነህና ፤
እልፍ ልጆችህ ይህችን አፅፍ
ስንዝር ስንዝር እንካፈላት ።

## ምስጢር

ልጆችን ማብላትና ማልበስ የወላጆች ግዴታ ነው ፤ ስንኳን ሰውና ወፍ ልጆቿን በአፏ እየለቀመች ትመግባቸዋለች በክንፎቿም አቅፋ ከብርድ ታድናቸዋለች ። ኤዎስጣቴዎስ የተባሉት ኢትዮጵያዊ ፃድቅ የቤተ ክርስቲያናቸው አገልጋዮች ካህናት የእመት ልብስና የእለት ጉርስ እንዲያገኙ የየቀኑን ተግባራቸውን መባረክ ይገባቸዋል ። የልጆች መራቆት ወላጆቻቸውን እንደሚያሳፍራቸው የካህናቱም እጦት ፃድቁን እማላጅ አያስኛቸውም ። የአቡነ ኤዎስጣቴዎስ ልብስ አንዲት ብትሆንም "ከሁለት ልብሶች አንዱን ቢቀሙህ ሁለተኛውንም ስጥ" እንደተባለው ያችው አንዲቱ ለረድኤት ትበቃናለች ይላሉ ባለቅኔው ።

## ታሪክ

በዘመነ እፀባ (በችግር ዘመን) በጎጃም ክፍለ ሀገር በደብረ ወርቅ ማርያም የኖሩ አንድ ሊቅ የሚለብሱት አጥተው በመቸገራቸው ለፃድቁ ለአቡነ ኤዎስጣቴዎስ በአል ዋዜማ ይህን ስላሴ ቅኔ መቀኘታቸው ይተረካል ።



# የባለቅኔዎች አጫጭር የሕይወት ታሪክ

### 1· ሃዲስ ኪዳናት /(ቄሰገበዝ ፡ ዘፅላሎ አማኑኤል)

ቄሰ ገበዝ ሃዲስ ኪዳናት በጎጃም ፡ ክፍለ ሃገር በባህር ዳር አውራጃ በይልማና ዴንሳ ወረዳ በፅላሎ አማኑኤል ደብር ከአባታቸው ከመምህር ኪዳናት ወልደ ሩፋኤል ከእናታቸው ከወይዘሮ የተመኙ ከብቴ በ1863 አ·ም ተወለዱ ።

ቄሰ ገበዝ ሃዲስ ኪዳናት ፀዋትወ ዜማ በደብሩ ከነበሩ መምህራን ተምረዋል ። ከአባታቸው ከመምህር ኪዳናት ወልደ ሩፋኤል ቅኔ ከነአግባቡ ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ። ከዚያም ወደ ጎንደር ክፍለ ሀገር ሄደው በጎንደር ከተማ ከነበሩ ሊቃውንት የመፃህፍት ትርጓሜ እጥንተዋል ። ወደ ቤተ ልሄም ሄደው ድጓ አስመስክረዋል ።

ቄሰ ገበዝ ሃዲስ ኪዳናት ወደ ትውልድ ቦታቸው ወደ ፅላሎ እማኑኤል ተመልሰው ቅኔና የመፃህፍት ትርጓሜ እያስተማሩ አያሌ መምህራንን መርቀው ሾመዋል ። እኚህ ሊቅ በማስተማር ስራቸው ሳይወሰኑ የደብሩ ቄሰገበዝ ሆነው ቅን አገልግሎት አበርክተዋል ።

ቄሰ ገበዝ ሃዲስ ኪዳናት ከሚወዱት የማስተማርና ምስጢረ መፃህፍትን የመመርመር ስራቸው ሳይለዩ በተወለዱ በ65 አመታቸው በ1928 አ·ም አርፈው በደብረ ፅላሎ አማኑኤል ተቀብረዋል ። (ታሪኩ የልጅ ልጃቸው አቶ ተሾመ ሃዲስ ካቀረቡት በምህፃር የቀረበ ነው)

### 2· መራሂ በየነ (አለቃ ፡ ዘጋዛ ቁስቋም

አለቃ መራሂ በየነ በጎንደር ክፍለ ሃገር በደብረ ታቦር አውራጃ በአንጋጫት ማርያም ደብር ከአባታቸው ከመሪጌታ በየነ እንግዳና ከእናታቸው ከወይዘሮ አስናቀች አስረስ በ1892 አ/ም ተወለዱ ። ንባብና ፀዋትወ ዜማ ከእያታቸው ከመሪጌታ እንግዳ ፡ ቅኔ ከነአገባቡ ከአለቃ ደስታ ጠይም በተድባበ ማርያም ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ።

አለቃ መራሂ በየነ በጋይንት አውራጃ የጉና ቅዱስ ሚካኤል ደብር የቅኔ መምህር ሆነው በማስተማር ላይ እንዳሉ የደብሩ ርእሰ ደብር ሆነው ሰርተዋል ። እኚህ ሊቅ ከ1972 እስከ 1976 አ·ም ድረስ የጋዛ ቁስቋምን ደብር በአለቅነት አስተዳድረዋል ።

አለቃ መራሂ በየነ በቅኔ ሙያቸው ከተመሰገኑት ሊቃውንት አንዱ



www.ethiopianorthodox.org

ናቸው ። እኚህ አረጋዊ ሊቅ ከሚወዱት ከማስተማርና ከትሩፋት ስራቸው ሳይለዩ ሰኔ 21 ቀን 1978 ዓ.ም. በተወለዱ በ86 አመታቸው አርፈው በጉና ቅዱስ ሚካኤል ደብር ተቀብረዋል ። (ታሪኩ ልጃቸው ቀሲስ ከፍያለው መራሂ ካቀረቡት በምህፃር የቀረበ ነው) ።

## 3· መዝሙር ካሳ (አለቃ)

አለቃ መዝሙር ካሳ በጎንደር ክፍለ ሀገር ተወለዱ ። በተወለዱበት ክፍለ ሀገር ተምረው የተመሰገኑ ምሁር ሆነዋል ። ምሁርነታቸው ከሚያፈልቀው የንግግራቸው ስምረት የተነሳ ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ያከብሯቸው ነበር ይባላል ።

አለቃ መዝሙር ካሳ የእንጦጦ ማርያምን ቤተ ክርስቲያን እያገለገሉ ሲኖሩ አርፈው በዚሁ ደብር ተቀብረዋል ።

## 4· ሳሙኤል ረታ (አለቃ)

አለቃ ሳሙኤል ረታ በወሎ ክፍለ ሃገር በየጁ አውራጃ በኩላማሶ ወረዳ ተወለዱ ። በዚሁ ክፍለ ሃገር ገዳማትና አድባራት ከነበሩ መምህራን ተምረው የተመሰገኑ ሊቅ ሆነዋል ።

አለቃ ሳሙኤል ረታ በቤተ ክህነት በታሪክና በድርሰት ክፍል ተመድበው በመስራት ላይ እንዳሉ በ1943 ዓ.ም አርፈው በመንበረ ፀባኦት ቅድስት ስላሴ ቤተ ክርስቲያን ተቀብረዋል ።

## 5· ሮብአም (መልአከ ፀሃይ ፡ ዘቁስቋም

መልአከ ፀሃይ ሮብአም በጎጃም ክፍለ ሃገር በሞጣ አውራጃ በመርጡለ ማርያም ሰበካ ተወልደዋል ። ፀዋትወ ዜማና ቅኔ በመርጡለ ማርያም ከነበሩ መምህራን ተማሩ ። ወደ ጎንደር ክፍለ ሀገር ሄደው በጎንደር ከተማ ከነበሩ መምህራን የመፃህፍተ ሊቃውንትን ትርጓሜ ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ።

መልአከ ፀሃይ ሮብአም በጎንደር ከተማ በቁስቋም ደብር የመፃህፍተ ሊቃውንትን ትርጓሜ በማስተማር አያሌ ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል። መልአከ ፀሃይ ተብለውም የቁስቋምን ደብር በአለቅነት አስተዳድረዋል ። እኚህ ሊቅ ከሚወዱት የማስተማርና ምስጢረ መፃህፍትን የመመርመር ስራ ሳይለዩ ኖረው አርፈዋል ።



## 6· ቀፀላ ሃይሉ (መምህር ፡ ዘዋሸራ)

መምህር ቀፀላ ሃይሉ በጎጃም ክፍለ ሃገር በዋሸራ ማርያም ሰበካ ተወልደዋል ። በተወለዱበት ክፍለ ሃገር አድባራትና ገዳማት ከነበሩ ሊቃውንት ተምረው የቅኔ መምህር ለመሆን በቅተዋል ።

የመምህር ቀፀላ ሃይሉ የመምህርነት ዘመን የአፄ ቴዎድሮስን ፣ የአፄ ዮሃንስንና የአፄ ምኒልክን ዘመነ መንግስት ያጠቃልላል ። በዚህም ጊዜ አያሌ ደቀ መዛሙርትን በቅኔ መምህርነት ሾመዋል ። እኚህ አረጋዊ ሊቅ ተወልደው ባስተማሩበት በዋሸራ ማርያም ደብር አርፈው በዚያው ተቀብረዋል ።

## 7· በሻህ (አለቃ ፡ ዘራጉኤል)

አለቃ በሻህ በሸዋ ክፍለ ሃገር ተወለዱ ። በዚሁ ክፍለ ሃገር ከነበሩ መምህራን ተምረው በቅኔ ሙያቸው የተመሰገኑ ሊቅ ሆነዋል ።

አለቃ በሻህ አንጎለላ ኪዳነ ምህረትን በአለቅነት አስተዳድረዋል ። እኚህ ሊቅ ከአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ አገራቸውንና ቤተ ክርስቲያንን በቅንነት ሲያገለግሉ ኖረው አርፈዋል ።

## 8· በቀለ ጎበና (አለቃ ፡ ዘየውሽ ሚካኤል)

አለቃ በቀለ ጎበና በጎጃም ክፍለ ሀገር በብቸና አውራጃ በእናርጅ እናውጋ ወረዳ በድንቻ ማርያም ለበካ ከአባታቸው ከግራዝማች ጎበና ካሳና ከእናታቸው ከወይዘሮ ለመች ሚያዝያ 17 ቀን 1892 ዓ.ም ተወለዱ።

አለቃ በቀለ ጎበና በተወለዱ በአራት አመታቸው በኩፍኝ ህመም አይናቸው ጠፋ ። አለቃ በቀለ ጎበና ከመጣያ ቅዱስ ሚካኤል መምህር ከመሪ ጌታ አለሙ ፀዋትወ ዜማ ፣ ከዋሸራው የቅኔ ሊቅ ከመምህር ተክሌ ቅኔና አገባብ ጠንቅቀው ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ። እኚህ ሊቅ የሃዲሳትንና የሃይማኖተ አበውን ትርጓሜ ከሞጣ ጊዮርጊስ ደብር መምህር ከአለቃ ተሰፋ ፣ የብሉያትን ትርጓሜ ከመርጡለ ማርያም ገዳም መምህር ከመምህር ፊላታዎስ ተምረው ለመምህርነት በቅተዋል ።

አለቃ በቀለ ጎበና ከ1918—1924 በወለጋ ክፍለ ሃገር ፍትሃ ነገስት አውጭ ሆነው ሰርተዋል ። እኚህ ሊቅ ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረችበት ወቅት የጎጃምንና የሸዋን አርበኞች በደብዳቤ በማገናኘትና



www.ethiopianorthodox.org

የጠላትን ምስጢር በማቀበል የአርበኝነት ተግባር ፈፅመዋል ።

አለቃ በቀለ ጎበና ከ1937 አ·ም· ጀምሮ በጎጃም ክፍለ ሃገር ደብረ ወርቅ ማርያምን በግብዝና ፥ በጋሞ ጎፋ ክፍለ ሀገር ብርብር ማርያምን ፤ በሸዋ ክፍለ ሃገር ጐጌቴ ገብርኤልን በጎጃም ክፍለ ሃገር ደብረመንክራት የውሽ ሚካኤልን በአለቅነት አገልግለዋል ።

አለቃ በቀለ ጎበና በአዲስ አበባ ከተማ የአራዳ ገነተ ፅጌ ጊየርጊስ የቅኔ መምህር ሆነው ሲያስተምሩ አያሌ ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል ። እኒህ አረጋዊ ሊቅ በተወለዱ በ86 አመታቸው በ1978 አርፈው በአዲስ አበባ ከተማ በደብረ ናዝሬት በቅዱስ ዮሴፍ ቤተ ክርስቲያን ተቀብረዋል (ታሪኩ ልጃቸው አቶ ዘርአ ያእቆብ በቀለ ካቀረቡት በምህፃር የቀረበ ነው)

## 9· ነጋሽ ሃይሉ (አለቃ)

አለቃ ነጋሽ ሃይሉ በጎንደር ክፍለ ሃገር በደብረ ታቦር አውራጃ በማህደረ ማርያም ሰበካ ተወለዱ ። ፀዋትወ ዜማ በተወለዱበት ደብር ተማሩ ። ከዚያም ወደ ጎጃም ክፍለ ሃገር ተሻግረው ከአለቃ ወልደ ጊዮርጊስ በዲማ ጊዮርጊስ ቅኔና የመፃህፍት ሊቃውንትን ትርጓሜ አጠኑ።

አለቃ ነጋሽ ሃይሉ በተለይም በቅኔ ሙያቸው የተመሰገኑ ነበሩ ። እኒህ ሊቅ የደብረ ፅጌ ቅዱስ ጊዮርጊስን ቤተ ክርስቲያን ሲያገለግሉ ኖረው አርፈዋል ።

## 10· አስራት ንዋይ (ድማሃ ገነት ፥ ዘደብረ ገነ[illegible] ኤልያስ)

ድማሃ ገነት አስራት ንዋይ በጎጃም ክፍለ ሃገር በደብረ ማርቆስ አውራጃ በደብረ ገነት ኤልያስ በ1844 አ·ም ተወለዱ ። በተወለዱበት ክፍለ ሃገር ገዳማትና አድባራት ከነበሩ መምህራን ተምረው የፀዋትወ ዜማ ፥ የቅኔና የመፃህፍት ትርጓሜ ሊቅ ለመሆን በቅተዋል ። እኒህ ሊቅ በቁም ፅህፈት ሙያም እጅግ የተመሰገኑ ነበሩ ።

ድማሃ ገነት አስራት የጎጃሙ ንጉስ የንጉስ ተክለ ሃይማኖት ፀሃፌ ትእዛዝ ሆነው ለብዙ አመታት ሰርተዋል ። እኒህ አረጋዊ ሊቅ መልአከ ሰላም ተብለው ደምበጫ ሚካኤልን ፥ መልአክ ገነት ሆነው ሞጣ



ጊዮርጊስን፡ ድማሃ ገነት ተሰኝተው ደብረ ገነት ኤልያስን አስተዳድረዋል።

ድማሃ ገነት አስራት ንዋይ ከንጉስ ተክለ ሃይማኖት ልጅ ከልኡል ራስ ሃይሉ ተክለ ሃይማኖት ጋር በአስተዳደር ስራ ተጣልተው ለአቤቱታ እንደመጡ ፋሽስት ኢጣልያ ኢትዮጵያን ስለወረረች እምስቱን የስቃይና የመከራ አመታት በአዲስ አበባ ከተማ ልጆቻቸውን ይዘው አሳልፈዋል ። ከጠላት ወረራ በሁዋላም ደብረ ገነት ኤልያስን እስከ 1944 አ·ም ድረስ አገልግለዋል ። የስእል ስጦታም ስለነበራቸው ከቀድሞው ንጉስ ቀዳማዊ ሃይለ ስላሴ ተሸልመዋል ።

ድማሃ ገነት አስራት ንዋይ በአስተዳደር ጉዳይ ለአቤቱታ እንደ መጡ በአዲስ አበባ ከተማ በ1944 አ·ም አርፈው በድናቸው በዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ታክሞ በተወለዱበት ደብር በደብረ ገነት ኤልያስ ቤተ ክርስቲያን እቃ ቤት ሳይቀበር አረፈ ።

ስለሹመታቸው ግን እኔ ያልተሾምሁበት ደብር የለም ይሉን ነበር ። እኛ ግን የደረስንበትና ያየነው "አሀዱ እምሊቃናት መልአከ ገነት አስራት" የሚል ማህተም ነው ። ይህም የሞጣ ጊዮርጊስ መሆኑ ነው ። (ታሪኩን በቃል ያፃፉን የልጅ ልጃቸው ዶክተር ኢሳይያስ አለሜ ናቸው)

## 11· አወቀ (አለቃ ፥ ዘወቄጣ ማርያም)

አለቃ አወቀ በወሎ ክፍለ ሃገር በላስታ አውራጃ በሽድሆ ወረዳ ባወቄጣ ማርያም ደብር ተወልደዋል ። በወሎ ፥ በጎንደርና በጎጃም ገዳማትና አድባራት ከነበሩ መምህራን ተምረው የተመሰገኑ የቅኔ መምህር ሆነዋል ።

አለቃ አወቀ በተወለዱበት ደብር በወቄጣ ማርያም ፥ በትግራይ ክፍለ ሃገር ቀቀማ በሚባለው ገዳምና በኤርትራ ክፍለ ሃገር በደብረ ቢዘን ገዳም ቅኔ አስተምረው አያሌ ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል ።

አለቃ አወቀ በዋልድባ ገዳም ስርአተ ምንኩስና ተቀብለው ሲኖሩ በ1929 አ·ም አርፈዋል ።

## 12· አፈወርቅ ትኩየ (መሪጌታ ፥ ዘሰይፍአጥራ ማርያም)

መሪጌታ አፈ ወርቅ ትኩየ ከአባታቸው ከደብተራ ትኩየ ለውጤና



www.ethiopianorthodox.org

ከእናታቸው ከወይዘሮ ግንብወግሽ ቢያበይን በጎንደር ክፍለ ሃገር በጎንደር ዙርያ አውራጃ በወይብላ በእታ ደብር በ1896 አ·ም ተወለዱ ።

በሰይፍ አጥራ ማርያም ከነበሩት ከአባ ገብረ ህይወት ንባብ ፤ መዝገበ ቅዳሴና ፀዋትወ ዜማ ተማሩ ። በለሳ ከሙር ሃንገብ ኪዳነ ምህረት ደብር መምህር ከመሪጌታ ተክለ ኢየሱስ ፡ ደንቢያ ከጉርአምባ ሚካኤል ደብር መምህር ከመሪጌታ ፅጌ ፡ መልዛ ከሳርንኮ ሚካኤል መምህር ከአለቃ ህሩይ ፤ ወገራ ከጉንትር አቦ መምህር ከመሪጌታ ብዙአየሁ ፤ ሊቦ ከሚካኤል ደብር መምህር ከጌቴ ገሞራው ቅኔ ከነአርባቅምሩና ከነአገባቡ ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ። መሪጌታ አፈወርቅ ትኩየ ከደንገርሳ ጊዮርጊስ መምህር ከመሪጌታ ሃይሉ የላይ ቤት አቋቋም ፤ በጎንደ ተክለ ሃይማኖት ከአባ ፅህማ ባህረ ሃሳብና አቡሻህር ቀፅለዋል ።

እኒህ ሊቅ ወገራ የማይልኮ ኢየሱስ ደብር የቅኔ መምህር ሆነው ባስተማሩባቸው አመታት እያሌ ደቀመዛሙርትን አፍርተዋል ። ከዚያም ወደ ሰይፍ አጥራ ማርያም ተመልሰው ፀዋትወ ዜማና መዝገበ ቅዳሴ እያስተማሩ ሲኖሩ በ1964 አ·ም በተወለዱ በ68 አመታቸው አርፈው በዚሁ ደብር ተቀብረዋል ። (ታሪኩ ልጃቸው አቶ ሳህለ ማርያም አፈ ወርቅ ካቀረቡት በምህፃር የቀረበ ነው) ።

## 13· ኪዳናት ወልደ ሩፋኤል (መምህር ፡ ዘፅላሎ አማኑኤል)

መምህር ኪዳናት ወልደ ሩፋኤል በጎጃም ክፍለ ሃገር በባህር ዳር አውራጃ በይልማና ዴንሳ ወረዳ በደብረ ፅላሎ አማኑኤል ሰበካ ከመምህር ወልደ ሩፋኤልና ከወይዘሮ ሂሩት በ1843 አ·ም ተወለዱ ።

ፀዋትወ ዜማ ፡ ቅኔና የመፃህፍት ትርጓሜ በደብረ ፅላሎ አማኑኤል ከነበሩ ሊቃውንት ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ። ከዚያም ወደዋድላ [illegible] በዚያው ከነበሩ ሊቃውንት የቅኔ ፡ አርባ ቅምርና [illegible] አደላድለው ወደትውልድ ደብራቸው ወደ ፅላሎ [illegible]ል ።

[illegible] ወልደ [illegible] የፅላሎ አማኑኤል ደብር የቅ[illegible] [illegible]ምህር [illegible] በ40 አመታት [illegible] [illegible] ተመርቀዋል ።

መምህር ኪዳናት ወልደ ሩፋኤል ከሚወዱት የማስተማርና ምስጢረ መፃህፍትን የመመርመር ስራቸው ሳይለዩ በተወለዱ በ61 አመታቸው በ1904 አ·ም· አርፈው በፅላሎ አማኑኤል ደብር ተቀብረዋል ። (ታሪኩን የባለታሪኩ የልጅ ልጅ አቶ ተሾመ ሃዲስ ካቀረቡት በምህፃር የቀረበ ነው) ።

## 14· ወልደ ኢየሱስ (ሊቀጠበብት ፡ ዘመንበረ መንግስት)

ሊቀ ጠበብት ወልደ ኢየሱስ በጎጃም ክፍለ ሃገር ተወልደዋል ። በተወለዱበት ክፍለ ሃገር ከሚገኙ ገዳማትና አድባራት ከነበሩ ሊቃውንት ፀዋትወ ዜማ ፡ ቅኔና የብሉያትን ትርጓሜ ተምረው የተመሰገኑ ሊቅ ሆነዋል ።

ሊቀ ጠበብት ወልደ ኢየሱስ በአዲስ አበባ ከተማ የመንበረ መንግስት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በመዘምርነት አገልግለዋል። በዚሁም ጊዜ የደብሩ ሊቀጠበብት ሆነው ሰርተዋል ።

ሊቀ ጠበብት ወልደ ኢየሱስ ሃምሌ 9 ቀን 1947 አ·ም· አርፈው በመንበረ ፃባኦት ቅድስት ስላሴ ቤተ ክርስቲያን ተቀብረዋል ።

## 15· ወልደ ሚካኤል (መምህር ፡ ዘዜና ማርቆስ)

መምህር ወልደ ሚካኤል በሸዋ ክፍለ ሃገር በዜና ማርቆስ ገዳም አካባቢ ተወልደዋል ። በትውልድ ስፍራቸው ከነበሩ መምህራን ፀዋትወ ዜማና ቅኔ ተምረዋል ።

መምህር ወልደ ሚካኤል ወደ ጎንደር ክፍለ ሃገር ሄደው በጎንደር ከተማ ከነበሩ ሊቃውንት የመፃህፍተ ሊቃውንትን ትርጓሜ ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ።

መምህር ወልደ ሚካኤል የዜና ማርቆስ ገዳም አስተዳዳሪ ሆነው በማገልገል ላይ እንዳሉ ፡ እርሳቸውና የገዳሙ መነኮሳት ለፋሽስቱ የኢጣልያ መንግስት አንገዛም በማለታቸው የፋሽስት ኢ[illegible]ልያ ጦር ግንቦት 21 ቀን 1929 አ·ም· ገዳሙን ሲያቃጥል በሰማእትነት አርፈዋል ።

## 16· ወልደ አብ (አለቃ)

አ[illegible] ወልደ አብ በሸዋ ክፍለ ሃገር ተወለዱ ። ፀዋትወ ዜማ

www.ethiopianorthodox.org

በተወለዱበት ክፍለ ሃገር ተማሩ ። ወደ ጎንደር ክፍለ ሃገር ሄደው በጎንደር ከተማ ከመምህር ኤስድሮስ የሃዲስ ኪዳንን ትርጓሜ ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ። እኒህ ሊቅ የአረብኛ ቋንቋ አጥንተው በአረብኛና በግእዝ የተፃፉ መፃህፍትን እየመረመሩ የተለያየውን እያስማሙ የጎደለውን ይሞሉ ነበር ይባላል ።

አለቃ ወልደ አብ የመምህራቸውን የመምህር ኤስድሮስን ጉባኤ ተረከበው በማስተማር አያሌ የሃዲስ ኪዳን ትርጓሜ መምህራንን መርቀው ሾመዋል ። እኒህ ሊቅ ከሚወዱት የማስተማርና ምስጢረ መፃህፍትን ከመመርመር ስራቸው ሳይለዩ ኖረው አርፈዋል ።

## 17· ወልደ ኪዳን ጀምበሬ (አለቃ ፡ ዘደብረ ታቦር)

አለቃ ወልደ ኪዳን ጀምበሬ በጎጃም ክፍለ ሃገር በአገው ምድር አውራጃ በአስዋ ሚካኤል ቀበሌ በ1893 ዓ·ም· ተወለዱ ። በአምስት አመታቸው በከፍኛ በሽታ አይነ ስውር ሆኑ ።

በተወለዱበት ደብር ዳዊት ከደገሙ በሁዋላ ወላጅ እናታቸው እየመሯቸው ወደ ደብረ ታቦር ኢየሱስ ሄዱ ። ከደብረ ታቦር ኢየሱስ የድጓ መምህር ከመምህር ወልደ ስላሴ ፀዋትወ ዜማ ፡ የተክሌ አቋቋም ምስክር ከነበሩት ከአለቃ መኮንን አቋቋም ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ።

ከኤልሻማ መድሃኔ አለም የቅኔ መምህር ከአለቃ ምስራቅ ቅኔ ተምረው በማስተማር ስራ መምህራቸውን እስከመርዳት ደርሰዋል ። የመዝሙረ ዳዊትና የፍትሃ ነገስት ትርጓሜም አጥንተዋል ።

አለቃ ወልደ ኪዳን ጀምበሬ በተማሩበት በደብረ ታቦር ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ከ40 አመታት በላይ ድጓና ፆመ ድጓ አስተምረው አያሌ ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል ። እኒህ ሊቅ በማህሌታዊ ድምፃቸው እጅግ የተደነቁ ነበሩ ። ከዚህም የተነሳ ራስ ጉግሳ ወሌ "ስለሃምሳ" በማለት ማህሌታዊ ድምፃቸው የ50 ደብተራ ድምፅ ያህል መሆኑን መስክረውላቸዋል ።

አለቃ ወልደ ኪዳን ጀምበሬ ከሚወዱት የማስተማርና የማህሌት ስራ ሳይለዩ በኖሩበት በደብረ ታቦር ኢየሱስ መስከረም 13 ቀን 1974 ዓ·ም· በተወለዱ በ81 አመታቸው አርፈው በዚሁ ደብር ተቀብረዋል ። (ታሪኩ ልጃቸው አቶ ማህቶት ወልደ ኪዳን ካቀረቡት በምህፃር የቀረበ ነው ።)



## 18· ዋሴ (አለቃ ፡ ዘድንግራ ማርያም)

አለቃ ዋሴ በጎጃም ክፍለ ሀገር ድንግራ ማርያም በምትባለው ደብር ተወልደዋል ። እኒህ ሊቅ በጎጃምና በጎንደር ከነበሩ ሊቃውንት ቅኔ ፡ አቋቋም ፡ የሃዲስና የፍትሃ ነገስት ትርጓሜ ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ።

አለቃ ዋሴ የድንግራ ማርያምን ደብር እያስተዳደሩ ቅኔ ፡ አቋቋም ፡ የሃዲስና የፍትሃ ነገስት ትርጓሜ አስተምረዋል ። እኒህ አረጋዊ ሊቅ ከሚወዱት የማስተማር ስራቸው ሳይለዩ ተምረው ባስተማሩበት ደብር በድንግራ ማርያም አርፈዋል ።

## 19· ደስታ ሃሊቡ (መምህር ፡ ዘዋሸራ)

መምህር ደስታ ሃሊቡ በጎጃም ክፍለ ሃገር በድንግራ ማርያም ደብር ሰበካ ተወለዱ ። መምህር ደስታ ሃሊቡ ቅኔ በጎንጅ ቴዎድሮስ ከቄስ ገበዝ በቃ ፤ ብሉይ ፡ ሃዲስና ፍትሃ ነገስት ከመምህር ገብረ መድህን በዋሸራ ማርያም ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ።

መምህር ደስታ ሃሊቡ በተማሩበት በዋሸራ ማርያም ደብር የብሉይን ፡ የሃዲስንና የፍትሃ ነገስትን ትርጓሜ አስተምረው አያሌ ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል ። እኒህ ሊቅ ከጉባኤያቸው ሳይለዩ የዋሸራ ማርያም አስተዳዳሪ ሆነው አገልግለዋል ።

መምህር ደስታ ሃሊቡ በሊቅነታቸው ብቻ ሳይሆን በምግባረ ሰናይም እጅግ የታወቁ ነበሩ ። ለተማሪዎቻቸው የአመት ልብስ የእለት ጉርስ እየሰጡ ስለሚያስተምሩ ፡ ደቀ መዝሙሮቻቸው ልብስና ምግብ ለማግኘት የሚያውሉትን ጊዜ በትምህርትና በጥናት ላይ ያውሉት ነበር ። አብሮአቸው የሚበላ እንግዳ ወይም ያጣ የነጣ ድሃ ሰው በቤታቸው ውስጥ ካልተገኘ ምግብ አይበሉም ነበር ይባላል ።

## 20· ዶሪ (አለቃ ፡ ዘጨለቆት ስላሴ)

አለቃ ዶሪ በትግራይ ክፍለ ሃገር በጨለቆት ስላሴ ደብር ተወለዱ ። በትግራይ ፡ በጎንደርና በጎጃም ከነበሩ ሊቃውንት ተምረው የተመሰገኑ የቅኔ መምህር ሆነዋል ። በትግራይና በሸዋ በሚገኙ አድባራትና ገዳማት ቅኔ አስተምረው አያሌ ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

አለቃ ዶሪ በአፄ ዮሃንስና በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት ሰፌ ጉባኤ የነበራቸው በመሆኑ "ዶሪ ቅኔ ፈጣሪ" እያለ ህዝቡ ሳይቀር ያመሰግናቸው እንደነበር ይነገራል ። እኚህ ሊቅ የሚወዱትን የቅኔ ሙያ በማስተማር ላይ እንዳሉ አርፈው በደብረ ሊባኖስ ገዳም ተቀብረዋል ።

## 21· ገላነሽ ሃዲስ (እማሆይ ፣ ዘፅላሎ አማኑኤል)

እማሆይ ገላነሽ ሃዲስ በጎጃም ክፍለ ሀገር በባህር ዳር አውራጃ በይልማና ዴንሳ ወረዳ በፅላሎ አማኑኤል ደብር ከአባታቸው ከቄስ ገበዝ ሃዲስ ኪዳናትና ከእናታቸው ከወይዘሮ ወርቅነሽ እንግዳ በ1898 ዓ·ም· ተወለዱ ። በተወለዱ በስምንት አመታቸው በኩፍኝ በሽታ አይናቸው ጠፋ ። በዚህም ምክንያት ቄስ ገበዝ ሃዲስ ኪዳናት ልጃቸው እማሆይ ገላነሽን ለማስተማር ወሰኑ ።

እማሆይ ገላነሽ ሃዲስ ከአባታቸው ከቄስ ገበዝ ኪዳናት ቅኔ ከነአገባቡ ፣ የብሉይንና የሃዲስን ኪዳኖች ትርጓሜ ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ። እማሆይ ገላነሽ ሃዲስ በመምህርነት ከተመረቁበት ጊዜ ጀምሮ አባታቸው ቄስ ገበዝ ሃዲስ ኪዳናት እስካረፉበት እስከ 1928 ዓ·ም· ድረስ በማስተማር ስራ አባታቸውን ረድተዋል ።

እማሆይ ገላነሽ ሃዲስ ተወልደው ባደጉበት ፣ ተምረውም ለመምህርነት በበቁበት በፅላሎ አማኑኤል ደብር ከ50 አመታት በላይ ቅኔ አስተምረው እያሌ መምህራንን በቅኔ መምህርነት መርቀው ሾመዋል ። እማሆይ ገላነሽ ሃዲስ ከሚወዱት የማስተማር ስራቸው ሳይለዩ ሃምሌ 12 ቀን 1978 ዓ·ም· በተወለዱ በ80 ዓመታቸው አርፈው በፅላሎ አማኑኤል ደብር ተቀብረዋል ። (ታሪኩ የእህታቸው ልጅ አቶ ተሾመ ሃዲስ ካቀረቡት በምህፃር የቀረበ ነው ) ።

## 22· ገብረ ኢየሱስ (አለቃ ፣ ዘደብረ ብርሃን)

አለቃ ገብረ ኢየሱስ በሸዋ ክፍለ ሃገር ተወለዱ ። በጎንደር ከተማ ከነበሩ ሊቃውንት የመፃህፍተ ሊቃውንትን ትርጓሜ ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ።

አለቃ ገብረ ኢየሱስ የመፃህፍተ ሊቃውንትን ትርጓሜ አስተምረው እያሌ ደቀ መዛሙርትን በመምህርነት ሾመዋል ። እኚህ ሊቅ በአፄ



ቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት ፍትሃ ነገስት አውጭ ሆነው ሰርተዋል ። በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት ደብረ ብርሃን ስላሴን በአለቅነት አስተዳድረዋል።

አለቃ ገብረ ኢየሱስ በቅኔ ሙያ ከሚመሰገኑት ሊቃውንት መካከል አንዱ ናቸው ። እኚህ ሊቅ በቅኔያቸው ብስለት ቅኔ ፈጣሪ የሚል ቅፅል ተሰጥቷቸዋል ።

አለቃ ገብረ ኢየሱስ ለቤተ ክርስቲያንና ለሃገራቸው የሚጠቅም አገልግሎት ሲያበረክቱ ኖረው አርፈዋል ።

## 23· ኀበዜ (አለቃ ፣ ዘደብረ ወርቅ)

አለቃ ኀበዜ በጎጃም ክፍለ ሃገር በደብረ ወርቅ ማርያም ሰበካ ተወልደዋል ። ፀዋትወ ዜማና ቅኔ ከደብረ ወርቅ ማርያም መምህራን ተማሩ ። የብሉይ ኪዳን ፣ የሃዲስ ኪዳንና የመፃህፍተ ሊቃውንትን ትርጓሜ ከመምህር ሰው አገኘሁና ከአለቃ ገብረ ኤልያስ ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ። እኚህ ሊቅ በተለይ በቅኔ ሙያ ከሚመሰገኑት ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት አንዱ ናቸው ።

አለቃ ኀበዜ የእንጦጦ ማርያምን ደብር በአለቅነት አስተዳድረዋል። የራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት አማካሪም ሆነው ሰርተዋል ።

አለቃ ኀበዜ ወደትውልድ ቦታቸው ወደ ደብረ ወርቅ ተመልሰው ምስጢረ መፃህፍትን እየመረመሩ ሲኖሩ አርፈው በዚሁ ደብር ተቀብረዋል ።

## 24· ጓሉ (ቄስ ገበዝ ፣ ዘዲማ)

ቄስ ገበዝ ጓሉ በጎጃም ክፍለ ሃገር በዲማ ጊዮርጊስ ሰበካ ተወለዱ ። ቄስ ገበዝ ጓሉ በተወለዱበት ገዳም ተምረው የተመሰገኑ የቅኔና የመፃሕፍት ትርጓሜ ሊቅ ሆነዋል ።

ቄስ ገበዝ ጓሉ የዲማ ጊዮርጊስን ገዳም በግብዝና ባገለገሉበት ወቅት ደጃዝማች ብሩ ጎሹ የገዳሙን ቅፈፍ ነጥቀው የወታደር መተዳደሪያ ባደረጉ ጊዜ አፈፃፀሙ ተገቢ አለመሆኑን በማስረዳት የገዳሙን መብት ለማስጠበቅ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል ። ይህንንም በተራ ቁጥር 3 በተተረጎመው ቅኔያቸው ገልጠውታል ።

ቄስ ገበዝ ጓሉ ተወልደው ያደጉበትን ፣ ተምረውም ሊቅ ለመባል የበቁበትን የዲማ ጊዮርጊስን ገዳም ሲያገለግሉ ኖረው አርፈዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

## 25· ጥሩነህ (አለቃ ፡ ዘቦታ ኪዳነ ምህረት)

አለቃ ጥሩነህ በጎጃም ክፍለ ሃገር በባህር ዳር አውራጃ በአቸፈር ወረዳ ተወለዱ ። አለቃ ጥሩነህ ከመምህር ተክሌ በዋሸራ ፡ ከመምህር ገሰሰ በይስማላ ጊዮርጊስ ቅኔ ከእነአርባ ቅምሩና ከነአገባቡ ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ። ወደጎንደርም ሄደው በበለሳና በዋድላ ከነበሩ መምህራን የየቤቱን አርባ ቅምር ፡ የአገባብና የቅኔ ጎዳና ልዩነት አጥንተው የቅኔ መምህርነት ሙያቸውን አደላድለዋል ።

አለቃ ጥሩነህ ወደወሎ ክፍለ ሃገር ሄደው በቦረና አውራጃ ከአደሬ ማርያም ደብር ሊቅ ከመምህር ጩፋ አቡሻህር አጥንተዋል ። የቅኔና የአቡሻህር ሊቅ የነበሩት መምህር ጩፋ ካረፉ በሁዋላ በመምህራቸው ወንበር ተተክተው አስተምረዋል ።

አለቃ ጥሩነህ ፋሽስት ኢጣልያ ኢትዮጵያን በወረረች ጊዜ የማስተማርና የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ስራቸውን በቦታ ኪዳነ ምህረት ቀጥለዋል ። እኚህ ሊቅ ከሚወዱት የማስተማርና የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ስራቸው ሳይለዩ አርፈው በቦታ ኪዳነ ምህረት ተቀብረዋል ። (ታሪኩ ደቀ መዝሙራቸው አለቃ አፈ ወርቅ ፀውዴ ካቀረቡት በምህፃር ቀርቧል) ።

## 26· ጥበቡ ካሳ (መሪጌታ ፡ ዘቦገና ግራር ኢየሱስ)

መሪጌታ ጥበቡ ካሳ በጎጃም ክፍለ ሃገር በደብረ ማርቆስ አውራጃ በቦገና ግራር ኢየሱስ ደብር ከአባታቸው ከመሪጌታ ካሳና ከእናታቸው ከወይዘሮ አለሙሽ ገብሬ በ1882 ዓ·ም· ተወለዱ ።

መሪጌታ ጥበቡ ካሳ ንባብና ፀዋትወ ዜማ ከአባታቸው ከመሪጌታ ካሳና ከአጎታቸው ከመሪጌታ ልመንህ ገብሬ ተምረዋል ። ቅኔና የመፃህፍተ ብሉያትን ትርጓሜ ከመምህር ተክሌ ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ። ወደ ዋድላም ሄደው በዚያ ከነበሩ መምህራን የቅኔና የአገባብ ሙያቸውን አደላድለዋል ።

መሪጌታ ጥበቡ ካሳ በተወለዱበት ደብር በቦገና ግራር ኢየሱስ ከ1916 ዓ·ም· ጀምሮ ቅኔና አገባብ በማስተማር አያሌ ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል ። እኚህ ሊቅ የሚወዱትን የማስተማር ስራ ሳያቋርጡ በተወለዱ በ74 አመታቸው በ1956 ዓ·ም· አርፈው በቦገና ግራር ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ተቀብረዋል ። (ታሪኩ የአጎታቸው የልጅ ልጅ ዶክተር ሃዲስ የሻነው ካቀረቡት በምህፃር የቀረበ ነው) ።



## ባለቅኔዎቹ
## በፊደል ተራ

(የቅኔዎቻቸው ቁጥሮች ከስሞቻቸው ጋር ሰፍረዋል ። ከስማቸው በፊት የኮከብ ምልክት የተደረገባቸው የህይወት ታሪካቸው ባጭሩ ተፅፎላቸዋል) ።

---


1 ሃብቴ (ደብተራ ፡ ዘሸንኩርት ሚካኤል) 7 ፡ 372
2 ሃብተ ድንግል (ራቅማስሬ) 50
3 ሃይለ ስላሴ (አለቃ) 257
★ 4 ሃዲስ ኪዳናት (ቄስ ገበዝ ፡ ዘዕላሎ) 51 ፡ 234
5 ሀሩይ ወልደ ስላሴ (ብላቴን ጌታ) 365
6 ሀሩይ ፋንታ (አለቃ) 390
7 ለማ ሀይሉ (አለቃ) 161
8 መርሃዕድቅ (ግራጌታ) 121
★ 9 መራሂ (አለቃ ፡ ዘጉና ሚካኤል) 311 ፡ 353
10 መርሻ (አለቃ) 230
11 መርሻ ሃይሉ (መጋቢ ፡ ዘዲማ ጊዮርጊስ) 333
12 መኮንን ስሎሞን (አለቃ) 337
★ 13 መዝሙር ካሳ (አለቃ) 338
14 ምሥራቅ (አለቃ ፡ ዘኤልሻማ) 26 ፡ 207 ፡ 286 ፡ 287 ፡ 290 ፡ 348 ፡ 349 ፡ 363
15 ምንደስይል (አባ) 249
16 ምንደስይል (ደብተራ) 103
17 ሞገስ (መምህር ፡ ዘግሽን ማርያም) 347
18 ራስወርቅ (መምህር) 213
★ 19 ሮብአም መልአከ ፀሃይ) 150
★ 20 ሳሙኤል (አለቃ ፡ ዘግሽን ማርያም) 324
★ 21 ቀፀላ ሃይሉ (መምህር ፡ ዘዋሸራ) 194
22 ቀፀላ (ሊቄ) 240
23 ቃማ (አባ) 156




www.ethiopianorthodox.org

★ 24 በሻህ (አለቃ ፣ ዘራጉኤል) 95
25 በቀለ ጎበና (አለቃ ፣ ዘየውሽ ሚካኤል) 232 ፣ 233 ፣ 385
26 በቃ (ቄስ ገበዝ ፣ ዘጎንጅ) 159 ፣ 219 ፣ 253
27 ተሰማ (አለቃ ፣ ዘቀራንዮ) 304
28 ተካልኝ (ቀኛዝማች ፣ ዘየነጃሚካኤል) 277 ፣ 315
29 ተክለ ማርያም (አለቃ) 319
30 ተክለ ስላሴ (አለቃ) 352
31 ተክሌ (መምህር ፡ ዘዋሸራ) 136 ፣ 199 ፣ 201 ፣ 359
32 ተክለ ፅዮን (አለቃ) 187 ፡ 188 ፣ 375
33 ተዋነይ ፡ 8
34 ተድላ (መምህር) 173
35 ተጠምቆ (አለቃ) 269 ፡ 342
36 ታመነ (አለቃ) 231
37 ቸኮል (ባህታዊ ፡ ዘወይበይኝ ማርያም) 395
38 ነቅአ ጥበብ (አለቃ) 96 ፡ 145
★ 39 ነጋሽ ሃይሉ (አለቃ) 37
40 ናሁዳ (አለቃ) 252 ፡ 386
41 ናትናኤል ፡ 134
42 አለማየሁ ፈንታ (አለቃ) 196
43 አልታሰብ (አለቃ ፣ ዘደብረ ሃይል) 42
44 አስበፃድቅ (አለቃ) 220
45 አስራት ንዋይ (ድማሃ ገነት ፡ ዘኤልያስ) 305
46 አስፋው (መሪጌታ ፡ ዘተድባበ ማርያም) 312
47 አርአያ ወረታ (አቶ) 178 ፣ 227
48 አካለወልድ (መምህር) 98 ፣ 203 ፣ 259
★ 49 አወቀ (አለቃ ፣ ዘወቄጣ ማርያም) 238
50 አድማሱ ጀንበሬ (መልአከብርሃን) 11 ፣ 12 ፣ 17 ፣ 52 ፣ 106 ፣
171 ፣ 216 ፣ 239 ፣ 244 ፣ 250 ፣318
51 አድማሱ ጌትየ (ንቡረ እድ) 280 ፣ 355
52 አፈወርቅ ዘውዴ (አለቃ) 30
★ 53 አፈወርቅ (መምህር ፣ ዘአክሱም) 21



54 አፈወርቅ ትኩየ (መሪጌታ ፣ ዘሰይፍአጥራ ማርያም) 131 ፣ 301
55 እሸቴ (መልአከ ገነት) 124
56 እንግዳወርቅ ሃይሉ (አለቃ) 126 ፣ 204
57 እንግዳ ደስታ (አለቃ) 326
★ 58 ኪዳናት ወልደሩፌአል (ቄስገበዝ ፣ ዘጎንጅ) 153 ፣ 190
59 ካሳ (አለቃ) 68
60 ካሳ (ቄስገበዝ ፣ ዘጎንጅ) 138
61 ክንፉ (አለቃ ፣ ዘራጉኤል) 93 ፣ 125
62 ክፍለዮሃንስ (መምህር ፣ ዘጎንደር) 129
63 ክፍሌ ፈለቀ (አለቃ) 295
64 ወልደመስቀል (አለቃ) ዘኡርኤል) 158
★ 65 ወልደሚካኤል (መምህር ፣ ዘዜና ማርቆስ) 200
66 ወልደማርያም ሃብቴ (አለቃ) 38 ፣ 181
67 ወልደ ሰንበት (ሊቀህሩያን) 272
68 ወልደስላሴ (አለቃ) 266 ፣ 399
69 ወልደትንሳኤ (መሪጌታ) 316
★ 70 ወልደአብ (አለቃ) 100
★ 71 ወልደ ኢየሱስ (ሊቀ ጠበብት ፣ 14 ፣ 71
★ 72 ወልደ ኪዳን ጀንበሬ (መሪጌታ ፣ ዘደብረ ታቦር) 263
73 ወልደ ዮሃንስ (መልአከ ብርሃን) 392
74 ወልደ ጊዮርጊስ (ሊቀ ጠበብት) 6
75 ወልደ ጊዮርጊስ (አለቃ) 268
76 ወርቅ አገኘሁ ተክሌ (አለቃ) 31 ፣ 164 ፣ 222
77 ወርቅነህ ዋሴ (መሪጌታ) 59
★ 78 ዋሴ (አለቃ ፣ ዘድንግራ ማርያም) 23
79 ውብሸት (ቄስገበዝ ፣ ዘብቸና) 160
80 ዘወልዴ (አለቃ) 18 ፣ 193 ፣ 202 ፣ 241
81 ዘዮሃንስ (አለቃ) 152 ፣ 198 ፣ 302 ፣ 384
82 ዘገየ (ሊቀህሩያን ፣ ዘደብረ መዊእ) 83
83 የማነብርሃን (ቄስገበዝ) 208
84 ያምሮት (አለቃ) 49
85 ይርጉ (አለቃ) 228 ፣ 289



www.ethiopianorthodox.org

86 ይትባረክ ቂርቆስ (መሪጌታ ፡ ዘደብረፅሙና) 225
87 ዮሃንስ ማምሻ (አጋፋሪ ፡ ዘመናገሻ ማርያም) 139
88 ዮፍታሄ ፡ 57
89 ደለለ (መሪጌታ ፡ ዘዋሸራ) 33
90 ደሴ ማእበል ፡ 215
★ 91 ደስታ ሃሊቡ (መምህር ፡ ዘዋሸራ) 343
92 ደስታ (አለቃ ፡ ዘተድባበ ማርያም) 327
93 ደስታ (አለቃ) 35 ፡ 367
94 ዳኜ (አለቃ) 360
95 ድንቄ (አለቃ) 175 ፡ 242 ፡ 262 ፡ 265 ፡ 344 ፡ 354
96 ድንቆ ማርቆስ ፡ 108
★ 97 ዶሪ (አለቃ ፡ ዘጨለቆት ስላሴ) 237
★ 98 ገላነሽ ሃዲስ (እማሆይ ፡ ዘፅላሎ) 82 ፡ 340
99 ገስስ (መምህር ፡ ዘየስማላ ጊዮርጊስ) 361 ፡ 368 ፡ 381 ፡ 393
100 ገብረ መድህን (አለቃ) ፡ ዘሌመንስላሴ) 276 ፡ 339
101 ገብረ ሚካኤል እውር ፡ 206
102 ገብረ ሚካኤል (ባህታዊ) 212
103 ገብረ ሚካኤል (አለቃ) 314
104 ገብረ ማርያም ቡሬ (መልአከ ሰላም) 329
105 ገብረ ማርያም (መምህር) 185
★ 106 ገብረ ኢየሱስ ቅኔፈጣሪ (አለቃ) 15
107 ገብረ ኢየሱስ (አለቃ ፡ ዘጠዳ) 195
108 ገብረ ኢየሱስ (መምህር ፡ ዘደብረ ሊባኖስ) 264
109 ገብረ ስላሴ (ንቡረ እድ) 357 ፡ 379
110 ገብረ ስላሴ ክንፉ (መምህር ፡ ዘኤልያስ) 1 ፡ 32 ፡ 36 ፡ 60 ፡ 73 ፡
87 ፡ 117 ፡ 122 ፡ 123 ፡ 130 ፡ 140 ፡ 217 ፡ 267 ፡ 271 ፡ 299 ፡
335 ፡ 336 ፡ 358 ፡ 364 ፡
111 ገብረ ጊዮርጊስ (መምህር ፡ ዘአክሱም) 366
112 ገዛኸኝ (ሚራጌታ ፡ ዘመርጡለ ማርያም) 77
113 ጌታሁን (አለቃ ፡ ዘሞጣ ጊዮርጊስ) 81
114 ግእዛን (ቄሰገበዝ) 307
115 ጎሹ አራት አይና ፡ 166



116 ጎበና (አለቃ) 270
★ 117 ጎበዜ (አለቃ ፡ ዘደብረወርቅ) 209 ፡ 292
★ 118 ጓሉ (ቄሰገበዝ ፡ ዘዲማ) 3
★ 119 ጥሩነህ (አለቃ ፡ ዘቦታ ኪዳነ ምህረት) 2 ፡ 22 ፡ 274 ፡ 275 ፡
310፡ 317 ፡ 321 ፡ 331 ፡ 350 ፡ 370 ፡ 397
★ 120 ጥበቡ ካሳ (መምህር ፡ ዘቦገና ግራር ኢየሱስ) 79 ፡ 351
121 ፀጋ (አለቃ) 148
122 ፈቃዶ (አቶ) 94 ፡ 398
123 ፈንታ ገብርየ (መልአከብርሃን) 53 ፡ 186
124 ፍስሃ ክርስቶስ (አባ) 255
125 ፍስሃ ጊዮርጊስ (ቄሰገበዝ ፡ ዘዳሞ) 356



www.ethiopianorthodox.org